# ክርስቲያናዊ ትምህርት

## በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ)
## መልክ የተዘጋጀ

ጸሑፍ:- ቢትሪስ ኮልማን
ትርጉም:- በመስፍን ታዬ
አርማት:- በጌቱ ግዛው

የመጀመሪያ እትም 1993 ዓ.ም (2001 A.D)
2ኛ እትም ጥቅምት 1995 ዓ.ም (2002 A.D)
3ኛ እትም ነሐሴ 1996 ዓ.ም (2004 A.D)

CHRISTIAN EDUCATION IN ETHIPIA
by Beatrice L. Coleman, 1998. Translated and Published in Amharic by SIM Publications in 1993 E.C (2001), Addis Ababa, Ethiopia. All rights reserved.

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

ይህ የጥናት መምሪያ
የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያን
አገልግሎት ላይ በተሰማሩ
ሰዎች ላይ ሲሆን የጥናት
መምሪያውን በብዙ የተለያዩ
መንገዶች መጠቀም ይቻላል።
በግል የእግዚአብሔርን ቃል
ለማጥናትም ሆነ በአዋቂዎች
የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም
በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት
ቤት መጠቀም ይቻላል።

ይሁንና መምሪያው የተዘጋጀው
በትምህርተ–መለኮት ማስፋፊያ
(ት.መ.ማ) መልክ ነው።
በመሆኑም ይህ መጽሐፍ
መምህርን ተክቶ ስለ መጽሐፍ
ቅዱስ ትምህርተ–መለኮት
ወይም አገልግሎት ለተማሪው
ጠቃሚ ትምህርቶችን
ያስተላልፋል። ተማሪው በዚህ
የጥናት መጽሐፍ እየተመራ
ጥያቄዎችን በመመለስና
የተማረውን ከሕይወቱ ጋር
በማዛመድ በቀን አንድ ሰዓት
ያህል ጊዜ ያሳልፋል።

ከሁሉም የላቀ ትርፍ
የሚገኘው ደግሞ ተማሪዎቹ
በሳምንት አንድ ቀን
ተሰባስበው የተማሩትን
ሲከልሱና የእግዚአብሔር ቃል
እንዴት ካሉበት ሁኔታ ጋር
እንደሚዛመድ ሲወያዩ ነው።

# ማውጫ

**መግቢያ** **ገጽ**


## ትምህርት አንድ፡- ክርስቲያናዊ ትምህርት ምንድን ነው?

1ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ማብራሪያ ....... 1
2ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነ መለኮታዊ መሠረቶች ....... 5
3ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍናና ዓላማዎች ....... 10
4ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ታሪክ ....... 13
5ኛ ቀን፡- የትምህርቱ ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....... 18

## ትምህርት ሁለት፡- የቤተክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት

1ኛ ቀን፡- ቤተክርስቲያን፤ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ት/ቤት ....... 19
2ኛ ቀን፡- በክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ማን ያስተምራል? ....... 25
3ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ትኩረት ....... 30
4ኛ ቀን፡- በክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የክርስቲያናዊ ትምህርትን ይዘት መግለጥ ....... 33
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....... 37

## ትምህርት ሦስት፡- ሕይወትን ለመለወጥ ማስተማር

1ኛ ቀን፡- የስብከት ትርጓሜ - ክፍል 1 ....... 38
2ኛ ቀን፡- የትምህርት ትርጓሜ - ክፍል 2 ....... 43
3ኛ ቀን፡- የመማር/ማስተማር ሂደት - ክፍል 1 ....... 48
4ኛ ቀን፡- የመማር/ማስተማር ሂደት - ክፍል 2 ....... 52
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....... 55

## ትምህርት አራት፡- መምህሩ

1ኛ ቀን፡- የመምህሩ የብቃት መመዘኛ - ክፍል 1 ....... 56
2ኛ ቀን፡- የአስተማሪነት የብቃት መመዘኛዎች - ክፍል 2 ....... 59
3ኛ ቀን፡- ትምህርቱን ከሕይወት ጋር ማዛመድ ....... 64
4ኛ ቀን፡- የአስተማሪው የብቃት መመዘኛዎች - ክፍል 3 ....... 66
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....... 69

## ትምህርት አምስት፡- ልጆችን ማስተማር


1ኛ ቀን፡- ልጆችን ለምን እናስተምራለን? ....................................70
2ኛ ቀን፡- ልጆችን ማስተማር ከቤት ይጀምራል ....................................73
3ኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት ቤት ....................................78
4ኛ ቀን፡- አስተማሪና ተማሪው ....................................82
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................................85


## ትምህርት ስድስት፡- የልጆች ባሕርያት በዕድሜ ክልል


1ኛ ቀን፡- መዋዕለ ሕፃናትን ማስተማር ....................................86
2ኛ ቀን፡- ጀማሪዎችን ማስተማር (ከ6-8 ዓመት) ....................................91
3ኛ ቀን፡- አንደኛ ደረጃዎችን ማስተማር (ከ9-11 ዓመት) ....................................95
4ኛ ቀን፡- መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃዎችን ማስተማር
(12-14 ዓመት) ....................................97
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................................101


## ትምህርት ሰባት ፡- ወጣቶችን ማገልገል


1ኛ ቀን፡- የወጣቶች ባሕርያት ....................................102
2ኛ ቀን፡- የወጣቶች ፍላጎቶች ....................................105
3ኛ ቀን፡- ለወጣቶች አገልግሎት ብቁ የሆኑ አዋቂ ሠራተኞች ....................................109
4ኛ ቀን፡- ፈቃደኞች የሆኑ አዋቂዎች ሥልጠና ....................................112
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................................116


## ትምህርት ስምንት፡- የወጣቶች አገልግሎት - ክፍል ሁለት


1ኛ ቀን፡- ለወጣቶች ፕሮግራም የቀረቡ አሳቦች ....................................117
2ኛ ቀን፡- በትውልድ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ ....................................121
3ኛ ቀን፡- ክርስቲያናዊ ሽርሽር - ሰዎችን ለማገልገል ሌላው
አማራጭ ....................................124
4ኛ ቀን፡- ሽርሽር - ለቤተክርስቲያን ትምህርት የመስጫ ዕድል ....................................128
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................................130


## ትምህርት ዘጠኝ፡- ወንዶችን ማገልገል


1ኛ ቀን፡- የወንዶች ባሕርያት እና ፍላጎቶቻቸው ....................................131
2ኛ ቀን፡- ውጤታማ የሆነ የወንዶች ሥርዓተ ትምህርት ....................................133
3ኛ ቀን፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ

ሰዎች አገልግሎት ......136
4ኛ ቀን፡- የወንዶች ለአገልግሎት ወደ ውጭ መውጣት ......139
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......141

ትምህርት አሥር፡- የሴቶች አገልግሎት

1ኛ ቀን፡- በአፍሪካ የሚገኙ ሴቶች ባሕርይና ፍላጎት ......142
2ኛ ቀን፡- ሳምንታዊው የሴቶች ስብሰባ ......147
3ኛ ቀን፡- የሚስት ሚና በቤት ውስጥ ......149
4ኛ ቀን፡- ቤተክርስቲያን ለቤተሰብ የምትሰጠው አገልግሎት ......152
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......156

ትምህርት አሥራ አንድ - መምህሩና ትምህርቱ

1ኛ ቀን፡- ትምህርቱን ማዘጋጀት ......157
2ኛ ቀን፡- የትምህርቱ ዓላማ ......160
3ኛ ቀን፡- የትምህርቱ መግቢያና ትምህርቱ ......165
4ኛ ቀን፡- የታሪኩ ትርጉምና ከሕይወት ጋር ያለው ተዛምዶ ......167
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......169

ትምህርት አሥራ ሁለት - የሰንበት ትምህርትን ለማስተማር ተጨማሪ መርጃዎች

1ኛ ቀን፡- መምህሩና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ 1 ......169
2ኛ ቀን፡- መምህሩና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ 2 ......173
3ኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት ሰዓት አደረጃጀት ......177
4ኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርትን ማደራጀት ......180
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......184

ትምህርት አሥራ ሦስት፡- የሰንበት ት/ቤትን ማደራጀት

1ኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራንን ማሠልጠን ......185
2ኛ ቀን፡- ሥርዓተ ትምህርትን ማቀድ ......189
3ኛ ቀን፡- በግል  የታቀደ ሥርዓተ ትምህርት ......193
4ኛ ቀን፡- መንፈሳዊ ምግብ ለሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ......195
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......199

## ትምህርት አሥራ አራት፡- የጥናት ንዑስ ቡድኖች


1ኛ ቀን፡- የጥናት ንዑስ ቡድኖች ዓላማ በቤተ ክርስቲያን ......201
2ኛ ቀን፡- የጥናት ንዑስ ቡድን አመራር ......203
3ኛ ቀን፡- የጥናት ንዑስ ቡድን መሪዎችን ሥልጠና ......205
4ኛ ቀን ፡- የጥናት ንዑስ ቡድኖችን ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ......208
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......212


## ትምህርት አሥራ አምስት፡- የወንጌል ስርጭትና ሌሎችን መድረስ


1ኛ ቀን፡- ወንጌላዊ ......212
2ኛ ቀን፡- መልእክቱ ......215
3ኛ ቀን፡- ሊገጥሙህ የሚችሉ ችግሮችና ተቃውሞዎች ......219
4ኛ ቀን፡- አንድ-ለአንድ በመሆን የሚደረግ አዲስ አማኞችን መርዳት ......221
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......224


## ትምህርት አሥራ ስድስት፡- ልዩ ክፍሎች


1ኛ ቀን፡- የአዲስ አማኞች ማስተማሪያ ክፍል ......225
2ኛ ቀን፡- ለውኃ ጥምቀትና ለጌታ እራት መዘጋጀት ......227
3ኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን አባልነት ......230
4ኛ ቀን፡- የቅድመ-ጋብቻ ምክር ......232
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......236


## ትምህርት አሥራ ሰባት፡- የመሪነት ሥልጠና


1ኛ ቀን፡- መሪ የመሆን ጥሪ ......237
2ኛ ቀን፡- መሪዎች የሚያሟሏቸው አስፈላጊ ብቃቶች 1 ......241
3ኛ ቀን፡- መሪዎች የሚያሟሏቸው አስፈላጊ ብቃቶች 2 ......243
4ኛ ቀን፡- በመሪነት ውስጥ ያሉ መሰናክሎች ......246
5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ......249

## ትምህርት አሥራ ስምንት፡- የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፥ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት


1ኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የብቃት መመዘኛዎች ....................250

2ኛ ቀን፡- የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ....................253

3ኛ ቀን፡- ውክልና፥ ተጠያቂነትና ችግሮችን ማቃለል ....................255

4ኛ ቀን፡- የመሪዎች የረዥም ጊዜ ዕቅድ ....................260

5ኛ ቀን፡- ክለሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................264


## ትምህርት አሥራ ዘጠኝ፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ግምገማ


1ኛ ቀን፡- የምንገመግመው ለምንድን ነው? ....................264

2ኛ ቀን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ይገመገማል? ....................267

3ኛ ቀን፡- ምን እንደምንገመግም? ....................270

4ኛ ቀን፡- መቼ እንደምንገመግም? ....................272

5ኛ ቀን፡- ክላሳና ሳምንታዊ ስብሰባ ....................275


## ትምህርት ሃያ፡- ክለሳ


የታላቁ ምሳሌያችን የኢየሱስ የማስተማር ዘዴዎች ....................275

ማጠቃለያ ....................277

# መግቢያ

ይህ የክርስቲያናዊ ትምህርት የትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ ኮርስ የተዘጋጀው ስለ ቤተክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ነው።

የክርስቲያናዊ ትምህርት ዓላማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን እያንዳንዱ የዕድሜ ክልል የትምህርት ፍላጎት ማሟላት ነው። የሚያተኩረውም በመምህሩ፥ በብቃቱና በዘዴዎቹ ላይ ነው። የማስተማሪያ መሣሪያዎቹንና ትምህርቱን ለሚቀበሉት የተለያየ ዕድሜ ክልል ቡድኖች ያለውን ተስማሚነትም አካትቷል። የእያንዳንዱን የዕድሜ ክልል ባሕርይ በመረዳት እንዴት በጥሩ ሁኔታ ልናስተምራቸው እንደምንችልም ይመራናል። እንዲሁም በተማሪዎቹ ሕይወት ውስጥ ትምህርቱ በሚያስከትለው ውጤት ላይም ያተኩራል።

በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ከሚታዩና ሊሸፈኑ ከማይችሉት ችግሮች አንዱ የተቀናጀ፥ በሚገባ የተዘጋጀና ተማሪውን ያማከለ ትምህርት እጦት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ትምህርት አስፈላጊነት በተደጋጋሚ በአጽንኦት ጽፎአል። በእምነት ልጁ ለሆነው ለጢሞቴዎስ፥ «ይህን እዘዝና አስተምር» (2ኛ ጢሞ. 4፡11)፤ እንዲሁም በቁጥር 13፥ « እስከመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ» ብሎታል።

ጌታችን ኢየሱስ እንድናስተምር አዝዞናል። የእርሱ የመጨረሻው ትእዛዝ፥ «. . . ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው» (ማቴ. 28፡20) የሚል ነው። እርሱ ከከተማ ወደ ከተማ እየዞረ የማስተማር ምሳሌ ትቶልናል። ሙሴም በብሉይ ኪዳን ታላቅ መምህር ነበር። እግዚአብሔር ለእርሱ የገለጠለትን ሁሉ ለሕዝቡ በትጋት አስተላልፎአል። እኛስ አርአያነቱን ልንከተል አይገባንምን?

ይህ ኮርስ ልክ እንደ ሌሎቹ ለከፍተኛ ደረጃ የት.መ.ማ ኮርሶች የተዘጋጀ ነው። የሃያ ሳምንታት ትምህርቶች አሉት። እያንዳንዱ ትምህርት በአራቱ ቀናት ትምህርቶች የተከፋፈለ ሲሆን፥ በአምስተኛው ቀን ተማሪው በአራቱ ቀናት የተሰጡትን ትምህርቶች መከለስና ለሳምንታዊ ስብሰባ መዘጋጀት ይኖርበታል። ይህ ስብሰባ ይህንኑ ኮርስ የሚወስዱ ተማሪዎች ከሌሎች ጋራ ባለፈው ሳምንት ስለተማሩአቸው ጉዳዮች የሚወያዩበት ጊዜ ነው። ከእነዚህ ርእሶች አብዛኞቹ በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ካለው አገልግሎት ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ። በርእሶቹ ላይ በምትወያዩበት ጊዜ በትምህርቱ ውስጥ የተሰጡትን አሳቦች በአሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያናችሁ ካለው ሁኔታ ጋር ብቻ አታወዳድሩአቸው። ይልቁኑ ለተማሪዎች ዕድገት አዳዲስ አሳቦችን በፕሮግራማችሁ ውስጥ እንዴት ልታስገቡ እንደምትችሉ አስቡ። በቤተ ክርስቲያናችሁም ውስጥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተዘረዘሩት የተሻሉ ፕሮግራሞች ይኖሯችሁ ይሆናል። እነዚያ የተሻሉ ፕሮግራሞች አሳቡ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል በማሳየት ሊያበረታቱአችሁ ይገባል።

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አስተማሪያችሁ ነው። ይህንን ኮርስ በምትማሩበት ጊዜ ሌላ የሚያስፈልጋችሁ ነገር የማስታወሻ ደብተራችሁ፥ እስክሪብቶ እና የራሳችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይሆናል። ብዙ ጥያቄዎች ስላሉ መልሶቻችሁን ሁሉ ለመያዝ የሚችል ተለቅ ያለ የማስታወሻ ደብተር ይኑራችሁ። እነዚህም በወደፊቱ አገልግሎታችሁ ሊጠቅሟችሁ የሚችሉ ይሆናሉ።

በየትምህርቱ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ ማንበባችሁ በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ክፍሎች የተጠቀሱት ግን አጽንኦት ለመስጠት ብቻ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ የተጻፉትንም ሆነ ያልተጻፉትን ጥቅሶች ጥያቄዎቹን በምትመልሱበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ ልታጠኑዋቸው ይገባል።

ኮርሱን በምትጨርሱበት ጊዜ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የተናገረውን ቃል አስቡ፤ «ብዙ ሰዎች የመሰከሩትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ (2ኛ ጢሞ. 2፡ 2)። የዚህ ጥናት ጸሐፊ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ጥልቀት ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የመስጠት አስፈላጊነትን በሚገባ እንድታስቡበትና ሕዝባችሁን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ለመመሥረት የምትችሉትን እንድታደርጉ ትልቅ ናፍቆት አላት። በምላሹ ሌሎችን እንዲያስተምሩ አሠልጥኗቸው። እኔም እስከ መጨረሻው ግባችሁ ይህ እንዲሆን ያለማቋረጥ እጸልያለሁ።

ቢ. ኮልማን

# ትምህርት አንድ

# ክርስቲያናዊ ትምህርት ምንድን ነው?

## 1ኛ ቀን፡— የክርስቲያናዊ ትምህርት ማብራሪያ (መግለጫ)

## የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍች

«ትምህርት» የሚለው ቃል በተለያዩ መንገዶች አገልግሏል። መንግሥታት ዜጎቻቸውን ስለ ማስተማር ይናገራሉ። ግለሰቦች ራሳቸውን በማሳደግ አንጻር ራሳቸውን ስለ ማስተማር ይናገራሉ። መምህራን ተማሪዎቻቸውን ስለ ማስተማር ይናገራሉ (ቡኮንዮሪ፥ 1993፥ ገጽ 11)።

የዌብስተር መዝገበ ቃላት ትምህርትን «ወጥ በሆነ መንገድ በትምህርት ቤት፥ በሥልጠና እውቀትን፥ አስተሳሰብንና ባሕርይን፥ ወዘተ... የማሠልጠንና የማሳደግ ሂደት፥ የመማርና የማስተማር ዘዴዎችና ንድፈ - አሳቦች የተቀናበረ ጥናት» ብሎ ይፈታዋል (ዌብስተር፤ ገጽ 444)።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡— ሀ) ስለ ክርስቲያናዊ ትምህርት ስታስብ ወደ አእምሮህ የሚመጣው ጥያቄ ምንድን ነው? ለ) ክርስቲያናዊ ትምህርት በሙሉ ምን ምን ማቀፍ አለበት? የመማሪያ መጽሐፉ ምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያናዊ ትምህርት መካሄድ ያለበት የት በታ ነው? መ) ለክርስቲያናዊ ትምህርት ኃላፊነቱን ማን ሊወስድ ይገባዋል? |

ስለ «ክርስቲያናዊ» ትምህርት በምናስብበት ጊዜ ግን ሰፋ ያለ ትንተና ልንሰጥ ይገባል። «ክርስቲያን» የሚለው ቃል ተማሪዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያውቁትና የሚወዱት እንዲሁም ተከታዮቹ የሆኑትን ሰዎች ያመለክተናል። በመጀመሪያ ደረጃ ክርስቲያናዊ ትምህርት አሳቦችን፥ እሴቶችንና እውቀቶችን ከቀደመው ትውልድ ወደ አዲሱ ትውልድ ማስተላለፍ ነው ማለት እንችላለን። ለክርስቲያኖች ይህ የወንጌሉን የምስራች ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው (2ኛ ጢሞ 2፡ 2)።

ክርስቲያናዊ ትምህርት የሕይወታችንን ፈርጅ ሁሉ መንካት ይኖርበታል። በአሁኑ ዓለም እንዴት እንደምንኖር ሊያሳየን ይገባል፤ ነገር ግን ደግሞ ከዚህ ባሻገር ከሞት በኋላ ለሚመጣው ሕይወት ሊያዘጋጀን ይገባል። የዘላለም ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። በምድር ያለን ሥጋዊ ኑሮ ትርጉምና ዓላማ ሊኖረው የሚችለው የዘላለም ሕይወት ሲኖረን ብቻ ነው።

ለክርስቲያናዊ ትምህርት መማሪያ መጽሐፋችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በጣም ጥልቅ ለሆኑት ጥያቄዎቻችን መልስ ልናገኝ የምንችለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው። «ከየት ነው የመጣሁት? እዚህ ያለሁት ለምንድን ነው? ወዴት ነው የምሄደው?» እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች ብዙ ጊዜ አዕምሮአችንን ይረብሻሉ፤ ያስጨንቃሉም። ስለሆነም ክርስቲያናዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊና የሕይወትን ከባድ ጥያቄዎች የሚመልስ መሆን አለበት።

ክርስቲያናዊ ትምህርት የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተክርስቲያን ማለት ሰዎች እንደሆኑ ማስታወስ ይኖርብናል። የምንሰበሰብበት ሕንጻ ወይም

መርሐ ግብሩ ሳይሆን የክርስቶስ አካል የሆኑት፥ ሰዎች ናቸው። ማበረታቻ ለመስጠት፥ እያንዳንዱ አማኝ በእምነቱ ሲያድግና ሲበስል ለማየት እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ለእያንዳንዱ አቻ አባል ግድ ሊለው ይገባል። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ይላል። « ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ» (ዕብ 10፡ 24–25)።

ክርስቲያናዊ ትምህርት በሰዎች ፍላጎት ላይ በማተኮር ያንን ለማሟላት የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር የሚካሄድ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የዕድሜ ክልሎች እንዲሁም ልዩ ቡድኖችን የሚሸፍን መሆን አለበት፤ ለዕድሜያቸው፥ ለችሎታቸው እና ለማንዛቤ ደረጃዎች የሚመጥን ትምህርት በማቀድ ይካሄዳል። ዋና ዓላማው ሕይወትን መለወጥ ነው።

2ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ኤፌሶን 4፡ 11–16 በጥንቃቄ አንብብ። ጌታ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሰዎች እንድታስተምር እና እንድታሠለጥን በሚገባ አስታጥቋታል። ከዚህ ምንባብ ይህንን መሥራት ያለባቸው ሰዎች እነማን ናቸው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በታማኝነት ከሚሰጥ ትምህርት የተነሣ የሚታዩ ቢያንስ ሦስት ውጤቶችን ዘርዝር።

እግዚአብሔር በቂ ስጦታና ችሎታ ያላቸው ሰዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን ማበርከት እንዲችሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዓይነት ስጦታዎችን ሰጥቷል። ከኤፌሶን 4፡ 11–16 ላይ እንደምንመለከተው ክርስቶስ ሐዋርያትን፥ ነቢያትን፥ ወንጌላውያንን፥ መጋቢያንንና አስተማሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። ዓላማውም አባላት በእምነት እንዲመሠረቱና እንዲታነጹ ነው። እግዚአብሔር ለመንጋው እረኛ የመሆን ኃላፊነትን ሰጥቷቸዋል።

በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐዋርያት የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት (1ኛ ቆሮ.9፡1–2)፥ የሞቱና የትንሣኤው (የሐዋ. 1፡21–22) የዓይን ምስክሮች ነበሩ። እነርሱ በእግዚአብሔር የተዘጋጀውን ታላቁን መዳን ለማወጅ በመለኮታዊ ውሳኔ የተመረጡ የክርስቶስ አምባሳደሮች ነበሩ (ዕብ. 2፡3)።

በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን ዘመን የነበሩት ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠላቸውን እውነት ለማስተማር ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚዘዋወሩ ሰዎች ነበሩ። በ1ኛ ቆሮ. 14፡3 እና 31 እንደምንመለከተው የእነርሱ አገልግሎት ማነጽ፥ መምከር፥ ማጽናናትና ማስተማር ነበር። በሐዋርያት ዘመን መጨረሻ ገደማ ይህንን አገልግሎት ሰዎችን ለማሳሳት የተጠቀሙበት ክፍሎች ነበሩ። በተጨማሪም 1ኛ ዮሐ. 4፡1–3 እና ራእይ 2፡20ን ይመልከቱ። በአንደኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ ወቅት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ ተሰባስበው ካበቁ በኋላ የሐዋርያትና የነቢያት ስጦታ አከትሟል። ነቢያት ከሐዋርያት ጋር በመሆን የቀድሞዪቱን ቤተ ክርስቲያን መሠረት በመጣል (ኤፌ. 2፡20) ወሳኝ አገልግሎት የነበራቸው ሲሆን፥ ዛሬ ግን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስላሉልን እነርሱ አያስፈልጉንም።

ወንጌላውያን የምስራቹ ቃል ነጋሪዎች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን የሚሰብኩትንና ሰዎችን እውነቱን ወደ ማወቅ የሚመሩትን ሰዎች ችላ ልትል አትችልም። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት በሙሉ ሳልዳኑት መመስከር ያለባቸው ቢሆንም፥ ወንጌላዊው ግን ወንዶችንና ሴቶችን፥ ወንዶች ልጆችንና ልጃገረዶችን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማዳን ወደ ማወቅ ለማምጣት የተለየ ስጦታ አለው።

መጋቢው መንጋውን የሚጠብቅ እረኛ ነው። እርሱ ለደከሙት፥ ለታመሙት እና ለባዘኑት ይጠነቀቃል። በተጨማሪም ወጣቶችን ያማክራል፥ የተቸገሩትን ይረዳል፥ ያዘኑትንም ያጽናናል። እርሱ የእረኛው ልብና የመጋቢነት ስጦታ ስላለው እነዚህን ተግባራት ደህና አድርጎ ያከናውናል።

መምህር መንጋውን ያስተምራል፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ታላላቅ እውነቶችን፥ ዶክትሪኖችን (አስተምህሮዎችን)፥ መርሖችን፥ ታሪኩን፥ ሥነ-መለኮቱን፥ ዓላማውንና ውጤቱን ያብራራል። መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር ያስተያያል (1ኛ ቆሮ. 2፡13)፥ እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ ከሰዎች ጋር ያደረገውን መስተጋብር ያመለክታል፥ እግዚአብሔር ለወደፊት ያዘጋጀውን ዕቅዱን ያስታውቃል። ሌሎች የእውነትን ቃል እንዴት ሊናገሩ እንደሚገባ ያስተምራቸዋል (2ኛ ጢሞ. 2፡15)፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አስደናቂነት እንዲገነዘቡ ዓይኖቻቸውን ይከፍትላቸዋል። መጋቢና አስተማሪ በመሆን ሁለቱንም አገልግሎቶች የሚይዙ ጥቂት ሰዎች ናቸው።

እግዚአብሔር በስጦታዎች ስላስታጠቃቸው ሰዎች የሚናገሩ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም አሉ። ለጊዜው የኤፌሶንን ክፍል ብቻ እንመለከታለን።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ የመጋቢነትና የማስተማር ጸጋ ያላቸው ሰዎች እነማን ይመስሉአችኋል? ለ) ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በመረዳት እንዲያድጉ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች የሚጠቀምባቸው እንዴት ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያን አባላት ዘንድ የባሕርይ ለውጥ እንዲመጣ ትምህርታቸው ምን ውጤት አስከትሏል? |

1. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ማዘጋጀት (ኤፌ.4፡11-13)

የእነዚህ መሪዎች ሥራ «ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆን ዘንድ» ነው (ኤፌ. 4፡ 12-13)።

እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን የሚፈልገው ቃሉንና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን እንድታስተምርና አባላቷ በሙሉ በእምነትና በእግዚአብሔር ልጅ እውቀት ወደ አንድነት ይመጡ ዘንድ ነው። የሚፈለጉትም ውጤቶች ብስለትና ክርስቶስን መምሰል ናቸው። ከዚያም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የአገልግሎትን ሥራ ለመሥራት (ማለትም ወንጌልን ለመመስከር፥ ለማስተማር፥ ለማማከርና አባላትን ለመንከባከብ) ዝግጁ ይሆናሉ።

4ኛ ጥያቄ፦ ሀ) 2ኛ ጴጥሮስ 2፡1-3፣ ይሁዳ 3-16 እና የሐዋርያት ሥራ 20፡25-31ን አንብብ። ጴጥሮስ፥ ይሁዳና ጳውሎስ የሚያመለክቱት ሊመጣ ያለው አደጋ ምንድን ነው? ለ) በእነዚህ ምንባቦች መሠረት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግልጽ ትምህርት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለእኛ ምሳሌያዊነት ያለው የቤሪያ ሰዎች ተግባር ምንድን ነው? (የሐዋ. 17፡11)

2. ከስሕተት መጠበቅ (ኤፌ. 4፡14)

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትምህርት አስፈላጊ የሆነበት ሌላው ዓላማ በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 ላይ ይገኛል። ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገባ ከተማሩ ወደ ሐሰተኛ ትምህርቶችና ኑፋቄዎች አይወሰዱም። ዛሬ ሰዎችን አታልለው ከክርስቶስ ለመውሰድ የሚፈልጉ ብዙ የሐሰት አስተማሪዎችና መናፍቃን አሉ። እንደገና 2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 1-3ን አንብብ። ልክ የቤሪያ ሰዎች እንዳደረጉት እያንዳንዱን አዲስ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በማስተያየት በቃሉ መሠረት መመርመር አለብን (የሐዋ. 17፡ 11)።

ጳውሎስ ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ለመጨረሻ ጊዜ በሚለይበት ጊዜ የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲጠብቁ አስጠንቅቋቸዋል። ምክንያቱም እውነትን በማጣመም ደቀ መዛሙርትን ወደኋላቸው የሚስቡና ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች በመካከላቸው ስለሚነሡ ነው (የሐዋ. 20፡ 25-31)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች ወደ ዓለም ወጥተው የራሳቸውን ምርኮ ከመሰብሰብ ይልቅ በሚገባ ያልተማሩና ደካማ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ይናጠቃሉ (1ኛ ጢሞ.4፡1-2)።

ጳውሎስ «ተጠንቀቁ» ብሏል። ማኅበረ ምእመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና አስተምህሮዎችን ካልተማረ እውነቱን ከስሕተት መለየት አይችልም። በባንክ ቤት የሚሠሩ ሰዎች በሐሰተኛና በእውነተኛ ገንዘብ መካከል መለየት እንዲችሉ ሠልጥነዋል። ትክክለኛ ያልሆነ ገንዘብ አትመው ከእውነተኛ ገንዘብ ጋር የሚያሰራጩ ሰዎች አሉ። የባንክ ቤት ገንዘብ ተቀባዮች ሐሰተኛውን ገንዘብ የሚያውቁት ትክክለኛውን ገንዘብ ለብዙ ጊዜ በመቁጠር ነው። በዚህ ዓይነት እጃቸው ሐሰተኛውን ገንዘብ በሚነካበት ጊዜ ወዲያውኑ ለይተው ሊያውቁት ይችላሉ። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር ቃል እውነት የተሞላን ሆነን እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነ ነገር በምንሰማበት ጊዜ በፍጥነት ልንለየው ይገባል። (1ኛ ጴጥ.3፡15-16ን በጥንቃቄ አንብብ)

5ኛ ጥያቄ፦ የቤተክርስቲያን ራስ ማን ነው? የአካሉ ክፍሎችስ እነማን ናቸው? የክርስቶስ አካል እንዴት እንደሚሠራ ለማሳየት እንዲረዳ ስለ ሰው አካል አሠራር አንድ ገለጻ አድርግ። ይህን ለማድረግ ይረዳህ ዘንድ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡ 12-30ን አንብብ።

3) የክርስቶስን አካል ማነጽና ማሳደግ (ኤፌ.4፡15-16)።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም ትምህርት የሚሰጥበት ሦስተኛው ምክንያት በኤፌሶን 4፡15-16 ውስጥ ተጽፎአል።

የዮሐንስ ወንጌል 15፡5 ከክርስቶስ ተለይተን ምንም ማድረግ እንደማንችል ያሳስበናል። ለአካሉ ዕድገት በዋነኛነት የሚያስፈልጉ አንድነትና የማደግ ፍላጎትን በዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖርና በተገቢው መንገድ እንዲሠራ የሚያደርገው ክርስቶስ ነው። የእኛ ፈንታ እውነትን በፍቅር እየተናገርን መታዘዝና እንደ ቃሉ መመላለስ ነው። ይህን ስናደርግ እርሱ የአማኞችን አካላት ኅብረት ልክ ድንጋዮችን በማያያዝ እንደሚያጣብቅና ለሕንፃው መገንባት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ አንድ አያደረገ አካሉን ይገነባል።

ስለዚህ ክርስቲያናዊ ትምህርት የቤተክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት ነው። ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጥባት ቦታ ናት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ግለሰብ የሚያስፈልገውን ትምህርትና መልካም ምሳሌነት አግኝቶ እንደ ክርስቶስ አካል አባል በሚገባ እንዲሠራ ይህ ትምህርት በጥንቃቄ ሊታቀድና ሊዘጋጅ ይገባል።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡— ሀ) እንደገና ይህን የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ አንብብ። ለክርስቲያናዊ ትምህርት ይስማማል ብለህ የምታምነውን ፍች ጻፍ። ለ) በዚህ ምዕራፍ እንደተገለጸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጠና የሚያስፈልግባቸውን ሦስት ምክንያቶች ጻፍ። ሐ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንህ ስላለው የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም/መርሐ ግብር/ ጥቂት መግለጫ ጻፍ። |

## ሁለተኛ ቀን፡— የክርስቲያናዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነ መለኮታዊ መሠረቶች

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ስለ ራሱ የገለጠበት መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ራሱንና ዓላማውን በቃሉ በኩል ለሰው ልጆች ገልጧል። የሥነ ምግባር ሕጉንና በፈቃዱ የምንኖርበትን መመሪያ ሰጥቶናል። በቤተክርስቲያን የምንቀበላቸው ትምህርቶች በጽናት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ፥ በምድር በምንኖርባት በዚህች አጭር ዘመናችን እምነታችንን፥ የአስተሳሰብ ሚዛናችንን እንዲሁም ልናደርግ ያለንን ነገር ሁሉ የሚቀርጹ ይሆናሉ። መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ በመሥራት የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምሥጢር በመግለጥ ትምህርቱ በልባችን እንዲታተም ያደርጋል። እንዲሁም በእነዚያ እውነቶች ላይ ተመሥርተን እንድንኖር ችሎታውን ይሰጠናል። ዮሐንስ 14፡26 ተመልከቱ።

### 1. እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ገለጠ

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡— ሀ) የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበብህ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ራሱ ስለገለጠው ነገር ምን እንደሚያስተምሩ ተናገር። መዝ. 19፡1፥ 2፥ 4፤ ሮሜ. 11፡20፤ ዘፍጥ. 1፡27። ለ) በፍጥረት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ምን ልንማር እንችላለን? |

#### ሀ. በፍጥረት ውስጥ

በተፈጥሮአዊ መገለጥ እግዚአብሔር ስለ ራሱ ብዙ አሳይቶናል። እርሱ ሰማይና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጥሮ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን አርፎአል። እርሱ በሠራቸው የሚታዩ ነገሮች ስለማይታየው

አምላካችን ብዙ ነገሮች ልንማር እንችላለን። መዝሙር 19፡ 1፥2፥4 እንዲህ ይላል።

« ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል
ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች
ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።
ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ
ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ»።

ጳውሎስም ስለዚህ ጉዳይ በሮሜ 1፡20 ላይ ተናግሯል። «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፥ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ»።

ስለ እግዚአብሔር በተፈጥሮ መገለጥ አማካይነት ብዙ ልንማር እንችላለን። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኃይልና መለኮታዊ ባሕርይ በእርሱ የመፍጠር ኃይልና በዙሪያችን ባለው ውብ ተፈጥሮ አማካኝነት በግልጥ ይታያል። እንዲህም ፍጥረትን አጽንቶ በመጠበቁና በየዕለቱ በዙሪያችን እንደምናየው በሚያደርግለት ዕድሳት ይታያል።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዮሐ 1፡ 1–3፤ ቆላ. 1፡ 15–18፤ ዮሐ. 1፡ 14፤ ዕብ. 1፡ 1–2 በማንበብ እግዚአብሔር ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት እንደገለጠ ተናገሩ። ለ) በእርግጥ እግዚአብሔርን ከክርስቶስ ኢየሱስ ውጪ ልናውቀው እንችላለን? ምክንያቶቻችሁን ግለጹ። |

ለ. በቃሉ በኩል

9ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባብህ ስለ እግዚአብሔር የምታውቃቸውን ቢያንስ ስድስት ነገሮች ጻፍ። መልሶችህን ለመደገፍ ጥቅሶችን ስጥ።

የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕርዩን ማወቅ እንድንጀምር እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ተገልጦአል።

1. ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» (ዮሐ. 4፡24)። «በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና» (ሉቃ. 24፡39)። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ማንኛውንም ዓይነት ምስል ስለ እግዚአብሔር እንዳንስል ተከልክለናል (ዘጸአት 20፡4–6)።

2. እርሱ የማይታይ አምላክ ነው። ዮሐንስ 1፡18 እንዲህ ይላል፤ «እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም»። ደግሞም 1ኛ ጢሞቴዎስ 16፡1–17 አንብብ።

3. እርሱ ሕያው ነው። እርሱ «ሕያው አምላክ» ተብሎ ተጠርቷል [ኢያ. 3፡10 መዝ. (84)፡2 ማቴ. 16፡16 ራእይ 7፡2]።

4. እርሱ አካል አለው። እርሱ እውቀት፥ ስሜት፥ ውሳኔ የማድረግ ብቃት አለው (ዘፍጥ. 18፡19፤ የሐዋ. 15፡18፤ ዘፍጥ. 6፡6፤ ዮሐ. 6፡38)። እርሱ ይናገራል (ዘፍጥ. 1፡3)፤ ያያል (ዘፍጥ. 11፡5)። ይሰማል [መዝ. (94)፡9]፤ ያዝናል (ዘፍጥ. 6፡6)። ይጸጸታል (ዘፍጥ. 6፡6)። ይቆጣል (ዘዳ. 1፡37)፤ ቀናተኛ ነው (ዘጸ. 20፡5)። ይራራል [መዝ. (111)፡4]።

5. በሁሉ ቦታ የሚገኝ ነው [1ኛ ነገ. 8፡27፤ መዝ. (139)፡7–10]።

6. ሁሉን የሚያውቅ ነው [መዝ. (147)፡5፤ ምሳ. 15፡3፤ ኤር. 23፡23–25፤ ዕብ. 4፡13]።

7. ሁሉን የሚችል ነው (ኢዮ. 42፡2፤ ማቴ. 19፡26፤ ኤር. 32፡17፤ ራእይ 19፡6)።

8. ለዘላለም ያው ነው። አይለዋወጥም [ያዕ. 1፡17፤ መዝ. (102)፡26፤ ሚል. 3፡6]።

9. ቅዱስ ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ ብቻ ከሠላሳ ጊዜ በላይ «ቅዱሱ» ተብሎ ተጠርቷል [ዘሌ. 11፡44፤ ኢያ. 24፡19፤ መዝ. (22)፡3፤ ኢሳ. 40፡25)] ወዘተ.

10. እርሱ ጻድቅ ነው (2ኛ ዜና 12፡6፤ ዕዝ. 9፡15፤ ነህ. 9፡33፤ ዳን. 9፡14፤ ዮሐ. 17፡25፤ ራእይ 16፡5)።

11. እርሱ መልካም ነው። ይህም ፍቅሩንና ደግነቱን፥ ምሕረቱንና ጸጋውን ያጠቃልላል (ማር. 10፡18፥ ኤፌ. 2፡4፥ ማቴ. 6፡26፥ የሐዋ. 14፡17)።

12. እርሱ የእውነት አምላክ ነው (ዮሐ. 17፡3)።

ሐ. በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል

ዕብራውያን 1፡1–2 እንዲህ ይላል፦ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን»። እንደገናም በዮሐ. 1፡18 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው»።

ሕያው ቃል የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ሊገልጥልን ወደ እኛ መጣ። እርሱ ራሱ እንዲህ ብሏል፦ «እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፥ አይታችሁትማል» (ዮሐ. 14፡7)። ሆኖም ፊሊጶስ ገና አብን ለማየት ይፈልግ ነበር።

ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ «እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ፦ አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል»። (ዮሐንስ 14፡9፤10)። ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ የመጣ የአብ መገለጥ ነው። ዮሐንስ እንዲህ ብሏል፤ «ስለ

ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን» (1ኛ ዮሐ. 1፡1)።

ዕብራውያን 1፡3፥ «እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ...» ሲል ይናገራል። የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና ትምህርት በምናጠናበት ጊዜ እርሱ ሊገልጠው ስለመጣው ስለ አብ እየተማርን ነው።

እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም በአንድ ሆነው ሥጋን በለበሰውና በመካከላችን በኖረው በኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጡልን (ዮሐንስ 1፡18)።

ስለ እግዚአብሔር ልንማር የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ነው። እርሱ ራሱን በፍጥረት፥ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ እንዲሁም በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል የገለጠና ከእኛም ጋር የሚገናኝ አምላክ ነው።

---

10ኛ ጥያቄ፡- በሁለቱም ኪዳኖች (ብሉይና አዲስ) ውስጥ የሚታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ማዕከላዊ መልእክት /ጭብጥ/ ምንድን ነው? ስለሚመጣው አዳኝ የተሰጠ ቀዳሚው የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

---

2. ክርስቶስ የቅዱሳት መጻሕፍት ማዕከላዊ ጭብጥ ነው።

ክርስቶስ በጽሑፍ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ የሚመሰክርለት የእግዚአብሔር ሕያው ቃል ነው (ዮሐ. 5፡39-46)። የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል በምናነብበት ጊዜ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መልእክት የሆነውን ክርስቶስን፥ በሰው ልጆች ፈንታ የተፈጸመውን በአብ በጥንቃቄ የታቀደውንና በልጁም የተፈጸመውን፥ የማዳን ሥራ መሳት የለብንም። በአዳም ውስጥ በአብርሃምና በሙሴ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሳይታጠፍ ተፈጽሞ እናየዋለን። በብሉይ ኪዳን እንደሚታየው ክርስቶስ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ዕቅድ ቀጥተኛው ፍጻሜ ነው።

በተጻፈው ቃል አማካኝነት ከእኛና ከተማሪዎቻችን ምላሽ የሚጠብቀውን ሕያው ቃል እናገኛለን። እርሱ የሚጠብቀው ምላሽ የተለወጠ ሕይወት ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡17)። መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው ቃል ነው፤ ምክንያቱም ባጠናነውና በታዘዝነው መጠን ሕያውን ቃል (ኢየሱስን) እንገናኛለን፤ በመንፈስ ቅዱስም አገልግሎት በእርሱ እንለወጣለን (ዮሐ. 14፡26)።

2. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሆነው ቃል

---

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 እና በ2ኛ ጢሞ. 3፡16-17 በመደገፍ «በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው» እና የእግዚአብሔር «መንፈስ ያለበት» የሚሉትን ቃላት አብራራ። ከእነዚህ የሚመሳሰል ቃል በሌላ በታ የት ይገኛል? ለ) የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ማን ነው?

---

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የጻፈው የግል ደብዳቤ ነው። ብዙዎች እግዚአብሔር ለልጆቹ የተናገረውን ለመመልከት መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ከማንበብ ይልቅ አንዳንድ ተወዳጅ ምዕራፎችን በመመልከት ብቻ ይወሰናሉ። ከጓደኛህ የደረሰህን ደብዳቤ ወዲያውኑ አንብበህ

እንደምትጨርሰው የማያጠራጥር ነው። ሆኖም ለእኛ የተላከውን የእግዚአብሔርን ልዩ ቃል ብዙ ጊዜ በዚያ ዓይነት ትጋት አናነብም። አንዳንዶች መዝሙረ ዳዊትን ስለሚወድዱ ከዚያ ብቻ ያነባሉ። አንዳንዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምልክት ያደረጉባቸውን ጥቂት ክፍሎች መላልሰው ያነብባሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ያነበባችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ?

እግዚአብሔር ቃሉ እንዲጻፍ ያደረገው እንዴት አድርጎ ነው? 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 እግዚአብሔር ቃሉን ለማጻፍ የተጠቀመበትን ሂደት ግልጽ ሥዕል ከሁሉ በተሻለ ሁኔታ የሚያሳየን ክፍል ሳይሆን አይቀርም። «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» የዚህ ነገር ውጤቱ እነዚህ ሰዎች የጻፉአቸው ቃላትና አሳቦች የእግዚአብሔር ቃላትና አሳቦች ነበሩ ማለት ነው። እውነተኛ፥ ትክክለኛና ሥልጣን ያላቸው ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ መጻፍ የሚያመለክተው ጸሐፊዎቹ ቃሉን በሚጽፉበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ተጽዕኖ ነው።

«መንፈስ ቅዱስ የጸሐፊዎችን ልዩ ማንነት በመጠቀም እርሱ የሚፈልገውን ሁሉ እንዲጽፉ እናም በትክክልና ያለ ስሕተት እንዲጽፉ ጸሐፊዎችን ይመራቸውና ይቆጣጠራቸው ነበር» («Thiessen» ቴስን፥ ገጽ 65)።

በ2ኛ ጢሞ. 3፡16–17 እንዲህ እናነባለን፡– «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል»። የ«እግዚአብሔር እስትንፋስ» የሚለውን ቃል እንደገና በመዝሙር (33)፡6 ላይ እናገኘዋለን። «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ»። ይህም ስለ ፍጥረት ሲናገር ነው። እንደገናም በዘፍጥረት 2፡7 እንዲህ እናነባለን፡– «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ»።

ስለዚህም ስለ ዓለምና ሞላዋ አፈጣጠር ወይም ከእግዚአብሔር ጋራ ኅብረት ለማድረግ ስለተፈጠረው ሰው ወይም ስለተጻፈው ቃል መገለጥ በምናስብበት ጊዜ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተከናወኑት በእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። በመሆኑም ቅዱሳት መጻሕፍት ከ40 በላይ በሆኑ ጸሐፊዎችና በ1600 ዓመታት ልዩነት መካከል ቢጻፉም ትክክለኛና ጽኑ መሆናቸው አስደናቂ አይሆንም። መለኮታዊው ደራሲ አንድ፥ መልእክቱም የተቀናጀና አንድ ነው ምክንያቱም የወጣው ከአንድ ደራሲ ስለሆነ ነው። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፡– «አዲሱ ኪዳን በአሮጌው ውስጥ ተቀምጦአል፤ አሮጌው በአዲሱ ውስጥ ተብራርቶአል»።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው እያንዳንዱ ክፍልና ቃል በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፈ ነው። ይህ የመጀመሪያዎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመለከታል። አሁን በተለያዩ ቋንቋዎች በመቶ የሚቆጠሩ ትርጉሞች አሉ።

በትርጉሙ ሥራ ላይ የስሕተት መገኘት ሊያጋጥም ይችላል፤ ነገር ግን በመጀመሪያ በተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ማለትም በዕብራይስጥ እና በአራማይክ የተጻፈው የብሉይ ኪዳንና በግሪክ የተጻፈው የአዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተጻፉ ነበሩ።

ለጢሞቴዎስ የተጻፈው ክፍል የሚነግረን ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር እስትንፋስ ተጽፈው የተላለፉልን ሕዝቡ እንዲያድግና እንዲገነባ መሆኑን ነው– «ለትምህርት፥ለተግሳጽ፥ ለዕርማት፥ እና በጽድቅ ላለ ምክር»። መጽሐፍ ቅዱስን በተገቢው መንገድ የመጠቀም ውጤቱ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራም ሁሉ የተዘጋጀ እንዲሆን» ነው። ስለዚህም በቤተክርስቲያን ውስጥ ባለን የማስተማር አገልግሎት ታማኝነት የሞላበት የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ሊተላለፍ ይገባል።

ሮይ ዙክ የተባሉ ሰው እንዲህ ብለዋል፡– «በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ የክርስትና ሕይወት መንፈሳዊ ኃይል ነው። መንፈስ ቅዱስ በመምህሩና በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ካልሠራ ክርስቲያናዊ ትምህርት ተግባራዊነቱ ያልተሳካና ከዓለማዊ ትምህርት ብዙም ያልተለየ ይሆናል።» («Zuck, Holy Spirit in C.E.» ዙክ፤ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ትምህርት፥ ገጽ 18።)

---

12ኛ ጥያቄ፡– ሀ) መጽሐፍ ቅዱስን የክርስቲያናዊ ትምህርት ዋና ማስተማሪያ መጽሐፍ አድርገን በልበ ሙሉነት ልንጠቀምበት የምንችልባቸውን አምስት ጥሩ ምክንያቶች ጻፍ። ለ) በቤተክርስቲያናችሁ የማኅበረ ምእመኑ አባላት በእግዚአብሔር ቃል ጽኑ መሠረት እንዲኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስን በተከታታይ እና በቅደም ተከተል ታስተምራላችሁን? ይህ ትምህርት የሚካሄደው እንዴት ነው?

---

## ሦስተኛ ቀን፡– የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍናና ዓላማዎች

### ፍችዎች

የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና– «ይህ በቤተክርስቲያን ትምህርታዊ መዋቅር ውስጥ ሂሳዊ አስተሳሰብን ማከል ነው። ይህም ሃይማኖታዊው ማኅበረሰብ እምነቱን ለማስተማር በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የሚጠቀምባቸውን መመሪያዎችና አመለካከቶችን መመርመር ነው»። (ዳንኤል ኤት፥ ገጽ 52)

የክርስቲያናዊ ትምህርት ዓላማዎች፡– የክርስቲያናዊ ትምህርትን ፍልስፍና ከጥቅም ላይ ለማዋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የእያንዳንዱን ዕድሜ ክልል ፍላጎቶች ለማሟላት በጥንቃቄ የመርሐ ግብሩን ዝርዝር ነገሮች ሁሉ ማቀድን ይጨምራል። ከቤተክርስቲያን ውጪ የሚካሄደውን የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት ዕቅድም ማካተት አለበት። ዓላማዎቹ ማካተት ያለባቸው ይዘቱን፥ ዘዴውንና የመጠቀሚያ መሣሪያዎችን እንዲሁም የክርስቲያናዊ ትምህርት መርሐ ግብሩን ተፈላጊ ውጤት ነው።

---

13ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና ለመቅረጽ ግንዛቤ ውስጥ ልታስገቡአቸው የሚገባችሁን አንዳንድ ነገሮች ጥቀሱ።

ለ) የክርስቲያናዊ ትምህርት ዓላማዎች ከክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና ጋር እንዴት ይተሳሰራሉ?

1) የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍናን መቅረጽ

ሀ. ስለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶችና እንዴት ለአባላት ልናደርሳቸው እንደምንችል በጽኑ ማሰብ ይገባል። የቤተ ክርስቲያንህ አባላት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጽኑ መሠረት ይኖራቸው ዘንድ እንዴት ከሁሉ በተሻለ ማስተማር እንደሚቻል በሚገባ ማሰብ ያሻል።

ስለሆነም እነዚህ መሠረታዊ ትምህርቶች ምን እንደሆኑና እንዴት አድርገን ልናስተላልፋቸው እንደምንችል በጣም ማሰብ አለብን። የሚከተለው የእምነት መግለጫ አቋም ናሙና ነው።

1. መጀመሪያ በተጻፈበት ወቅት እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ባረፈበት፥ ከስሕተት በጸዳውና ሥልጣን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን (2ኛ ጢሞ. 3፡15-17 ፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡21)።

አሐዱ ሥሉስ በሆነ አምላክ ማለትም በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን (ዘዳ. 6፡4፤ ማቴዎስ 28፡19፤ 2ኛ ጴጥ. 13፡14)።

ሀ. አብ፤ መንፈስ የሆነ የማይወሰን በባሕርዩ ዘላለማዊና የማይለወጥ የሆነ (የሐዋ. 4፡24፤ ዘጸአ. 34፡6)።

ለ. ወልድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ መለኮትነቱን፥ ከድንግል መወለዱን፥ ያለ ኃጢአት መኖሩን፥ የመሥዋዕትነት ሞት መሞቱን፥ በሥጋ ትንሣኤ፥ በአብ ቀኝ በክብር ከፍ ብሎ መቀመጡን፥ በአካል መመለሱን። (ዮሐ. 1፡1፤ ኢሳ. 7፡14፤ ዕብ. 7፡26፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡3-4፤ የሐዋ. 1፡11)።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አካል፥ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሆነና በባሕርዩ አንድ የሆነ (ዮሐ. 15፡26)።

3. ዲያብሎስ ተብሎ የሚጠራው ሰይጣን አካላዊ ህልውና እንዳለው እናምናለን (ራእይ 20፡12)።

4. በሰው ልጅ ውድቀትና ጥፋት ይህም ከእግዚአብሔር ፈጽሞ የመለየቱ ሁኔታ የአዲስ ልደትን አስፈላጊነት እንዳስከተለ እናምናለን (ሮሜ. 5፡12፤ ዮሐንስ 3፡5)።

5. በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምትክ ሞትና በፈሰሰው ደሙ በማመን በእግዚአብሔር ጸጋ ደኅንነት እንደሚገኝ እናምናለን (ቲቶ 3፡4-7፤ ኤፌ. 2፡8-9፤ ሮሜ. 5፡8)።

6. የጻኑት ሰዎች ለዘላለም እንደሚባረኩና የሚጠፉት የዘላለም ቅጣት እንደሚደርስባቸው እናምናለን (ማቴ. 25፡46፤ ፊልጵ. 3፡21)።

7. የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ገጽታ እንዳላትና በመንፈስ የተወለዱትን ሁሉ የምታካትት በመሆኗ፥ በመልክዓ ምድራዊ ክልል በአጥቢያ ደረጃ ለአምልኮ፥ ለመተናነጽ፥ ለምስክርነት የተመሠረተች መሆኗን እናምናለን (ኤፌ. 1፡22-23 ፤ 5፡25-32 የሐዋ. 15፡41 ፤ 16፡5)።

8. ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ለፍጥረታት ሁሉ ወንጌል እንድንሰብክ፥ በማስተማርና በማጥመቅ ደቀ መዛሙርት እንድናደርጋቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን በታላቁ ተልእኮ እናምናለን (ማቴ. 28፡18–20)።

የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና እነዚያን የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነቶች ለሰዎች የሚያስተላልፍበትን መንገድ ማዘጋጀት አለበት።

ለ. ሥርዓተ ትምህርት የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ ትምህርት ለማካሄድ የምንጠቀምበት መንገድ ነው። የክርስቲያናዊ ትምህርት ገጽታዎች በሙሉ ወደ መርሐ ግብሩ አካልነት የሚለወጡት በሥርዓተ ትምህርት ነው።

የእንግሊዘኛው መርሐ ግብር (ካሪኩለም) የሚለው መጀመሪያ ክብ (ሰርክል) ማለት ነበር። ይህም የተወሰደው የሰረገላ ውድድር ከሚካሄድበት ክብ የመሮጫ ሜዳ ነው። ቃሉ የሚያሳየን የሚደረስበት ግብ፥ ለድል የተዘጋጀ ውድድር፥ ልንከተለው የሚገባ የተወሰነ መስመር፥ እንዲሁም ግቡን ለመምታት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ተግባር ነው።

ሥርዓተ ትምህርት የፍልስፍናውን ግቦች ለመምታት የተወጠኑትን የትምህርት ልምምዶች በሙሉ የሚይዝ መሆን አለበት። ሥርዓተ ትምህርት ጠቅላላው መርሐ ግብር ነው ማለት እንችላለን።

በአንደኛ ቀን ከተመለከትነው ትምህርት አንድ፥ በቤተ ክርስቲያን ለሚካሄድ በሚገባ የተቀነባበረ ክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ሦስት በጣም ግልጽ ዓላማዎችን ጠቅሰናል። ከኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ አማኞች በእምነታቸውና ክርስቶስን ወደ መምሰል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለመገንባትና ከስሕተት እንዲጠበቁ፥ እንዲሁም አማኞች ያላቸውን አንድነት በማጠንከር በክርስቶስ አካልነት እግዚአብሔርን ለማክበር እንዲችሉ ለማድረግ እንደሆነ ተመልክተናል።

የክርስቶስ አካል ለእግዚአብሔር ክብር እንድትሠራ እነዚህ የክርስቲያናዊ ትምህርት ገጽታዎች በሙሉ ወደ ሥርዓተ ትምህርትነት መገንባት አለባቸው።

ሐ. መምህራን የቤተክርስቲያንን ትምህርት ለማስተላለፍ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ናቸው። እነርሱም ጥልቅ እና ጽኑ እምነት ያላቸውና የቃሉ ትጉህ ተማሪዎች ሊሆኑ ይገባል። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር የሚወዱ፥ እንዲሁም ተማሪዎቻቸው መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖራቸው የሚናፍቁ ሊሆኑ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በሥራቸው ሁሉ ከፍተኛ ችሎታና ብቃት ያላቸው፥ የነበራቸውን ክህሎት በሥልጠና ለማሻሻል ራሳቸውን ያዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል።

መ. የግንኙነት ዘዴዎችም በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች በተሻለ መንገድ እንዴት አድርገን የእግዚአብሔርን ቃል እንደምናስተላልፍ ብዙ የምንማረው ነገር አለ። ስለዚህም ፍልስፍናው ተከታታይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ዕቅድ መጨመር አለበት።

በማጠቃለያ ላይ የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና የትምህርቱን መርሐ ግብር አጣብቆ የሚይዝ ሙጫ ነው ማለት እንችላለን። ይህም ስለምናምነውና የምናምነውን ለምእመኖቻችን ስለምናስተላልፍበት ዘዴ የሚኖረን ጠንካራ ምርመራ መሠረታዊ ውጤት ነው።

2. የክርስቲያናዊ ትምህርት ዓላማዎች

ዓላማዎች ከትምህርት ፕሮግራማችን ልናይ የምንፈልገውን የመጨረሻ ውጤት ያመለክታሉ። ዓላማዎች የትምህርቱን ይዘት፥ ዘዴና በተማሪዎቻችን ሕይወት ውስጥ ልንፈጽም የምንፈልገውን ውጤት ይጨምራሉ። እንደ አስተማሪዎች በምንሠራው ሥራ ሁሉ ለለውጥ፥ ለተማሪዎቻችን ዕድገትና መታደስ ፍላጎት እንዲኖረን ያስፈልጋል። እንዲሁም እንደ አንጸባራቂ በዚህ ክፉ ዓለም የድል ሕይወት እንዲኖሩና የተባረከውን ተስፋ የክርስቶስን የክብር መገለጥ እንዲጠባበቁ ልንናፍቅ ይገባል።

ዓላማዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቡድኖችን ማለትም ልጆችን፥ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ለማስተማር መቀረጽ ይኖርባቸዋል። እነዚህ እንግዲህ የእያንዳንዱን ደረጃ ፍላጎት በዕድሜ፥ በችሎታና በመረዳት ደረጃ ለመድረስ ያሉ አጠቃላይ ዓላማዎች ናቸው። በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ፍላጎቶችንም ሊጨምር ይችላል።

ለተለያዩ ክፍለ ጊዜዎችም የሚሆኑ ዓላማዎች መቀረጽ ያስፈልጋቸዋል። የተወሰኑ ነገሮችን መቼ ማስተማር እንደሚገባ ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ትምህርት ዓላማዎች ያስፈልጉታል። እነዚህም ዓላማዎች ግቦች ሊባሉ ይችላሉ። ትርጉማቸው አንድ ዓይነት ነው። የሚያካትቱትም ከምናስተምረው ትምህርት የተነሣ በተማሪዎቹ ሕይወት ውስጥ ልናየው የምንፈልገውን ተግባርና ልናስተምር የምናቅደውን ነው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፦ ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የተሳካ የትምህርት ፕሮግራም እንዲካሄድ የሚያስችል ዓላማ በጽሑፍ አዘጋጅተህ አቅርብ። |

## አራተኛ ቀን፦ የክርስቲያናዊ ትምህርት ታሪክ

በአይሁድ ሕዝብ ታሪክም ሆነ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መሪዎች ለእምነታቸውና ለባሕላቸው ተስማሚ በመሰላቸው ዘዴዎች ትምህርት ሰጥተዋል። እምነታቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ትምህርት ሲሰጡ ቆይተዋል።

1. ማስተማር በብሉይ ኪዳን፥ ቅድመ–ምርኮ

በዘጸአት 13፡8–10 ሙሴ፥ አባቶች እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዲጠብቁት ያዘዘውን ትእዛዝና ልምምድ አስፈላጊነትና ትርጉም ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ መመሪያ ሲሰጥ እንመለከታለን። የታሪኩ ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ እና ከፈርኦን እጅ ነጻ ያወጣበት የፋሲካ በዓል የሚከበርበት ጊዜ ነበረ። እንዲህ ይላል፤ «በዚያን ቀን ከግብፅ በወጣሁ ጊዜ እግዚአብሔር ስላደረገልኝ ነው ስትል ለልጅህ ትነግረዋለህ። እግዚአብሔር በብርቱ እጅ ከግብፅ አውጥቶሃልና፥ የእግዚአብሔር ሕግ

በአፍህ ይሆን ዘንድ በእጅህ እንደ ምልክት በዓይኖችህም መካከል እንደ መታሰቢያ ይሁንልህ። በዓመት በዓመት በወራቱ ይህችን ሥርዓት ጠብቃት»።

ዘዳግም 6፡20–25 አንብብ። አባቶች አምላካቸው እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሥርዓቶች፥ ደንቦችና ሕግጋት ትርጉሞች ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ ታዝዘዋል።

መጽሐፈ ምሳሌ ከታማኝ አባት ለልጆች የተሰጡ መመሪያዎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። ሰሎሞን በምሳሌ ውስጥ ስንት ጊዜ «ልጄ ሆይ» ወይም «ልጆቼ ሆይ» እንዳለ አስተውላችኋልን? እርሱ ልጆቹን በመምከርና በማበረታታት ታማኝ ነበር።

---

15ኛ ጥያቄ፡– ሀ) መጽሐፈ ምሳሌን በመመልከት ሰሎሞን ለልጁ ወይም ለልጆቹ ስንት ጊዜ እንደተናገረ ተመልከት፤ የምትችለውን ያህል ጥቅሶች ጻፍ። ለ) ዘዳግም 6፡4–7ን አንብብ። አባቶች ልጆቻቸውን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ግለጽ።

---

## 2. ትምህርት በብሉይ ኪዳን፥ ከምርኮ በኋላ

ምኵራቦች የተመሠረቱት ከምርኮ በኋላ ነበር (ከ532 ዓ.ዓ በኋላ)፤ በኋላም የትምህርት፥ የአምልኮና የቅዱሳት መጻሕፍት ማንበቢያ ስፍራዎች ሆኑ። በየመንደሮች ወይም ከተማዎች ሁሉ ቢያንስ አንድ ምኵራብ ይገኝ ነበር። ያም ስፍራ የጸሎትና የሕጉን መመሪያ የመቀበያ ቦታ ነበር። «የሕግ መምህራኑ» በአይሁድ ኅብረተሰብ በጣም የተከበሩ ስለሆኑ ወላጆች ልጆቻቸው በእምነታቸው ሥር እንዲሰድዱ የሚልኩት ወደ እነርሱ ነበር።

ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ከወላጆቹ ጋር ሄዶ በመቅደስ ያመለከው በ12 ዓመቱ የምኵራብን ሥልጠና በጨረሰ ጊዜ እንደነበር እናስታውሳለን። አይሁዳውያን ወንዶች በሙሉ በኢየሩሳሌም ወዳለው መቅደስ ሄደው ለማምለክና መሥዋዕት ለማቅረብ የሚችሉት በዓመት ሦስት ጊዜ ብቻ ሲሆን፥ በቀሪዎቹ የዓመቱ ጊዜያት የሚያመልኩትና የሚማሩት በምኵራቦቻቸው ነበር።

ነህምያ በኖረባቸው ጊዜያት የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ከተሠሩ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በቤተመቅደሱ ግቢ ውስጥ ተሰብስበው ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ አምጥቶ እንዲያነብላቸው ጠየቁት። እንዲህ ይላል፤ «በውኃውም በር ፊት ባለው አደባባይ ላይ ቆሞ ወንዶችና ሴቶች የሚያስተውሉም ሲሰሙ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ አነበበው፥ የሕዝቡም ሁሉ ጆሮ የሕጉን መጽሐፍ ለመስማት ያደምጥ ነበር» (ነህ. 8፡3)። ቁጥር 8 በተጨማሪ እንዲህ ይላል፤ «የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ። ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር። ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር»።

## 3. ማስተማር በመጀመሪያዋ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን

ኢየሱስ ይታወቅ የነበረው «ረቡኒ» መምህር በሚለው አጠራር ነበር። ዘዴውም ትምህርታዊ እንጂ ንግግር (ዲስኩር) ብቻ አልነበረም። ለሐዋርያቱ የሰጠው የመጨረሻው ትእዛዝም፥ «… ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ደቀመዛሙርት አድርጓቸው… እያጠመቃችኋቸው… ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው…» (ማቴ 28፡20 የሚል ነበር)።

ከጴንጤቆስጤ በዓል በኋላ ወዲያውኑ ሐዋርያቱ በተለይም ጴጥሮስ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ወዳለ እምነት እንዲመጡ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ፥ ጥያቄዎቻቸውን ሲመልሱ፥ ሲለምኑአቸውና ሲያስጠነቅቁአቸው እናገኛቸዋለን። ብዙዎችም ወደ ጌታ መጡ። እነዚያም የመጀመሪያ አማኞች፥ «በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር» (የሐዋ. 2፡42)።

ሐዋርያቱን ወደ ሕዝብ ወኅኒ ከጣሉዋቸው በኋላም ጌታ በሮችን ከፍቶ ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ ይመራቸው ነበር (የሐዋ. 5፡21–25)። በምዕራፉ መጨረሻ ላይ ምንም እንኳን ባለሥልጣኖች በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ ቢያስጠነቅቁዋቸውና ቢያዝዟቸውም እንዲህ የሚል እናነባለን። «ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር» (ቁ. 42)።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ከኢየሩሳሌም ወደ አገሩ ይመለስ የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከትንቢተ ኢሳይያስ እያነበበ ሲሄድ ፊልጶስ ወደ ሠረገላው ወጥቶ ከእርሱ ጋር እንዲሄድና ጥያቄዎቹን እንዲመልስለት ጠየቀው። «እባክህ ነቢዩ ይህን ስለ ማን ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ? አለው። ፊልጶስም አፉን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት» (ቁ. 35)።

ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 20፡21–31 እና ቁ. 27 የሚከተለውን ተናግሯል። «ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ፥ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም።... የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና፥ ምንም አላስቀረሁባችሁም»።

ጳውሎስ በጊዜው የነበሩትን ክርስቲያኖች ለመምራትና ለማስተማር አሥራ ሦስት መልእክቶችን ጽፎአል። በቂ ምክንያት አቅርቦ ሰሚዎቹን ሊያሳምን የሚችል ድንቅ መምህር ነበር። በእርሱ ጊዜ የነበሩትን አማኞች በእምነታቸው እውነት ላይ የተመሠረቱና ሥር የሰደዱ እንዲሆኑ ሁሉንም ዓይነት መንገድ ማለትም ስብከትን፥ ማስተማርንና መጻፍን ይጠቀም ነበር።

በጢሞቴዎስና በቲቶ ላይ እንደተገለጠው ለዲያቆናትና ለሽማግሌዎች የወጣው መመዘኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስተማር የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ልብ ውስጥ ክርስቲያኖች የሚያምኑትን እንዲያውቁና በትምህርት እንዲያድጉ ማድረግ አንገብጋቢ ጉዳይ እንደነበረ እንመሰከራለን።

4. ትምህርት በዘመናት ውስጥ (ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ከታመነ የቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተገኘ መረጃ ነው።)

ሀ. በአንደኛው ክፍለ ዘመን

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከይሁዲነት የተለወጡ ነበሩ። በምዕራብ በሚሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለፉና ብሉይ ኪዳንን በሚገባ የሚያውቁ ነበሩ። የሚያስፈልጋቸው አዲስ ትምህርት ስለ ኢየሱስ፥ ስለ ትምህርቱ፥ ሕይወቱ፥ ሞቱና ትንሣኤው ነበር። ኢየሱስ ለብዙ ጊዜያት ሲጠበቅ የነበረው እውነተኛው መሢሑ እንደሆነ ሊገነዘቡ ያስፈልግ ነበረ። ትምህርቱ ይካሄድ የነበረው በዋናው የአገልግሎት ጊዜ ነበረ፤ ይህም ከምዕራብ አሠራር የቀጠለ ሲሆን ስብሰባው የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብንና ትርጉምን ያካትት ነበር።

በኋላ ይህ አሠራር በሁለት ተከፈለ። የመጀመሪያው ከጥምቀት በፊት ትምህርትን ለሚቀበሉ ሲሆን ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብንና ትርጉምን ያካትት ነበር። እነዚህ ሰዎች «ሰሚዎች» በመባል ይታወቁ ነበር። ሁለተኛው ክፍል ለቤተክርስቲያን አባላት የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የጌታ እራትን ይጨምር ነበር።

ለ. ከሁለተኛው እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን

ብዙ አረማውያን በዚህ ክፍለ ጊዜ ጌታን አምነው ተለውጠዋል። በዚህ ሁኔታ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ሰዎች ሕይወታቸው በሥነ ምግባር የታነጸና በማስተዋል እውቀት የተገነባ እንዲሆን ዝርዝርና ጥልቅ ትምህርት ያስፈልጋቸው ነበር። ይህ ሦስት ዓላማ ነበረው። «1) ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣውን ሰው ሥነ ምግባራዊ እውነተኛነት የመፈተኛ ጊዜ። 2) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለመስጠትና የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለማስተማር። 3) አማኙ ለጥምቀት እየተዘጋጀ ሳለ ውስጥና እውነተኛ ወደሆነ ክርስቲያናዊ ኅብረት ለማስገባት (ዳንኤል /«Daniels»፥ ገጽ 37)።

ለእነዚህ ሰዎች እንደ የግል ፍላጎቶቻቸው በቡድን ቀጥተኛ ያልሆነ ሥልጠናም ይሰጥ ነበር። ኦሪገን የተባለው በአሌክሳንደሪያ በ250 ዓ.ም አካባቢ ይኖር የነበረ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባት ይህንን በተመለከተ ስላለው የመርሐ ግብር ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ጽፏል። 1) የአዲስ አማኙን ግብረገባዊ ባሕርይና ተግባር የሚዳስስ የቅድሚያ ምርመራ፥ 2) አስፈላጊ ከሆነ ግላዊ የሆነ መመሪያ መስጠት፥ 3) እንደ «ሰሚ» በአምልኮ እንዲሳተፉ መቀበል፥ 4) ከአምልኮ አገልግሎቶች በኋላ ተጨማሪ መመሪያዎች የሚሰጥበት ጊዜ፥ 5) ተማሪው እንዲያድግ ዕውቀትንና ግብረገብነትን በተመለከተ ተጨማሪ የሆነ መጠይቅ፥ 6) ከጥምቀትና ከቤተ ክርስቲያን አባልነት በፊት ጥልቅና ዝርዝር የሆነ ትምህርት (ዳንኤል/ «Daniels»፥ ገጽ 37)።

አሁን እንደምንረዳው የክርስትና ትምህርት ርእሰ-ጉዳዮች ከሰሚዎቹ ሁኔታዎችና የመረዳት ደረጃዎች ጋር የተገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

በዚህ ጊዜ የሐሰት ትምህርት ዋና ችግር እየሆነ መጣ። ከቦታ ወደ ቦታ የሚዘዋወሩ አስተማሪዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ተቃራኒ የሆነ ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ያስፋፉ ጀመር። አንዳንዶቹ ግርዛትንና ሕግ መጠበቅን በአዳዲስ አማኞች ላይ ሊጭኑ የሚፈልጉ የአይሁዳዊነት እምነት አስፋፊዎች ነበሩ። (ጳውሎስ በገላትያና በቆሮንቶስ

መልእክቶች፥ ዮሐንስ ደግሞ በ1ኛ መልእክቱ ይህን ትምህርት ፋርሽ በማድረግ እንዴት እንዳስተማሩ ተመልከቱ።)

ወደ ቤተክርስቲያን ውስጥ እየመጡ የነበሩትን እነዚህን የስሕተት ትምህርቶች ለመቃወም የተጻፉ ጽሑፎች በመልእክቶች ውስጥ ብዙ ቦታ ሸፍነዋል። በሁለተኛ ቀን ላይ ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት የመጠበቅን አስፈላጊነት እንደተማርን ታስታውሳላችሁ፤ ይህ በቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ የክርስቲያናዊ ትምህርት አንዱ ተግባር መሆን አለበት።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሥረ- መሠረታቸው ከአይሁድ ወይም ከአረማውያን ለሆኑ ሰዎች ከቀረበው የትምህርት አሰጣጥ ልዩነት ያጤንኸው ምንድን ነው? ከዚህ ምን እንማራለን? ለ) በኢትዮጵያ የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ከሚፈታተኗት የስሕተት ትምህርቶች አንዳንዶቹን ጥቀስ። እነዚህን የስሕተት አስተማሪዎች በምትገናኛቸው ጊዜ እምነትህን ለመከላከል የምትናገረው ነገር ምንድን ነው? |

## ሐ. ከአምስተኛው እስከ አሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን እና ተሐድሶ።

በመቶዎቹ በሚቆጠሩት በእነዚህ ዓመታት በቤተክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት በቂ ጥረት ስላልተደረገ በተራው ምእመንም ሆነ በካህናቱ ዘንድ የነበረው ደካማነትና ያለማወቅ ገሃድ የወጣ ነበር። በገዳማት ተዘግተው የሚኖሩ ጥቂት መነኩሴዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጠበቅ ይፈልጉ ነበር። በአውሮፓ እና በእንግሊዝ አገር የሚገኙ ጥቂት ብርቱ መሪዎች ተሐድሶ ለማምጣት የሞከሩ ቢሆኑም እስከ አሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ውጤት ያለው አንዳችም ነገር አልተፈጸመም።

ለትምህርት በነበረ ታላቅ ጥማት ለዓለማዊ ትምህርት ዳግመኛ መወለድ በር የከፈተ የለውጥ እንቅስቃሴ በአውሮፓ ተከሰተ። ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጳጳሱን ሥልጣን በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን የተካ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መጣ። የዚህ እንቅስቃሴ አንዱ ትኩረት በእያንዳንዱ አማኝ ክህነት ላይ ስለነበር እያንዳንዱ አማኝ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለበትን የግል ኃላፊነት በመመርኮዝ ዓለም አቀፋዊ ትምህርትን አስፋፋ።

ሉተር፥ ሜላክተን፥ ዝዊንግሊ፥ ካልቪን እና ጆን ኖክስ የተባሉት የዘመኑ የተሐድሶ መሪዎች በጀርመን፥ በስዊዘርላንድ እና በስኮትላንድ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ለወንዶችና ለሴት ልጆች ትምህርት ቤት እንዲመሠረት እንዲያደርጉ አበረታቱ። እነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት በሕዝቡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ የሕዝቡን መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ የትምህርት ፍላጎት የሚያሟሉ ነበሩ። እነዚህ መሪዎች በተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ሕዝቡ ቋንቋ በመተርጎም ተራው ሕዝብ በሙሉ ሊያነባቸው እንዲችል አድርገዋል። እነዚህ ትርጉሞች በቤተ ክርስቲያን ይነበቡ፥ በቤት ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውሉና በትምህርት ቤትም ይጠኑ ነበር። እንዲሁም በሕዝቡ ቋንቋ መስበክ ጀምረው ነበር፤ ቀድሞ ግን ሁሉም ነገር በላቲን ቋንቋ ብቻ ነበር። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እጦት የተነሣ እየሞተች በነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መነቃቃትና መታደስን አመጣ።

በኋላም ይህ እንቅስቃሴ ወደ ኔዘርላንድ ተስፋፋ። በመጨረሻም ወደ አሜሪካ ተሰራጨ።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ጎተንበርግ የተባለው ሰው የማተሚያ መማሪያን ፈለሰፈ። በዚህም መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎች የጸሎት ጊዜ የጥሞና ጽሑፎች በተሻለ ፍጥነት ለማባዛትና ለመሰራጨት ቻሉ። መጻሕፍት በብዙ ቁጥር ለመታተም በመቻላቸው የሚያነባቸው ሰው ቁጥር ጨመረ።

መ. የሰንበት ትምህርት ቤት እንቅስቃሴ

በ1780 ዓ.ም ሮበርት ራኪስ የተባለ እንግሊዛዊ በፋብሪካ ውስጥ ወይም በማዕድን ቁፋሮ ተግባር ተቀጥረው በሳምንት ለስድስት ቀናት የሚሠሩና ለትምህርት ዕድል ያላገኙ ብዙ ድሆች ልጆችን ችግር ተመለከተ። እርሱም በፈቃደኛ መምህራን የሚሰጡ የሰንበት ትምህርት ቤቶችን በማደራጀት ልጆቹ ማንበብ እንዲችሉና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያጠኑ እንዲሁም መሠረታዊ ትምህርቶችን እንዲማሩ የሚደረግበትን ዕድል አዘጋጀ። ይህን እንቅስቃሴ በእንግሊዝ አገር ያለው ኖክስ ደገፈው፤ ወዲያውም ወደ አሜሪካ አገር ሁሉ ተሰራጨ። ከዚያን ጊዜ ወዲህም በአውሮፓ እና በአሜሪካ ከቤተክርስቲያን ተግባራት አንዱ ክፍል ሆኖ ቀጥሏል።

ይህ እንቅስቃሴ እያደገ በሄደ መጠን ዓለማዊውን ትምህርት መንግሥት ሲወስድ፥ ለልጆች የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀጠለ። ለወጣቶችና ለጎልማሶች የሚሆኑ ክፍሎችም ተከፈቱ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዱ የዕድሜ ክልልም ቀጣይ የሆነውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ለመቀበል እስከ ዛሬ ድረስ ችሏል።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያንን የክርስቲያናዊ ትምህርት ታሪክ በምትሰማበት ጊዜ በቀድሞ ዘመን ከነበረው ብርታትና ጥንካሬ የተማርከው ምንድን ነው? ለ) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስላለው ክርስቲያናዊ ትምህርት ፍላጎት በምታስብበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር ልታዛምደው የምትችለው አዎንታዊ አሳብ አለህን? |

5ኛ ቀን፡- ሳምንታዊ ስብሰባ

1. መሪው አምስት ደቂቃ የሚወስድ የጽሞና መልእክት ማዘጋጀት አለበት።

2. ለራሳችሁና በቤተ ክርስቲያን የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ስላላችሁ ተሳትፎ ለአሥር ደቂቃ ያህል ጸልዩ።

3. በዚህ የመጀመሪያ ሳምንት ትምህርት ጥያቄዎች ላይ አንድ ጊዜ ተነጋገሩባቸው፤ የዚህ ትምህርት ዓላማ የክርስቲያናዊ ትምህርት መሠረት የሆነው ያለፈው ታሪክ ምን እንደሆነ መረጃ መስጠት እንደሆነ ትረዳላችሁ። ለተማሪዎች አዲስ በሆኑ ንድፈ አሳቦችና አስተሳሰቦች ላይ ተነጋገሩባቸው።

4. ከዚህ በሚቀጥሉት ጥያቄዎች ላይ ትንሽ ጊዜ በመውሰድ ተወያዩ።

ሀ. ስለ ክርስቲያናዊ ትምህርት የራሳችሁን ትርጉም ከልሱ፣ ለክፍሉ አንብቡት። በአሳባችሁ ላይ ልትጨምሩት ወይም ልትቀንሱ የሚያስፈልግ ነጥብ ይኖራልን?

ለ. በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ባለው የክርስቲያናዊ ትምህርት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ ተወያዩ፣ መሻሻል ሊገኝ የሚቻልባቸውን የመፍትሔ አሳቦች ስጡ።

ሐ. ቤተ ክርስቲያናችሁ መተዳደሪያ ደንብ አላትን? የእምነት መግለጫስ? አጥንታችሁታልን? የክርስቲያን እምነት አስተምህሮዎችን በትክክል የያዘ ነውን? ካልሆነ መጨመር ያለበት ምንድን ነው?

መ. ከታሪክ ልንማር እንችላለን? እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ውስጥ በኃይል ስለ ሠራ አንጸባራቂና የምታድግ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር አድርጓል። ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት ምክንያት የሆኑ አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? አሉታዊ ተጽዕኖ የነበራቸው አንዳንድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

5. ስብሰባውን በጸሎት በመዝጋት እነዚህን ንድፈ አሳቦች በቤተ ክርስቲያናችሁ ሕይወት ውስጥ ለማየት እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁ።

# ትምህርት ሁለት

## የቤተ ክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት

### 1ኛ ቀን፡- ቤተ ክርስቲያን- የክርስቲያን ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላት ምን ነበሩ? ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፥15-20 ሉቃ. 24፥ 45-49 እና ዮሐ. 20፥21 አንብብ። ለ) ይህ ታላቁ ተልዕኮ ከዚህ ዘመን አገልግሎት ጋር ይዛመዳል? ሐ) ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲያደርጉ የተናገራቸው አራቱ ነገሮች ምንድን ነበሩ? መ) ለእነርሱ የገባላቸው የተስፋ ቃል ምን ነበር? |

1. ቤተክርስቲያን ማስተማር ያለባት ለምንድን ነው?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ፥ ከተቀበረ እና ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን በገሊላ ተራራ ላይ እንዲገናኙት ተናገራቸው። በተገናኙም ወቅት እንዲህ አላቸው። «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ 28፡18-20)።

ጌታ ወደ ሰማይ ዐርጎ በአብ ቀኝ የተቀመጠው እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ ነበር።

በዚህ ትምህርት ኢየሱስ በመጨረሻ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትእዛዝ ምንን እንደሚያመለክት እናያለን? አንድ የቤተሰብ ኃላፊ ሊሞት ሲቃረብ ቤተሰቡ የኑዛዜውን ቃል ወይንም በመጨረሻ ሊናገር የሚፈልገውን ፈቃዱን

ለማዳመጥ ይጓጓሉ። የክርስቶስ ቤተሰቦች የሆንን እኛም እንዲሁ ጌታችን የተናገራቸውን የመጨረሻ ቃላት ተጠንቅቀን ልንይዝ ይገባናል። ምክንያቱም ጌታችን ማስተማር እንዳለብን አዝዞናልና።

ደቀ መዛሙርቱ ከጌታ ጋር ለሦስት ዓመት ተኩል እንደተመላለሱና ሲነጋገሩ እንደቆዩ ማስታወስ አለብን። ጌታም በቃልና በምሳሌነት ታማኝ ሆኖ ያስተምራቸው ነበር። በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ፈቃድ ታዛዥ እንድትሆን የሚያደርጉ በቂ ሥልጠና የተሰጣቸው መሪዎች ያስፈልጋሉ።

2. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ዓለም ላካቸው

ሀ. የመጀመሪያው የኢየሱስ ትእዛዝ "ሂዱ" እና "ወንጌልን ስበኩ" የሚለው ነው።

1. ወንጌልንም ለመስበክ የሚያስችለውን ኃይል መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷቸዋል።

ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው የመጨረሻ ቃላት በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ተካትተዋል። በመጀመሪያ ጌታ ያዘዘው "ሂዱ" በማለት ነው። በማርቆስ ወንጌል እንደ ተጻፈው ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ «ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» (ማር. 16፡15)። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ (ቀደምት) ተግባሯ ወንጌልን ማሠራጨት ነው። በአብዛኛው ዛሬ ይህ ተግባሯ እንደ መጨረሻው ሥራ ተቆጥሮ የተተወ ወይንም ከነጭራሹ የተረሣ ነው። የጌታ የመጀመሪያ ትእዛዝ ግን "ሂዱ" የሚል ነው። ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ (ዮሐ. 20፡21)"

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1፡8 ላይ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። «...ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»።

መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ለወንጌል ሥራ ቅባትን ለመስጠት ተልኳል። ዮሐ.14፡17 እንዲህ ይላል፦ «...ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን....»። በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 26 «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል»። ዮሐንስም በምዕራፍ 16፡13–14 ላይ ጨምሮ ሲጽፍ፥ «...እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል፤ እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና»።

አማኙ ከተለወጠበት ጊዜ ጀምሮ በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በማስተማር፥ በመምራት፥ ኢየሱስ የተናገረውን በማሳሰብ ሥራውንም ለመሥራት የሚያስችል ኃይል እየሰጠ አብሮት ይኖራል።

2ኛ ጥያቄ፦ ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ 28፡13 አንብብ። ለእውነተኛ ንስሐ የሚያስፈልጉን ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው? ኢሳ. 55፡6-7 አንብብ። እውነተኛን ንስሐ ስንገባ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

**2. ንስሐ ስለመግባትና በክርስቶስ ላይ ስላለ እምነት ማስተማር አለብን።**

ጌታ ኢየሱስ ያዘዘን ወደ ዓለም ሁሉ "ሄደን" የእርሱ ምስክሮች እንድንሆን ነው። ለዚህ ደግሞ የሚያስችለንን በውስጣችን በሚኖር መንፈስ «ቅዱስ» አማካኝነት ሰጥቶናል። ይህ መንፈስ ቅዱስ «የእውነት መንፈስ» ነው። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ንጹሕ በሆነ ዕቃ ውስጥ ስለሚሠራ ራስን በሙላት እውነትን ለሚናገር ለእርሱ ማስረከብ ይገባል።

ወንጌልን ስናውጅ ወንጌል በጣም ግልጽ ሆኖ መቅረብ አለበት። (አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣት የሚያስችለንን ትምህርት ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት ትምህርት አምስት፥ አራተኛ ቀን ተመልከት።) ኢየሱስ በሉቃስ 24፡47 ስለ ራሱ ሲናገር፥ «በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል» ብሏል። መጥምቁ ዮሐንስና ኢየሱስ ሁለቱም የመጡት «የንስሐን» ስብከት እየሰበኩ ነበር።

ንስሐ መግባት ማለት የራስን አቋም መለወጥና ስለ ሠሩት የተሳሳተ ሥራ መጸጸት፥ ከክፋት መንገድ መመለስና ትክክለኛውን መንገድ ለመያዝ ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። በምሳሌ 28፡13 ላይ እንደተጻፈው «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል»። እንደገናም በኢሳይያስ 55፡6-7፥ «እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፥ ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ»።

ሰዎች ወደ እውነተኛው የንስሐ ሕይወት እንዲመጡ ከምስክርነት ጋር ኃጢአት ምን እንደሆነ ጥንቃቄ የሞላበትን ትምህርት በማዘመድ ማቅረብ አለብን። ኢየሱስ በሉቃስ 5፡31፥ «...ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም፥ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው»። አንድ ሰው በትክክል ለመዳን ያለምንም ተስፋ የጠፋ መሆኑን ማወቅ አለበት። በሮሜ 3፡10-12፥ «ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም» ተብሎ ተጽፎአል።

ለኃጢአተኛ ብቸኛ መፍትሔ ኃጢአቱን መናዘዝና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። ጌታ ኢየሱስ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ለማስወገድ የራሱን ሕይወት ሰጥቷልና። በኢሳይያስ 53፡6፥ «እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ (በክርስቶስ) ላይ አኖረ» ተብሎ ተጽፎአል። ተስፋችን እርሱ ጌታ ብቻ ነው። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ

የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3፡16)። «በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል» (ዮሐ 3፡16–18)።

ንስሐ ያልገባ ኃጢአተኛ ፍጻሜ በሌለው ዘላለማዊ ቅጣት ከእግዚአብሔር ተለይቶ በገሃነም እንዲኖር ተኮንኗል። ሉቃስ 16፡19–31፤ ዮሐ. 3፡36 አንብብ። ኃጢአትን መናዘዝና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ክርስቲያን ለመሆን የሚወሰዱ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። እነዚህን እርምጃዎች ያልወሰደ ሰው ዳግም ተወልዷል ማለት አጠራጣሪ ነው።

ለ. አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው

ደቀ መዝሙር ከአስተማሪው የተለያዩ ትምህርቶችን የተማረ ሰው ነው (Douglas/ዳግላስ፥ ገጽ 285)። በተጨማሪ ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍልም እንኳ ኢየሱስ የተናገረውን ማስቀደምን ይጨምራል።

ኢየሱስ በዙሪያው ላሉ ሕዝብና ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር፥ «... በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ» ብሏል።

አንድ ሰው ለደኅንነት የሚሆን ውሳኔ አድርጎ ወደ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንዲሰጥ የሚያስችለውን ትምህርት ይፈልጋል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 6፡19–20 ሲያስተምር፥ «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፥ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» ብሏል።

አዲስ አማኝ የክርስቶስ አካል ክፍል እንደሆነ ተገንዝቦ በሚያደርገው ነገር ሁሉ ጌታን ማክበር እንዳለበት መረዳት ይገባል። ወደዚህ መረዳት ደግሞ የሚመጣው ቅዱስ ቃሉን እየተማረ በክርስቶስ ውስጥ የሚኖር ሰው ሕይወት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት በሚገባ ሲገነዘብ ነው።

ሐ. በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው

ጥምቀት በኃጢአታችን ንስሐ ስለ መግባታችንና በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ማመናችን በሰዎች ፊት የምንሰጠው ምስክርነት ነው። በሐዋርያት ሥራ 2፡38–41 ላይ ጴጥሮስ ሰዎች ከኃጢአታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ በመወሰን እጅግ ጠንካራ የሆነ ትምህርት ሲሰጥ እንመለከተዋለን። ሰዎቹም ኃጢአተኝነታቸውን በማመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ እንደለመኑ እናያለን። በሐዋርያት ሥራ 3፡19 ጴጥሮስ፥ «...ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም» ብሏል። ከዚህም በኋላ እስካሁን ድረስ ባልተቀበሉት በመሢሑ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ነበረባቸው፡ ለአንድ አይሁዳዊ ይህን እርምጃ መውሰድ ከፍተኛ ነገር ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ኃጢአት የተሸከመ ደኅንነትን የሚሰጠው መሢሕ መሆኑን መቀበል ነበረበት። «መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት

ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)። ዛሬም ለእኛ እንዲሁ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ከተቀበሉ በኋላ ተጠምቀው ኃጢአታቸው ይቅር እንደተባለላቸው በማረጋገጥ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። በሮሜ 6:4 እንደ ተጻፈው፥ «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን»።

ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር ስለ መሞታችንና ከእርሱ ጋርም በአዲስ ሕይወት ሕያዋን ሆነን ስለ መነሣታችን በሰው ፊት የምንሰጠው ምስክርነት ነው። በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 11 ላይም «እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ» ተብሎ ተጽፎአል።

መ. ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው

ከጥምቀት በኋላም ትምህርት መቀጠል አለበት። ይህም ጥልቅ የሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዛትን መማር መቀጠል ስላለበት ነው። አዳዲስ የቤተክርስቲያን አባላትን ማስተማር ብዙ ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚገባ ተግባር ነው። ምክንያቱም የክርስትና ሕይወት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ገና ልጆች ናቸውና። በትምህርት 16፤ ከ1–4ኛ ባሉት ቀናት ለአዳዲስ አማኞች ምን ማስተማር እንዳለብን ተጨማሪ ትምህርት በስፋት እንሰጣለን።

3. ለአገልግሎት ማብቃት

ኢየሱስ ይህ ሥራ የእኛ ብቻ ያለመሆኑን በሁለት ነገሮች አረጋግጦልናል።

ሀ. ኢየሱስ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶታል (ማቴ. 28:18)።

ሰይጣን ለጌታ ኢየሱስ የዓለም መንግሥታትን ሥልጣንና ክብር ሁሉ አቅርቦለት ነበር። ሰይጣን በኩራት ተሞልቶ እንዲህ አለ፤ «ሥልጣንና የዓለምን መንግሥታት ክብራቸው ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶኛል ለምወደው ለማንም እሰጠዋለሁ አንተ ወድቀህ ብትሰግድልኝ እሰጥሃለሁ»።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ ጥቂት ጊዜ በፊት እንዲህ ብሏል፤ «አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል አሁን የዚህ ዓለም ገዢ ወደ ውጪ ይጣላል»። በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የሰይጣን ኃይልና ሥልጣን ተገፎአል። ኢየሱስ ክርስቶስ ድልን ተቀዳጅቷል። ስለዚህም ኢየሱስ ሥልጣን ሁሉ በሰማይ በምድር ተሰጠኝ ለማለት ይችላል። ስለሆነም እኛ ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ምንም ፍርሃት ሊሰማን አይገባም። «በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» (1ኛ ዮሐንስ 4:4)።

ለ. ከእኛ ጋር ሊኖር ቃል ገብቶልናል

ኢየሱስ ሥልጣን እንዳለው ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋር እንደሚሆንም ቃል ገብቶልናል። «እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28፡20)። እንደገና በማርቆስ ወንጌል 16፡15-18 ላይ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን እንዲሰብኩ ካዘዛቸው በኋላ «እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር» የሚል ቃል ቁ. 20 ላይ እናነባለን።

ልንሠራው የሚገባን ታላቅ ሥራ የተሰጠን ቢሆንም እንኳ እርሱ ሊመራንና ብቁ ሊያደርገን ከእኛ ጋር እንዳለ ዋስትና ተሰጥቶናል። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን መገንባት (ማደግ) እና በእምነት መጠንከር እንዳለባት ትእዛዝ ተሰጥቷታል። ይህ የሚሆነው ደግሞ ቃሉን በታማኝነት በማስተማር፥ ለትምህርቱ በመታዘዝና በዕለታዊ የሕይወት አኗኗር ተግባራዊ፥ በማድረግ ነው።

4. ጥንቃቄ የጎደለው ትምህርት ውጤት

ቤተክርስቲያን የማስተማር አገልግሎትን ችላ ካለች ምእመናን እንዴት መኖር እንዳለባቸው በመዘንጋት ከዕለት ወደ ዕለት የበለጠ ዓለምን እየመሰሉ ይሄዳሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስኬታማ በሆነ አገልግሎት ፊት የተደቀነው ትልቁ አደጋ ከውስጥ የሚነሣ ችግር ነው። ያለ በቂ ጥናት፥ ጸሎትና ዝግጅት የሚሰጥ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን እንድታንቀላፋ በማድረግ ለመከፋፈል በር ይከፍታል። አወዛጋቢና ወጥ ያልሆኑ ልምምዶችን ያስከትላል። የምእመናን ቁጥር እየቀነሰ ይመጣል፤ ምእመናን እሑድ ጠዋት ወይም የጸሎት ስብሰባዎች በሚደረጉባቸው ምሽቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ ይልቅ ሌላ ነገር ይመርጣሉ። ቤተ ክርስቲያን የአሕዛብ መሳለቂያ ትሆናለች።

ስማርት “Smart” በጻፈው መጽሐፍ በ32ኛው ገጽ ላይ፥ «ቤተክርስቲያን ወደ ተራራ በመውጣት የራሷን ሕይወትና እምነት በሁሉም አቅጣጫዎች መመርመር አለባት፤ ይህም የዓይነ-ስውርነትን፥ ያለማመንን፥ ያለመታመንንና ያኃጢአትን መኖር ተረድታ ጊዜው ሳያልፍ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት እንድትችል ነው» ብሏል።

5. ቤተክርስቲያን ለመኖር የግድ ማስተማር አለባት።

አማኞችም ለቃሉ ታዘው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ መኖር እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ቃል መማር አለባቸው። የእግዚአብሔርን ቃል የምትማርና ቃሉን የምትታዘዝ ቤተክርስቲያን ደግሞ ወንጌልን ለሌሎች ታደርሳለች።

> 3ኛ ጥያቄ፡- ቤተ ክርስቲያንህን አስብ። በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስላለው የማስተማር አገልግሎት በዝርዝር ተናገር። በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ያደጉ ይመስልሃል? ለምን?

> 4ኛ ጥያቄ፡- ቤተ ክርስቲያንህ ጌታን ለማያውቁ ሰዎች የመመስከርን ተግባር በሚገባ ትፈጽማለች? በቤተ ክርስቲያንህ አቅራቢያ የማያምኑ ሰዎች አሉን? ቤተ

ክርስቲያንህ እነዚህን ሰዎች ለመድረስ ምን ፕሮግራም አላት? እንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም ከሌላት ምን እንዲደረግ አሳብ ትሰጣለህ?

## ሁለተኛ ቀን፦ በክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ማን ያስተምራል?

5ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ፥ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ፥ እንዲያጠምቁና እንዲያስተምሩ ትእዛዝ የሰጠው ለማን ነበር? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የክርስትና ትምህርት ፕሮግራም ለማደራጀት መሪነቱን መውሰድ ያለበት ማን ነው? ሐ) ኃላፊነትን የሚወስዱ መሪዎች ምን ዓይነት ሥልጠና እንዲኖራቸው ያስፈልጋል? መ) ሥልጠና ከሌላቸው ሊሠለጥኑ የሚችሉባቸውን መንገዶች ጠቁም። 1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-4 አንብብ። ጴጥሮስ የሚናገረው ለማን ነበር? ስለ ራሱ ምን አለ? መንጋውን የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው ለማን ነው?

ቀደም ሲል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አንገብጋቢ በሆነ ሁኔታ ስለሚያስፈልግ ጥሩ ሥልጠና ተናጋግረናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳየነው ጥሩ ትምህርት እንዲሰጥ የእግዚአብሔርም ዓላማ ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ የምንመለከተው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማስተማሩን ኃላፊነት ማን መውሰድ እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ነው፤ ምን ዓይነት ሰዎች መሆን አለባቸው? ምን ዓይነት ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ ያስፈልጋል?

1) ክርስቲያናዊ ትምህርትን ማደራጀት ያለበት ማን ነው?

ሀ. ሽማግሌዎችና መጋቢው ኃላፊነት አለባቸው።

ጴጥሮስ በ5፡1-4 በታናሹ እስያ ተበታትነው ላሉት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ሲጽፍ ሽማግሌዎች ለመንጋው ካለባቸው ኃላፊነት አንጻር ትእዛዝ አስተላልፎአል። ይህንኑ ምንባብ በድጋሚ በጥንቃቄ አንብብ። ጴጥሮስ መንጋውን የመጠበቅን ኃላፊነት የጣለው በቀጥታ በሽማግሌዎች ጫንቃ ላይ ነው። ጴጥሮስ እራሱ ሽማግሌ ስለነበር የሚናገረው በሥልጣን እና ከልምድ የሚያውቀውንም ነው። በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔር መንጋ ጠብቁ ይላቸዋል (ቁ.2)።

እረኛው በጎቹን ይጠብቃል፤ ያውቃቸዋል። የለመለመ ሣርና ንጹህ ውኃ ወደ አለበት ስፍራ ይመራቸዋል። ሌሊቱን ሙሉ አብሮአቸው በመቆየት ከአደጋ ይጠብቃቸዋል። የጥንት የቅድስቲቱ ምድር እረኞች ይተኙ የነበረው በበጎቹ ግርግም አጠገብ ወይም በበረቱ መግቢያ በር ሥር ነበር። ይህም በጎቻቸውን ሊተናኮላቸው ከሚመጣው አውሬና ከሌቦች ለመከላከል ሲሉ ነበር። እረኛው በጎች ሲታመሙ ያክማቸዋል፤ ሲቆስሉም ቁስላቸውን ያሽጋላቸዋል።

1. እረኞች መንጋውን መመገብ አለባቸው

ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንጋ ስለመጠበቅ ሲናገር እረኞችና ሽማግሌዎች ለበጎች (ለምእመናን) እንክብካቤ ማድረግ እንዳለባቸው ፍላጎታቸውንም አውቀው መንፈሳዊ መብልና መጠጥ ሊሰጡአቸው አስፈላጊ እንደሆነ መናገሩ ነበር። መንፈሳዊ ጤንነታቸው መጠበቅ አለበት።

ከአደጋም መከለል አለባቸው። የስሕተት ትምህርት በዓለም እንደተሠራጨ ሁሉ በኢትዮጵያም እየተስፋፋ ነው። ጠላትም መንጋውን ለማሳት እየሞከረ ነው። መንጋውን ለመጠበቅ በጥሩ ሁኔታ ማስተማር፥ መገሠጽ፥ ማስተካከል እና በጽድቅ መንገድ ማሠልጠን ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ. 3:16–17)። ወደ ፊት በሚኖሩት ትምህርቶች ውስጥ መንጋውን ስለመመገብ ብዙ እንማራለን።

2. እረኞች ከአደጋ መከላከል አለባቸው

የዮሐንስ ወንጌል በ10ኛው ምዕራፍ የሚያሳስበን ሌቦችና ዘራፊዎች እንዳሉ፥ ያልታሰቡ እንግዶች መጥተው መንጋውን ለማሳትና ለመጉዳት እንደሚሞክሩ ነው። መንጋውን ለማጥፋት ወይም ለመበተን የሚሞክሩ ተኩላዎች አሉ (በቁጥር 12)። የማቴዎስ ወንጌል 7:15 «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ» ይላል።

ይሁዳ በእርሱ ጊዜ ለነበሩት ክርስቲያኖች ሲጽፍ አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎች ወደ እነርሱ ሾልከው ስለገቡ ለሃይማኖታቸው እንዲጋደሉ አጥብቆ አሳስቦአቸዋል። እነዚህ መልካሙን ትምህርት የማያስተምሩ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ነበሩ (ይሁዳ 3–4)።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡– በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሾልከው የገቡ የስሕተት ትምህርቶች አሉ። ከነዚህ የስሕተት ትምህርቶች የምታውቃቸውን ያህል ዘርዝር። በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ አማኞችን ከእነዚህ የስሕተት ትምህርቶች ልትጠብቃቸው ትችል ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፉ መልሶችን ጻፍ። |

አንዳንዶች ዛሬ የሥላሴን ትምህርት በመቃወም ያስተምራሉ። አንዳንዶች የሚያስፈልገን ኢየሱስ ብቻ ነው ይላሉ። ሌሎች የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ይክዳሉ። እስከ አሁንም ደግሞ ሌሎች ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሳሳተ ትምህርት አላቸው። ሌሎች ነፍስ የማትሞት መሆኑን ይክዳሉ። ሌሎች በእምነት ስለሚገኝ መዳን የተሳሳተ ትምህርት አላቸው። የእያንዳንዱን ትምህርት ስሕተት በአጭሩ እንመልከት።

ሀ. ሥላሴ

በብሉይ ኪዳን ዘፍ.1:26፤ 3:22፤ 11:7፤ እና ኢሳ. 6:8 በመሳሰሉ ጥቅሶች አሐዱ–ሥሉስ አምላክ በብዙ ቁጥር እንደተጠራ ጠንካራ ማስረጃ አለን። ጌታ ኢየሱስ (ወልድ) በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ሲናገር «እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» ብሏል። ኢሳ.48:16 እንደገናም በመዝ. (45):6 እና ኢሳ. 63:9፤10።

መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብ ተለይቶ እንመለከተዋለን። በዘፍጥረት 1:1 ስታነብ፥ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።» [ዘፍጥ. 6:3፤ ዘኍል. 27:18፤ መዝ. (51):11፤ ኢሳ. 40:13፤ ሐጌ 2:5 ተመልከቱ]።

የሥላሴ ትምህርት በአዲስ ኪዳን በግልጥ ይታወቃል። በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ከወረደ በኋላ የእግዚአብሔር ድምፅ ከሰማይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ገልጾአል (ማቴ. 3:16)። ደቀ

መዛሙርቱ እንዲያጠምቁ የታዘዙት በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው (ማቴ. 28:19)። እነዚህ የኢየሱስ ትእዛዛት ናቸው። ሐዋርያት ደግሞ በቡራኬያቸው ሦስቱን አንድ ላይ በማድረግ ይጠቀሙባቸዋል (2ኛ ቆሮ. 13:13)። ስለ ሥላሴ ትምህርት የበለጠ ለመረዳት "Thiessen, Lectures On Systematic Theology"፥ ገጽ 88–89 አንብብ።)

ለ. የክርስቶስ አምላክነት

የስሕተት አስተማሪዎች ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል አይደለም፤ ሁለቱም አንድ አይደሉም ይላሉ። ክርስቶስ የእግዚአብሔር በኩር ወይም ከእግዚአብሔር በቀጥታ የተፈጠረና ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንዳልሆነ አድርገው ይናገራሉ። ምንም እንኳን እንዲህ ቢሉም የእግዚአብሔር ቃል በዮሐ 20:13፤ ዮሐ. 5:17፥ 23፤ ዮሐ. 20:20፤ 14፥ 9፤ ቆላ. 1:15፤ ፊልጵ. 2:6፤ ዕብ. 1:3 የሚናገረውን አንብብ።

ሐ. የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት

አንዳንድ የስሕተት ትምህርቶች መንፈስ ቅዱስ ኃይል ወይም ተጽዕኖ እንጂ የሥላሴ አካል አይደለም ይላሉ። እኛ ግን አካላዊ ህልውና እንዳለው እንዲሁም ከአብና ከወልድ ጋር በመፍጠር ላይ አብሮ እንደሠራ እናምናለን (ዘፍጥ. 1:2)። መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ ስሞች አሉት፥ የዕውቀት መንፈስ (ኢሳይያስ 11:2)፥ የእውነት መንፈስ (ዮሐንስ 14:17)፥ የቅድስና መንፈስ (ሮሜ 1:14)፥ የእግዚአብሔር መንፈስ (ዘፍጥረት 1:2)፥ የክርስቶስ መንፈስ (ሮሜ. 8:9) እና የጌታ መንፈስ (የሐዋርያት ሥራ 5:9)። ሊያዝን ይችላል (ኤፌሶን 4:30)፥ ሊጠፋ ወይም ትቶ ሊሄድ ይችላል (1ኛ ተሰሎንቄ 5:19)። መንፈስ ቅዱስ ያስገነዝባል፥ ይመራል፥ ይናገራል (የሐዋርያት ሥራ 13:2)።

መ. የነፍስ ዘላለማዊነት

አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶች አካላዊ ሞት የህልውና ማብቃት ነው ብለው ይናገራሉ። ነፍስና መንፈስ ይሞታሉ፥ ይጠፋሉ እንጂ ከሞት ወዲያ አይኖሩም ይላሉ። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ከሕይወት በኋላ ነፍስ መኖሯን ትቀጥላለች። ይኸውም በዘለዓለማዊ ደስታ ወይም በዘላለማዊ ቅጣት ነው። መንፈሳዊ ሞት ከእግዚአብሔር መለየት እንጂ መጥፋት አይደለም። (ሉቃስ 16:23 እንዲሁም ፊልጵ. 1:23፤ 2ኛ ቆሮ. 5:8፤ ዮሐ. 11:25–26 ተመልከት)። በሞትና በትንሣኤ መካከል ሕይወትና ሕሊና መኖራቸውን ይቀጥላሉ (ኢሳይያስ 14:9–11፤ ማቴ. 22:32፤ ማር. 9:43–48፤ ሉቃስ 16:19–31፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 8:6–8፤ ፊልጵ. 1:21፤ ራእይ 6:9–11)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአተኞች ለዘላለም መጥፋት በየትም ቦታ አያስተምርም። ይልቁንም ለዘላለም እሳት ውስጥ ይጣላሉ (ማቴዎስ 25:41፤ 46፤ 1ኛ ተሰ. 1:9፤ ራእይ 19:20፡ 20:10)።

ሠ. ደኅንነት በእምነት ብቻ

ስሕተት የሚመጣበት ሌላው አቅጣጫ ደኅንነት በእምነት ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ካለመስጠት ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአይሁድ አስተማሪዎች በሚያስተምሩት ትምህርት

ውስጥ ሁል ጊዜ ሐዋርያትን ይከተሉ ነበር። የጳኑት መገረዝ እና የሙሴንም ሕግ መጠበቅ እንዳለባቸው ያስቡ ነበር። ጊዜው እንዲህ እየቀጠለ ሲሄድ ሌላ ስሕተት መልኩን ቀይሮ ብቅ አለ። ዛሬም በዘመናችን ክርስቶስ ሠርቶ በጨረሰው ሥራ ላይ ለመጨመር የሚሞክሩ እንዳሉ እናያለን። የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ አንዳንድ ቀናትን ይጠብቃሉ፤ ከምግብ ራሳቸውን ያገልላሉ፥ ወይም ወደ ተቀደሰ ስፍራ ይጓዛሉ፤ መልካምን ሥራ በመሥራት የመዳንን መንገድ እንደሚያገኙ ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ደኅንነት በእምነት ብቻ እንደሆነ ነው (ኤፌሶን 2፡8–9፤ የሐዋርያት ሥራ 4፡12)።

የዕብራውያን መልእክት 10፡12 እንደሚያሳስበን፥ «እርሱ ግን (ኢየሱስ) ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ።» ለሁልጊዜና ለሁሉም ኃጢአት በቂ የሆነውን ፍጹም መሥዋዕት ከአቀረበ በኋላ ተቀመጠ። ይህ አባባል ፍጻሜንና የተጠናቀቀ ሥራን ያሳያል። የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተጨማሪ ተመልከት (ዮሐንስ 3፡16፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡7–9፤ 5፡21፤ ዕብራውያን 7፡24፤ 25)።

---

7ኛ ጥያቄ. አንዳንድ የስሕተት አስተማሪዎች ያስተማሩአቸውን አምስት ስሕተቶች ዘርዝር። ወደ እግዚአብሔር ቃል እውነት እንዲመለሱ ትረዳቸው ዘንድ የሚያስችሉህን አምስት ጥቅሶች ዘርዝር።

---

ለ. የጥሩ መሪዎች ባሕርያት

1ኛ ጴጥ. 5፡3 እና ቲቶ 1፡7፥ 8ን አንብብ። ሽማግሌዎች (ኤጲስ ቆጶሳት) በቤተ ክርስቲያን ለመንጋው ከሁሉም የሚሻለውን የሚያደርጉና መልካም ምሳሌዎች ሊሆኑ እንጂ እንደ ጌቶች በኃይል መግዛት የለባቸውም (1ኛ ጴጥሮስ 5፡3)። ለሠሩት ሥራ ስለሚከፈላቸው ገንዘብ ማሰብ ሳይሆን፥ ጌታን ለማገልገል በሙሉ ልብ ፈቃደኞችና ደስተኞች መሆን አለባቸው።

ጳውሎስ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ሥራ ሲናገር በቲቶ 1፡7–8። «ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ የማይነቀፍ ሊሆን ይገበዋልና። የማይኮራ፥ የማይቆጣ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨ፥ ነውርኛ ረብ የማይወድ፥ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ ጠንቃቃ፥ ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ራሱን የሚገዛ ይሁን። ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና»።

በሕዝቅኤል 34፡1–10 ታማኝ ስላልሆኑ የእስራኤል እረኞች ሲናገር በብዙ አቅጣጫ የእረኝነት ተግባራቸውን በትክክል ያልተወጡ መሆናቸውን ያመለክታል።

1ኛ) ራሳቸውን ብቻ ያሰማሩ ነበር።

2ኛ) ጮማውን የሚበሉ፥ ጠጉሩንም የሚለብሱ፥ የወፈሩትን የሚያርዱ፥ በጎችን ግን የማያሰማሩ ነበሩ።

3ኛ) የደከመውን አላጸኑም፤ የታመመውንም አላከሙም ነበር።

4ኛ) የባዘነውን አልመለሱም፤ ደግሞም የጠፋውንም አልፈለጉም ነበር።

5ኛ) መንጋውን በኃይልና በጭቆና ይገዙ ነበር።

የዚህ ሁሉ ውጤት በጎች (የእስራኤል ልጆች) በአውሬዎች መበላት፥ ወደ ኮረብታዎችና ወደ ተራሮች መበተን፥ ያለፈላጊና ያለተንከባካቢ መቅረት ነበር።

ሐ. ሊታመኑ የሚችሉ ሰዎችን ማሠልጠን።

የእግዚአብሔርን መንጋ የሚጠብቁ መልካም እረኞች ለበጎች ይጠነቀቃሉ። የበጎቹን ፍላጎት ጠንቅቀው በመረዳት የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጡ ናቸው። ያስተምሯቸዋል ወይም ሌሎች እንዲረዱቸው ያደርጋሉ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎት ነበር። «ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2)።

ሽማግሌዎችና መጋቢው ሁሉንም ነገር ማድረግ አይችሉም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማስተማር ስጦታ ያላቸውንና ለመንጋው ግድ የሚላቸውን ሰዎች በእነርሱ ሥር ሆነው ያገለግሉ ዘንድ በመምረጥ ማሠልጠን ይጠበቅባቸዋል። ይህ ደግሞ ሌላ ኃላፊነት በእነርሱ ላይ ይጨምራል። ይህም ከአገልጋዮች መካከል ብቃት ያላቸውን አስተማሪዎች ማሠልጠን ነው። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላሉ ሰዎች በማስተማር የሚያገለግሉባቸውን ስጦታዎች ሰጥቷል። ቤተ ክርስቲያን የምታድገውና የምትባረከው ሰዎች እንደየስጦታቸው በማገልገል አንዱ የሌላውን ዕድገት ሲደግፍ ነው።

መ. ሥልጠና ለሽማግሌዎችና ለመጋቢዎች

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነቶችና ተግባራት እንዲህ ዓይነት የተለያዩ ሰፊ ሥራዎችን የሚያካትቱ ስለሆነ በቂ ሥልጠና እንዲኖራቸው የግድ አስፈላጊ ነው። ቢያንስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምረው የጨረሱበት የምስክር ወረቀት ያላቸው ሆነው ለመሪነት በሚሰጥ ሥልጠና በደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም፥ በሰንበት ትምህርት ቤት ሴሚናርና በወጣቶች አደረጃጀት፥ ወዘተ... የሚሰጡትን የተለያዩ ትምህርቶች ለመቅሰም የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በተጨማሪ ማንበብ የሚወዱና በማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ በንቃት የሚሳተፉ መሆን አለባቸው።

ይህ ጉዳይ በተጨማሪ የሚያመለክተን ጥቂት ሰዎች ሁሉንም ነገር ማድረግ ያለመቻላቸውን እውነታ ነው። ስለዚህ ሌሎችን በማሠልጠን ጊዜያቸውን የሚሰጡ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባሎቻቸው ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ የሚያበረታቱ ዓይነት ሰዎች መሆን አለባቸው። በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ብዙ ምእመኖቻችንን ስናይ በደንብ የተማሩ ናቸው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችንን ሽማግሌዎችና መጋቢዎች ችሎታ ለማሳደግ አብረን ስንሠራ ከምእመኑ የጊዜው ፍላጎት ጋር አብረው የሚጓዙና በሚገባ የሚያገለግሉ ይሆኑ ዘንድ ተግተን መሥራት አለብን።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፦ የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ለበለጠ ብቃት ራሳቸውን ለማዘጋጀት የሚሳተፉባቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው? |

9ኛ ጥያቄ፦ የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች ሊያግዙ የሚችሉ ምን ዓይነት ፕሮግራሞች በከተማህ ወይም በአካባቢህ ይገኛሉ?

10ኛ ጥያቄ፦ ፕሮግራሞች ከሌሉ፥ ከሌላ ስፍራ መጥተው ሊረዱአችሁ የሚችሉትን ሰዎች መጋበዝ ይቻላል? ይህን ማድረግ የሚችል ማን ይመስልሃል?

## 3ኛ ቀን፦ የክርስቲያናዊ ትምህርት ትኩረት

11ኛ ጥያቄ፦ ዮሐ. 21፡15-17 አንብብ። ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር ንግግር ያደረገበትን የዚህን ጊዜ ሁኔታ ግለጽ። ኢየሱስ ጴጥሮስን ስለ ታማኝነቱ ሦስት ጊዜ የጠየቀው ለምንድን ነው? ኢየሱስ ለጴጥሮስ ምን እንዲያደርግ ጠየቀው? ምንስ ማለቱ ነበር?

### መግቢያ

አንዳንዴ ቀጥሎ ያሉትን ዓይነት አባባሎች እንሰማለን። «ልጆች ምን ያውቃሉ? ወይም እኔ ሴት ነኝ፥ ምን ማድረግ እችላለሁ? ትምህርት ቤት አልሄድ ምን አውቃለሁ? ስለተማርህ አንተ ታውቃለህ!» እነዚህ አባባሎች ትክክል ናቸውን?

ማንም ሰው እውቀት አለው። እግዚአብሔር የምናውቅ ፍጡራን አድርጎ ፈጥሮናል። ማንኛውም ሰው ትምህርት ቤት ገብቶ መደበኛ ትምህርት የማግኘት ዕድል ቢኖረውም ባይኖረውም የተከማቸ እውቀት ይኖረዋል። ደግሞም እያንዳንዱ ሰው የመማር ፍላጎት አለው። ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እኛ ሲመጣ፥ አዲስና በፊት ሰምተነው የማናውቀው ነበር። ባለማቋረጥ በድግግሞሽ በተሰጠ ትምህርት፥ እግዚአብሔር እንደሚወደን ተረዳን፤ ለኃጢአታችን አንድያ ልጁ እንዲሞትልን እንደ ሰጠን ተገነዘብን። ኃጢአትን በመናዘዝ፥ ሰይጣንን በመካድና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፥ ምሕረትን እንደምናገኝና በኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንደምንሆን ተማርን፤ ይህን እርምጃም በመውሰድ እምነትን በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ በማድረግ አዲስ ሕይወት እንደሚያስገኝ በትክክል አረጋግጠናል። ከዚያን ጊዜ ጀምረን የክርስትና ሕይወት ኑሮ እንዴት መኖር እንዳለብን እየተማርን ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ የምናምነውን ነገር በሚገባ ማወቃችን እንጂ ግድየለሾች መሆናችን አይደለም። ሁሉም ሰው መማር ይችላልን?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንድንችል እስቲ በዮሐ. 21፡15-17 ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር ካደረገው ንግግር የምንማረውን እንመልከት።

1. ጴጥሮስ ከውድቀት በኋላ እንደገና ተሾመ።

በማቴዎስ 4፡18-20 እንደምናነበው፥ ጴጥሮስ በኢየሱስ ከተመረጡት ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር። ኢየሱስ ጴጥሮስን ወንድሙን እንድርያስን ደርሶ ሲጠራቸው ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። ጥሪው በደረሳቸው ወቅት ግን መረባቸውን ጥለው ጌታ ኢየሱስን እንደተከተሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ባገለገለባቸው ጊዜያት በጣም ከሚቀርቡት ከሦስቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ ጴጥሮስ ነበረ። ዮሐንስ እና ያዕቆብ ከኢየሱስ ጋር ሲሄዱ፥ ከጌታ ሲማሩና ሲሠሩ ጴጥሮስ ከእነርሱ ጋር እንደነበረ እንመለከታለን።

ኢየሱስ ተይዞ ወደ ሊቀ ካህኑ መኖሪያ በተወሰደበት ጊዜ እና በካህናቱ ሲጠየቅ አብሮት የቆየው ዮሐንስ ነበረ (ዮሐንስ 18፡15)። ጴጥሮስ ያደረገው ነገር ቢኖር ሊቀ ካህናቱ ግቢ መግባት ብቻ ነበር (ማቴዎስ 26፡58)። «ጴጥሮስም ከቤት ውጪ በአጥሩ ግቢ ተቀምጦ ነበር። አንዲት ገረድም ወደ እርሱ ቀርባ አንተ ደግሞ ከገሊላው ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው። እርሱ ግን፡- የምትይውን አላውቀውም ብሎ በሁሉ ፊት ካደ። ወደ በሩም ሲመጣ ሌላይቱ አየችውና፥ በዚያ ላሉት ይህ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበረ አለች። ዳግመኛም ሲምል ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ። ጥቂትም ቆይተው በዚያ ቆመው የነበሩ ቀርበው ጴጥሮስን፡- አነጋገርህ ይገልጥሃልና በእውነት አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ አሉት። በዚያን ጊዜ፡- ሰውዬውን አላውቀውም ብሎ ሊረገምና ሊምል ጀመር። ወዲያውም ዶሮ ጮኸ። ጴጥሮስም ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጪ ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ» (ማቴዎስ 26፡69–75)።

ጴጥሮስ ጌታን በመካዱ ትልቅ ኃዘን ተሰምቶት ንስሐ ገብቷል። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን አግኝቶታል። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለጴጥሮስ በተገለጠ ጊዜ ምን እንደተፈጸመ አናውቅም (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡5)። ዳሩ ግን ኢየሱስ በባሕሩ ዳር አካባቢ ከጴጥሮስና ከተቀሩት ደቀ መዛሙርት ጋር ስለመገናኘቱ የተጻፈ አስደናቂ ታሪክ እናገኛለን። ድርጊቱ የተፈጸመው ሌሊቱን ሙሉ ዓሣ ለማጥመድ ሞክረው ምንም ሳይሳካላቸው በቀረበት አንድ ማለዳ ነበረ። ኢየሱስ መረባቸውን ወደ ጥልቁ እንዲጥሉ ከነገራቸው በኋላ 153 ዓሣዎች ያዙ። መረባቸው ግን አልተቀደደም ነበር። ኢየሱስ ቁርሳቸውን ሰጥቶአቸው በልተው ከጠገቡ በኋላ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ዘንድ አብሮአቸው እንደተቀመጠ እንመለከታለን።

ኢየሱስ ጴጥሮስን፥ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» አለው።

ጴጥሮስ ዳግም ጌታውን በማገልገል ሊጠቅም ይችል እንደሆነ ሳያስብ አልቀረም። ኢየሱስ ጴጥሮስን በግል ይህንን ያለው የጴጥሮስን እውነተኛነት ለመመርመር ነበር። ጴጥሮስም ሲመልስ «አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው። ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለው «ግልገሎቼን አሰማራ»፤ («ግልገሎቼን መግብ» አዲሱ የአማርኛ ትርጉም)።

ደግሞ ሁለተኛ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን?» አለው።

«አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው።

ኢየሱስ «ጠቦቶቼን ጠብቅ» አለው።

ሦስተኛ ጊዜ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን?» አለው።

«ሦስተኛ፡- ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው»።

ኢየሱስም «በጎቼን አሰማራ» አለው።

ከዚህ ክንዋኔ ውስጥ ግልጽ የሆኑ ሁለት በጣም አስፈላጊ ትምህርቶችን እንማራለን።

ሀ) ሁላችን እንደምንፈተን አንዳንድ ጊዜም እንደምንወድቅ ማስታወስ አለብን። ያለፈው ነገራችን ምንም ዓይነት ይሁን፥ ወደ ጌታ ኢየሱስ በእውነተኛ ልብ ስንቀርብ ከኃጢአታችን ያነጻናል፤ ለአገልግሎቱም እንድንጠቅም ብቁዎች ያደርገናል። ጴጥሮስ በሚያሳዝን ሁኔታ በክህደት ወደቀ፤ ከዚያም ስለፈጸመው ክህደት ጥልቅ ኃዘን ተሰማው። ነገር ግን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አልቆየም። መራራ ለቅሶ በማልቀስ በጥፋቱ ተናዝዞ ንስሐ ገባ። ጌታ ኢየሱስም ይቅርታ አድርጎለትና በሕይወቱ ተሐድሶን አካሂዶ ወደሚጠቅምበት ስፍራ መለሰው።

ለ. 1) የጌታ ፈቃድ ግልገሎቹ በሚገባ እንዲጠበቁና እንክብካቤ እንዲያገኙ ነው። «ግልገሎቼን መግብ» አለው። ይህ የሚያሳየው የሚመቻቸውን ምግብ እንዲያገኙ ማድረግን ነው። ጎልማሶች የሚመገቡትን ለሕፃናት አንሰጥም። ስለዚህም በቀላሉ ሊያብላሉ የሚችሉትንና ለዕድገታቸው የሚጠቅማቸውን ምግብ እናዘጋጅላቸዋለን።

በተመሳሳይ መንገድ «በመንጋው» ላሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሕፃናት ለሆኑ የሚስማማቸውን ምግብ በጥንቃቄ ማዘጋጀት አለብን። ይህ ለሕፃናት ወይንም በእምነታቸው ሕፃናት ለሆኑ ለአዳዲስ አማኞች ሊሆን ይችላል። ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው በዕድሜያቸው እንደ ዓቅማቸው ለዕድገታቸው የሚያስፈልግ ምግብ ማግኘት ይገባቸዋል። በቂ ምግብ ካላገኙ ሕመምተኞች ወይንም ደካሞች ይሆናሉ። ጠንካራ ወይም ሊያላምጡት የማይችሉት ምግብ ከተሰጣቸው ከዚህ ምግብ ምንም አይጠቀሙም። ግልገሎችን የማስተማሪያ መንገድ በተገቢው ሁኔታ የሚያድጉበት ይሆን ዘንድ የታቀደ መሆን አለበት።

2. ጠቦቶች መጠበቅ አለባቸው። እነዚህ በቤተ ክርስቲያንና በሕዝቡ መካከል የሚያድጉ ወጣቶቻችን ናቸው። ከጌታና ከቤተ ክርስቲያን ያርቋቸው ዘንድ የሚያታልሉና የሚስቧቸው በርካታ ነገሮች ያሉባቸው ናቸው። የራሳቸው የአካል፥ የአእምሮ፥ የሥነ ልቡና እና የስሜት ዕድገት ያቅበጠብጣቸዋል። ለፈተናም ያጋልጣቸዋል። እነዚህ ብርቅዬ በጎች በሕይወታቸው የሚፈጸሙትን በርካታ ለውጦች መቋቋም ይችሉ ዘንድ በጥንቃቄና በጸሎት የተደገፈ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል። ለዕድሜያቸው ተስማሚ የሆኑ ተግባራት ሊታቀዱላቸው ይገባል። በቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ፕሮግራም ላይ ጌታን የሚያገለግሉበት የአገልግሎት በሮች ማመቻቸት የሚጠቅሙ እንደሆነ እንዲሰማቸውና የተረጋጉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

3. በመጨረሻም ኢየሱስ ጴጥሮስን ያለው «በጎቼን አሰማራ» ነበር። በጎች ራሳቸውን ለማጠንከርና ጌታን በማስደሰት ለመኖር ጠንካራ ምግብ ይሻሉ። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳለው «ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን። ጆሮቻችሁም ስለፈዘዙ በቃል ልንተረጉመው ጭንቅ ነው። ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና፥ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅ ቃል አያውቅምና። ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት

በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው» (ዕብራውያን 5፡11-14)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም የዕድሜ ደረጃና ችሎታ ግድ እንደሚለውና ጴጥሮስን በተለያየ ደረጃ ያሉትን የመንጋውን ክፍሎች እንዲመግብ፥ እንዲጠብቅ፥ እንዲንከባከብ እና እንዲያስማራ እንዳዘዘው ተመልክተናል።

አብያተ ክርስቲያኖቻችን ተመሳሳይ ዝንባሌና አትኩሮት ሊኖራቸው ይገባል። እያንዳንዱ ተማሪ የሚያስፈልገውን ተገቢ ትምህርት ያገኝ ዘንድ በየደረጃው ለሚገኙ ዕድሜዎች በሚገባ የታቀዱ ክፍሎች ሊኖሩን ይገባል። ልጆችን እንደምናስተምር ሽማግሌዎችን አናስተምርም፤ ለሕፃናትና ለጎልማሶች አንድ ዓይነት ምግብም አንሰጥም።

አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት፥ ወጣቶችና ጎልማሶች አንድ ዓይነት ትምህርት እንሰጥና ለምን እንደማያድጉ ግራ ይገባናል። የቤተ ክርስቲያን ዋናው የአምልኮ አገልግሎት ሁሉም ሰው በአንድነት የሚገናኝበትና ተጠቃሚ የሚሆንበት መሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን ሁሉም በሚገባ ይመገብ ዘንድ ለእያንዳንዱ ቡድን የሚዘጋጁ ልዩ ትምህርቶች ያስፈልጋሉ።

12ኛ ጥያቄ፡- ከእሑድ የአምልኮ አገልግሎት በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የተለዩ የመማሪያ ፕሮግራሞች አሉን? ካሉ እንዴት ተከፋፍለዋል? ማንስ ያስተምርባቸዋል?

13ኛ ጥያቄ፡- የተለዩ ክፍሎች ከሌሉ፥ በተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች መካከል የምታየው ድክመት ምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ሕፃናት የእግዚአብሔርን ቃል መሠረታዊ ትምህርቶች የተማሩ ይመስልሃል? ወጣቶችስ?

14ኛ ጥያቄ፡- አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ካለማንበባቸው የተነሣ ችላ የተባሉ ናቸው። እነርሱንስ ለማስተማር በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ምን ጥረት ተደርጓል? በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም አለን?

15ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የወንድሞች ኅብረት አለን? የፕሮግራማቸው ይዘትስ እንዴት ነው? በጸጋና እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ምን ያህል እየረዳቸው ነው?

## አራተኛ ቀን፡- በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ውስጥ የክርስቲያናዊ ትምህርትን ይዘት መግለጥ

የመጀመሪያዎቹን የሁለት ሳምንቶች ኮርሶቻችንን ተመልሰን ስንመለከት ክርስቲያናዊ ትምህርት የሚያካትታቸውን ነገሮች አግዝፈን በማየት እጅግ አጠቃላይ የሆኑትን የክርስቲያናዊ ትምህርት ገጽታዎች እንደሸፈንን ግልጥ ነው። ከዛሬ ጀምሮ የክርስቲያናዊ ትምህርትን ቀጥተኛ ይዘት ነጥለን ለመመልከትና ከቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ አገልግሎትና ዓላማ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ለማወቅ በሚያስችሉ አቅጣጫዎች ላይ እናተኩራለን።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ማቴ. 16፡13-18፤ ገላ. 3፡26-28፥ እና 1ኛ ቆሮ. 12፡13-27 አንብቡ። በእነዚህ ቁጥሮች በተገለጠው መሠረት የቤተ ክርስቲያን መሠረት ምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካተቱት እነማን ናቸው? በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ ምን ምን ቃላት ተግባር ላይ

ውሰዋል? ለ) ለቤተ ክርስቲያን ጥሩ ትርጓሜ ስጥ። ትርጓሜህ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማና ተግባር ያካተተ ይሁን።

## 1. ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?

በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነችና ተግባሯም ምን እንደሆነ መመልከት አለብን። ክርስቶስ በማቴዎስ 16፡13–18 አስቀድሞ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተናግሯል። ጊዜውም ደቀ መዛሙርቱን «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል» ብሎ በጠየቀበት ወቅት ነበር። ስምዖን ጴጥሮስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» በማለት በትክክል መልሷል። ኢየሱስም የጴጥሮስ መልስ ትክክል እንደሆነ ተቀበለው። በመቀጠልም «እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ። በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» (ቁ. 17–18) ብሎታል።

ኢየሱስ «አንተ ጴጥሮስ ነህ» ካለው ሐረግ በመነሣት አንዳንዶች ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን በጴጥሮስ ላይ እንደሚመሠርት ያስባሉ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ያለው ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠርተው በዚህ በ «ፔትራ» ላይ ነበር። ትርጉሙም ጴጥሮስ ተናግሮት የነበረው ዓለት ዓይነት እውነት ማለት ነው። ጴጥሮስም «አንተ ክርስቶስ» (ለረጅም ጊዜ የተጠበቅህ መሢሕ ነህ) ብሎታል። የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ይናገር የነበረው በራሱ ላይ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚሠራ ነበር። ያለውም ቤተ ክርስቲያኔን ነው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እንደሆነች ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን። ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ባለሥልጣን ነው። ጠላት ምንም ይሥራ ምንም ያድርግ ሊቋቋማት አይችልም– ጌታ ተናግሯልና።

ቤተ ክርስቲያን በግሪክ ቋንቋ «ተጠርተው የወጡ» ማለት ሲሆን፥ የክርስቶስን አካል ለመሥራት ከዓለም የተጠሩትን ያሳያል። በሐዋርያት መጽሐፍ ውስጥ ማየት እንደምንችለው ቤተ ክርስቲያን ታድግ ነበር። አባሎቿም ከሁሉ ጎሣና ሕዝብ የተሰበሰቡ ነበሩ። ይህ የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ አብርሃምን ሲጠራ፥ «የምድርም ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ብሎት ነበርና (ዘፍጥረት 12፡3)።

ገላትያ 3፡26–28 የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም እንደምታካትት ያሳያል። «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና»።

ለብሔረተኝነት፥ ለጎሳ ወይም ለቀለም ልዩነት ስፍራ የለም። በኢኮኖሚ ደረጃ የተሻለ በመሆን ምክንያት የበላይነት ለማሳየት ስፍራ የለም። ለጾታ የበላይነት ስፍራ የለም። «ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና»። በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድነትና ስምምነት እንጂ አድልዎ ወይም ቅንዓት ሊኖሩ አይገባም። እያንዳንዱ የሚገባውን ስፍራ ሊያገኝ ይገባል። አንዱ ሌላውን መርዳትና መደገፍ አለበት። 1ኛ ቆሮ. 12፡13–27ን

በጥንቃቄ አንብቡት። እያንዳንዱ የአካል ክፍል የራሱ የሆነ የተለየ ሥራ አለው። ያለዚህ አካል ክፍል አካል ሥራውን ሊሠራ አይችልም።

በሁለተኛው ምዕራፍ በ1ኛ ቀን ትምህርት የቤተ ክርስቲያንን ትርጉም ሰጥተናል። በዚያ ትርጉም ላይ ከላይ የተሰጠውን ገለጣ ማከል እንችላለን። ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ አካል አንዱ ለሌላው በማሰብ ለሁሉም በኅብረት በፍጹም ስምምነት አብረው የሚኖሩባትና የሚሠሩባት ናት። ይህ በእርግጥ በ1ኛ ቀን ትምህርት የተገለጠውና «ባለማቋረጥ ቃሉን በመታዘዝ ኑሩ» የሚለው ትምህርት ክፍል አካል ነው።

የቤተ ክርስቲያን ትርጉም፡— ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በደኅንነት ግንኙነት ያላቸው፥ ቃሉን በመታዘዝ ምሳሌያዊ ሕይወት የሚኖሩና የወንጌሉን የምስራች ለሌሎች ለማብሰር የሚፈልጉ የእግዚአብሔር ሰዎች ኅብረት ናት። አባሎቿም አንዱ አንዱን በሚያበረታታና ለሁሉም ጥቅም በሚሆን መልኩ የሚኖሩና የሚሠሩ ናቸው።

2. ተግባሯስ ምንድን ነው?

የቤተ ክርስቲያን ተግባሯ ወንጌልን ማሰራጨት፥ አዲስ የተለወጡ አማኞችን እምነት ማሳደግ እና ወደ ክርስቲያናዊ ኑሮ መምራት ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በተለያዩ መንገዶች ነው።

ሀ. በስብከት

ለ. በአምልኮ

ሐ. በማማከር

መ. በማስተማር

ሠ. በምስክርነት

በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ክርስቲያናዊ ትምህርት መኖሩ አንዱን ከሌላው ሙሉ ለሙሉ ለይቶ ለማሳየት አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከላይ የተጠቀሱት እያንዳንዳቸው ለቤተ ክርስቲያን ዓላማ ጠቃሚና አስፈላጊዎች ናቸው። ስብከት ለቤተ ክርስቲያን የግድ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በስብከት ውስጥ ማስተማር ስላለ ነው። አምልኮ ሲታቀድ ሰዎች አዲስን እውነት የሚማሩበት እንዲሆን ተደርጎ ሊታቀድ ይችላል። ማማከር ምክር ተቀባዩ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በሕይወቱ ላጋጠመው ሁኔታ እንዲጠቀም ማሳየት ስለሆነ ማስተማር አለበት። ምስክርነት ሰዎች ወንጌልን ለማድረስ የሚያደርጉትን ጥረት ብቁ የሚያደርግ መንገድን ስለሚጠቀም ማስተማርን ያካትታል። ስለዚህ ክርስቲያናዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የተጨመረ ነገር ሳይሆን የጠቅላላው አገልግሎት ወሳኝ ክፍል ነው።

አንዳንዶች «ስለ ክርስቲያናዊ ትምህርት በፊት ፈጽሞ ሰምተን አናውቅም። ቤተ ክርስቲያናችን ያለዚህ ትምህርት በነዚህ ሁሉ ዓመታት ሥራዋን በሚገባ ስታከናውን ቆይታለች። አሁን ይህ ለምን ያስፈልጋል?» ይላሉ። እውነቱ ግን ክርስቲያናዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ስሙ አልተጠራም። ማንኛውም ጤናማ ዕድገት ያለው ቤተ ክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት አለው። እኛም ክርስቲያናዊ ትምህርት

ብለን የምንጠራው ይህንን አገልግሎት ነው። ማስተማር ችላ ከተባለ የምእመናን ዕድገት እጅግ ዝቅተኛ ይሆናል። የሚያገኙት ምግብ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሣ በምግብ እጥረት ይሠቃያሉ።

3. የክርስቲያናዊ ትምህርት ይዘት

በቀጥታና በግልጽ ስናስቀምጠው፥ ክርስቲያናዊ ትምህርት የቤተ ክርስቲያን የማስተማር ፕሮግራም ገጽታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። የሚከተሉትንና እነርሱን የመሳሰሉትን ፕሮግራሞች ማካተት አለበት።

ሀ) የሰንበት ትምህርት ቤት፡- ብዙ ጊዜ የሰንበት ትምህርት ለሕፃናት ብቻ እንደሆነ አድርገን እናስባለን፤ በእርግጥም ነው። ነገር ግን ከሕፃናት እስከ አዋቂ ለእያንዳንዱ የዕድሜ ደረጃ ተከፋፍለው በሚገባ የተደራጁ ክፍሎችን ማካተት አለበት። እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሁሉ ወደ የክፍሉ በመግባት የእግዚአብሔርን ቃል በተቀናጀ መንገድ የሚማሩበት ሁኔታ መኖር አለበት። ይህ ዕለት ደግሞ ሁለቱም አዋቂና ሕፃናት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡበት አመቺ ጊዜ ነው። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚመጣው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በጥሩ መልኩ እንዲቀበል የተመቻቸ ጊዜ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡት ስብከቶች ብዙ ጊዜ በርእሰ-ጉዳዮች ላይ የተመሠረቱ ከሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጊዜ ቅደም ተከተል በተከታታይነት የሚሰጡ ትምህርቶች ያስፈልጉናል።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የወጣቶች ኅብረት

ሐ. የእህቶች ሳምንታዊ ስብሰባ።

መ. የወንድሞች ኅብረት

ሠ. ለአዲስ አማኞች የተለየ ክፍል፥ የጥምቀት ትምህርት ክፍል፥ የቤተ ክርስቲያን አባላት ክፍል እና የቤተሰብ ኅብረቶች ስብስብ፥ ወዘተ...

ረ. ቤተ ክርስቲያን ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ሌሎች ዕድሎች

ወደፊት በምንመለከታቸው ትምህርቶች በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ጥልቀት ያለው ጥናት እናደርጋለን። አሁን ግን የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰጥ ስለሚችለው ጥቅምና ተግባር አጠቃላይና አጭር ገለጣ እንደሰጠን ተስፋ እናደርጋለን። እያንዳንዱ ፕሮግራም በሚገባ የሚካሄድ ከሆነ አባላት ያድጋሉ። በፍቅር ይቀራረባሉ፥ በመንፈስ ቅዱስ ይመራሉ። ለእግዚአብሔርም ክብር ያመጣሉ።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ከሁሉም የላቀ ዓላማ «ክብሩ ይመስገን ዘንድ» ነው። (በኤፌ. 1፡6፥ 12፥ 14፥ ሮሜ. 15፥6፤ 9፤ ኤፌ. 3፡21፤ 2ኛ ተሰ. 1፡12፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡11) እግዚአብሔር በእኛ አምልኮ (ዮሐ. 4፡23፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ራእይ 22፡9)፥ በእኛ ጸሎትና ምስጋና [መዝ. (50)፡23፥ 1ኛ ጴጥ. 2፡9]፥ እርሱን በመታዘዝና በመውደድ ኑሮአችን ይከብራል (ዮሐንስ 15፡8)።

17ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተሰጡትን ጥቅሶች በሙሉ አንብብ። እግዚአብሔር በአምልኮአችን በየትኛው መንገድ ነው የሚከብረው? በጸሎታችንና በምስጋናችንስ? እግዚአብሔርን በመውደድና በመታዘዝ ኑሮአችን የሚከብረውስ እንዴት ነው? በቤተ

ክርስቲያንህ በሚገባ የሚካሄዱትን ፕሮግራሞች ዘርዝር። ሊታከሉ ይገባል የምትላቸውንም ዘርዝር።

5ኛ ቀን፡- ትምህርት ሁለትን ከልሱና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት የሚሆኑ ከዚህ በታች የተሰጡ የመወያያ ነጥቦችን ተመልከቱ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. በ5 ደቂቃ የጥሞና ጸሎት ፕሮግራሙን ጀምሩ።

2. ለ10 ደቂቃ ጸልዩ።

3. በትምህርት ሁለት ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በደንብ አጥኑና ሊመልሱት ያልቻሉት ጥያቄ ወይም ባስቸገራቸው ነገር ላይ ተወያዩ።

4. የመወያያ ጥያቄዎች

ሀ. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በሰጣቸው የመጨረሻ ትእዛዝ ውስጥ የሚገኙትን አራቱን ነጥቦች ከልስ። ይህንን ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያንህ እየታዘዘች ያለችው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ለ. የቤተ ክርስቲያንህ አመራር ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለው በምን ዓይነት መንገዶች ነው።

ሐ. ኢየሱስ፥ ጴጥሮስ እንዲያገለግል ስለነገረው ሦስት የተለያዩ ክፍሎች መግለጫ ስጥ። የእነዚህ ክፍሎች የመግር ፍላጎት በቤተ ክርስቲያንህ አገልግሎት ተሸፍኗልን።

መ. እያንዳንዱን ክፍል በብቃት ለመድረስ ምን ፕሮግራሞች መጨመር ያስፈልጋል? ፕሮግራሞች ቢበዙ ችግር ያመጣል?

5. በጸሎት ዝጉ።

# ትምህርት ሦስት

# ሕይወትን ለመለወጥ ማስተማር

## አንደኛ ቀን፡- የስብከት ትርጓሜ

1ኛ ጥያቄ፡- ስብከት ምንድን ነው? ከትምህርት እንዴት ይለያል?
2ኛ ጥያቄ፡- ከስብከትና ከትምህርት በጣም አስፈላጊው የትኛው ነው? ምክንያትህን ስጥ።

### ትርጓሜ

ስብከት፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከዓውዱ አኳያ መግለጽ ማለት ነው። የጸሐፊውን የመጀመሪያ አሳብና በታሪክ ውስጥ ያለውን ስፍራና ድርሻ ብሎም ከአሁን ጊዜ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመወሰን ክፍሉን በጥንቃቄ ማጥናትን ያካትታል።

በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ እውነትን ከሰባኪው ማንነትና ልምምድ ላይ ማዛመድ አለበት፤ ከዚያም በኋላ በሰባኪው በኩል ወደ አድማጮቹ መስረጽ ይኖርበታል (ከሮቢንሰን <Robinson> አሳብ የተወሰዱ፥ ገጽ 20)።

### የስብከት ተግባር አንገብጋቢነት

3ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1-3ን በጥንቃቄ አንብብ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ይህን ኃላፊነት የሰጠው ለምን ነበር? ያዘዘው ምን እንዲያደርግ ነበር? መቼ እንዲያደርግ ነበር? መልእክቱ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው? ሊያደርገው የሚገባው እንዴት ነበር? ሊያደርገው የሚገባው ለምን ነበር?

ጳውሎስ ወንጌልን የመስበክ ተግባር አንገብጋቢና አጣዳፊ መሆኑ ተሰምቶት ነበር። የጌታ መምጣትና ከዚያም በኋላ የሚሆነው ፍርድ የማይቀር ስለሆነ ጢሞቴዎስም ደግሞ ቃሉን እንዲሰብክ ግድ ይለዋል። ቃሉን እንዲሰብክ ብቻ ሳይሆን አድማጮቹ የተሳሳተ ግንዛቤ ሲኖራቸው ማስተካከል እንደሚጠበቅበት ይነግረዋል። እንደ እግዚአብሔር ቃል ሳይኖሩ ሲቀሩ እንዲገሥጻቸውም ያስፈልግ ነበር። በተጨማሪም እንዲያበረታታቸው ይገባ ነበር። ይህ ተግባር በከፍተኛ ትዕግሥት ጥንቃቄ የሞላበትን ትምህርት መስጠት የሚጠይቅ ነበር። በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟላ እንዲህ ዓይነቱ ስብከት ነው። አስቀድሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት በግልጽ መረዳት ደግሞም የሚያገለግላቸው ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በጥልቀት መረዳት ይገባዋል።

ጳውሎስ አስቀድሞ የሚያመለክተው ሌላው ምክንያት ደግሞ ሰዎች ጤናማ ትምህርት የማይቀበሉበት ቀን የሚመጣ መሆኑን ነው። ከታሪክ እንደምንገነዘበው ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የይሁዲነት አክራሪዎችና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወደ መንጋው በመምጣት በጎችን አታልለው ለማሳት ሞክረዋል። ዛሬም በተመሳሳይ መንገድ ይህ አንገብጋቢ ተግባርና ኃላፊነት በእኛ ላይ ወድቋል። እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖት ነፃነትን ለኢትዮጵያ ሰጥቷል። ስለዚህ ወንጌልን በታማኝነት የምንሰብክበት

ወቅት ነው። ይህ ነፃነት እስከ መቼ እንደሚቀጥል አናውቅም። ብዙ መናፍቃን ከሐሰት ትምህርቶቻቸው ጋር እየዘለቁ እየገቡ ነው።

4ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡14-16፤ 9፡16 አንብብ። «ግዴታ» የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ጳውሎስ ግዴታ አለብኝ የሚለው ለምንድ ነው? ጳውሎስ በወንጌል አለማፈሩን የተናገረበትን ምክንያት ስጥ። ወንጌልን እንዲሰብክ ያስገደደው ማን ነው?

ጳውሎስ ወንጌልን የመስበክ ጥሪ ከእግዚአብሔር ተቀበለ። መንፈስ ቅዱስም ይፈጥን ዘንድ ግድ አለው። እናም አገልግሎቱን ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ ታዘዘ። ጳውሎስ የዜግነትና የእውቀት ደረጃ ልዩነት ሳያደርግ ለሰው ሁሉ ወንጌል መስበክ እንዳለበት ግልጽ ሆኖለት ነበር። ጳውሎስ ምስክርነቱን ቢቀበሉ እና ቢያምኑ የእግዚአብሔር ኃይል የሚያምኑትን ሁሉ እንደሚያድን ያውቅ ነበር። «እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?» (ሮሜ 10፡14-15)። መልእክተኛ ያስፈልግ ነበር። እናም ጳውሎስ መልእክተኛ ይሆን ዘንድ ተገደደ።

የስብከቱ ዓላማ ወንዶችን እና ሴቶችን ወደ ክርስቶስ ማምጣትና ከዚያ በኋላ በእምነታቸው እየጎለመሱ ሲሄዱ ማየት ነበር። «እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው» (ቆላስይስ 1፡28)።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ኃይለኛ ስብከት ስለነበር ብዙዎች ለጌታ ተሸንፈው የቃሉን እውነቶች ተምረዋል። ቃሉን በታማኝነት የሚሰብኩ አገልጋዮች ስለነበሩ የአማኞች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ያድግ ነበር። ያመኑትም በቃሉ ጥልቅ እውቀት ያድጉ ነበር። ኢየሱስ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ ነግሯቸው ስለነበር በታማኝነት ትእዛዙን በተግባር ላይ አውለዋል።

5ኛ ጥያቄ፡-ስብከት በቤተ ክርስቲያን ሕይወት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ባለፈው እሑድ በቤተ ክርስቲያን የሰማኸውን ስብከት አስታውስ። ስብከቱ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሚያስፈልጋቸው ነገር በየትኛው አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ነበር? ሰባኪው መልእክቱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ለመስጠቱ ምን ማረጋገጫ ነበር? ከመልእክቱ ምን መጠበቅ እንደሚቻል በሚያሳይ መንገድ መግቢያውን አቅርቦአልን? ንግግሩን ያጠቃለለው እንዴት ነበር? መልእክቱ ከሕይወትህ አንድ ነገር እንድትለውጥ እንዴት አነሣሣህ? ለእግዚአብሔር የበለጠ ቀርበህ እንድትኖር መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደመራህ ተዛምዶውን ግለጽ።

2) ጥሩ የስብከት መልእክት እንዴት እንደሚዘጋጅ

ሀ. የምትዘጋጅበትን የመልእክት ክፍል ምረጥ።

ለመስበክ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መምረጥ፥ በተመረጠው ክፍል ላይ በመጸለይ ለስብከት በሰጠነው የትርጉም ትንታኔ መሠረት በጥንቃቄ መዘጋጀት ማስፈለጉ ግልጽ ነው። ማኅበረ ምእመናኑ በእምነት የጎለመሰ አባላትን ያቀፈ ሆኖ ለማየት እንደምትፈልጉ ማስታወስ ያስፈልጋል። ይህ

ከሆነ ለክርስቲያናዊ እድገትና ብስለት የሚያስፈልጉ የተለያዩ አቅጣጫዎች ይዳሰሱ ዘንድ የቅድሚያ ዕቅዶች መኖራቸው የግድ አስፈላጊ ይሆናል። ማንኛውም ሰባኪ እንደፈቀደው የሚሰብክ ከሆነ ሰዎች የተመጣጠነ እና ሙሉ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ሳያገኙ ይቀራሉ።

አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በሙሉ ምዕራፍ በምዕራፍ፥ ቁጥር በቁጥር፥ መሰበክ አለባቸው። አንድ ተናጋሪ ተከታታይ መልእክት በመስጠት አንድን መጽሐፍ ሊያጠቃልል ይችላል። አንድን ምዕራፍ ወይም አንቀጽ ይዞ አንድ ጭብጥ በመውሰድ መጽሐፉን በሙሉ ሊሸፍን ይችላል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ርእሰ–ጉዳዮች መዳሰሳቸውን ያረጋግጥልናል። በርእሰ–ጉዳይ በሚሰጡ ስብከቶች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችን ፈጽሞ ላናስተምር እንችላለን። አንዱ እንዲህ ብሏል። «እንደዚያማ አይሆንም! በየሳምንቱ የተለያየ ተናጋሪ ሊኖር ይገባል፤ አለበለዚያ ሰዎች ይሰለቻቸዋል።» አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ለማስተማር ሞክረህ ታውቃለህን? ሰዎች ከፍተኛ ፍላጎት አድሮባቸው በትጋት ሲማሩ በማየት ትደነቃለህ።

በሌላ ጊዜ ተናጋሪው ርእሰ–ጉዳይ መርጦ ሊሰብክ ይችላል። ይህም ከወቅቱ ጋር የሚሄድ እንደ ገና፥ ፋሲካ፥ ወዘተ...። ወይም የምናምናቸውን ነገሮች አንዳንድ ገጽታዎች ያካተተ የክርስትና አስተምህሮ ጥናት ሊሆን ይችላል። የትምህርቱ ማስረጃዎች ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊወሰዱ ይችላሉ። ወይም ሰዎች ላሉባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምራቸውን መልእክቶች ማቅረብ ይቻላል። በዚህ ውስጥ ጥፋተኝነት፥ ኃዘን፥ ብቸኝነት፥ ቀናተኝነት፥ጋብቻ፥ ፍቺ፥ ተስፋ መቁረጥና ኃጢአት ሊካተቱ ይችላሉ።

በርእሰ–ጉዳይ በሚሰጥ ስብከት ተናጋሪው የሚጠቀምባቸውን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች በትክክል መተርጎሙን ደግሞም ስለሚናገርበት ርእሰ–ጉዳይ የሚነሡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በሙሉ መጠቀሙን ማረጋገጥ አለበት። አንዳንድ ተወዳጅ የሆኑ ክፍሎችን ብቻ እየተጠቀሙ ማስተማር ሁልጊዜ ወደ ስሕተት የመምራት አደጋ አለው። በርእሱ ላይ ሙሉ መልእክትን ለማግኘት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫን መጠቀም ይረዳል።

ለ. የተመረጠውን ክፍል በጥንቃቄ አጥና።

የተመረጠው ክፍል የሚገኝበትን ሙሉ ዐውደ ንባብ ማንበብ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ከተመረጠው ክፍል በፊት እና በኋላ ያሉትን አሳቦች መገንዘብ እና ማጤን አስፈላጊ ነው ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ይህ ማለት የተመረጠው ክፍል የሚገኝበትን መጽሐፍ በሙሉ በማጥናት የመጽሐፉን ዋና አሳብ ማግኘትና በመጽሐፉ ውስጥ ይህ ክፍል እንዴት እንደሚካተት መገንዘብ ነው።

ሐ. የተመረጠውን የምንባብ ክፍል አወቃቀር፥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን ቃላትና የሰዋሰው አገባብ በጥንቃቄ ተመልከት።

ከአወቃቀሩ ቀጥሎ ቃላትንና የሰዋሰው አገባባቸውን በማስተዋል መመልከት ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችና መዝገበ ቃላት ለዚህ እገዛ ያደርጋሉ። ከዚህ ቀጥሎ የክፍሉን ዋና አሳብ መጻፍ መልካም ነው። የሚናገረው ስለ ምንድን ነው? የክፍሉ ርእስ ጉዳይ ምንድን ነው? ርእስ ጉዳዩን የሚደግፉ ወይም የሚገልጡ ተጨማሪ አሳቦች የትኞቹ ናቸው?

መ. ራስን ስለ ክፍሉ መጠየቅ

ራሳችንን ልንጠይቅ እና መልስ ልናገኝላቸው የሚገቡን ሦስት ጥያቄዎች አሉ።

1. ይህ ምን ማለት ነው? የክፍሉ ዋና ፍሬ አሳብ በሚገባ መፈተሽ አለበት።

2. እውነት ነውን? «አዎን እውነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ያለ ሁሉ እውነት ነው» ማለትህ አይቀርም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ እውነት ቢሆኑም እንኳ፥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው የተመዘገቡ ጉዳዮች ሙሉ ታሪካቸው እንዲሰፍር ሲያደርግ የሁሉንም ምሳሌነት እንድንከተል አይደለም። ስለዚህ የምንከተላቸውን ከማንከተላቸው መለየት አለብን። እግዚአብሔር የሰዎችን ደካማና ጠንካራ ጎን እንዲጻፍ አድርጓል። መጥፎ የሆኑትን ነገሮች እንደ ማስጠንቀቂያ እየወሰድን ከእነርሱ በመሸሽ በጎን ነገር በመከተል ከሁሉም ልንማር እንችላለን።

3. ምን ልዩነት ያመጣል? ይህ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን እውነቶች በተገቢው መንገድ ከሕይወት ጋር የማዛመድ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አብዛኞዎቹ የማጽናኛና የማበረታቻ ምክሮች ለማንኛውም ጊዜ እውነት የሆኑ በተጻፉበት ወቅት በአገለገሉበት መንገድ አሁንም ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ዛሬ ካለንበት የተለየ ሁኔታ በነበረበት ጊዜ የተሰጡ ስለሆኑ ቁም ነገሮቹን ወይም አጠቃላይ ዋና አሳባቸውን ብቻ በመውሰድ በዚያ መሠረት ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ናቸው።

ሠ. የክፍሉን ዋና አሳብ በአንድ ዓረፍተ ነገር መግለጽ።

የአድማጮችን እውቀት እና ልምድ ከግምት ውስጥ በማስገባት የክፍሉን ዋና አሳብ በጥንቃቄ እና በማይረሳ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መግለጽ አለብን። ይህ አጭር ዐረፍተ ነገር አብዛኛውን ጊዜ አይረሳም። ይህን አጭር ዐረፍተ ነገር ለማዘጋጀት ከሁሉም ይልቅ ከባድ ቢሆንም እንኳ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

ረ) ይህ የሚሰሙህ ሰዎች እንዲያደርጉ የምትፈልገውን ወይም በሕይወታቸው እንዲለወጡበት የምትፈልገውን በመግለጽ የመልእክትህን ዓላማ ጻፍ።

የመልእክቱ ዓላማ መጻፍ አለበት። መረጃ መስጠቱ ብቻ በቂ አይደለም። የአስቆሮቱ ይሁዳ እውነትን ያውቅ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሰይጣንም እንኳ እውነቱን ያውቃል። ይንቀጠቀጥማል። የሚያውቀውን

እውነት ግን በተግባር ላይ አያውለውም። ስለዚህ ሰባኪው የመልእክቱን ዓላማ መንጋዎቹን ለተግባር በሚያነሣሣ መንገድ በግልጽ ማቀድ እንዳለበት ከላይ በአራተኛ ደረጃ በተመለከተው እርምጃ የክፍሉን ዋና ትምህርት ወስነሃል። አሁን ደግሞ አድማጮችህ ከተማሩት ነገር አንጻር ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰን አለብህ።

ጳውሎስ፥ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ለምን እንደሚጽፍ እንዲህ በማለት ነግሮት ነበር። «ፈጥኜ ወደ አንተ እንድመጣ ተስፋ አድርጌ ይህን እጽፍልሃለሁ። ብዘገይ ግን፥ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው» (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14–15)።

በስብከት አገልግሎት ምንባቡ ለምን ዓላማ እንደተጻፈ መርምረን መረዳት አለብን። የተረዳነውን ዓላማ ደግሞ የራሳችን ዓላማ ማድረግ አለብን። ዓላማችን አዳማጮቻችን መልእክቱን ከሰሙ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የሚያካትት መሆን አለበት።

ሰ. አስተዋጽኦ አዘጋጁ

አሁን በስብከት የምታስተላልፈውን መልእክት ዋና ፍሬ አሳቦች በመጻፍ ከዋና ፍሬ አሳቦች ሥር ንዑሳን አሳቦችን በማከል አስተዋጽኦ አዘጋጅ። ይህም ሰባኪው የመልእክቱን የተለያዩ ክፍሎችና በሥራቸው የሚመጡ ትንተናዎችን በግልጽ እንዲያስብ ያግዘዋል። አድማጮቹም ሰባኪው የሚናገረው የትኛው ነጥብ እንደሆነ በግልጽ ተረድተው ለመከተል ያግዛቸዋል። ከአንድ ነጥብ ወደ ሌላው ነጥብ በሚሸጋገርበት ወቅት ልንከተለው ወይም ልንፈጽመው የሚገባን ይህን ብቻ አይደለም። ይህ ብቻ ሳይሆን፤ ደግሞም.... የሚሉ የመሸጋገሪያ ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም ይችላል። ወይም ደግሞ ባዘጋጃቸው አስተዋጽኦዎች ሲያስተምር አንደኛ..... ሁለተኛ..... እያለ መቀጠል ይችላል። የመሸጋገሪያ ዐረፍተ ነገሮች አዳማጮች ሁሉ ተናጋሪው የት ቦታ እንዳለ እንዲከተሉ የሚረዱቸው ሲሆን ማስታወሻ በጽሑፍ ለሚይዙ ደግሞ እጅግ ያግዛሉ።

ሸ. በጥሩ መግለጫዎች በመደገፍ በአስተዋጽኦው ዝርዝር ላይ ትንተና ስጥ።

በአስተዋጽኦው ውስጥ የሚገኙ ነጥቦች እያንዳንዳቸው በጥንቃቄ ሊገለጹና ለነጥቦቹ ተስማሚ በሆኑ ሌሎች ክፍሎች ወይም መግለጫዎች ሊተነተኑ ይገባል። በሚገባ የታቀዱ መግለጫዎች ሰዎች ስለ መልእክቱ በሚነጋገሩበት ወቅት በቀላሉ የሚያስታውሷቸው የሚደግሟቸው ናቸው። የክፍሉን ዋና ትምህርት በእውነት የሚደግፍ እስከሆነ ድረስ ማንኛውንም መግለጫ ለመጠቀም አትፍራ።

ቀ. በመጨረሻም ጥሩ የሆነ መግቢያ እና መደምደሚያ አዘጋጅ።

የመልእክቱ መግቢያ እና መደምደሚያ መታቀድ አለበት። መግቢያው በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት መፍትሔ የሚበጅለት የመጨረሻ ክፍል የሰውን ልጅ ችግር የሚያነሣ መሆን ይኖርበታል። የክብሪት እንጨት

የክብሪት ሳጥኑን በሚጭርበት ጊዜ እሳት እንደሚወጣ ሁሉ የሰዎች ችግር እንደ መጠሪያው አካል የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ሲጭር በሰው አእምሮ ውስጥ የሚቃጠል ብልጭታን ይፈጥራል። እያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገው ነገር አለ። እነዚህን ፍላጎቶች ማወቅና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ምላሽ መስጠት ግን የተናጋሪው ድርሻ ነው። ስለዚህ መግቢያ አጠር ብሎ የመልእክቱን ርእሰ-ጉዳይ የሚያስተዋውቅ መሆን አለበት።

መደምደሚያ የስብከቱን ገመዶች ሁሉ በአንድ ላይ ማሰር ይኖርበታል። አንዲት ልብስ ሰፊ ምንም ያህል ቆንጆ አድርጋ ብትሰፋ እንኳ ክሩን በስተ መጨረሻ ካልቋጠረችው ሥራዋ ሁሉ ከንቱ ይሆናል። እንደዚሁ ሰባኪው የመልእክቱን ዋና አሳቦች ሁሉ በማሰባሰብና በማሳጠር በመደምደሚያው ላይ ማጠቃለል አለበት። መደምደሚያው የማለቂያ ስሜት መፍጠር ይኖርበታል። አድማጮቹ የሰሙት የእግዚአብሔር እውነት ምን እንዲያደርጉ እንደሚጠበቅባቸው ሊያውቁና ሊሰማቸው ይገባል።

ከዚህ አገላለጽ የምንመለከተው ስብከት የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅን የሚያካትት በመሆኑ መልእክት በጥንቃቄ መዘጋጀት እና መቅረብ እንዳለበት ነው። መልእክት ከተናጋሪው ወደ አዳማጮቹ የሚተላለፍ የአንድ ቀጥተኛ መንገድ ግንኙነት ነው። ሰባኪው መልእክቱን ያስተላልፋል፤ አዳማጮቹም ይከታተሉታል። ዓላማው ለእድገትና ለለውጥ እንዲነሣሡ ነው።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡- ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ለሚመጣው ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድትናገር ስትጋበዝ የምትጠቀምበትን ጥሩ ስብከት አዘጋጅ። እግዚአብሔር በሁሉ በታ ላይ ይመራህ ዘንድ ስትዘጋጅ መጸለይህን አትርሳ። |

## ሁለተኛ ቀን፡- የትምህርት ትርጓሜ

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡- ካስተማሪዎችህ ሁሉ ይበልጥ ማንን ታደንቅ ነበር? የምታደንቀው ለምንድን ነበር? እስቲ ሲያስተምር የሚጠቀምባቸውን ስልቶች አስታውስ። አብዛኛውን ጊዜ ገለጻ ያደርግ ነበር? ወይስ ከተማሪዎች ጋር ይጠያየቅ ነበር? ሲያቀርባቸው የነበሩ አንዳንድ የውይይት ርእሶች ምንድን ነበሩ? ልትረሳው የማትችል ለቀጣይ ሕይወትህ የሚረዳ ምን አዲስ ነገር ተቀብለህ ነበር? |

## ትርጓሜ

ማስተማር- ማስተማር ማለት እውነትን ከአስተማሪው ወደ ተማሪው የማስተላለፍ ሂደት ነው። ይህ ሂደት ተማሪው ይማር ዘንድ የአስተማሪው ሁኔታዎችን የማመቻቸት፥ አንድ ሰው አንድ ነገር እንዴት እንደሚያደርግ የማሳየት ወይም የመርዳት፥ አንድን ርእስ ጉዳይ ያጠና ዘንድ የመምራት ወይም የማሳየት፥ እውቀትን ወይም አመለካከትን የመስጠት፥ አንድ ሰው እንዲያውቅ ወይም እንዲገባው የመርዳት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ የሚያካትት ነው። ማስተማር ከስብከት ይለያል። ግንኙነቱ የሁለት አቅጣጫ ነውና።

### 1. ትምህርት ከስብከት በምን ይለያል?

*ሀ. ትምህርት የሁለት አቅጣጫ ግንኙነት ነው።*

የስብከት እና የትምህርት አንዱ እና ዋናው ልዩነታቸው ትምህርት የሁለት አቅጣጫ ግንኙነት መሆኑ ነው። ትርጉሙን ብትመለከት አስተማሪው ቀዳሚ ቢሆንም እንኳ የትምህርቱ ዋና አትኩሮት ተማሪው መሆኑን ልትገነዘብ ትችላለህ። ይህ ትርጉም ከሚያመለክታቸው ነገሮች አንዱ እውቀት ከአስተማሪው ወደ ተማሪው መተላለፉንና ተማሪው በሚገባ እስኪያውቅ ድረስ አስተማሪው ያለመታከት መሥራቱን ነው። ሌላው ደግሞ ተማሪው በትምህርቱ ላይ ያተኩር ዘንድ አስተማሪው የማነቃቃት ተግባር የመፈጸሙ ጉዳይ ነው። አስተማሪ ሊመራ፥ ሊረዳ፥ ሊያሳይ፥ መረጃዎችን ሊያቀብል፥ ወዘተ... ይችላል። ነገር ግን መማር ያለበት ተማሪው ነው። ማንም አስተማሪ ለተማሪው ሊማር አይችልም። ተማሪው በሚያገኘው ርዳታ ሊጠቀም ይችላል። ወይም መመሪያው በሥራ ላይ እንዴት መዋል እንደሚገባው ባለማወቁ ጠቀሜታው ይቀርበታል።

አስተማሪው ተማሪው በጥያቄ እና መልስ አማካኝነት እንዲያስብ እና መረጃዎችን እንዲያገናዝብ ያነቃቃል። ለጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ሦስት ምንጮች አሉ።

1. አስተማሪዎች ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ ተማሪዎች ይመልሳሉ።

2. ተማሪዎች ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ አስተማሪዎች ይመልሳሉ።

3. ተማሪዎች ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ ተማሪዎች ይመልሳሉ።

ጥያቄዎች ለትምህርቱ ሂደት ቅመሞች ናቸው። አስተማሪው የተወሰነ መረጃ ከሰጠ በኋላ ተማሪው ተረድቶት እንደሆነ ለማረጋገጥ በጥንቃቄ በተመረጡ ቃላት ጥያቄዎችን ሊጠይቅ ይችላል። ወይም ደግሞ ተማሪው ያልተረዳውን ነገር ለመገንዘብ የሚያብራራ ጥያቄ ለመጠየቅ ይፈልግ ይሆናል። አልያም ደግሞ በክፍሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ይመልሰው ዘንድ ለሁሉም ክፍት የሆነ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል። ውይይቱ በአንድ ሰው ብቻ በሚሰጥ ትምህርት ሊደረስበት የማይችል የአንድን ችግር ወይም ጉዳይ እውነታና መፍትሔውን ሊያስገኝ በሚችል ሁኔታ የትምህርትን ሂደት የሚያነቃቃ ነው።

ለ) ትምህርት ተማሪን ማዕከል ያደረገ ነው።

አንድ አስተማሪ ወደ ክፍል ገብቶ በተማሪዎቹ ፊት ለፊት ቆሞ የተዘጋጀበትን ትምህርት አነብንቦ እንዳስተማረ ቆጥሮ የሚወጣበትን የገለጻ ዘዴ ሊመርጥ ይችላል። የትምህርቱን ዋና ነገሮች ለተማሪዎች ሊያጽፍ እነርሱም በጥንቃቄ በማስታወሻ ደብተራቸው ሊጽፉ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ በመሆኑ ተማሪዎቹ ተምረዋል ማለት ነውን?

በገለጻ (ሌክቸር) የማስተማር ስልት የትምህርት ሂደት አካል ሲሆን እጅግ በሚጠቅም ሁኔታ አገልግሎት ላይ ሊውል መቻሉ እርግጥ ነው። ብቸኛ የማስተማሪያ ስልት ከተደረገ ግን ሂደቱ ስብከት እንጂ ትምህርት ሊሆን አይችልም። እውነተኛ ትምህርት ሁልጊዜ የተማሪዎቹን የመረዳት ሁኔታ ከግንዛቤ የሚያስገባ ነው።

የአስተማሪው ዓላማ ተማሪዎች እንዲማሩ ነው። ስለዚህ ዓላማው እንዲሳካለት የተለያዩ ስልቶችን መቀየስ ይኖርበታል። አብዛኛዎቹን ስልቶች በኋላ እንመለከታቸዋለን።

ሐ. የክርስቲያን ትምህርት ጥሪት ሕይወትን መለወጥ መሆን አለበት

እንደ ስብከት ሁሉ የክርስቲያናዊ ትምህርት ጥሪት ሕይወትን መለወጥ ነው። ትምህርት ከስብከት የሚለየው በጣም ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የተማሪዎቹን ሕይወት ለለውጥ በመጋበዝና ምላሻቸውንም አቅጣጫ ለማስያዝ በመቻሉ ነው። በተማሪው እና በአስተማሪው መካከል የአሳብ ልውውጥ ስላለ የተማሪው ችግር በግል ወይም በቡድን ውይይት ሊፈታ ይችላል። አስተማሪው በተማሪው የእድገት ሂደት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ያስችለዋል። በክፍል ውስጥ በተነሡት አሳቦች መሠረት በቡድን ወይም በግል የምክር አገልግሎት ማከናወን ይቻላል።

በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቁጥር አብሮ መማር በትልቅ ጉባኤ ውስጥ ሊገኝ የማይችል መቀራረብና ጓደኝነት ይፈጥራል። አስተማሪው በክፍል ውስጥ የሰጠውን ትምህርት ለማጠናከር የቤት ሥራዎችን ማከል ይችላል። እነዚህም የቤት ሥራዎች ተማሪው የተማረውን ትምህርት ሳምንቱን በሙሉ እንዲያሰላስለውና ጌታም ጥበብን እንዲሰጠው እንዲጠይቅ ሊያደርጉት ይችላሉ።

የመማር ሌላው እጅግ ጠቃሚ ስልት የቃል ጥናት ነው። ተማሪው በቤቱ የሚያጠናው የቃል ጥናት ጥቅስ ሲሰጠው አእምሮው ሳምንቱን በሙሉ በጉዳዩ ላይ ንቁ እንዲሆን ያደርገዋል። ልጆች በተለይ የቃል ጥናት ጥቅስ ይወዳሉ። ዳዊት እንዲህ ብሏል። «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ. (119)፡11)። በተለይ በልጅነት ወራት በቃል የተጠና ጥቅስ እስከ ሕልፈተ–ሕይወት ድረስ አብዛኛውን ጊዜ አይረሳም፤ እናም በፈተና ጊዜ ወይም ውሳኔ ማድረግ በሚያስፈልግበት ወቅት ምሪትን ይሰጣል።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፡– በክፍል ውስጥ ተገኝተህ በተማርህባቸው ጊዜያት ሁሉ ተጠቃሚ ሆነሃልን? እስቲ ስላጋጠሙህ ስለ ጥቂት ደካማ አስተማሪዎች ተናገር? ለምንድን ነው ክፍላቸውን ያልወድድኸው? እንዴት ማሻሻል ይችሉ ነበር? |

## 2. የማስተማር ድክመቶች

### ሀ. የትምህርቱ አቀራረብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በታሰበለት ሁኔታ ስኬታማ የማይሆንባቸው ሁለት ዋና ደረጃዎች አሉ። የመጀመሪያው በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ነው። ይህ ጠንከር ያለ ድክመት አይደለም። መፍትሔውም በጣም ቀላል ነው።

ብዙ ጊዜ አስተማሪው ለዚህ ተግባር አዲስ በመሆኑ ወይንም በደንብ ባለመዘጋጀቱ ይፈራል። በዝግጅትም ሆነ በትምህርቱ ላይ ብዙ ልምድ ሲያገኝ ፍርሃቱ ይለቀዋል።

ክፍሉን ሊረብሽ የሚችል ወገኝነት ሊኖረው ይችላል። እጁ ላያርፍ ይችላል። ሁልጊዜ ሊቁነጠነጥ፥ እጁን ወደ ፊቱ ወይም ወደ ጸጉሩ

በማንቀሳቀስ እና ወይም ኪሱ ውስጥ በመከተት ፋታ ሊያጣ ይችላል። ከምስባኩ ላይ ሊተኛ ወይም በተደጋጋሚም ጉሮሮውን ሊያጸዳ እና ሲናገር ሊፈጥን ይችላል።

ብዙውን ጊዜ ይህ ዓይነቱ ችግር በቅርብ ተቆጣጣሪው ፍቅር የተሞላበት መጠነኛ ምክር ሊፈታ ይችላል።

ለ. ይዘት እና ዘዴን ማቀድ

አስተማሪው በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ሁሉን በትክክል ሠርቶ እንኳ የተዋጣለት ትምህርት ላይሰጥ ይችላል። ለእነዚህ ድክመቶች ብዙ ምክንያቶች አሉ።

1. የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በትክክል ለመተርጎም ያለመቻል

ሀ) አስተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን በትክክል እንዴት መተርጎም እንዳለባቸው የማያውቁበት አንዱ ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ዓይነት የአጻጻፍ ዘዴዎች መኖራቸውን ያለመገንዘባቸው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሥነ መለኮት እውነቶች፥ ታሪካዊ ክንውኖች፥ ትረካዎች፥ ግጥሞች፥ ዘይቤያዊ አነጋገሮች እና ምሳሌዎች፥ ወዘተ... ይገኛሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ዓይነት የአጻጻፍ ስልቶችን ጉዳይ በወደፊት ትምህርታችን እንመለከታለን።

ለ) የምንባቡን ዋና አሳብ ወይም ርእሰ-ጉዳይ ለመለየት ያለመቻል

በመልእክት (ስብከት) ዝግጅት ትምህርታችን ላይ የምንባቡን ዋና ፍሬ አሳብ ለይቶ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ብለን እንደነበረ ታስታውሳለህ። የምንባቡ ክፍል ተለይቶ የሚታወቀው በዚህ ዋና አሳብ ሲሆን የትምህርቱን ማዕከላዊ ዓላማ የሚገዛውም ይህ ዋና አሳብ ነው። ብዙ ጊዜ ሰነፍ አስተማሪዎች ብዙ የማይዛመዱ አሳቦችን ከአንድ ምንባብ ውስጥ ያወጣሉ። ትምህርቱን በማዳመጥ የተሳተፉ ሰዎችም አንዳች ግልጽ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሳያገኙ ይመለሳሉ። ስለዚህ የምንባቡን ማዕከላዊ እውነታ ለመገንዘብ በሚደረግ ጥረት ውስጥ ምንባቡ የሚገኝበትን ጠቅላላ አሳብ ማንበብና በምንባቡ ውስጥ ምን ለማለት እንደተፈለገ መረዳት አስፈላጊ ነው።

ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሉን ትቶ ወደ ሌሎች አስረጅ ጉዳዮች ማምራት

የምንባቡን ማዕከላዊ እውነት በሚገባ ያለመረዳት በአስተማሪዎች ላይ የሚያመጣው ፈተና ከምንባቡ ጋር ወደማይገናኝ ሌላ ጉዳይ ውስጥ መግባት ይሆናል። ምናልባትም የምንባቡን ክፍል ሊተረጉም ወደማይችል የቀልድ ንግግር ውስጥ በመግባት የተለያዩ መግለጫዎች ሊሰጡ ይችላሉ።

2. በአንድ ክፍለ ጊዜ ብዙ ለማስተማር መሞከር ሌላው ድካም ነው።

የምንባቡን ማዕከላዊ ትምህርት መፈለግ፥ በጥንቃቄ መተርጎምና ለማብራራት አጋዥ የሆኑ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መጠቀም፥ ገለጣ መስጠት፥ ጉዳዩን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን መጠየቅና በዚህም

የአድማጮች አእምሮ ወደ አንድ አሳብ እንዲያተኩር ማድረግ እጅግ የተሻለ ነው። ይህ ሲሆን ተማሪዎች አንድን እውነት በሚገባ ተምረው ይሄዳሉ።

3. ተማሪውን እጅግ ዝርዝር በሆኑ ጉዳዮች ማጨናነቅ

አንዳንድ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን እጅግ ብዙ በሆኑ የሰዎችና የቦታ ስሞችና ቀናት ያጨናንቃሉ። ለተማሪዎች የማይገቡ ቃላትን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በመጀመሪያ የተሰጠውን ጥቅስ አውጥተው ለመመልከት እየጣሩ ሳሉ እነርሱ በርከት ያሉ ሌሎች ጥቅሶችን በመጥቀስና ያለማቋረጥ በመናገር ተማሪዎቻቸውን ፋታ ያሳጣሉ።

4. ክፍተትን አለመሙላት።

«ክፍተትን መሙላት» የመጽሐፍ ቅዱስን አሳብ ከዘመናዊ አኗኗር ጋር በማዛመድ ትርጉም እንዲሰጥ የማድረግ ሂደት ነው። መጀመሪያ አስተማሪው ምንባቡን በሙሉ በሚገባ ማወቅ እና ተማሪው እንዲገነዘብ መርዳት አለበት። ከዚያም ተማሪውን ወደ ዛሬ ሕይወት ማምጣት እና እንዴት አድርጎ ዛሬ ባለበት ሁኔታ ውስጥ መጠቀም እንዳለበት ማሳየት አለበት።

## 3. ማስተማርን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል።

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማተኮር

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት መሆን አለበት። የአጻጻፉን ስልት መረዳትና በዚያው መልክ ማስተማር አለብን።

ለ. «ዋናውን አሳብ» መፈለግ

በሌላ አባባል ይህ ማለት የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ወይም ትምህርት ማግኘትና በዚያ ላይ ማተኮር ማለት ነው።

ሐ. ክፍሉን መተርጎም

ክፍሉን ከተመለከትን በኋላ ወደ ትርጉም መሄድ አለብን። ስለዚህ ጉዳይ ወደፊት በምንመለከታቸው በሌሎች ትምህርቶች ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያዎች እንሰጣለን።

መ. ክፍተትን መሙላት

በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያነበብነው ክፍል በተጻፈበት ጊዜ ለነበሩት ተደራሲያን የሰጠውን ትምህርት በሚገባ መገንዘብና መረዳት ያስፈልጋል። ከዚያ በመቀጠል አሁን ወዳለንበት ሁኔታ በመመለስ የትምህርቱን አጠቃላይ መመሪያ ማዛመድ ይኖርብናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች ብቻ መጠቀሚያ የሆነበት ወቅት ነበር። ተራው ምእመን አያነበውም ነበር። ከተሐድሶ እንቅስቃሴ ትኩረቶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ በተራው ምእመን እጅ እንዲገባ ማድረግ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቡ ዕለት ተዕለት ወደሚጠቀምባቸው ቋንቋዎች ተተረጎመ፤ ሕዝቡም ደስ ብሎአቸው አነበቡት። ይህም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንመለከተውን ተሐድሶና መነቃቃት አስከተለ፤ እኛም የዚሁ መነቃቃት ተጠቃሚዎች ለመሆን በቅተናል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

የሚገኙ ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፥ በተገቢው መንገድ በመተርጎምና በመገንዘብ በትምህርቱ የመኖር ጉጉት ይፈጠርባቸው ዘንድ ብቃት ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለመስጠት እንትጋ።

---

9ኛ ጥያቄ፡- ከዚህ ቀደም ያስተማርሃቸውን ክፍሎች መለስ ብለህ አስታውስ። አሁን ከተመለከትናቸው ጉዳዮች አንጻር በማስተማር ሂደት ውስጥ ስለነበሩህ ችግሮች ምን ተገነዘብህ?

---

## ሦስተኛ ቀን፡- የመማር ማስተማር ሂደት – ክፍል አንድ

መልካም አስተማሪ ለመሆን የመማር እና የማስተማርን ደንብ ማወቅ አለብን። በዚህና በሚቀጥለው ምዕራፍ የተዋጣለት መምህር ለመሆን በማስተማር ሂደት ውስጥ ልታካትታቸው የሚገቡ አሥር ነገሮችን እንመለከታለን።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡1–16 በጥንቃቄ አንብብ። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ራሱ ትምህርት ነው። በሚገባ የተማረ ሰው ነበር። በማስተማር ሂደቱ ውስጥ የተደገፈው እጅግ በላቀው ጥበቡ ነበርን? ወይስ በሚያስተምርበት ወቅት በሚገባ ለመናገር በነበረው ችሎታ? ትምህርቱ እጅግ ኃይል የሞላበት የነበረበትን ምክንያት ግለጽ። በሰብአዊ እውቀቱ ላይ ለመደገፍ ይፈራ የነበረበት ምክንያት ምን ነበር? ፍሬያማ ለሆነ የማስተማር አገልግሎት ብቸኛው እውነተኛ ኃይል ምን እንደሆነ ይመሰክራል? |

1. መምህሩ መንፈሳዊ ውጤቶችን ይቀዳጅ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መታመን አለበት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሂደት ሰዎችን በመሣሪያነት በመጠቀም የሚያስተምር መንፈስ ቅዱስ ነው። ጳውሎስ እንደተናገረው በራሱ ታላቅ ጥበብ ወይንም የመናገር ችሎታ አይደገፍም ነበር። ይልቁኑ ከተሰቀለው ከክርስቶስ ሌላ እንዳያውቅ ወስኖ ነበር። ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመታመን በብዙ ትሕትናና ፍርሃት አደረገ። መልእክቱን የተቀበሉና ያመኑ ሁሉ እምነታቸውን በመንፈስ ለሰዎች በተገለጠው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ የዘወትር ተግባሩ ነበር።

ሀ) ሰብአዊው መምህር የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ይገባዋል።

ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት በነበሩት በመጨረሻዎቹ ቀናት ደቀ መዛሙርቱን ሲያስተምር አብ ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር የሚሆን አጽናኝ እንዲልክላቸው እንደሚለምን ነግሮአቸው ነበር። «በመካከላችሁ ይሆናል በውስጣችሁም ይኖራል።»

ለ. ሰብአዊ መምህር በመንፈስ ቅዱስ መማር አለበት።

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፤ «...አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፥ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል» (ዮሐ. 14፡26)። ዮሐንስ 15፡26 ደግሞ አጽናኙ መንፈስ ስለ ክርስቶስ እንደሚመሰክር ይናገራል።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ይወቅሳል።

እንደገና በዮሐንስ 16 ላይ መንፈስ ቅዱስ «...ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» ተብሎ ተጽፎአል።

መ. ደግሞም እርሱ የእውነት መንፈስ ስለሆነ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል (ቁ. 13)።

የቆሮንቶስ መልእክት ጸሐፊ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምሥጢራት ማወቅ እንደተሰጠን ይናገራል። ምክንያቱም መንፈሱ ለእኛ ገልጦልናል። የእግዚአብሔርን አእምሮ የሚያውቀው መንፈሱ የእግዚአብሔርን እውነቶች ማለትም መንፈሳዊ እውነቶችን በመንፈሳዊ ቃላት ገለጠልን (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10–16)። ያልዳነው ሰው የእግዚአብሔርን ጥልቅ እውነቶች ለመረዳት አይችልም። ምክንያቱም መንፈሱ በውስጡ አይኖርም። መንፈሳዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ስለሚኖር የእግዚአብሔርን እውነት ለመቀበልና ለመለየት ይችላል።

ሰብአዊ መምህር አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሣሪያ ብቻ አይደለም። ለራሱ ሕያው የሆነ ትርጉም እስኪሰጠው ድረስ ቃሉን ማሰላሰል እንዳለበት ያውቃል። ለመልእክቱ አቀራረብ ሙሉ ለሙሉ በመንፈስ ቅዱስ በመታመን በጸሎት መንፈስ ሆኖ በሚገባ መዘጋጀት አለበት። በጸሎትና በምክር ይረዳቸው ዘንድ የአድማጮቹን ፍላጎት ለማወቅ ንቁ መሆን ይገባዋል። ግቡም በተማሪዎቹ ሕይወት ውስጥ ዘላቂ ውጤቶችን ማየት መሆን አለበት።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፡— 1ኛ ቆሮ. 11፡1፥ 4፥ 16፤ ፊልጵ. 3፡17፥ 4፤ 9፤ 1ኛ ተሰ. 1፡6፤ 2ኛ ተሰ. 3፡7 አንብብ። ጳውሎስ በተደጋጋሚ የሚሰጠው አንድ ትእዛዝ ምንድን ነው? ልትጠቅሰው ትችላለህን? ልትጠቅሰው ካልቻልህ ለምን? እስካሁን ምርጫ ባደረግህባቸው ጉዳዮች ስለዚያ አስበህ ታውቃለህን? ያለማቋረጥ የምታደርገውን ነገር የሚከታተል ሰው ቢኖር ጠባይህ እንዴት ይሆን ነበር? በአካባቢህ የሚኖሩ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቁት ነገር አለን? ግንዛቤ ከሌላቸው ፈሪሃ እግዚአብሔር የተሞላበትን የሕይወት ምሳሌነት ማየታቸው እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል? |

1. አስተማሪው ለተማሪዎቹ ምሳሌ መሆን አለበት

ጳውሎስ፥ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11፡1) ሊል አላፈረም ነበር። የክርስትና ሕይወት ጽንሰ–አሳብ በአጠቃላይ ለአድማጮቹ አዲስ ነበር። ስለ ብሉይ ኪዳን ትምህርት ምንም ግንዛቤ የሌላቸው አሕዛብ ነበሩ። ስለዚህ ጳውሎስ በጥንቃቄ ማስተማር ብቻ ሳይሆን የክርስቲያኖች ሕይወት ምሳሌ መሆን በጣም ያስፈልገው ነበር።

እንደ አስተማሪነታችን ልናስታውሰው የሚገባን ነገር ከንግግር ይልቅ አብዛኛው ጊዜ የምናስተምረው በተግባራችን መሆኑን ነው። ከብዙ ዓመታት በፊት ማሪዮ ሎሪያንስ ሲያብራሩ፥ «አንድ እንከን የሌለበት የሰንበት ትምህርት አስተማሪ አእምሮውን ለዝግጅቱ፥ ነፍሱን ለአቅርቦቱ፥ ሕይወቱን ለማብራሪያው የሰጠ ነው» ብለዋል።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡— ብዙ አስተማሪዎች ከተማሪዎቻቸው በጣም የራቁ ናቸው። ከተማሪዎቻቸው ጋር ከተቀራረቡ በክፍላቸው ውስጥ ሥነ ሥርዓትን ሊያስጠብቁ እንደማይችሉ ያስባሉ። ወይም በተማሪዎች ዘንድ በሚገባ የታወቁ መሆን መናናቅን |

የሚያመጣ ይመስላቸዋል። አስተማሪ ለተማሪዎቹ ሊኖረው የሚገባ ትክክለኛ ዝንባሌ ምን መሆን አለበት ትላለህ? ይህ ለማንኛውም የዕድሜ ክልል እውነት ነው?

3. አስተማሪው ለተማሪዎቹ ክርስቲያናዊ ፍቅርን ሊያሳያቸው ይገባል።

ታላቁ ምሳሌአችን ኢየሱስ ላገኛቸው ሁሉ ፍቅሩን ያሳይ ነበር። ፍቅሩን የሚገልጠው አንዳንድ ጊዜ በቃላት ቢሆንም እንኳ፥ ብዙውን ጊዜ ግን በተግባር ነበር። ስለ እነርሱ፥ በእርግጥ ይጠነቀቅ ነበር። ፍቅሩንም ለመግለጽ አይፈራም ነበር። ፍላጎታቸውን ሁሉ አርክቷል። ገንዘብ አልሰጣቸውም፥ አልፎ አልፎ ምግብን ይሰጥ ነበር። ያዝንላቸውና ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ ይረዳላቸው ነበር፤ ከዚያም ተገቢውን ድጋፍ ያደርግላቸዋል።

አሥራ ሁለት ጊዜ በወንጌል ውስጥ ለሕዝቡ እንደራራላቸው ተጽፎ እናነባለን። አንዳንዱ በትምህርት እጦት፥ የሚመራቸው ከማጣት የተነሣ፥ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ሆነው ስለተመለከተ ነበር። ለደቀ መዛሙርቱ የመከሩ ጌታ ለመከሩ ሠራተኞችን ያስነሣ ዘንድ እንዲጸልዩ አሳስቦአቸዋል (ማቴዎስ 9:36፤ ማርቆስ 6:34)። አንዳንድ ጊዜ የቁሳዊ ፍላጎት ጉዳይ ነበር (ማቴዎስ 14:14) እና ይመግባቸው ወይም ይፈውሳቸው ነበር (ማቴ. 20:34)። ኢየሱስ ወደ ሰማርያ መውረድ ያስፈለገው (ዮሐ. 4) ወደ ገሊላ በሚወስደው መንገድ ላይ አንዲትን ሳምራዊት ሴት በምንጭ አጠገብ እንደሚያገኝና ፍቅርን አሳይቶ ወደ እምነት ማምጣት እንዳለበት ስላወቀ ነበር። ለሰዎች ሁሉ ተገቢ እንክብካቤና ጥንቃቄ አደረገ፤ ራሱንም ሰጠ።

ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ ፍቅር ነው። መንፈስ ቅዱስ በሙላት ከተቆጣጠረንና በሕይወታችን ተቀዳሚውን ስፍራ ከያዘ መወደድ ለማይገባቸው እንኳን ሳይቀር ፍቅር እንዲኖረን ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን ፍቅር ይሰጠናል። ይህንን ፍቅር በትምህርታችን ውስጥ በምሳሌነታችን እና በድርጊታችን ልናሳይ እንችላለን (1ኛ ጴጥሮስ 3:8 አንብብ)፤ ዮሐንስ 13:35 እንዲህ ይላል፤ «እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ»።

13ኛ ጥያቄ፡- ብዙ ጊዜ አስተማሪው በክፍል ውስጥ የሚናገራቸው የመጀመሪያ ቃሎች የዕለቱን ትምህርት ከማስታወቃቸው ባሻገር ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት በማነሣሣት አትኩሮታቸውን ይስባሉ። ከዚህ በፊት ከተማርካቸው ትምህርቶች ማራኪ ነበር ብለህ የአሰብከውን ትምህርት አስታውስ፤ አስተማሪው ወደ ትምህርቱ ለመግባት የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበር? በክፍሉ ውስጥ ቆይተህ ትምህርቱን እንድትከታተል የሚያደርግ ነበርን? አንዳንድ አስተማሪዎች ለትምህርታቸው አጋር ሊሆን የሚችል ጥሩ መግቢያ አይጠቀሙም። እንደነዚህ ዓይነት አስተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዴት እንደሚጀምሩ ምሳሌ ስጥ። ከሁሉ የላቀ ትምህርት የተማርክበት ከየትኛው ነው?

4) አስተማሪው የተማሪዎቹን ቀልብ ለመሳብና ለመያዝ ተስማሚ የሆነ የአቀራረብ መንገድ መፍጠር አለበት።

በመማርና ማስተማር መመሪያዎች ገለጻ ውስጥ እስካሁን ድረስ «መምህሩን» ተመልክተናል። ቀጥሎ ደግሞ አስተማሪው ስለሚጠቀምባቸው «ዘዴዎች» ጥቂት እንመለከታለን።

ሀ. አስተማሪ አነቃቂ መግቢያ ለትምህርቱ ሊሰጥ ይገባዋል።

ይህ መንጠቆ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ተማሪዎቹን ለሚቀጥለው ትምህርት ንቁ ሆነው እንዲጠብቁ የሚያደርግና የሚስባቸው ነገር ማለት ነው። ኢየሱስ በምንጭ አጠገብ ላገኛት ሴት፥ «የሚጠጣ ውኃ ስጭኝ» ሲል ተናገራት። ይህ ነገር ለሴቲቱ የሚያስገርም ነበር። ምክንያቱም እርሱ አይሁዳዊ ነበር። እርሷ ደግሞ ሳምራዊት ነበረች። እርስ በርሳቸው መግባባት አልነበራቸውምና። ከዚያም እርሱ እንደሚሰጣት ተናገረ። ውኃ የሚቀዳበት እንዳችም ነገር በእጁ እንደሌለ ትመለከት ነበርና እንዲህ ማለቱ የበለጠ አስደነቃት። በዚህ ጊዜ እውነተኛ አትኩሮት አግኝቶ ነበር። ስለዚህ በመሢሑ ላይ እምነቷን የምታደርግበትን ትምህርት እስከ መጨረሻው ለማስተማር የሚችልበት ደረጃ ላይ ነበር።

ለ. አስተማሪው በትምህርቱ መግቢያ ያገኘውን የተማሪዎቹን አትኩሮት እስከ መጨረሻው ለማቆየት እንደ ሥዕሎች፥ ሞዴሎች፥ የተለያዩ ዕቃዎችና ተግባራትን በትምህርት መርጃ መሣሪያነት መጠቀም ይችላል። የትምህርቱ ሂደት በተማሪዎቹ አእምሮና ሕይወት ውስጥ የሚፈለገውን ውጤት በሚያመጣበት መንገድ ይቀጥል ዘንድ በሚገባ መታቀድ አለበት።

ሐ. የቤት ሥራ በሚገባ ከታቀደ የመማሩን ሂደት ሊረዳ እና በክፍሉ ውስጥ የተሰጠውን እውነት ለመተግበር ጽኑ ፍላጎት ሊያሳድር ይችላል።

እነዚህን ነገሮች በሚመጡት ትምህርቶች የበለጠ እንነጋገርባቸዋለን።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- አንድ አስተማሪ ከዚህ በፊት ፈጽሞ ለምተኸው የማታውቀውን ጽንሰ አሳብ በሚናገርበት ክፍል ውስጥ ተገኝተህ ታውቃለህን? ምን ማለቱ እንደሆነ በሚገባ አብራርቶ ነበርን? ምን ስሜት አሳደረብህ? |

5) አስተማሪው የሚጠቀምባቸው ቃላትና የሚያስተላልፋቸው ጽንሰ አሳቦች ተማሪዎች በሚገባ የሚረዱአቸው መሆን አለባቸው።

አስተማሪው የሚያስተምረው ማንኛውም ነገር በተማሪዎቹ ችሎታ እና በዕድሜያቸው ደረጃ በሚገባቸው መልኩ መብራራት አለበት። ይህም ተማሪዎችህን በሚገባ የማወቅና በዓቅማቸውና በመረዳት ችሎታቸው መጠን የማስተማርን አስፈላጊነት ያሳየናል። ልጆችንና አዋቂዎችን በተመሳሳይ ደረጃ አናስተምርም። አዋቂዎችንም እንኳ ከአስተዳደጋቸውና ከሥራ ጸባያቸው አንጻር በምናስተምራቸው ትምህርቶች መካከል ልዩነት ማድረግ ይጠበቅብናል። ገበሬዎችን የምታስተምር ከሆነ የሚገባቸውን ቋንቋ ትጠቀማለህ። በትምህርትህ የምትጠቀምባቸው መግለጫዎች መሬትን፥ ሰብልንና መንጋዎችን የሚጠቅሱ ይሆናሉ። ዶክተሮችን፥ ነርሶችን፥ ጠበቆችንና ልዩ ሙያ የማይጠይቁ ሥራዎችን የሚሠሩ ሰዎችን የምታስተምር ከሆነ ከልምዳቸውና ካገኙት ሥልጠና ጋር ተስማሚ የሆኑ መግለጫዎችንና ቋንቋዎችን መጠቀም ይጠበቅብሃል። የገጠር ወይም የከተማ ሰዎች መሆናቸው በትምህርት አሰጣጥህ ላይ የሚያመጣው ልዩነት ይኖራል።

ተማሪዎች ምን ያህል የተማሩትን ትምህርት እየተረዱት እንደሆነ የማወቂያው ውጤታማ መንገድ ጥያቄን መጠየቅ ነው። አሳቦችን የሚመዝኑና

የተሰጠውን ትምህርት ተማሪዎች ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት የሚጋብዙ በሚገባ የተሰጣቸው የታሰበባቸው የግንኙነት ሰንሰለት ያጠነክራሉ።

15ኛ ጥያቄ፦ ከዚያ ቀን በፊት ተለማምደኸው ከምታውቀው ነገር ጋር ፈጽሞ ግንኙነት የሌለው ትምህርት በሚሰጥበት ክፍል ተገኝተህ ታውቃለህን? መልስህ አዎን ከሆነ አስተማሪው ምን ማድረግ ነበረበት? አስተማሪው አንድን አዲስ አሳብ ለክፍሉ በሚያስተዋውቅበት ጊዜ በመጀመሪያ ምን ማድረግ ነበረበት? ጌታ ኢየሱስ አንድን አዲስ ጽንስ አሳብ ለማስተማር ከታወቀ እውነት የተነሣበትን ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ ስጥ።

6) አስተማሪው በመማር የማስተማር ሂደት ውስጥ አዲስ እውነትን ለመግለጥ ከሚታወቀው ነገር ወደ ማይታወቀው ቀለል ባለና ለሁሉም በሚገባ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ መሻገር አለበት።

ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ጥልቅ መንፈሳዊ ትምህርት ለመትከል ሲፈልግ በተፈጥሮ እና በግልጽ የሚታዩ ታሪኮች ይጠቀም ነበር። የዘሪውንና የዘሩን ምሳሌያዊ ታሪክ አስታውስ፤ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያዳምጡ ሰዎች ልብ የቃሉን ዘር ስለ መዝራትና ሰዎች ስለሚሰጡቸው የተለያዩ ምላሾች አድማጮቹ ይረዱ ዘንድ እያዘጋጃቸው ነበር እንጂ የግብርና ትምህርት እየሰጠ አልነበረም። ዘሩ በሚሰሙት ልብ ውስጥ የሚዘራውን የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚወክል ተናግሯል። ታሪኩ በአጠቃለለው አራት ዓይነት መሬቶች የተወከሉት አራት ዓይነት ልቦች ናቸው። ለተዘራው ቃል የሚሰጡ አራት ዓይነት ምላሾች በታሪኩ ውስጥ ተጠቃልለዋል። ማንኛውም አድማጭ ከዚህ ትምህርት የራሱን ልብ በመፈተን ምን ዓይነት አድማጭ እንደሆነ ይገነዘባል።

ልክ እንደ ኢየሱስ ትምህርታችንን ተማሪዎቻችን የሚያውቁትና እንግዳ የማይሆንባቸውን ነገር በመናገር መጀመር ይጠበቅብናል። እንደነዚህ ዓይነት ማብራሪያዎች ወይም እውነታዎች በጥንቃቄ ከተመረጡ አድማጩ ከዚህ ቀደም በሚገባ ከሚያውቀው ሊማር ወደሚገባው አዲስ ነገር ለመሸጋገር ይረዳሉ።

መማር ደረጃን እንደ መውጣት መምሰል አለበት። አስተማሪው ተማሪው ወደሚቀጥለው ደረጃ ከማሳለፉ በፊት እያንዳንዱ ደረጃ ለተማሪው አእምሮ ግልጽ መሆን አለበት።

16ኛ ጥያቄ፦ በዚህ ትምህርት የተገነዘብናቸውን ስድስቱን መመሪያዎች ጻፍ። በራስህ ትምህርት ላይ ተግባራዊ ልታደርጋቸው የምትችልበትን መንገድ በመፈለግ አዛምዳቸው።

## 4ኛ ቀን፦ የመማር ማስተማር ሂደት – ክፍል ሁለት

17ኛ ጥያቄ፦ ሕጻናትን በማስተማር ጊዜ አስተማሪዎች «ቁጭ በል!» ወይም «ዝም በል!» ወይም «ወደ እኔ ተመልከት» ወይም «እያዳመጣችሁ ነውን?» በማለት ደግመው ደጋግመው ይጮኻሉ። ይህን ነገር መናገር ለአስተማሪዎች ምን ጠቃሚነት አለው? የልጆችን አሳብ ለመሰብሰብ ሌሎች የተሻሉ መንገዶችን ዘርዝር።

7) አስተማሪው ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ብቻ ሳይሆን አንድ ጉዳይ ላይ ለመድረስ ጥረት እንዲያደርጉ ማነሣሣት መቻል አለበት።

አንዳንድ ትምህርቶች የሚተላለፉት በሚከተለው ሁኔታ ነው። መረጃዎች (አሳቦች) በማንኛውም ወገን አእምሮን ወይም ልብን ሳይነካው ከአስተማሪው ማስታወሻ ደብተር ወደ ተማሪው ማስታወሻ ደብተር ይተላለፋሉ። ይህ ትምህርት አይደለም። ተማሪዎች ያዳምጣሉ፤ አስተማሪያቸው የሚሰጣቸውን ጽሑፍ ይገለብጣሉ። ጽሑፉንም በቃላቸው አጥንተው ይይዛሉ። በመመዘኛ ፈተናው የሚያስታውሱትን ሁሉ በመጻፍ በትምህርቱ የማለፊያን ነጥብ ያገኛሉ። ከዚያም ትምህርቱን እንደ ጨረሱ የሚመሰክር የትምህርት ማስረጃ ወረቀት ይቀበላሉ።

በዚህ መንገድ የትምህርት መረጃ ያገኘ ሰው ተምሯል ማለት ይቻላልን? በክፍሎቻችን ውስጥ እንዲኖር የምንፈልገው ትምህርት እንደዚህ ዓይነት አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ትምህርት ሰዎችን ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ምላሽ የማይሰጡ ሙታን ያደርጋቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታዎች በሚገባ ያውቃሉ። ሆኖም በዕለታዊ ኑሮአቸው ሲተገብሩ ፈጽሞ አይታዩም። ሕይወታቸው ደረቅና ፍሬ የሌለው ነው። ስለ እውቀታቸው የሚኮሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ጥበብ ወይም በተግባር የተተረጎመ እውቀት የላቸውም።

ትምህርት እውነታን ማግኘትን ይጨምራል፤ በመጀመሪያ መምህሩ ከዚያም ደግሞ በመምህሩ መሪነት ተማሪው እውነትን ያገኛል። መምህሩ የማስተዋልን እና የመማርን በሮች በመክፈት ተማሪውን ለሚማረው ትምህርት ያመቻቸዋል። ወደ ርእሰ–ጉዳዩ በተለያዩ አቅጣጫዎች በመምጣት መረዳትን ለመፍጠር ድግግሞሽ ያደርጋል። ከዚያም በኋላ አስተማሪው በተማሪዎቹ ፍላጎት ላይ ያተኩራል። ተማሪዎቹ ትምህርቱ እንዴት በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ችግር ሊፈታው እንደሚችል እንዲያዩ ለማድረግ ይጥራል። እርሱ ሊያሳምናቸው ይገባል። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ መረዳትን እንዲያመጣ መጸለይ አለበት። በመጨረሻም ተማሪዎችን የሚያሳትፉና እንዲያዛምዱ የሚረዱ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

ተማሪው በትምህርቱ የሚያገኘው እውቀት ከሕይወቱ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ማየት አለበት። ለሕይወት ችግሮች መፍትሔ ከማግኘት የሚበልጥ ደስታ የለም። መምህሩ ተማሪዎችን በሚመራበት ጊዜ ተማሪዎች ይህንን በማወቅ የሚገኘውን ደስታ እንዲለማመዱ መጣር አለበት። ለሕይወት ጥያቄዎች የሚያረካ መልስ በማግኘት ውስጥ አስደናቂ ደስታ አለ።

8) አስተማሪው የተማሪዎችን ስሜታዊ ምላሽ ማነሣሣት አለበት።

አስተማሪው ለሕይወት ጥያቄ ተማሪው መፍትሔ እንዲያገኝ ካደረገ በኋላ መፍትሔው በሕይወቱ እንደሚሠራ እንዲያምን ማድረግ ይኖርበታል። ሮሜ 10፡10 እንዲህ ይላል፥ «ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል በአፉም መስክሮ ይድናል»። አንድ ጊዜ ልባችን አንድ ነገር እውነት እንደ ሆነ ካመነ፥ ከዚያ ስሜታችን ፈቃዳችንን በማነሣሣት እንዲለወጥና አዲስ ከተማርነው እውነት ጋር እንድንስማማ ያደርገናል። በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ጌታ ተስፋ

ወደገባላቸው ዕረፍት ስላልገቡት የእስራኤል ልጆች እናነባለን። እንዲህ ይላል፤ «... ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም» (4:2)።

«ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ጊዜ ተጠቅሶአል (ዕብ. 2:4፤ ሮሜ 1:17፤ ገላ. 3:11፤ እና ዕብ. 10:38)። ይህም የሚያመለክተው እውነታ የምንኖረው ኑሮ ለምናምነው እምነት ተገዢ እንደሆነ ነው። ስለዚህም ተማሪው እውነትን እንዲያገኝ ብቻ ሳይሆን እንዲያምን እና በሕይወቱ ውስጥ እንዲሠራ ማነሣሣት ያስፈልጋል።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፡- ያዕቆብ 2:14-26 አንብብ። ያዕቆብ እምነታችን በሥራችን ተገልጦ መታየት እንዳለበት ተናግሯል። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ እምነት በምንሠራው ሥራ መገለጥ እንዳለበት ያዕቆብ በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚሰጣቸውን ሦስት መግለጫዎች ጻፉ። |

9. አስተማሪው በትምህርት በተገኘ እውቀት በፈቃዳቸው ምላሽ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት።

አንድን ነገር በእውነት በምናምንበት ጊዜ የእምነት ሥራችን የፈቃዳችንን ምላሽ ያስነሣዋል። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዘመናዊ ትምህርት፥ ስሜትን የሚቀሰቅሱና የሚያነሣሡ ብዙ ነገሮች አሉ። ሆኖም በሕይወታችን ውስጥ መለወጥ ያለበት ነገር እንዲለወጥ ካላደረጉ ስሜት ብቻውን ምንም ጥቅም የለውም። አስተማሪው ይህንን አደጋ በመገንዘብ ስለ ስሜት ሁኔታዎች መጸለይና መሥራት አለበት። ፈቃዳቸው እንዲነግሥ መፈለግ አለበት። ትክክለኛውን ምላሽ የሚያገኘው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ወስዶ በሰሚዎች ልብ ላይ ሲሠራው ብቻ ነው።

ያዕቆብ በመልእክቱ እንደገለጠው በዘመኑ በነበረው ቤተ ክርስቲያን በሚሆነው ነገር አዝኖ ነበረ። ሰዎች እናምናለን እያሉ ሲናገሩ ቢሰማም ምላሽ ሲሰጡ ወይም ያመኑትን በተግባር ሲተረጉሙ አላየም ። ስለዚህ «እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው» (ያዕ. 2:26) ብሏል። እንዲያውም በመቀጠል እንዲህ ብሏል «በጎ ማድረግን አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው»።

እንደ አስተማሪዎች ተማሪዎቻችንን አንድ ነገር እውነት እንደሆነ ካሳመንናቸው በኋላ ያንን ወደ ተግባር እንዲለውጡ እና እምነታቸውን በሥራ እንዲያዩት ካላደረግን በደለኞች ነን።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፡- ያዕ. 3:13-18 አንብብ። ቁ 13ን በቃል አጥኑ። ከቁ. 14-16 በአንዳንድ አማኞች ሕይወት ውስጥ ይፋ የነበረው አሉታዊ ፈተና ምን ነበረ? እነዚህ ነገሮች በእኛ ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ሊሆኑ ይችላሉን? እነዚህን ለማረም ምን ማድረግ አለብን? |

10) አስተማሪው ተማሪዎች ትምህርቱን በየዕለታዊ ኑሮአቸው እንዲተገብሩት ሊረዳቸው ይገባል።

የተሳካ ትምህርት እውነተኛ መፈተኛ የሕይወት ለውጥ መታየቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በምናስተምርበት ጊዜ ዓላማችን ሊሆን የሚገባውም ይህ ነው። መምህሩ ተማሪው የተማረውን እውነት በተግባር የሚተረጉምበትን

ሁኔታ ማመቻቸት አለበት። ለልጆች ስለ እርስ በርስ ደግነት የምናስተምር ከሆነ፥ በሚቀጥለው ሳምንት ደግነታቸውን የሚያሳዩበትን መንገድ መፈለግ አለብን። ከዚያም በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እግዚአብሔር ለሌላ ሰው ደግነት እንዲያደርጉ እንዴት እንደረዳቸው እንሰማለን። እናም በአንድ ላይ ሆነን እግዚአብሔርን ይህን ለማድረግ ስላስቻላቸው እናመሰግነዋለን።

ዮሐንስ 15፡15 «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» የሚለውን እውነታ ያስታውሰናል። ይህ ቃል ለአስተማሪውም ሆነ ለተማሪው እውነት ነው። በሰሚዎቹ ልብ ውስጥ እንዲሠራ ሙሉ ለሙሉ በጌታ ላይ እንደገፋለን። በ3ኛው ቀን ትምህርት በመጀመሪያ ነጥብ ላይ እንደተገለጸው በተማሪዎቻችን ልብ ውስጥ እንዲሠራ በመንፈስ ቅዱስ እንደገፋለን። ሆኖም ይህ ከኃላፊነቶቻችን ማለትም በሚገባ ከመዘጋጀት፥ በሚገባ ከማስተማር፥ እንዲሁም በተግባር ከመተርጎምና ብዙ ከመጸለይ የሚያዘናጋን አይደለም።

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ከዓለም ሁሉ ታላቅ ሥራ ተሰጥቶታል። ይህም ወንዶችና ሴቶችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው። ይህንን ዕድልና ኃላፊነት እንደ ዋዛ ልናየው አይገባም። «የሚጠራችሁ የታመነ ነው እርሱ ደግሞ ያደርገዋል» (1ኛ ተሰ. 5፡24)።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፡- የዚህን ትምህርት አራት ነጥቦች ከልሱ። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉአቸው። በመሠረቱ እነዚህ አራት ነጥቦች በዋናነት የሚያመለክቱት ማንን ነው? ተማሪው በትምህርት ወቅት መሥራት ያለበት ምንድን ነው? አስተማሪው ተማሪው ለሚማረው ነገር ኃላፊ የሚሆነው በምን መንገድ ነው? ኃላፊ የማይሆነውስ በየትኛው መንገድ ነው? |

**አምስተኛ ቀን፡- በትምህርት ሦስት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ ከልስ።**

ለሳምንታዊ ስብሰባ የተዘረዘሩትን የመወያያ ነጥቦች ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለሳምንታዊ ስብሰባ የሚሆነውን የተለመደ አሠራር ተከተል። በሚከተሉት አሳቦች ላይ ተወያዩ።

1. የጥሩ ስብከት አዘጋጃጀትን ዘጠኝ ደረጃዎች በመዘርዘር በቡድናችሁ ውስጥ በክለሳ መልክ ተመልከቷቸው። የእያንዳንዱን ደረጃ አስፈላጊነት ተወያዩበት። በዚያ ቅደም ተከተል የተቀመጡት ለምንድን ነው? የተሰጡበትን ቅደም ተከተል መከተል ያለባችሁ ለምንድን ነው?

2. ማስተማር ከመስበክ የሚለይበትን ሦስት መንገዶች ተነጋገሩ። በሁለተኛ ቀን ትምህርት የተሰጠውን የማስተማርን ትርጉም ተነጋገሩበት።

3. ለተሳካ ማስተማር የተሰጡትን አሥር ነጥቦች ተመልከቷቸው። አዲስ የሆኑ አሳቦችን ተነጋገሩባቸው። በዓለማዊ ትምህርት ሕይወታችሁ ከተለማመዳችሁት እነዚህ ነጥቦች በምን መንገድ ይለያሉ? ክርስቲያናዊ ማስተማር ለምን የተለየ እንዲሆን አስፈለገ?

# ትምህርት አራት

## መምህሩ

### 1ኛ ቀን፡— የመምህሩ የብቃት መመዘኛ — ክፍል 1

ለማንኛውም ተግባር የብቃት መመዘኛ አለ። ለአንድ ክፍት የሥራ ቦታ ስታመለክት ዲፕሎማዎችህን ወይም ሠርተፊኬቶችህንና ያለህን ማንኛውንም የሥራ ልምድ እንድታቀርብ ይጠበቅብሃል። ታዲያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያስተምር ሰው የብቃት መመዘኛዎች ምንድን ናቸው?

1. መምህሩ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን መሆን አለበት።

የመምህሩ የመጀመሪያ የብቃት መመዘኛ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ የመቀበሉ ጉዳይ ነው። 1ኛ ዮሐ. 5፡12 እንዲህ ይላል፡— «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ግን ሕይወት የለውም»። ጌታ ኢየሱስ ራሱ በቀጥታ «ዳግም ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል» (ዮሐ. 3፡7) ብሏል። እጅን አንሥቶ ሌላው ሰው ያለውን «ከአሁን ጀምሮ ሰይጣንን ክጂያለሁ! ኢየሱስ ክርስቶስን አምኛለሁ»› ብሎ ሲናገር መድገም ብቻ አይበቃም። ማንኛውም ሰው ያንን ሊል ይችላል።

ሀ. ኃጢአተኛ ነህ

ተስፋ—ቢስ ሆነህ የጠፋህ ኃጢአተኛ መሆንህን መገንዘብ አለብህ። ኃጢአትህ ከእግዚአብሔር ለይቶሃል። እግዚአብሔር ባለማቋረጥ በፈጸምኸው ኃጢአት አዝኖ ፊቱን ከአንተ መልሷል። አሁን በአለህበት መንገድ ከቀጠልህ ለዘላለም በገሃነም መቀጣት ይጠብቅሃል። «በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ትኖራላችሁ» ከተባለላቸው ሰዎች አንዱ ነህ። ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር መንፈስ በእውነት ከተወለዱት ለዘላለም ተለይተህ ትኖራለህ። ለዘላለም መጥፋት እጅግ ከባድ ነገር ነው።

ኃጢአት ምንድን ነው? ኃጢአት እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ እንዳይኖረን ተናግሮናል (ዘጸ. 20፡3)። ከእግዚአብሔር አስበልጠህ የምትወደው ሌላ ነገር አለህን? እርሱ ሌላ አምላክ ነው።

የምታመልኩት ጣዖት አላችሁን? (ዘጸ. 20፡4—6)። በቤታችሁ የምታመልኩት የተቀረጸ ምስል ወይም ሥዕል አለን? ለተራሮች ወይም ለምንጮች ወይም ለትላልቅ ዛፎች መሥዋዕት ታቀርባላችሁን? ቅዱሳትን ወይም ግዑዝ አካላትን ለማምለክ የተቀደሱ የሚባል ጉዞዎችን ታደርጋላችሁን? እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ እንደ ሆነና ጣኦትን የምታመልኩ ከሆነ እናንተንና ልጆቻችሁን እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ እንደሚቀጣ ተናግሮአል።

የእግዚአብሔርን ስም ያለ አግባብ ትጠራላችሁን? በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ስም ወይም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም አክብሮት በጎደለው መልክ የሚጠሩ ብዙዎች ናቸው። መሃላ ለመፈጸም ወይም ቃልኪዳን

ለመግባት ይጠቀሙበታል። የእግዚአብሔር ስም የተቀደሰ ስለሆነ ስሙን ያለአግባብ መጠቀም ጥፋተኞች ያደርገናል (ዘጸ. 20፡7)።

እግዚአብሔር አባትና እናታችንን እንድናከብር አዝዞናል። ወላጆቻችሁን ታከብራላችሁን? ለሥልጣናቸውስ ትገዛላችሁን? ትታዘዟቸዋላችሁን? ዘጸ. 20፡12 የሚያሳስበን ካከበርናቸው በምድር ላይ ዕድሜያችን እንደሚረዝም ነው።

እግዚአብሔር አትግደል የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናል (ዘጸ. 20፡13)፥ አዲስ ኪዳን በወንድማችን ላይ መቆጣት የመግደልን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ በተጨማሪ አመልክቷል (ማቴዎስ 5፡21)። ቁጣና ጥላቻ ወደ መግደል ያመራል።

የሚቀጥለው ትእዛዝ አታመንዝር የሚል ነው። ለባሎቻችሁ ወይም ለሚስቶቻችሁ ታማኝ አይደላችሁምን? ያላገባችሁ ከሆነ ደግሞ ዝሙት እየፈጸማችሁ ነውን? እግዚአብሔር መፈጸም የለባችሁም ይላል።

8ኛው ትእዛዝ አትስረቅ የሚል ነው። የሌሎችን ንብረት ወስደሃልን? ይኼ ስርቆት ነው። እግዚአብሔር ያንን እንዳንፈጽም ከልክሏል። እንደዚያ ካደረግህ ሌባ ነህ። መጽሐፍ ቅዱስ የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ። ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጁ መልካምን እየሠራ ይድከም ይላል (ኤፌሶን 4፡28)።

ቀጥሎ በጎረቤቶቻችን ላይ በሐሰት እንዳንመሰክር እግዚአብሔር ተናግሮናል። አንደበታችን ንጹሕ እንዲሆንና እውነቱን ብቻ እንድንናገር ይጠብቅብናል (ዘጸ. 20፡16)። አንተንም ሆነ ምስክርነትህን የሚጎዳ ቢሆንም እንኳ ሁልጊዜ እውነትን ብቻ ለመናገር ትወስናለህን? «ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው» (ምሳሌ 12፡22)።

በመጨረሻ እግዚአብሔር አትመኝ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል። የባልንጀራህን ሚስት ወይም አገልጋዩን ወይም እንስሳውን ወይም ለእርሱ የሆነ ማንኛውንም ነገር መመኘት የለብህም (ዘጸ. 20፡17)።

እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ ትእዛዛት የሰጠው ኃጢአት በፊቱ ምን እንደሆነ ያሳየን ዘንድ ነው። ሮሜ 3፡23 «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» ይላል። ኃጢአተኛ ስለሆንህ አዳኝ ያስፈልግሃል። መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 53፡6 ላይ እንደዚህ ይላል፡- «እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) ላይ አኖረ»።

ለ. እግዚአብሔር እጅግ ስለሚወድህ ለኃጢአትህ ይሞትልህ ዘንድ ልጁን ላከልህ።

እግዚአብሔር እጅግ ይወድሃልና አንድያ ልጁን ለኃጢአትህ ይሞት ዘንድ ላከው። ሮሜ 5፡8 እንዲህ ይላል፡- «ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን

ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል»።

«የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል» (1ኛ ዮሐ. 1:7)። ጻግም ልደትን እናገኝ ዘንድ ትሕትና ተሞልተን ኃጢአታችንን በመናዘዝ ለኃጢአታችን መሥዋዕት በሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን አለብን። እርሱ ኃጢአትን አያውቅምና ለእኛ ኃጢአት ሊሞትልን የሚችል እርሱ ብቻ ነበር። «በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም» (ዮሐ. 3:36)። «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው» (ሮሜ 6:23)።

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት እንደ አዳኝህ ተቀበል።

ዳግመኛ መወለድህን የምትጠራጠር ከሆነ ኃጢአትህን ተናዘዝ፤ እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህ ጠይቅ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርገህ እመን፤ ከዚያም አዲስ ፍጥረት ትሆናለህ። ቲቶ 3:4–7ን አንብብ። የተወሰነ ክፍሉ እንዲህ ይላል «እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን...»። በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዲኖረን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፤ ሁሉም አዲስ ሆኖአል (2ኛ ቆሮ. 5:17)።

መ. ከሁሉ የተሻለ ጊዜ አሁን ነው

አሁኑኑ አድርገው። ሰይጣን እንዲህ ይልሃል፤ «ሌላ ጊዜ እስኪመጣ ጠብቅ»። መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ «እነሆ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው» (2ኛ ቆሮ. 6:2) እና «እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን?» (ዕብ. 2:3) ይላል።

ኢሳይያስ ለአንተ መልካም ቃል አለው። «እግዚአብሔርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው። ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፥ እርሱም ይምረዋል ይቅርታውም ብዙ ነውና»።

ከኃጢአትህ ለመመለስ፥ ኃጢአትህን ለጌታ መናዘዝና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ ለመቀበል ቆራጥ ውሳኔ ማድረግ በሕይወትህ ከምታደርጋቸው ውሳኔዎች ሁሉ የላቀ ነው፤ ይህን ካደረግህ በኋላ ለአንድ ክርስቲያን ስለ ጉዳዩ ንገረው። ይህንን ማድረግህ ለተቀበልኸው አዲስ ሕይወት ጥንካሬና ብርታት ይሆንልሃል።

ሠ. እግዚአብሔር ልጁ እንደሆንህ ራሱ ያረጋግጥልሃል።

ዮሐንስ 1:12 የእርሱ ልጅ መሆንህን ያረጋግጥልሃል። «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው»። ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ነው የተወለድከው እናም የእርሱ ልጅ ነህ።

ይህንን እውነት በሌላ መንገድ እንግለጠው ብንል በእግዚአብሔር መንጋ ውስጥ ያለህ በግ ነህ ማለት እንችላለን።

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም። ከእጄም ማንም አይወስዳቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉም ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ምንም አይችልም እኔ እና አብ አንድ ነን»።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ዛሬ ካመንህ መጽሐፍ ቅዱስ በየዕለቱ እንድታነብና እንድትጸልይ አበረታታሃለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ የእግዚአብሔር ቃል ነው እና ለመንፈሳዊ ዕድገትህ ማንበብ ያስፈልግሃል። በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቤተሰብ እስከሆንህ ድረስ ወደ እርሱ በመምጣት በጸሎት ማመስገን እና ጥያቄህን ማቅረብ ትችላለህ። ዳግመኛ የተወለደ አማኝ ፈልገህ ከእርሱ ጋር መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ፤ ጸልይ። |

## ሁለተኛ ቀን፡- የአስተማሪነት የብቃት መመዘኛዎች - ክፍል 2

2) የእግዚአብሔርን ቃል የሚማር መሆን አለበት።

ተማሪ ማለት የሚያጠና ሰው ማለት ነው። ሌላው የአስተማሪነት መመዘኛ የሚያስተምረውን በሚገባ የሚያውቅ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ይህ ሊመጣ የሚችለው የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ብቻ ነው። ሌሎችን ለማስተማር የምንበቃ እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳችን እንዴት ማጥናት አለብን?

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች አሉ። እነርሱም መመልከት፤ መተርጎም እና ከሕይወት ጋር ማዛመድ ናቸው።

- መመልከት = ምን እያየሁ ነው?
- መተርጎም = ይህ ምን ማለት ነው?
- ከሕይወት ጋር ማዛመድ =ከእኔ ሕይወት ጋር እንዴት ይሄዳል?

ከእኛ የሚጠበቀው «ገብቶኛል» ማለት ብቻ ሳይሆን «ስለዚህም አደርገዋለሁ» ጭምር ነው።

ይህ ዓይነቱ ጥናት ከዝርዝር ጉዳዮች ወደ አጠቃላይ ድምዳሜ የሚደረስበት (inductive) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይባላል። እያንዳንዱ ደረጃ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ከላይ እንደተገለጸው ቅደም ተከተል መሆን አለበት። አንዱ ከሌላው ጋር ግንኙነት አለው።

ሀ. መመልከት

1. ዋናውን አሳብ መለየትና የክፍሉን አጠቃላይ አሳብ መመልከት

የጸሐፊውን ዋና አሳብ ለማግኘት መጽሐፉን በሙሉ ማንበብ አስፈላጊ ነው። ለመጀመር አጭር መጽሐፍ መምረጥ መልካም ይሆናል። መጽሐፉን በአንድ ጊዜ በሙሉ አንብብ። የጸሐፊው ዋና አሳብ ምን እንደሆነ ራስህን ጠይቅ። አንዳንድ ስሕተቶችን እያረመ ነውን? የተወሰኑ ትምህርቶችን እየሰጠ ነውን? ታሪኮችን እየዘገበ ነውን? የመጽሐፉን ዋና አሳብ ለማግኘት

በምታጠናበት ጊዜ የእያንዳንዱን ክፍል ዓውደ-ንባብ ለመረዳት ያግዝሃል። ዓውደ-ንባብ የምንለው የመጽሐፉ አካል የሆነውን የተወሰነ አንቀጽ ነው። የአንድን ክፍል አሳብ ለመረዳት ከፊቱ እና ከኋላው ያለውን ነገር ማንበብ አለብህ።

---

2ኛ ጥያቄ፦ የቲቶን መጽሐፍ አንብብ። የዚህ ትንሽ መጽሐፍ ዋና ጭብጥ ምንድን ነው? የጸሐፊው ዋና አሳብ ምንድን ነው? በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፈው።

---

2. ግልጽ ሆነው የተጠቀሱትን ሰዎች፥ ቦታዎች እና ድርጊቶችን ተመልከት። እነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች የሚደጋገሙና በቀላሉ የምንለያቸው ናቸው።

---

3ኛ ጥያቄ፦ ይህንን አጭር ደብዳቤ የጻፈው ማን ነው? የተጻፈው ለማን ነበር? የደብዳቤው ተቀባይ የሚኖረው የት ነበር? የእርሱ ዋና ተግባር ምን ነበር?

---

3. ክፍሉ ስለ ራሱ ይናገር

ብዙ ጊዜ የምናነበው ለራሳችን አንድ ነገር ለማግኘት ነው። ይሁንና የጥናታችን የመጀመሪያ ደረጃ በሆነው በዚህ ጊዜ ቃሉ ራሱ ምን እንደሚል ማጻመጥ አለብን። እግዚአብሔር በእውነት እንድናውቀው ይፈልጋል። በትክክል ቃሉ የሚናገረውን ነገር እንቀበል።

በዚህ ጊዜ ለመተርጎምም ሆነ ከሕይወትህ ጋር ለማዛመድ አትሞክር። በእርግጥ ምን እንደሚል ለማወቅ ዝም ብለህ በጥንቃቄ አንብበው። ቃሎቹ ሊሉት የሚፈልጉት ነገር በዚያ የተጻፈውንና የሚሉትን እንደሆነ እውነታውን ተቀበል።

---

4ኛ ጥያቄ፦ ጸሐፊው በዚህ ደብዳቤ ከሚያነሣቸው ጉዳዮች ቢያንስ አምስቱን ዘርዝር።

---

4. እነዚህን ጥያቄዎች ለራስህ ጠይቅ

ሀ. የጻፈው ማን ነበር? የተናገረውስ ማን ነበር? ዋናዎቹ ተዋንያን እነ ማን ናቸው? ጸሐፊው የጻፈው ለማን ነበር?

ለ. ዋናዎቹ ድርጊቶች ምን ምን ናቸው? ዋናዎቹ አሳቦች ምን ምን ናቸው? ዋናው ትምህርት ምንድን ነው? ይህን በማለቱ የጸሐፊው ዓላማ ምንድን ነው?

ሐ. የተጻፈው መቼ ነበር? ይህ የተደረገው መቼ ነበር? የሚፈጸመውስ መቼ ነው? የተነገረው መቼ ነበር? የሚያደርገው መቼ ነው?

መ. የተፈጸመው የት ነበር? የተነገረው የት ነበር? የት ይፈጸማል?

ሠ. እንዲጻፍ ያስፈለገበት ጉዳይ ምን ነበር? ይህ የተጠቀሰው ለምን ነበር? ለዚህ ድርጊት ወይም ትምህርት ብዙ ወይም ትንሽ ስፍራ የተሰጠው ለምን ነበር?

ረ. የተደረገው እንዴት ነው? እንዴት ተከሰተ? ይህ እውነት የተገለጸው እንዴት ነበር?

ስድስት ዓይነት ጥያቄዎች እንዳሉ ተመልክተናል። እነዚህም ማን፥ ምን፥ መቼ፥ የት እና ለምን በተጨማሪም እንዴት የሚሉ ናቸው። እነዚህን ቀላል መጠይቅ በማቅረብ ብቻ እንደምትማር ስትመለከት ትደነቃለህ። ከምታጠናው ምንባብ እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መመለስ የማትችልባቸው ጊዜያት አሉ። በዚህ ሳትጨነቅ። ከክፍሉ ጋር በሚስማማ መንገድ የቻልከውን ያህል መልስ።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፡- ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መጠይቆች በመጠቀም ከቲቶ መጽሐፍ የምትችለውን ያህል መልስ ስጥ። |

5. የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን ለይ።

ከዚያም ራስህን ምን ዓይነት ጽሑፍ ነው ብለህ መጠየቅ አለብህ። ታሪክ ነውን? የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ ነውን? ግጥም ነውን? የምሳሌዎች ጥርቅም ነውን? ትንቢት ነውን? የሃይማኖት አስተምህሮዎችን የያዘ የመልእክት ትምህርት ነውን? ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የጽሑፍ ዓይነቶች ቅልቅል ነውን? ብዙ ዓይነት የአጻጻፍ ዘዴዎች ስላሉ ይህንን ነገር ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡- የቲቶ መጽሐፍ በየትኛው የአጻጻፍ ዘዴ እንደተጻፈ ለይ። |

6. ቁልፍ ቃላትና ሐረጎችን ተመልከት።

ብዙ ጊዜ ቁልፍ ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ ይደጋገማሉ። እነዚህ ቁልፍ ቃላት በክፍሉ ውስጥ የሚተኮርበት ነገር የቱ እንደ ሆነ እንድታውቅ ይረዱሃል? 1ኛ ዮሐንስ 4:7-12 ያለውን ተመልከት። ግልጽ የሆነው ቁልፍ ቃል የቱ ነው? ሉቃስ 9:57-62 ተመልከት። 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:17-19 ያለውን ደግመህ ተመልከት። በሁሉም ቦታ ያሉትን ቁልፍ ቃላት ጻፋቸው።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡- በቲቶ መጽሐፍ የተደገመ ቃል ወይም ሐረግ አግኝተሃልን? በማስታወሻ ደብተርህ ጻፋቸው። የመጽሐፉ ዋና አትኩሮት ምን እንደሆነ የምታውቅበት የተሻለ አሳብን ይሰጥሃል? በራስህ አባባል ጻፈው። (ፍንጭ ልስጥህ። 1:16፥ 2:7፥ 14፥ 3:1፥ 8፥ 14 ተመልከት።) ያለማቋረጥ እየተደጋገመ ያለን አሳብ አግኝተሃል? የመጽሐፉ ማዕከላዊ ነገር ይህ ነው ብለህ ታስባለህን? ለማስተማር ወይም ለመስበክ ይህ ነገር ይረዳኛል ብለህ ታስባለህን? ይህንን ቃል በተጠቀመ ጊዜ ሐዋርያው ለማን ነበር የሚናገረው? በሚገባ አስብበት። ከዚህ መጽሐፍ ሦስት ወይም አራት መልእክቶች ብታዘጋጅ ይህ ይረዳሃልን? |

አሁን ስለተዘጋጀን መጽሐፉን በአንቀጽ እና በምዕራፍ መከፋፈል እንችላለን። ከዚህ ቀደም ለመጽሐፉ በሙሉ እንዳደረግኸው እንዲሁ አድርግ። እያንዳንዱን ክፍል መርምር፤ የትኛው መጀመሪያ የትኛው ቀጥሎ እንደሚመጣ ልብ በል። ማጣቀሻዎችን በመጠቀም ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋርም አነጻጽር። ቅዱሳት መጻሕፍት እርስ በርሳቸው አይቃረኑም። አንዳንዶቹ ጥያቄዎች ቀደም ብለው ተመልሰዋል። ምዕራፎቹን ስትመረምር በመመልከት ጊዜ የተማርኸውን አስታውስ።

7. ትእዛዛትን፥ የምክንያትና ውጤት ዐረፍተ ነገሮችን፥ ንጽጽሮችን እና የማያያዥ ቃላትን ተመልከት። ጊዜያት የተገለጹበትን መንገድ ተመልከት። ትእዛዛት የተጻፉት እንድንታዘዛቸው ነው። ምክንያትና ውጤት የያዙ ዐረፍተ

ነገሮች «ይህንን ካደረግህ ይህ ይሆንልሃል።» ማነጻጸሪያዎች ብዙ ጊዜ የሚለዩት «እንደ» ወይም «የመሳሰሉት» በሚሉ ቃላት ሲሆን፥ ማነጻጸሪያዎች ደግሞ «ግን» ወይም «ይሁንና» በሚሉ ቃላት ነው። የማያያዣ ቃላት የምንላቸው «ስለዚህ»፥ «ነገር ግን»፥ «ስለሆነም»፥ «በምትኩ» እናም የመሳሰሉት ናቸው።

ለ. አተረጓጎም

ሙሉውን የቲቶ መጽሐፍ ከአንድ ጊዜ በላይ አንብበህ ዋናውንም አሳብ ጽፈሃል። እያንዳንዱን ምዕራፍ ስላጠናህ ከዋና አሳቡ ጋር እንዴት እንደሚሄድ አውቀሃል። የእያንዳንዱን ክፍል ይዘት አውቀሃል። ስለዚህ መጽሐፉ የሚለውን መሠረታዊ ነገር ታውቃለህ ማለት ነው። አሁን መጽሐፉን ለመተርጎም ዝግጁ ነህ።

መተርጎም ማለት ፍችውን መፈለግ ነው። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገረው «የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነው ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ» (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15) ብሎአል። የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳትና በትክክል ለመያዝ ተግቶ ማጥናትን ይጠይቃል።

1. ትርጉም ከይዘቱ ጋር ተያያዥነት ሊኖረው ይገባል።

ትርጉም በዙሪያው ካሉ ጥቅሶች፥ ጥቅሱ ከተገኘበት መጽሐፍና ከአጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ሁልጊዜ ይስማማል። እግዚአብሔር ከእራሱ ጋር አይቃረንም። በአንድ ቦታ አንድ ነገር በሌላ ቦታ ደግሞ ከዚያ ጋር የማይስማማ ሌላ ነገር አይናገርም።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው በላይ መናገር የለብንም። አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢኖርበት ጥሩ ነው ብለን እንመኛለን፤ ለመጨመርም ደግሞ እንፈተናለን። እዚህ ላይ በጣም ጥንቁቅ መሆን አለብን። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ሰጥቶናል። ቃሎቹን እንዳሉ መቀበልና በትክክልም ትርጉማቸውን መስጠት አለብን። «የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡3)። አንድን ነጥብ ለማስረዳት ወይም ለማረጋገጥ አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶችን ከየስፍራው እየወሰዱ መጠቀም ብዙ ነገር አበላሽቷል። ማስተማር ሁልጊዜ ከዓውደ–ንባቡ አኳያ ሊሆን ይገባል።

ለምሳሌ ዮሐንስ 15፡7 እንመልከት። ኢየሱስ «የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል» ብሏል። ይህ ማለቱ ማንኛውንም ነገር ስለመጠየቅ ነውን? መልሱ «አይደለም» ነው። 1ኛ ዮሐንስ 5፡14 ሲነግረን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መጠየቅ እንዳለብን ያስታውቀናል። ያዕቆብ 4፡3 ደግሞ ትክክለኛ በሆነ ውስጣዊ ፍላጎት ልንጠይቅ እንደሚገባን ያዝዘናል። ዮሐንስ 16፡24 ደግሞ በኢየሱስ ስም እንድንጸልይ ያስታውሰናል። ዕብራውያን 11፡6 ሲናገር ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም ይላል። ስለዚህ በትክክል እንዴት መጸለይ እንዳለብን ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት የሚያስተምራቸውን ትምህርቶች ሁሉ ማገናዘብ አለብን።

2. መጽሐፍ ቅዱስን ከሁሉ በተሻለ አኳኋን የሚተረጉመው እራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ብዙ ጊዜ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቦታ የተባለው ነገር ቀጥለው በሚገኙት ቁጥሮች ወይም በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይብራራል።

ጌታ ኢየሱስ የተናገራቸውን ብዙዎቹን ምሳሌዎች ያብራራላቸው ደቀ መዛሙርት ስላልገባቸው ነበር። ምሳሌ የሥነ ምግባር ትምህርትን ወይም እውነትን የሚያስተምር ታሪክ ነው። ሁልጊዜ እውነተኛ ታሪክ ላይሆን ቢችልም እንኳ ለሕይወት እውነት ነው። ምሳሌን ለመተርጎም ኢየሱስ ያስተማረበትን ማዕከላዊ እውነት ማግኘት አለብን። እናም ከዚያ እውነት በመነሣት መተርጎም አለብን። በእርግጥ የምሳሌው ሁሉም ክፍል መተርጎም አያስፈልገውም። አንዳንድ ሰዎች ወደ ስሕተት የሚያመሩት እያንዳንዱን የምሳሌ ክፍል ለመተርጎም በመሞከራቸው ነው። ደግሞም ምሳሌዎችን መተርጎም ያለብን አሁን ካለንበት ጊዜ ባሕል አንጻር ሳይሆን በኢየሱስ ዘመን በነበረው ባሕል ነው።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፤ – ሉቃስ 10፡25–37 አንብብ። ሕግ አዋቂው ኢየሱስን ምን ጠየቀው? ኢየሱስም በምላሹ ጠይቆታል። ጥያቄው ምን ነበር? የሰጠው መልስ ትክክል ነበርን? ሕግ አዋቂው እራሱን ያጸድቅ ዘንድ የሰጠው መልስ ምን ነበር? የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር? የዚህ ምሳሌ ማዕከላዊ አሳብ ምንድን ነው? ኢየሱስ ሰውየውን ሊያስተምረው የሞከረው ምን ነበር? |

3. ትንቢት–በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአስደሳችነታቸው እጅግ የሚስቡ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አንዱ የትንቢት መጻሕፍትን ማጥናት ነው። ይህም አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች እንደተፈጸሙ የምናይ ስለሆነ ነው። ትንቢት የተጻፈው ለቅዱሳን ነው። ማለት ቅዱሳን ሁሉ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ በማሰብ በከፍተኛ መሰጠትና ብርታት አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ይነሣሡ ዘንድ ነው። ለትንቢቶች ምሳሌነት የሚሆን ጥናት ለማድረግ የሚከተሉትን ክፍሎች ተመልከት።

| | |
|---|---|
| ማቴ. 24፤ ማር. 13 | የደብረ ዘይቱ ንግግር |
| ሉቃስ 21 | ስለ መጨረሻዎቹ ነገሮች |
| | መሠረታዊ ቅደም ተከተል። |
| 1ኛ ተሰ. 4፡13–18፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡51–58 | የአማኞች መነጠቅ |
| 1ኛ ቆሮ. 3፡9–17፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡10፤ | |
| ሮሜ 14፡10 | የአማኞች ፍርድ |
| ሕዝ. 37–39 | የእስራኤል የወደፊት ግጭቶች |
| 1ኛ ተሰ. 2፡1–12፤ ራእ. 6–18 | የታላቁ መከራ ጊዜ |
| ራእ. 19፡1–21፥ 12፡14–18፤ | |
| ሉቃ. 17፡22–37 | የክርስቶስ በክብር መገለጥ |
| ራእ. 20፡1–10፤ ኢሳ. 65፡17 | የሺህ ዓመት መንግሥት |

| | |
|---|---|
| ራእ. 20:11-15 | የጠፉ ነፍሳት የመጨረሻ ፍርድ |
| ራእ. 21-22 | አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር |

በአብዛኛው ጊዜ ትንቢትን ለማጥናት ከሁሉ የሚሻለው መንገድ ቃላቱ የሚሰጡትን ተራና ቀጥተኛ ትርጉም እንዳለ በመቀበል መቅረብ ነው። አንዳንድ ጊዜ ጸሐፊው በዘይቤያዊ ወይም በተምሳሌታዊ አነጋገር ይጠቀማል። እንደዚህ ዓይነቱ ትንቢት ሲገጥምህ የመጽሐፉን ዋና ጭብጥና የምንባቡን ይዘት ማሰብ ያስፈልጋል። ትርጓሜውን ለማግኘት ተመሳሳይ መልእክት የሚያስተላልፉትን ሌሎች ምንባቦች መመልከት ጥሩ ነው። አንዳንድ ትንቢቶችን አሁን ከሚደረገው ድርጊት ጋር እንዳታያይዝ በጣም ጠንቃቃ ሁን። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ትክክለኛውን ትርጉም ካልሰጠው በስተቀር ይህ ማለት ያ ነው ማለት ወደ ስሕተት ሊመራን ይችላል።

---

9ኛ ጥያቄ፡- የቲቶን መጽሐፍ ደግመህ አንብብ። አንድ ክፍል ውሰድና ስለዚያ ክፍል የአንተን ትርጓሜ ጻፈው።

---

## ሦስተኛ ቀን፡-የአስተማሪው የብቃት መመዘኛዎች-ከክፍል 2 የቀጠለ

### ሐ. ማዛመድ

---

10ኛ ጥያቄ፡- ያዕቆብ 1፡22-25 አንብብ። ቃሉን አውቀን ካልፈጸምነው ምን እያደረግን ነው? በቁጥር 23-24 ያዕቆብ የተጠቀመውን ማብራሪያ ግለጽ። የተባረከው ሰው ማን ነው? መዝ. (139)፡23-24 አንብብ። የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች ከማንበብህ በፊት ይኼንን ጸሎት ጸልይ። ከዚያ በኋላ በታማኝነት መልስ።

---

ትምህርቱን ከሕይወት ጋር ወደ ማዛመድ ስንመጣ ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባን ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ።

1. ይህ እውነት በአመለካከቴ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርገው እንዴት ነው? በአጠቃላይ ስለ እግዚአብሔር ስለ ሌሎች ሰዎች፥ ስለ አለሁበት ሁኔታ እና ስለ ሕይወት ባለኝ አመለካከት ላይ የሚያደርገው ተጽዕኖ ምንድን ነው? (ፊልጵስዩስ 4፡8-9)።

2. ይህ እውነት ባሕርዬን ሊለውጥ የሚገባው እንዴት ነው? መለወጥ ያለባቸው ባሕርዮቼ የትኞቹ ናቸው? ስለ ሌሎችና ከሌሎች ጋር በምናገርበት ጊዜ ልቀይራቸው የሚገቡ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? ይህ እውነት በአሁኑ ሰዓት ስለምሠራው ነገር የሚያረጋግጥልኝ ነገር አለን?

3. ከሌሎች ጋር ስለ አለኝ ግንኙነት ይህ እውነት የነካኝ እንዴት ነው? ሮሜ 12፡9-21፤ ኤፌ. 4፡25-32። ይቅርታ ላደርግለት የሚገባኝ ሰው አለን? ይቅር እንዲለኝ የምጠይቀው ሰው አለን? የማበረታታው ወይስ የምገሥጸው ሰው አለን? የበለጠ ራሴን ለሌላ ማስገዛት አለብኝ? (ኤፌሶን 5፡21)።

4. ይህ እውነት በሕይወቴ ውስጥ ያለኝን ውስጣዊ ዓላማ የሚነካው እንዴት ነው? ትክክለኛውን ነገር በተሳሳተ ውስጣዊ ዓላማ እያደረግሁ ነውን?

5. ይህ እውነት በሕይወቴ እንደ ቀም-ነገር የምቆጥራቸውን ነገሮች የሚነካው እንዴት ነው? አሁን ለእኔ አስፈላጊ ሆኖ የሚታየኝ ነገር ምንድን ነው? የሚያስፈልገኝ ነገር ምን ሊሆን ይገባል?

6. ይህ እውነት በሕይወቴ ቀዳሚ ካደረግኋቸው ነገሮች አንጻር የሚነካኝ እንዴት ነው? በሕይወቴ የመጀመሪያውን ስፍራ የሰጠሁት ለማንና ለምን ነው? ስፍራውን ልሰጠው የሚገባኝ ለማንና ለምን ነበር? (ኤፌሶን 5፡15፤ ዘጸ. 20፡ ዘዳ. 6፡4–9)።

7. ይህ እውነት ባሕርዬን እንዴት ሊነካ ይገባል? ራስ ወዳድ ነኝ ወይስ ክርስቶስን እመስላለሁ? ለሌሎች ሰዎች ይገደኛልን? ባይመቸኝም እንኳ ሌሎችን ለመርዳት ፈቃደኛ ነኝን? (ቆላስይስ 3፡12–14፥ 15–17)።

3) መምህሩ ጥሩ የጸሎት ሕይወት ሊኖረው ይገባል።

ጸሎት ለመምህሩ ተግባር በሙሉ አስፈላጊ የመሆኑ ጉዳይ ምንም ያህል ትኩረት ቢደረግበት አይበዛበትም። አንድ ሰው ካልጸለይን በስተቀር እግዚአብሔር ሊሠራ አይችልም ብሏል።

ሀ. ለማን መጸለይ ያስፈልጋል?

1. ለራስህ፥ ለሚስትህ፥ ለቤተሰብህ፥ ለዘመዶችህ ጸልይ።

2. ለተማሪዎችህ ጸልይ። አንዳንድ አስተማሪዎች የተማሪዎቻቸውን ስም የያዘ የስም መጥሪያ ደብተር የሚይዙበት ዋነኛው ምክንያት ሕፃናትም ሆኑ ወጣት ወይም ጎልማሳ ስማቸውን እየጠሩ ይጸልዩላቸው ዘንድ ነው።

3. ለቤተ ክርስቲያንህ ማለትም ለምእመኑ፥ ለሽማግሌዎችና መጋቢዎች ጸልይ። በቤተ ክርስቲያን ላሉ ፕሮግራሞች ሁሉ ጸልይ።

4. ከኅብረተሰብህ ላልዳኑት እና ለክርስቲያኖች ምስክርነት ጸልይ። በርካታ ያላመኑ ሰዎችን ስሞች መዝግበህ ጸልይላቸው።

5. በዓለም ዙሪያ ስለአለው የወንጌል ስርጭት ተግባር ጸልይ። «ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል» (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)። ከታናናሾች አንዱ እንኳን ይጠፋ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ አይደለም (ማቴዎስ 18፡14)።

ለ. ጸሎት ምንድን ነው?

1. ጸሎት ምስጋናና፥ አምልኮ ነው [መዝ. (34)፡1፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡18]።

2. ጸሎት ንስሐ መግባት ነው [1ኛ ዮሐንስ 1፡6–10፤ 2ኛ ዜና 7፡14፤ መዝ. (66)፡18፤ ምሳ. 28፡13]።

3. ጸሎት ልመና ነው [ማቴዎስ 7፡7፤ 9–11፥ 6፡25–32፤ ፊልጵስዩስ 4፡19፤ መዝ. (50)፡ 10–12]።

ሀ. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ (1ኛ ዮሐንስ 5፡14)።

ለ. በኢየሱስ ስም (ዮሐንስ 16፡23–24)።

ሐ. በእምነት (ዕብራውያን 11፡6፤ ያዕ. 1፡6–7)።

መ. በትክክለኛ ውስጣዊ ዓላማ (ያዕቆብ 4፡3)።

4. ጸሎት ምልጃ ነው (ኤፌሶን 6፡18–19)።

ፊልጵስዩስ 4፡5–7 «ጌታ ቅርብ ነው» ይላል። ስለዚህ ስለ ማንኛውም ነገር የምንጨነቅ መሆን የለብንም። ልመናዎቻችንን ሁሉ ከምስጋና ጋር ለጌታ እናቀርባለን። በመቀጠልም እንዲህ ይላል፡– «አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አእምሮአችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል»። ደግሞም እንደዚህ ይላል፡– «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» (1ኛ ጴጥሮስ 5፡7)።

11ኛ ጥያቄ፡– ጸሎት የአገልግሎታችን ዋነኛ ነገር ስለሆነ መዘንጋት የለበትም። የጸሎት ሕይወትህ እንዴት ነው? ዕለት ዕለት በጸሎት ብቻህን ከጌታ ጋር የምታሳልፍበት ጊዜ አለህን? (ማቴዎስ 6፡5–8 አንብብ)። የት እንጸልይ? ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መነጋገር አለብን? ስንጸልይ መጮህ ወይስ ረጅም ጊዜ ማሳለፍ ያስፈልገናልን? ስለ ጸሎት ከተማርሃቸው ቢያንስ አራት ነገሮች ጻፍ።

## አራተኛ ቀን፡– የአስተማሪው የብቃት መመዘኛዎች – ክፍል 3

12ኛ ጥያቄ፡– የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ሊኖሩት ይገባል ብለህ ከምታምንባቸው ብቃቶች አምስት ወይም ስድስቱን ጻፍ።

አስተማሪዎች በተማሪዎቹ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አላቸው። ከተማሪዎቻቸው የተሻለ የትምህርት ዕድል አግኝተዋል። በመሠረቱ ከተማሪዎች ይልቅ በዕድሜ የገፉ ናቸው። በክርስትና ሕይወት ከተማሪዎቻቸው ይልቅ የበሰሉ እንደሆኑ ይታሰባል።

ስለ እነዚህና ስለ ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎች ወደ አስተማሪዎቻቸው ይመለከታሉ። ትልቅ አክብሮትን እየሰጡ እንደ ምሳሌ አድርገው አስተማሪዎቻቸውን ይወስዳሉ። ልጆች ብዙ ጊዜ አስተማሪዎቻቸውን በማድነቅ የአስተማሪዎቻቸውን ሙያ መከተል ወይም እንደ እነርሱ መሆን ይፈልጋሉ።

ይህ እውነት ከሆነ አስተማሪዎች ለተማሪዎች በሚያመች መንገድ መልካም ምሳሌ ሆነው የመኖር ኃላፊነት አለባቸው። ይሁንና ስለ አስተማሪዎች በምናስብበት ወቅት በመጀመሪያ እያንዳንዱ ሰው ልዩ የሆነ ሰብእና እንዳለው ማወቅ አለብን። ለዚህ ሰው ክርስቶስ ሞቶለታል። በእግዚአብሔር ተወድዷል።

ጥሩ አስተማሪዎች ብዙ ጊዜ በሰዎች ላይ ያለውን መልካም ነገር ወደ ማየት ያዘነብላሉ። በማኅበራዊ ግንኙነት ይደሰታሉ። በግልጽ የመናገር ችሎታ አላቸው። ማንበብ ይወዳሉ። ለተማሪዎቻቸው ሁሉንም ነገር ከመናገር ይልቅ እውቀትን በማግኘት የሚደሰቱ ያደርጓቸዋል። ስሜታቸው ሚዛናዊና የተስተካከለ ነው። እነዚህ በአንድ ጥሩ አስተማሪ ላይ ልናያቸው የሚገቡ ብቃቶች ናቸው። ጨምረን እንዘርዝር።

1) መማር የሚወዱ፡– አስተማሪ ያለማቋረጥ የሚማር መሆን አለበት። አንድ መምህር ሊያስተምረው የሚችለው ከሁሉ የተሻለ ትምህርት የተማረውን ነው። አስተማሪ መማሩን ካቆመ የሚያስተምረው ምንም ነገር አይኖርም። አዲስ ዘዴን ለመፍጠር ፈቃደኛ መሆንና አዳዲስ መረጃዎች

ለማግኘት የሚፈልግ መሆን አለበት። ያኔ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያድግ ሰው ይሆናል።

2) ምሳሌ የሚሆኑ፡- ውጤታማ አስተማሪ ለሚያስተምረው ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ መሆን የሚችል ነው። አንዳንድ አስተማሪዎች «እኔ የምለውን አድርጉ እንጂ እኔ የማደርገውን አይደለም» ሊሉ ይችላሉ። እንደ አስተማሪነታችን ተማሪዎች እኛን የሚከተሉ እንደሆኑ የምንከደው ነገር አይደለም። ሕይወታችን ጥሩ ምሳሌ ካልሆነ ተማሪዎቻችንን ወደ ጥፋት እየመራናቸው ነው ማለት ነው። ሉቃስ 6:39–42 አንብብ። «እውር እውርን ሊመራው ይችላልን? ሁለቱ በጉድጓድ አብረው አይወድቁምን? ሲል ይጠይቃል። በቁጥር 40 እንዲህ ይላል፤ «ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል»። ተማሪዎችህ አንተን የሚከተሉ ናቸው። ተማሪዎችህ ወደ ጉድጓድ እንዳይወድቁ ራስህን ጥሩ ምሳሌ ለማድረግ ዛሬ ትወስናለህ? ለተጨማሪ ማብራሪያ ቁጥር 41 እና 42ን እንደገና አንብብ።

3) ዝንባሌ፡- አስተማሪዎች ለራሳቸው መልካም ዝንባሌ ሊኖራቸው ይገባል። አንተ ማን እንደሆንህ ታውቃለህን? «በእርግጥ አውቃለሁ» እንደምትል ይገባኛል። «ስሜ ለገሰ ይባላል። በኢትዮጵያ ተወለድሁ፤ ቤተሰቦቼም እከሌ እና እከሌ ናቸው»። እኔ የምለው እንደ እርሱ አይደለም። የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ ታውቃለህን? በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንህ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነህ። ኢየሱስ በጣም ስለሚወድህ በዓለም ውስጥ ያለኸው ሰው አንተ ብቻ ብትሆንም እንኳ ከኃጢአትህም ያድንህ ዘንድ ይሞትልህ ነበር። ከአንተም በፊት ስፍራን ያዘጋጅልህ ዘንድ ወደ ሰማይ ሄዷል። እንድትጸልይ ጥያቄህንና ምስጋናህን ለእርሱ እንድታቀርብ ጋብዞሃል። በፍጥረታት ሁሉ አምላክ ፊት ስለ አንተ ይቀርብ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት አማላጅ ሆኗል። አንተንም ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ይልካቸዋል። በአንተም ላይ ይኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶሃል። ሰውነትህ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው። አንተ የራስህ አይደለህም። በዋጋ የተገዛህ ነህ። ዋጋውም ክቡር ደሙ ነው። ከዚህም የሚበልጥ ነገር ደግሞ አለ። ዘርዝረን ልንጨርሰው አንችልም። የተለየህ ሰው ነህ። ለአንተ ስለአደረገው ነገር ራስህን ተቀብለህ ለጌታ ምስጋናን ታቀርባለህን? ዝንባሌህ የቀና ሆኖ በሙሉ ምስጋና ልትሞላ ይገባል። በእነዚህ ነገሮች ልትኩራራ አትችልም። ይሁንና ልታመሰግነውና ሊጠቀምብህ እንደሚፈልግ ልትረዳ ለእርሱም የምትጠቅም መሆንህን ልትገነዘብ ትችላለህ።

ማን እንደሆንህ ካወቅህ አንተ እንዳወቅኸው ደግሞ ሌሎች ያውቁ ዘንድ ወደ ጌታ ልታመጣ ትችላለህ። እናም በሕዝቦችህ ላይ መልካም ዝንባሌ ይኖርሃል። እነርሱም የምትወዳቸውና የምታከብራቸው መሆኑን ወዲያውኑ ያውቃሉ። ፍቅር ካሳየሃቸው ፍቅርን ይመልሱልሃል።

በማስተማር ጌታን ማገልገልን በተመለከተ ዝንባሌህ ምንድን ነው? ያደረገልህን ነገር ሁሉ ከተገነዘብህ አገልግሎትህ ፍቅርህን ለእርሱ የምትገልጽበት መንገድ መሆን አለበት። የምናስተምረው ማስተማር ስላለብን

አይደለም። የምናስተምረው ጌታን ስለምንወደውና ይህን ጌታ ሌሎች እንዲያውቁት ስለምንፈልግ ነው።

4) የተሰጡ፡- አስተማሪዎች ለሥራቸው የተሰጡና ጊዜን ለዚያ ነገር የሚያጠፉ ብሎም ለተማሪዎቻቸው ጊዜን የሚሰጡ መሆን አለባቸው። የእሑድ ክርስቲያን ነህን? እሑድ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትመጣው ልታደርገው የሚገባህ ነገር ስለሆነ ነውን? ለማስተማር የምትሄድ ከሆነ ጊዜህን፥ ኃይልህንና ገንዘብህን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለብህ። አስተማሪ መሆን መስጠትን ይጠይቃል። በእሑድ ትምህርት ወይም በየትኛውም ትምህርት የምትሰጥበት ክፍለ ጊዜ ለመገኘት ፈቃደኛ ነህን? ለዝግጅት በቂ ጊዜ ለመስጠት ትፈቅዳለህን? ከክፍልህ ውስጥ ለታመሙ ሰዎች ጉብኝት ለማድረግ ፈቃደኛ ነህን? የግልህ ከሆነው ገንዘብ ለትምህርትህ ማስተማሪያ የሚሆንን ነገር ለመግዛት ፈቃደኛ ትሆናለህን? አስተማሪ መሆን መስጠትን ይጠይቃል።

5) ተጫዋችነት፡- ውጤታማ አስተማሪ ጤናማ የሆነ የፈገግታ ስሜትን መጎናጸፍ አለበት። የሚያስቅ ነገር ስታገኝ መሳቅ ትችላለህን? ጤነኛ የመሳቂያ ስሜት ኖሮህ ከተማሪዎችህ ጋር መሳቅ አስፈላጊ ከሆነም አንዳንዴ በራስህ ላይ መሳቅ መቻል አለብህ። የተማሪዎችህን የመሳቅ ነገር ወይም ለራስህ በሚያጋጥሙህ የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚፈጠረውን ነገር ልታደንቅ ይገባል።

6) ጉጉት፡- ውጤታማ አስተማሪ ለሕይወት ጉጉ የሆነ፥ በክርስትና ሕይወት የሚደሰትና ከተማሪዎቹ ጋር ደስታውን በታላቅ ስሜት የሚካፈል ነው። አንዳንድ ጊዜ ደስተኛ መሆን ይቻላል። ነገር ግን ክርስቲያን መሆን ለዘላቂ ደስታ ምክንያት ነው። አንዱ የመንፈስ ፍሬ ደስታ ነው። ጌታን በምንታመንበትና በምንታዘዝበት ጊዜ ደስታውን በልባችን ውስጥ ያፈስሰዋል። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፤ «በሕይወትህ የነበረውን ደስታ ካጣህ ያለመታዘዝን እየተለማመድህ እንዳይሆን ራስህን መርምር»። ደስተኛ ካልሆንህ በሕይወትህ ንስሐ ያልገባህበት ኃጢአት አለ ማለት ነው። ምን እንደሆነ እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ጠይቀው። ከዚያም ንስሐ ግባ። ደስታህም ይመለስልሃል።

7) ተግባቢ፡- ጥሩ አስተማሪ ጓደኛ የሚሆንና ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ የሚችል ነው። የእርሱ ዓላማ ሰዎች ጌታን ወደማወቅ እንዲመጡ መርዳት እንደሆነ ይገባዋል። በጌታ ምሪት ፍላጎታቸውን በቶሎ በማወቅ ሰዎች እርሱን ወደማወቅ ይደርሱ ዘንድ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህም ለእነርሱ በመጠንቀቅ እና የፍቅር ዝምድና በማሳየት በሚገኝ አመኔታ ከግብ በማድረስ ብቻ የሚመጣ ነው። በዚህ ዓይነት ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማስማት የተዘጋጁ ይሆናሉ።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፡- ከዚህ በላይ የተመዘገቡትን መመዘኛዎች ስትመለከት አስተማሪ ለመሆን ብቃት ያለህ በየትኞቹ አካባቢ ነው? ደካማ ጎን ያለህስ በየትኛው አካባቢ ነው? ልታስተካክላቸው የሚገቡትን ነገሮች አመልክት። እነዚህን ደካማ ጎኖች |

እንድትለውጥ ሊረዳህ የተዘጋጀ ማን ነው? አሳብህን በቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች አስረግጥ።

**አምስተኛ ቀን፡—** በትምህርት አራት ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች በሙሉ ከልስ። ከዚህ በታች ያሉትን የመወያያ ርእሶች በመመልከት በውይይት ለመሳተፍ ራስህን አዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለሳምንታዊ ስብሰባ የተለመደውን አሠራር ተከተል። በሚከተሉት ርእሶች ላይ ተወያይባቸው።

1. ዳግመኛ የመወለድን አምስት ቅደም ተከተሎችን ከልስ። እያንዳንዱን ነጥብ ተወያይበትና እያንዳንዱ የቡድን አባል መቼና እንዴት ዳግም እንደተወለደ እንዲናገር አድርግ። እርግጠኛ ያልሆኑበት ነገር ከተገኘ የተሰጡትን ጥቅሶች በመጠቀም በቅደም ተከተሎቹ በመምራት እያንዳንዱ ሰው ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ/ አድርጋ ለመቀበሉ እርግጠኛ ሁኑ።

2. ከዝርዝር ነጥቦች ወደ አጠቃላይ ድምዳሜ በሚመራ የአጠናን ዘዴ ውስጥ የሚገኙትን ሦስት ደረጃዎች ዘርዝር። ለምንድን ነው እያንዳንዱ ደረጃ አስፈላጊ የሚሆነው? በጥናታችን ብዙውን ጊዜ ችል የምንለው የትኛውን ደረጃ ነው? ውጤቱስ ምንድን ነው?

3. የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ከሕይወታችን ጋር ከማዛመድ የምናፈገፍገው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል የመታዘዝ ውጤቱ ምንድን ነው? አሳብህን የሚደግፍ ጥቅስ ስጥ። የአለመታዘዝ ውጤትስ ምንድን ነው?

# ትምህርት አምስት
# ልጆችን ማስተማር

## 1ኛ ቀን፡- ልጆችን ለምን እናስተምራለን?

**1. ልጆች የጌታ ስጦታዎች ናቸው።**

«እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው» [መዝ. (127)፡3]። ጌታ ለእርሱ ክብር እንዲያደርጓቸው ለወላጆች በኃላፊነት የሰጣቸው ናቸው። የሚወለዱት ትናንሽ፥ ዓቅመ-ቢስና የሰዎችን እርዳታ የሚፈልጉ ሆነው ነው። ራሳቸውን ለመግለጽ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ልቅሶ ነው። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጡራን መካከል ራሳቸውን ለመርዳት ከሁሉ ያነሰ ዓቅም ያላቸው የሰው ልጆች የሆኑት ሕፃናት ናቸው።

ልጆች የሚወለዱት ከባልና ሚስት ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ወንድና ሴት እንዲወልዱና በቁጥር እንዲበዙ አዘዛቸው። ልጆች የሚጠነቀቁላቸው፥ የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርቡላቸው፥ የሚያሠለጥኗቸውና የሚያስተምሯቸው ሁለት ወላጆች አሏቸው። ለብዙ ዓመታት ለየዕለቱ ፍላጎታቸው በወላጆቻቸው ላይ ተደግፈው ይኖራሉ። በእነዚያ ጊዜያት እግዚአብሔር ወላጆች ልጆቻቸውን ከቤታቸው ወጥተው የራሳቸውን ቤት ለሚመሠርቱበትና ልጆችን ለሚወልዱበት ጊዜ እንዲያዘጋጇቸው ይፈልጋል።

በዚህ ትምህርት ልጆችን በሚገባ የማስተማርና የማሠልጠን አስፈላጊነት እጅግ ዋና ጉዳይ መሆኑን እንነጋገራለን።

---

1ኛ ጥያቄ፡- ልጆችን መመልከት ጀምር። የሚነጋገሩት ስለ ምንድን ነው?

2ኛ ጥያቄ፡- ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁት ነገር አለን?

3ኛ ጥያቄ፡- በጣም ትንንሽ የሆኑ ሕፃናት መማር ይችላሉን? ምን መማር ይችላሉ?

---

**1. እግዚአብሔር ለልጆች ያለው አመለካከት።**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕፃናትን እንደሚወድ ግልጽ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ ሲያመጡ እንመለከታለን። ደቀ መዛሙርቱ ትዕግሥት በማጣታቸው ጌታን እንዳያስቸግሩት ወላጆችን ነግረዋቸው ነበር። «ሥራ በዝቶበታል» የሚሉ ይመስላል። ነገር ግን ኢየሱስ ምን አለ? (ማር. 10፡14-16)። «ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው»። ከዚያም ሕፃናቱን አቀፋቸው፥ እጆቹንም ጭኖ ባረካቸው፥ ወደዳቸው። ስለዚህም ከእነርሱ ጋር ጊዜ አሳለፈ።

አንድ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ መጥተው «በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ማን ነው?» የሚል ጥያቄ ጠየቁት። ሕፃን በመካከላቸው አቁሞ እንዲህም አለ፤ «እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። እንግዲህ እንደዚህ

ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው» (ማቴዎስ 18፡1-4)። ኢየሱስ የሕፃናትን ቅንነትና ትሑት እምነት ያከብራል።

የሕፃን ልጅ ትሑትና ዝቅተኛ አመለካከት በቀላሉ በእግዚአብሔር እንዲያምን ያደርጉታል። ለእግዚአብሔር ክፍትና እርሱን ለማወቅ የሚፈልግ ነው። ልጆችን ትንንሾች ሆነው እያሉ የወንጌልን እውነት ብናስተምራቸውና እንዲረዱ ብናደርጋቸው በማወቅ ሊያምኑና ሊድኑ ይችላሉ።

ከዚያም ከነዚህ ከሚያምኑ ሕፃናት አንዱን በኃጢአት ለሚያሰናክል ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል «...በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር» (ማቴዎስ 18፡6)። ኢየሱስ ትንንሽ ልጆችን እንዳናሰናክል ወይም ወደ ስሕተት እንዳንመራ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል። ለጌታ ውድ መሆናቸውን መረዳት አለብን። አእምሮአቸው ክፍት ስለሆነ በአሳባቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ ስለምንዘራው የዘር ዓይነት መጠንቀቅ አለብን።

<table>
<tr><td>4ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ለልጆች ስላለው አመለካከት የተማርኻቸውን ሦስት ነጥቦች ግለጽ?<br><br>5ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ የወፍጮ ድንጋይን በመግለጫነት ተጠቅሞ በሚናገርበት ጊዜ ምን እያስተማረ ነበር?<br><br>6ኛ ጥያቄ፡- ይህ ማስጠንቀቂያ ለአንተ ምን ማለት ነው? ስለ ልጆች ያለህን ዝንባሌ መለወጥ ይኖርብሃልን? እንዴት? ከቡድንህ አባላት ጋር በክፍል ውስጥ ተነጋገሩበትና መልሶችህን ጻፍ።</td></tr>
</table>

እንደገና በማቴዎስ 18 ላይ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፤ «ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር የአባቴን ፊት ያያሉ» (ቁ. 10-11)። የእግዚአብሔር መላእክት ልጆችን እንደሚጠብቁና እንደሚያገለግሏቸው እናውቃለን [መዝ. (34)፡7፤ ዕብ. 1፡14]። ኢየሱስ ሕፃናትን የሚጠብቁት መላእክት ከእግዚአብሔር ዙፋን ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ስላላቸው በምድር ላይ ያሉትን ሕፃናት እንዴት እንደሚጠብቋቸው መመሪያ ይሰጣቸዋል ማለቱ ነበር። እርሱ ይህን ያህል ለእነርሱ ግድ ካለው፥ ታዲያ እኛ ከፍ ያለ ክብር ልንሰጣቸው አይገባምን? ብዙ ጊዜ «ልጆች ምንም አያውቁም» እንላለን፤ ይህ እውነት ነውን?

ከቁጥር 12-13 ኢየሱስ ስለ ጠፋው በግ ታሪክ ይናገራል። የታሪኩ ዓውድ እንደሚያሳየው እየተናገረ ያለው ስለ ልጆች ነው። አንዱ እንኳን ቢጠፋ እረኛው ዘጠና ዘጠኙን በጎች ትቶ የጠፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው ወጥቶ ይሄዳል። በሚያገኘው ጊዜ ካልባዘኑት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ በተገኘው በአንዱ እጅግ ደስ ይለዋል። ከዚያም እንዲህ ብሏል፡- «እንደዚሁ፥ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም (ማቴዎስ 18፡14)።

<table>
<tr><td>7ኛ ጥያቄ፡- ልጆችን እንዴት በማይገባ ሁኔታ ልንመለከታቸው እንችላለን? ኢየሱስ ልጆችን እንዴት አያቸው? ስለ ጠፋው በግ ከሰጠው ምሳሌ ምን ልትማሩ ትችላላችሁ?</td></tr>
</table>

8ኛ ጥያቄ፦ ኢየሱስ የሕፃናትን ግልጽነትና ትሕትና፥ የመማር ናፍቆት እና ለእምነት ዝግጁነትን ካደነቀ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ሕፃናት ለመድረስ የሚያስችሉ መንገዶችን ጻፍ።

### 3. በብሉይ ኪዳን ሕፃናትን ስለ ማስተማር የተሰጠ መመሪያ

እግዚአብሔር ልጆች በጥንቃቄ እንዲማሩ መፈለጉ ከብሉይ ኪዳን ጊዜ ጀምሮ የተረጋገጠ ነው። እግዚአብሔር በሙሴ ለእስራኤል ልጆች መመሪያን በሰጠ ጊዜ ሕፃናትንም አብሮ ጠቅሶ ነበር። በዘዳግም መጽሐፍ ላይ ሙሴ አዲሱን የእስራኤል ትውልድ እያሳሰበ ነበር። በዘዳግም 4፡5–8 ላይ ምን እንደሚል ካነበብህ በኋላ በቁጥር 9 ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ አስተውል። «... ዓይኖችህ ያዩትን ነገር እንዳትረሣ በሕይወትህም ዘመን ከልብህ እንዳይወድቅ ተጠንቀቅ፥ ነፍስህንም በትጋት ጠብቅ፥ ለልጆችህም፥ ለልጅ ልጆችህም አስታውቀው»።

ለእኛ በጣም ውድ የሆኑትን እውነቶች ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ በጣም አስፈላጊ ሲሆን፥ ለወንጌሉ ቀጣይ እርምጃም ዋና ነገር ነው። ሙሴ በዘዳግም 5 ላይ አሥርቱን ትእዛዛት ከደገመ በኋላ ትርጉማቸውን ለእስራኤላውያን ሲያስረዳ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንዲህ ብሏል። «ለእነርሱ ለዘላለምም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ፥ እንዲፈሩኝ ሁልጊዜም ትእዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው!» (ቁ. 29)።

በዘዳግም 6፡1–9 ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተላልፍ እንደገና እነዚህን ነጥቦች አጥብቆ ተናገረ።

- እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤
- አንተም አምላክህን እንግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።
- ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ።
- በልጆችህ ላይ ተናገረው።
- በቤት ውስጥ ስትቀመጥ ስለ እርሱ ተነጋገር
- በመንገድ ላይ ስትሄድ ተጫወተው
- በመኝታህ ሳለህ አሰላስለው
- በመነሣትህ ጊዜ ተጫወተው።
- በእጆችህም ምልክት አድርገህ እሰረው፤ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ።
- በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።

የእምነታችንን መሠረታዊ እውነቶች በልባችን ለመያዝ በመጀመሪያ «መስማት» አለብን። ሁለተኛ በመላ ማንነታችን አምላካችንን መውደድ አለብን። በሕይወታችን ውስጥ እርሱ የመጀመሪያውን ስፍራ መውሰድ

አለበት። ሦስተኛ፥ የጌታን ትእዛዛት በልባችን ውስጥ ማከማቸት አለብን። በመጨረሻም ለልጆቻችን በየዕለቱ ልናስተምርና በሥራ ልንተረጉመው ይገባል። እግዚአብሔር ለኢያሱ እንደተናገረው በቀንና በሌሊት ልናሰላስለው ይገባል (ኢያሱ 1፡9)።

ይህ በሙሉ በዘዳግም 11፡19–21 በድጋሚ ሌላ የተስፋ ቃል ተጨምሮበት ተጽፎአል። እነዚህን ነገሮች ካደረግን እንደዚህ ይላል፦ «እንደ ሰማይ ዘመን በምድር ላይ ዘመናችሁ የልጆቻችሁም ዘመን ይረዝም ዘንድ በቤትህ መቃኖችና በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው» (ቁጥር 21)። በተጨማሪ ኢሳይያስ 39፡19 ተመልከት።

ልጆቻችንን በታማኝነት ካላስተማርናቸውና በጽድቅ መንገድ ካልመራናቸው የክርስትና እምነታችን በአንድ ትውልድ ውስጥ በቀላሉ ሊከስም ይችላል። ለሚመጡት ትውልዶች ድንቅ የሆኑትን የእግዚአብሔርን ቃሎች ካላስተላለፍን፥ በፊታቸው መልካም ምስክርነት ያለው ሕይወት ካልኖርን እናም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በግል ወደ ማወቅ ካልመራናቸው፥ ክርስትናችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምድረ ገጽ ሊጠፋ ይችላል። ስለዚህ እምነታችንን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፋችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ማስተማርና ተገቢ የሕይወት ተዛምዶ በጣም አስፈላጊ ነው።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፦ ልጆችን ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ የምታምንባቸውን ቢያንስ አራት ምክንያቶች ጻፍ። የሚቻል ከሆነ መልስህን በጥቅስ አስደግፈህ ጻፍ። |

## ሁለተኛ ቀን፦ ልጆችን ማስተማር ከቤት ይጀምራል።

### 1. አባቶች ልጆቻቸውን ማስተማር አለባቸው።

እግዚአብሔር ልጆችን በቤት ውስጥ ስለ ማስተማር ግልጽ መመሪያ ሰጥቷል። እስቲ ኤፌሶን 6፡4 እንመልከት። «እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጡአቸው»። «እናንተም ወላጆች ሆይ፥ በጌታ ኢየሱስ ሥርዓትና ምክር አሳድጉአቸው እንጂ ልጆቻችሁን በማስቆጣት አታስመርሩአቸው» (አዲስ ትርጉም)።

ልጆችን የማስተማርና የማሠልጠን ኃላፊነት ለወላጆች ተሰጥቷል። ከጌታ የተሰጠው ምክር አባቶች የክርስትናን መርሆ ለልጆቻቸው በቤት ውስጥ እንዲያስተምሩ ነው። ብዙ ቤተሰቦች ይህንን ጉዳይ ችላ በማለት ልጆች ማሠልጠንን ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለትምህርት ቤት በመተው፥ ምንም ኃላፊነት አይወስዱም። በሌሎች ቤቶች ደግሞ ልጆችን የሚያሠለጥኑት እናቶች ብቻ ናቸው። አንዳንድ ታማኝ እናቶች ልጆቻቸውን በማሠልጠን ድንቅ ሥራ ሠርተዋል። ሆኖም ይህ የመጀመሪያው የጌታ ዕቅድ አልነበረም። እናቶች አባቶች በሚያስተምሩበት ጊዜ ልጆች የተማሩትን በተግባር እንዲተረጉሙ መርዳት አለባቸው። በዚህ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ይሁንና፥ ዋናው ኃላፊነት ለአባቶች ተሰጥቷል። ብዙ አባቶች ይህንን ዋና ሥራ ለመሥራት ጊዜ እንደሌላቸው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ከቤት ለብዙ ጊዜ በመራቅ ኃላፊነታቸው እንዲታሰር ያደርጋሉ።

## 2. በቤት ውስጥ በቂ ትምህርት ያለመስጠት ውጤቶች

በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ ብዙ ልጆች በጌታ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን መሠረታዊ ነገር ሳያገኙ ያድጋሉ። ከዚህ የሚብሰው ደግሞ ከክርስቶስ ተለይተው የጠፉ የመሆናቸውን እውነታ ፊት ለፊት ተጋፍጠው አያውቁም። እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማደጋቸው እና ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ከመካፈላቸው፥ አልፎም በመዘምራን ቡድንና በወጣቶች መሪነት ከማገልገላቸው የተነሣ የጸኑ እና ስለ ምንም ነገር ማሰብ የማያስፈልጋቸው ይመስላቸዋል።

ዛሬ ለልጆቻቸው ጥሩ መሠረታዊ ሥልጠና በቤት ባለመስጠታቸው ልጆቻቸው ከጌታ ስለራቁባቸው የሚያዝኑ ወላጆች ስንቶች ናቸው? ብዙዎች ለወንጌል እምቢተኞች ናቸው። ከክርስትና ጋርም ምንም ግንኙነት የላቸውም። በዘመናት መካከል እንደነዚህ ዓይነቶቹ ወጣቶች እጅግ ከፉዎችና በጣም አደገኛ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ሆነዋል። ሃይማኖታዊ ቋንቋ ያውቃሉ። ነገር ግን በልባቸው ያለውን የክርስቶስን እውነታ አያውቁም።

ከክርስቲያን ቤተሰብ የመጡ አንዳንድ ልጆች መራራ ናቸው። ምክንያቱም ወላጆቻቸው ከእነርሱ ጋር ጊዜ አልነበራቸውም። በፈንታው የጌታ አገልግሎት ወይም ሌላ ሥራ እንደበዛባቸው ወይም ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉባቸው እየተናገሩ ልጆቻቸውን ችላ ብለው ነበር። እነዚህ ልጆች ጥልቅ የሆነ መራርነት እና ጉዳት አለባቸው። ይህ እስኪፈወስም ዓመታት ይወስዳል። አንዳንዶቹ ከዚህ ጉዳታቸው ለመላቀቅ ስለማይችሉ መራራ ሆነው ይቆያሉ፤ ሕይወታቸውን በሙሉ ከጌታ ርቀው ይኖራሉ። እነዚህን መሰናክሎች ለማስወገድ አባቶች በቤት ውስጥ ምን ዓይነት አመራር መስጠት ይኖርባቸዋል?

> 10ኛ ጥያቄ፦ ከላይ ከተጠቀሱት ክፍሎች ውስጥ፥ አባቶች ልጆቻቸውን በሚያሠለጥኑበት ጊዜ ሊያስታውሱ የሚገባቸውን ሦስት ነገሮችን ዘርዝር።
>
> 11ኛ ጥያቄ፦ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ወጣቶችን በምትመለከትበት ጊዜ ያየሃቸው አንዳንድ ድክመቶች ምን ምን ናቸው? ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት ምን ማድረግ ይቻላል?

## 3. ተከታታይና አዎንታዊ ትምህርት አስፈላጊ ነገር ነው።

አባቶች ልጆቻቸውን ማስተማራቸው የተለየ ኃላፊነት እና ክብር ነው። በጢሞቴዎስና በቲቶ መጻሕፍት ውስጥ ለሽማግሌዎችና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመዘኛ እንደተጻፈ እናነባለን። «ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፥ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?» (1ኛ ጢሞ. 3፡4-5፤ ቲቶ 1፡6ን በተጨማሪ ተመልከት)።

በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ ዕለታዊ የቤተሰብ አምልኮ መቅረት የሌለበት ፕሮግራም ሊሆን ያሻል። ይህ ፕሮግራም በአባት መመራት አለበት። እርሱ ለቤተሰቡ ስለሚያካፍላቸው ነገር በጸሎት መዘጋጀት አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ክትትል ውስጥ በማለፍ አስቸጋሪ ክፍሎችን በማብራራት መቀጠል ጥሩ ነው። የክፍሎቹን አጭር ማብራሪያ በቀላሉ መስጠትና

ተግባራዊነታቸውን ማሳየት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እና በየዕለቱ የምንኖረው ኑሮ የማይለያዩ መሆናቸውን ልጆች እንዲረዱ ያደርጋል። በየዕለታዊ ሕይወታችን ትምህርቱን እንዴት ልንተረጉመው እንደምንችል ማሳየት ለልጁ ትምህርቱ ትርጉም የሚሰጥ ይሆንለታል። አባቶች ከሚስቶች ጋር በመመካከር የልጆቻቸውን ፍላጎቶች መድረስ ያስፈልጋቸዋል። አባት በቤት በማይኖርበት ጊዜ እናቶች ፕሮግራሙን ማካሄድ መቀጠል አለባቸው። በዚህ ጊዜ ልጆች በየዕለቱ መንፈሳዊ ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ይማራሉ።

ከዚህ የሚከተሉት በየዕለቱ የጥሞና ጊዜዎቻችሁ ልታደርጉ የምትችሏቸው መግቢያ ነጥቦች ናቸው።

ሀ. ጥቂት አዝማቾች ዘምሩ። ሕጻናት መዘመር ይወዳሉ። በቶሎ ቃሉን ይማራሉ።

ለ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አንብቡ፤ ተከታታይ ታሪክ ይመረጣል። ለምሳሌ የዮሴፍ ታሪክ (ዘፍጥ. 37–50)። ብዙ አንቀጾችን ከታሪኩ ምዕራፍ እንደየዕድሜያቸው በመመርኮዝ አንብቡ። ልጆቻችሁ ታዳጊ ወጣቶች ከሆኑ ከመልእክቶች ውስጥ ማንበብ ጥሩ ነው።

ሐ. ከተነበበው ክፍል ውስጥ ልትማሩ የምትችሉትን ተወያዩ። የቤተሰቡ አባላት የተማሩትን በዕለታዊ ኑሮአቸው ውስጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉ እርዱአቸው። ምስክርነቶች ካሉ ለመስማት ጊዜ ስጡ። ጥያቄዎችን መልሱ።

መ. በየሳምንቱ የሚሰጠውን ትምህርት ለመደገፍ ጥቅሶችን በቃል አጥኑ። በየዕለቱ ከልሱ።

ሠ. እንደገና መዝሙር ዘምራችሁ በጸሎት ፕሮግራሙን ፈጽሙ።

ልጆችን በማሳደግ የሥልጠና መርሆ እና በቅጣት ላይ ባልና ሚስት መስማማታቸው እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ልጆችን የማሠልጠን ዓላማን በተመለከተ እንዲሁም ልጆች ካልታዘዙ በሚቀጡበት ዘዴ ላይ ባልና ሚስት ሊወያዩ ይገባል። ውሳኔዎቻቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ በጥብቅ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይገባል። እነዚህን ዓላማዎች በቀጣይነት ለመቀጠል መዘጋጀትም አለባቸው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡– በዕለታዊ የጥሞና ጊዜ ላይ ለትንንሽ ሕፃናት ልታስተምር የምትችላቸው ቢያንስ አምስት ትምህርቶች አመልከት። |
| 13ኛ ጥያቄ፡– ለታዳጊ ወጣቶች የሚሆኑ የትምህርት ዓይነቶችን አመልከት። |

4. መታዘዝን ማስተማር።

መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ይናገራል (ዘጸ. 20፡12፤ ኤፌ. 6፡1–3፤ ቆላ. 3፡20 አንብብ)። ይሁንና፥ መታዘዝን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ በማየታቸው ብቻ ሊማሩት አይችሉም። ወላጆች ለሚሰጡት ትእዛዝ ሁሉ ልጆች የሚታዘዙ መሆኑን በትጋት መከታተል አለባቸው። ልጆችን ስለማዘዝ ልናስታውሳቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ።

ሀ. ልጁ ሊታዘዘው የሚችለውን ትእዛዝ ብቻ መስጠት።

ለ. ትእዛዛትን ከሰጣችሁ በኋላ ልጁ መታዘዙን በሚገባ መከታተል ይኖርባችኋል።

ሐ. ብዙ ትእዛዞችን አትስጡ። አንዳንድ እናቶች ልጆቻቸው ላይ ቀኑን ሙሉ ይጮኹባቸዋል። ይህ ልጆች ከሚችሉት በላይ ነው።

መ. ልጃችሁ እያወቀ አልታዘዝም በሚልበት ጊዜ ልትቀጡት ይገባል። የምትሰጡት ፍርዳችሁ ትክክለኛ እንጂ የሚያዳላ መሆን የለበትም። ቅጣታችሁ ንዴታችሁን ለማብረድ ሳይሆን ልጆችን ለማሻሻል መሆን አለበት። ፈጽሞ በቁጣ መቅጣት የለባችሁም። መቅጣት ያለባችሁ ለልጆቻችሁ መሻሻል ስለሆነ የቅጣቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ማስረዳት ያስፈልጋል። ከቅጣቱ በኋላ ከልጁ ጋር የጸሎት ጊዜ በመውሰድ ያጠፋውን ጥፋት ከባድነት መግለጽና እንደገና ያንን ዓይነት ጥፋት እንዳያጠፋ እግዚአብሔርን መጠየቅ ያስፈልጋል (ምሳሌ 22፡15፤ 13፡24፤ 23፡13–14 አንብቡ)።

ቅጣት የተለያየ ዓይነት ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ልጅን በበትር መምታት አስፈላጊ ነው። ይህንን ቅጣት በተግባር ለማዋል እግዚአብሔር ጥሩ ስፍራ አዘጋጅቷል። ይህም በመቀመጫው ላይ ነው። ፈጽሞ በጭንቅላቱ ላይ፥ ፊቱን፥ እጁን፥ ወይም እግሩን አይደለም። በሌላ ጊዜ እርሱን ማነጋገር ወይም አንዳንድ መዝናኛዎችን መከልከል ወይም ደግሞ ስለ ጥፋቱ ከባድነት ለብቻው እንዲያስብ ወደ ክፍሉ ሄዶ እንዲቀመጥ ማዘዝ ይቻላል።

ከዚህ በኋላ እንደምትወዱት እና ከእርሱ ትልቅ ነገር እንደምትጠብቁ ንገሩት።

5. ሌሎች የልጆች ሥልጠና አስፈላጊ ገጽታዎች

ሀ. ልጆች እግዚአብሔርንና ሰዎችን ስለማክበር ሊማሩ ያሻል (ዘጸአት 20፡12፤ ኤፌሶን 6፡2–3፤ ዘሌዋውያን 19፡32፤ ሮሜ 13፡1–5)።

ለ. እውነትን የሚናገሩና ታማኞች እንዲሆኑ መማር አለባቸው (ምሳሌ 12፡22፤ ቆላስይስ 3፡9፤ ራእይ 21፡27፤ ምሳሌ 6፡16–19፤ ኤፌሶን 4፡25)።

ሐ. ለሌሎች ርኅሩኅ፥ ደግና አሳቢ ሆነው መገኘታቸው አስፈላጊ ነው (ኤፌ. 4፡32)። ከወላጆቻቸው ምሳሌነት በጣም ብዙ ይማራሉ።

መ. ኃላፊነትን መውሰድም መማር አለባቸው (ሰቆ. ኤር. 3፡27)። በየዕለቱ የሚደረግ ሥራን መሥራታቸው የሥራን ክቡርነት እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። በየዕለቱ ሊያከናውኑት የሚገባ ሥራ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል፤ እናም ያለ ተቆጣጣሪ እንዲሠሩ ይገባል።

---

14ኛ ጥያቄ፦ የመጽሐፍ ቅዱስን የንባብ ክፍሎች አንብቡና መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማስታወሻ ያዙ። ልጆችን ስለ ማስተማርና ማሠልጠን ከቀረቡት አምስት ክፍሎች የእያንዳንዱን ክፍል ዓላማ የሚገልጹ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አስቡና አስተምሩ።

---

## 5. የልጆች ሥልጠና መግለጫ ታሪኮች

### ሀ) አብርሃም

የመልካም አባትን ምሳሌነት በአብርሃም ሕይወት እናገኛለን። እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንዲህ ብሏል፤ «ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና፤ ይህም እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ የተናገረውን ነገር ሁሉ ያመጣ ዘንድ ነው» (ዘፍጥረት 18፡19)። እግዚአብሔር አብርሃም ልጆቹንና ቤተሰቡን በሚገባ እንደሚያሠለጥን ሊተማመንበት ይችል ነበር።

### ለ. ዔሊ

ምንም እንኳ በሴሎ በሚገኘው የመገናኛ ድንኳን ካህንና መንፈሳዊ መሪ ቢሆንም መልካም አባት አልነበረም። የዔሊ ልጆች ካህናት ቢሆኑም የማይጠቅሙና እግዚአብሔርንም የማያውቁ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ኛ ሳሙ. 2፡12)። የኤሊ ልጆች እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ በሚጻረር መንገድ እስራኤላውያን ለመሥዋዕት ከሚያመጡት ሥጋ ውስጥ ጥሩ ጥሩውን ከመጠበሱ በፊት እንዲሰጧቸው ያስገድዱቸው ነበር (ቁጥር 13–17)። እንዲሁም በመቅደሱ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ያመነዝሩ ነበር። ቁጥር 22 እንዲህ ይላል። «ዔሊም እጅግ አረጀ፤ ልጆቹም በእስራኤል ሁሉ ላይ ያደረጉትን ሁሉ፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደተኙ ሰማ»።

ይህንን ሲሰማ ገሠጻቸው፤ ነገር ግን ጊዜው በጣም አልፎ ነበር። እነርሱ ልጆች በነበሩ ጊዜ አልጀመረም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ «...የአባታቸውን ቃል አልሰሙም» (ቁጥር 25)። በኋላም እግዚአብሔር ዔሊን ለመገሠጽ ነቢይ ላከ። እንዲህም አለው። «የሕዝቤን የእስራኤልን ቁርባን ሁሉ መጀመሪያ በመብላታችሁ ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ?.... በቤትህም ለዘላለም ሽማግሌ አይገኝም... ይህ በሁለቱ ልጆችህ በአፍኒና በፊንሐስ ላይ የሚመጣ ለአንተ ምልክት ነው፤ ሁለቱ በአንድ ቀን ይሞታሉ» (1ኛ ሳሙ. 2፡29፥ 32፥ 34)። ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው ታቦቱ በጠላት ተማረከ፤ ሁለቱ ልጆቹም በአንድ ቀን ሞቱ፤ ዔሊም ተቀምጦበት ከነበረበት ወንበር ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ (1ኛ ሳሙ. 4፡ 17–18)። ምሳሌ 10፡1 እንዲህ ይላል። «ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፥ ሰነፍ ልጅ ግን ለእናቱ ኀዘን ነው»።

ይህ አሳዛኝ ታሪክ ነው። ነገር ግን ልጆችን ከሕፃንነታቸው ጀምረን ማስተማርና ማሠልጠን፥ እንዲሁም በአስፈላጊው ጊዜ ማረም እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። እግዚአብሔር ቤትን ለዚህ ዓይነቱ ሥልጠና ማካሄጃ እንዲሆን ይጠብቃል። እንደ አባቶችና እናቶች፥ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ማኖርና ቃሉን ለልጆቻችን በጸሎት መመገብ አለብን።

ለዚህ ጉዳይ ከሚረዱ የመርጃ ጽሑፎች መካከል «የልጆች አስተዳደግ» በሚል ርእስ የተዘጋጀው መጽሐፍ ከኤስ. አይ. ኤም መጻሕፍት መደብር ይገኛል።

## ሦስተኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት ቤት

ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤት ሁሉ ልጆችን የማስተማር ኃላፊነት አለባት። ማስተማር በቤት ይጀምራል ብለን ብንናገርም ቤተ ክርስቲያን በሚገባ የተቀናጀ የማስተማር ፕሮግራም ለክርስቲያን ቤተሰብ ልጆች ማዘጋጀቷ አስፈላጊ ነገር ነው። ከዚህም አልፎ ወንጌልን ለመስማት ዕድል ያላገኙትንና ከክርስቲያን ቤተሰብ ያልሆኑትን የኅብረተሰቡን ልጆች ለመድረስ ድንቅ መንገድ ነው።

የሰንበት ትምህርት ሕፃናትን፥ ወጣቶችንና ጎልማሶችን የማስተማሪያ ፕሮግራም ነው። በሚቀጥሉት ጥቂት ትምህርቶች ለልጆች ስለሚሆነው የሰንበት ትምህርት እንነጋገራለን።

### 1. አንደኛው ዓይነት የሰንበት ትምህርት ቤት

አንድ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ ባለች አንዲት ከተማ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሰንበት ትምህርት ቤት ነበረ። ከጠዋቱ 3:15 አሑድ ጥዋት ነበር። አንዳንድ ሕፃናትም መጥተው ነበር። በሩ እስከ አሁን ስላልተከፈተና ወደ ሰፍራው የደረሰ አስተማሪ ባለመኖሩ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ይጠባበቃሉ።

ትምህርቱ በ3:00 ሰዓት መጀመር ነበረበት። ነገር ግን መምህራኑ አልነበሩም። በአካባቢው የነበረ አስተማሪ አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም በዚያ ሰዓት በቤቱ ሻይ እየጠጣ መጽሐፍ ቅዱሱን በማገላበጥ ሊያስተምራቸው ስለሚችለው ነገር እያሰበ ነበር። አንድ አዘወትሮ የሚነበብ ክፍል ከመረጠ በኋላ በብስክሌት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገሠገሠ።

በቤተ ክርስቲያን ልጆቹ በየስፍራቸው ይጫወቱ ነበር። አንዳንዶቹ አስተማሪው ካልመጣ ወደ ቤታችን ብንሄድ እያሉ እያሰቡ ነበር። ልክ ያን ጊዜ አስተማሪው በብስክሌት ሲመጣ ተመለከቱ።

እርሱም የቤተ ክርስቲያኑን በር ከፈተ። ከዚያም ሁሉም ልጆች ትልልቆቹ ትንንሾቹ አንዳንዶቹ በታላላቅ ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው ታዝለው መቶ ወይም ከመቶ የሚበልጡ እየተንጋጉ ወደ ውስጥ ገቡ። ያሉትን አግዳሚ ወንበሮች በሙሉ ሞሉአቸው። ነገር ግን ተጨማሪ ልጆችም ነበሩ። አንዳንዶቹ መቆም ነበረባቸው።

የአስተማሪው ስም ያዕቆብ ይባላል፤ ትምህርቱን በጥያቄ ለመጀመር ሞከረ፤ አንዳንዶቹ ጥያቄውን ፎክ ብለው በመናገር መለሱ። አንዳንዶቹ ገና የሚመጡትን ይመለከታሉ። አንዳንዶቹ ያወራሉ።፤ ያዕቆብን የሚሰማው አልነበረም።

አርፍዶ ስለመጣና በጊዜ ስላልጀመረ ለመጨረስ መፍጠን ነበረበት። ስለዚህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ማንበብ ጀመረ። ትምህርቱ የሚስብ ስላልነበረ ልጆቹ ወዲያውኑ ሰለቻቸው። ሥዕሎች አልነበሩም፤ ሊያዩት ወይም ሊሠሩት የሚችሉትም ምንም ነገር አልነበረም። እርስ በርሳቸው መነጋገርና መጫወት ጀመሩ። እንዲያውም አንዳንዶቹ መከራከርና መጣላት ጀመሩ። ነገር ግን ያዕቆብ ትምህርቱን መጨረስ ስላለበት ማንበቡን ቀጠለ።

በመጨረሻም የሰንበት ትምህርቱ አበቃ። ልጆቹ አሁን ቤተ ክርስቲያኑን መልቀቅ አለባቸው። ምክንያቱም ትላልቆቹ ለዋናው ፕሮግራም መምጣት ጀምረው ነበረ።

ያዕቆብ ተስፋ ቆረጠ። ልጆቹ ዐርፈው በጸጥታ አልተቀመጡም። አልሰሙትም። ሕፃናት እያለቀሱ ሁሉን ይረብሹ ነበር። ያዕቆብ ወደ ሽማግሌዎቹና ወደ መጋቢው ሄዶ ከዛሬ ወዲህ የሰንበት ትምህርት አላስተምርም ብሎ ችግሩን ተናገረ።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፦ ይህ የሰንበት ትምህርት ቤት ደካማ የሆነው ለምንድን ነው? በእንዲህ ዓይነቱ የሰንበት ትምህርት ውስጥ ያያችኋቸውን ደካማ ነጥቦች ዘርዝራችሁ ጻፉ። |

2. የሰንበት ትምህርት ቤት ዓላማዎች

ስለ ሰንበት ትምህርት ቤት ማጥናት ከመጀመራችን በፊት፥ የሰንበት ትምህርት ቤት ዓላማዎችን ማሰብ አለብን። በሰንበት ትምህርት ቤቱ አማካኝነት ልንፈጽመው የምንፈልገው ምንድን ነው? ከግብ እንድንደርስ የፈለግን እንደሆነ ለሰንበት ትምህርት ቤታችን ግልጽ የሆነ ዓላማ መወሰን ያስፈልገናል።

ሀ. የሰንበት ትምህርት ቤት *መሠረታዊ* ዓላማ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ማስተማር ነው።

ለልጆች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች ማስተማርና ለየዕለቱ ሕይወታቸው የሚሰጠው ትርጉም እንዲገባቸው መርዳት ይኖርብናል።

ለ. እያንዳንዱ ልጅ ኢየሱስ የሕይወቱ አዳኝ እንደሆነ ማወቅ አለበት።

ማቴዎስ 18፡6 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል። «በእኔም ከሚያምኑት ከነዚህ ከታናናሾቹ» ትንሽ ልጅ በኢየሱስ ሊያምን ይችላልን? በስንት ዓመቱ? በ10፥ በ12 ወይም በ6 ልትሉ ትችላላችሁ። ሁሉም መልስ ትክክል ነው። ትናንሽ ልጆች የመዳንን መንገድ እውነት በአግባቡ ከተማሩ (ይህንን እንደገና እንነጋገርበታለን) መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ውስጥ ስለሚሠራ ገና በለጋ ዕድሜ እንኳን ጌታን በማወቅ ለመቀበል ይችላሉ። ከማቴዎስ 18፡14 ላይ አንድ ትንሽ ልጅ ብቻ እንኳን እንዲጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይደለ እናነባለን። ስለዚህ ልናስተምራቸው እናም ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ለመዳን እንዲደርሱ ወደዚያ እውቀት ልንመራቸው ያስፈልጋል።

ሐ) ማንኛውም ልጅ ሕይወቱን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት ይኖርበታል።

ጌታ በማንም ሰው ሕይወት ውስጥ እውነተኛ ሥራውን እንዲሠራ ሰውዬው ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ መስጠት አለበት። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች ለመታዘዝ መሻት አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግም ይናፍቃል። ግን በሚለወጥበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰውዬው ሕይወት ውስጥ በመግባት አዲስ ያደርገዋል። በኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ብሎም እግዚአብሔርን በማስደሰት እንዲኖር አሸናፊ ኃይል ይሰጠዋል።

መ. ልጁ በእምነቱ እየጠነከረ ማደግ አለበት።

አንድ ሕፃን በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ወላጆቹ በጥሩ ሁኔታ ሲያድግ እና ሲጠነክር ደስ ይላቸዋል። አንድ ልጅ ወይም ጎልማሳ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ከሆነ፥ በፍቅርና እርሱን በማወቅ ሲያድጉ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ይህ ሊሆን የሚችለው አንድ ሰው ደኅንነት ምን እንደሆነ እንዲረዳ ከሚሰጠው ትምህርት የተነሣ ብቻ ነው። የክርስትና ሕይወትን እንዴት እንደሚኖሩ መመሪያ ያስፈልጋቸዋል።

ምሳሌ 22፡6 እንዲህ ይላል። «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም»። ሕፃን ልጅ መብላት፥ መጠጣት እና የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልገዋል። እንዲሁም የሚያድጉ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ምግብና መጠጥ እንዲሁም የሰውነት እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይገባል። የሚያስፈልጋቸው የምግብ ዓይነት የእግዚአብሔር ቃል ነው። የሚያስፈልጋቸው እንቅስቃሴ በክርስቶስ ስላላቸው እምነት ለሌሎች መናገር ነው። ከዚያም በጥንካሬ ያድጋሉ።

ልጆች በክርስትና ሕይወታቸው ሲያድጉ ከመዘምራን ቡድን ጋር ለመዘመር፥ የጸሎት ፕሮግራሞችን ለመካፈል ብሎም አገልግሎትን ለመርዳት ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ይፈልጋሉ። በሥራ ውስጥ በመሳተፍ እንዲረዱ ሊበረታቱ ይገባል። ውኃ በማምጣት፥ ቤተ ክርስቲያን በማጽዳት፥ ወንበሮችንና አግዳሚ ወንበሮችን በማንጓጓዝ እያደጉ በሄዱ መጠን የታመሙትን በመጠየቅ፥ እንጨት በመፍለጥ ብሎም ምግብ ለእነርሱ በመውሰድ ሊረዱ ይችላሉ። ብዙ ኃይል ስላላቸው እንደየችሎታቸው የቤተ ክርስቲያንን ሥራ በማገዝ ሊረዱ ይችላሉ። ይህም ደስ ያሰኛቸዋል።

---

16ኛ ጥያቄ፡— የሰንበት ትምህርት ቤትን ዓላማ ጻፉ። አስቡባቸው። ከዚያም በኋላ ቤተ ክርስቲያናችሁ በሚሰጥ የልጆች ትምህርት ከነዚህ ዓላማዎች ውስጥ የትኞች እንደተካተቱ በማስመር አመልክቱ።

---

3. በሚገባ የተደራጀ የሰንበት ትምህርት

እስቲ የተደራጀ የሰንበት ትምህርት ቤት ወዳላት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጎራ እንበል። ቀድመን መድረስ ነበረብንና የደረስነው ጠዋት 2፡30 ላይ ነው። ነገር ግን አስተማሪዎች በሙሉ በዚያ ነበሩ። ከእነርሱ አንዱ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጥቁር ሠሌዳው ላይ እየጻፈ ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ ልጆቹ ትምህርቱ እንዲገባቸው የሚረዳ ሥዕል እየሰቀለ ነበር። ሌሎች ደግሞ የትምህርት መርጃዎቻቸውን ከሳጥኑ ውስጥ በማውጣት ወደየክፍላቸው ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር። እያንዳንዱ ለትምህርቱ እየተዘጋጁ ነበር።

ከዚያም ልጆቹ ከመምጣታቸው በፊት ለጥቂት ደቂቃዎች ጸሎት ያደርጋሉ። ለሦስት ሰዓት አምስት ደቂቃ ጉዳይ አካባቢ ሲሆን አስተማሪዎች ልጆቹን ለመቀበል ወደ ውጪ ወጡ። ይህ የእሑድ የሰንበት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ልጆቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለትና ከልጆቹ ጋር ጥቂት ለመጫወት ዕድል ይሰጣቸዋል።

አስተማሪዎቹ ከተማሪዎቻቸው ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት በሥርዓትና በጸጥታ ሆነው በየክፍላቸው ይቀመጣሉ። ለእያንዳንዱ ሰው በቂ መቀመጫ እንዳለም ያረጋግጣሉ።

የሰንበት ትምህርት በመዝሙር ይጀምራል። ልጆቻቸው መዝሙሩን በቃላቸው ስለሚያውቁ ብቻቸውን በደስታ መዘመር ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ መዝሙሩን በእንቅስቃሴ ይዘምሩታል። መዝሙሩ ላይ ያለውን ቃል ትርጉም በምልክት እየገለጡ ማለት ነው።

ከዚያም መሪው ልጆቹ የጸሎት ጥያቄ እንዳላቸው ይጠይቃቸዋል። አንዱ ልጅ እንዲህ ይላል፤ «እስቲ እግዚአብሔርን ምድሪቱን ለማደስ ስለሚያዘንበው ዝናብ እናመስግነው»። ሌላው ደግሞ፥ «አባቴ ታምሞ በሆስፒታል ተኝቷል፥ እባካችሁ ጸልዩለት»። ትንሿ ሴት ልጅ ደግሞ፥ «እናቴ በዚህ ሳምንት ልጅ ወልዳለች፤ ከእኛ ጋር ጌታን አመስግኑ»። ከዚያም መሪው በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ እና እርሱ በሚጨምራቸው ላይ ይጸልያል።

ዛሬ አንዱ አስተማሪ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ለማስታወስ ጥያቄዎችን አዘጋጅቷል። ጥያቄዎችን እንዲሁ ከመጠየቅ ቡድኑን ለሁለት ከፍሎ በየተራ እየጠየቀ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ነጥባቸውን በመያዝ ማን እንደሚያሸንፍ ይጠብቃል። ልጆቹ እንደዚህ ዓይነት ጨዋታ ይወዳሉ። ወዲያውም ትምህርታቸውን ይከልሳሉ።

ከዚያ በኋላ መባ ይሰበሰባሉ። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ልጆች የራሳቸውን መባ እንዲያመጡ ይበረታታሉ። ይህ የሰንበት ትምህርት ቤቱን መርጃ ዕቃዎች ለመግዛት ይጠቅማል፤ በተጨማሪም ለወንጌላውያን ገንዘብን ለመስጠት ይጠቅማል። መባውን የሚሰበስቡት ሕፃናቱ ራሳቸው ናቸው። ይህ ለእነርሱ መልካም ሥልጠና ነው።

ቀጥሎም አንዳንድ አዝማቾች ከዘመሩ በኋላ ወደየክፍሎቻቸው ይሄዳሉ። ይህም እንደየዕድሜያቸውና እንደየክፍል ደረጃቸው ነው። እያንዳንዱ አስተማሪ ክፍላቸውን አዘጋጅቶላቸዋል። አንዳንዶቹ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለሁሉም የሚበቃ ቦታ ስለሌላት በጥላ ሥር ይማራሉ። ሌሎች ደግሞ በቤት ውስጥ ይማራሉ። እያንዳንዱ አስተማሪ እንደየተማሪዎቹ ችሎታ ያስተምራል። እያንዳንዳቸው ልዩ የሆነ ሥልጠና ስለወሰዱ የልጆቹን ትኩረት መሳብ ይችላሉ። ምክንያቱም የዕድሜያቸውን ባሕርይ በሚገባ ይረዳሉ።

የሰንበት ትምህርት ቤት ዋና አካል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱ ነው። የሰንበት ትምህርት አስተማሪው በጥንቃቄ የተዘጋጀው እንዲሁም በተለያዩ ክፍሎች በትምህርት ጊዜ የሚያስተምረው ለዚህ ነው።

በመጨረሻም አስተማሪው ስም ጠርቶ ማስታወቂያ ከተናገረ በኋላ በጸሎት ይዘጋል። ጊዜ ከተረፋቸው ተጨማሪ አዝማቾች መዘመር ይችላሉ። ከዚያም ልጆቹ ወደ ቤታቸው መጓዝ ወይም ወደ ዋናው የአምልኮ ፕሮግራም መሄድ ይፈቀድላቸዋል።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- በሁለተኛው የሰንበት ትምህርት ቤት ያየሃቸውን ጥሩ ነጥቦች ጻፍ። ልጆች እዚህ ትምህርት ቤት መማር የሚፈልጉባቸውን ሦስት ምክንያቶች ጻፍ። |

## አራተኛ ቀን፦ አስተማሪውና ተማሪው

የሰንበት ትምህርት ቤት ዓላማዎችን ታስታውሳለህን? እንከልሳቸው።

- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶችን ለማስተማር
- ልጆች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ እንዲያውቁ
- እራሳቸውን ለእርሱ ጌትነትና አዛዥነት እንዲሰጡ እና
- በክርስትና ሕይወት እንዲያድጉ ነው።

እነዚህን ዓላማዎችን ለመፈጸም አስተማሪው ስለ ተማሪዎቹ የተለያዩ ነገሮችን ማወቁ አስፈላጊ ነው።

1. ተማሪዎችን በግል ማወቅ አለበት።

አስተማሪው እያንዳንዱን ተማሪ በግል ማወቅ ያስፈልገዋል። የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎቻችንን በቁጥር አንጠራቸውም። እነርሱ ጌታ የሚወዳቸው ትንንሽ ሰዎች ስለሆኑ ስማቸውን ለማወቅ፥ ስለ ቤተሰባቸው አንዳንድ ነገሮች ለመረዳት እንዲሁም የሚወድዱት ወይም የሚጠሉት ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ መውሰድ አለብን። ስንተኛ ክፍል እንደሚማሩ፥ የት ትምህርት ቤት እንደሚማሩ፥ እንዲሁም በትምህርታቸው ምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማወቅ አለብን።

አስተማሪው የተማሪውን ቤት ሊጎበኝ ይችላል። ቤተሰቦቹን ሊተዋወቅ እንዲሁም ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይመጡም ከሆነ እንዲመጡ ሊጋብዛቸው ይችላል። ተማሪዎችን ወደ ቤቱ ሊጠራቸው ወይም ምሳ ሊጋብዛቸው ይችላል።

አስተማሪው የተማሪው ፍላጎት ምን እንደሆነ ማወቅ አለበት። እግር ኳስ፥ የእጅ ኳስ፥ ወይስ ውኃ ዋና ነው መጫወት የሚፈልገው? ሁልጊዜ የሚያደርጋቸው ነገሮች አሉን? ሥዕል ይሥላል? ግጥም ይጽፋል? በመዘምራን ቡድን ይዘምራል? መጻሕፍት ማንበብስ ይወዳል?

---

18ኛ ጥያቄ፦ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ከሆንህ በክፍልህ ውስጥ ስንት ልጆች ነበሩ? የእያንዳንዱን ስም አጥንተኸው ነበርን? ወላጆቻቸውን እንዴት ልታውቃቸው ቻልህ? በቤትህ ወይም በእነርሱ ቤት አብረሃቸው ምን ያህል ጊዜ ታጠፋለህ?

---

2. የልጆቹን ፍላጎት ማወቅ አለበት።

ልጆች ይሰርቃሉ፤ ይዋሻሉ፤ በትምህርት ቤት ያታልላሉ። የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸውን ይደበድባሉ። ለወላጆቻቸው አንታዘዝም ይላሉ። ብዙ ጊዜ ይፈራሉ። ስለሆነም ብዙ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። አስተማሪው ልጆችን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና ለክርስቶስ እንዲኖሩ ለማድረግ ትምህርቱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ማሰብ አለበት።

ልጆች ሊያዝኑ ይችላሉ። እስቲ አባቱ ስለሞተበትና እናቱ እርሱን ትምህርት ቤት ለመላክ ምንም ገንዘብ ስለሌላት መጽሐፍና ደብተር ልትገዛለት ስለማትችል ትንሽ ልጅ አስብ። ሌሎች ልጆች አዲስ ልብስ ለብሰውና ደብተሮች በቦርሳቸው ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ሲያይ

ምን ይሰማዋል? እንደዚህ ዓይነቱ ልጅ መጽናናት ይፈልጋል። ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንዲችል አስተማሪው ሊረዳው ይችል ይሆናል። እንዲሁም ተስፋ የሚቆርጥበትን ጊዜ ጨምሮ በሁሉም ጊዜ አብሮት የሚቆየውን ኢየሱስን ማወቅ ያስፈልገዋል። ልጆች ብዙ ፍላጎቶች አሉአቸው። መምህሩ እነዚህን ሁሉ ማሰብና በትምህርቱና በወዳጅነቱ ልጆቹ ለችግራቸው ከክርስቶስ መልስ ማግኘትን እንዲማሩ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ልጆችን ፍላጎት ዘርዝር። እነዚያን ፍላጎቶች በትምህርትህ ለመድረስ የምትችለው እንዴት ነው? |

3. መምህሩ የልጆቹን ባሕርይ ማወቅ አለበት።

ልጆች በተለያዩ ዕድሜዎች የተለያዩ ባሕርያት ስላሏቸው መምህሩ በተሳካ መንገድ ለማስተማር ከፈለገ እነዚህን ልዩነቶች ማወቅ ያስፈልገዋል። ልጆቹን በተለያዩ ክፍሎች መከፋፈል ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው። እያንዳንዱ ቡድን እንደየችሎታቸውና እንደ ትምህርት አቀባበሉ ሂደት ሊማር ይችላል። የልጆችን ባሕርይ በጥልቀት ስለምናጠና በሚገባ ታውቋቸዋላችሁ።

4. መምህሩ ተማሪዎቹ እንዴት እንደሚማሩ ማወቅ አለበት።

ሀ/ ልጆች መስማት ይወዳሉ። መሰማት የሚችል ነገር እንዲኖረው መምህሩ በሚገባ መዘጋጀቱ ዋና ነገር ነው። ልጆቹ እንዲሰሙት ጮክ ብሎ መናገር አለበት። ልጆቹ የሚረዱትን ቃላት መጠቀም አለበት። ከረጅም ዓረፍተ ነገሮች አጫጭሮቹን መምረጥ ይኖርበታል።

ለ/ ልጆች በማየትም ይማራሉ። ልጆች አንድ ነገር ማየት ከቻሉ ረዘም ላለ ጊዜ ሊያስታውሱት ይችላሉ። ስለዚህ ልጆች ማስታወስ እንዲችሉ መምህሩ ሥዕሎችን፥ ሞዴሎችን፥ መርጃ መሣሪያዎችን እና የራሱን እንቅስቃሴ እንኳን መጠቀም አለበት።

ሐ. ልጆች በንግግር ይማራሉ። መልካም አስተማሪ ተማሪዎቹ እንዲናገሩ ብዙ ዕድል ይሰጣል። ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ተማሪዎቹ የመሰላቸውን እንዲናገሩ ያበረታታል። ውይይትን ከፍ ላሉ ልጆች መጠቀም ይቻላል።

መ. ልጆች በተግባር ይማራሉ። ከጥሩ ትምህርት በኋላ አስተማሪው ለልጆቹ የትወና ድርሻ በመስጠት ታሪኩን በድራማ መልክ እንዲያቀርቡት ሊያደርጋቸው ይችላል። ስለ ትምህርቱ ሥዕሎችን ሊሥሉ ይችላሉ። አስተማሪው ላዘጋጃቸው ጥያቄዎች በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልስ መስጠት ይችላሉ። ጥቁር ሠሌዳ ላይ በመጻፍ ሊረዱ ይችላሉ።

የሚሰማ፥ የሚያይ፥ የሚናገርና የሚሠራ፥ ተማሪ ከተማረው ብዙውን ነገር ያስታውሳል። ልጆች በሚማሩበት ጊዜ

- በመስማት ብቻ 10 %

- በመስማትና በማየት 60 %

- በመስማት፥ በማየትና በመናገር 70 %

- በመስማት፥ በማየት፥ በመናገርና በማድረግ 90% እንደሚማሩ ተደርሶበታል።

ስለዚህ ለልጆቹ ከመናገር የበለጠ ነገር ማድረጉ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ልታዩ ትችላላችሁ። ያዕቆብ ትምህርቱን በማንበብ ብቻ በማቅረቡ የሚሰማው አላገኘም።

---

20ኛ ጥያቄ፡- ልጅ የሚማርባቸውን ሦስት መንገዶች ጻፍ። ተማሪውን ከላይ በተጠቀሱት የመማሪያ መንገዶች ሁሉ ይማር ዘንድ ልትረዳ የምትችልባቸውን መንገዶች ጥቀስ።

---

5. አስተማሪው አንድን ተማሪ እንዴት ወደ ጌታ እንደሚመራ ማወቅ አለበት።

የትምህርት አራትን አንደኛ ቀን ትምህርት እንደገና አንብብ። ልክ አስተማሪው ዳግመኛ መወለድ እንደሚያስፈልገው እያንዳንዱ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ መቀበል አለበት። ልጁን ወደ ክርስቶስ ለመምራት አስተማሪው ማወቅ ያለባቸው ዋና ነገሮች አሉ። እነዚህን ትምህርቶች ለልጆች በታማኝነት መስጠት አለበት። በልጆቹ ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሲሠራና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያስፈልጋቸው ሲያውቁ ወደ እናንተ መጥተው እንዲያምኑ እንድትረዱአቸው ይጠይቋችኋል። ልጆችን በፍጹም ማስገደድ የለብንም። ምክንያቱም አስተማሪውን ማስደሰት ስለሚፈልጉ ብቻ ማስገደድን በቀላሉ ሊቀበሉ ይችላሉ። ማመን የሚፈልጉት አስተማሪው እንዲያምኑ ስላበረታታቸው ነው። ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን በአስተማራችሁት ትምህርት መሠረት በልባቸው ውስጥ እስኪሠራ መጠበቅ በጣም የተሻለ ነገር ነው። ያን ጊዜ ጌታን በእውነት እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል የተዘጋጁ ይሆናሉ።

ቤተ ክርስቲያኖቻችን እጆቻቸውን ከፍ አድርገው ሰይጣንን ባወገዙና ክርስቶስን ተቀብለናል በሚሉ ሰዎች የተሞሉ ናቸው። እነዚህ ወገኖች ለምን ይህን ውሳኔ እንዳሳለፉ የማያውቁና ዳግም ያልተወለዱ የአፍ ክርስቲያኖች ናቸው። በጣም መጠንቀቅ አለብን።

አንድ ልጅ ጌታን እንዲቀበልና እንዲድን ቢያንስ አምስት ነገሮችን መረዳት አለበት።

ሀ) እግዚአብሔር ይወደዋል (ዮሐንስ 3፡16)

ለ) ኃጢአተኛ ነው (ሮሜ 3፡23)

ሐ) ስለ ኃጢአቱ ኢየሱስ ሞቶለታል (ሮሜ 5፡8)

መ) ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያድነው ማመን አለበት (ሉቃስ 16)

ሠ) ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ መቀበል አለበት (ዮሐንስ 1፡12)

በምናስተምርበት ጊዜ ሁሉ ከእነዚህ ነጥቦች አንዳንዶቹን መጨመር አለብን። እናም አንድ ልጅ ጌታን ለመቀበል ከፈለገ እንደገና እነዚህን ነጥቦች

ከእርሱ ጋር አብረን እናያቸዋለን ማለት ነው። ይህንን ጸሎት ከእናንተ በኋላ እንዲጸልይ ጠይቃችሁት መጸለይ ትችላላችሁ።

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ እንደሆንሁ አውቄያለሁ። ከኃጢአት እንድታድነኝም እፈልጋለሁ። በመስቀል ሞተህ የኃጢአት ቅጣቴን እንደወሰድህ አምናለሁ። እባክህ ወደኔ ና። በልቤም ውስጥ ኑር። ለአንተ ለመታዘዝ እና የሕይወቴ ጌታ ላደርግህ ዝግጁ ነኝ አሜን።»

ከዚህ ጸሎት በኋላ አሁን እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማውጣት ልታሳዩት ይገባል (ዮሐ. 1፡12፤ 10፡29–30)። ለክርስቲያኖች መዳኑን እንዲናገር አበረታቱት። ወደ ቤተ ክርስቲያን ጋብዙት። ሊያበረታቱት የሚችሉ ክርስቲያን ጓደኞች እንዲኖሩትም እርዱት።

ወዲያውኑ ተከታታይ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እንዲኖረው እና መጸለይ እንዲጀምር ልትረዱት ይገባል። ልክ ሕፃን ልጅ ቀስ በቀስ መሄድ እንደሚለማመድ የክርስቲያን ሕይወትን እንዲኖር ልትመሩት ትችላላችሁ።

> 21ኛ ጥያቄ፡– አስተማሪው ስለ ተማሪዎቹ ማወቅ ያለባቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝሩ። ከዚህ በፊት አንድን ሰው እንዴት ወደ ጌታ እንዳመጣችሁ ጻፉ።

**አምስተኛ ቀን፡–** በአምስተኛ ትምህርት ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ ከልሱ። በሳምንታዊው ስብሰባ ላይ ለውይይት የተዘጋጁትን ርእሶች ተመልከታችሁ በስብሰባው ላይ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ተዘጋጁ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለሳምንታዊ ስብሰባ የተለመደውን አሠራር ተከተሉ። ለጥሞና ጊዜ አንድ ተማሪ ወይም የስብሰባ መሪ ከርእሱ ጋር የሚስማማ አጭር መልእክት እንዲያዘጋጅ አድርጉ።

### የመወያያ ጥያቄዎች።

1. ልጆችን ማስተማር ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ከቡድኑ ጋር ተነጋገሩ። የልጆች አስተማሪ መሆን ያለበት ማን ነው? በኅብረተሰባችሁ ውስጥ አባቶች ኃላፊነታቸውን ይወጣሉን?
2. በኅብረተሰባችሁና በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አግባብ ያለው ትምህርት ለልጆች ያለመስጠት ውጤት በሆኑ ነገሮች ላይ ተወያዩ። በቤተ ክርስቲያናችሁ በሚገኙ ልጆች ላይ የምታዩአቸው መጥፎ ዝንባሌዎች ምንድን ናቸው? አግባብ ያለው ትምህርት እና ቅጣት እነዚህን ዝንባሌዎች ሊያርማቸው ይችላልን? እንዴት?
3. በሦስተኛ ቀን የተጠቀሱት ሁለት ዓይነት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ ተወያዩባቸው። የናንተን ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት የሚመስለው የትኛው ነው?
4. አስተማሪው ስለ ተማሪዎቹ ሊያውቃቸው የሚገባቸው አምስት ነገሮች? እያንዳንዱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

# ትምህርት ስድስት

## የልጆች ባሕርያት በዕድሜ ክልል

### 1ኛ ቀን፦ መዋዕለ ሕፃናትን ማስተማር

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለት መጨረሻ እንዲህ ይላል፦ «ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር»። በእውቀት፥ በአካል፥ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ መስክ አድጓል። ለኢየሱስ በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ማደግ አስፈላጊ ከነበረ የእኛም ልጆች እንዲሁ እንዲያድጉ በጣም አስፈላጊ ነው።

ባለፈው ትምህርት እንደተጠቀሰው እኛም «ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም» (ምሳ 22፡6) የሚለውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ አለብን። እነዚህ የተመሠረቱት ጥሩ መሠረቶች ልጅን በሕይወቱ ሁሉ ይመሩታል።

ከዓለም ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሕፃናትና ወጣቶች እንደሆኑ ታውቃለህን? በምናስተምርበት ክፍል ውስጥ ያሉት ልጆች ሲያድጉ ምን እንደሚሆኑ አናውቅም። አንዳንዶቹ መጋቢ፥ ወንጌላውያን፥ የመንግሥት ሠራተኞች፥ ወታደሮች፥ ፖሊሶች፥ መምህራን ይሆናሉ። ወደፊት በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በአገር ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያደርጋሉ። ያን ጊዜ የሚያደርጉት ተጽዕኖ የሚደገፈው ዛሬ በምናስተምራቸው ነገር ላይ ይሆናል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአሜሪካ አንድ ጥናት ተደርጎ ነበር። ይኸውም «አንዳንድ ልጆች ጨዋ፤ ደግ እና ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ ሆነው ሲያድጉ አንዳንዶች ደግሞ የማይገዙ ዓመፀኞች እና ሕግን ባለማክበር ችግር ውስጥ የሚገቡ የሆኑት ለምንድን ነው?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነበር። ከልጆች ጋር ከተደረገው ቃለ ምልልስ ከሚከተለው ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

- መጥፎ ልጆች የሆኑት ከወላጆቻቸው ወይም ከአስተማሪዎቻቸው ምንም ፍቅር ያላዩ ናቸው። የተጣሉና በምሬት ያደጉ ነበሩ።

- ጥሩ ልጆች የሆኑት ደግሞ በወላጆቻቸው የተወደዱ፥ ፍቅር ያጠመዳቸውና ልባቸውን በዚህ የጠበቁ ናቸው።

በሁሉም የዕድሜ ክልል ልጆች እንዲወዱዱና የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ በጣም አስፈላጊ ነው። ዘዳ 31፡11-13፤ ማር 9፡33-37፤ 10፡13-16። ኢየሱስ ልጆችን በእርግጥ ይወድድ ነበር። ወደ እርሱም እንዳይመጡ አይከለክላቸውም ነበር። ልጆችን በጥንቃቄ በማስተማር ዝግጁ በሚሆኑበት ጊዜ ወደ ጌታ ለመምራት እንትጋ።

1. የተለያዩ የዕድሜ ክልሎች ባሕርያትን የመረዳት አስፈላጊነት

ሀ) የእያንዳንዱን ዕድሜ ክልል የአካል፥ የአእምሮ፥ የስሜት፥ የማኅበራዊና መንፈሳዊ ዕድገት በይበልጥ እንረዳለን።

ለ) በችሎታቸው መጠን በይበልጥ መምራት እንችላለን።

ሐ) ትምህርታችንን ለሚያስፈልጓቸው ነገሮች በሚስማማ መንገድ ማዘጋጀት እንችላለን።

መ) ራሳችንን ለተማሪዎች እንዴት እንደምናቀርብ ይበልጥ እናውቃለን።

2. ከተወለዱ እስከ ሁለት ዓመት ያሉ ልጆች ባሕርያት

ልክ የቤት መሠረት የቤቱን ዘላቂነት እንደሚወስን ሁሉ በሕይወትም የተጣለ መሠረት ጠቅላላ የሕይወትን ባሕርያትና አቅጣጫ ይወስናል። አንድ ልጅ መማር የሚጀምረው መቼ ነው? መልሱ «በተወለደበት ደቂቃ መማር ይጀምራል» ነው። የመጀመሪያዎቹን ሁለት ዓመታት ያህል በሕፃኑ ዕድሜ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ጊዜ የለም። ሕፃኑ ከሌላው የሕይወቱ ጊዜ ይልቅ በይበልጥ በዚህ ወቅት ብዙ ይማራል። ሆኖም ግን ብዙ ጊዜ ሕፃን ልጅ ምንም አያውቅም እንላለን። አንድ ነገር እናስታውስ፤ የርሱ አእምሮ ልክ እንደ ነጭ ወረቀት የጠራና ንጹሕ ነው። በዚያ ወረቀት ላይ ምን እንደምንጽፍ ልንጠንቀቅ ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ፕርግራም በሕፃኑ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው።

ሀ. አካላዊ እድገት፡- በሕይወቱ አንደኛ ዓመት ዕድሜው ሲወለድ ከነበረው ክብደት በሦስት እጥፍ ይጨምራል። በቁመቱም በእጥፍ ያድጋል። ይህ ማለት በሰውነቱ መጠን በክብደቱም ሆነ በቁመቱ ላይ ትልቅ ለውጥ ያሳያል። በዚህ ደረጃ ላይ የሕፃኑ ትላልቅ ጅማቶች (ጡንቻዎቹ) ያድጋሉ። መራመድ ይጀምራል። ሆኖም ትምህርት ቤት እስኪገባ ትንንሽ ጡንቻዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለማያድጉ ከባድ ሥራዎችን ለመሥራት አስቸጋሪ ይሆንበታል። መራመድ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በኋላ በጣም ንቁና ተንቀሳቃሽ ነው።

ለ. የአእምሮ ዕድገት፡- ከተወለደ ጀምሮ በዙሪያው የሚሆነውን ነገር ሁሉ ያዳምጥ ስለነበረ አንዳንድ ቃላትን ማለት ይጀምራል። (በተለይ ስሞችንና እና ግሦችን) እናም በሁለት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቀላል ዐረፍተ ነገሮችን በትክክል ማገጣጠም ይችላል። ምንም እንኳን በአንዳንዶች ላይ ችግር ቢኖረውም የቃላትን ድምፅ በትክክል ማውጣትን ይማራል። የማስተዋል ወይም ነገሮችን በአትኩሮት የመከተል ችሎታው በእያንዳንዱ የዕድሜው ዓመት አንድ ደቂቃ ነው። አንድ ሕፃን ማገናዘብ ወይም ምክንያቶችን መስጠት አይችልም። ነገሮችን የሚያስበው በሚዳስሰውና በሚሰማው ነገር ላይ ተመሥርቶ ነው።

ሐ) ማኅበራዊ ዕድገት፡- በዚህ ደረጃ ሕፃኑ ስለ ሌሎች እምብዛም የማይገደው ሲሆን፥ ዓለሙ በእኔነት የተቆለፈ ነው። ብቻውን ይጫወታል። ምናልባት ሌሎች ልጆች እንደሚያደርጉት ሊያደርግ ይፈልግ ይሆናል። ነገር ግን ራሱ ብቻውን ሊያደርግ ይፈልጋል። በትንንሽ አሻንጉሊቶች መጫወት በጣም ያስደስተዋል።

መ) ስሜታዊነት፡- እንግዳ ሰዎችን ይፈራ ይሆናል። የለመደውንና የሚያውቀውን አካባቢ ይፈልጋል።

ሠ) መንፈሳዊ ዕድገት፡- በዚህ ደረጃ ብዙውን ጊዜ ሕፃን ከሚያየው ከሚሰማው እና ከሚዳስሰው ነገር ይማራል። ፍቅርንና ተቀባይነትን ይፈልጋል። ፈጣሪንና ፍጥረትን ማድነቅ ይጀምራል።

እነዚህን ትንንሽ ልጆች ምን ልናስተምራቸው እንችላለን?

- መዝሙሮችን ይወዳሉ። ብዙ ዘምሩላቸው። መዘመርን እንዲሞክሩም አድርጉ።

- እንዴት መጸለይ እንዳለባቸውም መማር ይችላሉ። አዋቂዎች በምግብ ጊዜም ሆነ ወደ መኝታ ከመሄዳቸው በፊት ሲጸልዩ እጆቻቸውን ሊያጣምሩና አንገቶቻቸውን ዝቅ ሊያደርጉ ይችላሉ።

- ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና እንክብካቤ አስተምሯቸው።

- ስለ እግዚአብሔር ፍጥረታት አስተምሯቸው።

- ትንሽ ሕፃን ሆኖ ስለተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯቸው።

- ቀለል ያሉ ታሪኮችን ለማስረዳት ቀላል ሥዕሎችን ለማብራሪያነት ተጠቀሙ።

እነዚህን ትናንሽ ልጆች ማስተማር በግዴለሽነት መታየት የለበትም። «አንድ ዛፍ የሚያድገው በዘመመበት አቅጣጫ ነው» የሚለው አባባል ትክክለኛ ነው። እነዚህን ትናንሾች ልጆች በማስተማር ወላጆቻቸውንም ልንደርስ እንችላለን። ገና ድክ ድክ የሚሉ ሕፃናትን የሚጨምር የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ቢታቀድ እናቶችም ፕሮግራሙን ለመካፈል እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ይህም እናቶች አገልግሎት ላይ በመገኘት ጌታን እንዲያውቁ ወይም በክርስትና ሕይወታቸው እንዲጠነክሩ ይረዳቸዋል።

22ኛ ጥያቄ፡- አንድ የምታውቀውንና ዕድሜው ከሁለት ዓመት በታች የሆነ ሕፃን አስብ። ከላይ የተዘረዘሩትን ባሕርያት ከልጁ ጋር አወዳድርና አስፈላጊ ነው ብለህ የምታምነውን ነጥብ ጨምርበት።

3. ከሁለት እስከ አራት ዓመት።

ሀ. አካላዊ ዕድገት፡- ሁለተኛ ዓመቱ ላይ ሕፃኑ ሚዛኑን የመጠበቅ ችሎታው ደካማ ነው። አልፎ አልፎ ይወድቃል ይነሣል። በጣም ንቁ ተንቀሳቃሽ ነው። ማደጉ ይቀጥላል። ነገር ግን ፍጥነቱ እንደ መጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት አይሆንም። አንዳንድ ጊዜ ከመንተባተብ በስተቀር ማለት የሚፈልገውን በሙሉ በትክክል ይላል። አሁንም ከሰዓት በኋላ ከ1-2 ሰዓት እና ሌሊት ለ12 ሰዓታት መተኛት ያስፈልገዋል። ሦስት ዓመት ሲሆነው ልብሱን ራሱ መልበስም ሆነ ማውለቅ ይችላል። ነገሮችን መሞከር ሁሉን ነገር መነካካት ይወዳል። ብዙ ጊዜ የሚሰበሩ ነገሮችን ያንኮታኩታቸዋል። ስለሆነም በዚህ ጊዜ ተሰባሪ ነገሮችን ከእርሱ ማራቅ አለብን።

ለ) አእምሮአዊ፡- አእምሮው በጣም የነቃና በጥያቄ የተሞላ ነው። ስለ አካባቢው ሁሉ ማወቅ ይፈልጋል። ስለ ነገሮች ሁኔታ መጠየቅ ይወድዳል። ከአምስት ደቂቃ በላይ ማዳመጥ አይችልም። በቀላሉ ይረሳል። ስለዚህም

የታሪኮች ድግግሞሽ የሚያሰለቻቸው አይመስልም። ይህ ጊዜ ጥሩ የአመጋገብና የመተኛት ልማድ የሚያዳብርበት፥ ሽንቱንና ሰገራውን መቆጣጠር የሚማርበትና አብሮ መኖርን እንኳ የሚያውቅበት ጊዜ ነው።

ሐ) ስሜታዊና ማኅበራዊ፡- በቀላሉ ያለቅሳል። በወላጆቹ ላይ የሚደገፍና የነርሱን ርዳታና መተማመኛ የሚፈልግ ነው። ከሌሎች ጋር ብዙ ይጫወታል። ጎልማሶችን መኮረጅ ይጀምራል። እናም በአብዛኛው የሚጫወተው ትልልቆች የሚያደርጉትን በማድረግ ነው። ሕፃናትንና ሌሎች ትንንሽ ልጆችንም ይወዳል።

መ) መንፈሳዊ፡- ስለ አካባቢው ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ያገኛል። እግዚአብሔር እንደሚወደው፥ እርሱ ዓለምን ሁሉ እንደፈጠረና ጥሩና ታዛዥ ልጅ ይሆን ዘንድ እንደሚፈልግ ማስረዳት ይቻላል።

ምን ልናስተምራቸው እንችላለን?

-እግዚአብሔር እንደሚወደው፥ በዙሪያው ያለውን ዓለም እንደፈጠረ፥ ስለ እርሱ እንደሚጠነቀቅ፥ ሊረዳውም እንደሚፈልግ፥ ሁልጊዜም አብሮት እንዳለ።

- ኢየሱስ እንደሚወደው፥ በጣም የቅርብ ወዳጁና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ

- እናትና አባቱ እንደሚጠነቀቁለትና እንደሚወድዱት

- ወንድሞቹንና እህቶቹን መርዳትና መውደድ እንዳለበት።

- ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መነጋገር እንደሚችል፥ እግዚአብሔርን ሊያስደስተውና የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ እንደሚችል

- ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በጸጥታ መሆን አለበት።

- መዝሙር መዘመር ይወዳል፥ እናም በመረዳት መጸለይ መጀመር ይችላል።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ ትንንሾች ልጆች ሊሰሟቸውና ሊማሯቸው ይችላሉ ብለህ የምታስባቸውን አምስት መዝሙሮች ጻፍ። |

4. የአራትና የአምስት ዓመት ዕድሜ

በእነዚህ የመሠራት ዓመታት ልጆች ስለ ራሳቸው መልካም አመለካከት ማዳበር የሚችሉበት የተወሰነ ነፃነትን የሚለማመዱበት፥ ለእኩዮቻቸውና ለታላላቆች ጤናማ የሆነ አመለካከት የሚያሳድጉበት ጊዜ ይመጣል። ይህም ተቀባይነትን የማግኘት ስሜትንና ራስን የመግዛት መለኪያን ይጨምራል።

ከእነርሱ ጋር ባለን ነገር ሊታመኑብን እንዲችሉ በማድረግ ልናበረታታቸው ያስፈልጋል። ፈጽሞ ውሸት ልንነግራቸው አይገባም። ልናስፈራራቸው ወይም ደግሞ ልንቀልድባቸው አይገባም። ልጆች ስለማይገባቸው ግራ ሊጋቡ ይችላሉ። በእኛ መተማመን እንዲችሉ ከተማሩ በእግዚአብሔር መታመንንም ሊማሩ ይችላሉ።

እያደጉ በሄዱ ቁጥር ነፃነትን እየተማሩ ይሄዳሉ። እነርሱ ለራሳቸው ማድረግ የሚችሉአቸውን ነገሮች ልንሠራላቸው አያስፈልግም። እያደጉ ሲሄዱ ራሳቸውን መመገብ፥ ልብሳቸውን መልበስ፥ በትናንሽ ሥራ መርዳት ይችላሉ። ይህ ሁሉ ነፃነታቸው እንዲያድግ ይረዳል። ደስተኛ የሆነ መንፈስ እንዲኖራቸው መበረታታትና ምስጋና ያስፈልጋቸዋል።

ራስን ስለ መግዛት ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል። አንድ ነገር በሚሆንበት ጊዜ ያለማቋረጥ ማልቀስ የለባቸውም። ማድረግ የሚፈቀድላቸውንና የማይፈቀድላቸውን ነገር መማር አለባቸው። ወላጆችና መምህራን በሁሉም ጊዜ አንድ ዓይነት እና ጽኑ የሆነ መለኪያን መጠበቅ አለባቸው። አንድ ቀን መፍቀድ ሌላ ቀን ደግሞ መከልከል የለባቸውም። ላለመታዘዝ እንደ ጥፋቱ ተስማሚ የሆነ ቅጣት መስጠት ያስፈልጋል።

የአራትና የአምስት ዓመት ዕድሜ ልጆች ሁሉንም ነገር ለራሳቸው ይፈልጋሉ። ሌሎችን መኮረጅ ይወዳሉ። ሌላውን ሰው አስቀይማለሁ ሳይሉ ሁሉንም ነገር ይደግማሉ። ከሰዎች ጋር መሆን ይወዳሉ፤ እናም በሌሎች መወደድ ይፈልጋሉ፤ በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ዘንድ መፈለግንና ሞገስን ማግኘት ይሻሉ። በሁሉም ነገር ላይ ፍላጎት ያላቸው ሲሆኑ በትናንሽ ነገሮች የሚደነቁ ናቸው። ከሚገባው በላይ በነገሮች የሚሳቡ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ ጊዜ አሁን የተማሩትን በሕይወታቸው ሙሉ አይረሱም። ታላላቆቻቸው የሚናገሩትን ደግሞ በሙሉ ያምናሉ።

ሀ. አካላዊ፡- በዚህ ደረጃ በፍጥነት የሚያድጉ ሲሆን፥ የማያቋርጥ እንቅስቃሴና ጩኸት ይስተዋልባቸዋል። በጸጥታ ሊቀመጡ የሚችሉት ከአምስት እስከ አሥር ደቂቃ ብቻ ነው። ጡንቻዎቻቸው በማደግ ላይ ስለሆኑ በእርሳስ ለመጻፍ ወይም ጥሩ ሥራ ለመሥራት ይፈልጋሉ። ዜማን ተከትለው ለመዘመር የሚጀምሩበት ጊዜ ነው። ከእንቅስቃሴ ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮችን በተለይም የሚያስቆሙትን እና ወዲያና ወዲህ እንዲሉ የሚያደርጓቸውን ይወድዳሉ።

ለ. አእምሯዊ፡- ገና ማንበብ አይችሉም፤ ነገር ግን መስማትን፥ ሥዕሎችን ወይም ቅርፆችን መመልከት እንዲሁም በትምህርት ውስጥ በንቃት መሳተፍን ይወዳሉ። አእምሮአቸው በጣም የነቃ ሆነው በጥያቄዎች የተሞሉ ናቸው።

ሐ. ማኅበራዊ፡- ከሌሎች ልጆች ጋር ለመጫወት ፍላጎት አላቸው። ብዙ ጊዜም ከነርሱ ጋር የሚጫወት ሰው ፍለጋ ይወጣሉ። ማካፈልንና ከሌሎች ጋር መሆንን በተሻለ ሁኔታ እየተማሩ ነው።

መ) ስሜታዊ፡- ብዙ ጊዜ በዚህ የዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ልጆች ጥልቅ የሆኑ ስሜቶች አሏቸው። ለምሳሌ በጣም መደሰት ወይም በጣም ማዘን፥ በጣም መደነቅ ወይም በጣም መቆዘም ይችላሉ። ፍርሃት ያጋጥማቸዋል። ፍቅርንና ጥበቃን እንዲሁም አዎንታዊ አመለካከት ያላቸውንና ደስተኛ የሆኑ ጎልማሶችን ይፈልጋሉ።

ሠ) መንፈሳዊ፡- እነዚህ ልጆች የእግዚአብሔር ታላቅነት፥ ድንቅ ሥራው እና ፍቅሩ ሊሰማቸው ይችላል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አፍቃሪ እና

ተንከባካቢ ጓደኛ ሊያስቡት ይችላሉ። የምንነግራቸውን በሙሉ ስለሚያምኑ የምናስተምራቸው ትምህርት በእውነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ትክክል የሆነና ስሕተት የሆነ ነገርን ማወቅ መጀመር ይችላሉ።

ምን ልናስተምራቸው እንችላለን?

- የሚሰሙትን በሙሉ ስለሚያምኑ እውነትን ማስተማር አለብን።

- ተደናቂና ተገራሚዎች ስለሆኑ ወደ አምልኮ ልንመራቸው እንችላለን።

- መወደድን ስለሚፈልጉ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ልናስተምራቸው እንችላለን።


- ለመማር በጣም የተዘጋጁ ስለሆኑ ወንጌልን ለእነርሱ ለማስረዳት መጀመር እንችላለን።

-እግዚአብሔር ራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደገለጠ ልናስተምራቸው እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ እና የማንበብም ፍላጎት በልባቸው ውስጥ እንዲፈጠር ማድረግ እንችላለን።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- ለአራትና አምስት ዓመት ልጆች የሚሆን የአንድ ሰዓት ፕሮግራም አዘጋጅ። የምታዘምራቸው መዝሙሮች፣ የምታስተምረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና በቃል ሊያጠኑት የሚችሉትን ጥቅስ ያካተተ መሆን ይገባዋል። |

ሁለተኛ ቀን፡- ጀማሪዎችን ማስተማር (ከ6-8 ዓመት)

በዚህ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ ልጆች ሕይወት ገና ያልተነካ ሙሉ ነው። እነዚህን ሦስት ሻማዎች ተመልከቱ።



1 2 3

ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው ያመኑ ሦስት ሰዎችን ይወክላሉ። አንዱ ያረጀ ሰው ነው። ሌላው ደግሞ ገና ሥራ የጀመረ ወጣት ነው። አንደኛው ደግሞ ገና ትንሽ ልጅ ነው። እያንዳንዱ ሻማ የሚወክለው የትኛውን ሰው ይመስልሃል?

1. ከሁሉ ያነሰው የምድር ላይ ዕድሜው ሊያልቅ የተቃረበን ሽማግሌ ሰው ይወክላል። ወደ ሰማይ ቤት ከመጠራቱ በፊት ያለውን የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን ለማብራት ያለው ጊዜ ጥቂት ብቻ ነው።

2. ይኼኛው ደግሞ ትምህርቱን የጨረሰ ወጣት ነው። ገና ሥራ ለመጀመር ተዘጋጅቶአል። ካለው ዕድሜ ጥቂቱን የተጠቀመበት ሲሆን ጌታን ለማገልገልገም በቂ ጊዜ አለው።

3. ረጅሙ ሻማ ትንሹን ልጅ ይወክላል። ምናልባትም ገና የጀማሪ ክፍል ተማሪ ይሆናል። ለኢየሱስ ለመኖር ከፊቱ ገና ረጅም ጊዜ አለው። በጥንቃቄ ካስተማርነውና ለእምነቱ መልካም መሠረትን ከሰጠነው ለብዙ ዓመታት ለጌታ አንጸባራቂ ምስክር ሊሆን ይችላል። በተቃራኒው ወደ ጌታ ካልመራነውና ካላስተማርነው ጠቅላላ ሕይወቱን የጌታ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት ሆኖ ይኖራል። በመጨረሻም ክርስቶስ የለሽ ወደ ሆነ የዘላለም ኑሮ ውስጥ (ገሃነም) ይገባል።

ጀማሪው ልጅ ንቁና በጣም ተንቀሳቃሽ ነው። በግልጽ ይናገራል፥ ከሰዎች ጋር መሆን ያስደስተዋል። እንዲሁም ንባብ እየጀመረ ነው። ማለቂያ የሌለው ኃይል አለው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ይህንን ነገር ምን እንደሚያደርገው ስለማያውቅ የማይሆን ነገር ውስጥ ይገባል። ጥበበኛ የሆነ አስተማሪ በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴን ይፈቅዳል። ነገሮችን ከማቅረብ ይልቅ ልጆቹ ተነሥተው እንዲወስዱ ማድረግ ይመረጣል።

መዝሙር እና ጸሎት በመምራት እንዲሁም መባ በመሰብሰብ አሳትፋቸው። ለጥያቄዎች ቆመው መልስ እንዲሰጡ አድርግ። ከእንቅስቃሴ ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮችን አዘምራቸው። በተቻለ መጠን ብዙ እንቅስቃሴ ያለበት ጊዜ እንዲሆን ዐቅድ። በጸጥታ ዐርፈው መቀመጥ የሚችሉት ከ10-15 ደቂቃ ያህል ብቻ ስለሆነ እና ከዚያ በላይ መቀመጥ ስለማይችሉ፥ በክፍሉ ውስጥ ሥነ ሥርዓትን ለማስጠበቅ ፕሮግራሙ በጸጥታ ጊዜዎች እና በእንቅስቃሴዎች የተከፋፈለ መሆን አለበት።

በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ከመዋዕለ ሕፃናት ሕይወት ብዙ ልምድ አካብተዋል። ሊዘልሉና ሊሮጡ እንዲሁም እርሳሶችንና ባለ ቀለም እርሳሶችን (ከለሮችን) ሊጠቀሙ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ ወንዶችና ሴቶች ልጆች በአንድ ላይ ሊማሩ ይችላሉ። ስምንት ዓመት በሚሆናቸው ጊዜ ወንዶች ልጆች ከሴቶች ልጆች ይልቅ ጠንካሮች ይሆናሉ። እንቅስቃሴያቸውም አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህም ብዙ ጊዜ ሴቶች ልጆች ከእነርሱ ጋር መጫወት አይፈልጉም።

1. የቃል ጥናት

ጀማሪዎች በሚገባ በቃላቸው ማጥናት ይችላሉ። ማንበብ መጀመራቸው ስለሆነ በሰሌዳው ላይ ጥቅሶች ሊጻፍላቸውና በቃላቸው ሊያጠኑ ይችላሉ። ምንባቦችን ወይም ምዕራፎችን በቃል ማጥናት ለቤት ሥራ ሊሰጣቸው ይችላል። መምህሩ በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርቱን ሲደግሙት እንደሚሰማቸው መንገርና ወደፊትም እንደሚከልሰው ሊያረጋግጥላቸው

ይገባል። ዳዊት «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ. (119)፡11] ብሏል። የእግዚአብሔር ቃል በትንሹ ልጅ ልብ ውስጥ ካለ በፈተና ጊዜዎች ከኃጢአት ሊጠብቀውና በወደፊት ሕይወቱ ምሪትን ሊሰጠው ይችላል።

የቃል ጥናትን በተመለከተ ሊታወሱ የሚገባቸው ነገሮች

- ልጆች መረዳት የማይችሉትን ነገር ማስታወስ አይችሉም። ስለዚህም አስቸጋሪ የሆኑ ቃላት ሊብራሩላቸውና እንግዳ የሆኑ ጽንሰ–አሳቦች ግልጽ ሊሆኑላቸው ይገባል።

- ልጆች በቶሎ በቃላቸው ይይዛሉ። ነገር ግን በአእምሮአቸው ለማስቀመጥ ተከታታይ ድግግሞሽ ያስፈልጋቸዋል።

- በአንድ ጊዜ አንድ ጥቅስ ብቻ እያጠኑ በሌላ ጊዜ ከማገጣጠም ይልቅ ጠቅላላውን ምንባቡን ደጋግመው በማንበብ የተሻለ ሊማሩ ይችላሉ።

-መምህሩ ሁሉም ልጆች ክፍሉን ከተማሩ በኋላም እንኳን በይበልጥ ለመማር እንዲችሉ መከለሱን መቀጠል አለበት። ይህ ትምህርቱን በልቦና ለማስቀረት ይረዳል።

- የቃል ጥናቱ ከትምህርቱ ጭብጥ ወይም ከተሰጡት የትምህርት ምዕራፎች ጋር የሚስማማ መሆን አለበት። መምህሩ ትምህርቶቹን በሚያቅድበት ጊዜ የሚመርጣቸው የቃል ጥናት ሥራዎች ተመሳሳይ ዓላማ ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። ይህንን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደገና እንነጋገርበታለን።

- መምህሩ ጥቅሶቹን ማብራራትና ከልጁ ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማሳየት አለበት።

ለምሳሌ መዝሙር 23ን እንመልከት። ለትምህርት አንድ ለልጆቹ የበግ ሥዕል አሳያቸው ወይም በግ እንዲያዩ ከክፍል ወደ ውጪ ውሰዳቸው። ስለ በግ ተናገር፥ ምን እንደሚበሉ፥ ምን ዓይነት ውኃ እንደሚጠጡ፥ ስለ እረኛቸው ስለ ምርኩዙ፥ ስለ በትሩ፥ የዘይት ጥቅም ምን እንደሆነ ተናገር።

በሚቀጥለው ትምህርት መዝሙሩን መስመር በመስመር እያነበብህ ከአንተ በኋላ እንዲናገሩ አድርግ። ወይም ከጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲያነቡ አድርጋቸው። ከበድ ያሉ ናቸው የምትላቸውን ቃላት አብራራላቸው ለምሳሌ «ጽዋዬ ተርፎአል» ወይም «የእግዚአብሔር ቤት» የሚሉትን።

በሦስተኛ ትምህርት መዝሙሩን አንድ ላይ አንብብ። የበጎች እና የእረኛ ሥዕል በእጅህ ካለ አሳያቸው። ለማንበብ በሚጀምሩበት ጊዜ በአንድ እግራቸው እንዲቆሙ ወይም እግራቸውን አጣምረው ጥቅሱን እንዲያነቡ አድርጋቸው። እንቅስቃሴንና የተለያዩ ነገሮችን ለመጨመር የሆነ ነገር አምጥተህ ተጠቀም። ጥያቄዎችን ጠይቅ «በጎች ጠላት አላቸውን?» «እነማን ናቸው?» «ልጆች ጠላት ወይም የሚፈሩአቸው ነገሮች አሏቸውን?» «እረኛው ይህን በተመለከተ ምን ማድረግ አለበት?»

በአራተኛ ትምህርት «መለሳት» የሚለው ቃል «መልሶ አዲስ ያደርጋል» ለማለት መሆኑን አብራራ። ታምሞ ስለነበረና እረኛው ዘይት ስላደረገለት እንደገና ስለተሻለው በግ ተናገር፤ መዝሙሩን በአንድ ጥቁር ሰሌዳ ወይም ሥዕሎች በመጠቀም ደጋግመህ አንብብ።

በአምስተኛ ትምህርት መዝሙሩን እንደገና ካነበብክ በኋላ ከዚህ በፊት ስለተብራሩት ነጥቦች ጥያቄዎችን ጠይቅ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከስምንት እስከ አሥራ ሁለት ሳምንት ልጆች መዝሙሩን በሚገባ በቃላቸው እስከሚያጠኑት ድረስ ቀጥል። በእንደዚህ ዓይነት ድግግሞሽ ልጁ መዝሙሩን ለብዙ ዓመታት ያስታውሰዋል። በኋላ አእምሮውን ለማደስ ክለሳ ማድረግ ይቻላል። በ12 ሳምንታት መጨረሻ ላይ ልጆቹ መዝሙሩን በቤተ ክርስቲያን ወይም በተለየ የወላጆች ፕሮግራም ላይ እንዲያቀርቡት አድርግ። በዚህ ጊዜ ያለምንም ስሕተት ወይንም ማቋረጥ ጥቅሱን ማለት መቻል አለባቸው።

---

1ኛ ጥያቄ፡- ለዚህ የዕድሜ ክልል የቃል ጥናት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? በቃል ሊያጠኗቸው የሚችሉአቸውን ጥቅሶችና ምዕራፎች ጻፍ።

---

1. የጀማሪ ልጅ ባሕርያት

ሀ. አካላዊ፡- በጣም ንቁ ነው፥ መጫወት ይወድዳል፥ በኃይል ይሠራል ነገር ግን ይደክማል።

ለ. አእምሮአዊ፡- ቀላል ነገሮችን ማንበብና መጻፍ ይችላል። በሁሉም ነገሮች ላይ ፍላጎት ስላለው ድንጋይ፥ ቴምብር፥ ሳንቲም፥ ወዘተ... መሰብሰብ ይወድዳል። መማር እና መመርመር ይወድዳል፥ ብዙ ጊዜ ነገሮችን የሚበታትን ቢሆንም እንደገና መሰብሰቡ አይገደውም። እስከአሁን ድረስ መገንዘብና ማሰብ የሚችለው ተጨባጭ ነገሮችን እንጂ ወደ ረቂቅ ማንዛቤ ገና አልተሸጋገረም። አትኩሮት መስጠት የሚችለው ከ10 እስከ 15 ደቂቃ ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው።

ሐ) ማኅበራዊ/ ስሜታዊ፡- ስሜቱ በጣም በቀላሉ ይጎዳል። ስለ ሰዎችም በጣም ግድ የሚለውና አዛኝም ነው። በማንኛውም ችግር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን መርዳት ይወድዳል። ስሜቶቹን መግለጥ ብዙ ጊዜ ሲያስቸግረው ያገኘዋል። በጣም ራስ ወዳድ ሊሆን ይችላል። ሰዎችን ይወድዳል። በሰዎችም መወደድ ይፈልጋል።

መ) መንፈሳዊ፡- ማንበብ ስለሚችል መጽሐፍ ቅዱስን ለራሱ እንዲያነብ መበረታታት ያስፈልገዋል። ትክክል የሆነውን ከስሕተት ለይቶ መረዳት ይችላል (1ኛ ጢሞቴዎስ 4:7-8)።

ለጀማሪዎች ምን ማስተማር እንችላለን?

በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ታሪክ ይወድዳሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጀግኖች ታሪክ ማስተማር የሚገባን በዚህ ጊዜ ነው። ስለ ዮሴፍ፥ አብርሃም፥ ዳዊት፥ ሰሎሞን፥ ዳንኤል፥ ዮናስ፥ ወዘተ... መስማት ይወድዳሉ። እነዚህ እንዴት እንደኖሩ ሊማሩ ይችላሉ። እንዲሁም እንደ እነርሱ ለመሆን ሊመኙ ወይም ከስሕተታቸው ሊማሩ ይፈልጋሉ።

በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና አስተምህሮዎች ብዙ ሊማሩ ይችላሉ። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ባሕርዩ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ፥ ስለ ኃጢአትና ደኅንነት፥ ስለ መንግሥተ ሰማይ፥ ስለ ሲዖልና ሞት፥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊማሩ ይችላሉ። በደረጃቸው ሊረዱዋቸው የሚችሉትን ቀላል ቃላት በመጠቀም ማስተማር ይገባል። እነዚህ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ተደግፈውና ከእነርሱ ፍላጎትና ችግር ጋር ተስማምተው መቅረብ አለባቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶቻችን የልጆችን ጥያቄዎች ለመመለስ የተዛመዱ እና የሚገጥሟቸውን ችግሮች መፍታት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

ልጆች መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ መበረታታት አለባቸው። ልጆች በሚያነቡበት ጊዜ ማስተዋል እንዲችሉ (በማስተዋል እንዲያነቡ) መምህሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል። በክፍል ውስጥ የማንበብ ዕድል እንዲኖራቸው በማድረግ የማንበብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ አሳብ መስጠት ይቻላል። ንባብ በሚቀረው ሕይወታቸው በሙሉ የሚጠቀሙበት ብቃት ነው።

ከሁሉ በላይ ለተማሪዎቻችን በምናስተምራቸው ትምህርት ደኅንነት እንዲያገኙ መጸለይ አለብን። ለልጆች ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ይህ ድንቅ ዕድሜ ነው። ልጅን ወደ ክርስቶስ ስለ መምራት የምዕራፍ አምስት አራተኛ ቀን ትምህርትን ከልስ።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፦ ጀማሪዎች ከስድስት እስከ ስምንት ዓመት ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ሲሆኑ፥ ትምህርት ቤት የመሄድ ዕድል ካገኙ ከአንደኛ እስከ 3ኛ ክፍል ይደርሳሉ። በዚህ ዕድሜ የሚገኙ አምስት ወይም ስድስት ልጆች ሰብስበህ አነጋግራቸው። ስለ እግዚአብሔር ምን ያስባሉ? ዓለምን የሠራው ማን ነው ብለው ያስባሉ? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያውቃሉ? ትክክል ያልሆኑ ናቸው የሚሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? የተገነዘብሃቸውን ነገሮች በጽሑፍ ካሠፈርህ በኋላ ከእነርሱ ጋር መነጋገርህ እንዴት ልታስተምራቸው እንደምትችል እንደረዳህ አብራራ። |

## ሦስተኛ ቀን፦ አንደኛ ደረጃዎችን ማስተማር (ከ9–11 ዓመት)

አንደኛ ደረጃዎች ከሚገባው በላይ ንቁ ናቸው። በትምህርት ቤት የአራተኛ፥ አምስተኛና ስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። እናም ከጠቅላላው ሕይወታቸው እጅግ በጣም ጥሩ በሆነው ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ብዙ ኃይል አላቸው፥ በአብዛኛው ብዙውን የሕፃንነት ወራት በሽታዎች አልፈዋል። አእምሮአቸው ፈጣን ነው፤ እናም ለመማር ትልቅ ፍላጎት አላቸው።

### 1. የአንደኛ ደረጃዎች ባሕርያት

ሀ) አካላዊ ዕድገት፦ በጣም ንቁ ከመሆናቸው የተነሣ ፈጽሞ የሚደክማቸው አይመስልም። ከቤት ውጪ መሆን ይወድዳሉ። ፍላጎቱ ካላቸውና የሚወድዱት ከሆነ በሚገባ የተቀናጀ ስለሆኑ ጥሩ ሥራ መሥራት ይችላሉ።

ለ. አእምሮአዊ ዕድገት፡- ንቁ፥ ጉጉና ሃያሲያን ናቸው። በጣም አስቸጋሪ የሆኑ አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። አመክኖአዊ በሆነ መንገድ ማሰብ ይችላሉ። ረቀቅ ነገርን ለማሰብ ገና መጀመራቸው ነው። ስለ ወደፊቱ ፍላጎት ያላቸው ስለሆኑ ብዙ ጊዜ ሲያድጉ ምን እንደሚሆኑ ያወራሉ። በቃላቸው በሚገባ ማጥናት ይችላሉ። አትኩሮት ሰጥተው ማድመጥ የሚችሉት ከ15 እስከ 20 ደቂቃ ድረስ ነው።

ሐ) ማኅበራዊ/ ስሜታዊ ዕድገት፡- ፍርሃታቸው ከእነርሱ ዕድሜ በታች ካሉ ልጆች ያነሰ ነው። ለመደሰት የተዘጋጁና ጥሩ ስሜት ስላላቸው መሳቅ ይወድዳሉ። በኃይል ሊናደዱ ይችላሉ። እናም ስለሚናገሩት ነገር አይጠነቀቁም። ከተቃራኒ ጾታ አባላት ጋር አብሮ መሆን አይወዱም። ሰዎች የሚሠሩትን ሥራ አስመስለው መሥራት ይወዳሉ። በአጭር ተውኔት (ድራማ) መሳተፍ ያስደስታቸዋል። መታወቅንና መመስገንን ይፈልጋሉ።

መ) መንፈሳዊ ዕድገት፡- መንፈሳዊ እውነቶችን ለማወቅ እውነተኛ የሆነ ፍላጎት አላቸው። ጀግኖችን ያደንቃሉ። እንደ እነርሱ መሆንም ይፈልጋሉ። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ፍጹም ምሳሌ እንዲከተሉት ለማድረግ በጣም ጥሩ ጊዜ ነው። በጥንቃቄ ከተማሩ ለደኅንነትና ለክርስቲያናዊ ዕድገት በጣም ምላሽ ሰጪ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለመመርመር እና ለራሳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገሮችን ለማግኘት ይችላሉ። ትክክለኛ በሆነ እና ባልሆነ ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ። እናም ስለ እግዚአብሔር መልካም ሕሊና አላቸው። ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው የተቀበሉት እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ከተማሩ ዕለታዊ የጥሞና ጊዜን ማድረግ ይችላሉ።

2. ምን ልናስተምራቸው እንችላለን?

ሀ) በበቂ ሁኔታ ስላደጉ አሁን ስለ ኃጢአትና ስለ ፍርድ ማወቅን መጀመር ይችላሉ። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይወድዳል፥ ነገር ግን ኃጢአትን ይጠላል። እነርሱ ራሳቸው በፍትሕ እና በመልካም አስተሳሰብ ስለሚያምኑ የፍትሕ አስፈላጊነት በሚገባ ይገባቸዋል።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በሁሉም ቦታ የሚገኝ፥ ከሁሉ በላይ ኃያል፥ ከሁሉ በላይ ጠቢብ፥ ፍጹም ቅዱስ እና እውነተኛ ፈራጅ ነው። ለልጆች የሚጠነቀቅና ልጆቹን የሚጠብቃቸው ነው። ለእርሱ የሚያቅተው ከባድ ነገር የለም።

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከድንግል የተወለደ፥ በምድር ላይ ኖሮ ያስተማረ እና በአጭር የሕይወት ዘመኑ ተአምራት የሠራ ነው። ኃጢአታችንን ለመሸከም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ። ተቀበረም፤ በሦስተኛው ቀን አዲስ ሕይወት ሊሰጠን ከሙታን ተነሣ። እርሱ አሁን ስለ እኛ እየጸለየ በሰማይ ነው።

ሐ) መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ እየኖረ ቅዱስ ሕይወትን እንኖር ዘንድ ኃይል እንዲሰጠን እንዲያስተምረን፥ እንዲሁም ወደ እውነት እንዲመራን ላከው።

መ) ስለ መልካምና ክፉ መላእክት ማስተማር መጀመር እንችላለን። እንዲሁም ስለ መጨረሻው ጊዜ ነገሮች ማስተማር እንችላለን።

ሠ) በልጁ ሕይወት ውስጥ የማንበብና የማጥናት ጥማት በመፍጠር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ለሕይወት የሚያስፈልገን መመሪያ እና ዕለታዊ ምግባችን ነው። አንድን ልጅ እንዴት እንደሚጸልይ ምራው፤ ከዚያም በክፍል ውስጥ እንዲጸልይ ዕድል ስጠው።

ረ) ምንም እንኳ በአንደኛ ደረጃ የሚገኘው ልጅ በክርስቶስ ቢያምንም እምነቱ ስስ ስለሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙት እና እንደ እንድርያስ፥ ያዕቆብ፥ ጴጥሮስና ጳውሎስ ባሉት ገጸ ባሕርያት ሕይወት መለወጥ አለበት።

ከላይ እንደተጠቀሰው ለዚህ የዕድሜ ክልል ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያለበትን ትምህርት ማስተማር መጀመር እንችላለን። ነገር ግን ሁልጊዜ የምናስተምራቸው ተማሪዎቻችን ልጆች መሆናቸውን መርሳት የለብንም። ስለዚህም የሚገባቸውን ቋንቋ በመጠቀም ልናስተምራቸው ይገባል። ረቂቅ በሆነ መንገድ አስቦ ለመረዳት ገና መጀመራቸው ነው። ስለዚህም ምሳሌያዊ ነገሮችን በተመለከተ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ከሕይወት ጋር በማዛመድ ልንረዳቸው ያስፈልጋል። ይህንንም ጥያቄዎችን በመጠየቅ፥ በውይይት፥ በአጭር ተውኔት (ድራማ)፥ ወዘተ... በመጠቀም ልናደርገው እንችላለን። ገቢራዊ ነገሮችን መጠቀም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ከዕለታዊ ኑሮአቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ ልጆቹ እንዲያዩ ሊረዳ ይችላል። በምናስተምረው ትምህርት ሁሉ ለውጥ ለማምጣት እንደምናስተምር ሳናቋርጥ በአእምሮአችን ውስጥ ማስቀመጥ አለብን። ይህም ማለት የትምህርታችንን የማዛመድ ክፍል ልጆች በሰንበት ትምህርት ቤት የተማሩትን የትምህርት መርሆዎች በሳምንት ውስጥ ከራሳቸው ጋር ማዛመድ እንዲችሉ አድርገን ማቀድ ያስፈልገናል።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- ያጠናናቸውን የአምስት ዕድሜ ክልሎች ዋና ባሕርያት በዝርዝር ጻፍ። እያንዳንዱ ቡድን ለምን ያህል ጊዜ በጸጥታ መስማት እንደሚችል ጻፍ። ያ በትምህርት ዝግጅትህ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? |
| 4ኛ ጥያቄ፡- ከላይ ከተጠቀሱት የልጆች ዕድሜ ክልል ውስጥ አንዱን ምረጥ። መሠረታዊ ከሆኑ የአስተምህሮ ጽንሰ አሳቦች ውስጥ ምን ልታስተምራቸው ትችላለህ? ማዕከላዊ የሆነውን እውነት በሳምንት ውስጥ ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ትምህርትህን እንዴት አድርገህ ታቅደዋለህ? |

## አራተኛ ቀን፡- መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃዎችን ማስተማር (ከ12 እስከ 14 ዓመት ቅድመ–ጉርምስና ዕድሜ)

የቅድመ – ጉርምስና ዕድሜ በአንድ ወጣት ሕይወት ውስጥ ብዙ ለውጦች የሚካሄዱበት ጊዜ ነው። ይህ ከልጅነት ወደ ጉርምስና የሚደረገው ሽግግር የሚጀመርበት ነው። በሁሉም የዕድገት አቅጣጫዎች ለውጦች ይኖራሉ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ለውጦችን አንድ በአንድ በማንሣት በዕድገት ላይ ያሉ ወጣቶቻችንን በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ እንዴት ልንመራቸው እንደምንችል ግንዛቤ ለማግኘት እንጥራለን።

5ኛ ጥያቄ፦ በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ በነበርህ ጊዜ ከነበሩ አንዳንድ አካላዊ ለውጦች የምታስታውሳቸውን በዝርዝር ጻፍ።

1. አካላዊ እድገት፦ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ወደ ትልቅ ወንድነት እና ትልቅ ሴትነት የሚያሸጋግራቸውን አብዛኛውን አካላዊ ዕድገት የሚያካሂዱት በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ በሚሆኑበት ጊዜ ነው።

ለሴቶች ልጆች እነዚህ ለውጦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) የአካሏ ቅርጽ ይለወጣል። ቆዳዋ ለስላሳ እና የበለጠ ቆንጆ ይሆናል። ጡትዋ ቅርጹን መያዝ ይጀምራል። የወር አበባም ማየት ትጀምራለች። ብዙ ጊዜ ለሚሰማት ፍርሃት በቤት ምንም ርዳታ ስለማታገኝ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዋ በሰውነቷ ላይ እየሆነ ያለውን እንድትገነዘብ ለመርዳት ንቁ መሆን አለበት።

ለ) በዕድሜ እኩያዋ ከሆኑ ወንዶች ይልቅ ቁመትም ሆነ ክብደት በመጨመር በፍጥነት ታድጋለች። ልብሶችዋ በሙሉ ስለማይበቋት ተለቅ ያሉ ልብሶች ያስፈልጓታል።

ሐ) በቆዳዋ ላይ በብጉርና በጥቁር ነጥብጣቦች ልትቸገር ትችላለች። ይህንን በየቀኑ በሳሙናና በውኃ በመታጠብ ልትቆጣጠረው ትችላለች። መምህሩ እነዚህ ለውጦች ሁሉ ያሉ እና የዕድገታችን ክፍሎች መሆናቸውን ለማስረዳት የሚያግዘውን «በተለይ ለወጣቶች» ምዕራፍ 2፥ 3፥ እና 4ን ማንበብ ያስፈልገዋል።

በወንዶች ልጆች ላይ የሚታዩ ለውጦች

ሀ) ፈጣን የሆነ የቁመት መርዘም፥ የትከሻዎች መስፋት፥ እንዲሁም የእጆች እና የእግሮች መጠን ማደግ ይኖራል። ሆኖም ወጣት ወንዶች ዕድገታቸውንና ለውጣቸውን የሚጀምሩት ከሴት ልጆች በኋላ ሁለት ዓመት ቆይተው ነው። ይህ ለሁለት ዓመታት ያህል ትላልቅ ሴቶችና ትናንሽ ወንዶች ልጆች የሚታዩበት ወቅት ነው። ወንዶቹ ልጆች ማደግ ከጀመሩ በኋላ በፍጥነት ይቀጥሉና ሴቶች ልጆችን ይበልጧቸዋል። በአንድ ዓመት ውስጥ ጫማቸውና ልብሳቸው ሁሉ እስከማይበቃቸው ድረስ ማደግ ይችላሉ።

ለ) ፊታቸው ረዘም ይልና አፍንጫቸው እና አገጫቸው ከበፊቱ የበለጠ ሾጣጣ ይሆናል። እና በሌሎች የአካል ክፍሎች ላይ የጺምና የፀጉር ምልክት ይታያል። ብጉር ሊያስቸግራቸው ይችላል።

ሐ) የድምፅ ሳጥናቸው ያድጋል። ማንቁርታቸው ተለቅ ይላል። እናም ድምፃቸው ጎርነን እያለ ይሄዳል።

6ኛ ጥያቄ፦ የ12 ና 14 ዓመት ልጅ በነበርህበት ጊዜ ምን ዓይነት ምኞቶች ነበሩህ? ያን ጊዜ የነበሩህን ጥርጣሬዎችና ፍርሃቶች ዘርዝር። በዛን ጊዜ ማን ነበረ የረዳህ?

2. አእምሮአዊ ዕድገት

በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ጥያቄ መጠየቅና ስለ ሁሉም ነገር ማጉረምረም ይጀምራሉ። ብዙ ጊዜ ተቃራኒውን ይሆናሉ። እናም መተባበር

ወይም መታዘዝ አይፈልጉም። ጥሩ ያልሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን ይናገራሉ፤ ውሸት መሆኑን ቢያውቁም እንኳ የተናገሩትን እንደገና አያርሙም። በዚህ ዕድሜ አሳባቸውን በጽሑፍ ማስፈር ይወዳሉ። በአንድ ነገር ላይ ከ20-25 ደቂቃ ያህል ማተኮር ይችላሉ።

ከቀድሞ የበለጠ አስታውሎታዊና ረቂቅ አሳቦችን ማውጠንጠን ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ተምሳሌቶችና ንጽጽሮች ይረዳሉ። በክፍላቸው ውስጥ በውይይት ለመሳተፍ እና ማጠቃለያ ነጥብ ላይ ለመድረስ የተዘጋጁ ናቸው። በሕፃንነታቸው የተማሩዋቸውን ነገሮች እንደገና ለማሰብ የሚጀምሩት በዚህ ጊዜ ነው። የተማሩትን መንፈሳዊ ትምህርት ለራሳቸው ሊቀበሉ ወይም ላይቀበሉ የራሳቸውን ውሳኔ ያደርጋሉ። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በፊታቸው መልካም ምሳሌና ጽኑ የሆነ ሕይወትን የሚኖሩ ወላጅ እና አስተማሪ የሚፈልጉበት ጊዜ ነው።

ምንም እንኳን በአእምሮአቸው ንቁ ቢሆኑም በዚህ ዕድሜ ሰነፍ ሊሆኑና በትምህርት ቤት ዝቅተኛ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ። እነዚህን መምህሩ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በኃይል እንዲሠሩ ለማነሣሣት ሊተጋ ይገባል። መምህሩ ተማሪዎችን በግል በማወቅ ጊዜ ወስዶ ማነጋገርና ስሜታቸውንና አሳባቸውን መረዳት ያስፈልገዋል።

በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች በቀላሉ የሚሰላቹ ስለሆኑ የመማር ፍላጎታቸውን ለማነሣሣት ትምህርቶቹንና ዘዴዎቹን መለዋወጥ ያስፈልገዋል።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፦ በዚህ ዕድሜ የነበሩህ ጠንካራ ስሜቶች ምን ነበሩ? |

3. ስሜታዊ ዕድገት

በዚህ ዕድሜ ብዙ ጊዜ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ሳቅ ሊያበዙና በክፍል ውስጥ ሊረብሹ ይችላሉ። አንዳንዶቹ እየጮኹ ሲረብሹ ሌሎቹ ደግሞ ዓይናፋርና ጸጥተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በትንሽ ነገር ቁጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተቃራኒ ፆታ ጋር በፍቅር ውስጥ የገቡ ሊመስላቸውና በጣም ጥልቅ የሆነ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ከእነርሱ በዕድሜ ከፍ ያለ እንደ አስተማሪያቸው ያለ ወይም የሚያደንቁትን ሰው ይወድዳሉ። ስሜታቸው ተለዋዋጭ እና ያልተረጋጋ ነው። ስለዚህ መምህሩ በዚህ ዕድሜ በሚገኙ ልጆች ላይ ስሜታዊ ግፊት ማድረጉ ትክክል አይደለም። ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ በሚጠይቅበት ጊዜ ልጆቹ በስሜታቸው ምላሽ በመስጠት መሠረት የሌለው እና ውጪያዊ የሆነ ውሳኔ እንዳይወስኑ መምህሩ በስሜታቸው ላይ ተመሥርቶ መጠየቅ የለበትም። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ዕድሜ የሚገኝ አንድ ልጅ በመንፈሳዊ ሁኔታው የተረበሸ መስሎ ወደ መምህሩ ከመጣ፥ መምህሩ በርኅራኄ አድምጦ የሚችለውን ያህል ሊረዳው መሞከር አለበት።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፦ ከሁሉም በላይ የምትወዳቸው ጓደኞችህ እነማን ነበሩ? በአንተ ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ አሉታዊ ነበር ወይስ አዎንታዊ? አብራራ። |

4. ማኅበራዊ ዕድገት

በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ወጣቶች ትርጉም ያለው ጓደኝነት ይፈልጋሉ። ጓደኞች ማለት ሊተማመኑባቸው የሚችሉ፥ የሚያዳምጡዋቸውና ስሜታቸውን የሚረዱላቸው ናቸው። ብቸኝነትን የሚጠሉና በቀላሉ የሚሰላቹ ናቸው። የቡድን አባል መሆን ይፈልጋሉ፤ እንዲሁም የቅርብ ጓደኞችን ይመኛሉ። በነጻነት መመላለስ ይፈልጋሉ። ይህም የቤተሰብ ሥልጣንን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል። ለእነርሱ የሆነ ቀጥተኛ ትእዛዝን ይጋፋሉ ነገር ግን መመስገንንና መታወቅን ይወዳሉ። ታዋቂ መሆንን ይፈልጋሉ። በተጨማሪም መሪ ለመሆን ይመኛሉ።

የደስታ ስሜት በሚሰጧቸውና በሚያስደንቋቸው ነገሮች ውስጥ መሳተፍ ይፈልጋሉ። አሰልቺ የሆነ ክፍል የማይስባቸው ለዚህ ነው። ከዚህም ይልቅ መሀል ከተማ ወርደው የሙዚቃ ጋጋታ እያሰሙ የዕድሜ እኩዮቻቸው ከሆኑ ወጣቶች ጋር ቢደንሱ ይመርጣሉ።

በዚህ ደረጃ ወደሚረዳቸውና ዕድገታቸውን ወደማይገድብ ጓደኝነት ውስጥ እንዲገቡ መምራት ያስፈልጋል። 1ኛ ቆሮ. 15፡33 እንደዚህ ይላል። «አትሳቱ፥ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል»።

---

9ኛ ጥያቄ፦ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ የተቀበልኸው በየትኛው ዕድሜህ ነው? በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነበርህን? መልስህ «አዎን» ከሆነ ወደ ክርስቶስ የመራህ ማን ነው?

---

### 5. መንፈሳዊ ዕድገት

እነዚህ ልጆች ወንጌልን ተረድተው ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው በጥሩ ግንዛቤ ሊቀበሉ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ አንድ ልጅ ክርስቶስን ለመቀበል እንደሚፈልግ ለአስተማሪው መጥቶ ይነግራል። በዚህ ጊዜ መምህሩ እርሱን ወደ ክርስቶስ ለመምራት ታላቅ ዕድል ይኖረዋል ማለት ነው።

አንድ ቀን ከትምህርት በኋላ ዓሊ የተባለው ተማሪ ወደ መምህሩ መጥቶ ክርስቶስን እንደ አዳኙ መቀበል እንደሚፈልግ ተናገረ። መምህሩም «ዓሊ፥ በጣም አዝናለሁ አሁን አንተን ለማነጋገር ጊዜ የለኝም። የመዝሙር ጥናት ጊዜ ስለደረሰብኝ ቸኩያለሁ። ሌላ ቀን ተመልሰህ ና፤ ያን ጊዜ አነጋግርሃለሁ» አለው።

በሚቀጥለው እሑድ ዓሊ ወደ ክፍል አልመጣም ነበረ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ መምህሩ ዓሊ የአንድ ነጋዴ ዕቃ ተሸክሞ በገበያ መካከል ሲሄድ አገኘው። ከዚያም እንዲህ አለው። «ዓሊ፥ ክፍል ውስጥ ባለመገኘትህ እኮ አዝኛለሁ»። ዓሊም እንደዚህ ብሎ መለሰ። «ወደ ክፍል ለመምጣት ጊዜ የለኝም። እሑድ እሑድ እዚህ ገበያ ሥራ አለኝ»። ከጥቂት ዓመታት በኋላ መምህሩ ዓሊን እንደገና አየ። አሁን ዓሊ ሀብታም ነጋዴ ነበረ፤ የሙስሊም ቆብ አድርጓል። ጌታን ለመቀበል በፈለገበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ጊዜ ቢወስድ ኖሮ መምህሩ በዚህ ወጣት ሕይወት ውስጥ ምን ያህል ልዩነት ያመጣ ነበር? በዚህ ዕድሜ ያላቸውን ዕድገትና የልባቸውን አሳብ በሚገባ ካልተረዳን፥ ልጆቹ በቀላሉ ሊጎዱና ለዘላለሙ ከጌታ ሊርቁ ይችላሉ።

እነዚህ ወጣቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመርና የራሳቸው የሆነ የልጅነት እምነት ለመጀመር በበቂ ሁኔታ አድገዋል። ብዙ ጊዜ የሕሊና ወቀሳ ሊሰማቸው ስለሚችል ንስሐ እንዲገቡ ልንረዳቸው ይገባል። ያለባቸውን ፍርሃትና ስለ ወደፊቱ ያለ ጭንቀት ለቅርብ እኩያቸው ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው ለማንም አያካፍሉም። መምህራን ለእነዚህ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃዎች በጣም መጠንቀቅና በዚህ የዕድገት ደረጃቸው እነርሱን ለመርዳት የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

ምን ልናስተምራቸው ይገባል?

1. ለክርስቲያኖችም ሆነ ክርስቲያን ላልሆኑት ስለ ንስሐ ልናስተምራቸው ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ እነዚህ ወጣቶች የሕሊና ወቀሳ ስለሚሰማቸው፥ በእውነት ንስሐ ከገቡ በክርስቶስ ምሕረት (ይቅርታ) እንዳለ ማስተማሩ ተገቢ ነው።

2. ቅብጥብጦች ስለሆኑና ያሉበትን ሁኔታ ብዙ ጊዜ መለወጥ ስለሚፈልጉ በክርስቶስ አዲስ አቅጣጫ እናሳያቸው።

3. እንቅስቃሴንና ሕያው የሆነ ነገርን ስለሚወድዱ የምንዘምራቸው መዝሙሮች የሚስብ ቃና ሊኖራቸው፥ ትምህርቶችም አጓጊና ጥሩ ይዘት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

4. ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርገው ያልተቀበሉ ከሆነ እየጸለይን ወንጌሉን መንገርና መዳን እንደሚያስፈልጋቸውም ማብራራት ይገባናል።

5. በዚህ ደረጃ ስለ ዕድገታቸው መማር ያስፈልጋቸዋል። ስለ ክርስቲያን ጋብቻና እውነተኛ ፍቅር ለማስተማር ጊዜው አሁን ነው።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፡- ከ12-14 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ወጣቶች መካከል ጓደኞችን አፍራ። በዚህ ትምህርት የጠቀስናቸው ባሕርያት እንዳሉአቸው ትስማማለህን? የተመለከትሃቸው ተጨማሪ ባሕርያት ካሉ በዝርዝር ጥቀሳቸው። |

ዋቢ መጽሐፍ፡- በተለይ ለወጣቶች፥ ኤስ.አይ.ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል።

አምስተኛ ቀን፡- የተለያዩ የዕድሜ ክልሎችን ባሕርያት ከልስ። በእያንዳንዱ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆችን በአእምሮህ በመሳል በየቡድኑ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ እንደምትችል ተመልከት። እያንዳንዱ ቡድን ለስንት ደቂቃ ያህል መምህሩን ለማድመጥ እንደሚችል አስብ። ይህ ነገር መምህሩ ትምህርቱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድርበት ይችላል?

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለሳምንታዊ ስብሰባ የተለመደውን አካሄድ ተከተል። ልጆች እንዲደሰቱ በእንቅስቃሴ የሚዘመሩ መዝሙሮችን በትምህርቱ መካከል አስገባ። በቡድኑ ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ ሰው መዘመር እንደሚችል፥ ቃላቱን እንደሚያውቅና በሚገባ በመንቀሳቀስ ንቁ ተሳትፎ ማድረጉን አረጋግጥ። ምንም እንኳን በመጀመሪያ ጊዜ ጅልነት ቢመስላቸውም ለልጆች የእንቅስቃሴ መዝሙር ምን ያህል ዋጋ እንዳለው እንዲያውቁ በጽናት አስተምር።

የመወያያ ርእሶች

1. ዕድሜያቸው እስከ 4 ዓመት ስለሆኑ ትንንሽ ልጆች ባሕርያት ተወያዩ። መማር ያለባቸው በሰንበት ትምህርት ቤት ነው ወይስ በቤታቸው? ብዙውን ጊዜ ዕድሜያቸው እስከ 4 ዓመት ለሚደርሱ በጣም ትናንሽ ሕፃናት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ምንም ፕሮግራም የላቸውም። በቤት የሚማሩ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ለወላጆች እንዴት ሕፃናቱን ማስተማር እንዳለባቸው መመሪያ መስጠት ያስፈልጋታል። ከዚህ ኮርስ ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚያስተምሩ ለማሠልጠን እንደ መረጃ ልትጠቀምበት የምትችለው ክፍል የትኛው ነው?

2. ጀማሪዎች በትክክለኛው መንገድ የሚመሯቸው ጥሩ አስተማሪዎች ያስፈልጓቸዋል። ለዚህ የዕድሜ ክልል ተስማሚ ስለሆኑ ትምህርቶች ተወያዩ።

3. መለስተኞች ማንበብና በረቂቅ መንገድ ማሰብ መጀመር ይችላሉ። በአንተ የማስተማር ዘዴ ላይ ይህ ምን ልዩነት ያመጣል?

4. ለምንድን ነው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዕድሜ ለተማሪዎች አስቸጋሪ ጊዜ የሆነው? እነዚህን ወጣት ልጆች ገንቢ በሆነ መንገድ እንዴት ልትረዷቸው እንደምትችሉ ተወያዩ?

# ትምህርት ሰባት

# ወጣቶችን ማገልገል

## አንደኛ ቀን፡- የወጣቶች ባሕርያት

እስከ አሁን ድረስ ባለው ትምህርታችን ለክርስቲያናዊ ትምህርት መሠረትን ጥለናል። እንዲሁም በተለያዩ የመማርና ማስተማር ሂደት ውስጥ አልፈን የሰንበት ትምህርትን በተመለከተ በዝርዝር ነገሮችን አይተናል።

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው የሰንበት ትምህርት ልጆችን ብቻ የሚያካትት አይደለም። ጥሩ የሰንበት ትምህርት ወጣቶችንና አዋቂዎችንም የሚጨምር ክፍል ይኖረዋል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህ ክፍሎች የሰንበት ትምህርት አካሎች ናቸው። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የወጣቶችና የአዋቂዎች ፕሮግራሞች በሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚጠቃለሉ አይደለም። ነገር ግን በሌሎቹ የሳምንት ቀናት ውስጥ ይካሄዳሉ። ሁለቱም መንገድ ጥሩ ነው። ዋነኛው ነገር ለወጣቶችና ለአዋቂዎች በሚገባ የታቀደ ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያን መኖሩ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ስለ ወጣቶች ፕሮግራም እንነጋገራለን። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት የወጣቶች አስተባባሪዎች ለወጣቶች ፕሮግራሞችን ያዘጋጃሉ። እንደዚያም ከሆነ በክርስቲያናዊ ትምህርት ክፍል ወይም በሽማግሌዎች ቦርድ ሥር ሆኖ ቋሚ ሪፖርት ሊቀርብበት ያስፈልጋል።

---

1ኛ ጥያቄ፡- 1. ወጣቶች የወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ግን እንዳልጠራ አልማዝ ናቸው። የታዳጊ ወጣቶችን ባሕርይ በጥቂቱ ጻፍ።

---

1. ወጣቶችን ማስተዋወቅ

ወጣቶች ከጥገኝነት ራስን ወደ መቻል፥ ከልጅነት ወደ አዋቂነት የሚገዙ ናቸው። ይህም በሕይወታቸው ውስጥ ሁልጊዜ ግራ የሚያጋባ፥ አስጨናቂና ተስፋ አስቆራጭ ጊዜ ነው።

ሀ. መፈንደቅና መደሰትን ይፈልጋሉ። ይህ ጊዜ ብዙ ደስታን የሚፈልጉበትና ብዙ የሚፈትናቸው ነገር የሚመጣበት ጊዜ ነው። ሁል ጊዜ እራሳቸውን በአደጋ ላይ ሊጥሉ እና ሊጎዱቸው ወደሚችሉ ወደ ተለያዩ የጀብደኝነት ሥራዎች ሊገቡ ይችላሉ። ለአልኮል፥ ለሲጋራና ለፍትወት የጠነከረ ፍላጎት ይኖራቸዋል።

ለ. ሕይወታቸው የተጠመደው አሁን ባሉበት ወቅት ነው። ያለፈውን ጊዜ እንደ ሩቅ፥ የወደፊቱን እንደ ማይደረስበት ስለሚቆጥሩ ፍልስፍናቸው የአሁኑን ጊዜ በተቻለ መጠን በሚገባ መጠቀም ነው። የሚያደርጉት ነገር ስለሚያስከትለው ውጤት ብዙ ጊዜ አያስቡም። ብዙ ጊዜ በችግር ውስጥ ይገባሉ። ለመጸጸት ዕድል የሚያገኙት ቆይተው ነው።

ሐ. ነፃ ለመሆን ትልቅ ፍላጎት አላቸው። ቁጥጥርንና ማንኛውንም ዓይነት ሥልጣን በጽኑ ይቃወማሉ። ነፃ ሲሆኑ ብቻ ደስተኛ እንደሚሆኑ ያምናሉ። ብዙ ጊዜም ወላጆቻቸው ከደስተኛ ሕይወት የሚከለክሏቸው ይመስላቸዋል።

መ. በዕድሜያቸው ክልል ውስጥ ካሉት ወጣቶች ጋር እጅግ ይቀራረባሉ። እንደ እነርሱ መልበስ፥ እንደ እነርሱ መናገር እና ከቡድናቸው አንዱ መሆን ይፈልጋሉ። የቡድናቸው አመለካከት ብዙ ጊዜ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል።

ሠ. ስሜታቸው እንደነዳቸው ከማድረጋቸው ሌላ ቋንቋቸው ፀያፍ ነው። ውሳኔ በሚወስኑበት ጊዜ ብዙ አያስቡም። እናም የተሳሳቱ መሆናቸውን እያወቁ እንኳን የተናገሩትን ቃል አይለውጡትም። ቤተሰቦቻቸውን አሳንሰው በማየት ከቤተሰቦቻቸው በላይ እንደሚያውቁ አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ።

ረ. ለሕይወታቸው አዲስ አቅጣጫ ይፈልጋሉ። ይህ ምናልባት ከቤታቸው ጠፍተው የሚወጡበት ወይም ትምህርታቸውን የሚያቆሙበት ጊዜ ነው። በቤት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ነገሮች ይሰለቿቸዋል። ብዙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን ሊያቋርጡ ይፈልጋሉ። እርካታን ለማግኘት ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እርካታው የት እንዳለ አያውቁም።

ሰ. ሁሉንም ነገር ይጠይቃሉ። ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ ለመውጣት እንደምትታገል እንዲሁ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጥገኝነት ለመውጣትና ራሳቸው ሙሉ ሰው ሆነው ለመገኘት ይጥራሉ። ከጫጩቶቹ በተለየ መንገድ ሂደቱ ሊረዝም ይችላል። ይህም ብዙ ጊዜ 5 ወይም 6 ዓመት ሊፈጅ ይችላል። ይህም ማለት በእነዚህ ጊዜያት ተሳከቶላቸው እንዲያዩዋቸው ከወላጆችና ከወጣት መሪዎቻቸው ብዙ ትዕግሥት ያስፈልጋል ማለት ነው።

2. የወጣቶች ባሕርያት

ሀ. አካላዊ ዕድገት

- ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በሙላት ያድጋሉ። ወንዶች በአብዛኛው ከሴቶች በቁመት ይረዝማሉ።

- ጠቅላላ ጤንነታቸው ጥሩ ነው። ብዙ ጉልበትም አላቸው።
- ወንዶች በተለይ ከፍተኛ የፍትወተ ሥጋ ስሜት አላቸው።
- ከፍተኛ የምግብ ፍላጎት ስላላቸው ሁል ጊዜ ይርባቸዋል።
- በሰውነታቸው ጠንካራ ስለሆኑ በጉልበታቸው ለመመካት ይወዳሉ።

ለ) የአእምሮ ብስለት

- በአእምሮ እየበሰሉ ስለሆነ «ለምን?» «ምን?» እና «እንዴት?» በሚሉት ጥያቄዎች የተከበቡ ናቸው።
- ስለ ወደፊት ኑሮአቸው አጥብቀው ያስባሉ።
- በአሁን ጊዜ ለረቂቅ አሳቦች ከፍተኛ ችሎታ ስላላቸው መከራከር፥ መወያየትና አሳብ መለዋወጥ ደስ ይላቸዋል።
- ከቤተሰቦቻቸው የወረሷቸውን እምነቶችና አስተሳሰቦችን በጥልቅ ያስቧቸዋል፤ ይፈትኗቸዋል።
- ጥሩ የማስታወስ ችሎታና የነቃ አእምሮ አላቸው።
- የዕድሜ ጓደኞቻቸውን አስተያየት በከፍተኛ ደረጃ ይወስዳሉ።

ሐ. ማኅበራዊ ዕድገት

- ቤተሰቦቻቸው በእነርሱ ላይ የሚያደርጉትን ማንኛውንም እገዳ በጥብቅ ይቃወማሉ።
- ከልክ ያለፈ ቤተሰባዊ ጥበቃን አይፈልጉም።
- ከቡድናቸው ጋር መመሳሰል በጣም ይፈልጋሉ። እንደ እነዚያ መልበስ፥ መናገር ይፈልጋሉ። የጓደኞቻቸውን ድጋፍና ማበረታታት ይፈልጋሉ።
- በዕድሜያቸው ክልል ከሚገኙት ተወዳጅና ታዋቂ ለመሆን ይመኛሉ።
- መሪ ለመሆን ይፈልጋሉ።
- በችግር ውስጥ ለሚያልፉ ይራራሉ። በተለይ በዕድሜያቸው ክልል ውስጥ ላሉት፥ ለመርዳትና ለማገልገል ይፈልጋሉ።
- በተቃራኒ ጾታ ይሳባሉ።
- በስፖርት መሳተፍና በቡድን ውስጥ መሆን ያስደስታቸዋል

መ. ስሜታዊ ዕድገት።

- እኔ ብቻ የሚሉ እና አንዳንድ ጊዜም «ራስ ወዳድ» እና «ጉረኛ» ናቸው።
- በስሜት ይዋልላሉ፤ አንዳንዴ በጣም ደስተኛ ሲሆኑ አንዳንዴ ያዝናሉ፤ ዓመለኛ ይሆናሉ።
- ፍርሃት፥ ቁጣ እና ፍቅር ጠንካራ ስሜታቸው ነው።
- የእነርሱ ትልቁ ፍላጎታቸው ተቀባይነት እና ዋስትናን ማግኘት ነው።

- ብዙ ጊዜ አለመግባባት፥ ግራ መጋባት እና ተስፋ መቁረጥን የሚፈጥርባቸው ጥልቅ ስሜት አላቸው።

- መታገሥና መጠበቅን ይጠላሉ።

- ስለ ወደፊቱም ነገር ይጨነቃሉ።

ሠ. መንፈሳዊ ዕድገት።

- ጠያቂ በሆነው አእምሮአቸው ምክንያት በመንፈሳዊ እውነታዎች ላይ ጥርጣሬ ያድርባቸውና መጠየቅ ይጀምራሉ።

- ፍትሕን ለሚፈልጉ ሰዎች፥ ለሐቀኝነት እንዲሁም እውነተኝነት ላለበት የሌሎች ክርስትና ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ።

- ክርስቲያኖች ቢሆኑም ባይሆኑም የተከናወነላቸውን ሰዎች ያደንቃሉ። ሊመስሉዋቸውም ይፈልጋሉ።

ወጣቶች ምን እንደሚመስሉ በዚህ መሠረት እንደታኘነው በሕይወታቸው ሊከናወን የሚገባ ታላቅ የመሠረት ግንባታ ልናይ እንችላለን። የታመቀ ኃይል እና ብዙ ጉልበት አላቸው። ከእምነቶቻቸው ጋርም ይታገላሉ። ጥያቄ እየጠየቁ ነው ያሉት። በሚቀጥለው ትምህርታችን ፍላጎታቸውንና የሚነዳ ስሜታቸውን ለመድረስ በወጣቶች ፕሮግራም ላይ ምን መካተት እንዳለበት መነጋገር እንጀምራለን።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፡- ወጣቶች ሊወዱቸው ይችላሉ ብለህ የምታስባቸውን ሁለት ርእሰ-ጉዳዮች ጻፍ። ርእሰ-ጉዳዮቹን የመረጥህበትን ምክንያት ግለጽ። እያንዳንዱን እንዴት እንደምታስተምር አስተዋፅኦ አውጣ። በዚያም ጥቅሶችንና የማስረጃ መግለጫዎችን ስጥ። |

ሁለተኛ ቀን፡- የወጣቶች ፍላጎቶች

በአሁኑ ወቅት ያሉትን ወጣቶች ስንመለከት ሁል ጊዜ ተስፋ ወደ መቁረጡ እናዘነብላለን። እነርሱ እኛ የምንወደውን ዓይነት አለባበስ ላይለብሱ ይችላሉ። እኛ እንደምንወደው ዓይነት ንግግር ላይነጋገሩ ይችላሉ። እኛ እንደምንወደው ዓይነት ድርጊት ላያደርጉ ይችላሉ። ስለ እነርሱም ተስፋ ቆርጠን «ለወጣቶቻችን ምን እናድርግ?» ብለን ልንናገር እንችላለን።

ልናስታውሳቸው የሚገባን አንዳንድ ነገሮች አሉ። አንድ ጊዜ እኛም ወጣት ነበርን። እናም የሚታገሡን ሰዎች ያስፈልጉን ነበር። አሁን ያደግን ሰዎች ብንሆንም እንኳ እኛም በአንድ ወቅት ልክ እንደ ዛሬዎቹ ወጣቶች ነበርን።

የዛሬዎቹ ወጣቶች አንዳንድ ጥልቅ የሆኑ ፍላጎቶች አሏቸው። ስለሆነም ይህንን ለመድረስ መንገድ መፈለግ አለብን። ወጣቶቻችንን ለሰይጣንና ለክፋት ሥራው መጠቀሚያ ዕቃ እንዲሆኑ አሳልፈን መስጠት አንችልም። ዛሬና በቀረው ዘመናቸው በትክክለኛው በጌታ መንገድ ላይ ሲሄዱ ለማየት እንችል ዘንድ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

1. የዛሬው ዘመን ወጣት ፍላጎቶች

ሀ. ፍቅር

የእኛን ፍቅር ይፈልጋሉ። ልንወዳቸው ይገባል። የሚያደርጉትንና የሚሠሩትን ላንወድ እንችል ይሆናል። እንደዚያም ሆኖ እንደምንወዳቸው ሊያውቁ ይገባል። የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲህ ያለ ነው። ኃጢአትን ይጠላል፥ ነገር ግን ኃጢአተኛውን ይወዳልና። ፍቅሩ ጽኑ እና ዘላቂ ነው። የእኛም እንዲሁ ሊሆን ይገባል።

ለ. ተቀባይነት ማግኘት

ረባሽ፥ ጉረኛ፥ በራሳቸው የሚመሩ ግትር ቢሆኑም እንኳን እንዳሉ ልንቀበላቸው ይገባል። ከውጫዊ ነገራቸውና ድርጊታቸው አልፈን በውስጣቸው የታመቀውን ችሎታቸውን ልንመለከት ይገባል። ሁሉም ኃይላቸውና፥ ፈጣን አእምሮአቸው ለጌታ ሊሆኑ ይችላሉ። እዚህ እስክንደርስ ድረስ እንሥራ።

ሐ. ፈቅዶ ማድመጥ

ወደ ጥልቅ አስተሳሰብ መግባት እየጀመሩ ነው። ስለ ሁሉም ነገር ሺህ ጥያቄ አላቸው። ልንሰማቸውም ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ለችግሮቻቸው የራሳቸው የሆነ መልስን ያገኛሉ። ይሁንና እኛም ልንሰማቸው ጆሮቻችንን መስጠት ይገባናል። ከእኛም ቀላል መልስን አይፈልጉም። በዝግታ ከመራናቸውና ወደ ውሳኔ ራሳቸው እንዲደርሱ ከተውናቸው ብዙ ይማራሉ።

መ. ደኅንነት

የተደላደለ ቤት እና በቤተ ክርስቲያን ደግሞ የተሟላ መንፈሳዊ ምግብ የሚያገኙበትና እንደ ቤታቸው የሚሰማቸው ቡድን ይፈልጋሉ። ማድረግ የሚችሉትንና ማድረግ የማይችሉትን ነገሮች ድንበሮች ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ለነፃነት እየታገሉ ስለሆነ አንዳንድ የወጣት መሪዎች ሁሉም ነፃነት ለእነርሱ መስጠት አለበት ብለው ያስባሉ። በእርግጥ ምንም እንኳን ነፃነታቸውን ለማግኘት ቢታገሉም እንደ ክርስቲያን ወጣቶች ማድረግ እንደተፈቀደላቸው እና እንዳልተፈቀደላቸው በማወቅ ዋስትና ይፈልጋሉ። ይህም እነርሱን ቁጥር በሌለው ሕግና ደንብ ውስጥ መገደብ ማለት አይደለም። ሆኖም ተቀባይነት ያለው ክርስቲያናዊ ባሕርይ ከእነርሱ እንደሚጠብቅ ማወቅ አለባቸው ማለት ነው።

ሠ. የሚከተሉት መልካም ምሳሌ

የወጣቶች ረጂዎች፥ አስተማሪዎችና ወላጆች በጣም ጠቃሚ የሚሆኑበት ቦታ ይህ ነው። እንደ መሪነታቸው ሁልጊዜ ይመለከቱናል። ወጣቶች ምንም እንኳን ለራሳቸው የዚያን ዓይነት ደረጃ ባይሰጡም ራሳችንን እንዴት መምራት እንደሚገባን ያውቃሉ። ስለ አኗኗራችን ከፍተኛ ሚዛን ያላቸው ሲሆን፥ እንዲያውም ፍጹም እንድንሆን ይጠብቃሉ። እኛ ሁላችን ልንወድቅ የምንችል እንደሆንን እና ስሕተትም እንደምንሠራ ሊያውቁ ያስፈልጋል። እንደዚህ ካደረግን ለእነርሱ ልንነግራቸውና ከችግሮቻችን እንዴት እንደምንላቀቅ ልናሳውቃቸው ይገባል።

ሕይወታችን በፊታቸው የተገለጠና እውነተኛ መሆን አለበት። ከተሳሳትን ለእግዚአብሔርም ለእነርሱም ልንናዘዘው ይገባል። በአለመስማማት ውስጥ ከገባን እንዴት እንደምንፈታው ለእነርሱ ማሳየት አለብን። ከተፈተንን ፈተናችንን እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል ልናሳያቸው ይገባል። ሕይወታችን ለእነርሱ የተፈተነ መጽሐፍ ሊሆን ይገባዋል። ከትምህርታችን ይበልጥ ከሕይወታችን ብዙ ትምህርትን ሊማሩ ይችላሉ።

ረ. ለክርስቶስ መስጠት

በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ ወጣቶች ከዚህ ቀደም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ ተቀብለውታል ብለን ሙሉ ተስፋ አለን። ያልተቀበሉትም አንዳንድ ይኖራሉ። የደኅንነትን መንገድ ለእነርሱ ግልጽ አድርጎ በማቅረብ ታማኝ መሆን አለብን። ይህም በማንኛውም ጥርጥር ውስጥ ያሉ ወይም ያልዳኑ ካሉ ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ እና ከእግዚአብሔርም ይቅርታን በመቀበል ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው ለመቀበል ዕድል እንዲኖራቸው ነው።

ለወጣቶች የሆነው የትምህርት ፕሮግራማችን እነርሱን ከጌታ ጋር ተቀራርበው እንዲሄዱ ሊያደርጋቸው ይገባል። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልናወጣቸው ያሻል። ሁሉንም ትምህርት የምንሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በመቆፈር ለራሳቸው መልስን ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ እያሳየናቸው ነው። የወጣቶች ፕሮግራም በምናቅድበት ጊዜ እነርሱን ማዝናናት እንዳለብን አስበን ልንፈተን እንችላለን። በእርግጥም ጥሩ ሙዚቃ፥ ሕያው ዝማሬና እና የሚያነቃቁ ምስክርነቶች ያስፈልጋሉ። ሆኖም በእውነት ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው ቃሉን ለራሳቸው ማጥናት ነው። ስለ ፍላጎታቸው የሚናገሩ ጥናቶችን መምረጥ አለብን። ለጥሩ ጥሩ ጥያቄዎች መልሶችን እንዲያገኙና እንዲመሩ፥ እንዲሁም መሪ የሆኑ ውይይቶችን እንዲወያዩ ማድረግ አለብን።

በምሳሌነታችን እና በትምህርታችን ዕለታዊ የጥሞና ጊዜ እንዲኖራቸው ልንመራቸው ይገባል። እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ምሪት ያስፈልጋቸዋል። እንዴት መመስከርና ሌሎችን ወደ ክርስቶስ መምራት እንደሚቻል ጥናት ማድረግ ይችላሉ።

በራሳቸው ፕሮግራም ላይ ስለ አመራርም ሥልጠና ልንሰጣቸው ይገባል። የመምራት ችሎታ ያላቸው የወጣቶች ፕሮግራም በማቀድ፥ በመምራትና በማስተዳደር ሊሳተፉ ይገባል።

ሰ. ደስታ፥ ጆብደኝነትና ትርጉም ያላቸው እንቅስቃሴዎች

የሚፍለቀለቀው የወጣቶች ኃይል ትርፋማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ ሊውል ያስፈልጋል። ከዚህ በታች አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ተዘርዝረዋል። አንዳንዶቹ ታዋቂ ለመሆን የሚደረጉ ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ደግሞ ወጣቶች የሥራ ክቡርነትን እንዲያውቁ የሚያደርጉ ናቸው።

1) ስፖርት፡- ወጣቶች በስፖርት ውስጥ በመሳተፍ ትልቅ ነገር ሊማሩ ይችላሉ። ከቡድኑ አባላት ጋር መተባበርን ይማራሉ። ስሜታዊ ባሕርያቸውን መግታትና መሸነፍን በጸጋ የመቀበል ጉዳይ፥ ማሸነፍን ያለ ኩራት ማስተናገድ ለእርስ በራሳቸው ተገቢውን ክብር መስጠት ይማራሉ። በአንድ ሰው ውስጥ ያለው ባሕርይ ጠንካራ እና ደካማ ጎን በስፖርት ጨዋታዎች ጊዜ በቶሎ ስለሚገለጥ ብልህ የሆነ የወጣቶች መሪ ይህንን ወጣት ወደተሻለ አመለካከትና ስሜታዊ ምላሽ ለመምራት መንገድን ይፈልጋል።

2. የመስክ መዝናኛ፡- አንድ ቡድን ይዘህ ወደ ዓይነሥውራን ትምህርት ቤት፥ መስማት ወደተሳናቸው ትምህርት ቤት፥ ወደ አካል ጉዳተኞች መቆያ ስፍራ፥ ወደ ወህኒ ቤት፥ ፋብሪካ፥ እጅ ሥራ ማዕከል፥ ሙዚየም ሂድ። ይህ በከንቱ የሚጠፋ ጊዜ አይደለም። በመጀመሪያ ወጣቶች የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ለማስፋት ብዙ ይማራሉ። በተጨማሪም ወጣቶችንና መሪዎችን በማዝናናት በአንድ ላይ በማገናኘት ጠቃሚ የሆነ የአሳብ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል። የወጣት መሪዎች የወጣቶቻቸውን ፍላጎቶችና የማይፈልጓቸውን ተምረው ለጥናት የሚሆኑ አሳቦችን ማግኘትና በኋላም በክፍል ውስጥ ማስተማር አለባቸው።

3. የቡድን አገልግሎት

ሀ. መዘምራን፡- በሚገባ ከተደራጀና ቁጥጥር ከተደረገበት ለወጣቶች ትልቅ የአገልግሎት መስክ እና ለቤተ ክርስቲያናቸውም በረከት ሊሆን ይችላሉ። መዘምራን በሚገባ የታቀደ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ የጸሎት፥ እንዲሁም የመዝሙር ልምምድ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል።

ለ. ሠራተኛ ንቦች ፡- ቤተ ክርስቲያንን በማጽዳትና ቀለም በመቀባት፥ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የአትክልት ስፍራ በማዘጋጀት፥ በሥራ የደከመውን የቤተ ክርስቲያን አባል በማገዝ እንጨት በመፈለግ፥ ውኃ በመሸከም፥ ለስብሰባዎች ምግብ እና ጠቅላላ አስፈላጊ ነገሮችን በማዘጋጀት መሳተፍ ነው። ተካፋይ መሆን፥ መርዳትን መማርና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ያሉ ፍላጎቶችን ለማሟላት መንቀሳቀስ ለእነርሱ ትርፍን ሊያስገኝላቸው ይችላል።

ሐ. በወንጌል ሌሎችን መድረስ፡- ወጣቶች በመመስከር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራት እንዲያውቁ ማሠልጠን ያስፈልጋል። በውጪ ያሉትን የመድረስ ጊዜ፥ የወንጌል ዘመቻ እንዲሁም የጉብኝት በተጨማሪ እሑድ ቀን በራሪ ጽሑፎች (ትራክት) የሚሰራጩበት ጊዜ ይዘጋጅ። አንድ ወጣት አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ከመራና ደቀ መዝሙርም እንዲሆን ከረዳው፥ እንደገና በፍጹም እንደ ድሮው ሊሆን አይችልም።

መ. ድሆችን መርዳት። በማንኛውም ኅብረተሰብ በገጠርም ሆነ በከተማ ካለባቸው ድኅነት፥ የጤንነት ችግር፥ ወይም ተፈጥሮአዊ አደጋ የተነሣ የተለየ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አሉ። ወጣቶችም ምግብ በማሰራጨት፥ በልብስ አቅርቦት፥ መስኮችን ለማልማት በወጣው ፕሮግራም፥ ቤቶችን በመገንባት ሊሳተፉ ይገባል። የሚያስፈልገው ነገር ሁልጊዜ ጠንክሮ በመሥራት ሊገኝ ይችላል። ወጣቶች ለዚህ የሚሆን ኃይል አላቸው። ስለዚህም ተጠቀምበት!

2ኛ ጥያቄ፡- ለወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አዘጋጅ። ምንባቡን ከመረጥህ በኋላ ዋና አሳቡንና ዓላማውን ጻፍ። ሊታተኩርበት የሚገባህን ወይም በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ምረጥ። የጥናቱንም ዋና ነጥቦች ጻፍ። ወጣቶችን እንዴት እንደምታሳትፍ ወስን። እንዲያስቡ የሚያደርጓቸውን እና መልስ የሚያዘጋጁላቸውን ጥሩ ጥሩ ጥያቄዎች አዘጋጅ። ምንባቡ ከዕለታዊ ኑሮ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አስብ። ለተማሪዎቹ ከፍተትን መሙላት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅ። እንደገናም ጥያቄዎችንና የመወያያ ነጥቦችን በማንሣት በዚያ ሳምንት ከሕይወታቸው ጋር ማዛመድ ይችሉ ዘንድ እርዳ።

## 2. በዕድሜ ከፍ ያሉትን ወጣቶች ማገልገል

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በ20 እና በ30 ዓመት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ያላገቡ ሰዎች ሁሉ እንደ ወጣት ይቆጠራሉ። ብዙ አስቸጋሪ ነገሮችም ያጋጥሟቸዋል።

ሀ. ሥራ አጥነት፡- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ሊኖራቸው ይችላል። ሥራ ግን ሊያገኙ አልቻሉም። ብዙዎችም ወደ ግብርና፥ ንግድና ወደ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች ተመልሰዋል።

ለ. ለማግባት አለመቻል። በብዙ ቦታዎች ከሚጠየቀው ከፍ ያለ ጥሎሽ የተነሣ ወጣቶች አርባ ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ እንኳን ለማግባት የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን አልቻሉም።

ሐ. ውሳኔያቸውን የሚቀበላቸው ማጣት፡- ወጣቶች ስለሆኑ የእነርሱ አስተያየት እና አሳብ በመሪዎች ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም።

የእነዚህን ወጣቶች ታላቅ የታመቀ ችሎታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው ሥራ ለመጠቀም የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው ያሻል። እነዚህን ወጣቶች ልጆችን ለማስተማር፥ ወጣቶችን ለማስተማር፥ ለወንጌል አገልግሎትና ሌሎችን ለመድረስ ወዘተ. . . ተጠቀሙባቸው። በቤተሰብ ኃላፊነት የታሰሩ ስላልሆኑ ጊዜን ሊሰጡና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመምራት፥ በማቀድ፥ በማስተማር፥ በጉልበት ሥራ ወዘተ፥ እጅግ ጠቃሚ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ። የሚሳተፉበትን ዕድል በመስጠት ተፈላጊነት እንዲሰማቸው እንዲሰማቸው አድርጉ።

3ኛ ጥያቄ፡- ምናልባትም አንተ በዕድሜ ከፍ ያልህ ወጣት ትሆናለህ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየትኛው አገልግሎት ትሳተፋለህ? በአንተ የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ነገር በመሥራት ያገለግላሉ? በሌላ በምን መንገድ ልትረዳ ትችላለህ?

## ሦስተኛ ቀን፡- ለወጣቶች አገልግሎት ብቁ የሆኑ አዋቂ ሠራተኞች

ብዙ የወጣት መሪዎች ጠንክረው ይሠራሉ። እነርሱ ራሳቸው ብቻ ሥራውን በሙሉ መሥራት እንዳለባቸው ያምናሉ። ወይም የወጣቶችን ፕሮግራም ለመምራት ብቁ የሆኑት እነርሱ ብቻ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። በዕቅድ አውጭ ስብሰባ ላይ በመገኘት፥ በማማከር፥ በሽተኞችን በመጎብኘት፥ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና በወጣቶች ስብሰባዎች በመገኘት ወደ ሠርግ በመሄድ፥ ማስተማር ያለባቸውን ትምህርት በማጥናት፥

የሥልጠናን ሴሚናር በማዘጋጀት ለሚስቶቻቸው ታማኝ ባል ለመሆን በመጣር፥ በቤታቸውም ለልጆቻቸው ጥሩ አባት ለመሆን በመታገል ከቀን ወደ ቀን ያለማቋረጥ ይሮጣሉ። ከጌታ ጋር በየቀኑ የጥሞና ጊዜ እንዲኖራቸው ይሞክራሉ።

ይህ የማይቻል በመሆኑ እርዳታ ሊደረግላቸው ይገባል!

ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ካወጣ በኋላ አማቱ ዮቶር ሊጎበኘው መጥቶ ነበር። ሙሴም በእስራኤል ሕዝቦች መካከል አለመግባባታቸውን ይዳኝ ነበር። በጣም ኃይለኛ ችግር ሲጋፈጥ ተመለከተ። ሊፈታ የሚገባው ችግር ካለው ጊዜ የላቀ ነበር። ስለዚህም ሥራ ከመጠን በላይ በዝቶበት ነበር። ዮቶር ጥበበኛ ሰው ነበርና ለሙሴ እንዲህ አለው። «አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም። ይህ ነገር ይከብድብሃልና አንተም ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደክማላችሁ። አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም።» ሙሴንም መምከር ቀጥሎ ሕጉን እና መመሪያዎችን እንዲያስተምራቸውና እንዴት እንደሚኖሩ እንዲሁም ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን ተግባራት እንዲያሳያቸው መከረው። የእርሱ ድርሻ ይኸው መሆን ነበረበት። ከዚያም ችሎታ ያላቸውንና በሕዝቡም ላይ መፍረድ የሚችሉትን ሰዎች መምረጥ ነበረበት። ሊፈርዱና፥ ሊወስኑበት ያልቻሉት ጉዳይ ካለ ወደ ሙሴ ሊያመጡት ይችሉ ነበር (ዘጸ. 18፡17-23)። በዚህ መንገድ ሕዝቡ በሚያገኘው አገልግሎት ረክቶ ሊመለስ ይችል ነበር።

ከዚህ ትምህርት፥ ለብቻ ሆኖ ለመሥራት መሞከር ከንቱና መባከን እንደሆነ እንማራለን። የመጨረሻው ቁጥር ቁ. 23 እንደሚያመለክተን ሙሴ ይጠቀምበት የነበረው የዳኝነት አሠራር ሕዝቡን አላረካቸውም ነበር። ችግራቸው እንዲሰማላቸው ብዙ ሰዓት የመጠበቅ ግዴታ ነበረባቸው (ቁ. 13-14)።

በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ ላለው እንዲህ ዓይነት ችግር መፍትሔው ከአዋቂዎች ፈቃደኞችን በማሠልጠን የሥራውን ሸክም አብሮ ማገዝ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ በሚያስተምራቸው አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ተከቦ ነበር። እናም እንዲሰብኩ፥ እንዲያስተምሩና በሽተኞችን እንዲፈውሱ ወደ ከተማና መንደሮች ይልካቸው ነበር። ጳውሎስም ይህን የማሠልጠንና የመወከልን መርሆ ተጠቅሟል። የእርሱ ፍላጎት ሥራው በዘላለማዊነት እንዲቀጥልና እያንዳንዱ የሠለጠነም አሠልጣኝ እንዲሆን ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡2)።

በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ መሪው ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂዎችን ከእርሱ ጋር እንዲሠሩ ሊያሠለጥን ይገባል።

1. ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂዎች መመዘኛ
   - የሌለህን ነገር መስጠት
   - ራስህ እየተራብህ ሌላውን መመገብ
   - ሄደህ ወደማታውቀው ስፍራ አንድን ሰው መምራት ፈጽሞ የማይቻል ነው (‹Roadcup› ሮድካፕ፥ ገጽ 85)።

በትምህርት አራት ላይ በዝርዝር ተጠቅሰው የነበሩት መመዘኛዎች ለአዋቂዎች አገልጋዮች ሁሉ ሊሆኑ ይገባል። በዚህ ትምህርት ሁለተኛ ቀንም ደግሞ የወጣቶችን ፍላጎት ተነጋግረናል። ከወጣት መሪው ጋር የሚሠራው አዋቂ ሰው እነዚያን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚችል መሆን አለበት።

ስለዚህ የሚከተሉት ብቃቶች ሊኖሯቸው ይገባል።

- ወጣቶችን የሚወዱ
- እንደ ጠባያቸው እንዳሉ ለመቀበል የሚችሉ
- የሚያጳምጧቸው እና ለችግራቸው መፍትሔ እንዲያገኙ መርዳት የሚችሉ
- ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋስትና እንዲሰማቸው የሚያደርጉ
- ምሳሌያዊ ሕይወት የሚኖሩ
- ወጣቶችን ሕይወታቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ የሚመሩ
- ለወጣቶች ተስማሚ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ የሚችሉ።

በተጨማሪም

- በስሜታዊና በመንፈሳዊ ነገር የበሰሉ
- ለወጣቶች ባሕርይ የሚጠነቀቁና መረዳት የሚችሉ
- የፈጠራ ችሎታ ያላቸው
- ልንተማመንባቸው የምንችል
- ግልጽ እና ታማኝ
- ከውድቀት የሚማሩ መሆን አለባቸው። በመውደቅ ጊዜ አንድ ሰው ንስሐ ሊገባና ከዚያ ሊማር ይገባዋል። እናም ወደፊት መቀጠል አለበት።

2. ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂ ሠራተኞችን መምረጥ

<u>ደረጃ 1</u>፡- በነገሩ በትጋት ጸልይ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለወጣቶች ፕሮግራም ቀና የሆነ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ወደሚችሉ ትክክለኛ ሰዎች እንዲመራህ ጌታን ጠይቅ።

<u>ደረጃ 2</u>፡- የሚያስፈልግህ ምን እንደሆነ ወስን። በፕሮግራሙ ላይ የሚሳተፉት ወጣቶች ምን ያህል ናቸው? ወጣቶቹን ከአንድ በላይ በሆነ ቡድን ልትከፍላቸው ትችላለህን? በየቡድኑ ምን ያህል ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ያስፈልጉሃል? ምን ኃላፊነት ነው ለእነርሱ የምትሰጣቸው? ለዚህ ዓይነቱ ሥራ ጥንድ ባለትዳሮችን ማድረግ ጥሩ እንደሆነ ይታመናል። ባልና ሚስቱ መልካም የጋብቻ ሕይወት የሚመሩ ከሆነ ለወጣቶች ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ። ደግሞም ቤታቸውን ለአንዳንድ የወጣቶች ፕሮግራም መስጠት ይችላሉ። ያላገቡም በጣም ሊረዱ የሚችሉ ናቸው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዓትን ለሥራው ይሰጣሉና።

ደረጃ 3፡- ምሳሌ የሚሆኑ ነገሮች መፈለግ ጀምር። ወጣት ባልና ሚስቶች በጣም ጥሩ የሆኑ አማካሪዎች ይወጣቸዋል። ምክንያቱም የሕይወት ኑሮአቸውን አደላድለው ቢጀምሩም አስቸጋሪ የሆነውን የወጣትነት ጊዜያቸውን አልረሱም። የበሰሉ ወጣት ወንደላጤዎችም ለወጣቶች ፍሬያማ አገልግሎት ሊኖራቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ሳይታይ የሚታለፈው እውነታ ግን በዕድሜ የገፉ ባልና ሚስት ለወጣቶች ፕሮግራም በጣም አዎንታዊ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ መቻላቸው ነው። ወጣቶችን የሚወዱ ከ60 ዓመት በላይ የሆኑት ሰዎች እንኳን ትክክለኛ የሆነን ተጽዕኖና ጥበብ የተሞላ ማማከርን ሊሰጡዋቸው ይችላሉ።

ደረጃ 4፡- የሚያስፈልግህን ነገር ለጉባኤ ተናገር። ፈቃደኞች የሆኑ እንዳሉ ጠይቅ። የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ ዘርዝርላቸውና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ መመዘኛዎች አስረዳቸው። የወጣቶች አማካሪን ኃላፊነት በተመለከተ አጭር ገለጻ አድርግላቸው። ደግሞም ከአንተ ጋር ጉባኤው ሁሉ ለወጣቶች ፕሮግራም እንዲጸልይ ጠይቅ።

ደረጃ 5፡- ፈቃደኞችን ወይም ወደፊት እጠቀምባቸዋለሁ የምትላቸውን ሰዎች ጎብኝ። የምታስበውን ሰው መጎበኘት እጅግ ጥበብ ነው። ከእነርሱ ጋር ጊዜ ወስደህ የወጣቶችን ፕሮግራም ጠቃሚነት እንዲረዱ አድርጋቸው። እነርሱ እንዲያደርጉ ስለምትጠብቀው ነገር ግልጽ የሆነ አሳብን ስጣቸው። ባልና ሚስት የሆኑ እንደሆነ የተደላደለ ቤትና እርስ በርስ ባላቸው ፍቅር ምክንያት በወጣቶች ላይ ሊያሳድሩ ስለሚችሉት ተጽዕኖ እንዲያውቁ በአንድ ላይ ቁጭ አድርገህ አነጋግራቸው።

ደረጃ 6፡- ፈቃደኛ ለሆኑልህ ሰዎች የሥልጠና ሴሚናር አካሂድ። ለወጣቶች አገልግሎት ጥሩ ጅማሬ ይሆንላቸው ዘንድ ይህን መጽሐፍ ወይም ሌሎች ነገሮች በመጠቀም ኮርሱን አዳብረው። ከወጣቶች ጋር አገልግሎትን እንዲጀምሩ ይህ መሠረት ሊሆናቸው ይችላል።

ደረጃ 7፡- ከሴሚናሩ በኋላ ፈቃደኞችን እንደገና ጎብኝ። ማንኛውንም ጥያቄያቸውን አብራራ። ለተወሰነ ጊዜ ያህል ራሳቸውን እንዲሰጡ ጠይቃቸው። ለተወሰነ ጊዜ ራሳቸውን የሚሰጡ ከሆነ በጊዜው መጨረሻ ላይ እንደገና ልትገመግማቸው ትችላለህ። ለውጥ ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ የሚያሳፍር ነገር አይኖረውም፤ ምክንያቱም ፈቃደኛነታቸው ለተወሰነ ጊዜ ነበርና። በአሠራሩ ሁሉም ሰው የተደሰተ ከሆነ መስጠቱ ሊራዘም ይችላል።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስላሉት ወጣቶች አስብ። በወጣቶች ቡድን የሚመደቡ ናቸውን? እነርሱን በመደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ለማሳተፍ ምን ጥረት ተደርጓል? በሕይወታቸው የሚታይ ዕድገት አለን? መልስህን የምትሰጠው በምን መሠረት ላይ ነው? ፕሮግራሙ እንዲሻሻል ምን መደረግ እንዳለበት ታስባለህ? በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ በመምራት ወይም ፈቃደኛ ሠራተኛ በመሆን ለመሳተፍ አሳብ አለህን? መልስህ አዎን ከሆነ የሚቀጥለው እርምጃህ ምንድን ነው? |

አራተኛ ቀን፡- ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂዎች ሥልጠና

በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ የሚረዱህን አዋቂዎች በምታሠለጥንበት ጊዜ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ።

1. የሠራተኞች ሥልጠና

ሀ. ጥራት ያለው ሥልጠና ዓመቱን ሙሉ መቀጠል አለበት። የመጀመሪያው ሴሚናር ከላይ እንደተጠቀሰው በጣም ጠቃሚ እና ጥሩ ጅምር ነው። በእርግጠኝነት ውጤታማ በመሆን ከአንተ ጋር የሚሠሩ ሰዎችን ለማግኘት ግን የሚቀጥልና ቋሚ ሥልጠናን ልታዘጋጅላቸው ይገባል።

ለ. ጥራት ያላቸው መረጃዎች ተዘጋጅተው መቅረብ አለባቸው። ፈቃደኞች የሆኑት የአንተ ሰዎች የወጣቶችን ባሕርያት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎችን፥ ወጣቶችን ሥነሥርዓት የማስያዝ ብልሃትን፥ የማስተማር ዘዴንና የፕሮግራም ዕቅዶችን ማወቅ አለባቸው። ችሎታቸውንም ለማዳበር ለማንበብና ለማጥናት ሊበረታቱ ይገባል።

ሐ. የፈቃደኞችን ሕይወት መገንባት ያሻል። የግል የጥሞና ሕይወታቸው ሊሻሻል ይገባዋል። ስለ መልካም የጋብቻ ግንኙነት፥ ልጆችን ስለ ማሳደግ፥ ባሕርይን ስለ ማሻሻል፥ ስለ ምስክርነት ዘዴዎች መማርና መበረታታት ይገባቸዋል።

2. ለመጀመሪያ ሥልጠና ሴሚናር ሊሠራበት የሚችል ሞዴል

ሀ. ዓላማዎች፡- ለወጣቶች ፕሮግራም ዓላማዎችን መጻፍና ለፈቃደኞቹ ሰዎች ማካፈል ይገባሃል። ዓላማዎችን እንዴት ልትደርስ እንደሆነ ዕቅድህን አካፍላቸው። ዓላማዎቹ እንዲደረስባቸው የሚያስችሉ መንገዶችን አሳብ በማቅረብ መርዳት እንዲችሉ አድርግ።

ለ. በሴሚናርህ ሊካተቱ የሚገቡ ርእሰ-ጉዳዮች

- የወጣቶች አገልግሎት አስፈላጊነት
- ፈቃደኛ አገልጋዮች በፕሮግራሙ የሚያደርጉት ሚና መግለጫ
- የስኬታማ ወጣት ሠራተኛ ባሕርይ
- በወጣቶች ሥራ ውስጥ ዓበይትና ንዑሳን ዓላማዎች
- ወደ ግቦች ለመድረስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች

1. ደቀ መዝሙርነት- በወጣቶች ሕይወት ውስጥ ጥሩ መሠረትን መጣል
2. ውጤታማ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት
3. ኅብረተሰባዊ መቀባበልን የሚያሳድጉ ሁኔታዎች
4. የአምልኮ ምሪት
5. መመሪያ መቀበል እና የጸሎትን ሕይወት ማዳበር።

(ከእነዚህ ርእሶች አብዛኞዎቹ በዚህ ኮርስ ውስጥ ተጠቃልለዋል። የእኛም እምነት ይህ መጽሐፍ ሌሎችን ለማሠልጠን እንደ መሪ መጽሐፍ እንደሚሆናችሁ ነው።)

3. በሦስት ወር የሚደረግ የፈቃደኛ ሠራተኞች ኮንፍራንስ።

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚሳተፉበት የወጣቶች ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሁሉ የተደራጀ እንደሆነ የሳምንቱን መጨረሻ እንድትጠቀምበት የሚያስችል የፈቃደኛ ሠራተኞች ሥልጠና ኮንፍራንስ ሊዘጋጅ ይችላል። ይህ የሳምንት መጨረሻ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

ሀ) በወጣቶች አገልግሎት ላይ ሊያስተምር የሚችል ችሎታ ያለው ተናጋሪ

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት

ሐ. በዝማሬ የታጀበ አምልኮ እና ምስጋና

መ. ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ምስክርነትና ሪፖርት ሲመጡ መካፈል። ብዙ ጊዜ በሌላ ስፍራ እየተደረገ ስላለው ነገር በመስማት ትምህርት ሊገኝ ይችላል።

ሠ. በመዝናኛ ጊዜ በኅብረት ምግብ መቁረስ ሊበረታታ ይቻላል።

4. የፈቃደኛ ሠራተኞች የዕረፍት ጊዜ

የሠራተኞች ዕረፍት ጊዜ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ቤተ ክርስቲያንህ ከተሳተፈች ብቻ ነው። ወደ ካምፕ ወይም ወደዚያው ቤተ ክርስቲያንህ በመሄድ መመሪያን የመቀበያ፥ የማካፈልና የኅብረት ቀናት ለሠራተኞችህ ሊኖር ይችላል። በዚህ ጊዜ አብዛኛውን መመሪያ አንተው ልትሰጥ ይገባህ ይሆናል። በዚህ ሰዓት ሠራተኞቹ የሚገጥማቸውን ችግር ወይም ድል ያገኙበትን ነገር ወይም ደግሞ የጸሎት ርእሶች ከእነርሱ በቀጥታ ለመስማት ዕድል ማግኘትህ ለአንተ ትልቅ ትርፋማ ጊዜ ነው። ይህ ጊዜ አንዱ ለአንዱ የውስጥ ግጭትና ፍርሃትን በተመለከተ የሚጸልይበት፥ እርስ በርስ በመበረታታት እና በእምነት አንዱ ከሌላው ጋር የሚታነጽበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። የፕሮግራምህን ዕድገት የምትገመግምበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። የተለየ የወጣቶችህን ፍላጎት የምትገመግምበት እናም ፍላጎታቸውን ለመድረስ የተሻለ መንገድ የምትቀይስበት ሊሆን ይችላል።

5. ምንጮች፡- ሠራተኞችህ ስለ አገልግሎቱ በተጨማሪ እንዲማሩ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን የመረጃ ክምችት ማሳደግ በጣም ይረዳል። እያንዳንዱ ያለውን ነገር አምጥቶ ሌሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጠቀሙበት ዘንድ በሚቆለፍ ሳጥን ውስጥ ሊያስቀምጠው ይችላል። በወጣቶች ፕሮግራም ላይ ይጠቀሙበት ዘንድ አንዳንድ መጻሕፍትንና አቅርቦቶችን ለመግዛት የሚያስችሉም የገንዘብ እርዳታዎች ሊገኙ ይችላሉ።

ሠራተኞች ሳያቋርጡ ራሳቸውን ለማሻሻል እንዲጥሩ ሊበረታቱ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀታቸውን ያሳድጉ ዘንድ ሊወስዱቸው የሚችሉ የት. መ.ማ ኮርሶች አሉ። እንደ ወጣት መሪ ራሳቸውን ለማሻሻል የሚረዱአቸው በራሳቸው ወጪ ሊካፈሉዋቸው የሚችሉአቸው የሥልጠና ሴሚናሮች ብዙ አሉ።

መማር መቀጠል አለበት። ማስተማር የሚችለው የሚማር ሰው ብቻ ነው። አንድ ሰው አንድ ጊዜ መማሩን ካቆመ በመሠረቱ ሌላውን ለማስተማር ውጤታማ አይሆንም። ትኩስ ምግብን ሁላችንም እንወዳለን። ይሁንና በተደጋጋሚ የሚሞቅ ነገር አንፈልግም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መዓዛ አይኖረውም። ልክ እንደዚሁ ተማሪዎች ራሱን ሁል ጊዜ ከሚያስተምረው አስተማሪ በብዙ ይጠቀማሉ።

6. ከፈቃደኞች ሠራተኞችህ ጋር መልካም የሆነ ግንኙነትን ገንባ። አንዳንድ ወጣት መሪዎች ፈቃደኞች ሠራተኞችን ዝም ብለው ሲጠቀሙ ይቆዩና ቀስ በቀስ ተስፋ ይቆርጣሉ። ይመረራሉም። አዎን በፕሮግራሙ ሊረዱቸው ነው በዚያ ያሉት፤ ይሁንና አንድ ጊዜ እንኳን ከልብ አመሰግናለሁ ብሎ ማለት ከባድ ይሆንባቸዋል።

ሀ. ለግላዊና ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዕድገት ግድ እንደሚልህ አረጋግጥላቸው። ማደግ እንዲችሉ የምትችለውን ዕርዳታ ሁሉ አድርግላቸው።

ለ. ከሥራው ውጪ ከእነርሱ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ፈቃደኛ ሁን።

ሐ. ሠራተኞችህ በራስ መተማመንን እንዲያሳድጉ እርዳቸው። ጥሩ ሥራ በሠሩ ጊዜ አበረታታቸው። ስሕተታቸውንም ለመንገር አትፍራቸው።

መ. ከሠራተኞችህ አሳብና ደጋፊ አስተያየቶችን አዳምጥ። የወጣቶችን ፕሮግራም ለማሻሻል ብዙ ጊዜ የእነርሱ ምልከታ ሊረዳ ይችላል።

ሠ. በእሑድ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፊት እነርሱን የምታቀርብበትን ቀን ዐቅድ። ስለ ሥራቸው ተናገር። ከዚያም በሽማግሌዎች እጅ መጫንና በጸሎት እንደገና ለጌታ እንዲሰጡ አድርግ። በምግብ ዝግጅት ወይም በሻይና ዳቦ ግብዣ ፕሮግራሙ ይጠቃለል።

የወጣቶች ፕሮግራም ውጤታማነት ወይም ውድቀት የሚወሰነው በወጣት መሪው ነው። እርሱ ፕሮግራሙን በማቀድና በማደራጀት ላይ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም መደረግ ያለበትን ነገር ሁሉ ሊያደርግ በፍጹም አይችልም። ጥበበኛ የሆነ የወጣት መሪ በፕሮግራሞች ሁሉ ሊረዱት በሚችሉ ፈቃደኞች ሠራተኞች ራሱን በመከበብ የተሳካ አገልግሎት እንዲገኝ ያደርጋል። መከናወን ማለት የቤተ ክርስቲያን ወጣቶቻችንን በእግዚአብሔር ቃል ላይ በደንብ ተተክለው ጌታን የሚያስደስት ኑሮን መኖርን ሲጀምሩ ማየት ነው።

በቤተ ክርስቲያን ያለው የወጣቶች ፕሮግራም ውጤታማ እንዲሆንና የወጣቶች መሪው ለወጣቶች ፕሮግራም በቂ ጊዜ እንዲሰጥ እርሱ የቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ መሆን አለበት። ያለዚያ ሊሠራ የሚገባውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት ጊዜ አይኖረውም። ይህ የአገልግሎት ቦታ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሊተኮርበት የሚገባ ቦታ ነው። በአሁኗ አፍሪካ ወጣቶች በብዙ ቁጥር ወደ ክርስቶስ እየመጡ ናቸው። ደህና አድርገን በእግዚአብሔር ቃል ካላስተማርናቸውና ካልተከልናቸው ከሃይማኖት ወደ ሃይማኖት ከስሕተት ወደ ስሕተት ሲንከራተቱ ይኖራሉ። የወጣቶች አገልግሎት ዋና ነገር ነው። እነርሱ የነገ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው። ለወደፊት እኛን የሚመሩት አሁን በሚማሩትና በሚሠለጥኑበት ነገር ላይ በመመርኮዝ ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- አዋቂና በዕድሜ የገፉ በወጣቶች ሥራ ውስጥ እንዲረዱ መገኘታቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ወጣት መሪ ከሠራተኞቹ ጋር ጥሩ ግንኙነትን የመፍጠሩ አስፈላጊነት ምን ላይ ነው? ያን ሊያደርግ የሚችልበትን ቢያንስ አምስት መንገዶችን ተናገር።

**አምስተኛ ቀን፡-** ትምህርት ሰባትን በሙሉ ከልስ። በአሥራ ቤቶች ስለሚገኙትና ተለቅ ስላሉት ወጣቶች አስብ። በሳምንታዊ ስብሰባ የተሰጡትን ርእሶች ለመወያየት ተዘጋጁ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ።

1. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን የታዳጊ ወጣቶች ፍላጎት እንሥታችሁ ተወያዩ። ኢየሱስም ለጴጥሮስ አለው፡- «ጠቦቶቼን ጠብቅ»። የእነዚህን ወጣቶች ፍላጎት ለመድረስ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ምን እየተደረገ ነው?

2. በዕድሜ ትልቅ የሆኑትን ወጣቶች ፍላጎቶችና ችግሮች እንሥታችሁ ተወያዩ። እንዴት እንዲያገለግሉ ይገባል? እንዴት በአገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ይደረጋል?

3. ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂ ሠራተኞችን በወጣቶች ፕሮግራም ላይ አሳትፋችኋልን? ካላሳተፋችሁ ለምን? ይጠቅማል ብለህ ታስባለህ? ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. ማገልገል የምትችልበትን መንገድ እና ፈቃደኛ የሆኑ አዋቂ ሠራተኞችን በምታበረታታበት መንገድ ላይ ተወያዩ።

# ትምህርት ስምንት
# የወጣቶች አገልግሎት
# (ክፍል ሁለት)

## አንደኛ ቀን፦ ለወጣቶች ፕሮግራም የቀረቡ አሳቦች

በትምህርት ሰባት ስለ ወጣቶች ብዙ ነገሮችን ተምረናል። አሁን ወደ ወጣቶች ፕሮግራም ሊስቧቸውና፥ በሚያስፈልጋቸው ነገር ሊደርሱላቸው ጠቃሚ የሆኑትን መንገዶችን እንመልከት።

ጥሩ ወጣት መሪ እና ፈቃደኛ ሠራተኞች ጥራት ላለው የወጣቶች ፕሮግራም ቁልፎች ናቸው። አንድ የድሮ ምሳሌ እንዲህ ይላል፦ «በአንበሳ የሚመሩ የበጎች መንጋ በበግ የሚመራን የአንበሶች መንጋ ያሸንፋሉ» (AEAM/ ኤ.ኢ.ኤ.ኤም፥ ገጽ 253)። ለወጣቶች አገልግሎት ጥራት ያለው መሪነት እንደሚያስፈልግ ልንክድ አንችልም። የወጣት መሪ ወጣቶችን ማገልገል በሚጀምርበት ጊዜ በጥብቅ ሊያስብባቸው የሚገቡ ጥቂት ነገሮች አሉ።

1. እያንዳንዱ የወጣቶች ቡድን አባል በእኩል ደረጃ አቀባበልና አድናቆት ሊደረግለት ይገባል። በወጣቶች ቡድን ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሁሉ እርስ በርስ ለእያንዳንዳቸው ጥሩ ስሜት እንደሚሰማቸው እርግጠኛ ሁን።

2. ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ወጣቶችን አስተምር። ለምሳሌ ወጣትን የሚፈትን ማን ነው? የፈተናው ምንጭ ምንድን ነው? በፈተና አልፎ የመሰጠት ውጤቶች ምንድን ናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዳህ ዘንድ ያዕቆብ 1፡13-15ን አንብብ። ብዙ ጊዜ ስለ ሁሉም ነገር ዲያብሎስን መውቀስ እንፈልጋለን። ነገር ግን ምሳሌ 19፡3 ሲናገር «የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምምበታለች» ይላል።

አንድ ወጣት ወደ አንድ ዓይነት ፈተና ቢሳብ ምን ማድረግ አለበት? ለምሳሌ ቢዋሽ፥ ቢሰርቅ፥ ቢያታልል፥ ዝሙትን ቢሠራ፥ እንዲሁም ለወላጆቹ ወይም ለሽማግሌዎች አክብሮት ካላሳየ የኃጢአት ይቅርታ ይኖራልን? ምሳሌ 28፡13፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡9ን ከአነበብህ በኋላ እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። በምሳሌ 28፡13 እንደተጠቀሰው ምሕረትንና ይቅርታን ለማግኘት ማድረግ የሌለብን አንድ ነገር ምንድን ነው? የምናደርጋቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ለምሳሌነት የሚበቃ ሕይወት ባላቸው ሰዎች ታሪክ፥ ለምሳሌ ዳንኤል፥ ዮሴፍ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በማተኮር ትምህርትን ስጥ። እነዚህ ሰዎች ችግር በገጠማቸው ጊዜ እንዴት እንደተጋፈጡት እና ፈተና እና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንዴት እንዳስተናገዱ አጥና።

4. አንተ ራስህ ጥሩ ምሳሌ ሁን። ጳውሎስ እንዲሁ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎ ነበር፦ «በቃልና በኑሮ በፍቅርም፥ በእምነትም፥ በንጽሕናም፥

ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው» (1ኛ ጢሞ. 4፥12)።

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች እንዲህ ለማለት ችሎ ነበር፦ «እነዚህን አስቡ ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ። የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል» (4፥9)። ምሳሌነት ያለው ሕይወት በተለይ በወጣቶች ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፦ ወጣት መሪዎችን ለመርዳት የቆመ ማን አለ? ማቴ. 11፥28–30 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ ለእርዳታ ወደ እርሱ በመጣን ጊዜ ምን ሊያደርግልን ነው ቃል ኪዳን የሰጠን? የእርሱን ቀንበር እንድንሸከም ሲል ምን ማለቱ ነው? አንድ በሬ ብቻውን ቀንበር ተሸክሞ ሊያርስ ይችላልን? ምን ያህል በሬዎች ያስፈልጋሉ? የጌታን ቀንበር ከተሸከምን ከእኛ ጋር አብሮ የሚጠመድስ ማን ነው? ይህ ነገር የሚያበረታታን እንዴት ነው? |

5) ጊዜያዊ ችግሮች በወጣቶች መካከል በዚህ በሠለጠነ ዘመን ባሉት ወጣቶች መካከል ጌታን የማያስደስቱና ለክርስትና ሕይወት ዕድገት የማይበጁ ልምምዶች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም።

ሀ. ለስሜታዊነት ጠንከር ያለ ትኩረት ይሰጣል። አያንዳንዳችን ጌታን ስለ ማመስገንና በነገር ሁሉ ለእርሱ ክብር መስጠትን መማር እንፈልጋለን። ይሁንና ከስሜት ይልቅ በብዙ የተቀደሰ ኑሮ መኖር እንደሚገባን ማወቅ አለብን። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ብዙ አትኩሮት ስንሰጥ፥ ነገር ግን ወደ ተቀደሰ ኑሮ ስለሚመራን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የምንሰማው በጣም ጥቂት ብቻ ነው (ገላ. 5፥22–26 አንብብ)።

የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደሶች እንደሆንን ወደ መዘንጋት እናዘነብላለን (1ኛ ቆሮ. 6፥19–20)። የቆሮንቶስ ሰዎች ይህንን ነገር አለማወቃቸው ጳውሎስን አስደንቆት ነበር። ስለዚህ እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፤ «ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም። ስለዚህ በሥጋችሁ ጌታን አክብሩ»።

የእግዚአብሔር መንፈስ መንፈስ ቅዱስ ነው። በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ትልቅ ሥራ ስለ ኃጢአት መውቀስና ቅዱስ የሆነ ሕይወትን እንዲኖር ማስቻል ነው (1ኛ ተሰ. 4፥7–8፤ 1ኛ ጴጥ. 1፥14–15 አንብብ)።

ወጣቶቻችንን የሚመለከት ርእሰ–ጉዳይ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን መጻሕፍት በማስተማር የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ በታማኝነት ልናስተምር እንችላለን። ጳውሎስ እንዲህ ለማለት ችሎ ነበር፦ «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም» (የሐዋ. 20፥27)። በትንተና ላይ ያተኮረ ትምህርት አጠቃላይ የሆነውን «የእግዚአብሔርን ምክር» ለማወጅ በጣም አስፈላጊ ነው።

«በአፍሪካ ያለው ክርስትና የኪሎ ሜትር ስፋት እና የሳንቲ ሜትር ጥልቀት ያለው ነው» ሲባል ቆይቷል። ይህም እውነት ከሆነ መፍትሔው በጥንቃቄና በታማኝነት የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርና ማጥናት ነው።

የጸናንና የበሰልን ክርስቲያኖች የምንሆነው ሁላችን በእግዚአብሔር የእውነት ቃል ሥራችንን ወደ ታች መዘርጋት ከቻልን ብቻ ነው።

በወጣቶች ፕሮግራም ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጠንከር ያለ አትኩሮት መስጠት እና ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሮ በእውነት በዕለታዊ ሕይወት ላይ ለመተርጎም የሚደረግ ትምህርት ማካታት እንዳለብን የማይካድ ነው። በግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው እና በቋሚ የጥሞናና የጸሎት ጊዜያቸው እንዲበረታቱ ልናደርጋቸው ይገባል።

ለ. ወጣቶች ሁልጊዜም ተቀባይነት ካለው ሥነ ምግባራዊ ሕይወት ይዘት ጋር አይጣጣሙም።

በአንዳንድ ቦታዎች ወጣቶች በወረዳቸው ውስጥ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመዘዋወር ስብሰባቸውን ያካሂዳሉ። ቅዳሜ ይገናኛሉ። ስብሰባም ያደርጋሉ፤ ሌሊቱንም አብረው ያሳልፋሉ፤ ወደ ቤታቸው ከመበታተናቸው በፊት የእሑድ ፕሮግራም በዚያው ይካፈላሉ። ስለ ፕሮግራማቸው ጉዳይ ለመነጋገር ሽማግሌዎች ሲቀርቧቸው ለመመከር አይፈልጉም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስጠነቅቀን ከወጣትነት ክፉ ምኞት እንድንርቅ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የክፋትን ገጽታ ሁሉ እንድናስወግድ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:8፤ 1ኛ ተሰ. 4:1-8፤ 5:22 አንብብ)። ያለ ዕድሜ የሚከሰት እርግዝና እና ከግብረገብ ውጪ የሆነ ሥራ እግዚአብሔርን በጣም የሚያሳዝነው ሲሆን የቤተ ክርስቲያንን ዋጋና ክብርም ይቀንሳል።

ሐ. የመገዛት መንፈስ እጥረት

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች መገዛት እነርሱን ብቻ እንደማይመለከት ይዘነጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል። «ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ» (ኤፌ. 5:21)። በክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ የመገዛት መንፈስ ሊኖር ይገባል። ይህም በማንኛውም ቦታ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ባሕርይ መሆን አለበት። እናም ይህ ወጣቶችንም የሚያጠቃልል ነው።

> 2ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ልብሱን አስቀምጦ ወገቡን በማበሻ ጨርቅ በመታጠቅ ውኃ በሳህን ቀድቶ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሊያጥብ በመነሣቱ ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ትቶልናል ( ዮሐ. 13:12-17 አንብብ)። አንዱ የሌላውን እግር የማጠብ መንፈሳዊ ትርጉሙ ምንድን ነው? አዎን አንዳችን የሌላችንን እግር የምናጥብበት ጊዜ አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለማስተላለፍ የፈለገው ትምህርት ብቻ ይሆንን? ይህ በዕለታዊ ኑሮአችን ምን ማለት እንደሆነ አብራራ።

መ. ሥራ አጥነት

ለአንድ ወጣት የሁለተኛ ደረጃን ትምህርት አጠናቅቆና የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ተቀብሎ ሥራ ማግኘት አለመቻል ስብእና የሚያሳጣ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። በአፍሪካ ግብርና ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጠው ሥራ ነው። ዘመናዊ ትምህርትን ከተማሩ በኋላ ወደ ግብርና መመለስ በደረጃ ዝቅ እንደ ማለት ይቆጠራል። ይሁንና፥ ወጣቶቻችን የጉልበት ሥራን ክቡርነት እንዲረዱ ልንረዳቸው ይገባል። «እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት» (1ኛ ቆሮ. 10:31)።

ሡ. ድኅነት

ብዙ ወጣቶች ሌሎች ችግሮች አሏቸው። ለእነርሱ የሚሆን ቦታ ስለሌለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አይቀበሏቸውም። አንዳንዶች በድኅነት ምክንያት በቤተሰብ ውስጥ በመጣ ሕመም ወይም በቤተሰብ ሞት ምክንያት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ባለመቻላቸው ለጎዳና–አዳሪነትና ለልመና ተዳርገዋል። ለንጹሕ ውኃ እና ለምግብ፥ ለልብስና ለሕክምና ከሚሆን ነገር ጋር ለመገናኘት መንገዱን አያገኙም። ለሕገ ወጥ ወሲብ እና ለወንጀል ድርጊቶች ተጋልጠው ይኖራሉ። አንዳንዶች ወጣቶች ዓይነ ሥውር፥ ደንቆሮ ወይም ሽባ ሆነዋል። ልጃገረዶች የገጠሩን ኑሮአቸውን በመልቀቅ ወደ ከተማ በሚመጡበት ጊዜ ሊወድቁ የሚችሉበት የኑሮ ሁኔታ ዝሙት አዳሪነት ብቻ ነው።

በጨለማ ኃጢአት ለተያዙና ራሳቸውን ላዋረዱ ለእነዚህ ወጣቶች ለመድረስ የቤተ ክርስቲያን ሪጅም ክንድ ወዴት ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካላችው ከትንሺ ክበባችን በስቲያ ያለብንን ለእነዚህ ወጣቶች የመድረስ ኃላፊነት በማስታወስ ክርስቲያናዊ ተግባራችንን ለሚናፍቁት የፍቅርና የርኅራኄ ልብን እናሳይ። ይህ ክርስቲያን ወጣቶች የክርስቶስን ፍቅር አሳይተው የደረሰ ሰብል የሚያገኙበት የአገልግሎት ስፍራ ነው።

የወጣቶችን ፕሮግራም በሚያዘጋጅበት ጊዜ የወጣት መሪው

1. አዲስ ነገር ፈጣሪ መሆን አለበት። ይህም ማለት አንድ ዓይነት ነገርን በአዲስና አነቃቂ በሆነ መንገድ ማድረግ ወይም መሥራት ማለት ነው። አንድ ሰው ሲናገር የመጨረሻው መጥፎ ዕቅድ ለሚቀጥለው ስብሰባ ያለፈው ሳምንት የተጠቀምክበት ዕቅድ ነው ብሏል። ወጣቶች ቀበጥባጦች እና የተለያየ ነገር የሚፈልጉ ናቸው። ይህም ማለት መሪው ትልቅ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታ ለማቅረብ አዲስ መንገድ መፍጠር አለበት ማለት ነው። ድራማ፥ ውይይት፥ ክርክር፥ በተወሰኑ አርእስት ቀልዶች፥ የክፍል ተሳታፊነት፥ የመድረክ ውይይት፥ በሪፖርት፥ በፊልም በቃለ ምልልስ፥ ወዘተ. . . ልትጠቀም ትችላለህ። አስፈላጊ እውነታዎችን ለማስተማር የታቀዱ ይሁኑ እንጂ አዳዲስ አሳቦችን ለመጠቀም አትፍራ።

2. የግል ተነሣሽነት ይኑርህ። ከወጣቶች ጋር የምትሠራ ከሆነ ብዙ ኃይልን መጠቀም እንዳለብህ አትዘንጋ። ፈልሳፊና ፈጣሪ መሆን ይኖርብሃል። አሳቦችን ለማሳደግ የምትችል መሆን አለብህ። በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎችን ማሳተፍ መቻል አለብህ። ወጣቶች በጣም እንደምትወዳቸውና ለዕድገታቸው እንደምታስብ ካወቁ ጥሩ ፕሮግራምን ለማቀናጀት ከአንተ ጋር ሊተባበሩ ይችላሉ። በማንኛውም ሁኔታ መሳተፍን ይወዳሉ። ጥሩ ፕሮግራም በመፍጠር ኅብረተሰብን ለማገልገል ተጠቅምባቸው።

3. ተሳትፎን ማበረታታት። ወጣቶች፥ ዝማሬ በመምራት፥ ጸሎት በመምራት፥ አዲስ ጎብኝዎችን በመቀበል፥ በማስተናገድ፥ መቀመጫዎችን በማስተካከል ሊሳተፉ ይችላሉ። የነገ መሪዎች ስለሆኑ አሁን እንዲሳተፉ ፍቀድ።

4. አንገብጋቢ ችግሮቻቸውን መፍታት። ፕሮግራሙ ለብዙ ነገር በሚገባ መልኩ ጊዜያዊና ወቅታዊ ፍላጎቶችን ለመመለስ መቻል አለበት። እንደ ሞርሞኒዝም፥ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (ኒው ኤጅ)፥ የይሖዋ ምስክሮች ያሉት የስሕተት ትምህርቶች ወደ አካባቢያችሁ ቢመጡ በወጣቶች ፕሮግራም ላይ ስሕተታቸው የት ላይ እንደሆነ ማሳየትና ከእነዚህ ትምህርቶች ጋር ሲጋፈጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ እንዲኖራቸው ትምህርት መስጠት አለበት።

ወጣቶች ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ ሊጠየቁ ይችላሉ። እናም ይህ በዝርዝር ተመዝግቦ በወጣቶች ፕሮግራም ላይ በተገቢው መንገድ ሊቀርብ ያስፈልጋል። በወጣቶች የፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ሊካተቱ የተገባቸው እነርሱ ልብ ያላሏቸው ነገሮችም ይኖራሉ።

- በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተሞላ ሕይወት ትምህርት
- የኢየሱስን ጌትነት የተመለከተ ትምህርት
- ምስክርነትን በተመለከተ መመሪያ
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መስጠት ምን እንደሚያስተምር

ዝርዝሩ ሊቀጥል ይችላል። ነገር ግን ራስህ ልትጨምርበት ትችላለህ።

በዚህ ትምህርታችን ላይ ልናተኩርበት የምንፈልገው ነገር ቢኖር የወጣት ፕሮግራማችን ወጣቶችን የሚስብ መሆኑን እና በተጨማሪም የሚያስተምር ፕሮግራም የሚሆንበትን መንገድ ነው። ስብሰባው የወጣቶችን ፍላጎት የሚደርስ ስብሰባ ከሆነ ወደ ፕሮግራምህ ሊጎርፉ ይችላሉ።

ሁለተኛ ቀን፡- በትውልድ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- በትውልድ መካከል ያለ ልዩነት ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህን ልዩነት ምን ፈጠረው? በአፍሪካ ካለው ሥልጣኔ ጋር የመጣ አዲስ ነገር ነውን? አደገኛና አስጊ ነገር ነውን? ይህ ልዩነት እንዲፈጠር ምክንያት የሆነው ማን ነው? ይህን ልዩነት ለማጥበብ መደረግ ያለባቸውን ነገሮች ዘርዝር። |

ወደዚህ አዲስ ትምህርት ከመግባትህ በፊት ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች ጥቂት ጊዜ ወስደህ መልስን ስጥ።

1. በትውልድ መካከል ያለ ልዩነት ምንድን ነው?

«ጎልማሶችና ወጣቶች በሰው ልጅ ኅብረተሰብ ውስጥ እርስ በርስ የሚረዳዱ ሁለት የደም ሕዋሳት ናቸው። ብዙ ጊዜ ግን ሰላማዊ በሆነ አብሮ መኖር አንድነትን ላያገኙ ይችላሉ» (<Jean-Calvin Traore, Church in Africa Today and Tomorrow> ጂን-ካልቪን ትራወሬ፥ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪካ ዛሬ እና ነገ፥ ገጽ 242)።

አሁን የምንናገረው ትውልዳዊ ክፍተት በጎልማሶችና በወጣቶች መካከል ያለውን አለመግባባት ነው። ከሥልጣኔ እና ከትምህርት ተያይዞ የመጣ አዲስ ነገር አይደለም። ሆኖም ትውልዳዊ ክፍተት በዚህ አዲስ ዕድገት ብዙ ጊዜ ሲባባስና ሲጋነን እንመለከታለን። ይህ በትውልድ መካከል ያለ ልዩነት

በዘመናት ሁሉ በተለያየ መንገድ ራሱን እያሳየ ሲኖር ቆይቷል። የዚህ ችግር ምክንያት በከፊል በጎልማሶች በር ላይ ያረፈ ነው።

ሀ. ጎልማሶች የሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።

በአፍሪካ ወግና ባሕል ሥልጣንን የሚጨብጡት ጎልማሶች ናቸው። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ነገር የመፍቀድም ሆነ ያለመፍቀድ ኃላፊነት የእነርሱ ነው። እነርሱ ነገሮችን እንዲከናወኑ የማድረግ ኃይል አላቸው። እንዲሁም የሚሰጡት ፍርድ መከበር አለበት።

ይህም ለጎልማሶች ከወጣቶች ይልቅ የተሻለ ዕድል ሲሰጣቸው፥ በወጣቶች ዘንድ እምብዛም ተቀባይነት የለውም። በጎልማሶች የባለ ሥልጣንነት አመለካከት የተነሣ የወጣቶች አሳብ ብዙ ጊዜ ተቀባይነት አላገኝም።

መሠረት ያለው ኅብረተሰብና የቆየ ልማድን ጠብቆ ለማኖር ጎልማሶች በጣም ስለሚፈልጉ በወጣቶች ላይ ጠንከር ያለ መመሪያና ደንብ ለማውጣት ይፈተናሉ። ይህም ደግሞ በወጣቶች ዘንድ ዓመጽን፥ አለመስማማትን፥ እንዲሁም ድጋፍ ማጣትን ሊያስከትል ይችላል።

ለ. ጎልማሶች ጥበበኞች ናቸው።

ጎልማሶች እንደ ጥበበኞችና ባለ ሥልጣናት ይቆጠራሉ። ይህም ማለት ወጣቶች ብዙውን ጊዜ የበታችና ከሌላው ሰው ዝቅ ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው። የእነርሱ አመለካከት ዋጋ እንዳለው አይቆጠርም። ስለዚህም ለጎልማሶች ያላቸው አመለካከት በጥያቄ የተሞላ ነው። ጎልማሶች ብዙውን ጊዜ ውሳኔያቸውን የሚሰጡት አስቀድሞ ካለፉበት ሕይወት በመነሣት ነው። ያለፉበት ልምምዳቸውን መመዘኛ አድርገው ይጠቀሙበታል። ስለዚህ ነው «የዚህ ዓይነት ነገር ከዚህ በፊት ሠርተን አናውቅም» ወይም «ሁልጊዜ እንደዚህ ነው የምንሠራው» የሚሉትን አባባሎችን የምንሰማው።

ሳይታይ የታለፈ ነገር ቢኖር ሁኔታዎች እንደሚቀያየሩና ብዙ ጊዜም ከዓመታት በፊት እንደነበሩት አለመሆናቸው ነው። ይህም ማለት ባለፈው ጊዜ የነበሩት ጠቃሚ መፍትሔዎች በአሁኑ ጊዜ ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ ማለት ነው። በተጨማሪም ጎልማሶች በተደላደለ ማኅበረሰብ ውስጥ የነበሩትን ልማዶች ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴን በቀላሉ ታግሠው እንደማያልፉት የታወቀ ነው።

በጣም ብዙ ወጣቶች ትምህርት ቤት ገብተው ተጨማሪ እውቀቶችን የማግኘት ዕድል አላቸው። ይህም በተለይ በከተማ አካባቢ ፈጣን ለውጥ እስኪመጣ ድረስ ዕረፍት ያሳጣቸዋል። ወጣቶች ብዙ ጊዜ ጎልማሶች እውቀት እንደሌላቸው ወይም ጥንታዊና ምንም የማይጠቅም እውቀት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የአባቶቻቸው ጥልቅ እምነት እና የባሕርይ ጥንካሬ ውጤት እንደሆነ ይዘነጋሉ።

የዚህ ትውልዳዊ ክፍተት ሌላው መንሥኤ የሚያርፈው በወጣቶች ላይ ነው።

ሀ. ወጣቶች ትዕግሥት የላቸውም። በትምህርት ሰባት እንደተጠቀሰው ወጣቶች ነገሮች እንዲሆኑ የሚፈልጉት አሁን ነው። አዲስ መንገድ እና አዲስ አቅጣጫ ለማግኘት ስለሚናፍቁ የጎልማሶች ዝግተኛነት አንዳንዴ በጣም ያበሳጫቸዋል።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ከሽመገሉ ሰዎች ይልቅ ወጣቶች የተማሩ ናቸው። ስለዚህ የበላይነት እና የኩራት መንፈስ ቀስ በቀስ ሊገባ ይችላል። ከጎልማሶች ይልቅ የተሻለ የሚያውቁ ይመስላቸውና ጎልማሶች በመጻሕፍት ሊገኝ የማይችል የዳበረ የሕይወት ልምድ ትምህርት እንዳላቸው ይረሳሉ።

ሐ. ወጣቶች ለትዕቢት በመዳረግ በግልጽም ሆነ በምሥጢር አሳባቸውን በኃይል ለመግለጥ ሊሞክሩ ይችላሉ። የአሉበትን አቋም በመጠየቅ እና በግለሰብ ግንኙነቶች ጉዳይ ላይ ጣልቃ በመግባት ችግርን ይፈጥራሉ። በማንኛውም ሁኔታ ሊዳብር የሚገባው ነገር በመሪነት ውስጥ ያለ መልካም ግንኙነት ነው።

እነዚህ ችግሮች አዲስ እንዳልሆኑ ተናግረናል፣ ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ናቸው። እስኪ ጌታ ስለ እነዚህ ችግሮች የተናገረውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት።

4ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጢሞ. 5፥1–2 አንብብ። ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ በአራት ዓይነት ደረጃ ላሉ ሰዎች ሊያሳይ ስለሚገባው ባሕርይ ተናግሯል። ዘርዝራቸው። ለእያንዳንዱ መልስ ተቃራኒውን ከሰጠህ በኋላ እያንዳንዱ እንዴት መስተናገድ እንዳለበት ጻፍ።

5ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጢሞ. 5፥17 አንብብ። ለታመኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምንሰጠው አክብሮት ምንድን ነው?

6ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጴጥ. 5፥1–4 አንብብ። ይህ ምንባብ ለሽማግሌዎች ነው። ማኅበሩን ማገልገል ያለባቸው እንዴት ነው? ሽማግሌዎች ማድረግ የሌለባቸውን ሦስት ነገሮች ጻፍ። ከዚያም በዚህ ምንባብ ከተጠቀሰው የተሻለውን የማገልገል መንገድም ጻፍ።

7ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጴጥ. 5፥5 አንብብ። የወጣት ሰዎች አመለካከት እንዴት መሆን እንዳለበት ነው የምትመለከተው?

8ኛ ጥያቄ፦ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የእያንዳንዳቸው ዝንባሌ እንዴት ሊሆን ይገባል? (1ኛ ጴጥ. 5፥5–7)። የቅዱሳት መጻሕፍትን ምክር ብንቀበል በትውልድ መካከል ያለውን ችግር ማሸነፍ እንችላለን ብለህ ታምናለህን?

በመደምደሚያው ላይ እንዲህ እንበል።

1. በሁሉም የዕድሜ ክልል አንዳችን ለአንዳችን መጸለይ አለብን።

2. በትሕትና አንዳችን ለአንዳችን ትዕግሥት ሊኖረን ይገባል።

3. እያንዳንዱ በእግዚአብሔር የተወደደ ነውና እርስ በርሳችን መከባበር አለብን።

4. የእግዚአብሔርን ቃል በዕለት ኑሮአችን በመኖር ማስተማር አለብን።

ሦስተኛ ቀን፡- የክርስቲያኖች ሽርሽር፡-

## ሌላው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መንገድ

ፀሐያማ ቀን ነው። ከአናት በላይ ነጩ ደመና ተንጣሏል፤ ወፎች ዝማሬዎችን ያስነካሉ። በአጠገቡ ያለው ትንሽ ወንዝ በድንጋዮች ላይ እየፈሰሰ በፍጥነት ወደ ትልቁ ወንዝ ይገባል። እየሄደም ሳለ የሚዘምር ይመስላል። በዙሪያህ ያሉትን የእጁን ሥራዎች በመመልከት ለዓለም ሁሉ ፈጣሪ ምስጋናን ለመስጠት መንፈስህ ይነሣሣል። በአጠገብህ እንዳለ ያህልም ይመስልሃል።

መዝ. 19፡1-6 አንብብ። ዳዊት የእግዚአብሔርን ቅርበት በተፈጠሩት ነገሮች ይረዳ ነበር። የመዝሙር 19ኝን ይህን ክፍል በጻፈ ጊዜ ዳዊት በየትኛው የእግዚአብሔር ፍጥረት ደስ ይሰኝ እንደነበር ጻፍ። በመንገድ ላይ ብቻህን በምትጓዝበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቅርብነት የተረዳህበትን ገጠመኝ ጻፍ።

### I. ክርስቲያናዊ ሽርሽር ማለት ምን ማለት ነው?

ትርጓሜ፡- ክርስቲያናዊ ሽርሽር ማለት ከመዝናኛ ዓይነቶች አንዱ ማለት ነው። ለሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮች በአብዛኛው በውጪ የሚሠሩበት የተደራጀ ፕሮግራም ቦታ ነው። ተሳታፊዎቹ በትንንሽ ድንኳኖች ወይም ቤቶች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። አንድ ላይ ይበላሉ፥ ያመልካሉ፥ ይማራሉ፥ ይወያያሉ፤ አንድ ላይም ደግሞ ይጫወታሉ። ሌሎችን ተግባራት ሁሉ በመተው ጸጥ ወዳለ ስፍራ በመሄድ ስለ እግዚአብሔር ተጨማሪ ነገር ለመማርና የክርስትናን ሕይወት እንዴት መኖር እንደምንችል የማወቅ ጊዜ ነው።

አንድ ሰው እንዲህ ብሏል ሽርሽር ማለት «የእንቅስቃሴ ለውጥ እና የቦታ ለውጥ ማለት ነው»። ወደዚያ መሄድ እና በእግዚአብሔር የሚያስደንቅ ምድር በመፈንጠዝ ወደ እርሱ ለመጠጋት፥ ቃሉን ለማሰላሰልና ለመጸለይም የሚያስችል ዕድል ነው። የመዝናኛ ሽርሽር ለሕፃናት፥ ለወጣቶችና ለጎልማሶች ይሆናል። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እና የእምነት ክፍሎች የሽርሽርን ጠቃሚነት ስለ ተማሩ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ በቋሚነት ይጠቀሙበታል።

ብዙ ጊዜ እያንዳንዱ ሽርሽር የሚያተኩረው ውሱን በሆነ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው። ከ9-11 ዓመት ላሉት የአንድ ሳምንት ጊዜ ሊሆን ይችላል፤ ከ12-14 ሌላ ሳምንት፤ ከ15-20 ላሉት ወጣቶች ደግሞ ሌላ ሳምንት፤ እንደገናም ከ21-40 ላሉት ወጣቶች ሌላ ሳምንት። ለጎልማሶች፥ ለቤተሰብና ለልጆች ሌላ ጊዜ ይታቀዳሉ። ሽርሽር ልጆቻቸው አድገው ለተለዩአቸው ሽማግሌዎችም ሊታቀድ ይችላል። እነርሱም መበረታታት እና መማር ያስፈልጋቸዋል።

በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ጠቃሚ ውጤት ያስገኙ የሽርሽር ቦታዎች ቁጥር እያደገ ነው። በሠለጠነው ዘመን ከፍተኛ የጊዜ ውጥረት ከሚታይበት ሕይወት ወጣ ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር እርሱ በሠራው የሚያምር ዓለም

ውስጥ ጊዜን የማሳለፍ አስፈላጊነት እየታወቀ ነው። «በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንልሃል» (ኢሳ. 30፡15)። ዳዊት በታላቁ የእረኛ ቅኔው (መዝ. 23) ስለ ለመለመው መስክ እና የዕረፍት ውኃ ይናገራል። ተፈጥሮን በመመልከትና ከእነርሱም በመማር ትልቅ የሆነ ደስታ ይሰማዋል። እናም ብዙ ጊዜ በጽሑፉ ላይ ይናገረዋል።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፡- ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የመዝናኛ ሽርሽር ፕሮግራም የሚያበረክታቸውን አስተዋጽኦዎች ዘርዝር። የሚቀጥለውን ክፍል ከማየታችን በፊት የሽርሽር ፕሮግራም ምን ዓይነት ዓላማ ሊኖረው እንደሚገባ ጻፍ። |

2. የመዝናኛ ዓላማ ምንድን ነው?

ሀ. በተሳታፊው ሕይወት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር።

ለ. ተሳታፊውን ወደ መጀመሪያው የክርስትና ሕይወቱ እና መሰጠቱ ለማምጣት።

ሐ. የክርስትና ዕድገትን ለማበረታታት።

መ. የጋራ የሆነ መቀባበል እና ፍቅር፥ ኅብረት፥ አዲስ ጓደኛ ለማፍራት ለመወያየት እና አሳብ ለመለዋወጥ፥ አንድ ላይ ለመመገብ ዕድል ይከፍታል።

ሠ. ለዕረፍትና ለፀጥታ እንዲሁም ከቤት ውጪ ወጥቶ ለመጫወት እና ለመደሰት ዕድልን ይሰጣል።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እና ጥናት እንዲሁም ለቃል ጥናት ጊዜ በሳምንት ምን ያህል ሰዓት ትሰጣላችሁ? የቤተ ክርስቲያን አባሎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በሚገባ የተተከሉ እንደሆኑ ልትሰጠው የምትችለው ማረጋገጫ አለህን። ከሌለህ ለምን? |

በቤተ ክርስቲያንህ ፕሮግራም አንድ ሰው ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት ድረስ በየሳምንቱ ለሦስት ሰዓት በቤተ ክርስቲያን ጊዜውን ቢያሳልፍ ይህ በጠቅላላው አንድ ልጅ በመደበኛ ትምህርት ቤት በ1ኛ እና በ2ኛ ክፍል የሚያሳልፈው የጊዜ መጠን ያህል ብቻ ነው። ስለዚህ ከ18-20 ዓመት ያሉ በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ወጣቶች በክርስትና እምነታቸው ገና የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው ማለት እንችላለን። ብዙ ወጣቶች ዩኒቨርስቲ ለመግባት በተዘጋጁ ጊዜ በቃሉ ላይ በቂ የሆነ እምነት የሌላቸውና ለእምነታቸው ጸንተው ለመቆም የማይችሉት በዚህ ምክንያት ይሆን? በአንድ ሙሉ ሳምንት መዝናኛ ሽርሽር ውስጥ በሕፃናትም ሆነ በወጣቶች፥ በቤተሰብ እና በሽማግሌዎች ላይ ጥልቅ የሆነ ተጽዕኖ ያሳድራል። ምክንያቱም ጠቅላላው ፕሮግራሙ የሚዘጋጀው በክፍል ውስጥ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመስጠትና ከክፍል ውጭ በሚደረጉ ማንኛውም ተግባራትም ትምህርት ሰጪ እንደሆኑ የሚታቀዱ ናቸው። በዚህ ዓይነት የክርስትና ሕይወት ጥልቅ መመሪያዎችን ማስተማር ይቻላል።

3. የኢየሱስ ምሳሌ

ጌታ ኢየሱስ ከዕለታዊ ትግል ወጥቶ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ መታደስን የማግኘት ዋጋን ያውቅ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን። አንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርት በአገልግሎት መጨናነቅ የተነካ በደከሙ ጊዜ እንዲህ አላቸው። «እናንተ ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት ዕረፉ... በታንኳም ብቻቸውን ወደ ምድረበዳ ሄዱ» (ማር. 6፡31–32)።

ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ እናነባለን። «ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ። ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ» (ማር. 1፡35)። ኢየሱስ ጌታችን በሰንበት ጊዜ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ሰዎችን በማስተማርና በመፈወስ ሥራ በዝቶበት እናገኘዋለን (ማር. 21፡34)። ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን በጠዋት በማለዳ ወደ ጸሎት ሲሄድ እናየዋለን። ይህ ለአባቱ የሚሰጠው የሰንበት አምልኮ ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ልማዱ ነበር።

10ኛ ጥያቄ፦ ማቴ. 14፡23፤ 26፡36፤ ማር. 6፡46፤ 14፡32፤ ሉቃ. 6፡12፤ 9፡28 አንብብ። ከእነዚህ ጥቅሶች የምትማረው አንድ ትምህርት ምንድን ነው? ለኢየሱስ ውጤታማ አገልግሎት እና ከእርሱ ለሚመጣ ኃይል ምንጩ ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

### 4) የሽርሽር ዕለታዊ ፕሮግራም

እነዚህ ለጥሩ የሽርሽር ፕሮግራም የተሰጡ የፕሮግራም አሳቦች ናቸው።

| | |
|---|---|
| 1:00–2:00 | መልበስና የግል የጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር |
| 2:00–3:00 | ቁርስ በጸሎትና በዝማሬ መከፈቻ። |
| 3:00 | ዳስን ወይም ድንኳንን ማጽዳትና የሽርሽር ተሳታፊዎች የየዕለት ተግባር የሆነውን ዕቃዎችን ማጠብና መጥረግ፥ ለምግብ አትክልቶችን ማዘጋጀት፥ ውኃ መቅዳት፥ አካባቢን ማፅዳት በመሳሰሉት መርዳት አለባቸው። |
| 3:45–4:45 | የጠዋት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ መሪነት |
| 4:45–5:15 | በአማካሪዎች አማካኝነት ጥቅሶችን በቃል የማጥኛ ጊዜ |
| 5:15–6:15 | በቡድን ተከፍሎ መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር፥ ውይይት ወይም የሕፃናትን መጻሕፍት ባዶ ቦታ በመሙላት መሥራት። |
| 6:15–7:15 | የምሳ ጊዜ |
| 7:15–8:30 | የዕረፍትና የፀጥታ ጊዜ (ሕፃናት የቃል ጥናት ያጠናሉ) |
| 8:30–10:30 | መዝናናት፥ መንሸራሸር፥ መረብ ኳስ፥ እግር ኳስ፥ ዋና፥ በጀልባ መንሳፈፍ፥ ማውራትና መጎብኘት፥ የማንበብ ጊዜ። |
| 10:30–11:30 | በአስተማሪው የሚመራ የከሰዓት በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት– (ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍለ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ያልተጠናውን የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ |

እንድናጠና ዕድልን ይሰጣል)

11:30–1:30　　የማታ እራትና ነፃ ጊዜ

1:30–3–00　　የማታ ፕሮግራም መዝሙርና የወንጌል መልእክት

ከአንተ ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ ይህን ፕሮግራም ማስተካከል ይቻላል። ነገር ግን የሽርሽር ፕሮግራም በምናስተካክልበት ጊዜ አንዳንድ ሊታወሱ የሚገቡ ነገሮች አሉ።

1) ይህ ውድ ጊዜ ነው። ጥሩ አድርገህ ተጠቀምበት። የሚከተሉትን ጨምር።

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መስጠት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ፍሬ አሳቦች ላይ በቡድን መወያየት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን በተለያዩ የዕድሜ ክልል ባሉት ሰዎች ላይ መተግበር አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ለ. ወንጌልን ማዳረስ ደግሞ ሰፊ ቦታ ሊሰጠው ይገባል። የደኅንነት መልእክት በአንድ ለአንድ ምስክርነት ሲነገርም ሆነ ለቡድኑ በሙሉ ሊሰበክ በሚገባ ግልጽ መሆን አለበት።

ሐ. መዝሙር አስፈላጊ ነው። አዲስ መዝሙርንና አዝማቾችን ለመማር ጊዜን አዘጋጅ። በመዝናኛ ሽርሽር ቦታ መዘመር ቡድኑን ደስተኛ ያደርገዋል። በሙዚቃ ብቁ ችሎታ ኖሯቸው ሰዎችን አዳዲስ መዝሙሮችና አዝማቾችን ማስተማርና መምራት የሚችሉ ሰዎች እንዳሉህ እርግጠኛ ሁን። ከዚህ በፊት የተዘመሩ አዝማቾችና መዝሙሮችን በከንቱ የመደጋገም ጉዳይ ሳይኖር በጥሩ ቃላት የተሞሉ እና በደስታ፥ በማሰላሰል የሚዘመሩ ከሆኑ ትልቅ በረከት ሊሆኑ ይችላሉ።

መ. አምልኮ አጠቃላይ የስብሰባ ጊዜ እና ለጥቂት ቡድን ሥራ ጥምር በጥንቃቄ ሊታቀድ ይገባዋል።

ሠ. በመዝናኛ የሽርሽር ቦታ እሳት ማንደድ የተለመደ ነገር ነው። እያንዳንዱ ሳምንታዊ ሽርሽር በመጨረሻው ማታ በጥሩ ሁኔታ በሚነድ እሳት ዙሪያ ቁጭ በማለት እያንዳንዱ ሰው በዚያ ሽርሽር ቦታ እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዴት እንደባረከውና በሽርሽር ቦታ ምን አዲስ ነገር እንደተማረ ምስክርነት በመስጠት መጠናቀቅ አለበት። በተለይ ለአዲስ አማኞች የመጀመሪያ ምስክርነታቸውን ለመስጠት እና እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸው ለመናገር ጥሩ አጋጣሚ ነው። በልባቸውና በሕይወታቸው ስለሚደረገው ነገር እግዚአብሔርን በታላቅ ደስታ የሚያመሰግኑበት ጊዜ ይሆናል። ጠንክሮ ለሚሠራው ክፍል ደግሞ የመበረታቻ ጊዜ ሊሆን ይችላል።

2. መታወቅ ያለባቸው አንዳንድ ነገሮች

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ወይም ሰንበት ት/ቤት ወይም በወጣቶች ፕሮግራም ላይ የተማሩትን ነገር በሽርሽር ቦታ አትደገም። አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጥናት ወይም አዲስ ርእስን ለሽርሽሩ ቦታ አዘጋጅ።

ለ. በጥንቃቄ ዐቅድ። ለተንሸራሻሪዎቹ በረከት ሊሆን የሚችል ማንኛውንም የፕሮግራም መልክ ቸል ልትል አይገባም። ይህም መዝሙርን፥ ተናጋሪዎችን፥ ለተንሸራሻሪዎቹም ትልቅ በረከት ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች በተመለከተ ጥበብን የተከተለ ዕቅድን ያካትታል።

ሐ. በተንሸራሻሪዎች ላይ ጫና አታብዛ ወይም ሠራተኞችን በሥራ ብዙ አትጥመድ። ፕሮግራሙ በተለያየ እና በተመጣጠነ ነገር ላይ እንዲሁም ጥበብ የተሞላ የጊዜና የኃይል አጠቃቀም ላይ ማተኮር አለበት። የመዝናኛ ሽርሽር እና የደስታ ቦታ መሆን አለበት እንጂ ከአንዱ ፕሮግራም ወደ ሌላው ፕሮግራም የምንቸኩልበት ዓይነት መሆን የለበትም። ሊያሰላስሉ፥ ሊያስቡ፥ ሊጸልዩ፥ ሊነበኙ፥ አዳዲስ ሰዎችን ሊተዋወቁ፥ እንዲሁም ከቀረበው መንፈሳዊ ነገር ተመሳሳይ ውጤትን የሚያገኙበት ጊዜ መሆን አለበት።

ሕፃናት በሚሳኡ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገብተው እንዳይገኙ የሕፃናት የመዝናኛ ሽርሽር ተገቢ ቁጥጥር ያስፈልገዋል። በተለይም ለልጆችና ለወጣቶች የማማከር ሠራተኞች በጣም ጠቃሚ ናቸው። ስለ ተግባራቸውና ስለ ሥልጠናቸው በሚቀጥለው ትምህርት ላይ እንነጋገራለን።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፦ ባለህበት ቦታ የመጽሐፍ ቅዱስ የመዝናኛ ሽርሽር ለማድረግ ይቻላልን? የማይቻል ከሆነ ልትጠቀምበት የምትችለው ቦታ እንዳለ አስብ፦ ቤተ ክርስቲያንህን ተጠቅመህበት ከሆነ የገጠማችሁ ችግር ምን ነበር? የመዝናኛ ሽርሽሩ ከቤተ ክርስቲያን ኮንፈራንስ የተለየ ነውን? በምን መንገድ? |

## አራተኛ ቀን፦ የክርስቲያን ሽርሽር፥

## ለቤተ ክርስቲያን ሌላ የማስተማሪያ ዕድል

1. የሽርሽር ቦታ አደረጃጀትና አስተዳደር።

ሀ. የሽርሽሩ አዘጋጅ ቦርድ። በዚህ ቦርድ ውስጥ ያሉት ሰዎች ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም አውራጃ ወይም ደግሞ ከአንድ ዘን ቢመጡም እንኳ የሚገለገል ኅብረተሰብ ወኪሎች ናቸው።

ተግባራቸው የሽርሽሩን የተግባር መርሆ ማዘጋጀት፥ የሽርሽሩን ዓላማ መንደፍ፥ ሠራተኞችን መቆጣጠር፥ ስለ ገንዘብ ኃላፊነትን መውሰድ እና አጠቃላይ ለሽርሽሩ የሚወጣውን ወጪ ሁሉ ማካሄድ ነው።

ለ. የሽርሽሩ የሥራ መሪ። ቦርዱ የሽርሽር መሪ ሆኖ ሊመራ የሚችል አንድ ብቃት ያለው ሰው መፈለግ አለበት። ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ልምምድ ያለው፥ የማደራጀትና የመወከል ችሎታ ያለው፥ ከሰዎች ጋር አብሮ መሥራት የሚችል እና ለልጆች፥ ለወጣቶችና ለጎልማሶች ፍቅር ያለው መሆን አለበት። ከቦርዱ ጋር በተግባራትና ዕቅዱ ላይ በሙሉ መተባበር አለበት።

ሐ. የሽርሽሩ ጸሐፊ። ቦርዱ የሥራ መሪውን መዝገቦች በጥንቃቄ በመያዝ፥ በመላክ እና በማስታወቂያ ሥራ ያግዘው ዘንድ ጸሐፊ መፈለግ አለበት። ይህ ሽርሽር በየዓመቱ ለብዙ ሳምንታት ለተለያዩ የዕድሜ ክልሎች የሚካሄድና የቤተ ክርስቲያኒቱ ከዓመት ዓመት የሚቀጥል ፕሮግራም ከሆነ ጸሐፊ መመደብ የማይታለፍ ተግባር ነው።

መ. የመዝናኛ የሽርሽር ስፍራ ሰባኪዎች፥ ዘማሪዎችና የፕሮግራም መሪዎች። ቦርዱ ቀደም ብሎ ውጤታማ ሰባኪዎች፥ አስተማሪዎችና መሪዎች በማዘጋጀት ጥሩ ፕሮግራም ያቅዳል። የመዝናኛ ሥራ መሪ ቦርዱን ያግዛል።

ሠ. የሽርሽሩ ሠራተኞች

1. አማካሪዎች፡- ቦርዱ እንደ አማካሪ ሆነው የሚያገለግሉ ቅጥር ወይም ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ለማግኘት ኃላፊነቱን ይወስዳል።

2. የሽርሽሩ ነርስ፡- በሽርሽሩ ተሳታፊዎች መካከል ሊደርስ ለሚችል ሕመም እርዳታ ለመስጠት።

3. ምግብ ሠሪዎችና ገዢዎች፥ የጥገና ሠራተኞች፥ የልዩ ልዩ እንቅስቃሴ አስተባባሪዎች፥ ሐይቅ አካባቢ ከሆነና ዋና የሚኖር ከሆነ የሕይወት አድን ሠራተኞች መዘጋጀት አለባቸው። ብዙ ጊዜ እነዚህን ዓይነት ሥራዎች ለመሥራት ኃላፊነት የሚወስዱ ዝግጅቱን ካቀዱት አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ዘንድ ይኖራሉ።

2) የመዝናኛ የሽርሽር ስፍራ አማካሪዎች ኃላፊነት

ለልጆች የሚደረገው የመዝናኛ ሽርሽር ዋና ዓላማ ከ6 እስከ 8 ለሚሆኑ ተካፋዮች አንድ አማካሪ ኖሮአቸው ለሁልጊዜ አብሮአቸው እንዲሆን ነው። ይህም ማለት፥ በድንኳናቸው ወይም በክፍላቸው ውስጥ አብሯቸው በመቆየት በቀን ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴ መቆጣጠር፥ የየዕለቱን የጥሞና ጊዜ ማካሄድ፥ በቃል ጥናት ጊዜ ተካፋዮቹን መምራት እና ለክፍሎች የቤት ሥራዎቻቸውን ማሠራት ናቸው። ተካፋዮቹን ለማነጋገር ሁልጊዜ ተዘጋጅተው ይገኛሉ። ችግሮቻቸውን ይፈታሉ። እንዲሁም በክርስቶስ ስለ መኖር ያማክሯቸዋል። ብዙ ጊዜ ልጆችን ወደ ክርስቶስ የሚመሩና ከደኅንነት በኋላ የሚያበረታቷቸው ናቸው። በመዝናኛ ሽርሽር አገልግሎት ከፍተኛ ሚና አላቸው።

3) የሽርሽር ቦታ አማካሪ ማን ሊሆን ይችላል?

በመጀመሪያ የሽርሽር አማካሪዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ ያወቁ መሆን አለባቸው። ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እና ተቀባይነት ያላቸውና የክርስቲያን ባሕርይ የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። ጤንነታቸው የተጠበቀና ወንዶችና ሴቶች ልጆችን የሚወዱ መሆን አለባቸው።

4. አማካሪዎችን ማሠልጠን

የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን ለማሠልጠን የተጠቀምንበት መመሪያ ለአማካሪዎች በጣም ጥሩ ነው። በትምህርት አራት፥ አምስትና ስድስት ውስጥ ያለውን ተጠቀሙ። ይህ ሥልጠና ለአማካሪው በቤቱ እንዲያጠናው ትምህርቱ ተልኮለት ሊጀመር ይቻላል። ከዚያም የመዝናኛ ሽርሽሩ ከመጀመሩ በፊት አማካሪዎች ለአንድ ሳምንት ሥልጠና መምጣት አለባቸው።

በተጨማሪ አማካሪዎች በሽርሽሩ ዓላማ መርሆዎችና የጠባይ እና የቅጣት አሠራሮች ላይ አንድ አቋም መያዝ አለባቸው። በሽርሽር ስፍራ ከልጆች ጋር ስለሚገጥም ነገር አልጋ ላይ መሽናት፥ ናፍቆት፥ አለመታዘዝ፥ ከሌሎች ልጆች ጋር መጋጨት ይህ ሁሉ ሊገለጥላቸው ይገባል። የሽርሽር ጉዞው ኃላፊ እንደ እነዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ነገሮችን የሽርሽሩ ተካፋዮች ሕይወት በሚያ ሳድግ መንገድ እንዴት መፍትሔ እንደሚሰጥባቸው አማካሪዎችን መርዳት አለበት።

የሽርሽሩ አስፈላጊነት ተንሸራሻሪዎች በመንፈሳዊ፥ በአእምሮ፥ በማኅበራዊና እና በስሜት እንዲያድጉ ነው። በዕድሜያቸው ክልል ካሉት ጋር አብሮ መኖርና መቆየት ከላይ በተዘረዘሩት መንገዶች ሁሉ ሊረዳቸው ይችላል።

ዳይሬክተሩ እና አማካሪዎች፥ አስተማሪዎች፥ ዘማሪዎች፥ እና አስተባባሪዎች ሁሉ ለመነጋገር፥ ለመካፈልና አብሮ ለመሆን እንዲችሉ በእያንዳንዱ ቀን ከቁርስ በኋላ በጽዳት ሰዓት የሠራተኞች ስብሰባ ማድረጉ መልካም ነው። አጭር የጥሞና ጊዜን በአንድነት ሊካፈሉ ይችላሉ። በየቀኑ ችግሮችን እየተወያዩ ሊጸልዩባቸው ይችላሉ። ወደ ጌታ ስለመጡ ሰዎች ከተንሸራሻሪዎቹ የሚመጣው ጥሩ ዜና ወይም መባረክ፥ ሪፖርት ተደርጎ አንድ ላይ ደስታን መካፈል ይቻላል።

አማካሪዎችም ልጆች በትምህርት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ወይም ሌሎች ሥራ በሚያሠሯቸው ጊዜ ዕረፍትን ሊያገኙ ይችላሉ። ማማከር ከባድ ሥራ ነው፤ እናም ጠንካራ ወጣቶችን ይጠይቃል።

> 12ኛ ጥያቄ፡— ስለ ቤተ ክርስቲያንህ አስብ። የሽርሽር ፕሮግራም ለትምህርት ፕሮግራም እንዴት ሊጠቅም ይችላል? ሽርሽር ለማድረግ የተሰጡ ኀልማሰችን ይጠይቃል። ቤተ ክርስቲያንህ የሽርሽሩን አገልግሎት መምራት ይችላል ብላ ልትጠራ የምትችለው ሰው አላትን?

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. አስተማሪው በአጭር የጥሞና ጊዜ ይምራ።

2. የጸሎትና የምስጋና ርእሶች ተከፋፍላችሁ የጸሎት ጊዜ ይኑራችሁ።

3. ከተማሪዎች ሊነሣ የሚችለውን ጥያቄ ውሰድ።

4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይባቸው።

ሀ. ለምንድን ነው ብዙ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን የሚተዉት? ከእምነት ውጪ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው? በትምህርት 7 እና 8 ላይ ከተማርከው ለዚህ ችግር መፍትሔ ነው የምትለውን ፈልግ።

ለ. የትውልድ መጋጨት በቤተ ክርስቲያንህ አለን? ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው? የትውልዱን የአሳብ ልዩነት ለማጥበብ አንተ ምን ልትረዳ እንደምትችል አስብ።

ሐ. የሽርሽር ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያንህ አካባቢ ሊሠራበት የሚችል ነገር ነውን? ከእንደዚህ ዓይነቱ ፕሮግራም የሚገኙ መልካም ውጤቶችን ጥቀስ። ሊያጋጥሙ ይችላሉ ብለህ የምታስባቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

# ትምህርት ዘጠኝ

# ወንዶችን ማገልገል

## አንደኛ ቀን፡— የወንዶች ባሕርያትና እና ፍላጎቶቻቸው

ወንዶች በጣም አስፈላጊ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው። ከጠቅላላው አባላት ቢያንስ 40 በመቶ ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ፥ ትልቅ ተጽዕኖ የማሳደር ብቃት አላቸው። ይሁንና፥ ለመንፈሳዊ ዕድገታቸው የሚያግዝ ፕሮግራም አይታቀድም። በእርግጥ በእሑድ አገልግሎት በታማኝነት ይካፈላሉ። ይሁንና ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ወንዶች እንደ ፍላጎታቸው ሊታነጹ የሚችሉበትን ትምህርት ወይም የአገልግሎት ሥልጠና አታዘጋጅም።

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ወንዶችን ለማስተማርና ለማሠልጠን ሁነኛ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል። አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች ሳምንታዊና ወርሃዊ ስብሰባዎች በሚገባ ተዘጋጅተው ይካሄዳሉ። ነገር ግን ለወንዶች እንዲህ ዓይነት ፕሮግራም አይዘጋጅም።

1. የወንዶች ባሕርይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚታየው

ሀ. በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸው። ዘፍ. 1:26-27፥ 31 እና 2:7። በእነዚህ ጥቅሶች እይታ «ሰው» የሚለው ቃል የሚወክለው ሁለቱንም ጾታ ስለሆነ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩት ወንዶችም ሴቶችም ናቸው። ይህ የሚከተሉትን አሳቦች ያካትታል።

1. ሰው በአመክኒዮ ረገድ እንደ እግዚአብሔር ነው። ሰው ማሰብ፥ ምክንያት መስጠት እና ማስታወስ ይችላል።

2. ሰው በስሜታዊ ሂደቱ እግዚአብሔርን ይመስላል። ሰው ሊያፈቅርና ሊፈቀር ይችላል። ሊናደድ ወይም ገርነቱን ሊያሳይ ወይም ሊሰማው ይችላል።

3. ሰው የመምረጥ ችሎታ ስላለው እግዚአብሔርን ይመስላል። የመምረጥ ነፃነት ስላለው፥ ሰው እግዚአብሔርን በሚመስል ኑሮ ወይም ከተሰጠው መለኮታዊ ውክልና በሚጻረር መልኩ ሊኖር ይችላል።

4. ሰው በግብረገባዊ ተፈጥሮው እግዚአብሔርን ይመስላል። ሰው የእግዚአብሔርን እሴቶች ወደ መጋራቱ ሊያድግ የሚችል ሕሊና አለው። ሰው የሕሊና ወቀሳን ስለሚለማመድ በመልካምና በክፉ መካከል መምረጥ ይችላል። ሰው የመምረጥ ነጻነት ስላለው በተገቢው መንገድ ሊያድግ፥ ሊበላሽ ወይም ሊደነድን ይችላል።

5. ሰው የማይሞት መንፈስ ስለአለው እግዚአብሔርን ይመስላል። የሰው ሥጋዊ አካሉ ይሞታል፤ መንፈሱ ግን እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል።

6. ሰው በሥጋዊ አካሉ ሳይሆን በማንነቱ ማለትም በጠቅላላ ስብእናው እግዚአብሔርን ይመስላል። እናም ይህ «እኔነት» ተብሎ ይጠራል። ኃጢአትን የሚመርጠው እኔነት ነው። ክፋት ከእኔነት ይወጣል። መለወጥ ለጽድቅ መሠረትን እንደገና ይጥላል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን የውስጥ ሰውነት ስለሚለውጥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማት እንደገና ማደግ ይችላል። (ይህ አስተዋጽኦ የተወሰደው ከ<Daniel, Introduction to Christian Education> ዳንኤል፥ የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ ነው።)

ለ. ወንዶች ከፈጣሪያቸው ጋር ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ አላቸው።

«ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክ ድምፅ በገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ» (ዘፍ. 3፡8)። አዳምና ሔዋንን እየፈለገ ነበር። ከእነርሱም ጋር ኅብረት ለማድረግ ይፈልግ ነበር። 1ኛ ዮሐ. 1፡4 ሲናገር «ኅብረታችን ከአብ ደግሞም ከልጁ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ነው» ይላል።

በዚህ ቦታ ሰው የሚለው አጠቃላይ ስም ለወንድም ለሴትም የሚሆን መጠሪያ ነው። አሁን ደግሞ «ሰው» የሚለው ቃል በተለይ ወንድን ብቻ የሚያመለክተውን እንመርምር።

ሐ. ወንድ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ የሚያደርግ ኃላፊነት አለበት።

እግዚአብሔር በዔድን ገነት ከአዳም ጋር በተነጋገረበት ጊዜ የተለየ ኃላፊነት ሰጥቶት ነበር። ገነትን እንዲንከባከባት እና እንዲጠብቃት ነግሮት ነበር። ደግሞም መልካምንና ክፉ የምታስታውቀውንም ዛፍ እንዳይበላ ከልክሎት ነበር። ይህ ትእዛዝ የተሰጠው ከአዳም ጎን በተወሰደ የጎድን አጥንት ሴት ከመሠራቷ በፊት እንደሆነ ይታወቃል። ወንድ ስለ እነዚህ ነገሮች በቀጥታ ተጠያቂነት ለእግዚአብሔር ነበረበት። ስለሚሠራውም ነገር ሁሉ መልስ መስጠት ነበረበት (ዘፍ. 2፡28–30፤ 2፡15–17)።

መ. ሰው ክብር አለው።

ያዕቆብ 3፡9–10 ሲናገር «በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን ከአንድ አፍ በረከት እና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞች ሆይ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም» ይላል።

ሚስቶች ለባሎቻቸው ሊታዘዙ፥ ሊያከብሩዋቸውና ሊፈሩአቸው ይገባል። በቤት ውስጥ ያለውን የበላይነት መብት እግዚአብሔር ለወንድ ሰጥቶአል (ኤፌ. 5፡22–24፥ 32)። ሣራ ለአብርሃም እየታዘዘችለት ጌታዬ ብላ ትጠራው ነበር።

«ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም። ሴት ግን የወንድ ክብር ናት» (1ኛ ቆሮ. 11፡7)።

«ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ» (1ኛ ቆሮ. 11፡3)።

በተፈጥሮ ውስጥ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነ የሥልጣን ሰንሰለት አለ፤ ስናከብረውም ደስታንና እኩልነትን በምድራዊ ግንኙነት ላይ ይፈጥራል።

ሠ. ወንዶች ከሚስቶቻቸው ጋር የሕይወት ጸጋ ተካፋዮች ናቸው (1ኛ ጴጥ. 3:7)።

ከሚስቶቻቸው ጋር በሚኖሩበት ጊዜ ግድ ሊላቸውና በአክብሮት ሊያኖሯቸው ይገባል። በ1ኛ ጴጥሮስ 3:7 ለሁሉም ሰው የተላለፈ መልእክት አለ፤ «እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፥ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሯቸው»።

ረ. ወንዶች ልጆቻቸውን የሚያሳተምሩና ቤታቸውን የሚመሩ ናቸው።

መዝሙር (78):3–7፤ ዘዳግም 4:9፤ እና 6:4–9 አንብብ። በተጨማሪ 1ኛ ጢሞቴዎስ 3:4–5፥ ኤፌሶን 6:4፤ እና ቆላስይስ 3:21 አንብብ። እነዚህን ጥቅሶች ሁሉ በዚህ ኮርስ ብዙ አይተናቸዋል፤ ይሁንና እንደገና መከለሱ መልካም ነው። እግዚአብሔር ለወንዶች ልጆችን በማሠልጠንና በማሳደግ ረገድ ትልቅ ኃላፊነት ሰጥቷል።

2) የወንዶች ፍላጎት

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በጎልማሳነታቸው ጊዜ ብዙ የተለያዩ ደረጃዎችን ያልፋሉ። ወጣቶች ጎልማሳ በሚሆኑበት ጊዜ ተጽዕኖ ከሚያደርጉባቸው ገጠመኞች ውስጥ የሥራ መስክን መምረጥ፥ ራስን መቻል፥ ጋብቻና ቤትንና ቤተሰብን ማስተዳደር ይገኙባቸዋል። መካከለኛ ጎልማሳነት በሁለት ትውልዶች መካከል ማለትም ዕድሜያቸው እየገፋ በሚሄድ ወላጆችና ቤታቸውን ለቅቀው ለመውጣት በሚዘጋጁ ልጆች የተያዘ ነው። በዕድሜ የገፉ ጎልማሶች ወደ ማርጀትና ወደ ሽምግልና እየገቡ ናቸው። ልጆቻቸው ሁሉ አድገው የራሳቸውን ኑሮ ይመሠርታሉ። የትዳር ጓደኛን ከማጣት የሚመጣ ኃዘንና ብቸኝነት ሊከሰት እንደሚችል የታወቀ ነገር ነው።

እንግዲህ በዚህ የለውጥ ጊዜ ውስጥ ጎልማሶች ሴቶችና ወንዶችም በተለያዩ የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ እንዴት እንደሚያልፉ ከሚመሩአቸው ጠቢብና ግድ ከሚላቸው አስተማሪዎች መንፈሳዊ ዕውቀትን ማግኘት እንዳለባቸው ግልጽ ነው።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ በወንዶችና በፍላጎቶቻቸው ላይ በተለይ ያነጣጠረ ምን ፕሮግራም ይካሄዳል? ከሌለ የወንዶችን ፍላጎት ለመድረስ አንተ የምታቀርበው አሳብ ምንድን ነው? |

## ሁለተኛ ቀን፡- ውጤታማ የሆነ የወንዶች ሥርዓተ ትምህርት

1.ጎልማሶች እንዴት እንደሚማሩ

ጎልማሳ ተማሪዎች ከደገ ልጅ በጣም የራቁ ናቸው። ስለዚህም ጎልማሳን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች የተለየ አቀራረብ መጠቀም አለባቸው።

ሀ. እያንዳንዱ ጎልማሳ በራሱ ግላዊ ታሪክ እና ፍላጎቶች የታጠረ ልዩ ሰው ነው። ስለዚህም አስተማሪ በክፍሉ ውስጥ ስለ አለው ግለሰብ ሥረ-መሠረት፥ በኅብረተሰቡ ውስጥ ስላለው ቦታ፥ ስለሚያስበው ነገር፥ እንዲሁም ስለሚያስቡት ጉዳዮች ሊያውቅ ያስፈልገዋል።

ለ. ጎልማሳው በሚማርበት ጊዜ የቀለም እውቀትን ብቻ ሳይሆን፥ እንደ ሙሉ ሰው ይማራል። በክፍል ውስጥ የሰማውን ከዕለታዊ ኑሮው ጋር እያዛመደ በተግባር እንዴት እንደሚሠራውም ያስባል።

ሐ. ዋጋ ያለው ልምድ፥ ተጨባጭ አሳብና በሚገባ የተቀናጁ ዝንባሌዎችን ወደ ትምህርቱ ያመጣል።

መ. ንቁ ተሳታፊ በሚሆንበት ጊዜ ከሁሉ በተሻለ ሁኔታ ይማራል። ይሁንና ተሳታፊ የሚሆነው በፈቃደኝነት ብቻ እንጂ በቃል ብዛት አይደለም። ስለዚህ ተሳትፎው እንዲነሣሣ አስተማሪው በጥንቃቄ ማቀድ አለበት።

ሠ. ከሌሎች ጋር አሳብ በመለዋወጥና በቡድን ውስጥ በመታቀፍ ይማራል። በክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ከተማመነ እና ዋጋ ያላቸው መሆናቸውን ከተረዳ በኋላ አመለካከታቸውን ለመቀበል ራሱን ያዘጋጃል፤ እንዲሁም በእነዚያ አመለካከቶችና ዝንባሌዎች ራሱን ያያል፤ ሕይወትን ይመዝናል።

2. ጎልማሶችን የማስተማር ግቦች

ለጎልማሶች አስተማሪ አቅጣጫን የሚሰጡ ሦስት መሠረታዊ ግቦች አሉ።

ሀ. አስተማሪው ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ማቅረብ አለበት። አስተማሪው ተማሪዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል በጥበብ መርምረው ለዘመኑ ያለውን መልእክት እንዲያገኙ ይመራቸዋል። ትምህርቱ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን የሚከልስና የነገሩንም ፍች ለተማሪዎች ሕይወት መርምሮ ትርጉም የሚሰጥ ማድረግ ይገባዋል።

ለ. በተጨማሪም አስተማሪው ተማሪዎቹ የተማሩት ትምህርት እንዴት ለዕለታዊ ሕይወታቸው እንደሚጠቅማቸው ሊመራቸው ይገባል። ስለዚህ ሁለተኛው ግብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ካለንበት ሕይወት ጋር ማዛመድ ነው።

ሐ. ሦስተኛው ግብ ጎልማሶችን ለአገልግሎት ማስታጠቅ ነው። አንድ ጊዜ መሠረታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የጎልማሶችን ሕይወት ከቀረጸ በኋላ ውጤቱ ለሌሎች ግድ የሚለን መሆን አለበት። አስተማሪው ክፍሉ የተማረውን ተግባራዊ በሆነ መንገድ በዕለታዊ ሕይወቱ እንዲጠቀምበት ሊመራ ይፈልጋል። የእርሱን ክፍል በወንጌል ስርጭትና በደቀ መዝሙርነት ሊያሠለጥን ከዚያም ሌሎችን ሰዎች እንዲያገለግሉ ዕድል እንዲያገኙ መንገድ ሊፈልግ ይገባል።

2ኛ ጥያቄ፦ ቲቶ. 2፡1–2 አንብብ። ቲቶ አዋቂ ሰዎችን እንዲያስተምር ተነግሮት የነበረውን አሳብ በዝርዝር ጻፍ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን ገጸ ባሕርያት አስብና ስማቸውን ከእያንዳንዱ መመዘኛ ትይዩ ክፍል ጻፍ። ይህ አዋቂዎችን ለማስተማር ጥሩ ትምህርት ሊሆን እንደሚችል ትመለከታለህን? በጥንቃቄ ጥናት ብታደርግበት ስድስት ትምህርቶች ይወጣዋል።

3ኛ ጥያቄ፦ ቲቶ አዋቂ ሴቶችንም እንዲያስተምርና ከዚያም እርሱ ያስተማራቸው አሮጊቶች ሴቶች ደግሞ ወጣት ሴቶችን እንዲያስተምሩ ተነግሮታል። ቲቶ. 2፡3–5 አንብብ። ቲቶ ለአዋቂ ሴቶች የሚያስተምራቸው ምን ነበር? አዋቂ ሴቶች ወጣት

ሴቶችን ምን ነበር የሚያስተምሯቸው? በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ወጣት ሴቶችን ሊያስተምሩ የሚችሉ ሴቶች አሉን? ይህ ትምህርት የተዘጋጀውና የተደራጀው በቤተ ክርስቲያን ነውን? ወይስ አዋቂ ሴቶች ራሳቸው ዐቅደው የሚያደራጁት ነው?

4ኛ ጥያቄ፡- ቲቶ ለወጣት ወንዶች የሚያስተምራቸው ምንድን ነበር? ቲቶ ምን ዓይነት አስተማሪ እንደነበረ ግለጽ።

5ኛ ጥያቄ፡- ቲቶ 2፡9-10 አንብብ። በዚህ ቁጥር ቲቶ እንዲያስተምራቸው የተጠቀሱት ቡድኖች እነማን ነበሩ? ይህ ቡድን በአሁኑ ጊዜ አለን? በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ሠራተኛ ስለ አሠሪው ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት ልናዛምደው የምንችለው መመሪያ አለን?

6ኛ ጥያቄ፡- ቲቶ. 2፡11-15 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች የተጻፉት ለማን ነው? እዚህ ምን ትእዛዛት እናገኛለን? በዝርዝር ጻፋቸው።

**ጳውሎስ ከእርሱ ጋር አብሮ ለሚሠራው ለቲቶ እንዴት ማስተማር እንደሚገባው እየጻፈለት ነበር። እያንዳንዱ ሰው ያከብረው ዘንድ በሥልጣን የሚናገርና ራሱን የሚገዛ እንዲሆን ያበረታታዋል።**

**ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 5 ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ በቁጥር 1 እና 2 ላይ የሚለውን አንብብ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚመክረው አዋቂዎችን እንዴት ማነጋገር እንዳለበት ነው። ወጣቶች ወንዶችን ማነጋገር ያለበት እንዴት ነበር? አዋቂ ሴቶችንስ? ወጣት ሴቶችንስ? ይህ ጥሩ ምክር ነበር ብለህ ታስባለህን?**

**የቤተ ክርስቲያን ጉዳይን በሚገባ የሚመሩትን መሪዎች በተለይም በመስበክና በማስተማር የሚያገለግሉትን ጳውሎስ ያከብራል። 1ኛ ጢሞ. 5፡17-18። እጥፍ ክብር እንደሚገባቸውና ደመወዛቸውን መክፈሉ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በታማኝነት ከሳምንት ሳምንት ለሚያስተምሩና ለሚሰብኩ አገልጋዮች የሚገባቸውን ክብር እንስጣቸው። ለእነርሱም እንጸልይ፤ በጸጋው ዙፋን ሥር ይዘናቸው በመቅረብ ፍላጎታቸው ሁሉ እንደተሟላ እርግጠኛ እንሁን።**

3. ወንዶችን ምን እንደምናስተምር

**ወንዶች በየዕለቱ የግል የጥሞና ጊዜ የመውሰዱን ጥቅምና ዘዴ እንዲያውቁ ሊማሩ ይገባል። ይህ ልምምድ የየዕለቱ ልምምድ ከሆነ ለአንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለመረዳትና ከሕይወቱ ጋር ለማዛመድ በጣም ጥሩ ከሆኑት መንገዶች አንዱ ነው።**

**ወንዶች ስለ ጸሎት መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ስለ ጸሎት ያወራሉ። ጠቃሚ እንደሆነም ያውቃሉ፤ ነገር ግን ለመጸለይ ጊዜ አይወስዱም። በቤተ ክርስቲያን የሚካሄድ የጸሎት ስብሰባ የኅብረት ጸሎትን ቢያበረታታም፥ ወንዶች በግል ጸሎት መጠመድ ያስፈልጋቸዋል። ማቴዎስ 6፡5-14 አንብብ። ማቴዎስ ወደ ቤት የመግባትን ከዚያም በር ዘግቶ ወደ አብ የመጸለይን አስፈላጊነት ይናገራል።**

**ወንዶች ስለ ምስክርነት መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል። መሠረታዊ የደኅንነት ደረጃዎችንና እንዴት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራት እንዳለባቸው በጥንቃቄ መማር አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ በብዙ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች**

አእምሮ ውስጥ ስለ ደኅንነት ብዙ የተምታቱ ነገሮች አሉ። በየጊዜው ሳያቋርጡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ነገር ግን ያልዳኑ ሰዎች አሉ። የመዳንን መንገድ በጥንቃቄ የሚያብራራላቸው አላገኙም፤ ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ፈጽሞ አልተቀበሉም። ይህ አሳዛኝ ስለሆነ ሊስተካከል ይገባዋል።

ወንዶች ጥበባዊ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ሊበረታቱ ይገባል። ጥሩ የሆኑ የት.መ.ግ ኮርሶች አሉ። እንዲሁም ወንዶች ሰዎችን በእምነታቸው ይገነቡ ዘንድ የሚመሩ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ አሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ገጸ ባሕርያት ማጥናቱ ለወንዶች ትልቅ በረከት ሊሆን ይችላል። የአብርሃምን፥ የሎጥን፥ የይስሐቅን፥ የያዕቆብን፥ የዮሴፍን፥ የሙሴን፥ የኢያሱን፥ የጌዴዎንን፥ የሳኦልን፥ የዳዊትን የሰሎሞንን፥ የኤልያስን፥ የኤልሳዕን፥ የዳንኤልንና የኢሳይያስን ሕይወት ማጥናት በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ጥንካሬና ድካም በመማር በዚህ ክፉ ዓለም እንዴት መኖር እንደምንችል ብዙ መመሪያ ሊሰጠን ይችላል።

## ሦስተኛ ቀን፦ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች አገልግሎት

### 1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የአገልግሎት ሥራ ይካሄድ ዘንድ እግዚአብሔር ስጦታ ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች ሰጥቷል። ስለዚህም መጋቢውና ሽማግሌዎች አገልግሎቱ ይካሄድ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን አባላትን የሚያሠለጥኑ፥ የሚወክሉና የሚያዘጋጁ መሆን አለባቸው።

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህ አሳብ የላቸውም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ እነርሱ መሸከም እንዳለባቸው ይሰማቸዋል። እነርሱ ብቻ በደንብ እንደሠለጠኑ ያስባሉ። ሥራውንም እነርሱ ብቻ ካልሠሩት በስተቀር በትክክል የሚሠራ አይመስላቸውም። አንዳንዶች ደግሞ ከፍተኛ የሥልጣን ጥማት ስላላቸው ያሉበትን የኃላፊነት ስፍራ በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ሥልጣናቸውን ለማሳየት ይጠቀሙበታል። ይህም ጉባኤውን በዝምታ ተቀምጦ የሚነገረውን ብቻ የሚቀበል ተመልካች ያደርገዋል። ወደ ውጪ ለመድረስና የሌሎቹን ሕይወት ለመንካት ኃላፊነት የለባቸውም። እንዲህም ሊሉ ይችላሉ፤ «ደህና፥ ሳምንቱን ሙሉ ተግተን እንሠራለን፤ የፓስተራችንን ደመወዝ እንከፍላለን። ሌላ ተጨማሪ ነገር መሥራት ለምን ያስፈልገናል?»

ቤተ ክርስቲያንህ እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ካላት አገልግሎትን ወደ ተራው ሕዝብ ለማድረስና ለማካፈል ብዙ ጸሎትንና ቆራጥነትን በርጋታና በጥንካሬ መሥራትን ይጠይቃል። መጋቢው በጣም ጎበዝና ውጤታማ ቢሆንም እንኳ ቤተ ክርስቲያኒቷ በተገቢው መንገድ እንድትንቀሳቀስ አስፈላጊ የሆኑትን ሥራዎች ሁሉ መሥራት አይችልም።

ወደ ላይ ከፍ ከፍ ብሎ ያረገው ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሰዎች ለአገልግሎት ሥራ ያዘጋጅ ዘንድ ስጦታን ሰጠ። ኤፌ. 4፡11-16 አንብብ። በዚህ ክፍል ውስጥ ስጦታን የሰጠው ማን ነው? የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታ ከግልጋሎት ላይ ቢያውሉት አካሉ በጤናማ ሁኔታ የሚሠራ ይሆናል።

7ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡12-30 አንብብ። ጳውሎስ ስለ አካል በዚህ ስፍራ ምን ያስተምራል? እያንዳንዱ የአካል ክፍል ሁሉ የተሰጠውን ተግባር ከፈጸመ ውጤቱ ምን ይሆናል? ከቁጥር 29-30 ለጥያቄዎቹ የተሰጠው ግልጽ መልስ ምንድን ነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡11 አንብብ። ለወንዶች ስጦታን የሰጠው ማን ነው? የትኛው ስጦታ መሰጠት እንዳለበት የሚወስነው ማን ነው?

8ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 12፡3-8 አንብብ። እዚህም እንደገና ስጦታ «አካሉ» በሚገባ እንዲንቀሳቀስ ሲሰጥ እናያለን። ሁሉም ስጦታ ለአንድ ሰው አልተሰጠም። በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በዝርዝር ጻፍ። እያንዳንዳቸው ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጤንነት ሊያበረክቱ የሚችሉትን ነገር ተናገር። እነዚህን ስጦታዎች እግዚአብሔር ከሰጠን የበላይ ነኝ ለሚል አስተሳሰብና ለራስ ጽድቅ ቦታ ይኖረው ይሆንን? ቁጥር 6፥ «በተሰጠን ጸጋ መጠን የተለያየ ስጦታ አለን» ይላል። ስለዚህ ምክንያት ስጦታችንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ለማነጽና ለመገንባት መጠቀም አለብን።

9ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጴጥ. 4፡10-11 አንብብ። ስጦታዎች የተሰጡት ለግል ጥቅም ነውን? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የስጦታዎች ዋናው ዓላማ ምንድን ነው? የመንፈሳዊ ስጦታዎች የመጨረሻ ግብ ምንድን ነው?

መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ለመገንባትና ለማበረታታት እንደሆነ ተመልክተናል። ሁሉንም ስጦታ የያዘ አንድም ሰው የለም። ነገር ግን አሐዱ-ሥሉስ የሆነው አምላክ እንደወደደ ይሰጣል። የስጦታዎቹ መሰጠት ዋና ዓላማ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ይወደስና ይመስገን ዘንድ ነው።

## 2. መንፈሳዊ ስጦታዎችን ልንጠቀምባቸውና ልናሳድጋቸው ያስፈልጋል

መንፈሳዊ ስጦታዎች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ቢሆኑም፥ እኛ ልጆቹ ልናሳድጋቸው ይገባል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሏል፤ «እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ» (2ኛ ጢሞ. 1፡6)። እንደገና በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15 እንዲህ እናነባለን፤ «የእውነት ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ»።

10ኛ ጥያቄ፦ ፊልጵስዩስ 2፡19-24 አንብብ። ጳውሎስ ከእርሱ ጋር አብሮት በሚሠራው በዚህ ወጣት ላይ ትልቅ እምነት ነበረው። ይህ ወጣት ማን ነበር? ጳውሎስ ያደነቀው በእርሱ ውስጥ ያለው ዓይነተኛ መልካም ነገር ምን ነበር?

11ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ጢሞ. 6፡11-12 አንብብ። በ1ኛ ጢሞ. 6፡3-10 ላይ እንደተዘረዘሩት ክርስቲያን ሠራተኛ ከሚሠራው ሥራ ተዘናግቶ ወደ ሌላ እንዲያስብ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ። በቁጥር 11 እና በ12 ላይ ለእኛ ጥሩ ምክር የሚሆን ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሚናገረው ምንድን ነው?

3. በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ለፈቃደኛ ምእመናን መክፈት

አንዱ ሌላውን የሚያገለግልበት ማንኛውም የአገልግሎት ቦታ በቤተ ክርስቲያን ላለው ሙሉ ጊዜውን ላልሰጠው ፈቃደኛ አገልጋይ ሊከፈት ይችላል። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ጉብኝት

በሽተኞችን መጎብኘትና ኃዘንተኞችን ማጽናናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሴቶችና ወንዶች ሊሳተፉ የሚችሉበት የፍቅር አገልግሎት ነው። እንዲሁም ተስፋ የቆረጡትን፥ የተጨነቁትን ወይም በተለያየ ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ የማይመጡትን መጎብኘትም ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሁሉ መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። የሚጎበኛቸው የቤተ ክርስቲያን አባል ከእነርሱ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፥ አብሮ መጸለይ እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲያገኙ ለመርዳት መሞከር አለበት።

ለ. ወንጌልን ማሰራጨት

የቤተ ክርስቲያን አባላት የጠፉትን ሰዎች የመፈለግና እንዴት እንደሚደርሷቸው ማሰብ አለባቸው። እንደ ክርስቲያኖች፥ ከክርስቶስ ውጪ ላሉ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ ገሃነመ እሳትና የፍርድ ቦታ እንደሚጠብቃቸው እናምናለንን? ያለ ክርስቶስ የሚኖሩ ቤተሰቦቻችን፥ ጓደኞቻችንና ጎረቤቶቻችን ወደዚያ ስፍራ እንዳይሄዱ ግድ ብሎን እንጠነቀቅላቸዋለን? ይህን ካወቅንና ካመንን በክርስቶስ ሆነው እንድናያቸውና የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ ጥልቅ የሆነ ግዴታ ሊሰማንና የምንችለውን ሁሉ ልናደርግ ይገባል። ጌታ ኢየሱስ፥ «ሂዱ» ብሎናል። ሊድኑበት የሚችሉት መንገድ ይህ ብቻ ነው። የማያምኑ ሰዎች ብዙም ወደ ቤተ ክርስቲያን አይመጡም። ቤተ ክርስቲያን ወደ እነርሱ ልትሄድ የተገባ ነው።

ሐ. ማስተማር

ፈቃደኛ የሆነው ምእመን ሊሠለጥንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ወይም ትንንሽ ቡድኖችን ሊመራ ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታቸው ጥሩ የሆነ መሠረት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፤ እናም ሌሎችን በማስተማር ረገድ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። በትንሽ ቡድን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት በኅብረትና በጸሎት ብዙ ጥቅም ለቤተ ክርስቲያን አባላት ሊያገኙ ይችላሉ። ስለ ጥናት ቡድን ትምህርት አሥራ አራትን እይ።

መ. ማማከር

ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት በማማከርና በማበረታታት ረገድ ስጦታ አላቸው። በመሪነት ምሳሌ ውስጥ ሰዎች አንዱ የሌላውን ሕይወት በመቀበል፥ በማበረታታትና በማነሣሣት ከጌታ ጋር የተጣበቀ ሕይወት እንዲኖራቸው መገፋፋት ያስፈልጋል።

12ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 10፡19-25 አንብብ። «እናድርግ» የሚለውን ቃል በዚህ ክፍል አምስት ጊዜ እናገኛለን። እነዚህ አምስቱ ትእዛዝ- አዘል አነጋገሮች ለእግዚአብሔርና ለባልንጀሮቻችን ስላሉብን ኃላፊነቶች ብዙ ያስተምሩናል። እነዚህን ቃሎች በልባችን

ውስጥ «እናድርግ» እና ሌሎች ለጌታ ባላቸው ፍቅርና መሰጠት እንዲያድጉ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንጠቀምባቸው።

ሠ. አስተዳደር

በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የማስተዳደር ችሎታ ያላቸው ወይም ሥልጠና የወሰዱ አባላትን የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን በመልካም ሁኔታ እንዲያግዙ ተጠቀሙባቸው። እነዚህ ሽማግሌዎች ጸሐፊዎች፥ ገንዘብ ያዦች፥ የኮሚቴ መሪዎች፥ የሕንፃ ሥራ አስኪያጆች ሊሆኑ ይችላሉ።

ረ. ጸሎት

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው የጸሎት አገልግሎት ውስጥ ድርሻ ሊኖረው ይገባል። ይህ የጸሎት ስብሰባዎችን እንዲሁም በቤት የሚደረግ የግል ጸሎትን ሊያጠቃልል ይችላል። የማንኛውም ሥራ መሠረቱ ጸሎት ነው። ቤተ ክርስቲያን የሰይጣንን ግዛት ማጥቃት ከጀመረች ሰይጣንም የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ማጥቃት ይጀምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ሳናቋርጥ እንድንጸልይ ይነግረናል። ከእኛም እንዲሸሽ ሰይጣንን መቃወም ያስፈልገናል።

በማንኛውም ቦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ፈቃደኛ ሕዝብ እንደ ስጦታውና እንደ ችሎታው በዋነኛነት መሳተፍ አለበት። እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ ስፍራ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት። የምትሠራ ቤተ ክርስቲያን የምታድግ ቤተ ክርስቲያን ናት። እያንዳንዱ ሰው የቤተ ክርስቲያኑ አንድ ክፍል እንደሆነ ሲሰማው ሌሎችን የሚጠቅም ጽኑ ፍላጎትና በዚያም የሚገኝ ደስታ በሚያስደንቅ መንገድ ሊከሰት ይችላል።

ብዙ ጊዜ የሚሠራ አንድ ስሕተት አለ። ይህም ሰዎችን ስጦታቸው ባልሆነ ቦታ አስቀምጦ ኃላፊነት መስጠት ነው። አባላትን በማጤን እግዚአብሔር በምን በኩል እንደሚጠቀምባቸውና እንደሚባርካቸው ማየት ያስፈልጋል። ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ማንኛውም ስጦታ ስንጠቀምበት በረከቱ ለሌሎች ሰዎች ይከተላል። ደግሞም ስጦታው ላለው ሰው አገልግሎትን የመፈጸምና የማሟላት ነገር በሕይወቱ ይሰማዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባላትን በጥንቃቄ በመመልከት እንደየስጦታቸው በየቦታው ሊመድቧቸው ይገባል። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በረከት ይፈስሳል።

## አራተኛ ቀን፦ የወንዶች ለአገልግሎት ወደ ውጪ መውጣት

1) በአፍሪካ ኅብረተሰብ ውስጥ ወንዶች ያላቸው ከፍተኛ ስፍራ

በአፍሪካ ኅብረተሰብ ዘንድ ወንዶች እንደ ውሳኔ ሰጪዎችና የሥልጣን ባለቤቶች በመሆን አክብሮትን ያገኛሉ። በብዙ ስፍራ የቤተሰብ መጋቢዎች፥ እንዲሁም የኅብረተሰቡ ሃይማኖትና ባሕል ጠባቂዎች ናቸው። (Church in Africa Today and Tomorrow, p. 165)

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የተናገራቸው ጥቂት የመጨረሻ ቃላት በማርቆስ 16፡15–18 ይገኛሉ። እንዲህም አላቸው «ሂዱ እና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ...»

ይህ ዓለምን በወንጌል የማዳረስ ኃላፊነት የተጫነው በወንዶች ላይ ነው። እውነት ነው በአንዳንድ የምዕራብ ዓለም ክፍል በወንጌል መልእክተኛነት የሚያገለግሉ ሴተላጤዎች አሉ። ነገር ግን የዚህ ምክንያት የሚመስለው ወንዶች ለመሄድ አለመፈለጋቸው ነው። ብዙ ወንዶች የቤት ደስታና ምቾትን እንዲሁም የተደራጀ ገቢን በመምረጥ ለተልዕኮው ጥሪ ጆሮ ዳባ ልበስ ሲሉ ሴቶች ከገርነትና ከእሺ ባይ መንፈሳቸው የተነሣ ለጥሪው ምላሽ ሰጥተዋል።

2) በአፍሪካ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምላሽ ምን መሆን አለበት?

ሀ. በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ውጪ ወንጌልን የማሠራጨት አስፈላጊነት በስፋት ይታያል። ይህም ማለት በራሳቸው አገር ውስጥ ወደሚገኝ ወደ ሌላ ጎሣ መሄድ ማለት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ከራሳቸው አገር ወሰን በማለፍ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ሰዎችን ለክርስቶስ መድረስ ማለት ነው።

ለ. ይህ የመልካም ዕድል ቀን ነው። ዶክተር ቢያንግ ካቶ፥ «እነዚህ ቀኖች በአፍሪካ ውስጥ የደስታ ቀናት እንደሆኑ አበክሬ ለመናገር እፈልጋለሁ። ዕድሎች ገደብ የላቸውም። በጫፍ ላይ ነን ያለነው፤ ልናቆመው በማንችለው የነፍሳት መከርና በሺህ የሚቆጠሩ አማኞችን ደቀ መዝሙር በማድረጉ ዋና ጥርመሳ ላይ ነን፥ ወይም ክርስትና በአፍሪካ ውስጥ ገጥሞት የማያውቀውን ኃይለኛ የጨለማ ሰዓት ሊጋፈጥ ነው ማለት ነው። ይህም የሚወሰነው የመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመስማትና ለመታዘዝ ባላቸው ንቃት ነው። (Church in Africa Today and Tomorrow, p. 166)

ሐ. «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» ለሚለው የኢየሱስ ቃል ምላሽ ለሰጡ ሰዎች ሥልጠና ሊሰጥ ያስፈልጋል። መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና የመጀመሪያው ቀዳሚ ተግባር ነው። ከዚያም ከባሕል–ዘለል አገልግሎት ጋር እንዴት እንደሚስማማ መመሪያ ማግኘት አስፈላጊ ነው። በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ያሉ ሙስሊሞች፥ አረማውያን፥ ኦርቶዶክሶች ወይም ሌሎች ሊደረሱ የታሰቡ ቡድኖች ለመድረስ፥ ሰዎችን ለማዘጋጀት ኮርሶችን እንዲወስዱ ማድረግ አስፈላጊ ይሆን ይሆናል።

መ. «በጥሪ ለሚወጡ» ለእነዚህ ሰዎች መጓጓዣ፥ ምግብና ማረፊያ እንዲሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ መስጠት አለባት።

ሠ. የእነዚህም ወንዶች ሚስቶች በሌላው አገር ባሕል ውስጥ ለመኖር ሊሠለጥኑና ከባሎቻቸው የሚፈለግባቸውን «ተስማሚ ረዳትነት» እንደሚገባ መወጣት ይፈለግባቸዋል።

ረ. የእነዚህን ቤተሰብ ልጆች ትምህርት በተመለከተ ሊታሰብ ይገባል።

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፤ «እናንተ፥ ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ» ( ዮሐ. 4፡35)።

«ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም። ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ ጴጥ. 3፡9)

ጌታም መከሩ አሁን እንደደረሰ ተናግሯል። እያንዳንዱ ሰው ወደ ንስሐ ይመጣ ዘንድ የእርሱ ምኞት ነው። የምንዘገየው እኛ ብቻ ነን ። ወደ እያንዳንዱ የዓለም ማዕዘን ይህንን ወንጌል ተሸክመን እንድንዞር የእኛን ምላሽ እየጠበቀ ነው።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፡- በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁሉ፥ ለአሕዛብ ሁሉ በረከት ይሆኑ ዘንድ አይሁዶችን መባረክ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር። ዘፍጥረት 12፡2-3 አንብብ። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ምን ነበር? በተስፋው ላይ የተገባለት ተጨማሪ ቃል ኪዳን ምን ነበር? ምንስ ተጨማሪ ውጤት ተስፋ ተገብቶለታል? ዘፍጥረት 18፡18 አንብብ። በዚህ ጥቅስ በኩል ማን ነበር በአብርሃም የሚባረከው? |

እንደ አብርሃም ቀን ዛሬም እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ በኩል አሕዛብን ሊባርክ ይፈልጋል። ከጨለማ ወደ ብርሃን እንደ መሻገርና፥ ከኩነኔና ከፍርድ አምልጦ ከወቀሳ ነፃ በመውጣት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደተገኘው የክብር ነፃነት መድረስን የመሰለ ትልቅ በረከት ሊኖር አይችልም። ልናውጀው የሚገባ መልእክት ይህ ነው። ሁሉም ሰው ይህን አዋጅ የሚሰማበትን ቀን ማፍጠን አለብን።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- በአንተ አካባቢ ወንጌልን ያልሰሙ ወይም ምላሽን ያልሰጡትን የሰዎች ቡድኖች ስማቸውን በዝርዝር ጻፍና አዘጋጅ። እነርሱን ለመድረስ ምን ጥረት ተደርጎ እንደነበር ጻፍ። ለአንተ ጎሳ ቀና አመለካከት አላቸው ወይስ የጠላትነት? የአንተ ቤተ ክርስቲያን እነርሱን ለመድረስ ሸክም አላትን? እነርሱን በወንጌል ለመድረስ እስካሁን የተደረገ ጥረት አለን? ምላሹስ ምንድን ነበር? |

5ኛ ቀን፡- ትምህርትን ዘጠኝን ሁሉ ከልስ። ለሳምንታዊ ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለሳምንታዊ ስብሰባ የተለመደውን መንገድ ተከተል።

### የመወያያ ርእሶች

1. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ወንዶችን ለማስተማር በአሁኑ ጊዜ ምን እየተደረገ እንዳለ ተወያዩ። ወንዶችን ለማስተማር ይህ ትምህርት የሰጠህ አዳዲስ አሳቦች አሉን? ምን ምን ናቸው?

2. በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው በአገልግሎት ንቁ ተሳትፎ አላቸውን? ካልሆነ ምን ማድረግ ይችሉ ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ብዙ ሰዎችን በኅብረተሰብህና በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ንቁ አገልግሎት እንዲሰጡ እንዴት ማሳተፍ ትችላለህ?

3. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ምን የታቀደ ወንጌልን የማዳረስ ፕሮግራም አለህ? ምን ያህል ሰዎች ይሳተፉበታል? መደበኛ ያልሆነ የወንጌል ስርጭት ይካሄዳልን? የቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች ለጎረቤቶቻቸው ይመሰክራሉን? በሥራ ቦታ አብረዋቸው ለሚሠሩ፥ ለዘመዶቻቸውና ለጓደኞቻቸው ይመሰክራሉን? እነርሱን ለማሠልጠን ምን ፕሮግራም አለህ?

# ትምህርት አሥር

# የሴቶች አገልግሎት

## አንደኛ ቀን፡- በአፍሪካ የሚገኙ ሴቶች ባሕርይና ፍላጎት

1. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማወቅና መታዘዝ ሕይወትን ይለውጣል።

ለሴቶች ሁሉ የሚሆን የታወቀው ታሪክ የማርታና የማርያም ነው። አንድ ቀን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ሊጎበኟቸው ወደ ቤታቸው መጡ። ማርታ የቤተሰቡ ታላቅ እኅት ልትሆን ትችላለች። ለኢየሱስና ለደቀ መዛሙርቱ ቤቷን ከፈተች። የእርሷ እኅት ማርያም ኢየሱስ የሚያስተምረውን ነገር ለመስማት ከእግሩ ሥር ተቀመጠች።

ለብዙ ሰዎች የሚሆን ምግብ ለማዘጋጀት ማርታ በሥራ ተወጥራ ነበር። እኅቷ ስላልረዳቻት በጣም ተጨንቃና ተናድዳም ነበር። በመጨረሻም ልትቋቋመው ስላልቻለች ወደ ጌታ መጥታ አቤቱታ አቀረበች። «ሥራውን ብቻዬን እንድሠራ እህቴ ስትተወኝ አንተ ግድ አይልህምን? እንድታግዘኝ ንገራት» አለች።

ኢየሱስም መልሶ፥ «ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ ትታወኪማለሽ፥ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አለ» (ሉቃ. 10፡38-42)።

ጌታ ትኩረቷን ለመሳብና አንድ ነገር ብቻ ያስፈልግ እንደነበር ያስታውሳት ዘንድ ሁለት ጊዜ ስሟን ጠራ። ይህ በሁለት መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡- ምናልባት ጌታ እንዲህ ማለቱ ሊሆን ይችላል፡- «ብዙ ዓይነት ምግብ መብላት አያስፈልገንም። አንድ ነገር ብቻ ይበቃል»። እንደ ሴቶች ልንማር የሚገባን አንድ ነገር ይህ ነው። ጌታ በቤት ውስጥ ያለውን ነገር ያውቃል እናም «ያ አንድ ነገር» በደስታ ቢቀርብ እርሱ ይባርከዋል። ሌላኛው ትርጉም ሊሆን የሚችለው ደግሞ አንድ የሚያስፈልገው ነገር ከእግሩ ሥር ቁጭ ብሎ እርሱ የሚያስተምረውን መስማት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ማርያም የተሻለውን ነገር መርጣለች። በቤት ባለ ኃላፊነት በቀላሉ መያዝና መጠመድ በዚህም ምክንያት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መርሳት ቀላል ነገር ነው። ማርያም መስማትንና መማርን መርጣለች። ኢየሱስም ይህንን ደግፎላታል።

በዮሐንስ 11 እንደገና ስለ እነዚህ እህትማማቾች እናስብ። ማርታና ማርያምን በዚህ ስፍራ በትልቅ ችግር ውስጥ እናገኛቸዋለን። ምክንያቱም የሚወዱት ወንድማቸው አልዓዛር በከባድ እና ለሞት በሚያስጋ በሽታ ታሞ

ነበር። ወዲያውኑ ወደ ኢየሱስ መልእክትን ላኩ። ቀጥሎ የሚያስገርም ነገር እናነባለን። «ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር። እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ዋለ» (ዮሐ.11፡5–6)። ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እስከ አሁን ድረስ አራት ቀን ሆኖት አገኘው። ሆኖም ኢየሱስ የሚያደርገውን ያውቅ ነበር። አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት ብቻ ሳይሆን በዚያም የተከታዮቹንም እምነት ማጠንከር ነበር።

ታሪኩን ለመከለስ ዮሐንስ. 11፡7–14 አንብብ። ኢየሱስ በደረሰ ጊዜ ማርታም ኢየሱስን፥ «ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፤ አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው»። አሁን «አውቃለሁ» ብላለች። የተለየች ማርታ እንደሆነች እናያለን። ቁጥር 24 ላይ ይህንኑ ደግማ ትናገራለች። «በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ»። የተሻለውን ነገር እንድትመርጥ ማርታ የኢየሱስን ግሣጼ ተቀብላ ነበር። የእርሱንም ትምህርት እየተማረች ነበር። ሁለት ጊዜ «አውቃለሁ» ብላለች። ኢየሱስ ትንሣኤና ሕይወት እርሱ እንደሆነ ከተናገረ በኋላ እንደዚህ አለች። «አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ» አለችው (ቁ. 27)። አሁን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሢሑ እንደሆነ አመነች። ይህ አይሁዳዊት ለሆነች ለአንዲት ሴት ትልቅ እርምጃ ነው። ኢየሱስን በእርግጥ እንደ ተስፋው መሢሕ አድርጎ መቀበል በማንዛቤዋ ላይ ያለውን እድገት እናያለን። እናም እርሷ በአደባባይ ልታገኘው ፍርሃት አልነበረባትም።

እርሷ የተረዳችውን ነገር በግልጽ የመናገሯ ጉዳይ ከባሕርይ ለውጥ የመጣ ነበር። በቀስታ ወደ እኅቷ ማርያም ቀጥ ብላ ሄደችና፥ «መምህሩ በደጅ ነው አንቺንም ይጠይቃል» አለቻት። ኢየሱስን እንደ አስተማሪ ተረዳችው። እናም በፈቃደኝነት ከእርሱ ለመስማትና ለመማር ቻለች። አሁን በእኅቷ ላይ አልተቆጣችም። ነገር ግን በዝግታ እኅቷን ጠራቻትና ተናገረቻት፤ «ኢየሱስ ይፈልግሻል»። እርሷ የተለወጠች ማርታ ናት።

መዝሙር (119)፡129–130፥ «ምስክሮችህ ድንቆች ናቸው፤ ስለዚህ ነፍሴ ፈለገቻቸው። የቃልህ ፍቺ ያበራል። ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል» ይላል።

እንግዲህ በጥንቃቄ በተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በኩል እግዚአብሔር በሴቶች ሕይወት መሥራት የሚችለው ይኸው ነው። ኢየሱስ በዮሐንስ 15፡3፥ «እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ» ብሏል።

> 1ኛ ጥያቄ፦ በቤተ ክርስቲያናችሁ የሴቶች ቁጥር ከመቶ ምን ያህል እጅ ነው? ከሴቶች ባሕርያት ጥቂቶቹን ጥቀስ? ሴቶች ከወንዶች በምን ይለያሉ? በአፍሪካ ያሉ ሴቶች ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ጥቂቶቹን ጥቀስ።

2. የሴቶች ባሕርያት

ሴቶች ከወንዶች የሚለዩባቸው ብዙ መልካም ብቃቶች አሏቸው። እግዚአብሔር ሴትን የፈጠረው የተለየች አድርጎ ነው። እንደ ወንድ እንድትሆን ሳይሆን ለወንድ የሌለውን እንድታሟላ ነው።

ሀ. የሚያዝንና የሚራራ ልብ አላቸው

ለ. አፍቃሪ

ሐ. እንግዳ ተቀባይ

መ. የሰዎች ስሜትና ፍላጎት በቶሎ የሚሰማቸው

ሠ. ዓይነአፋርና አንዳንዴ ገለል ማለት የሚወዱ

ረ. ቤትን ቤት የሚያደርጉ

ሰ. የቤት ውስጥ ሥራ የተማሩ (ሙያ ያላቸው)

ሸ. መንፈሳዊ ምላሽን መስጠት የሚችሉ

ቀ. ለሥራ የተሰጡና ብዙ ጊዜ ስለ ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ የሚጠነቀቁ

በ. ለመቅረብ የማይከብዱ

ተ. የባል ረዳት

ቸ. ለልጆቻቸው የሚራሩና የሚንከባከቡ

ሚስቶችና እናቶች የቤተሰብ የልብ ትርታ ናቸው ልንል እንችላለን። በቤት ውስጥ የተደላደለች ጽኑ ማዕዘን በመሆንዋ፥ የልጆችን ከክፉ መጠበቅ፥ የባሏን ደስታ፥ እንዲሁም የቤቱ አኗኗር በሰላም የመካሄዱን ጉዳይ በተመለከተ ዋናውን አስተዋጽኦ ታበረክታለች።

3. የአፍሪካ ሴቶች በተለይ በገጠር የሚኖሩት የሚጋፈጡአቸው ችግሮች፥

2ኛ ጥያቄ፦ በተለይ ሴቶች ብቻ የሚጋፈጡዋቸውን ችግሮች ዘርዝር። አንዳንዶቹ ዓለም አቀፍ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ በአፍሪካ ብቻ ያሉ ናቸው። እነዚህን ችግሮች ሊያሸንፉ የሚችሉባቸውን አዲስ ፈጠራዎች በዝርዝር ጻፍ።

ሀ. ብዙ ጊዜ ሴቶች ለራሳቸው ካላቸው ዝቅተኛ አመለካከት የተነሣ ይጎዳሉ። ከወንዶች በታች ያነሰ ዋጋ እንዳላቸው ሆኖ ይሰማቸዋል። ራሳቸውን እንደ ተቀጣሪ ሠራተኛ፥ ልጅ አሳዳጊ፥ የቤተሰብ ሸክም ተሸካሚ፥ በቤት ውስጥ ያሉ ፍላጎቶች አሟይ አድርገው ይቆጥራሉ።

ለ. በየቀኑ ለረጅም ሰዓት ይሠራሉ፤ ብዙውን ጊዜ በቤት ውስጥ በመሥራት፥ ሕፃናትን በመንከባከብ፥ ምግብን በማዘጋጀት፥ በእርሻ ውስጥ በመሥራትና ከብቶችን በመጠበቅ በኃይል ይሠራሉ። ብዙ ጊዜ በጣም ይደክማቸዋል።

ሐ. ከቤት ኃላፊነት ጎን ቀላል ሸቀጦችን ማለትም ቅቤ፥ አይብ፥ እህል፥ ማር፥ ዶሮ፥ አትክልት እና የተዘጋጁ ምግቦችን ወደ ገበያ በመውሰድ ይሸጣሉ። ይህም ከባድ ሸክምን፥ ወደ ገበያ መውሰድን፥ ብሎም ቀኑን ሙሉ በፀሐይ ቁጭ ብሎ መሸጥን ያካትታል።

መ. ብዙዎቹ ባሎቻቸው በቤት አይኖሩም፤ ጊዜያቸውን ሁሉ በሥራቸው ላይ ስለሚያውሉ ወይም ከቤት ርቀው ለአገልግሎት ስለሚወጡ ወደ ቤት የሚመጡት በዕረፍት ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ልጆችን የማሠልጠንና የቤት ውስጥ ጉዳዮችን በተመለከተ አብዛኛውን ውሳኔ የማድረግ ኃላፊነት በእነርሱ ላይ ይወድቃል።

በአንዳንድ ባህል በባልና በሚስት መካከል ያለው ፍቅር አነስተኛ ነው። ሴቶች የወንዶችን ምኞት ለመጠበቅ ብቻ ይኖራሉ። ይህ ስለ እራሷ ያላትን ዋጋ ያለው ሰብዕና ይቀንሳል።

ሠ. ሴቶች በየዓመቱ ወይም በየሁለት ዓመቱ ልጅ ይወልዳሉ። ይህም ጥንካሬንና ንቃትን ከሰውነቷ እንድትቀንስ ያደርጋታል። እናም ደካማና በቀላሉ በበሽታ የምትጠቃ አካሏም እንደሚገባ የማይሠራ እንድትሆን ያደርጋታል። የሴቶች መገረዝ የደም ሥር መበጣጠስን በማምጣት በወሊድ ጊዜ ችግርን ያስከትላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካለመሆኑም በላይ፥ ለግል ንጽሕናም የማይጠቅም ነገር ነው።

ረ. ብዙ ሴቶች በጣዖት አምልኮና በአንዳንድ የጥንቆላ ሥራዎች ውስጥ ይሳተፋሉ። ይህም ለሰይጣናዊ ተጽዕኖ ያጋልጣቸዋል። ብዙ ሴቶች በስውር በሚደረግ የጣዖት አምልኮና ገንዘብን ለመሥዋዕት በማዋላቸው ይህ ወደ እስራት ውስጥ እየጠለቁ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል።

ሰ. የዓለማዊም ሆነ የመንፈሳዊ ትምህርት አለማግኘቷ ለጥቅሉ ሕይወት አነስተኛ አመለካከት ያለው አእምሮ እንዲኖራት አድርጓል።

ሸ. ብዙ ሴቶች የወል የሆነ መረዳዳት እጥረት ስለ አለባቸው ሌሎችን እንዳይረዱ እነዚያም ተመልሰው እንዳይረዷቸው ሆኗል። በአንዳንድ ባህሎች ይህ ነገር ዳብሯል። በሌሎች ደግሞ ከነጭራሹም የለም።

> 3ኛ ጥያቄ፦ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ በአንተ ኅብረተሰብ ውስጥ ላሉ ሴቶች እውነት የሆኑት ምን ያህሉ ናቸው? ልማድን መለወጥ አስቸጋሪና ከባድ ነገር ነው። ሴቶች ወደ ክርስቲያናዊ አቋም ቀስ እያሉ እንዲመጡ ምን አሳብ ማቅረብ ትችላለህ?

4. እግዚአብሔር ለሴቶች ያቀደው ደረጃ

ሀ. በፍጥረት

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ወንድ እና ሴትን በአምሳሉ ፈጠራቸው (ዘፍ. 1:27)። እግዚአብሔር ስም ያወጣላቸው ዘንድ እንስሳትንና አዕዋፋትን ወደ አዳም እንዴት እንዳመጣቸውና፥ ከእነርሱም መካከል ለአዳም የሚስማማ ረዳት ጓደኛ እንዳልተገኘ የሚናገረው ታሪክ የታወቀ ነው። ስለዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገና የጎኑን አጥንት ከእርሱ አውጥቶ ሴትን ሠራ። እግዚአብሔርም ወደ አዳም በአመጣት ጊዜ አዳም እንዲህ አለ፤ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት። ከወንድም ተገኝታለችና ሴት ትባል» (ዘፍ. 2:23)።

በዕብራውያን ቋንቋ ስንመለከት «ረዳት» የሚለው «አንድ ዓይነት፥ እንደ እርሱ ያለ» ማለት ነው። ይህም ማለት አቻ፥ ተዛማች፥ ግማሽ አካሉ ማለት

ነው። የበላይነትም ሆነ የበታችነት ስሜት በሁለቱም በኩል የለም። እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው። እናም ፍጹም የምትስማማው ናት። ማቲው ሄነሪ በሴትና በወንድ መካከል ያለውን እኩልነት በጣም ጥሩ አድርገው እንዲህ ገልጸውታል።

«ሴት ከወንድ ጎን ከወጣ አጥንት የተሠራች ናት። ከእርሱ በላይ ሆና ትገዛው ዘንድ ከራስ ቅሉ የወጣች አይደለችም። እርሱ በላይ ሆኖ እንዲረግጣትም ከእግሩ የወጣች አይደለችም። ነገር ግን ከክንዱ ሥር ሆና እንዲንከባከባት፥ ከልቡ አጠገብ ሆና እንዲወድዳት ከጎኑ ፈጠራት»።

የሚያሳዝነው ይኼና አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ሴቶች ምንም የመብት ጥያቄ ሳያቀርቡ በጭፍን እንዲታዘዙና እንዲገዙ የሚያስተምሩ ተደርገው መተርጎማቸው ነው። በአንዳንድ አገሮች ይህ ሴት ለወንድ ተገዢ ባሪያ፥ የጭቆና ሰለባ እንዲሁም የፍላጎቱ ማርኪያ እንድትሆን አድርጓል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር የፈለገው የእርሱ ጓደኛ፥ እኩያው፥ ረዳቱና አማካሪው እንድትሆን ነው።

«አንድ ሥጋ» ስለሚለው ጽንሰ አሳብም ትክክለኛ ያልሆነ መረዳት አለ። ብዙ ባሕሎች ይህንን ሲያስቡ እግዚአብሔር በሰፊው ያለውን እነርሱ ሥጋዊ በሆነው መንገድ ብቻ ያዩታል። እንደ ጓደኞዎች በአስተሳሰብ፥ በስሜት እንዲሁም በመንፈሳዊ ዓለም አንድ እንዲሆኑ ነበር የታሰበው።

በሰው ውድቀት ታሪክ ውስጥ (ዘፍ. 3) ሰይጣን ሔዋንን በተንኮሉ እንዳታለላት እናያለን። እርሷም ሙሉ በሙሉ ተታለለች። በመተላለፍም ወደቀች (1ኛ ጢ.ሞ. 2:14)። ፍሬውንም ለአዳም ሰጠችው። እርሱም በላው። ሔዋን ተታልላ ነበር፤ ነገር ግን አዳም ዓይኖቹ እያዩ ኃጢአት ሠራ። ጳውሎስ እንደሚነግረን እርሱ አልተታለለም፤ በፈቃዱ ነው የመረጠው። እርሷ የመታለል ሰለባ የሆነች ኃጢአተኛ ነች። እርሱ በፈቃዱ ነው ኃጢአት ያደረገው። ስለዚህ የእርሱ በደል ትልቅ ነው። ሮሜ 5:12 በግልጽ አብራርቶ እንደሚነግረን «በአንድ ሰው ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ ሞትም በኃጢአት» (1ኛ ቆሮ. 15:22)። ደግሞ «በአዳም ሁሉም ሞቱ»።

እግዚአብሔር ወደ ገነት በመጣ ጊዜ አዳም አለመታዘዙን በእግዚአብሔርና ሔዋን ላይ አላከከ። ሔዋን ግን በግልጽነት «እባብ እንዳሳታት» «እንደበላችም» ተናገረች (ዘፍ. 3:13)። ይህ እውነተኛ ዓረፍተ ነገር ነበር።

ለ. በአዲስ ኪዳን

> 3ኛ ጥያቄ፦ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ በተናገራቸውና ባገለገለበት ስፍራ ሁሉ እኩልነትን ለሴቶች ሲሰጥ እናያለን። ሉቃ. 8:2–3 አንብብ። የተጠቀሱትን የሴቶች ስም መዝግብ። ለእያንዳንዳቸው ኢየሱስ ያደረገላቸው ምን ነበር? ለእነርሱ ፍቅርንና አክብሮትን እንዴት ያሳይ ነበር?
>
> 4ኛ ጥያቄ፦ በአዲስ ኪዳን ብዙ ኢየሱስን የተከተሉ ሴቶች እንደነበሩ ተጠቅሷል። በሚከተሉት ምንባቦች ውስጥ የተጠቀሱትን ሰዎች ስማቸውን ጻፍ። ስለ እያንዳንዳቸውም አንድ ነገር ተናገር።

ሉቃስ 1:28፤ 35:41–45 ዮሐ. 19:25

ሉቃስ 2፡36–38 ማር. 15፡40–41
ዮሐ. 4፡1–42 ማቴ. 26፡6–13
እና ዮሐ. 12፡1–3 ዮሐ. 20፡17–18

ኢየሱስ ታላቁን ተልዕኮ በሰጠበት ጊዜ ትእዛዙን የሰሙ ወንዶችም ሴቶችም እንደነበሩ እናውቃለን። ስለሆነም የምሥራቹን ለማስፋፋት ሴቶች ተሳትፈው እንደነበር እንረዳለን። ምክንያቱም ሳውል ቤተ ክርስቲያንን ሊያሳድድ በወጣ ጊዜ ወንዶችን እና ሴቶችን ነበር ወደ እስር ቤት የጣላቸው (የሐዋ. 8፡3፤ 9፡1–2ና ደግሞ የሐዋ. 22፡4) ተመልከት።

ሐ. በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ዶርቃን (9፡36–42)፥ ልዲያ (16፡13–15)፥ ኤዎድያንና ሲንጤኪን (ፊልጵ. 4፡3)፥ የፊሊጶስ አራት ልጆች (የሐዋ. ሥራ 21፡8–9) እንመለከታለን። በሮሜ 16፡12 ጳውሎስ አሥር ሴቶችን ይጠቅሳል። ስምንቱን በስም እንደ ረዳቱ የሆኑ «በጌታ ሥራ የሚደክሙ» ብሎ ይጠራቸዋል። ከዚያም ፌቤን የምትባል በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ብሎ ጳውሎስ የሚናገርላት ነበረች (ሮሜ. 16፡1)። ይህ በግሪክ «ዲያኮኖስ» የሚለው ቃል ለጳውሎስ እና ለአጵሎስ የተሰጠው ነበረ። ሲተረጎም ዲያቆን ነው።

ደግሞም ጵርስቅላን በሮሜ 16፡3 እናያለን ጳውሎስ «በክርስቶስ ኢየሱስ የምትረዳኝ» ብሎ የሚጠራት። ሌላው ትርጉም «አብራኝ የምትሠራ» ብሎ ይጠራታል። ጵርስቅላ ከባሏ ከአቂላ ጋር ወንጌላዊ እና አስተማሪ ነበረች። ስሟ ከስድስት ጊዜ አራት ጊዜ ቀድሞ ስለ ተጻፈ ዋና ታዋቂ አስተማሪ እንደነበረች ይታመናል።

ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ነገር ግን በመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ሴቶች በጣም ንቁ ተሳትፎ ያደርጉ እንደነበረ በመግለጹ ልናጠቃልል እንችላለን። ወንጌልን በማሠራጨቱም ረገድ በሐዋርያው ጳውሎስ የተከበሩና አብረው ለመሥራት ተቀባይነት ያገኙ ሴቶች ነበሩ። ሴቶችን በአገልግሎታቸው ልንወስናቸው የተገባ አይደለም። ከወንዶች ጋር አብሮ ለመመስከርና ለማገልገል የሚያስችል ከፍተኛ ዓቅም አላቸው። ሊበረታቱና ሊማሩ ይገባቸዋል። ምግብን ከማዘጋጀት የሚበልጥ ነገር እንዳላቸው መገንዘብ አለብን። እነርሱም ደግሞ ወንጌልን በማሰራጨትና በማስተማር ውጤታማ አገልግሎት ሊኖራቸው ይችላል።

ሁለተኛ ቀን፡– ሳምንታዊ የሴቶች ስብሰባ

1. በሴቶች ስብሰባ ላይ በአገልግሎቱ ሊደረስባቸው የሚገቡ የሴቶች ፍላጎቶች

እያንዳንዳቸው ሴቶች የተለያዩ ፍላጎቶችና ችግሮች አሏቸው። አንዳንድ ሴቶች ብዙ ኅብረት ያስፈልጋቸዋል። ከሌሎች ሴቶች ተለይተው ለብቻቸው የሚኖሩ ስለሆኑ የመኅብኘት፥ የኅብረት ፍላጎታቸውን የማካፈል ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ከሌሎች ሴቶች ጋር የጸሎት ጊዜ በማድረግ ብዙ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ።

አንዳንድ ሴቶች ጊዜያቸው እጅግ የተጣበበ ነው። ከቤት ውጪ ይሠራሉ። በቤታቸው የሚንከባከቡዋቸው ልጆች አሏቸው። መበረታታትና በጸጥታ ቁጭ ብለው ስለ ጌታና ስለ ቃሉ ለማሰብ ጊዜ እንዲያገኙ ዕድሉ ያስፈልጋቸዋል። መንፈሳዊ ምግብም ይሻሉ።

አንዳንድ ሴቶች ዝምተኛና ዓይነአፋር ስለሆኑ አሳባቸውንና የሚያሳስባቸውን ነገር እንዲናገሩ ዕድል ሊሰጣቸው ያስፈልጋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በውይይት ከሌሎች ሰዎች ጋር ነፃ ሆነው አሳባቸውን መግለጥን ቀስ በቀስ ይማራሉ።

በቤታቸው ውስጥ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ያለመግባባትና ግጭት ያለባቸው ሴቶች ደግሞ አሉ። ከሌሎች ሴቶች ጋር ተገናኝተው ችግራቸውን የሚያካፍሉበትና የሚበረታቱበት ዕድል ያስፈልጋቸዋል።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ኅብረት ፍላጎታቸውን ሊያሟሉ ይችላሉ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ጊዜን ያካተተው ሳምንታዊ ስብሰባ በአፍቃሪ እኩዮቻቸው መካከል እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህም ሴቶች የወገናዊነትና የዋስትና ስሜት እንዲያገኙ ይረዳል። በሕመም ጊዜ፥ የቤተሰብ ሞት ሲያጋጥም፥ እንዲሁም በደስታና በበዓል ጊዜ በቡድን ውስጥ ካሉት ከሌሎች ሴቶች የሚያገኙት ድጋፍ አለ። አብረው ሲማሩ እርስ በርስ በመከፋፈልና በመጸለይ አንድ ላይ ይጣበቃሉ።

3. ለሴቶች ፕሮግራም መሪዎች

ከሴቶች መካከል የፕሮግራም መሪዎች በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው። የሚመረጡበት መለኪያም መንፈሳዊነታቸው፥ ብስለታቸውና ለቡድኑ አንድነትና ፍቅር የሚያስገኙ መሆናቸው መሆን አለበት። ለቡድኑ መሠረታዊ የሆኑ ሕጎችን ማስቀመጥ አለባቸው። ጥሩ ተግባቢዎች በመሆን መልካም የንግግር ልውውጥና መቀባበልን በስብሰባው ውስጥ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። መሪዎች የሴቶችን ፍላጎት በእውነት ሊያሟላና ሊደረስ የሚችል ፕሮግራም ለማዘጋጀት አብረው በመጸለይ እና በማቀድ ጊዜያቸውን ማጥፋት አለባቸው። የውጪ ተናጋሪ በጊዜው ሊጠራ ይችላል። ነገር ግን ፍላጎታቸውን በተመለከተ ቡድኑ ውስጥ የሚቀጥል ዋና የትምህርት ፕሮግራም መኖር አለበት። ይህም ልክ ከዚህ በላይ እንደተሰጠው መመሪያ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ትምህርትና የስብሰባ አመራር መሠረት መሆን አለበት።

የሴቶች የጸሎት አገልግሎት በሚገባ ሊዳብር ይገባል። አንድ ሰው፥ እንዲህ፥ አለ፡— «የጸሎት እጦረት የችግሮች ሁሉ ሥር ነው» ብሏል።

4. በሴቶች ፕሮግራም ሊሸፈኑ የሚገባቸው አካባቢዎች

ሀ. ሴቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመድረስ ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች መሸፈን አለባቸው።

1. ለግላዊ ዕድገቷ የሚያስፈልጋት ነገር ሊሰጣት ያስፈልጋል።

ፍላጎቷም መታየትና መሟላት አለበት። ማንበብና መጻፍ የማትችል ከሆነች ማንበብ ትችል ዘንድ የምትማርበት ክፍል ሊዘጋጅላት ይገባል። ይህን የመማር ዕድል ከዚህ በፊት ያላገኙትን ሴቶች አስተማሪዎቻቸው በብዙ ትዕግሥት ሊያስተምሯቸው ይገባል።

ጌታን እንደ ግል አዳኟ አድርጋ በእርግጥ አውቃለችን? ትልቁ እና የመጀመሪያው ልታውቀው የሚገባት ነገር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኟና ጌታዋ በመቀበሏ የሚገኘውን ከኃጢአትና ከፍርሃት ነፃ መውጣት ነው።

ሳምንታዊ የሴቶች ስብሰባ በመሠረታዊ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል (የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ከትንሽ ጊዜ በኋላ እናያለን)።

እግዚአብሔር የእርሱን ልጆች ጸሎት ሁልጊዜ እንደሚሰማና በጸሎት በማንኛውም ሰዓትና ቦታ ከእርሱ ጋር ልትነጋገር እንደምትችል መማር ትችላለች።

የሌሎች ሴቶችን ኅብረትና መበረታታት በሳምንታዊው ክፍለ ጊዜ ውስጥ ልታገኘው ይገባል።

2. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እና በወንጌል መልእክተኛነት ስፍራዎች ማገልገል

ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሴቶችን ፕሮግራም በመምራት፥ በእንግዳ ተቀባይነት፥ በምስክርነት፥ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት በሚያደርጉት የገንዘብና የጸሎት ድጋፍ ትልቅ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ።

3. ኅብረተሰቡን መድረስ

የወንጌልን መሠረታዊ አሳቦች የተረዱ ሴቶች ሁሉ በምስክርነታቸው፥ በደግ ሥራቸው፥ የታመሙትን በመጎብኘት፥ በቀብር ቦታ እርዳታ በማድረግ፥ በሠርግና በአንዳንድ ማኅበራዊ ሥራዎች በመሳተፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፦ በሴቶች ስብሰባ ጊዜ ሊሸፈኑ የሚገባቸውን ሦስት የአገልግሎት ገጽታዎች በዝርዝር ጻፍ። |

## ሦስተኛ ቀን፦ በቤት ውስጥ የሚስቶች ሚና

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፦ ምሳሌ 31፡10-31 አንብብ። በዚህ ስፍራ የሚናገረው ማን ነው? ይህ ምክር የተሰጠው ለማን ነው? ጥሩ ሚስቶችና እናቶች የሚሳተፉባቸውን ቢያንስ 6 ነገሮችን ዘርዝር። |

1. ልባም ሴት

በዚህ ማራኪ ምዕራፍ ውስጥ በንጉሥ ልሙኤል እናት የተቀረጸችውን ልባም ሴት ሥዕላዊ መግለጫ እናገኛለን። ለልጇ በሚያገባበት ጊዜ ምን ዓይነት ሴት መምረጥ እንዳለበት እንደምትመክረው ጥርጥር የለውም። ስለዚህም ይህ የአንዲት በሕይወት የምትኖር ሴት መግለጫ አይደለም። ነገር

ግን ልሙኤል የወደፊት ሚስቱን በሚፈልግበት ጊዜ የሚጠቀምባቸው ዓይነተኛ መመዘኛዎች ናቸው።

በዚህ መግለጫ እግዚአብሔርን ስለምታከብርና በሥራዋ ሁሉ ትጉህ ስለሆነች አንዲት ሴት ትልቅ ነገር መማር ይቻላል።

ክፍሉን በአነበብን ጊዜ እንዲህ ልንል እንችላለን። «እህ እንደዚህች ዓይነት ሴት በፍጹም ልሆን አልችልም!» ይህ እውነት ነው፤ ነገር ግን እንደ ሚስቶችና እና እንደ እናቶች የእርሷን ምሳሌ በመውሰድ ራሳችንን ማበረታታትና እንደሚገባ መሆን አለብን።

ሀ. ለባልዋ ታማኝ ደጋፊ ነበረች (ቁ. 12)። በእርሷ ትልቅ መተማመን ነበረው። «ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም።» እርሱ በአደባባዮች የተከበረ ሰው ነው ምክንያቱም በቤት ውስጥ በምትሠራው ሥራ ታታሪ ናት። ቁ. 27 «የቤትዋን ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም» ይላል።

ለ. ለቤተሰቧ የሚሞቅ ልብስን ትሠራለች (ቁ. 13፥19፥21)። በጥበብም ትገበያለች፤ ምርጥ ዕቃዎችን ታገኛለች። ትሸምናለች፤ ትሰፋማለች፤ ቀዝቃዛ ወቅት በመጣ ጊዜ ከቤተሰቧ ያልለበሰ ሰው አይገኝም።

ሐ. የምግብ አዘጋጃጀቷና አገበያየቷ በጥበብ ነው (ቁ. 14፥15)። በወቅቱ በቁጠባ ለመግዛት ዋጋን ሁሉ ታውቃለች። ቤተሰቦቿ በጥሩ ሁኔታ ይመገባሉ። ጥሩ ጤንነትም አላቸው።

መ. ጥሩ የንግድ አስተሳሰብ አላት (ቁ. 16፥ 17፥ 18፥ 24)። በዋጋ ክርክርና መዋዕለ ንዋይ አወጣጥዋ ላይ ጥበበኛ ናት። በጥንቃቄ ትገዛለች፤ ትሸጣለች። ገበያውንና የጊዜውን አስፈላጊ ነገር ታውቃለች። የሐር ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፤ ለነጋዴም ድግ ታቀርባለች።

ሠ. ቤቷን በማስጌጥና በማስተካከል ታስውበዋለች፤ ጥሩ ልብስም ትለብሳለች (ቁ. 22)።

ረ. አካላዊና፥ ስሜታዊ ገጽታዋ ደግሞ የተስተካከለ ነው (ቁ. 17-25)።

ሰ. እጅዋን ወደ ድሃ ትዘረጋለች (ቁ. 20)።

ሸ. አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፤ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ (ቁ. 26)።

ጥረቷ ሁሉ ቤቷና ቤተሰቦቿን ዋስትና ባለው መንገድ በደኅንነት ተጠብቀው እንዲኖሩ በማድረጉ ላይ ያተኮረ ነው። የኑሮዋ ምሥጢር የሚያርፈው ጌታን በመፍራቷና በምታደርገው ነገር ሁሉ እርሱን ለማስደሰት በመፈለግዋ ጭብጥ ላይ ነው። ይህም ደግሞ የጥበበኛነቷ መሠረት ነው።

«እማማ፥ የተባረክሽ ነሽ» የሚለው የልጆቿ ሙገሳ ሽልማቷ ነው። ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል፤ «መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፤ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ» (ቁ. 28 ና 29)። ይህች ሴት ትክክለኛ እርካታንና መሙላትን ታውቃለች፤ ምክንያቱም በሕይወት ያላትን በታዋን በደስታ ተቀብላዋለችና፤ በተቻላት መጠን ሚስትና እናት ለመሆን ተግታ

ሠርታለችና። ኃላፊነት የሚሰማት፥ ችሎታ ያላት፥ ጠንካራ ሠራተኛና ፍጹም ታማኝ ናት።

2. የሴቶች ደካማ ጎኖች

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ በሴቶች ላይ የሚገኙትን ጥቂት ደካማ ጎኖች ሳይናገር አላለፈም። መጽሐፈ ምሳሌ የሚናገረው ስለ ልባም ሴት ብቻ ሳይሆን ልባም ስላልሆኑት ሴቶችም ጭምር ነው። ከጠባዮቻቸው ጥቂቶቹም፦

ሀ. በቤተሰቡ ላይ ኃፍረትን ያመጣሉ (12:4)

ለ. ጠብን ይፈጥራሉ (19:13፥ 21:9፡19፤ 25:24)። ማንም ወንድ ከራሱ፥ ከልጆቹ ወይም ከጎረቤት ጋር ከምትጨቃጨቅና ከምትናቆር ሴት ጋር መኖር አይፈልግም።

7ኛ ጥያቄ፦ እንደነዚህ ዓይነት ደካማ ጎኖች በሴቶች ዘንድ እንዳሉ ብታውቅ ሴቶችን በስብሰባቸው ላይ እንዴት ታስተምራቸዋለህ? የትኞቹን ክፍሎች ትጠቀማለህ?

8ኛ ጥያቄ፦ በባሕልህ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዴት ነው የሚያስተናግዱት? እንደ እኩያቸው ነው ወይስ እንደ የበታቻቸው ነው የሚያዩአቸው? (ኤፌ. 5:21-33 አንብብ።) ከዚህ ምንባብ እንደምትረዳው ባሎች ለሚስቶቻቸው ሊኖራቸው የሚገባ አስተያየት ምን መሆን አለበት? ሴቶችስ ለባሎቻቸው ምን አስተያየት ሊኖራቸው ይገባል?

3. ሚስት ከባልዋ ጋር ያላት ግንኙነት

አንድ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር በእግዚአብሔር ፊት ባሎችና ሚስቶች፥ ወንዶችና ሴቶች ሁሉም እኩል ናቸው። ይህም በገላትያ 3:28 ተገልጾአል፤ «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ»። የደኅንነት መንገድና ለክርስቲያናዊ አኗኗር ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበልናቸው ነገሮች ለሴትም ሆነ ለወንድ አንድ ዓይነት ናቸው።

ወደ ኤፌሶን 5:21-33 በምንሄድበት ጊዜ ከሁሉም በፊት ሁላችንም «በክርስቶስ ፍርሃት መገዛት» እንዳለብን እንረዳለን። ክርስቶስን አብረን ስንከተለው ሳለ አንዳችን ለሌላችን ልንገዛ ይገባል። ሚስቶች ለጌታ እንደሚገዙ ሁሉ እንዲሁ ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው። ልክ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን፥ የአካሉ ራስ እንደሆነ ባልም የሚስቱ ራስ እንዲሆን እግዚአብሔር ሾሞታል። ሚስት በማንኛውም ነገር ለባሏ መገዛት አለባት። ይህም ቤቱን በጥሩ ሁኔታ ለማስተዳደር የተሰጠ ነው። በቤት ውስጥ ሁለት ራሶች ካሉ ሁልጊዜ ጥልና አለመግባባት ይኖራል። ባልና ሚስት ችግሮቻቸውን በአንድ ላይ ተወያይተው ወደ አንድ ውሳኔ አብረው መድረስ አለባቸው። ሚስት የመጨረሻው ውሳኔ የባል እንደሆነ ማስታወስ አለባት። እናም አንድ ጊዜ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ ሁለቱም በዚህ አሳብ የመኖር ግዴታ አለባቸው።

እንደ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፥ አፍቃሪ ራስ ለሆነና እኛም አካል ለሆንንለት ለክርስቶስ እንገዛለን። መገዛታችን የፍርሃት ሳይሆን የማፍቀርና የአክብሮት ነው። እንዲሁ ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው።

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደና ራሱንም ለእርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፥ ባልም ሚስቱን እንዲሁ መውደድ አለበት። የእርሱ ፍላጎት ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገ የሚያስፈልጋትን መስጠት እና ማስተማር፥ በእግዚአብሔር ቃል ማበረታታትና ማጠንከር፥ በክርስትና ሕይወትም ያደገችና ቅድስት ንጽሕት እንድትሆን መደገፍ ሊሆን ያሻል። ብዙ ጊዜ ባል ሚስቱን እንዲወድድ ምክር ተሰጥቶታል።

ሚስትም በተራዋ ለባልዋ ልትገዛና ልታከብረው ይገባል። ይህንን እርሱ የባልነት ድርሻውን ሲያደርግ በፈቃዷ ታደርገዋለች።

የባልና የሚስት አንድነት በዓለም ላይ ካሉት አስደሳች ግንኙነቶች አንዱ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ትዳር ለሁለቱም ተጋቢዎች ሙሉ እርካታንና ደስታን እንዲሰጥ ዐቅዷል። አንድ ላይ ሙሉ፥ አንድ ሥጋ ይሆናሉ። እስቲ ልባችንንና ሕይወታችንን እንመርምር። እናም በዚህ ነገር የእግዚአብሔርን መመዘኛዎች በሙሉ አሟልተን እንደሆነ እንመልከት። ሚስቶች ባሪያዎች አይደሉም። ነገር ግን እናከብራቸው ዘንድ እኩል ናቸው፤ ሊሆኑ የሚችሉትን እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸው ሊሰጣቸውና ሊበረታቱ ይገባል። ባሎች የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በመውሰድ ለሚስቶቻችሁ የሚገባትን አክብሮት እና ፍቅርን በመስጠት ቤታችሁን የደስታ እና የእኩልነት ቤት አድርጉት። መሆን የሚገባትን የእግዚአብሔር ሴት ሆና ማደግ እንድትችል እርሷን መንከባከብና መጠበቅ የእናንተ ኃላፊነት ነው።

9ኛ ጥያቄ፡— ያገባህ ከሆንህ ከሕይወት ጓደኛህ ጋር ባለህ ግንኙነት ማስተካከል እንዳለብህ ያወቅኸው ነገር ምን አለ? በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል እየተከተልህ ነውን? የኑሮ ጓደኛህን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የምትመግበት ብትሆን በኅብረተሰቡ ዘንድ ነቀፋና ትችት ይደርስብህ ይሆንን? ከሆነ ለምን? ለነቀፋዎቹ እንዴት ነው የምትመልሰው?

10ኛ ጥያቄ፡— ካላገባህ ይህንን ምዕራፍ እንዳጠናኸው የሕይወት ተካፋይህን በተመለከተ ምን ዓይነት አሳብ አገኘህ? በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሙሉ ለሙሉ የተመሠረተን የጋብቻ ግንኙነት ለመመሥረት ልትደፍር ትችላለህን? የእርሱን ቃል ሙሉ ለሙሉ ከተከተልህ እግዚአብሔር እንደሚያከብርህና ጥሩ ጋብቻ እንደሚሰጥህ ታስባለህን? መልስህ አዎን ከሆነ፥ ይህ በምን ዓይነት መንገድ የሚከናወን ይመስልሃል?

## አራተኛ ቀን፡— ቤተ ክርስቲያን ለቤተሰብ የምትሰጠው አገልግሎት

11ኛ ጥያቄ፡— ልጆቻቸውን በማሠልጠን ረገድ የእናትና የአባት ድርሻ ምንድን ነው? ልጆቻቸውን በሚገባ ስለማሳደግ ወላጆችን ለማሠልጠን ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት መውሰድ አለባትን? እንዴት ይህን ልታደርግ ትችላለች?

እግዚአብሔር ስለ ቤተሰብ ያለው አሳብ ግልጽ በሆነ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀምጧል። ሔዋን የአዳም የሕይወት ተካፋዩ ነበረች። የቤተሰብ መፈጠር ምዕራፍ ለፍጥረት ሁሉ ቁንጮ ነበር። አዳም እና ሔዋን

በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ የሚገዙ ነበሩ፥ እናም ፍጥረትም በእነርሱ ጥበቃና እንክብካቤ ሥር ነበር። ደግሞም እንዲበዙና ምድርንም እንዲሞሏት ታዘው ነበር።

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ለቤተሰብ እና ለቤተሰብ ሕይወት መመሪያ የሚሰጡ ብዙ ምንባቦች አሉ። በአዲስ ኪዳን አካባቢ ግን ለቤተሰብ የሚሆን በጣም ብዙ ትእዛዛትን አናገኝም፤ ምክንያቱም ቤት የቤተ ክርስቲያን ትንሽ ምሳሌ እንድትሆን የእግዚአብሔር አሳብ ስለነበር፥ ማናቸውም ለቤተ ክርስቲያን በአዲስ ኪዳን የተሰጡ ትእዛዛት ሁሉ ለቤተሰብ ኑሮ የሚሠሩ ናቸው። እውነተኛ የክርስቲያን ቤተሰብ የበሰለችን የቤተ ክርስቲያን አሠራር ያሳያል።

ቤተሰቦች እንዴት በአንድ ላይ መኖር እንደሚችሉ፥ ወላጆች እንዴት ልጆቻቸውን እንደሚያሠለጥኑና ቤተሰባቸውን በሚያሳድጉበት ጊዜ የባልና የሚስት ድርሻ ምን እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን የማስተማር ኃላፊነት አለባት። ቤተ ክርስቲያን ልታስተምራቸው የምትችላቸው አንዳንድ ነገሮች በዚህ ትምህርት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. ቤተሰቦች በቃል ንግግር መማር አለባቸው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡- መዝ. (78)፡1-8 አንብብ። አባቶች ያስተማሩት ማንን ነበር? ያስተማሯቸው ለምን ነበር? ዘዳ. 6፡4-9 ደግሞ አንብብ። ይህ ትምህርት ምን ያህል ትውልድ ነው የሚነካው? |

አባቶች በቤት ውስጥ ልጆቻቸውን የማስተማር ኃላፊነት እንዳለባቸው በግልጽ ተቀምጦአል። ኤፌሶን 6፡4 «እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጡአቸው» ይላል።

2. ቤተሰብ በሕይወት ምሳሌ መማር አለበት።

ልጆች ወላጆቻቸውን ያያሉ። ወላጆቻቸውንም ይኮርጃሉ። ወላጆቻቸው የሚያስተምሯቸውና የሚያደርጓቸው ነገሮች መስማማታቸውን ለማረጋገጥ ባለማቋረጥ ይከታተላሉ። ለደስታ፥ ለኃዘን፥ ለአደጋ፥ ለግጭት ወላጆቻቸው የሚሰጡዋቸውን ምላሾች ይመለከታሉ። ከዚያም ብዙውን ጊዜ እነርሱም በዚያው መንገድ ምላሽን ይሰጣሉ።

እንደ ወላጆች ራሳችንን በልጆቻችን ውስጥ ያየነው ስንት ጊዜ ነው? በጨዋታቸው፥ በአነጋገራቸው፥ እርስ በርሳቸው በሚለዋወጡአቸው ቃላት፥ በአገላለጻቸው ሁሉ የሚታይባቸው ነገር በቤት አካባቢ የሚሰሙት ነው። ልጆቻችንን በምንመራበት ጊዜ መጠንቀቅ ያለብን ምን ያህል ነው።

3. ቤተሰብ ሥነ ሥርዓትን መማር አለበት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ልጆች የተሰጠው ቀጥተኛ መመሪያ መታዘዝን የሚመለከት ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን በሥርዓት እንዲይዙና እንዲታዘዙ እንዲያስተምሩአቸው ታዞዋል። ኤፌሶን 6፡1-3፥ ልጆች በጌታ ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ የተገባ እንደሆነ ያስረዳል።

13ኛ ጥያቄ፡- ምሳ. 29፡15፤ 13፡24፤ 29፡ 17፤ 22፡6 አንብብ። የሥነ ሥርዓት ጉድለት አንዳንድ አሉታዊ ውጤቶች ምንድን ናቸው? ተገቢ የሆነ ሥርዓት አዎንታዊ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ሥነ ሥርዓት ከእርማት የሚበልጥ ነው። ልጁ ጤናማ የሆነ ግላዊ ሥነ ሥርዓት ይኖረው ዘንድ ወላጆች የልጁን ባሕርይ ወደ ተገቢው መንገድ መምራት ይኖርባቸዋል። ኤፌሶን 6፡4 እንደገና ተመልከት። ሥርዓት ማስያዝ በቀጥታ፥ በቀናና በፍቅር መንፈስ ሁል ጊዜም ለልጁ በጎ የሆነውን ነገር በማሰብ መደረግ አለበት። ወላጆች ሥነ ሥርዓት በሚያስይዙበት ጊዜ የልጁን የዕድሜ ደረጃ፥ ችሎታ፥ እንዲሁም ስሜታዊ ምላሹን ማሰብ አለባቸው። መንፈሱን ማሳዘን የለባቸውም። ነገር ግን ከሚጎዳ ጠባይና አመለካከት ወደ ጤናማ ምላሽ መምራት አለባቸው።

ለልጆች ሥነ ሥርዓት ዘላቂ የሆነ የታማኝነት እንክብካቤ በሚሰጥበት ቤት ውስጥ ደስታ ይኖራል፤ እንዲሁም ልጆች ስለ ራሳቸው ጤናማ የሆነ አስተሳሰብና ሌሎችን የመውደድና ለሌሎች የመጠንቀቅ ችሎታ ኖሮአቸው ያድጋሉ።

አባቶች ልጆቻቸውን ማስተማርና መምራት አለባቸው። እናቶችም ልጆችን በማሳደግ ላይ በጣም አስፈላጊ ድርሻ አላቸው። በአባቶች ለሚሰጠው ትምህርት ደጋፊና አስፈጻሚ ናቸው። እናቶች ቀኑን ሙሉ ከልጆቻቸው ጋር ይውላሉ። ስለዚህም የተሰጠውን ትምህርት መደገፍ አለባቸው። ልጆቹ በአባቶቻቸው የተሰጠውን ትእዛዝ እንዲያደርጉ ይቆጣጠራሉ። አባቶች ይህንን ኃላፊነት ባልወሰዱበት ሁኔታ ብዙ እናቶች ልጆቻቸውን ለእግዚአብሔር ክብር በማሳደግ ጥሩ ሥራ ሠርተዋል። ነገር ግን ቀላል አይደለም። እንዲሁም ትክክለኛው መንገድ አይደለም።

ይህም በጣም አስፈላጊ ወደሆነ ርእስ ያመጣናል። ባልና ሚስት በቤተሰቦቻቸው ውስጥ ስለሚጠቀሙት የሥነ ሥርዓት ዘዴ መስማማት አለባቸው። ከተስማሙ በኋላ እርስ በርስ ሊረዳዱ ይገባል። አባትየው ለልጆች ትእዛዝ ከሰጠ እርሱ በሌለበት ጊዜ ሚስቶች ልጆቹ ትእዛዙን ፈጽመው እንደሆነ መከታተልና ማየት አለባቸው። በዚህ ዓይነት እናትየው ልጆችዋ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዘች አባትየው ሊደግፋትና ልጆቹ እንዲታዘዙ ሊከታተል ይገባል። ይህ ካልሆነ አለመታዘዝን እያስተማሩ ነው። ልጆች በወላጆቻቸው መካከል አንድነት እንደሌለ ከተመለከቱ አንዱን ከአንዱ ጋር ለማጣላት ጥሩ ዕድል ያገኛሉ። ወላጆች አንድ አሳብ ሊኖራቸው ያሻል። በአንዳንድ ምክንያት አንደኛው ወገን በአንዱ ቅጣት ያልተስማማ እንደሆነ ልጆቹ በማይሰሙበት መንገድ ሊወያዩበት እና ወደ መስማማት ሊደርሱ ይገባል። በፍጹም በልጆች ፊት መወያየት አይገባም። ለልጆቻቸው የአንድነት ግንባር ማሳየት አለባቸው።

4. ልጆችን በማሠልጠን የምንፈልጋቸው ግቦች

14ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 6፡1-3 እና ቆላ. 3፡20 አንብብ። ለልጆች የተሰጠ አንድ አስፈላጊ ትእዛዝ ምንድን ነው? ልጆች መጽሐፍ ቅዱስን አንብበው ወዲያውኑ ይህንን ትምህርት ይማራሉን? ማስተማር ያለበት ማን ነው?

ሀ. መታዘዝ፦ እንደተጠቀሰው ልጆች መታዘዝን መማር እንዳለባቸው በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ተጽፎአል። መታዘዝን ማስተማር ያለባቸው ወላጆቻቸው ናቸው። መታዘዝ ከቤት ውስጥ መጀመር አለበት። አንድ የትልቅ ቤተሰብ እናት ሲናገሩ፥ «አንድ ሕፃን የሁለት ዓመት ዕድሜ እስኪሆነው ድረስ መታዘዝን ካልተማረ እርሱን የማሠልጠኑ ጉዳይ እጅግ ከባድ ይሆናል» ብለዋል። ብዙ ጊዜ ወላጆች ትናንሽ ልጆቻቸው ምንም የማያውቁ እንደሆኑ ያስባሉ፤ ስለዚህም ካላደጉ በስተቀር መታዘዝን ሊማሩ እንደማይችሉ ያስባሉ። ሆኖም ወደ ሁለት ዓመት አካባቢ የሞላውን ልጅ ስታነጋግሩት «አይሆንም» ሊል ይችላል። ያን ጊዜ በዝግታ ነገር ግን በጽናት መታዘዝ እንዳለበት ማሳየት አለብን። ከተቃወመ ወደ መቀመጫው ላይ በመምታት ወይም መታዘዝ እንዳለበት እስኪገባው ድረስ የሚፈልገውን ደስታ በመከልከል ማስተማር ያስፈልጋል። ልጆቻችሁ እንዲታዘዙአችሁ በሚገባና በጽናት ካስተማራችኋቸውና ከተከታተላችኋቸው እናንተንና ቤተሰባችሁን ይባርካሉ። ቤትም ከጠብ፥ ከክርክርና ከጭቅጭቅ ነፃ ይሆናል። ይህም ማለት ደስተኛ ቤት ነው ማለት ነው።

እግዚአብሔር ለሳሙኤል በሌሊት በተናገረው ጊዜ የተፈጸመውን ድንቅ ታሪክ ልንረሳ አንችልም (1ኛ ሳሙ. 3፡3–14 አንብብ)። ሦስት ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማቱ፥ ዔሊ የጠራው እየመሰለው ከሞቀ አልጋው ተነሥቶ ጥሪውን ለመታዘዝ ሄዷል። በእያንዳንዱ ጊዜ ዔሊ እንዳልጠራው ሲነግረው ሳሙኤል ወደ መኝታው እየሄደ ይተኛ ነበር። በመጨረሻም ዔሊ ሳሙኤልን እግዚአብሔር እንዲጠራው አስተውሎ እንዲህ ብሎ እንዲመልስ መከረው፤ «ጌታ ሆይ፥ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር»። ከዚያም እግዚአብሔር ለሳሙኤል በዔሊ ቤት ላይ በልጆቹ ኃጢአት ምክንያት እንደሚፈርድበት ተናገረው።

በዚህ ታሪክ የምንመለከተው ገና ከወላጆቹ ጋር ሳለ መታዘዝን ስለተማረ ልጅ ነው። አሁን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሲያገለግል በዚያው ዓይነት መታዘዝን ቀጠለ።

ለ. ሰውንና እግዚአብሔርን ማክበር

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፦ 2ኛ ነገ. 2፡23–25 አንብብ። በዚህ ታሪክ ወጣቶቹ ያደረጉት ምንድን ነበር? ምን አደጋ ደረሰባቸው? ዘጸ. 19፡3 እና ዘጸ. 20፡12 ደግሞ አንብብ። ደግሞም ኤፌ. 6፡2–3። በእነዚህ ቁጥሮች መሠረት ልጆች ማክበርና መፍራት የሚገባቸው ማንን ነው? አሁን ደግሞ ዘሌ. 19፡32 እና የሐዋ. 23፡5 አንብብ። በእነዚህ ክፍሎች መሠረት ልጆች ማክበር ያለባቸው እነማንን ነው? |

በእነዚህ ቁጥሮች ልጆች እግዚአብሔርን ማክበርና መፍራትን መማር ቤቱንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማክበር እንዲሁም ወላጆቻቸውንም መታዘዝና ማክበር እንዳለባቸው እናያለን። ደግሞም ሽማግሌዎችንና የመንግሥት ባለሥልጣናትን ማክበር አለባቸው። እነዚህን ነገሮች በቤት ውስጥ ሳሉ መማር አለባቸው። ይህንን ሁሉ በንግግር፥ በትምህርትና በቤተሰቦቻቸው ምሳሌነት ሊማሩት ይገባል።

ሐ. እውነተኝነትና ታማኝነት

ልጆች እውነትን እንዲናገሩ መማር አለባቸው። ልጆች በተለይ ስሕተት ሠርተው ስሕተታቸውን ለመሸፈን በሚጥሩበት ጊዜ መዋሸት ትልቅ ፈተናቸው ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በመዝሙር (119):104 ና 108 እንደተገለጠው የዋሾችን መንገድ ይጠላል። ቆላስይስ 3:9 «እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ» ይላል። ምሳሌ 12:22 የሚዋሽን ከንፈር እግዚአብሔር እንደሚጠላ ያስታውሰናል። ልጆቻችን እውነትን እንዲናገሩ ልንገፋፋቸው ይገባል። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ መዋሸትን እንዲፈሩ መቀጣት አለባቸው።

ታማኝነትን ደግሞ መማር አለባቸው። ዘጸአት 20:15 «አትስረቅ» ይላል። ልጆች አንድ ነገር ባዩ ጊዜ ያ ነገር እንዲኖራቸው ስለሚፈልጉ ለራሳቸው ወስደው በመደበቅ ለማስቀረት ይፈተናሉ። ይህ ነገር እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን ሊማሩ ይገባል። የሌሎችን ሰዎች ንብረት ማክበር መማር አለባቸው።

መ. ኃላፊነትን ለመቀበል

ልጆች ገና ለጋ እያሉ መሥራትን ሊማሩና ኃላፊነት መቀበልን ሊለማመዱ ይገባል። ይህንን በትናንሽ ነገሮች መጀመር ይቻላል። ነገር ግን ለወደፊት ጥሩ ልምድ ነው። ሰቆቃወ ኤር. 3:27 «ሰው በታናሽነቱ ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው» ይላል። በቤት ውስጥ ትናንሽ ሥራ ከተሰጣቸውና ያንን በታማኝነትም እንዲሠሩ ከተተወላቸው ባደጉ ጊዜ ትልቅና ጠቃሚ ነገር ይማራሉ።

በእነዚህ ሁሉ አካባቢዎች ይህንን እንደ ዓላማ አድርገው በመውሰድ በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ ማስለመድ የሚችሉት ወላጆች ናቸው። እናት ከልጆቿ ጋር ብዙውን ጊዜ በቤት ውስጥ ስለምታሳልፍ፥ ለልጆቻቸው ያላቸውን ዓላማ ልጆች ማድረጋቸውን የምትከታተል እርሷ ናት። እናቶች ልጆቻቸውን ለማሠልጠን በሚፈጽሙት ተግባር እግዚአብሔር ይባርካቸው፤ ጥበብንና ጥንካሬን ይስጣቸው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፦ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ባሉ ፕሮግራሞች ውስጥ የወላጆችን የማስተማር ጊዜ እንዴት ለማካተት ትችላላችሁ? ለዚህ ትምህርት ልዩ ክፍሎች እንዲኖሩ ታደርጋለህን? ቤተሰብን በተመለከተ ተከታታይ የስብከት ጊዜ ማዘጋጀት ጥቅሙ ምንድን ነው? ወላጆችን ብቻ ከመጥቀም የላቀ ተግባር ሊፈጽም ይችላልን? |

አምስተኛ ቀን፦ ይህን ትምህርት ከልስ። የመወያያ ርእሶች ስታዘጋጅ ስለ ሚስትህ፥ ስለ እናትህ፥ ስለ ጎረቤትህ ሴቶች አስብ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

በሴቶች ስብሰባ ላይ ሊጠቀሙት የሚችሉትን አጭር ትምህርት አንድ ተማሪ እንዲያዘጋጅ አድርግ። ትምህርቱ ለሴቶች ስብሰባ ተስማሚ እንደሆነና እንዳልሆነ እንዲወያዩበት አድርግ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የሴቶችን ኅብረት ፕሮግራም ወይም የሴቶችን ሳምንታዊ ስብሰባ ተወያዩበት። ጥልቀት ያለው ትምህርት እየተሰጣቸው ነውን? የመመስከር ችሎታቸውን፥ የግል ጥሞናቸውን፥ የማንበብ ችሎታቸውን፥ የቤት ሥራቸውን፥ ልጆችን የማሠልጠን ችሎታቸውን ለማሳደግ ሥልጠና አግኝተዋልን?

2. በቤተሰብ ርእስ – ጉዳዮች ላይ ቢሰበክ ቤተሰቦችን ይረዳ ይሆን?

3. በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያሉትን የክርስቲያን ልጆችን ባሕርይ አስመልክታችሁ ተወያዩ! እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት የወላጆችን ኃላፊነት በመወጣት ረገድ ድክመቶችን ያየኸው የት ላይ ነው? ስለዚህ ነገር ምን ሊደረግ ይችላል?

# ትምህርት አሥራ አንድ

## መምህሩ እና ትምህርቱ

### አንደኛ ቀን፡– ትምህርቱን ማዘጋጀት

1. የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ

ተማሪዎችን በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በጌታ መንገድ ለመምራት በመምህሩ ላይ የተጣለው ኃላፊነት ትልቅ ነው። ጠንከር ባለ አባባል ለመግለጽ ቃላት ቢያጥርም ቤተ ክርስቲያን፥ መጋቢዋ፥ ሽማግሌዎች እና ማኅበረ ምእመኑ በግብረገባዊ ድጋፍና በጸሎታቸው ከመምህሩ ጎን መቆም አለባቸው። ለማንኛውም አገልግሎት ጸሎት ብቸኛው መሠረት ነው። የሰንበት ትምህርት ቤትም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም።

መምህሩ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የሚያውቅ መሆን አለበት፥ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ የሚከተል፥ የነቃ የጸሎት ሕይወት ያለው እና ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ሰው መሆን አለበት።

እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል የሚወድና ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጥናት በቂ ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ከቃሉ የተማረውን ለመታዘዝ ያለማቋረጥ የሚፈልግ መሆን አለበት።

ልጆችን የሚወድድና አሳባቸውን የሚረዳ ሰው ሊሆን ይገባል። ሊጸልይላቸው ይገባል፥ ከእነርሱ ጋር ጊዜ ሊወስድና አሳባቸው ምን እንደሆን ለመረዳት የሚሉትን ሊሰማ ይገባዋል። የሚኖሩበትን ቤት ለመጎብኘትና ቤተሰቦቻቸውን፥ በዚያውም የአኗኗር ሁኔታቸውን ለማወቅ ፈቃደኛ መሆን አለበት።

በመጨረሻም በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስተማር መምህሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ያለው መሆኑ አስፈላጊ ነው። ወደዚያ ውስጥ በግድ እንዲገባ ከተደረገ ወይም ማስተማር ካልፈለገ ጥሩ አስተማሪ አይሆንም።

2. የመምህሩ መሣሪያዎች

አናጢ ሥራውን ለመሥራት መሣሪያዎች ያስፈልጉታል። እነዚያ መሣሪያዎች ምንድን ናቸው? አዎን፥ እንጨት፥ መጋዝ፥ መዶሻ፥ ምስማር፥ ውኃ ልክ እና እስኪድራ ናቸው። ጠቃሚ ነገር ለመሥራት፥ በትንሹ የሚያስፈልጉት ነገሮች እነዚህ ናቸው።

ልብስ ሰፊም እንደዚሁ መሣሪያዎች ያስፈልጉታል። እነዚያ ምን ምን ናቸው? ልብስ፥ መርፌ፥ የወረቀት መርፌ፥ መቀስ፥ የስፌት መኪና እና የሚቀመጥበት ወንበር ያስፈልገዋል። ያለ እነዚህ መሣሪያዎች በሚገባ መስፋት አይችልም።

እንደዚሁም የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ መሣሪያዎች ያስፈልጉታል። በትንሹ የሚያስፈልጉት ነገሮች የራሱ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ማስታወሻ ደብተርና ብዕር፥ የስም መጥሪያ ደብተር፥ ለጥናት የሚሆን ጠረጴዛና ወንበር ናቸው። የጥቅስ ማውጫ መጽሐፍ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እና አትላስ ካርታ ያለው ከሆነ ለማጣቀሻነት ሊጠቀምባቸው ይችላል። ለሚያስተምረው ትምህርት የመምህሩ መምሪያ ቢኖረው በጣም ይረዳዋል።

3. የትምህርት ዕቅዱ አስተዋጽኦ

በመጀመሪያ ትምህርት ለማዘጋጀት በዕቅድ ውስጥ መካተት ያለበት ነገር ምንድን ነው?

ሀ) የምናስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ መመረጥ አለበት።

ለ) የትምህርቱ ዓላማ በጥንቃቄ ሊታሰብበትና በጽሑፍ ሊሰፍር ይገባል።

ሐ) ዓላማውን የሚደግፍና ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡ ጋር የሚስማማ በቃል የሚጠና ጥቅስ መፈለግ አለበት።

መ) ጥሩ የሆነ መግቢያ መታቀድ አለበት።

ሠ) የትምህርቱ ዋና ክፍል ማለትም አንተ የምታስተምረውና ልጆችን የምታሳትፍበት መዘርዘር አለበት።

ረ) «ክፍተትን መሙላት» ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ለዛሬው ዓለም እንዲሆን ማድረግ ነው። ልጆቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለዛሬ ሊሆን እንደሚችል እንዲያዩ ይኸኛው ክፍል በሚገባ ሊታሰብበትና ሊብራራ ይገባል።

ሰ) ከሕይወት ጋር ማዛመድ ትምህርቱ ለሕይወታችን ምን መልእክት እንዳለውና በዚህ ሳምንት ከሕይወታችን ጋር እንዴት እንደምናዛምደው መታቀድ አለበት።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ሰባት የትምህርት ዕቅድ ነጥቦችን ጻፍ። በቃልህ አጥናቸው። |

አሁን በዚህና በሚቀጥለው ትምህርት እነዚህን ነጥቦች ደረጃ በደረጃ እንመለከታቸዋለን።

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡን መምረጥ

የሰንበት ትምህርት ቤት መመሪያ መጽሐፍ የምትከተል ከሆነ ምንባቡ ተመርጦ ተዘጋጅቷል። ሆኖም መመሪያውን የማትጠቀም ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን እንደ ቅደም ተከተላቸው በመጠቀም የተለያዩ እውነቶችን ማስተማሩ መልካም ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በርእሰ-ጉዳዮች ላይ ያተኮረ አሰባበክ አመዝኖ ይታያል፤ ይህም ሰዎች ጥሩና አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እንዲጎድላቸው አድርጓል። ይህ ማለት በእግዚአብሔር ቃል በተገቢው ሁኔታ መሠረት የያዙ ሰዎች በብዛት የሉም ማለት ነው። ይህ አሳሳቢ ሁኔታ ነው። የእግዚአብሔር ቃል መሠረታችንና የወደፊት ተስፋችን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በጠቅላላ አሳቡ ማወቅ ያስፈልገናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደተጻፉ ካለማስተማር የተነሣ ብዙ ጉዳት ደርሷል።

ከመልካም ጓደኛህ ደብዳቤ ቢደርስህ አያንዳንዱን ቃል እስከትጨርስ ድረስ ታነባለህ እንጂ እንዲሁ አታስቀምጠውም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተላከልንን ደብዳቤ እዚያና እዚህ እናነባለን። ጥቂት የምንወዳቸውን ጥቅሶች ብቻ በማንበብ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ራሱን እንደገለጠልንና ለእኛም የሰጠው እርሱን እንድናውቀው መሆኑን እንረሳለን። ከአሪት ዘፍጥረት ጀምረህ መጽሐፍ ቅዱስህን በሙሉ እንድታነበውና እግዚአብሔር አንተ ስለ እርሱ እንድታውቅ የሚፈልገውን እንድትረዳ አጥብቄ እጠይቅሃለሁ። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ያስቀመጠውን ታላቅ ዕቅድ አንድ ጊዜ ማየት ከጀመርን በጣም ስለሚመስጠን መጽሐፉን ማስቀመጥ አንፈልግም። አሁኑኑ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ለራስህ ለማንበብ ጀምር።

በዚህም ምክንያት አንድ መጽሐፍ መርጠህ ሙሉ በሙሉ እንድታስተምር አሳስብሃለሁ። እርግጥ ነው ለተለያዩ የዕድሜ ክልሎች የትኞቹን ክፍሎች ተማሪዎችህ ሊረዱ እንደሚችሉ መምረጥ ይኖርብሃል። ከባድ አስተምህሮ ያለባቸውን እንደ ሮሜ መልእክት ወይም ሌሎች መልእክቶችን ጀማሪዎችን ለማስተማር አትመርጥም።

ትናንሽ ልጆች ታሪኮችን ስለሚወዱ ለመስማት ፍላጎት አላቸው። እነርሱ እንዲያስታውሱት ብትደጋግመው እንኳን አይሰለቹም። የብሉይ ኪዳን የእምነት ጀግኖችን ወይም የክርስቶስን ሕይወት ታሪኮች ምረጥ። ለመስማት ፍላጎት እንዲኖራቸው ታሪኮችን ሕያው አድርገህ ተርክ።

ሀ) ስለዚህ መጀመሪያ ማድረግ ያለብህ የምታስተምረውን ምንባብ መምረጥ ነው። የታሪኩ ቅደም ተከተል በአእምሮህ ግልጽ እስኪሆን ብዙ ጊዜ ደጋግመህ አንብበው። የንባቡን ዐውድ ለማግኘት ከምንባቡ ፊትና ኋላ ምን እንደሚመጣ አንብብ።

ለ) ጸልይ። እግዚአብሔር በመንፈሱ እውነቱን እንዲገልጥልህ ጠይቀው።

ሐ) እንደተረዳኸው እርግጠኛ ስትሆን ለምንባቡ ተጨማሪ መረጃና እውነታዎችን እንድታገኝ ሌሎች ዋቢ መጻሕፍትን ተመልከት።

መ) መመሪያ ያለህ ከሆነ መመሪያው ምን እንደሚል ለማየት ጊዜው አሁን ነው። የራስህን ንባብና ምርምር በመጀመሪያ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በመመሪያው ላይ ያለውን ብቻ እየገለበጥህ የምታስተምር ከሆነ ጥሩ አስተማሪ አይደለህም።

ሠ) በመጨረሻም ተማሪዎችህ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ማሰብህ አስፈላጊ ነው። ይህ ምንባብ ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አሰላስል። ያላቸው ድካም ምን ይሆን? ሊወጡ እየታገሉ ካሉባቸው ችግሮች አንዳንዶቹ ምን ምን ናቸው? ብዙ ጊዜ የሚወድቁባቸው ኃጢአቶች ምንድን ናቸው? የሚገጥሟቸው ፈተናዎች ምንድን ናቸው? ይህ ምንባብ እነዚህን ፈተናዎች ለማሸነፍ እንዴት ይረዳቸዋል? የዚህን እውነት ትርጉም መያዝ እንዲችሉ በምን ዓይነት መንገድ ላቀርብላቸው ይገባል? የምንባቡ እውነት ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እንዲረዱ የሚሳተፉባቸውን እንቅስቃሴዎች ልወጥን?

ትምህርቱን እያዘጋጀህ ሳለ እነዚህና ሌሎች ብዙ ጥያቄዎች ወደ አእምሮህ ሊመጡ ያስፈልጋል። የስም መጥሪያ ደብተርህን አንሥተህ ለእያንዳንዱ ተማሪ ለመጸለይ አሁን ጥሩ ጊዜ ነው። ስለ ቤታቸው፥ ስለ ቤተሰቦቻቸው፥ ስለ ትምህርት ቤታቸው፥ ስለ ጎረቤቶቻቸው አስብ። በአሁኑ ሰዓት የሚፈልጉት እርዳታ ምን ዓይነት ነው?

---

2ኛ ጥያቄ፡- የተማሪዎችህን ፍላጎት በምታስብበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደ አእምሮህ የሚያመጣቸውን ነገሮች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ። ይህ ዓላማህን ለማዘጋጀት፥ የቃል ጥናት ጥቅስ ለመምረጥ፥ መግቢያ ለማዘጋጀት እና ትምህርቱን ለማዘጋጀት ይረዳሃል። እንዲሁም ተማሪዎችህ ትምህርቱን ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ለመርዳት ምሪት ይሰጥሃል።

---

## ሁለተኛ ቀን፡- የትምህርቱ ዓላማ

1. ትርጓሜ፡- የአንድ ትምህርት ዓላማው ምንድን ነው? በቀላል አነጋገር ዓላማ መምህሩ ለማከናወን ተስፋ የሚያደርገው አንድ አሳብ ነው። ነገር ግን በዓላማ ውስጥ መካተት ያለበት ነገር ምንድን ነው? ዓላማው ለተማሪዎቹ የሚቀርበውን ትምህርት የሚያጠቃልል መሆን አለበት። ይህም ማለት መምህሩ የሚያስተምረው ነገር አጭር መግለጫ ማለት ነው። እንዲሁም ትምህርቱ ከዛሬ ዘመን ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ጨምሮ መናገር አለበት። በሦስተኛ ደረጃ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከዕለት ሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱ እንዴት አድርገን እንደምንረዳቸው መገለጽ አለበት። ደጋግመን የምናስተምረው ሕይወትን ለመለወጥ እንደሆነ ተናግረናል። የማስተማራችን ዒላማ የሆነውን ይህን መሠረታዊ ነገር ፈጽሞ መሳት የለብንም። ስለዚህም የትምህርት ዓላማ በተማሪዎቻችን ሕይወት ውስጥ ትምህርታችንን ከተማሩ በኋላ እንዲኖር የምንፈልገውን ነገር ማካተት አለበት።

---

3ኛ ጥያቄ፡- በራስህ ቋንቋ የዓላማን ሦስት ክፍሎች ጻፍ። እያንዳንዱ ክፍል አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

---

2. የጥሩ ዓላማ ዓይነተኛ መመዘኛዎች።

ሀ) ዓላማው መታወስ እንዲችል አጠር ማለት አለበት። ዓላማው በአንድ ዓረፍተ ነገር ሊጠቃለል ይገባዋል።

ለ) ሊጻፍ እንዲችል በሚገባ ግልጽ መሆን አለበት። አንዳንድ መምህራን ለማስተማር ስለሚፈልጉት ነገር ያላቸው አሳብ አሻሚ ነው። በጽሑፍ ለማስፈርም ፈጽሞ አይሞክሩም። በሚገባ የታሰበበት ዓላማ ለመጻፍ የሚያስቸግር መሆን የለበትም።

ሐ) ሊፈጸም እንዲችል ውሱን የሆነ አሳብ ሊኖረው ያሻል። ብዙውን ጊዜ ለትምህርታችን ያለን ጊዜ የተወሰነ ነው። ምክንያቱም የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍለ ጊዜ ከዋናው የእሑድ ጧት ፕሮግራም በፊት ስለሚሆንና ተማሪዎች በተወሰነ ጊዜ መለቀቅ ስላለባቸው ነው። ወይም ደግሞ ትምህርቱ በሳምንት ውስጥ ይሆንና ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ መጥተው ከመምሸቱ በፊት ወደ ቤታቸው መድረስ ስላለባቸው ነው። ዓላማዎቻችን የተወሰኑ፥ ግልጽና ባለን ጊዜ ውስጥ የምንፈጽማቸው መሆን አለባቸው።

ዓላማውን በክፍል ውስጥ መግለጽ ይኖርብናል ወይ ብለን እንጠይቅ ይሆናል። መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ዓላማ ከሆነ በትምህርቱ መግቢያ ላይ ቢጨመር ጥሩ ይሆናል። መንፈሳዊ መረዳትን ለመስጠት ወይም የባሕርይ ምላሽ ለማምጣት የተዘጋጀ ዓላማ ከሆነ በክፍል ውስጥ ባንገልጸው ጥሩ ነው። በእነዚህ ሦስት ዓይነት ዓላማዎች ላይ ቀጥለን እንነጋገርባቸዋለን።

3. የዓላማ ዓይነቶች

እንደጠቀስነው የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪው ለትምህርቱ ግልጽ የሆነ ዓላማ ሊኖረው ይገባል። እነርሱም እውቀትን ለማካፈል፥ ምሪትን ለመስጠት፥ እና የባሕርይ ምላሽን ለማስገኘት ናቸው። መምህሩ በአንድ ትምህርት ውስጥ እነዚህን ዓላማዎች በሙሉ በአጭሩ ሊነካካ እንደሚችል እውነት ነው። ነገር ግን በትምህርቱ ውስጥ በሙሉ አንድ ዋነኛ ዓላማ ቢኖረው የተሻለ ነው።

ሀ) እውቀትን ለማካፈል:- እንደጠቀስነው ተማሪዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህም በማሳወቅ ዓላማ መምህሩ እውነታዎችን ያስተምራል። እንዲሁም መረጃዎችን ይሰጣል። ትርጉሙን እርሱ ያብራራል። የሰጠውን መረጃ መማራቸውን ለመፈተን የሚጠቀምበትንም ዘዴ በትምህርቱ ውስጥ ያካትታል። በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ተማሪው በመረጃው ላይ ሙሉ እውቀት ይኖረዋል። መምህሩ በተማሪው የተጠየቀውን ሲመልስ ተማሪው ምን መረጃ እንዳገኘ ያውቃል። ተማሪው የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች መልሶ መናገር መቻል አለበት።

የትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስት እውነታዎችን ማስተማር እና ተማሪዎቹ የምዕራፉን ክስተቶች በትክክለኛው ቅደም ተከተል በራሳቸው አነጋገር እንደገና እንዲተርኩት ማድረግ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት ተማሪዎቹ ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ያሳለፈውን ታሪክ አስፈላጊ ነጥቦችን ሳይተዉ መናገር መቻላቸው ሊሆን ይችላል። የንጉሡን ስም፥ አስተዳዳሪዎቹና ሹማምንቶቹ እነማን እንደነበሩ ማወቅ አለባቸው። አስቸጋሪ

የሆኑትን ቃላት ትርጉም መረዳት አለባቸው። በንጉሡ ሥር የነበሩት የሌሎቹ ሠራተኞች ቅናት ምክንያት ምን እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ገገርዎቹ በዳንኤል ላይ ያደረጉትንና እግዚአብሔር እንዴት ጣልቃ እንደገባ ሊያውቁ ይገባል።

ለ) ማነቃቂያ፡- መንፈሳዊ መነቃቃትን የመስጠት ዓላማ የቅዱሳት መጻሕፍትን መርሆዎች ማስተማርና ከሚማሩትም የእግዚአብሔር ቃል የተነሣ የተማሪዎቹ አመለካከትና እሴቶችን መለወጡ ነው። አንድ ሰው በመንፈሳዊ መንገድ እንዲረዳ የእግዚአብሔር ቃልን ሚዛን ከተማሪው ፍላጎቶች ጋር ከፍ አድርገን በማንሣት እነዚያን ፍላጎቶች ማሸነፍ ነው። መንፈሳዊ መነቃቃትን መስጠት ማለት ማነሣሣት፥ መቀስቀስ፥ ወይም ማበረታታት ማለት ነው።

«ተማሪዎቹ በምንም ሁኔታ ውስጥ ለጌታ ጸንተው ይቆሙ ዘንድ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን ማስተማር» የሚለው አሳብ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። የትምህርቱ ዓላማ የምዕራፍ ስድስትን ይዘት በማስተማር እግዚአብሔር እንዴት ዳንኤልን እንዳዳነው ማሳየትና ምንም ነገር ቢመጣባቸው ያለ ፍርሃት ለጌታ እንዲቆሙ መንፈሳቸውን ማነቃቃት ነው።

እንዲህ ዓይነቱን ዓላማ መለካት ይቸግራል። ተማሪዎቹ ክርስትናቸውን በመደበቅ ፈንታ ለጌታ በቆሙባቸው ጊዜያት እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳቸው ምስክርነት እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል።

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ወታደርነት ተቀጠረና ከቤቱ፥ ከክርስቲያን ጓደኞቹና ከቤተ ክርስቲያኑ ተለይቶ ሄደ። በመጀመሪያው የዕረፍት ጊዜው ወደ ቤት ሲመለስ አንድ ጓደኛው እንዲህ ብሎ ጠየቀው። «የክርስትና ሕይወትህ እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስህን ታነባለህ? ትጸልያለህን?» ወጣቱም እያፈረ እንዲህ ብሎ መለሰ «ያንን እንኳ አላደርግም። ከሌላው ሰው መለየትን እፈራለሁ»።

ዳንኤልም እንደዚያ ሊያደርግ ይችል ነበር። በንጉሥ ናቡከደነፆር የአረመኔዎች አደባባይ ጌታን የሚወድ እርሱ ብቻ ነበር። መብራቱን ከዕንቅብ በታች ለመደበቅ ይችል ነበር። ነገር ግን በየቀኑ ሦስት ጊዜ መጸለዩንና ለጌታ ብሎ መኖሩን ቀጠለ። ስለ እርሱ እንዲህ ተብሏል። «የዚያን ጊዜም አለቆችና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን የታመነ ነበረና፥ ስሕተትና በደልም አልተገኘበትምና በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ያገኙበት ዘንድ አልቻሉም» (ዳን. 6:4)።

ሐ) የባሕርይ ምላሽ ዓላማ

የባሕርይ ምላሽ ዓላማ አሳብ በተማሪው ጠባይና ሕይወት ውስጥ ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ማየት ነው። በአንዳንድ የሕይወታቸው አቅጣጫ በተወሰነ ክርስቲያናዊ መንገድ መኖር መጀመር አለባቸው። የሚታይና ተጨባጭ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ መነቃቃት ይኖርባቸዋል።

መምህሩ ለዕለቱ በተመረጠው ክፍል ላይ በመመሥረት መረጃ መስጠት እንዳለበት እውነት ነው። ማስተዋል የተሞላበት ምላሽ በእውቀት ላይ

የተመሠረተ መሆን አለበት። እንዲሁም መምህሩ የተማሪውን ስሜት መንካት ወይም መንፈሱን ማነቃቃት አለበት። ነገር ግን ተጨባጭ የሆነ እርምጃ እስካልወሰደ ድረስ ዓላማው ግቡን አልመታም። እስቲ በእነዚህ ሦስት የዓላማ ዓይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት በምሳሌ እንግለጽ።

የእውቀት ዓላማ። ተማሪው የምዕራፉን ክንውኖች በትክክለኛው ቅደም ተከተል አውቆ ከዚያም በራሱ አባባል እንዲናገር የዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን ጭብጦች ማስተማር።

የመንፈሳዊ ማነቃቂያ ዓላማ። ተማሪው በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለ ፍርሃት ለጌታ እንዲቆም ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን ማስተማር።

የባሕርይ ምላሽ አላማ። ተማሪዎች ቋሚ የሆነ ዕለታዊ ጸሎት እንዲጀምሩ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን ማስተማር። ከተማሪዎች ጋር በመወያየት የጸሎት ሰዓታቸውንና ጥያቄዎቻቸውን ለመጻፍ የሚጠቀሙበትን ወረቀት አዘጋጅ።

በእነዚህ ሦስት ምሳሌዎች እያንዳንዱ ክፍል አንድ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን በተለያየ ዓላማ እንደሚያጠኑ ማየት ትችላለህ። አንደኛው ዓላማ ከሌላው ይሻላል እያልን አይደለም። ለሁሉም ቦታ አላቸው። ነገር ግን የተለወጡ ሕይወቶች ለማየት የባሕርይ ምላሽ ዓላማዎች በቋሚነት ሊኖሩን እንደሚገባ ማስተዋል አለብን። ብዙ ጊዜ ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን ከዕለታዊ ኑሮአቸው ጋር እንዴት እንደሚያዛምዱት አያውቁም። መምህሩ ተጨባጭ የባሕርይ ምላሽ ዓላማዎችን መጠቀሙ አማራጭ የሌለው የሚሆነው ስለዚህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ጥሩ ነው። ሰዎች ለነገሮች የሚሰጡትን ዋጋና አመለካከታቸውን እንዲለውጡ ማስተማር የተሻለ ጥሩ ነው። ነገር ግን እየተማሩ ያሉትን ጉዳይ በክርስትና ሕይወታቸው መለማመዳቸው አስፈላጊ ነገር ነው።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- ያዕቆብ 1፡22-25 አንብብ። በምዕራፍ አራት 3ኛ ቀን እነዚህን ጥቅሶች ተመልክተናቸዋል። እንደገና በምትመለከታቸው ጊዜ ያዕቆብ በዘመኑ በነበሩት ክርስቲያኖች ሕይወት ያየው ድካም ምን ነበር? የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በምንሰማበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብን? |

4. የቃል ጥናት ጥቅስ መምረጥ።

ትምህርቱን በማቀድ ውስጥ የሚቀጥለው ደረጃ ተስማሚ የቃል ጥናት ጥቅስ መምረጥ ነው። ለትምህርታችን ዓላማን ከጻፍን በኋላ ዓላማውን የሚደግፍ ጥቅስ መምረጥ አለብን። ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት የዓላማ ዓይነቶች ተመልሰን እንመልከት።

ሀ) መረጃ የመስጠት ዓላማ፡- ለዚህ ዓላማ እንደ ዳንኤል 6፡22 ዓይነት ጥቅስ መምረጥ እንችላለን። ይህ ተማሪው ዳንኤል የወሰደው አቋም ያመጣውን ውጤት እንዲረዳ ይረዳዋል። ይህንንም ጥቅስ በቃል በማጥናት ታሪኩን ለመረዳት ተጨማሪ መረጃ ይሆንላቸዋል።

ለ) መንፈሳዊ ማነቃቂያን የመስጠት ዓላማ፡- በዚህ ዓላማ እንደ ኢሳይያስ 41፡10 ያለውን ጥቅስ መምረጥ እንችላለን። «እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤

እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፥ እረዳህማለሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ»። ይህ ጥቅስ ተማሪው በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ጌታ ከእርሱ ጋር ስላለ ለጌታ መቆም እንደሚችል እንዲያውቅ ይረዳዋል።

ሐ) የባሕርይ ለውጥ ምላሽ ዓላማ፡- በዚህ ዓላማ ውስጥ እንደ አንደኛ ተሰሎንቄ 5፡17–18 ያለውን ጥቅስ መምረጥ ይቻላል። «ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና»። ይህ ለዕለታዊ የጸሎት ጊዜያቸውና ያለማቋረጥ እንዲጸልዩ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ላላቸው አዲስ ዕቅድ ሊያበረታታቸው ይችላል።

5. የቃል ጥናት ጥቅስ ማስተማር

ማንበብ ለማይችሉ ትንንሽ ልጆች አጫጭር የሆኑ ጥቅሶች ሊመረጡና በመደጋገም ብቻ ሊማሯቸው ይችላሉ። መምህሩ ጥቅሱን በቃሉ ከተናገረ በኋላ ልጆች ከእርሱ በኋላ እንዲደግሙት ማድረግ አለበት። ትንንሾቹ ልጆች ቃላቱን እንደተረዱለት እርግጠኛ መሆን አለበት። መምህሩ ሥዕሎች ወይም የመርጃ መሣሪያዎችን ከተጠቀመ ልጁ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲያስታውስ ይረዳዋል። «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው» [መዝ. (119)፡105] የሚለውን የሚያስተምር ከሆነ የመብራት ሥዕል ወይም ኩራዝ፥ ወይም ደግሞ ፋኖስ ሊያመጣ ይችላል። የባትሪ መብራትም ሊሠራ ይችላል። ከዚያም መምህሩ እንዴት መብራቱ በጨለማ ውስጥ እንዲሄድ እንደሚረዳው ለተማሪዎቹ ያሳያል። በዚሁ ዓይነት መንገድ የእግዚአብሔር ቃል በክርስትና ሕይወት እንድንራመድ ይረዳናል።

ለትላልቅ ልጆች በጥቁር ሠሌዳ ላይ መጻፍ በጣም ጥሩው መንገድ ነው። ልጆቹ ከአንተ በኋላ ብዙ ጊዜ ደግመው እንዲናገሩት አድርግ። ከዚያም አንዳንድ ቃላት አልፎ አልፎ በማጥፋት ማንበብ እንዲቀጥሉ አድርግ። ጠቅላላው ምንባብና ጥቅሱ እስኪጠፋ ድረስ ቃላትን ማጥፋትህን ቀጥል። በዚህ ጊዜ ልጆቹ ቃላቱን በሙሉ ተምረዋቸዋል። ከዚያም አንዳንድ ልጆች ብቻቸውን ከዚያም በቡድን እንዲሉት ማድረግ ጥሩ ነገር ነው። ድግግሞሽ የቃል ጥናት ምሥጢር ነው። ቋሚ በሆነ መንገድ መከለስ አለበት፤ ያለበለዚያ ይረሳል።

ጥቅሱ ለወጣቶችና ለጎልማሶች ለቤት ሥራ ከተሰጠ በኋላ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እንደ ቡድኑ በአንድነት ሊናገሩት ያሻል። ምንባቦች ወይም ደግሞ ሙሉ መጻሕፍት በወጣቶች በቃል ሊጠኑ ይችላሉ፤ አንዳንድ የሚያነሣሡ ነገሮች፥ ማለትም እንደ ውድድር ብዙ ጥቅሶችን በመስጠት መጠቀም ይቻላል። የተወሰኑ ጥቅሶችን በአእምሮ ከያዙና በአንድ ጊዜ ከተናገሯቸው መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌላ ሽልማት ሊሰጥ ይችላል።

ዳዊት እንዲህ ብሏል። «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ. (119)፡11]።

5ኛ ጥያቄ፡- ማርቆስ 2፡1-12 አንብብ። ለዚህ ታሪክ ሦስት ዓይነት ዓላማዎችን ጻፍ። ከእያንዳንዱ ዓላማህ ጋር የሚሄዱ ተስማሚ የቃል ጥናት ጥቅሶች ምረጥ።

## ሦስተኛ ቀን፡- የትምህርቱ መግቢያና ትምህርቱ

ለክፍላችን የመረጥነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በጥንቃቄ አጥንተናል። የምንባቡን ዋና ትምህርት እንድንረዳ ጌታ አእምሮአችንን እንዲከፍትልን ጸልየናል። ስለ ምንባቡ ተጨማሪ መረዳትን ለማግኘት ደግሞ ሌሎች የማጣቀሻ መጻሕፍትን ተመልክተናል። ከተገኘ ደግሞ የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍን አንብበናል።

እንዲሁም ስለ ተማሪዎቻችን ፍላጎት አስበናል። ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚያስፈልጋቸው ካሰብን በኋላ የትምህርታችንን ዓላማ በጽሑፍ አስፍረናል። ከዚያም ከእርሱ ጋር እንዲሄድ ጥሩ ደጋፊ የቃል ጥናት ጥቅስ መርጠናል። አሁን ወደሚቀጥለው ትምህርት የማዘጋጀት ደረጃ ለመሄድ ዝግጁ ነን።

1. መግቢያ

መግቢያው የተማሪዎቹን ፍላጎት እንዲያነሣሣ ሆኖ መታቀድ አለበት። እንዲሁም ለተማሪዎቹ እንግዳ ያልሆነ ነገር መሆን አለበት። መግቢያ የትምህርቱ «ቁልፍ» ነው። እናም የተማሪዎቹን አእምሮ በመክፈት በትምህርቱ ውስጥ ምን እንደሚመጣ ለማወቅ ተጨማሪ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ለምሳሌ መንፈሳዊ መነቃቃትን መስጠት የሚለውን ዓላማ ብንጠቀም የዳንኤልን ስድስተኛ ምዕራፍ ስናስተምር የተለየ ለመሆን ስለፈራው ወጣት ወታደር ታሪክ መንገር እንችላለን። ከዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንድ የተለየ ለመሆን ስላልፈራ ሰው እንማራለን ብለን መናገር እንችላለን። ተማሪዎቹ በትምህርቱ ውስጥ ምን ተከትሎ እንደሚመጣ እንዲገነዘቡ መግቢያው አእምሮአቸውን እንዴት እንደከፈተ ታያለህን?

መግቢያው ረጅም መሆን የለበትም። ነገር ግን የተማሪዎቹን ቀልብ ወደ ትምህርቱ መሳብ አለበት። በጣም የለመዱት ነገር መሆን አለበት። ትምህርቱን ለመክፈት ቁልፍ ነውና።

አንዳንድ ጊዜ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለልጆቹ የተለመደ ዕቃ በማምጣት ለትምህርቱ መግቢያ መስጠት ትችላለህ። መረዳት እንድትችል እስቲ አንድ ምሳሌ እናቅርብ።

«ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ» የሚል ትምህርት ልታስተምር ነው እንበል። ዓላማህ የባሕርይ ምላሽ ማግኘት ነው። ልጆቹ ዕለታዊ የጸሎት ጊዜ እንዲኖራቸው ማለት ነው። በቃል የሚጠናው ጥቅስ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17-18 ነው። የሚከተለውን ለመግቢያነት ልትጠቀምበት ትችላለህ።

ጸሎት ምንድን ነው? (መልሶቻቸውን ስማ።) ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገር ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንችላለን። እንድንጸልይ የጋበዘን እርሱ ነው። ጸሎታችንን

ለመመለስም ተስፋ ገብቶልናል። እስቲ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከፍተን ዮሐንስ 16፡23 -24 እናንብብ። (መረዳት እንዲችሉ ስለ ጥቅሶቹ ጥያቄዎች ጠይቃቸው።) ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኝና በየቀኑ ስለሚጸልይ አንድ ሰው ታሪክ እንሰማለን። እንዲያውም ይህ ሰው በቀን ሦስት ጊዜ ይጸልይ ነበር። እግዚአብሔርም በሚያስደንቅ ሁኔታ ይጠብቀው ነበር። ከታሪኩ መስማት ትፈልጋላችሁን? በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በዳንኤል ምዕራፍ ስድስት ላይ እናገኘዋለን። እባካችሁ ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን አውጡ።

ከዚያም ልታስተምረው ያለህን ትምህርት ትቀጥላለህ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡- ማርቆስ 2፡1-12 አንብብና ለታሪኩ ጥሩ መግቢያ ጻፍ። |

2. ትምህርቱ

የዳንኤልን ስድስተኛ ምዕራፍ ባጠናህ ጊዜ ወደ ተለያዩ ክፍሎች እንደሚከፋፈል አይተሃል።

ሀ. ዳንኤል በንጉሥ ዳርዮስ ሥር ሆኖ እንዲያስተዳድር ተመረጠ (ቁ. 1-3)።

ለ. አስተዳዳሪዎችና ሹማምንቱ በዳንኤል ላይ ቀኑበት (ቁ. 4-5)።

ሐ. አስተዳዳሪዎቹ ንጉሡ አዲስ ሕግ እንዲያወጣ ገፋፉት (ቁ. 6-9)።

መ. ዳንኤል ለአዲሱ ሕግ አልታዘዘም (ቁ. 10-12)።

ሠ. ንጉሡ ሕጉን እንዳይለውጥ አስተዳዳሪዎች ገፋፉት (ቁ. 13-15)።

ረ. ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ ተጣለ (ቁ. 16-20)።

ሰ. እግዚአብሔር ዳንኤልን ጠበቀው፤ ክፉ የሠሩትንም ቀጣቸው (ቁ. 21-24)።

ሸ. ንጉሡ ለሚገዛቸው ግዛቶች ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ጻፈ (ቁ. 25-28)።

ለእያንዳንዱ ክፍል ቦታ እየተውህ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መጻፍ ይገባሃል። ተጨማሪ ማስታወሻዎችም እንጨምራለን።

ለምሳሌ ከላይ ባለው ‹ሀ› ሥር ከዚህ እንዲሚከተለው ማስታወሻ ማስፈር እንችላለን። ከደብተሩ ጠርዝ በስተቀኝ በኩል ቀጥተኛ መስመር ማስመር እንችላለን። ከመስመሩ በስተግራ በኩል የምናስተምረው ማስታወሻዎች፥ የምንነጋገራቸው ነገሮች ይኖራሉ። ከመስመሩ በስተቀኝ እኛ የምንሠራቸውን ወይም ተማሪዎቹ የሚሠሯቸውን ነገሮች እንጽፋለን።

ሀ. ዳንኤል በንጉሥ ዳርዮስ ሥር ሆኖ እንዲያስተዳድር ተመረጠ (ቁ. 1-3)።

- እስቲ ዳንኤልን እንመልከት ምዕራፍ 6፡1-3 - አንድ ልጅ ቁ. 1-3 ያንብብ።

- ንጉሥ ዳርዮስ 120 ሹማምንቶችን ሾመ (ቁ.1-3)።

- ዳንኤልን ከሦስቱ አስተዳዳሪዎች አንዱ አደርጎ መረጠው። ከበድ ያሉ ቃላት ካሉ አብራራ።
- ዳንኤል ጨዋ ሰው ነበረ። ንጉሥ በሁሉ ላይ አለቃ ሊያደርገው ዐቀደ።

በዚህ ዓይነት ከላይ በተዘረዘረው በእያንዳንዱ ክፍል ሥር የተለያዩ ማስታወሻዎችን መያዝ ያስፈልጋል። በስተግራ በኩል ስለምትናገራቸው ነገሮች የሚያሳስቡህ አጫጭር ነገሮች ይኖራሉ። ይህንን በጥንቃቄ ከተከተልህ እንዲሁም ወደ ክፍል ከመሄድህ በፊት በቤት ከተለማመድኸው ሳትሳሳት ታሪኩን በትክክለኛው አካሄድ ልትናገር ትችላለህ።

በስተቀኝ በኩል አንተ የምታደርጋቸው ወይም ተማሪዎችህ እንዲያደርጉ የምታዝዛቸው ነገሮች ሊሰፍሩ ይገባል። አንዳንድ ጊዜ በስተቀኝ በኩል ያለውን በቀይ እስክሪብቶ መጻፍ ጥሩ ነው። ከዚያም በምታስተምርበት ጊዜ እነዚያን ማስታወሻዎች በቀላሉ ታገኛቸዋለህ። ለልጆቹ የሚሠሩትን ነገር መጨመር አስፈላጊ ነው። ምናልባትም አንድ ነጥብ ላይ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የሚሄድ አንድ አዝማች ቆመው እንዲዘምሩ ማድረግ ትችላለህ። ወይም ደግሞ ቆመው የቃል ጥናት ጥቅሱን ደግመው እንዲሉት ታደርጋለህ። ወይም በተወሰነ ነጥብ ላይ ከትምህርቱ ጋር የሚሄድ አንድ ሥዕል ወይም ደግሞ አንድ ዕቃ ታሳያቸዋለህ። እነዚህን ነገሮች በስተቀኝ በኩል የምትጠቀምበት ቦታ ላይ ከጻፍሃቸው አትረሳቸውም።

ልጆች ታሪክ ስለሚወድዱ አተራረክህን በጥሩ ኢትዮጵያዊ አቀራረብ ልትለማመድ ያስፈልግሃል። አታንብብላቸው። በራስህ ቋንቋ ተናገረው። እንቅስቃሴዎችን ተጠቀም። በታሪኩ ውስጥ የሚገኘው ሰው ያደረገውን ነገር ለልጆቹ በእንቅስቃሴ አሳያቸው። በታሪኩ ውስጥ የሚገኘው ሰው ደስተኛ ከሆነ ደስተኛ ፊት፥ ያዘነ ከሆነ ያዘነ ፊት፥ የተቆጣ ከሆነ ደግሞ ቁጡ ፊት አሳያቸው። ታሪኩን በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ሕይወት ያለው ካደረግኸው ልጆቹ ንቁ የሆነ አትኩሮት ሲሰጡህ ታገኛቸዋለህ። አስታውስ በማየት፥ በመናገር እና በማድረግ እንዲሁም በመስማት ካስተማርህ ተማሪዎቹ (ልጆቹ) የትምህርቱን ጭብጥ ረዘም ላለ ጊዜ ያስታውሱታል።

ስለ እያንዳንዱ ክፍል ማስታወሻ እየጻፍህ ጠቅላላውን ትምህርት በዚሁ መንገድ ቀጥል።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡- የማርቆስ ወንጌል 1፡12ን እንደገና አንብበህ ከላይ በተጠቀሰው ዘዴ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አዘጋጅ። |

## አራተኛ ቀን፡- የታሪኩ ትርጉምና ከሕይወት ጋር ያለው ተዛምዶ

ለትምህርታችን ስለሚያስፈልገን ጥሩ መግቢያ ተምረናል። እንዲሁም በተገቢው መንገድ ለማስተማር እንዴት አስተዋጽኦ ማውጣት እንዳለብን ተምረናል። በተጨማሪም እኛ እንድናደርገው ወይም ተማሪዎቻችን እንዲያደርጉት የምንፈልገውን ነገር የምንጽፍበትን በስተቀኝ ያለ ክፍል ስለ

መሥራት ተምረናል። ዝግጅታችንን ከመጨረሳችን በፊት ልንሠራቸው የሚገቡ ሁለት ነገሮች ገና ይቀሩናል።

8ኛ ጥያቄ፦ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተጻፈ ይህ ትምህርት ለእኛ ዛሬ ምን ይነግረናል? ለዛሬ እንዴት ልንተረጉመው እንችላለን? በቀጥታ እንዳለ በሥራ ላይ ማዋል እንችላለንን? አሁን ላለንበት ሁኔታ ወስደን ልናስማማው ይገባናል?

1. የትምህርቱን ትርጉም መረዳት

ይኸኛው የትምህርቱ ዝግጅት ክፍል «ድልድይ ስለ መሥራት» ነው የሚናገረው። እስቲ እንደገና ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን እናንብብ። ቅጣት የሚያስፈልጋቸውን ወንጀለኞች የምንወረውርባቸው የአንበሳ ጉድጓዶች ዛሬ አሉን? ሕግን ለሚያፈርሱ ሰዎች የሚደረገው ይኼ ነውን? ምን እናደርጋቸዋለን? በዚህ አገር ሕግ አፍራሾች እንዴት ነው የሚቀጡት?

በታሪካችን ውስጥ የተከሰሰው ሰው ጥፋት የለበትም ነበር፤ ነገር ግን እንደ ማንኛውም ወንጀለኛ ተቀጣ። ይህ ዛሬ አንዳንዴ ይከሰታል? ይህ በእኛ ላይ የሚደርስ ቢሆን ምን እናደርጋለን? እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሊጠብቀን ይችላልን? ጥፋተኞች ሳንሆን መቀጣት ቢኖርብን እስር ቤት መግባት ወይም ዳግም መገረፍ ቢደርስብን፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናልን? ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ስለ ተቀጣ የምታውቀው ሰው መናገር ትችላለህን? እግዚአብሔር እርሱን ጠበቀውን?

የዳንኤልን ታሪክ አሁን ላለንበት ሁኔታ ጠቃሚ እንዲሆን ከላይ በተጠቀሱት ጥያቄዎች እንዴት እንዳስማማነው አየህን? «ድልድይ መሥራት» ስንል ይህን ማለታችን ነው። በታሪኩ ውስጥ ካለው ሁኔታ እኛ ወዳለንበት ሁኔታ ድልድይ እየሠራን ነው።

2. ከሕይወት ጋር ማዛመድ።

በዚህ የትምህርቱ የመጨረሻ ክፍል ተማሪው የትምህርቱን ማዕከላዊ እውነት ከግል ሕይወቱ ጋር እንዲያዛምድ ልንረዳው ይገባል። መንፈሳዊ መነቃቃትን የመስጠት ዓላማ ሁለተኛ ቀንን በመጠቀም ኢሳይያስ 41፡10 ያለውን የቃል ጥናት ጥቅስ በማስታወስ ክፍሉን መጨረስ እንችላለን። እንዲህ ይላል። «እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፥ እረዳህማለሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ»።

ዓላማችን ተማሪዎቻችን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ሳይፈሩ ለጌታ እንዲቆሙ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትን ማስተማር ነበር።

የቃል ጥናት ጥቅሳችን ደግሞ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ስለገባልን መፍራት እንደማያስፈልገን ያረጋግጥልናል። መታወክ የለብንም። እርሱ አምላካችን ነው። እርሱ እንደሚያበረታንና እንደሚረዳን ተናግሯል። ደግሞም ይረዳናል። እንዲያውም በጽድቁ ቀኝ እጁ ደግፎ ይይዘናል። ከዚህ በላይ ምን እንፈልጋለን? እግዚአብሔር እውነት ነው። እውነትንም ስለሚናገር መታመናችንን በእርሱና በቃሉ ላይ ማድረግ እንችላለን። እግዚአብሔር በፍጹም አይዋሽም። ስለዚህም በዚህ ሕይወት ምንም ዓይነት

ችግር ልንጋፈጥ የተጠራን ብንሆን እርሱ ከእኛ ጋር እንደሚሆንና እንደሚረዳን ዋስትና አለን።

9ኛ ጥያቄ፦ እንደገና ማርቆስ 2፡1–12 አንብብ። ተመልሰህ ዓላማህን፥ የቃል ጥናት ጥቅስህን፥ መግቢያህንና ትምህርትህን ተመልከት። በታሪኩ ትምህርት እና ዛሬ ባለንበት ሁኔታ መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት ድልድይ ሥራ። ከዚያም ትምህርቱ ዛሬ ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር እንዴት ሊዛመድ እንደሚችል አሳይ።

አምስተኛ ቀን፦ ክለሳ። ለሳምንታዊ የውይይት ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

የጥሞና መልእክትን የሚያቀርበው ሰው ጥሩ ትምህርት ለማዘጋጀት የሚረዱትን ደረጃዎች እንዲከተል አበረታታው። ምንም እንኳን አጭር ቢሆንም በእያንዳንዱ ደረጃ ማለፍ አለበት። በሚቀጥሉት ስብሰባዎች ሌሎች ትምህርት እንዲያዘጋጁና እንዲያስተምሩ ዕድል ስጣቸው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቡድኑ በአእምሮው የትምህርቱን ጠቅላላ ገጽታ ማስታወስ መቻል አለበት። በትክክለኛው መንገድ መስጠቱን እርግጠኛ ሁን።
2. የዓላማን ሦስት ክፍሎች ተነጋገርባቸው። ለምንድን ነው አስፈላጊ የሆኑት?
3. ስለ ሦስቱ የዓላማ ዓይነቶች እና እንዴት እንደሚለያዩ ተነጋገሩ። ዓላማዎች ተማሪውን ማዕከል ያደረጉና ተማሪው ከትምህርቱ መጨረሻ በኋላ ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ሊሆኑ ይገባል።
4. ጥሩ መግቢያ የሚያስፈልገን ለምን እንደሆነ ተወያዩ። መግቢያው መፈጸም ያለበት ተግባር ምንድን ነው?
5. የትምህርቱን ይዘት በምታቀርብበት ጊዜ፥ በትንንሽ ክፍሎች መከፋፈልህ ለምን ይረዳሃል? በስተግራ ያለው መስመር ለምን ይረዳል? በስተቀኝስ ያለው?
6. የትምህርት ዝግጅትን የመጨረሻ ሁለት ክፍሎች በተመለከተ ተወያዩ? እያንዳንዳቸው ለምን አስፈለጉ?

## ትምህርት አሥራ ሁለት

## የሰንበት ትምህርትን ለማስተማር ተጨማሪ መርጃዎች

አንደኛ ቀን፦ መምህሩና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ (1)

1ኛ ጥያቄ፦ ወደ ክፍል አምስት ሦስተኛ ቀን ትምህርት ተመለስ እና አራቱን የሰንበት ትምህርት ዓላማዎች ጻፍ። እስከ አሁን በነበሩን ትምህርቶች የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ዓላማዎችን ለመከተል እንዴት እንፈልግ እንደነበር ለማየት ችለሃልን? በኮርሳችን ውስጥ እነዚያን ዓላማዎች መከተላችንን የሚያሳዩ ቢያንስ አምስት መንገዶችን ዘርዝር።

ባለፈው ሳምንት ጥሩ ትምህርት እንዴት እንደምናዘጋጅ ተምረናል። ዛሬ ደግሞ አስተማሪው በይበልጥ በክፍል ውስጥ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸውን ዘዴዎች እንነጋገራለን።

ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የሚመጡት ልጆች የተለያየ ዕድሜ ያላቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ገና ትምህርትም አልጀመሩም። ሌሎቹ ከአምስት እስከ ስምንት ዓመት በትምህርት ላይ የቆዩ ናቸው። እንደየዕድሜያቸውና እንደ ችሎታቸው የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው።

1. ትረካ

ልጆች ታሪክ ይወዳሉ። በልጆች ዕድሜ ታሪኮችን በሚገባ መጠቀም እንችላለን። በተለይ ትንንሾቹ ልጆች ታሪኮችን ይወዳሉ። ታሪክ በምንልበት ጊዜ ልብወለድ ታሪኮችን ማለታችን አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንደገና መተረክ ማለታችን እንጂ። በመምህርነቱ ተወዳዳሪ ያልነበረው ጌታ ኢየሱስ የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች ከተመለከትን፥ ታሪኮችንና ምሳሌዎችን አዋቂዎችን ጨምሮ ለሁሉ ዕድሜ በሚስማማ መንገድ ይጠቀም ነበር።

ኢየሱስ የጠፋውን በግ ታሪክ እንደተናገረ ታስታውሳላችሁ። ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር ለኃጢአተኛው ያለውን ፍቅር ለማስረዳት ነው። ማቴ. 18:12–14 እና ሉቃ 15:3–7 አንብብ። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በጎችና እረኞች በሕዝቡ የታወቁ ነበሩ።

ኢየሱስ ለእነርሱ የተለመዱትን እና ደስ የሚሏቸውን ነገሮች ይመርጥና በመጨረሻ ትምህርቱን ከዕለታዊ ኑሮአቸው ጋር ያዛምድ ነበር።

አስተማሪው ታሪክን በሚናገርበት ጊዜ

- የታሪኩን እውነታዎች ሁሉ ማወቅ አለበት። ከዝርዝሮቹ ነገሮች ጋር ራሱን ለማለማመድ ደግሞ ደጋግሞ ሊያነበው ይገባል።
- በአእምሮው ውስጥ ታሪኩን ሊስለው ይገባል።
- ታሪኩን በትክክለኛው ቅደም ተከተል መተረክ አለበት።
- እንቅስቃሴዎችን መጠቀም ያሻዋል።
- ቀላል ቋንቋ መጠቀም ተገቢ ነው።
- በቤቱ መለማመድ አለበት።

አስተማሪው በታሪክ ውስጥ የሚሆነውን ሁኔታ መግለጥ ያስፈልገዋል። ለምሳሌ ኢያኢሮስ ኢየሱስን ወደ ቤቱ መጥቶ ሴት ልጁን እንዲፈውስለት ስለመለመኑ የሚያስተምር ከሆነ፥ ልክ ኢያኢሮስ ያደርግ እንደነበረ ተንበርክኮ ኢየሱስ ወደ ቤቱ እንዲመጣ መለመን አለበት። በፊቱ ላይ ኃዘን መታየት አለበት። ምናልባትም ኢየሱስን እንዲመጣ በሚለምንበት ጊዜ እጆቹን ወደ ላይ ሊያነሣ ይችላል።

ስለ ዘኬዎስ የሚያስተምርም ከሆነ ዛፍ ላይ እንደሚወጣ ሰው መምሰል አለበት። ኢየሱስ ወደ ዛፉ በመጣበትም ጊዜ ስለሆነው ጉዳይ ለመናገር ዘኬዎስን በቅርንጫፎች ወደ ላይ መመልከት አለበት። ከዚያም ዘኬዎስ

በሚወርድበት ጊዜ፥ አስተማሪው እንዴት ፈጥኖ ከዛፉ እንደወረደ ያሳያል። ይህን ሁሉ በሚያደርግበት ጊዜ ታሪኩን እየተረከ ነው።

ይህ ማለት አስተማሪው ወደ ክፍል ከመምጣቱ በፊት ታሪኩን በሚገባ ማወቅ አለበት ማለት ነው። ታሪኩን መጽሐፍ ቅዱስ ሳያይ መተረክ መቻል አለበት። አስተማሪው ሁልጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማስተማር አለበት፤ ተማሪዎቹም ታሪኮቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። ነገር ግን በክፍል ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይመለከት ታሪኩን ይነግራቸዋል።

2. ጥያቄዎችና መልሶች

ጥያቄዎች የትምህርት «ቅመሞች» ናቸው። ጥያቄዎች ቀላልና ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። ዓላማቸው ተማሪዎች የሚያውቁት ምን እንደሆነ ለማወቅ፥ ፍላጎታቸውን ለማነሣሣት፥ እንዲሁም ማሰብ እንዲችሉ ማድረግ ነው።

ዓላማችን ልጆቻችን መረጃዎችን እንዲያውቁ ብቻ አይደለም፤ በሚማሩበት ጊዜ እንዲያስቡና ምክንያቶችን እንዲያውቁ እንፈልጋለን። ስለዚህም የ«አዎን» ወይም የ«አይደለም» ምላሽን የሚጠብቁ ጥያቄዎች ጥሩ ጥያቄዎች አይደሉም። ጥያቄዎች ተማሪውን ማነሣሣትና እንዲያስብ፥ ከዚያም መልሱን እንዲሰጥ የሚያደርጉ መሆን ይገባቸዋል።

ጥያቄ በምንጠይቅበት ጊዜ፥ ልጆች በሙሉ በአንድ ላይ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲጮኹ ማድረግ የለብንም። በክፍላችን ውስጥ ሥነ ሥርዓት ማስከበር አለብን። ልጆቹ መልሱን የሚያውቁት ከሆነ እጃቸውን ወደ ላይ እንሥተው ፈቃድ እንዲጠይቁና ስማቸው ተጠርቶ እስኪፈቀድላቸው ድረስ መጠበቅ እንዳለባቸው መመሪያ መስጠት አለብን። በብዙ ቦታዎች ተማሪው መልስ በሚሰጥበት ጊዜ እንዲቆም ይደረጋል። ይህ ጥሩ ልምምድ ነው። ምክንያቱም ለአስተማሪው አክብሮትን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ተማሪው እንዲንቀሳቀስ ዕድል ስለሚሰጠው ነው። ልጆች ለብዙ ጊዜያት በአንድ ነገር ላይ አተኩረው መቆየት እንደማይችሉ ማስታወስ አለብን። ስለዚህም በመካከል ዕረፍትን የሚሰጡ ድርጊቶች ትርፋማ ናቸው።

3. ሊታዩ የሚችሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

በክፍል አምስት አራተኛ ቀን ልጆች በጆሮአቸው በመስማት ብቻ እንደማይማሩ ተምረናል። በማየት፥ በመንካት፥ እጆቻቸውን በመጠቀም እና በትምህርቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግም ይማራሉ። ስለዚህም በእነዚህ ሁሉ መንገዶች እንዲማሩ አስተማሪው ምን በማድረግ ሊረዳቸው ይችላል?

ሀ. ሥዕሎች ከፍተኛ የመርጃ መሣሪያዎች ናቸው። ግልጽ እና ትክክለኛውን መልእክት የሚያስተላልፉ መሆን አለባቸው። አስተማሪው ሁሉም ልጆች ሊመለከቱ በሚችሉበት ሁኔታ በእጁ ከፍ አድርጎ ሥዕሉን ይይዛል። ከዚያም በትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ታሪኮች በሥዕሉ ላይ ያመለክታል። የመልካም እረኛና የበጎች ሥዕል የሆነ እንደሆነ እረኛው የለበሰውን ልብስ፥ በትሩንና ምርኩዙን ያሳያቸዋል። እረኛው እንዴት በጎቹን

እንደሚወድድ እና የተጎዳችውንም ትንሿን ግልገል እንዴት እንደተሸከመ ማሳየት ይችላል።

ሥዕሎችን መግዛት አይኖርባችሁም። በሌሎች መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ሥዕሎችን መገልበጥ ትችላላችሁ። "Todays English Version" የተባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ልትሥሏቸው የምትችሏቸው ጥሩ ሥዕሎች አሉት። ልጆቹ ማየት እንዲችሉ ትልልቅ ሥዕሎች ለመሆናቸው እርግጠኞች ሁኑ። በጥቁር ሰሌዳ ላይም ሥዕሎችን መሣል ትችላላችሁ። አንዳንድ ጊዜ ሕፃናቱ ራሳቸው ሥዕል ሊሥሉ ይችላሉ። ከመጽሔቶች ላይ በትምህርት ፋይላችሁ ውስጥ ሥዕሎችን በማያያዝ ለሰንበት ትምህርት እንዲጠቅሙአችሁ ልታስቀምጡአቸው ትችላላችሁ።

ለ. ካርታዎች

ተማሪዎቻችሁ አራተኛ ክፍልና ከዚያም በላይ የሆኑ እንደሆነ ካርታዎችን መረዳት ሊጀምሩ ይችላሉ። ኢየሱስ የት እንዳስተማረ በምትናገሩበት ጊዜ፥ በካርታው ላይ ልታሳዩዋቸው ትችላላችሁ። ስለ ጳውሎስ የወንጌል ስርጭት ጉዞዎች የምታስተምሩ ከሆነ በካርታው ላይ አሳዩዋቸው። ይህ ልጆቹ የት እንደሄደና በየአንዳንዱ ስፍራ ምን እንዳደረገ በአእምሮአቸው እንዲሥሉ ሊረዳቸው ይችላል።

ሐ. ጥቁር ሰሌዳዎች

ጥቁር ሰሌዳ ሊኖራችሁ ከሚገቡና ከሁሉም የተሻሉ ከሚባሉት የትምህርት መርጃዎች አንዱ ነው። እያንዳንዱ ክፍል አንድ ሰሌዳ ሊኖረው ይገባል። ጥቁር ሰሌዳ ለብዙ ነገሮች ሊያገለግል ይችላል። ሥዕሎችን መሣል ትችላላችሁ። የትምህርቱን ከባድ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ማስፈር የቃል ጥናት ጥቅሱን መጻፍ ትችላላችሁ። የምትማሩአቸውን መዝሙሮች እዚያው ላይ ጻፉአቸው። ልጆቹ የሚሰሙትን ያህል የሚያዩ ከሆነ በቶሎ ብዙ ነገሮችን ይማራሉ።

የራሳችሁን ጣውላ ወይም ጡብ እና ቀለም ገዝቶ በትክክለኛው መጠን በመቁረጥ እና ለክፍል በሚስማማ መንገድ በማዘጋጀት መቀባት ይቻላል። ጠመኔ በመባ ከሚሰበሰብ ገንዘብ ሊገዛ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጦ ለሰንበት ትምህርት አገልግሎት ሊውል ይችላል።

መ. ሌሎች ነገሮች

ምንም ይሁን ምን ስታስተምር ልጆቹ እንዲገባቸው የሚረዳ አንድ የሆነ ዕቃ ማግኘት እንደምትችል ጥርጥር የለውም። ስለ ጎልያድ የምታስተምር ከሆነ ልክ እንደ ጎልያድ ረጅም የሆነ የሸምበቆ እንጨት ልትቆረጥ ትችላለህ። ከዚያም ልጆቹ ጎልያድ ምን ያህል ረጅም እንደነበረ ማየት ይችላሉ። ወይም ደግሞ ዳዊት ያንን ትልቅ ሰው በምን እንደገደለ ለማሳየት ወንጭፍ አሳያቸው። አምስቱን ጠጠሮች አትርሳ!

ሠ. ሞዴሎች

አንድ ጎበዝ አስተማሪ ለተማሪዎቹ በሚቀጥለው ሳምንት ኖኅ ስለሠራው ትልቅ መርከብ እና እግዚአብሔር እርሱን የሚወድዱትንና በመርከቡ ውስጥ

የነበሩትን እንዴት እንዳዳናቸው እንደሚያስተምር ነገራቸው። እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ እንስሳ ጥንዱን አድኗል። ስለዚህም ተማሪዎቹ ከጭቃ፥ ከጭድ እንዲሁም ድንች እና ስንጥሮች በማድረግ እንስሶች ሠርተው ለሚቀጥለው ሰንበት እንዲያመጡ ነገራቸው። ልጆቹ በጣም ደስ ተሰኙ። የተለያዩ እንስሶች ሠርተውም አመጡ። አስተማሪው ከካርድ ማስቀመጫ ሳጥን ጀልባ የሚመስል ነገር እንደ ኖኅ መርከብ ዓይነት ሠራ። ልጆቹ የተሠሩትን እንስሶች በሙሉ እግዚአብሔር በሩን ከመዝጋቱ በፊት ወደ መርከቡ ለመግባት እንደ ተዘጋጁ አድርገው ከጠረጴዛው ላይ ከጀልባው ውስጥ በማስቀመጥ አስተማሪውን ረዱት። እነዚህ ልጆች የኖኅንና የመርከቡን ታሪክ ፈጽሞ አይረሱም!

ትምህርታችሁን በምታዘጋጁበት ጊዜ በጥንቃቄ ካሰባችሁ በቤታችሁ ባሉ ቀላል ነገሮች ለትምህርታችሁ ማስረጃ የሚሆኑ ጥሩ መግለጫዎች ማግኘት ትችላላሁ።

ጥሩ አስተማሪ ልጆች አንድን ነገር ካዩና በመማሩ ሂደት ላይ ተሳታፊዎች ከሆኑ በተሻለ ሁኔታ ሊማሩ እንደሚችሉ ይረዳል። አንድ ነገር እንዲሠሩ ስጧቸው፤ ያን ጊዜ የሰንበት ትምህርትን ይወድዳሉ። በጣም ደስ ከመሰኘታቸው የተነሣ የሰንበት ትምህርት መጀመሪያ ሰዓት ሲደርስ በሩጫ ይመጣሉ።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፡- ዕድሜያቸው ከ6–8 ለሆኑ ሕፃናት ልታስተምር የምትችላቸውን አምስት ታሪኮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጻፍ። እያንዳንዱን ታሪክ ለማስረዳት የሚጠቅምህ ቢያንስ አንድ ነገር ጻፍ። |

## ሁለተኛ ቀን፡- መምህሩና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ (2)

በማስተማር ሂደት ውስጥ ታሪክን ስለ መናገር፥ ጥያቄ እና መልስን ስለመጠቀም፥ እንዲሁም ለማስተማር የሚረዱን የተለያዩ የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎችን፥ የመገልገልን ጠቃሚነት አሁን ተምረናል። ዛሬ ስለ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊነት እንነጋገራለን። በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ ስለሚገኙ ልጆች ባሕርይ በምንነጋገርበት ጊዜ በየዕድሜ ደረጃቸው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሰሙን እንደተመለከትን ታስታውሳላችሁ። በጣም ትናንሽ የሆኑት ለሁለት ደቂቃ ያህል ይሰማሉ። እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ከ20–25 ደቂቃ ለሚሆን ረዘም ላለ ጊዜ መስማት ይችላሉ።

ይህንን ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ይህ ማለት ከተወሰነው ጊዜ በላይ ያስተማራችኋቸው እንደሆነ አሳባቸው ወደ ሌላ ቦታ ስለሚወስድ በከንቱ ትደክማላችሁ ማለት ነው። ከዚያ ወዲያ ምንም ያህል ትምህርታችሁ አስደሳች ቢሆንም እንኳን አይሰሟችሁም።

ስለዚህ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? አንዳንድ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ለዚህ ችግር መልሶች ናቸው? ነገር ግን ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ልንጠቀም እንችላለን?

### 1. እንቅስቃሴዎች

እንቅስቃሴዎች የእያንዳንዱ ትምህርት በጣም አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው።

– ደስታን ይሰጣሉ። ደስተኛ የሆነው ተማሪ ብዙ ይማራል።

– ፍላጎትን ያሳድራሉ። የተማሪዎችን አትኩሮት ካላገኘን በስተቀር ምንም ዓይነት ነገር ልናስተምራቸው አንችልም።

– ለድርጊት እንቅስቃሴ ምክንያት ይሆናሉ። በእንቅስቃሴ ውስጥ ተማሪው አካሉን ያንቀሳቅሳል፤ እናም እንቅስቃሴው እንዳበቃ ወደ ቦታው ተመልሶ በፀጥታ በስፍራው እንዲቀመጥ ይረዳዋል። የማስተማርን ሂደት ይረዳሉ (ያግዛሉ)። አፎቻቸውን፥ እጆቻቸውን፥ እግሮቻቸውን፥ ጆሮዎቻቸውንና ዓይኖቻቸውንም ጥምር እየተጠቀሙ ነው።

– ግንዛቤን ይፈትናሉ። ብዙ ትናንሽ ልጆች የተሰጣቸውን መመሪያ እንዴት እንደሚተገብሩት አያውቁም። አንድ ነገር እንዲሠሩ ስታዝዟቸው ግን መታዘዝን እንዲማሩና ትምህርቱን በተሻለ መንገድ እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

– ተማሪው የትምህርቱን እውነታ ከሕይወቱ ጋር እንዲያዛምድ ይረዳዋል።

እንቅስቃሴዎች አስተማሪው ተማሪው ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀስ ይገባዋል ብሎ በሚያስብበት ጊዜ ሁሉ ሊከናወኑ ይችላሉ።

ሀ. በምልክት የሚዘመሩ አዝማቾች

በምልክት የሚዘመሩ አዝማቾች ሁልጊዜ ለልጆች አስደሳች ናቸው። «ዚኪዮስ ትንሽ ሰው ነበር፤ አጭር ሰው ነበር» የሚለውን መዝሙር ዘምሩ። ወደ ሾላ ዛፍ ላይ እንዴት እንደወጣ፥ ኢየሱስ መጥቶ እንዴት እንዳየው፥ እንዴት ከዛፍ ላይ እንደወረደና ኢየሱስን ቤቱ እንደወሰደው በእንቅስቃሴ አሳያቸው። እንዴት እንደ አመነ እና በደስታ እንደተሞላ አሳይ። እንደነዚህ ብዙ ዓይነት በምልክት የሚዘመሩ ታሪካዊ መዝሙሮች አሉ። እነርሱን ለልጆች ማስተማር ትችላላችሁ።

ለ. መልመጃ ጥያቄዎች

በዕድሜ ከፍ ያሉ ልጆች የመልመጃ ጥያቄዎችን ይወድዳሉ። መምህሩ ጥያቄዎችን ያዘጋጃል። ይህም ምናልባት ካለፈው ሳምንት ትምህርት ውስጥ ከሆነ ለመከለስ ጥሩ መንገድ ነው። ክፍሉም በሁለት ቡድን ይከፈላል። እያንዳንዱ ቡድን ጥያቄ የመመለስ ዕድል ይኖረዋል። በትክክል ከመለሱ ለቡድናቸው ነጥብ ያስገኛሉ። መመለስ ካልቻሉ ጥያቄው ለሌላኛው ቡድን ይተላለፋል። በሚመልሱበት ጊዜ እጃቸውን በማንሣት መሆን አለበት። መልሱንም በጩኸት እና በጫጫታ መናገር የለባቸውም። ስማቸው በሚጠራበት ጊዜ ቆመው መልሱን ይናገራሉ። በዚህ መንገድ ለሁሉም ለማዳረስ ዕድል ሊኖር ይችላል። በተጨማሪም የመልመጃ ጥያቄዎች አስደሳችነት ለልጆች ጥሩ ማነቃቂያ ነው።

ሐ. ድራማ (አጭር የመድረክ ትዕይንት)

ድራማንም እንደ እንቅስቃሴ ልንጠቀምበት እንችላለን። ልጆች የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በሚገባ ከተማሩ በኋላ ለእያንዳንዳቸው የታሪኩን ገጸ ባሕርይ

በመስጠት እንደ ድራማ እንዴት አድርገው እንደሚሠሩት ልናሳያቸው እንችላለን። ይህ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ እነርሱ ቦታ መለወጥ እንዲችሉ ዕድል ለመስጠት የሚደረግ በጣም አጭር ትዕይንት ነው። ይህም ራሱ ትምህርቱን እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል። እናም የክለሳ አንድ መልክ ሊሆን ይችላል።

ረዘም ያለ ድራማ አዘጋጅተው በተለየ የእሑድ ቀን ወይም በወላጆቻቸው የስብሰባ ቀን ለጠቅላላ ቤተ ክርስቲያንም ማሳየት ይችላሉ። ድራማ ለጠቅላላው ምእመን ትልቅ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። ወላጆችም ልጆቻቸው በሚገባ ሲሠሩ ማየት ይወዳሉ።

መ. ሥዕል

ልጆች ሥዕል መሣል ይወዳሉ። ከትምህርቱ በኋላ መምህሩ ወንዶችና ሴቶችን ልጆች የትምህርቱን ዋና ክፍል የሚያሳይ ሥዕል እንዲሥሉ ሊጠይቅ ይችላል። ከዚያም ለክፍሉ በሚያሳዩበት ጊዜ ምን እንደሣሉ ማስረዳት ይችላሉ። በመጨረሻም ወደ ቤታቸው ሊወስዱትና ለወላጆቻቸው፥ ለእኅቶቻቸውና ለወንድሞቻቸው ሊያብራሩት ይችላሉ።

አስተማሪው ለክፍሉ የሚበቃ እርሳስ ወይም እስክሪብቶ ከሌለው ወይም ልጆቹ የራሳቸው የሆነ ደብተርና እርሳስ ከሌላቸው ከክፍል ወደ ውጪ ወጥቶ በእንጨት በመሬት ላይ በመሣል ምን እንደሠሩ መናገር ይቻላል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የማይጠቅሙ ይመስላሉ። ነገር ግን ልጆች አንድ የሚሠሩት ነገር ከሰጠናቸው ብዙ ሊያስታውሱ እንደሚችሉ መረዳት እንችላለን።

እንደ አስተማሪነትህ ሁሉ ይሳተፉና ይማሩም ዘንድ እነዚህን እንቅስቃሴዎች በጥንቃቄ ማቀድ ይኖርብሃል። ተማሪዎች ያለ ሥራ ዙሪያውን ከብበው የሚቆሙ ከሆነ ይህ ለእነርሱ ጊዜን እንደማባከን ነው።

ሠ. የቃል ጥናት

ተማሪዎቻችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶችን በተለይም በዕለቱ የተሰጠውን ትምህርት ሊያስረዱና እንዳይዘነጉ ሊያደርጉ የሚችሉትን ጥቅሶች እንዲማሩ የማድረግን ኃላፊነት ተነጋግረናል።

ልጆች በጣም የተከፈተ አእምሮ ስላላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቦታ ቦታ እየዘለልን ጥቅሶችን በማስተማር ችሎታቸውን መገደብ የለብንም። ምንባቦችን ሊማሩ ይችላሉ። መዝሙሮችን በሙሉ፥ ወይም በማቴዎስ 2 እና በሉቃስ 2 ላይ እንደሚገኘው ዓይነት የልደት ታሪክ ሊማሩ ይችላሉ። ይህን ደግሞ በጠቅላላው ምእመን ፊት በልደት ፕሮግራም ጊዜ በቃላቸው ሊወጡት ይችላሉ። አንዳንድ ተለቅ ያሉ ልጆች የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ መጽሐፍ ሙሉ ተምረዋል። ለምን የኤፌሶንን ወይም የፊልጵስዩስን መጽሐፍ በቃል አያጠኑም? ይህ ለቀረው የሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የሚጠቅም ትልቅ በረከትና እርዳታ ሊሆንላቸው ይችላል።

ጥቅሶችን ለመማር የሚያስችሉ ብዙ ዘዴዎች አሉ። ነገር ግን የቃል ጥናት ማዕከላዊ ዘዴ መደጋገም (ድግግሞሽ) ነው። ቃላቱ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከተጻፉ

በኋላ ከአስተማሪው ቀጥሎ ሊናገሩት ይችላሉ። አስተማሪው ጥቅሶችን በወረቀት ላይ ሊጽፍላቸው ይችላል። እናም ተማሪዎቹ በሳምንት ውስጥ በቃል ሊያጠኗቸው ይችላሉ። ልጆቹ በየቤታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ካላቸው እንደ የቤት ሥራ ሊሰጣቸው ይችላል።

ልጆች በቀላሉ ሊያጠኗቸው የሚችሏቸው ነገሮች፡-

- የዳዊት መዝሙሮች
- የአንድ መጽሐፍ ምዕራፍ ወይም መጽሐፍ በሙሉ
- የጌታችን ጸሎት
- የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስሞች
- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስሞች
- መዝሙሮች
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶች

ከላይ እንደተጠቀሱት ዓይነት ድርጊቶች ልጆች በፕሮግራሙ ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን እንዲያገኙ የተለያዩ አቀራረቦች ለመጠቀም ይረዳሉ። ልጆቹ በሙሉ ፈጽሞ ሊንቀሳቀሱ እስከ ማይችሉ ድረስ የተጠቀጠቀውን የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል አይታችኋል። በዚያ ልጆቹ ለብዙ ሰዓታት በጸጥታ እንዲቀመጡ ተደርገዋል።

አንድ እሑድ አንድ ትንሽ ልጅ ከሰንበት ትምህርት ቤት ወደ ቤቱ መጣ። እናቱም እንዲህ አለችው፡- «ታገሡ፥ ዛሬ በሰንበት ትምህርት ቤት ምን ተማርህ?»

እርሱም ለትንሽ ጊዜ ካሰበ በኋላ «ምንም» ብሎ መለሰ።

እርሷም በመደነቅ «ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ሄደ ምንም አልተማርሁም ነው የምትለኝ?» አለችው።

እንደገና ለጥቂት ጊዜ አሰብ አደረገና «ተደጋግሞ ሲነገር የሰማሁት አንድ ነገር ቢኖር ‹ቁጭ በሉ! ጸጥ በሉ› የሚለውን ቃል ነው» አላት።

የዚያ የሰንበት ትምህርት ቤት ችግር ምን ነበር? ሊሆን የሚችለው ምናልባት አስተማሪው ቁጥራቸው ከመጠን ያለፈ ልጆች በአንድ ክፍል ውስጥ ነበሩት ማለት ነው። ትምህርቱን የሚስብና የሚያጓጓ እንዳላደረገው ጥርጥር የለንም። ምናልባትም በምልክት የሚዘመሩ መዝሙሮችን አላዘመረም። ወይም ደግሞ የክፍሉን ጸጥታ ማስከበር ስላልቻለ በክፍል ውስጥ ብዙ ጩኸትና ንግግር ነበር። የዚህ ሁሉ ውጤት የሆነው የትንሹ ልጅ ምንም ያለመማር ነበር። የሰንበት ትምህርት ቤትን አስደሳችና የሚስብ የሚያጓጓም ለማድረግ የምንችለውን ጥረት ማሳየት አለብን። የሰንበት ትምህርት ቤት ልጆች የወንጌልን ድንቅ እውነቶች የሚማሩበት ቦታ ነው። ይህ ቦታ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አምነው ድነው በክርስትና ሕይወታቸው የሚያድጉበት ቦታ መሆን አለበት። እስቲ የማስተማር ብቃታችንን አሳድገን ልጆች የሰንበት ትምህርት ቤትን ሊርቁት የማይችሉ ስፍራ እናድርገው።

3ኛ ጥያቄ፡- የምታውቃቸውንና ልጆች ሊማሩዋቸው የሚችሏቸውን አራት አዝማቾች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ። ያለ አንዳች ችግር ልትዘምረው እስከምትችል ድረስ በምልክት እንዴት እንደሚዘምሩ ተለማመድ።

4ኛ ጥያቄ፡-ከላይ እንደተመለከተው ዓይነት ሌሎችን አራት ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ጻፍ።

ሦስተኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት ሰዓት አደረጃጀት

ስለ ሰንበት ትምህርት አዘገጃጀት እና ትምህርቶቻችንን የሚስቡ ለማድረግ በእንዴት ያለ ሁኔታ ማስተማር እንደሚገባ በሰፊው ተነጋግረናል። በምናስተምርበት ጊዜ ዓላማችን ተማሪዎቻችን እንዲማሩ የሚቻለንን ማንኛውንም ነገር ሁሉ ማድረግ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ በሕይወታቸው ውስጥ ለውጥንና ዕድገትን እንድናይ እንመኛለን።

አሁን በዚህ ትምህርት ከልጆች ጋር የሚኖረንን ጊዜ ሁሉ በሚገባ እንድንጠቀምበት ጊዜያችንን እንዴት አድርገን እንደምናደራጅ እንነጋገራለን።

የሚከተለው ለሰንበት ትምህርት ሰዓት የተሰጠ የጊዜ ሠንጠረዥ ነው።

3:00 -3:20 ልጆች ሁሉ በአንድነት ሆነው የመክፈቻ ክፍለ ጊዜ

3:20 - 3:50 አስተማሪው የዕለቱን ትምህርት የሚያስተምርበት ጊዜ ሲሆን ተማሪዎች እንደ ዕድሜያቸውና እንደየችሎታቸው በየክፍሉ ይከፋፈላሉ።

3:50- 4:00 የመዝጊያ ጊዜ

ይህ ለሰንበት ትምህርት በጣም አጭር ጊዜ ነው። ነገር ግን ይህ ለሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ በሌለበት ከጠዋት የአምልኮ ጊዜ በፊት የሚደርግ ሲሆን ጥሩ ይሆን ይሆናል።

የሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜን ልታስረዝሙት ትችሉ ይሆናል። ልታስታውሱ የሚገባችሁ ግን በሚገባ ካልታቀደና በየመሐሉ ክፍት ጊዜ ካለበት የሁለት ሰዓት ጊዜ ይልቅ ልጆቻችሁ በእርግጠኝነት በታቀደ የአንድ ሰዓት ጊዜ በሚገባ ይማራሉ። ልጆች ቁጭ ብሎ መጠበቁን አይወዱትም። ብዙ ጊዜ የሚቅበጠበጡት፥ መሳሳቅ የሚጀምሩት እና ወሬ የሚያወሩት እንዲያውም የሚደባደቡት በዚህ ጊዜ ነው። ስለዚህም ረብሻውን የመፍጠሩ ስሕተት በእውነተኛ መንገድ ካየነው የአስተማሪው እንጂ የልጆቹ አይደለም።

1. የመክፈቻ ጊዜ

የመጀመሪያዎቹ አሥራ አምስትና ሃያ ደቂቃዎች እንደሚከተለው ሊሆኑ ይችላሉ።

ሀ) <u>አዝማቾች</u>፡- ከዕለቱ የትምህርት ዓላማ ጋር የሚሄዱ አዝማቾችን ዘምሩ። ምልክቶችን ተጠቀሙ። አዝማቹን ከሦስት ወይም ከአራት ጊዜ በላይ በፍጹም አትዘምሩ። የምንዘምረው ለእግዚአብሔር ክብር ስለሆነ መጀመሪያ ላይ ገና ስንዘምር እርሱ ይሰማናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን አሕዛብ ከንቱ የሆነ ድግግሞሽ ያደርጋሉ። እንደ እግዚአብሔር

ልጆች ደግመን ደጋግመን መዘመር አያስፈልገንም። እንደዚያ ዓይነቱ ስሜትን ለማሞቅ ብቻ ስለሆነ ጌታን ለማምለክ ጤናማ መንገድ አይደለም።

ለ. <u>መባን መሰብሰብ</u>፡- ይህ መባ ለመሰብሰብ ጥሩ ጊዜ ነው። ልጆች ገንዘባቸውን ይዘው ለመቆየት ይከብዳቸዋል። እናም ይጥሉትና ይጠፋል ወይም ይጫወቱበታል። ከልጆቹ መካከል ተለቅ ያሉት መባውን ይሰብስቡ። ይህ ለእነርሱ መልካም ልምምድ ነው። በኋላ ትልቅ ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይረዳሉ።

ሐ. <u>የመክፈቻ ጸሎት</u>፡- ልጆቹ የጸሎት ጥያቄ ካላቸው ይናገሩ። ከዚያም አስተማሪው ወይም ሌላ ሽማግሌ በጸሎት ሊመራ ይችላል። መባ ከተሰበሰበ ይህ ጊዜ እግዚአብሔር እንዲባርከውና ለመንግሥቱ ጥቅም እንዲያውለው ጌታን መጠየቂያ ጊዜም ይሆናል።

መ. <u>አጭር ክለሳ</u>፡- ሁሉም ክፍሎች የሚማሩት ትምህርት አንድ ዓይነት ከሆነ ክለሳ ሁሉም በአንድነት ባሉበት ጉባዔ ላይ ሊደረግ ይችላል። ይህ በመልመጃ ጥያቄ መልክ ወይም ማንም ሰው ሊመልስ እንዲችል ከክለሳ ጥያቄዎች ወይም ደግሞ ብዙ ልጆች ወደፊት እየመጡ እያንዳንዳቸው ባለፈው ሳምንት ከተማሩት አንዱን ክፍል እንዲናገሩ በማድረግ ሊከናወን ይችላል።

ሠ. <u>ማስታወቂያዎች</u>፡- ልጆችን የሚመለከቱ ሁኔታዎች ሊነገሩ ይቻላል።

ረ. <u>አስፈላጊ ከሆነ አዝማቾች እንደገና መዘመር</u>፡- ከዚያም ልጆቹ ወደየክፍላቸው እንዲሄዱ ማድረግ።

2. በየክፍሉ መከፋፈል

ልጆችን እንደየዕድሜያቸውና እንደየችሎታቸው ለማስተማር በየክፍሎች መከፋፈል በጣም አስፈላጊ ነው። ዕድሜያቸው ከ4-14 ዓመት የሚደርሱ ልጆች ቁጥር ከ100 በታች ከሆነ በሚከተለው መንገድ ልትከፍሉዋቸው ትችላላችሁ።

ሀ. 4 እና 5 ዓመት ሁለት አስተማሪዎችና አንድ ረዳት

ለ. ከ6-8 ዓመት ሁለት አስተማሪዎችና አንድ ረዳት

ሐ. ከ9-11 ዓመት ሁለት አስተማሪዎች

ሠ. ከ12-14 ዓመት ሁለት አስተማሪዎች

በእያንዳንዱ ክፍል ከአንድ በላይ ጎልማሳ እንዲገኝ ያስፈለገባቸው አያሌ ምክንያቶች አሉ።

1. አንዱ አስተማሪ ጥሩ የሆነ ትምህርት አዘጋጅቶ ሲያስተምር ሌላኛው የቃል ጥናት ጥቅስ ያስተምራል፤ አንድ ዓይነት ድርጊታዊ እንቅስቃሴ ያዘጋጃል። አዳዲስ አዝማቾች ያስተምራል፥ ወዘተ...። ይህ ማለት በመቀራረብ መሥራትና ትምህርቱን አብረው ማቀድ አለባቸው ማለት ነው።

2. አንደኛው አስተማሪ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ካለበት ሌላኛው ማስተማር ይችላል። ይህ ለተማሪዎቹ ቀጣይነትን ይሰጣቸዋል። የሚያውቋቸው አስተማሪዎች ሲኖሯቸው እንግድነት አይሰማቸውም።

3. ለትንንሾቹ ልጆች ጸጥ እንዲሉና ይከታተሉ ዘንድ ረዳት ቢኖር ጥሩ ነው። ይኸኛውም ሰው ምናልባት የሰንበት ትምህርት ሥልጠና ያልወሰደ ከሆነ እርሱ ራሱ ሊማርና ለወደፊቱ ጥሩ አስተማሪ ሊሆን ይችላል።

ከ100 በላይ ተማሪዎች ካሏችሁ፥ ክፍሎችን መጨምር ይኖርባችኋል። በመሆኑም በእያንዳንዱ ክፍል ከ20 ወይም 25 ልጆች በላይ አይኖሩም ማለት ነው። የተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ በሆነ ቁጥር እያንዳንዱ ልጅ የተሻለ ይማራል። እንዲሁም እያንዳንዱን ተማሪ ለማወቅ፥ ለእያንዳንዱ ተማሪ ለመጸለይ፥ እንዲሁም ትምህርቱን ከተማሪው ፍላጎት አንጻር ማስተካከል ለአስተማሪው ይቀለዋል።

ለእነዚህ ሁሉ የተለያዩ የዕድሜ ክልሎች በቤተ ክርስቲያን በቂ ቦታ ባይኖር ምን ሊደረግ ይችላል? በበጋ ወቅት፥ ክፍሎችን በዛፍ ሥር በጥላ ውስጥ ማካሄድ ይቀላል። ለመክፈቻ ክፍለ ጊዜው ተማሪዎቹ በሙሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰበሰቡ ይችላሉ። ከዚያም ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ወደየክፍሎቻቸው ይሄዳሉ። በክረምት ወራት የበለጠ አስቸጋሪ ነው። ምናልባት ተማሪዎች በቤተ ክርስቲያኑ ጥጎች ወደየግድግዳው ዞረው ተቀምጠው ማስተማር ይቻል ይሆናል። ልጆቹ እናንተን ከብበው በሚቀመጡበት ሁኔታ አግዳሚ ወንበሮቹን ማዘጋጀት ሌሎቹን ክፍሎች ሳታዩና ሳትረብሹ ለማስተማር ይረዳል። ከዚያም አስተማሪው ሌሎችን እንዳይረብሽ ድምፁን ዝቅ ማድረግ አለበት። እንዲሁም በሌሎች ክፍሎች ያለውን ትምህርት ስለሚያሰናክል በክፍል ውስጥ መዘመር ያስቸግራል።

አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፤ «ፈቃደኝነት ካለ፥ መውጪያ መንገድ አለ»። ለእያንዳንዱ ክፍል የማስተማሪያ ቦታ ለማግኘት የፈጠራ ችሎታችንን መጠቀም አለብን። ጌታን ጥበብ ከጠየቅነው በልግስና እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል።

3. ትምህርቱ

የትምህርቱን ደረጃዎች በምዕራፍ ሰባት በሚገባ ሠርተናል። በዚህ ጊዜ በጥንቃቄ ያዘጋጀኸውን ትምህርት ታስተምራለህ። ትምህርትህ ቢያንስ 30 ደቂቃ መውሰድ አለበት። ልጆች የዚያን ያህል ጊዜ መታገሥ ስለማይችሉ ሰውነታቸውን በተለያየ ጊዜ እንዲያንቀሳቅሱ አድርገህ ትምህርትህን ማቀድ አለብህ። ይህ የቃል ጥናት ጥቅሱን ለማጥናት በመነሣት ወይም ዓላማህን ለመደገፍ የሚችል መዝሙር በመዘመር ሊደረግ ይችላል።

4. የመዝጊያ ጊዜ

ይህ የመጨረሻ ማስታወቂያ ካለ፥ ወይም ጊዜ ካለ የመጨረሻ አዝማች የሚዘመርበትና በጸሎት የሚዘጋበት በጣም አጭር ጊዜ ነው። ከዚያም ልጆቹ ወጥተው ዋናው አምልኮ ቦታ ወይም ወደ ቤታቸው፥ እንዲሄዱ ይደረጋል። ይህም በወላጆቻቸው ፈቃድ የሚወሰን ነው።

5ኛ ጥያቄ፦ ስለ ቤተ ክርስቲያንህና ስለሚመጡት ልጆች አስብ። በቤተ ክርስቲያንህ የሰንበት ትምህርት ቤት አለን? ስንት ክፍሎች አሉ? እያንዳንዱ አስተማሪ በተለየ ምክንያት ወደ ውጪ መሄድ ካለበት ሊተካው የሚችል ሰው አለን? የትንንሾቹን ልጆች ክፍል በተመለከተ ሁለት አስተማሪና አንድ ረዳት ለእያንዳንዱ ክፍል መኖር ያለበት ለምንድን ነው?

## አራተኛ ቀን፦ የሰንበት ትምህርትን ማደራጀት

6ኛ ጥያቄ፦ ስለ ሰንበት ትምህርት የተሰጡትን እነዚህን ትምህርቶች እና ልጆችን ስለማስተማር ካጠናህ ዘንድ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሰንበት ትምህርት ቤት እንዴት ይደራጃል ብለህ ታስባለህ? በሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ሽማግሌዎች የሚኖራቸው ቦታ ምንድን ነው? ፕሮግራሙን የሚያቀነባብሩትና የሚመሩት እነርሱ ናቸውን? ካልሆኑ ማን ነው ማድረግ ያለበት? በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለልጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማደራጀትና ለመምራት ብቃት ያለው አንድ ሰው ማሰብ ትችላለህን? ይህን አንተ ሊኖርህ እንደሚገባ አገልግሎት ማሰብ ይገባህ ይሆንን?

የሰንበት ትምህርት ቤት የተሳካ እንዲሆን፥ በሚገባ መደራጀት አለበት። የመጀመሪያው አስፈላጊ ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆችን ለማስተማር ሸክም ሊኖራቸው ይገባል። እንደሚያስፈልግ ካለሰቡ ምንም መሥራት አይቻልም። አሁን አንተ ይህን ኮርስ እየወሰድህ ነው። ለሽማግሌዎች፥ ለመጋቢዎችና ለወንጌላውያን ስለ ልጆች ስላለህ ሸክም ልትነግራቸው ይገባል። ልጆችን ለማስተማር ስላለህ ሸክም ለመናገር ከምዕራፍ ሁለትና አምስት ያሉትን አሳቦች መጠቀም ትችላለህ።

1. ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ስለ አስፈላጊነቱ ተነጋገር።

በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ፕሮግራም ውጤት ያለውና የሚጸና እንዲሆን ከመሪዎች ድጋፍ ማግኘት አለበት። ለልጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን አስፈላጊነት አስረዳቸው። እንደዚያ ዓይነት ፕሮግራም ሊጀመር የሚችልበትን መንገድ በተመለከተ አሳብ ስጣቸው። የዚህ ምዕራፍ የቀረው ክፍል ይረዳህ ይሆናል። እነርሱም ተጨማሪ የሚያቀርቡት አሳብ ይኖራል። ልጆችን ለማስተማር የተዘጋጀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መመሪያ አሳያቸው። የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎችን ለማሠልጠን የሚያገለግለውን የማሠልጠኛ መጽሐፍ አሳያቸው። ፕሮግራሙን ለማስጀመር የሚቻልህን ሁሉ እንደምታደርግ ንገራቸው።

- የፕሮግራሙ ኃላፊ የሚሆን ሰው እንዲመርጡ ጠይቃቸው። የኃላፊው ተጠሪነት ለእነርሱ ይሆንና ሪፖርት ያቀርብላቸዋል።

- አስተማሪዎችን በመፈለግ እርዳቸው።

- ፕሮግራሙ በቤተ ክርስቲያን አባላትና በልጆች እንዲታወቅ አድርግ።

- በቤተ ክርስቲያን በጀት ለፕሮግራሙ የሚያስፈልግ ወጪ እንዲያዝ አድርግ። አቅርቦቶችን ለመግዛት ገንዘብ ያስፈልጋል።

- ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና ለሚመጡት ልጆች ጸልይ።

2. የሰንበት ትምህርት ቤት አስተባባሪ የሚሆነውን ሰው ምረጥ።

ይህ በጣም ዋነኛ ቦታ ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሕፃናትን እንዲያስተምሯቸውና ወደ እርሱ ከመምጣት እንዳይከለክሏቸው ነግሯቸዋል። እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት ዋነኛ ነው። ይህንን ቦታ የሚሸፍነው ሰው በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በቤተ ክርስቲያን በሚሰጠው የልጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሐከል መካከለኛ አገናኝ ነው። ስለዚህም የዚህ ፕሮግራም ኃላፊ የሚሆነውን ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መምረጣቸው አስፈላጊ ነው። ሰውዬው ራሱ ሽማግሌ ቢሆን ጥሩ ሊሆን ይችላል።

3. የሰንበት ትምህርት ቤት አስተባባሪ ኃላፊነቶች

ሀ. ጠንካራ ክርስቲያኖች እንዲሆኑና የተሻሉ አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ ሳምንታዊ የአስተማሪዎች ስብሰባ ማዘጋጀት። እንዲሁም ሳምንታዊ ትምህርቶቻቸውን ሲያዘጋጁ ሊረዳቸው ይችላል።

ለ. አስተማሪዎች የልጆችን ቤት እንዲጎበኙና ተጨማሪ ልጆች ወደ ሰንበት ትምህርት እንዲጋብዙ ያበረታታል።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን ለመከፈት በጊዜ ይመጣል።

መ. የመክፈቻውን ክፍለ ጊዜ ይመራል፤ ወይም አንድ ሰው ቀደም ብሎ እንዲያደርገው ይመርጣል።

ሠ. ልጆችን ወደየክፍላቸው ይመራል፤ እናም ክፍሎች በየዕድሜው እንዲከፋፈሉ ይረዳል።

ረ. ቋሚ አስተማሪዎች ያልተገኙ ከሆነ ተክቶ ያስተምራል።

ሰ. የትምህርት መመሪያዎች እንዲደርሱ ያዝዛል፥ ያከፋፍላል።

ሸ. የስም ጥሪ፥ የመባ እና የእምነት ምስክርነቶች በተገቢው መንገድ እንዲመዘገቡ ያዘጋጃል።

ቀ. የሰንበት ትምህርት ቤቱን እድገት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያሳውቃል።

በ. በቤተ ክርስቲያን ስለ ሰንበት ትምህርት ማስታወቂያ በመናገር ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲልኩ ያበረታታል።

4. የሰንበት ትምህርት ቤት አስተባባሪ መመዘኛ

ሀ. ዳግመኛ የተወለደ እና ምሳሌያዊ ሕይወት ያለው ክርስቲያን መሆን አለበት።

ለ. የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አለበት።

ሐ. አዋቂዎችንም ሆነ ልጆችን የማስተማር ችሎታ ሊኖረው ይገባል። የማስተማር ሥልጠና የወሰደ መሆን አለበት። ይህም ሌሎችን እንዲያሠለጥን ነው።

መ. ልጆችን የሚወድድ እና ስለ እነርሱ ሸክም ያለው መሆን አለበት። እርሱ ራሱ አባት ሆኖ ቢገኝ ጥሩ ነው።

ሠ. ታማኝና እምነት የሚጣልበት መሆንና ለዚህ አስፈላጊ ሥራ ጊዜውን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት።

የልጆችን የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት መሪ ኃላፊነቶችንና መመዘኛዎችን እንዳየነው ይህን ፕሮግራም በመምራት ውስጥ ብዙ ሥራ እንዳለ እንገነዘባለን። ስለዚህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሥራ የሌለው ሰው መሆን አለበት። እንዲሁም ለፕሮግራሙ በቂ ሰዓት ለመስጠት ፈቃደኛ ሰው መሆን አለበት። ፕሮግራሙ በሚገባ እንዲካሄድ ፕሮግራሙን ማስተባበርና አስተማሪዎችን መቆጣጠር አለበት። ፕሮግራሙ የሚበላሸው በቋሚነት፥ በታማኝነት ባለመሆን ማቀድ እና ማስተባበር እንዲሁም አስፈላጊውን ጊዜ ባለመስጠት ነው።

5. አስተማሪዎችን መፈለግ

የአስተማሪዎች መመዘኛ የአስተባባሪው ዓይነት መሆን አለበት። በተጨማሪ በየሳምንቱ ለማስተማር ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። ልጆችን የሚወድና የሚታገሡአቸው መሆን አለባቸው። የልጆችን ስም በክፍላቸው ማወቅ እና በየቤታቸው መጎብኘት ይኖርባቸዋል።

አስተማሪዎች የትምህርቱን መጻሕፍት እንዴት መጠቀም እንደሚችሉና ሥራቸውን በሚገባ እንዲሠሩ ሥልጠና ሊሰጣቸው ያሻል። ይህ በአስተማሪዎች ስብሰባ ወይም በተለየ የሴሚናር ጊዜ ሊደረግ ይቻላል።

6. የሰንበት ትምህርት ለማካሄድ ጥሩው ጊዜ

የእሑድ ትምህርት ቤት ወይም የሰንበት ትምህርት ቤት ብለነዋል። ምንም ተብሎ ቢጠራ ስሙ ችግር የለውም። ዋናው ነገር ልጆቹ መማራቸው ነው። የሰንበት ትምህርት ሊካሄድ የሚችልበትን ጊዜ ማቀድ አለባችሁ። እሑድ ቀን ብቻ መሆን የለበትም። ሽማግሌዎች ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመጡ ይችላሉ ብለው በሚያስቡት በማንኛውም ቀን ሊሆን ይችላል። እርግጥ ነው ከቅዳሜ በስተቀር በሳምንቱ ቀናት በትምህርት ቤት ናቸው። ብዙ ጊዜ ቅዳሜ የገበያ ቀን ስለሆነ በጠዋት ካላደረግነው በስተቀር በጣም ቀላል አይሆንም።

ብዙ ጊዜ የሚመቸው ቀን እሑድ ነው። ጠዋት ከአምልኮ በፊት ወይም በኋላ ሊሆን ይችላል። እሑድ ከሰዓት በኋላም ደግሞ ሊሆን ይችላል። ጊዜው አሳሳቢ አይሆንም። ዋናው ነገር ልጆቹ መማራቸው ነው። ለሁሉም ሰው፥ ለልጆቹ፥ ለወላጆቻቸው እንዲሁም ለአስተማሪዎች የሚስማማ ጊዜ መሆን አለበት።

7. በክፍል ውስጥ ሥርዓት እንዴት እናስጠብቃለን?

በመደጋገም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ ነው። ይህን ለእስራኤል ልጆች በሰጠው መመሪያ ላይ አሳይቶአል። በመገናኛቸው ድንኳን እንዴት አድርገው እርሱን እንደሚያመልኩት፥ በምን አኳኋን ድንኳኑን እንደሚያጓጉዙ፥ እያንዳንዱን ሥራ ማን እንደሚያከናውን እርሱ ራሱ እያንዳንዱን ትንንሽ ነገር ሁሉ አደራጅቷል። እንዲሁም አቀናጅቷል። እንዴት እንደሚያመልኩትና መሥዋዕትን እንደሚያመጡለት፥ የሚያመጡት መሥዋዕት ምን ዓይነት እንደሆነ፥ ማን እንደሚያቀርብ፥ ሥጋው ወይም ምግቡ እንዴት እንደሚቆራረጥ ነግሯቸዋል፤ እያንዳንዱ ዝርዝር ነገር የተሠራ ነበር።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ «ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን» ይላል (1ኛ ቆሮ. 14:40)።

አንድን የመማሪያ ክፍል ከሥርዓት ውጪ የሚያደርጉ መንሥዔዎች ምንድን ናቸው? ከዚህ በታች ሦስት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል። ሀ) ያልተስተካከለ የመማሪያ ክፍል፥ ለ) ያልተስተካከለ አስተማሪ፥ ሐ) ያልተስተካከሉ ተማሪዎች። በመጀመሪያ ከሥርዓት ውጪ የመሆንን መንሥዔ ካወቅን የሚቀጥለው ደረጃ እርማት መውሰድና ሥርዓትን ማምጣት ነው። ስለዚህም ቀጥሎ አንዳንድ አሳቦች ተሰጥተዋል።

ሀ) የመማሪያ ክፍሉ በጥራትና በንጽሕና ይጠበቅ። ተማሪዎች ተመቻችተው እንዲቀመጡና አስተማሪውንና የጥቁር ሰሌዳውን እንዲመለከቱ ዕቃዎች በሥርዓት ተደርድረው መቀመጥ አለባቸው። አርፍደው የሚመጡ ልጆች ወደፊት አልፈው በተማሪዎችና በአስተማሪው ፊት በመሄድ እንዳይረብሹና ሥርዓት እንዳያውኩ በጸጥታ ገብተው በኋላ እንዲቀመጡ መቀመጫዎች በሚገባ መደርደር አለባቸው። ቤቱ የተጠረገና ንጹሕ መሆን አለበት። ምንጣፎች ትናንሽ መቀመጫዎች ወይም አግዳሚ ወንበሮች ለሕፃናት በጣም ጥሩ ናቸው። ልጆች እንቅልፍ እንዳይወስዳቸውና ንጹሕ አየር እንዲዘዋወር መስኮቶች ክፍት ይሁኑ።

ለ. አስተማሪውም ደግሞ የተስተካከለና ንጹሕ መሆን አለበት። ልብሱን በንጽሕና የሚጠብቅና ፀጉሩንም የሚያበጥር ሊሆን ይገባል። አትኩሮትን ወደ ራስህ ለመሳብ አትልበስ።

የአስተማሪውን ትዕግሥት የሚፈትኑ ብዙ ነገሮች አሉ። ሌሎችን ለመቆጣጠር እንዲችል ያለማቋረጥ በጽናት ራሱን መቆጣጠር መቻል አለበት። አስተማሪው በሚገባ የተዘጋጀ መሆን አለበት። ይህም በሚያስተምርበት ጊዜ በራስ መተማመንንና ዕረፍትን ይሰጠዋል። አስተማሪው በሚገባ ያልተዘጋጀ ከሆነ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ፍላጎት በማጣት መጫወትና ማውራት ይጀምራሉ።

ሐ) አስተማሪው ተማሪዎቹን ማወቅ አለበት።

በክፍል ውስጥ ረብሻ እንዲፈጠር የሚያደርጉ የተወሰኑ ተማሪዎች አሉ። እነርሱም፡—

1. ግድ የለሹ ተማሪ፡— ጫጫታ ስለሚወድ ሌሎችን ይረብሻል። ይህንንም የሚያደርገው መጥፎ ልጅ ለመሆን ሳይሆን ግድየለሽ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ጊዜ ወስዶ እንዲህ ዓይነቱን ተማሪ ማነጋገር እንዲለወጥ ለማድረግ በቂ ነው።

2. ቁንጥንጥ ተማሪ፡— አንዳንድ ተማሪዎች በተፈጥሮአቸው አርፈው መቀመጥ አይችሉም። ሳያቋርጡ ይንቀሳቀሳሉ። አንድ የሚሠራው ነገር ስጡት። ሥዕሉን ለክፍሉ ልጆች ለማሳየት ይዞ እንዲቆም አድርጉት ወይም ሠሌዳውን ይጥረግ። ሰውነቱን ማንቀሳቀስ ስለሚያስፈልገው አንድ የሚሠራው ነገር ስጡት። እንዲሁም በምልክት የሚዘመሩ አዝማቾችን ተጠቀሙ። የክፍሉ ተማሪዎች ቆመው የቃል ጥናት እንዲያጠኑ ይሁን። ቁንጥንጥ የሆኑትን ለመርዳት የተለያዩ ነገሮችን አድርጉ።

3. ራስ ወዳድ ተማሪ፡- ፊቱን በመለወጥ፥ ቀልድ በማውራት፥ አስቂኝ ነገር ለመሥራት በመሞከር እና ሁሉንም ዓይነት ነገር በማድረግ ሌሎች ልጆች በሙሉ ወደ እርሱ እንዲመለከቱና እንዲስቁ ለማድረግ ብዙ ይሞክራል። ሌሎች ልጆች የሚከተሏቸውን ሕግጋትና ደንቦች ለመታዘዝ መማር አለበት። በተማሪዎቹ ፊት ቆሞ አዝማች እንዲያዘምር አድርጉት። ያለፈውን ሳምንት ትምህርት በድርጊት እንዲገልጽ ወይም በጸሎት እንዲመራ ይደረግ። ይህ እርሱ በሌሎች እንዲታይ ዕድል ሲሰጠው ራሱ ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችን ይማራል።

4. ችግር ፈጣሪው ተማሪ፡- ወደ ክፍል የሚመጣው ችግር ለመፍጠር ነው። ይህንንም ወደ ክፍል ከመምጣቱ በፊት ዐቅዶ ይመጣል። እርሱን ማነጋገር አለባችሁ። በዚያው ከቀጠለም ምናልባት ከክፍል ማስወጣት ይኖርባችሁ ይሆናል። ወደዚህ ውሳኔ ከመድረሳችሁ በፊት በሳምንቱ ቀናት ውስጥ ወዳጅነት የተሞላ ግንኙነት ከእርሱ ጋር ለማድረግ ሞክሩ።

* ቤቱን ልትጎበኙ ትችላላችሁ።

* ደስ የሚሉት ነገሮች ምን እንደሆኑ ፈልጉ።

* በራስ መተማመኑን ከእርሱ ለማስወገድ ሞክሩ።

* እናንተ እንደምትወዱት፥ እግዚአብሔርም እንደሚወደው እና ልጁ እንዲሆን እንደሚፈልግ ንገሩት። እግዚአብሔር ሊለውጠው እንደሚችል ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አሳዩት።

ሥነ ሥርዓት በክፍል ውስጥ መጠበቅ አለበት። ከልጆች ጋር በምትሠሩበት ጊዜ እንዴት አድርጋችሁ እንደምትቆጣጠሩዋቸው እየተማራችሁ ትመጣላችሁ። የሰንበት ትምህርት ቤቱ በሚገባ የማይካሄድ ከሆነና ቁጥጥር ከሌለበት ተማሪዎቹ (ልጆቹ) ለጌታ እንዴት እንደሚኖሩ ከመማር ይልቅ ነዝናዞችና ረባሾች መሆንን ይማራሉ። ልጆች በእውነት እንዲማሩና ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያድጉ ጥሩ የሰንበት ትምህርት ቤት እንዲኖር ማድረግ የእናንተ ኃላፊነት ነው። ወላጆች ወደዚህ ዓይነቱ የሰንበት ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን መላክ ደስ ያሰኛቸዋል።

---

7ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ለመረበሽ ስለሚመጡ ልጆች አስቡ። እነዚህን ልጆች ለመርዳት ብዙ አሳቦችን ጻፉ። እግዚአብሔር የሚወድዳቸው ከሆነ እኛም ልንወዳቸውና ለክርስቶስ ልንማርካቸው መፈለግ አለብን።

---

አምስተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ስብሰባ ክለሳና ዝግጅት አድርግ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለጥሞና ጊዜ በሚገባ የተዘጋጀ አጭር ትምህርት ሌላ ተማሪ አዘጋጅቶ እንዲያመጣ አድርግ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ልጆችን በማስተማር ጊዜ የምንጠቀምባቸውን ሦስት ዘዴዎች ተነጋገሩባቸው። እነዚህ ዘዴዎች በንግግር ብቻ ከማስተማር የተሻሉ የሆኑት ለምንድን ነው?
2. የሰንበት ትምህርት ቤት ድርጊቶችን ማቀድ እና እነርሱን የመጠቀም ዋጋ ምንድን ነው?
3. ስለ ሰንበት ትምህርት ቤት አስተባባሪ ተነጋገሩ። በቤተ ክርስቲያናችሁ ይህንን ሥራ ሊወስድ ስለሚችል ሰው ተወያዩ። ምናልባት አንተ ትሆናለህ። አስተባባሪ ለመሆን ፈቃደኛ ትሆናለህን?

# ትምህርት አሥራ ሦስት

# የሰንበት ትምህርት ቤትን ማደራጀት

## አንደኛ ቀን፡- የሰንበት ትምህርት መምህራንን ማሠልጠን

1ኛ ጥያቄ፡- ሁልጊዜ የሚያጋጥመን አንዱ አንገብጋቢ ጥያቄ እንዴት የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን ማግኘት እንችላለን የሚለው ነው። ልጆችን ለማስተማርና በእውነት ለመውደድ የሚፈልጉ አስተማሪዎችን ለማግኘት ምን ዓይነት አሳብ ይኖርሃል? ቤተ ክርስቲያን ለሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን እንዴት ማግኘት እንዳለበት ምን ዓይነት አሳብ ትሰጣለህ? እነዚህ መምህራን በምን ዓይነት መንገድ ለትምህርቱ መሠልጠን ይችላሉ?

ለማንኛውም የመንፈሳዊ ሥራ ዋነኛ መሠረቱ ጸሎት ነው። ቤተ ክርስቲያን ማድረግ የሚገባት የመጀመሪያው ነገር መጸለይ ነው። በሚጸልዩበትና ከእግዚአብሔር ምሪት በሚጠይቁበት ወቅት ልጆቻቸው መማር እንዳለባቸው በእርግጥ የሚያምኑ ከሆነ ለማስተማር ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች እግዚአብሔር ያዘጋጃል። በተጨማሪም የማሠልጠኛ ትምህርቶችን በማቀድና በማዘጋጀት ውስጥ ምሪትን ይሰጣል።

ለሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሊዘጋጅ የሚችል ሁለት ዓይነት ሥልጠና አለ። እነዚህም በተግባር ላይ የሚሰጥ ሥልጠና እና የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሥልጠና ሴሚናሮች ናቸው።

1. በተግባር ላይ የሚሰጥ ሥልጠና

የሰንበት ትምህርት የበላይ ኃላፊ ሆኖ የሚሠራው ሰው የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን ለማሠልጠን ከሁሉ በላቀ ትክክለኛው ሰው ነው። ከዚህ ቀደም ብለን በተመለከትነው ትምህርት የተሰጠውን ዝርዝር በሚገባ ካሟላ ራሱ የሠለጠነ ሰው ይሆናል። በመሆኑም አዳዲስ አስተማሪዎችን የሚያሠለጥን ይሆናል።

በተግባር ላይ ሥልጠናን ለመስጠት በጣም ጥሩ ቦታ ሳምንታዊው የአስተማሪዎች ስብሰባ ነው። በዚህ ስብሰባ ጊዜ ልታደርገው የሚገባ ከሁሉ የተሻለ ነገር ለሚመጣው እሑድ ልታስተምረው የተዘጋጀህበትን ነገር በአንድ ላይ ማጥናት ነው። ይህንንም መሪው ትምህርቱን በሙሉ ልክ ተማሪዎችን

እንደሚያስተምር አድርጎ ይሰጣል። በተለይ በመጀመሪያ አካባቢ አስተማሪዎች በቂ ልምድ በሌላቸው ጊዜ ትምህርቱ በተገቢ ሁኔታ እንደሚሰጥ የማረጋገጫ መንገድ ይሆናል። በኋላም አንድ አስተማሪ ተመርጦ በውይይት መልክ ጥናቱን ሊመራ ይችላል።

በዚያው ስብሰባ ላይ የቃል ጥናት ጥቅሶችን ሁሉም አስተማሪዎች ሊያጠኗቸው ይገባል። አስተማሪዎች አጥንተው ጥቅሶችን በቃል መናገር ቢችሉ ለልጆች መልካም ምሳሌ ይሆናሉ።

በዚህ ስብሰባ ላይ የተሻሉ የማስተማር ዘዴዎችንና አዳዲስ የማስተማሪያ አሠራሮችን ልትወያዩና አሳብ ልትለዋወጡ ትችላላችሁ። ልጆች ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ተግባራትን ማቀድና አዳዲስ መዝሙሮችን መማር ይቻላል። እንደ ጥቁር ሰሌዳ፥ ጠመኔ፥ መጽሐፍ ቅዱስ፥ የአስተማሪ መምሪያ የመሳሰሉ ነገሮች ሊዘጋጁ ወይም ሊገዙ ይችላሉ።

ይህ ስብሰባ ለአስተማሪዎች ለመበረታታትና ችግሮችን ለመከፋፈል የተመቻ ዕድል ይከፍትላቸዋል። ስለ ችግሮቻችሁ፥ ስለ ተማሪዎቻችሁ፥ በተጨማሪ ስለ ሌሎች አንዳችሁ ለሌላችሁ ልትጸልዩ ትችላላችሁ። ስለ አርዳታውም በአንድ ላይ ጌታን ማመስገን ትችላላችሁ።

ይህ ስብሰባ ይበልጥ ጠቃሚ የሚሆነው ኃላፊው መምህር በዚህ ጥናት እስካሁን እንደተመለከትነው በየሳምንቱ አንዳንድ ትምህርት በመውሰድ ለማሠልጠን በመቻሉ ነው። ወይም «የአስተማሪዎች ሥልጠና መመሪያ» የሚለው መጽሐፍ በመጠቀም አንድ ክፍል በየሳምንቱ ሊያስተምር ይችላል። ይህ ነገር አስተማሪዎች ለተለየ ሥልጠና ወደ ሩቅ ቦታ እንዳይሄዱ ሊያደርጋቸው ይችላል።

2. የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሥልጠና ሴሚናር

ሀ. ለሴሚናሩ የሚያስፈልጉህ ነገሮች

1. የአስተማሪዎች ማሠልጠኛ መምሪያ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እና የሰንበት ትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፍ (ጥናት በዘዴ ወይም ሌላ መጽሐፍ) ለእያንዳንዱ ተሳታፊዎች እና መምህራን

2. በቂ እና ሰፊ የመሰበሰቢያ ቦታ

3. ጥቁር ሠሌዳ እና ጠመኔ

4. ትምህርቱን ለመግለጥ የሚያግዙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ለ. ልታደርገው የሚገባህ ዝግጅት

1. ጥናቱን ማስታወቅ፦ ጥናቱን በቅድሚያ መናገር በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ቢያንስ ከስድስት ሳምንት በፊት ይሁን። ብዙ ሰዎች በበርካታ የተለያዩ ጉዳዮች ስለሚያዙ ይህንንም በዕቅዳቸው ውስጥ ማስገባት እንዲችሉ ማድረግ አለብህ።

2. ስለምትሰበሰቡበት ቀንና ሰዓት አስቀድማችሁ ዕቅዱን አውጡ፦ በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ሁለት የተጠቆሙ ዕቅዶች እንዳሉ ትመለከታለህ።

ዕቅድ «ሀ» የሁለት ቀን ሥልጠና በቅርብ ላሉ እናም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማደር ለማያስፈልጋቸው ሰዎች ነው። ዕቅድ «ለ» የአንድ ቀን ከግማሽ ሥልጠና ነው። ይህ ከሩቅ ስፍራ ለሚመጡና ሌሊቱን በዚያው ማሳለፍ ላለባቸው ሰዎች ነው።

3. በሥልጠናው ላይ ሊያስተምሩ የሚችሉ ረዳቶችን ፈልግ፡- አንድ አስተማሪ ሁሉንም ክፍለ ጊዜ ከአስተማረ በጣም ሊደክመው ይችላልና ኮርሱን ለመስጠት ሁለት ወይም ሦስት የሠለጠኑ መምህራን ቢገኙ በጣም ጥሩ ነው። እያንዳንዱ መምህር የትኞቹን ክፍለ ጊዜያት እንደሚሸፍን ለማቀድ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በአንድ ላይ ተገናኙ።

4. ሠርቶ ማሳያ ትምህርቶችን ዐቅድ፡- ከጥናት በዘዴ መጽሐፍ ወይም ከሌላ የትምህርት መምሪያ ውስጥ ትምህርቱን ምረጥና ተማሪዎች ይረዱት ዘንድ ሊማሩት እንደሚገባ አድርገህ አቅርብ። ይህም መምህራኑ እንዴት እንደሚያስተምሩ ምሳሌ ይሆንላቸዋል።

እነዚህን ትምህርቶች እንዲያቀርቡ ጥሩ አስተማሪዎችን ምረጥ። ለዝግጅት በቂ የሆነ ጊዜ ስጣቸው። በሚቻልም ጊዜ ሁሉ እርዳቸው። ከሠርቶ ማሳያ ትምህርቱም በኋላ ውይይት ይደረግ። ጥሩዎቹ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? ምን ምን ነገሮች ናቸው መሻሻል ያለባቸው? መዝሙሮችና ለተግባራዊ ተሳትፎ የታቀዱ ነገሮች በትክክል ተዘጋጅተዋልን? ይህ በኅብረት ከመማር እጅግ ጠቃሚ መንገዶች አንዱ ሊሆን ይችላል።

5. የምግብና የማረፊያ ስፍራ ጉዳይን ዐቅድ፡- አስተማሪዎችህ ከሩቅ ስፍራ የሚመጡ ከሆኑ የመመገቢያና የመኝታ ስፍራቸውን ማቀድ ይኖርብሃል።

6. ጸልይ፡- በዕቅድህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ። ከአንተም ጋር ለሚሠሩ በሚዘጋጁበት ወቅት ጸልይላቸው። ለተማሪዎችም በኮርሱ ለእግዚአብሔር ቃል የተሻሉ አስተማሪዎች ለመሆን እንዲችሉና መደፋፈር እንዲያገኙ ጸልይ። ለሚያስተምሯቸው ልጆችም ጸልይ።

ሐ. የአስተማሪዎች ሥልጠና ዝግጅት ዕቅድ (መርሃ ግብር)

የጊዜ ሰሌዳ «ሀ» (ለቀን ሥልጠና ማታ ማታ ተማሪዎች ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።)

| ሰዓት | አንደኛ ቀን | ሁለተኛ ቀን |
|---|---|---|
| 4:00 | መዝሙር፥ ጸሎትና መልእክት | መዝሙር፥ ጸሎትና መልእክት |
| 4:30–5:00 | ምዕራፍ 1 ማስተማር አስፈላጊ ነው። ወይም የት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 5፥ የመጀመሪያ ግማሽ 1/2 | ምዕራፍ 4 ትምህርት እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን? ክለሳ ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 7፥ የመጀመሪያው 1/2 |
| 5:30–6:30 | ምዕራፍ 2 ልጆች እንዴት ይማራሉ? | የክለሳ ትምህርት ት.መ.ግ |

| | | |
|---|---|---|
| | ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 5፥ ሁለተኛ 1/2 | ኮርስ ክፍል 7፥ 2ኛ 1/2 |
| 6:30–8:00 | ምሳና ዕረፍት | ምሳና ዕረፍት |
| 8:00–9:00 | ምዕራፍ 3–በይበልጥ ስለ ልጆች ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 6፥ መጀመሪያ 1/2 | ምዕራፍ 5 ሕፃናትን ወደ ክርስቶስ መምራት ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 8፥ መጀመሪያ 1/2 |
| 9:00–10:00 | ምዕራፍ 4 ትምህርት እንዴት እንደሚዘጋጅ ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 6፥ ሁለተኛ 1/2<br>የቤት ሥራ እንደ ላይኛው ትምህርትን ለማዘጋጀት | ምዕራፍ 6 የትምህርትን ጊዜ እንዴት ማቀዳጀት ይቻላል ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 8፥ ሁለተኛ 1/2 |

## ዕቅድ «ለ» (ተማሪዎች እያደሩ ሥልጠናውን ይካፈላሉ)

| ሰዓት | አንደኛ ቀን | ሁለተኛ ቀን |
|---|---|---|
| 2:30-3:00 | | መዝሙር፥ ጸሎት እና መልእክት |
| 3:00–4:00 | | ምዕራፍ 4– ክለሳ ትምህርትን እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል? ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 7፥ መጀመሪያ 1/2 |
| 4:00–5:00 | መዝሙር፥ ጸሎት፥ መልእክት | የሠርቶ ማሳያ ትምህርት ትመግ ኮርስ ክፍል 7፥ ሁለተኛ 1/2 |
| 5:00–6:00 | ምዕራፍ 1 የማስተማር አስፈላጊነት ወይም ትመግ ኮርስ ክፍል 5፥ አንደኛ 1/2 | ምዕራፍ 5 ልጆችን ወደ ክርስቶስ መምራት ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 8፥ አንደኛ 1/2 |
| 6:00–7:30 | ምሳና ዕረፍት | ምሳና ዕረፍት |
| 7:30–8:30 | ምዕራፍ 2 ልጆች እንዴት መማር እንደሚችሉ ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 5፥ ሁለተኛ 1/2 | ምዕራፍ 6 የማስተማሪያ ክፍለ ጊዜን እንዴት ማቀናጀት እንችላለን? ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 8፥ ሁለተኛ 1/2 |
| 8:30–9:30 | ምዕራፍ 3 ሕፃናትን በተመለከተ ተጨማሪ ትምህርት ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 6፥ አንደኛ 1/2 | አስተማሪዎች ወደ ቤት ለመሄድ ካልቸኮሉ የትምህርቱ ግምገማ ይኑር ወይም እግዚአብሔር በአካባቢያቸው ስለሚያደርገው የምስክርነት ጊዜ ይኑር። |
| 9:30–10:30 | ምዕራፍ 4 ትምህርትን እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን ወይም ት.መ.ግ ኮርስ ክፍል 6፥ ሁለተኛ | |

| | 1/2 | |
|---|---|---|
| 12፡00–1፡00 | መዝሙር፥ ጸሎት እና መልእክት | |
| 1፡00–2፡00 | የቤት ሥራ፡– ከዚህ በላይ እንደተማርነው የተሟላ ትምህርትን ማዘጋጀት። | |

2ኛ ጥያቄ፡– የዚህን የትመማ ኮርስ ምዕራፍ 5–8 ከተመለከትህ በኋላ በዚህ መረጃ በመጠቀም እንዴት የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሥልጠና ልታካሄድ እንደምትችል ዕቅድ፡ ሁሉንም ማካተት እንድትችል አንዳንድ ነገሮችን ማሳጠር ይኖርብሃል። ከም.1–4 አንዳንድ ነጥቦችን መጨመር ትችል ይሆናል፤ ምንም የማስተማር ልምድ ለሌላቸው ማስተማር ያለብህ ዋና ነገር ምን እንደሆነ በጥንቃቄ አስብ። በደንብ ሥራውና በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ገልብጠው። በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ላሉ የማስተማር ብቃት ላላቸው ሰዎች ኮርስ በምታዘጋጅበት ጊዜ ይህ ብዙ ጊዜ ሊቆጥብልህ ይችላል።

3ኛ ጥያቄ፡– በሁለቱ የማሠልጠኛ ዘዴዎች መጠቀም የሚሰጠው ጥቅም አለን? የሠለጠነ ኃላፊ ካለህ በተግባር ላይ ላሉ የሚሰጥ ሥልጠና ዓመቱን ሙሉ ሊቀጥል ይችላል። ለማነቃቂያ ኮርስ ወይም አዲስ ነገርን ለመማሪያ ጊዜ የሴሚናር ዕቅድ አውጣ።

## ሁለተኛ ቀን፡– ሥርዓተ ትምህርትን ማቀድ

ትርጓሜ፡– ሥርዓተ ትምህርት በቀላሉ ሲተነተን የምታስተምረው ነገር ማለት ነው። የምታስተምረው ነገር ሁሉ በአንድ ላይ መደራጀት እንዳለበት መታወቅ ያለበት ነገር ነው። በየሳምንቱ አንድ ዓይነት ትምህርት ብቻ ማስተማር አትፈልግም። ከዓመት ዓመትም አንድ ዓይነት ትምህርት መስጠት አትፈልግም። ስለዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማለት ዕቅድ ማለት ሲሆን፥ ይህም መማር– ማስተማርን በጥበባዊ ዘዴ ማድረግ ማለት ነው።

ከምትጠይቃቸው ጥያቄዎች አንዱ «በሰንበት ትምህርት ቤታችን ውስጥ ምን ማስተማር አለብን?» የሚለውን ነው። መምህራንን አሠልጥነናል። የሰንበት ትምህርት ቤታችን በመስከረም ወር እንደሚጀምር ማስታወቂያ ተናግረናል። ነገር ግን ምን ማስተማር አለብን? ይህ በዚህ ትምህርት ውስጥ ልንመልሰው የምንሞክረው በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው።

### 1. የጥሩ ሥርዓተ ትምህርት አስፈላጊ ነገሮች

### ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ማዕከል ያደረገ።

በዚህ ኮርስ ብዙ ጊዜ እንዳተኮርነው በክርስቲያናዊ ትምህርት ውስጥ የመጨረሻ ግባችን መጽሐፍ ቅዱስን ለማንኛውም የዕድሜ ክልል በሚገባ ማስተማር ነው። የእኛ መሻት በጉባኤያችን የሚገኙ ምእመናን በሙሉ ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዲኖራቸው ነው። የማስተማሪያ መጽሐፋችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

የምንፈልገው ሕዝባችን ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እንዲኖረው ብቻ ሳይሆን፥ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው በእግዚአብሔር መጽሐፍ መርሆዎች

እንዲኖሩም ነው። እንዲሁም ጥሩ ምስክር እንዲሆኑ፥ ሰዎችንም በማስተማር ወደ መዳን መንገድ እና ክርስቶስን ወደ ማመን ማድረስ እንዲችሉ እንሻለን። በክርስቶስ ስለ አለ እምነታቸው ለትችቶች ወይም በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ለስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች መልስን መስጠት ይቻላቸው ዘንድ እንፈልጋለን።

እነዚህ ዓላማዎች ግብ ሊመቱ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ ሕይወትን ለመለወጥ በሚያስችል በጥንቃቄ እና በጥበባዊ ስልት በታቀደ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ነው።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ባደረገው የመጀመሪያ ጸሎት የእግዚአብሔርን ቃል የምናስተምርባቸውን ምክንያቶችና በማስተማራችን ልንጠብቃቸው የሚገቡ ውጤቶችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት እናገኛለን።

---

4ኛ ጥያቄ፡- ቆላ. 1፡9-11 አንብብ። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ የማስተማር ውጤቶች የሆኑትን አምስት ነጥቦች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ።

---

1. «የፈቃዱን እውቀት» (ፈቃዱን እንድናውቅ)- መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አሳቡን፥ ዕቅዱን፥ እና ውሳኔውን፥ ለሰው ልጆች እንደገለጸ ያስተምረናል። ይህንንም መረጃ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እናገኛለን። መንፈሳዊ ዕድገት ሁልጊዜ የሚጀምረው የእርሱን ቃል ከማወቅ ነው (ኤፌ. 5፡17)።

2. «መንፈሳዊ ጥበብና አእምሮን ሁሉ» - እንደ መረጃ ሆኖ ብቻ መቅረት ሳይሆን በሚሰሙት ዘንድ ሁሉ ማስተዋልና ግንዛቤ ሊገኝበት ይገባል። ተማሪዎችም የየዕለት ሕይወታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር ያለውን ዝምድና ሊያስተውሉ ይገባል።

3. «በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ»። የእውቀት ውጤት የተለወጠ ሕይወት መሆን አለበት። በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ስለተነገረላቸው የቆሮንቶስ ሰዎች አስብ። ብዙ ነገር ያውቃሉ። ነገር ግን በዕለታዊ ኑሮአቸው ውስጥ አይለማመዱትም ነበር። ጳውሎስም ገሠጻቸው። ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ (6፡2)፥ ኃጥኣን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ (6፡9)፥ ሰውነታቸውም የክርስቶስ አካል (ብልት) እና (6፡15) የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ (6፡19) ያውቁ ነበር። ይሁንና ያላቸውን እውቀት በዕለታዊ ኑሮአቸው ላይ አላዋሉትም ነበር። በአማኞችም መካከል ክሶች ነበሩ። የቤተ ክርስቲያንን የሥነ ሥርዓት ቅጣት አላጠናከሩም ነበር። በሥነ ምግባር ንጽሕና ለመኖርም አልቻሉም። መረጃ ነበራቸው፤ ነገር ግን አልኖሩበትም። ጳውሎስ ስለ እነርሱ ሲናገር «እኔም ወንድሞች ሆይ የሥጋ እንደ መሆናችሁ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም» (1ኛ ቆሮ. 3፡1) ይላል።

ይህ መግለጫ የተማርነውን ነገር በተግባር ላይ የማዋልን አስፈላጊነት ያጎላል።

4. «በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ።» ፍሬ ማፍራት ከእውቀት፥ ከማስተዋልና ከምላሽ ቀጥሎ የሚመጣ ነው። ክርስቲያን ቃሉን ማጥናት፥ ሕይወቱንም በቃሉ እየመረመረ ምላሽ መስጠት አለበት። ይሁንና ፍሬን ማፍራት ከራሱ ጥረት ውጪ የሚመጣ ነው። ለቃሉ ምላሽ በመስጠቱ ውስጥ እግዚአብሔር ፍሬን ያፈራል።

5. «በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ»– ይህ በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናገኘው የመጨረሻው ውጤት ነው። እኛ ለእግዚአብሔር ቃል መልስ መስጠት በጀመርን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ እየተገለጠ ይመጣል። ዮሐንስ 14፡21፥ «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ» ይላል።

ለ. በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ያተኮረ

ስኬታማ ሥርዓተ ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያሟላ ይገበዋል። ዕድሜያቸው ምን ያህል ነው? ከዚህ በፊት ምን ነገር አውቀዋል? ችሎታቸውስ ምንድን ነው? እንዴት የተሻለ ሊማሩ ይችላሉ? የሚሉትን፥ ጥያቄዎች ሊያካትት ይገባል። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች የሚገጥሟቸው ፈተናዎችና ችግሮች በሚሰጠው ትምህርት እንዲፈታ እና ፍላጎታቸው እንዲሟላ ሊታሰብ ይገባል።

ሥርዓተ ትምህርትን በምናዘጋጅበት ጊዜ ለራሳችን ልናቀርባቸው የሚገቡ ጥቂት ጥያቄዎች አሉ።

1. ይኼኛው የዕድሜ ክልል የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው ሊያስተውለው የሚችለው?

2. ለዚህ የዕድሜ ክልል በጣም አስፈላጊ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው?

3. እነዚህ ተማሪዎች በተሳካ ሁኔታ የሚማሩት እንዴት ነው?

4. ይህንን የትምህርት ክፍል በምን ዓይነት ቅደም ተከተል ማስተማር አለብን?

የልጆችን የእያንዳንዱን የዕድሜ ክልል ባሕርይ ወደ አጠናንበት ወደ ክፍል 6 ተመለስ። ይህ በዕቅድህ ውስጥ ሊረዳህ ይችላል። በተጨማሪም በምዕራፍ አሥር ስለ ወጣቶች ባሕርይ፥ በምዕራፍ አሥራ ሁለት ስለ ጎልማሶች ባሕርይ እናም በምዕራፍ አሥራ ሦስት ስለ ሴቶች ባሕርይ፥ ታገኛለህ። አዎ፥ ሥርዓተ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሁሉም ዕድሜ አኳያ ሊታቀድ ይገባል።

ሐ. የምንጠቀምባቸው የማስተማር ዘዴዎች

ተማሪዎቻችን በመስማት፥ በማየት፥ በመናገርና በንቁ ተሳትፎ እንደሚማሩ ማስታወስ አለብን። ይህ ለሁሉም የዕድሜ ክልል፥ እስከ እርጅና ዕድሜ እውነት ነው። የመስበክና የማስተማርን ልዩነቶች ተመልክተናል። በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ስብከት የመግቢያ መንገድ ነው። ሆኖም

በስንበት ትምህርት ፕሮግራማችን እያስተማርን እንጂ እየሰበክን አይደለም። በክፍላችን ለተማሪዎች ተሳትፎ በቂ ዕድል ልንሰጥ ይገባል። ወጣቶችና ጎልማሶች ለክፍል የሚያቀርቡት ብዙ አሳብ ስላለ እነርሱ ወደ ውይይት እንዲገቡና አሳባቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲያካፍሉ አድርገን ዕቅድ ማውጣት አለብን። ያለበለዚያ ግን በተለይ ለጎልማሶች የማስረዳትን ዘዴ ብቻ ብንጠቀም ይሰለቻሉ። እናም የሰሙትን በሙሉ ይረሳሉ። ክፍሉ ሕይወት ያለበት የተነቃቃ እና የሚስብ ሊሆን ይገባል። ካልሆነ ለመምጣት አይፈልጉም። ይህ ለሁሉም የዕድሜ ክልል እውነት ነው።

መ. ለሥርዓተ ትምህርቱ የተለያዩ ዕቅዶች

1. አንድ ወጥ ዕቅድ

ምንም እንኳን በተለያየ ደረጃ እንደ ችሎታቸው መጠን ሆነው ቢመሩም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለሁሉም ክፍሎች አንድ ዓይነት ትምህርትን ያስተምራሉ። የዚህ ጥቅሙ እያንዳንዱ በቤተሰብ ውስጥ ያለ ሁሉ አንድ ዓይነት ትምህርት ማግኘቱ ነው። በቤታቸውም ሊወያዩበትና ለሚቀጥለው እሑድ እንኳን በአንድነት ሊያጠኑት ይችላሉ።

2. በክፍል ደረጃ ዙር ማስተማር

እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓተ ትምህርት ለአንድ የዕድሜ ክልል ብቻ የታቀደ ነው። ያም ማለት ለአራትና ለአምስት ዓመት ዕድሜዎች ነው። ሥርዓተ ትምህርቱ ለሁለት ዓመት ዙር ይሆንና ሁሉም የአራትና የአምስት ዓመት ዕድሜዎች አንድ ዓይነት ትምህርት ሊማሩ ይችላሉ። ከዚያም ከስድስት እስከ ስምንት ወዳለው ክፍል ሲሸጋገሩ የሚቀጥሉት አራት እና አምስት ዕድሜዎች የዙር ትምህርቱን ሊደግሙ ይችላሉ። ከ6 እስከ 8 ያሉት የሦስት ዓመት ዙር ይኖራቸዋል። ትምህርቱ ከዕድሜ ደረጃቸው ጋር ተስማሚ ሆኖ ይታቀዳል። የሦስት ዓመቱን ትምህርት በአጠናቀቁ ጊዜ ከ9 ወደ 11 የዕድሜ ክልል ያልፋሉ። በዚያም ሌላ የሦስት ዓመት የትምህርት ዙር አለ። ትምህርቱ እንደቀደሙት ክፍሎች አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል። እናም ከፍ ባለ ደረጃና ከበድ ባሉ ጽንሰ - አሳቦች ሊታቀድ ይችላል።

3. ጠበብ ያለ የክፍል ደረጃ

ይህ ዕቅድ ለእያንዳንዱ ደረጃ ትምህርት ሊኖረው ይችላል። የሚሠራበትም በሕዝብ ትምህርት ቤት የትምህርት ዓይነቶች እንደሚታቀዱት ዓይነት ነው። የእያንዳንዱ ዓመት ትምህርት ከአለፈው ዓመት ትምህርት መነሻነት እየተገነባ የሚመጣ ይሆናል።

4. ተመራጮች

እንዲህ ያለው የሥርዓተ ትምህርት ዕቅድ የሚሠራው ለወጣቶችና ለአዋቂዎች ነው። በርከት ያሉ ኮርሶች ቀርበው ወጣቶችና አዋቂዎች የትኛውን ዓይነት ትምህርት እንደሚፈልጉ ሊመርጡ ይችላሉ። ለምሳሌ የዘሌዋውያንና የዕብራውያን መጽሐፍ ጥናት ወይም አንድ ስለ ውጤታማ የክርስቲያን ምስክርነት እናም ሌላ የዮሐንስ ወንጌል ጥናት ይኖራል። ይህም ማለት በሦስት በተለያዩ አስተማሪዎች ሦስት ክፍል ሊኖር ይችላል። እናም

ወጣቶችና አዋቂዎች የትኛውን ትምህርት መማር እንደሚፈልጉ ለመምረጥ ይችላሉ ማለት ነው። ሰዎች ከዚህ በፊት ያላገኙትን ዕድል እንደገና ያገኙት ዘንድ በኋላ ሊደገም ይችላል። በዚህም በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ጥቂት ሰዎችን የሚያካትት ብቻ ይሆናል። ጥቅሙም የተሻለ የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል። እንዲሁም ጥያቄዎችን ለመነጋገርና አሳብ ለመከፋፈል ዕድሉ የሰፋ ይሆናል።

አስቀድሞ የተዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሑፎች የምታገኝ ቢሆን ይመረጣል። ለአዋቂዎች የሚሆኑ የተመረጡ የመጽሐፍ ጥናቶች ይኖራሉ። እናም ብዙ ኮርሶች መምረጥ ይቻላል። በክርስቲያን መጻሕፍት መደብር ውስጥ ወይም በኤስ. አይ. ኤም ወይም በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ክፍል ምን እንደሚገኝ አጣራ። ተማሪው የጥናቱን መጽሐፍ ከገዛ እቤቱ አጥንቶና ተዘጋጅቶ ሊመጣ ይችላል። ወጣቶችና አዋቂዎችን በጥበባዊ መጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ለማሳተፍ ይህ ጥሩ ዕድል ነው።

ለልጆችም የሚሆኑ መጻሕፍት አሉ። በአዲስ አበባ ውስጥ ያለው ግሎብ የሥነ ጽሑፍ ድርጅት ለተማሪዎችና ለመምህራን ያዘጋጃቸው መጻሕፍት አሉ። ጥናት በዘዴ የሚለው መጽሐፍ 1፥ 2፥ እና 3 በኤስ. አይ. ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ይገኛል። በተጨማሪም ተከታታይ የሆነ ሕፃናት በዓይነ ሕሊና ታሪኮችን እንዲያዩ የሚጠቅማቸው ትልቅ የሥዕል ገበታ አለ። ለወጣቶች የማርቆስ መጽሐፍ ጥናት አለ። ለሴቶች ደግሞ «አገርዋና ቤቷ» የሚል የጥናት መጽሐፍ አለ። ለአዋቂ ሴቶችና ወንዶች ጥናት በዘዴ የሚል መጽሐፍና ብዙ ጥሩ የጥናት መጻሕፍት ሊኖሩ ይችላሉ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፦ የአሁን የትምህርት መማሪያዎች በዝርዝር መዝግባቸው። ከዚያም በሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ልትጠቀምባቸው የምትችላቸውን ተጨማሪ የመጻሕፍት ዝርዝር ጻፍ። ለወደፊቱ ለሰንበት ትምህርት ሊዘጋጁ የሚገባቸው ምን ምን መጻሕፍት ናቸው ብለህ ታስባለህ? |

## ሦስተኛ ቀን፦ በግል የታቀደ ሥርዓተ ትምህርት

በዚህ ትምህርት ውስጥ ልንነጋገርበት የምንፈልገው ሊረዳን የሚችል ነገር ከሌለን ለሰንበት ትምህርት ቤት ስለሚሆን ሥርዓተ ትምህርት ነው። የአስተማሪዎቹ መመሪያም ሆነ ምንም የተማሪዎች መጽሐፍ ከሌለን ምን ማድረግ አለብን?

ከሁሉም መጀመሪያ ሥርዓተ ትምህርትን በማቀድ የሠለጠነና ሊረዳን የሚችል አንድ ሰው እንደሚያስፈልገን መገንዘብ አለብን። ቢያንስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ጥሩ መረዳት ያለው እና የማስተማር ዘዴ እውቀት ያለው በሰንበት ትምህርት ቤት ያሉትን የተለያዩ የዕድሜ ክልል ባሕርያትን ሊረዳ የሚችል ሰው ያስፈልገናል። ምናልባትም የመንግሥት ትምህርት ቤት አስተማሪ የሆነና በዚህ ነገር የሠለጠነ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣ ሰው ሊሆን ይችላል።

1. ልንመለከታችው የሚገቡ አካባቢዎች

ሀ. ልጆች እያደጉ ሲሄዱ የሚያልፉአቸው ደረጃዎች። ይህን ሥርዓተ ትምህርት የሚያቅድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የዕድሜ ክልል ባሕሪዎች ሊገነዘብ ይገባዋል። ትንንሽ ልጆች ተጨባጭ ነገርን ብቻ የሚያስተውሉ መሆኑን ማስታወስ ይገባል። ይህም ማለት ሊማሩ የሚችሉት የተጨበጡ እውነቶችን ነው። ስለ ተፈጥሮ፥ በዙሪያቸው ስላሉት ድንቅ ሥራዎች፥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ፥ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እንዲሁም በምዕራፍ 6 ውስጥ በአንደኛና ሁለተኛ ቀኖች ትምህርቶች ውስጥ «ምን ልናስተምራቸው እንችላለን?» በሚለው ርእስ የተጠቀሱ ሌሎች ነገሮችን ማለት ነው።

ልጆች ከዘጠኝ እስከ አሥራ አንድ ዓመታት ዕድሜ በደረሱ ጊዜ ምክንያታዊ ምላሽን መስጠት፥ ተምሳሌቶችን መረዳት፥ ምሳሌዎችን ማስተዋል እና ረቂቅ ነገሮችን መረዳት ይጀምራሉ።

በተጨማሪም የወጣቶችንና የአዋቂዎችን የመማር ባሕርይ ከግንዛቤ ሊያስገባ ያሻል። ሁሉም አዋቂዎች በአንድ ዓይነት መንገድ ስለማይማሩ ለእነርሱም ዕቅዱን በሚነድፍበት ጊዜ ይህንን ነገር ማሰብ አለበት። ወጣቶች ፈጣን አእምሮ እና ቶሎም የመረዳት ብቃት ስላላቸው እነዚህ ሁሉ ፈርጆች መታሰብ ይኖርባቸዋል።

ለ) ይህ ሰው የመማር ማስተማር ሂደቱን የተረዳ መሆን አለበት። ይህም ሲሆን ዕቅዱ በክፍል ውስጥ ከሚካሄዱት የተለያዩ የመማርና ማስተማር ዓይነቶች ጋር የሚስማማ ይሆናል።

ሐ. ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምባቸው ክፍሎች በቤቶች ግንባታ ውስጥ እንዳሉ ጡቦች ናቸው። በዚህ ዓመት የተሰጠው ትምህርት እንደገና በሚቀጥለው ዓመት ከፍ ባለ ደረጃ መሰጠት አለበት። ጥሩ መሠረት በወጣትነት መጣል አለበት። ወደፊት ደግሞ ግንባታው ይቀጥላል።

መ. መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜም የማስተማሪያ መጽሐፉ ሊሆን ስለሚገባ የእግዚአብሔር ቃል ጥሩ መረዳት እንዲኖረው ያስፈልጋል።

2. ሥርዓተ ትምህርት ሲነደፍ ሊታወሱ የሚገባቸው ሁለት ነገሮች

ሀ. ሥርዓት ትምህርቱ ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስን አሳብ ሊያሳይ ይገባዋል። ማንኛውም ሥርዓተ ትምህርት አርቃቂ ወደ ራሱ ግላዊ እይታ ሊገፋው አያስፈልግም። ከቤተ ክርስቲያን እምነት አቋም እና ሥርዓት ጋር የተስማማ መሆን አለበት። በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚሰበከው በሰንበት ትምህርት ቤት ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የአቋምና የአመለካከት ልዩነት ከታየበት አሳዛኝ ይሆናል።

ለ) ሥርዓተ ትምህርቱ መልካም ጠባይን ለማስገኘት የሚያስችሉ መረጃዎችን መስጠት አለበት።

3. ሥርዓተ ትምህርትን እንዴት ነው የምንመሠርተው?

ሀ. ዓመታዊና የሦስት ወር ዕቅድ

በመጀመሪያ ዓመታዊ ዕቅድ ለእያንዳንዱ የዕድሜ ክልል መውጣት አለበት። የዓመቱ አጠቃላይ ዋና አሳብ እና የየሦስቱ ወሩ ዋና አሳብ (ርእስ) በየሦስት ወሩ የምትመድባቸው ትምህርቶች ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ እንደሚሆኑ ለማየት ይረዳሃል።

የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትምህርት ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል። ጥሩ መሠረትን በሕይወት ውስጥ ለመጣል የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ማስተማር አስፈላጊ ነው።

በልጆች አእምሮና ልብ ውስጥ ለመቅረጽ የምትፈልጋቸውን እውነቶች ለማስተማር በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በጣም ጥሩ ታሪክ ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች ታሪክ መርጠህ ተጠቀም።

ለ. ሳምንታዊ ዕቅድ

ቀጥሎም ትምህርቱ በየሳምንቱ ይማሩት ዘንድ ለየብቻው ሊከፋፈል ይገባል።

የሰንበት ትምህርት ከስብከት ፕሮግራም ጋር አብሮ ከተደራጀ አንዱ ሌላውን ሊደግፍ ይችላል። ይህም ማለት ሥርዓተ ትምህርቱን ለማዘጋጀት መጋቢዎችና ሽማግሌዎች በሚገባ መሳተፍ አለባቸው ማለት ነው። ዕቅዱን የሚያወጡትም እነርሱ ሊሆኑ ይችላሉ ማለትም ይሆናል።

ሥርዓተ ትምህርት ማውጣት ቀላል ወይም አጭር ሥራ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን ጥሩ የሆነ የሰንበት ትምህርትን ለማከናወን ዋናው ክፍል እንደሆነ የታወቀ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያተኮረ እውነተኛ ሥርዓተ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያንህ የትምህርት ፕሮግራም እንድታደራጅ እግዚአብሔር ይምራህ።

## አራተኛ ቀን፡- መንፈሳዊ ምግብ ለሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች

ለሰንበት ትምህርት ክፍል አዳዲስ አስተማሪዎች ስታሠለጥን ቆይተሃል። ጌታን፥ ቃሉን፥ ልጆችን፥ ወጣቶችንና አዋቂዎችንም ሁሉ የሚወዱትን ወንዶችና ሴቶች በጥንቃቄ መርጠሃል። በተጨማሪ ማስተማር የሚወዱ ናቸው።

በዚህ ትምህርት ስለ አንድ ነገር ለመወያየት እንፈልጋለን። መምህራኑ በሕይወታቸው ልማድ አድርገው ከያዙት በዘመናቸው ሁሉ የማያቋርጥ በረከት የሚሆንላቸው ነው። ይህም በየቀኑ የጥሞና ጊዜን ማድረግ ነው።

ኢየሱስም እንዲህ አለ። «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ. 4፡4)። በአዎንታዊ ገጽታ ካየኸው፥ ሰው በምን እንደሚኖር ታያለህ። «ሰው ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል ሁሉ ይኖራል።» በጸሎትና በጥሞና በታ ሆነህ ቃሉን ስታሰላስል እግዚአብሔር ለነፍስህ የሚናገረው ቃል ነው። እንደዚህ ነው ሰው በሕይወት የሚኖረው። በአስተምህሮ ጉዳይ ትክክለኛ ሆነህ በመንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ ሙት ልትሆን ትችላለህ። በሕይወት የምትኖረው መጽሐፍ ቅዱስህን ባነበብህ ጊዜና ባሰላሰልኸው ጊዜ ለነፍስህ በሚናገርህ ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

1. ዕለታዊ የጥሞና ጊዜ አስፈላጊነት

ሀ. ለመንፈሳዊ ጤንነት፡- 1ኛ ጴጥሮስ 2፡2 ሲናገር፥ «ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ» ብሏል። ትናንሽ ሕፃናት ቶሎ ቶሎ የእናታቸውን ወተት እንደሚፈልጉ፥ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች፥ በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል ከማንበብ የሚመጣውን መንፈሳዊ ምግብ ልንመገብ ይገባል።

በቀን ምን ያህል ጊዜ ለመመገብ ትፈልጋለህ? «ሦስት ጊዜ፥ ካገኘሁም አራት ጊዜ» ልትል ትችላለህ። ይሁንና ብዙዎቻችን እሑድ ብቻ የሚሰበከውን ቃል ለመስማት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን። ከዚያም የሚቀጥለው እሑድ እስከሚደርስ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል አናነብም፥ አንሰማም። አንድ ሕፃን በሳምንት አንድ ቀን እየተመገበ ጤነኛ የሚሆን ይመስልሃልን? እንደዚያ ቢሆን ምን ይሆን ነበር? የእግዚአብሔርን መልካም ቃል ካልተመገብህ በስተቀር በአንተም እንደዚሁ ይሆንብሃል።

7ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 5፡11-14 አንብብ። የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ዕብራውያን ክርስቲያኖች ግድ ብሎታል። ምን ስለሆኑ ነበር የሚወቅሳቸው? እንዴት መሆን ነበረባቸው? ምን ዓይነት መንፈሳዊ ምግብ መውሰድ መቻል ነበረባቸው? ውጤቱስ ምን ይሆን ነበር?

ጳውሎስ ዕብራውያንን በሳል ስላልሆኑ ይገሥጻቸው ነበር። የቀደመው የመጀመሪያ ትምህርት እንዲደገምላቸው ይሹ ነበር። ምክንያቱም በፊት የሰሙትን ሁሉ ረስተው ነበርና። ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ በተለየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው እንደ ተናገራቸው እናስታውሳለን። «እርሱም መጥቶ ዓለምን ስለ ኃጢአት ስለ ፍርድም ስለ ጽድቅም ይወቅሳል።» ደግሞም «ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» እናም «የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፥ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።» «እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ከአለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» (ዮሐ. 16፡8-15)።

መንፈሳዊ ሕይወታችን ሕያው ሆኖ የሚቆየው ውድ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ የተመገብን እንደሆነ ነው። መንፈስ ቅዱስም ያንን ቃል ወስዶ ለአንተ ይገልጥልሃል። በመንፈሳዊ ጤንነት እንድትጠበቅ የሚያደርግህም ያ ነው።

ለ. ንጹሕ ልብን ይዞ ለመኖር

8ኛ ጥያቄ፡- መዝ. (11)9፡91 ዮሐ. 15፡3 እና 1ኛ ዮሐ. 1፡9 አንብብ። ልባችንን ንጹሕ አድርጎ ለመጠበቅ ምን ነገር ያስፈልገናል? ልባችንን በንጽሕና የመጠበቅ ብቸኛ መንገድ ምንድን ነው? ሌላውስ መንገድ ምንድን ነው?

መዝ. (66)፡17-19 ዳዊት ወደ እግዚአብሔር እንደጮኸ ይናገራል። በልቡ ኃጢአት ቢኖር ኖሮ እግዚአብሔር ባልሰማውም ነበር። እኛም በንጹሕ ልብና በታጠበ እጅ ወደ ጌታ ልንቀርብ ይገባል። ምሕረትን በመጠየቅ ንስሐን በየቀኑ ብንገባ እኛን የሚያነጻን አለ።

ሐ. ምክርንና ምሪትን ለመቀበል

9ኛ ጥያቄ፦ 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17 አንብብ። እንዴት ነበር እግዚአብሔር ቃሉን የሰጠን? የቅዱሳት መጻሕፍት አራት ጠቀሜታዎችን ዘርዝር። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ማንበብ ምን ውጤት ያስገኛል?

ቆላ. 3፡16 ደግሞ አንብብ። እንዲህ ተብሎ ተነግሮናል። «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ፥ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ»። የእግዚአብሔር ቃል ሥራውን በሕይወትህ እንዲሠራ ካልፈቀድህለት በስተቀር፥ የጽድቅና የቅድስናን ሕይወት የሚወስኑ እውነተኛ መርሆዎችን ልታውቅ አትችልም።

መ. ለጥንካሬና ለመንፈሳዊ ውጊያ

10ኛ ጥያቄ፦ ማቴ. 4፡1-11 ኤፌ. 6፡16-17 አንብብ። ኢየሱስን በምድረበዳ የፈተነው ማን ነበር? ዘዴዎቹስ ምን ምን ነበሩ? ተሳክቶለት ነበርን? ኢየሱስ ሰይጣንን ያሸነፈው በምን መንገድ ነበር? በኤፌሶን መጽሐፍ በፈተና ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን ነው የተማርነው? ክፉውን እንዴት ማሸነፍ እንችላለን?

ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን ለማሸነፍ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተደገፎ ነበር። ሰይጣንም ፈጽሞ ተረታ እንጂ ሊቋቋመው አልቻለም። ሰይጣንን ለማሸነፍ የእግዚአብሔርን ቃል እንደተሳለ ስለታም ሰይፍ መጠቀምን ልንማር ይገባል (ኤፌ. 6፡17)። አንዳንዶቹ ይህ የሚሆነው ሰይጣን እንዲለቅ በማዘዝ ወይም በመገሠጽ እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በጸጥታ በመጠቀም ብቻ ጠላትን ሲያባርር እናያለን። ቃሉ የተሳለ ስለታም ሰይፍ ስለሆነ በምንጠቀምበት ጊዜ ማንም ሊቋቋመው አይችልም።

ሠ. ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና ከእርሱም ለመስማት

11ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 4፡16 አንብብ። በቁ. 14 ላይ እንዲህ ተብለናል። «እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስለአለን...» እርሱ ልክ እንደኛ በሁሉም ነገር የተፈተነ ነው። ስለሚረዳን ምን እንድናደርግ ነው የተነገረን? ከእርሱ የምንቀበለው ምንድን ነው?

አስደናቂው እውነታ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ለመገናኘት መፈለጉ ነው። ስለዚህም ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ጊዜ መውሰድ ግዴታና ኃላፊነት ሳይሆን መልካም ዕድል እና ክብር ነው። ዮሐ. 4፡23 እንዲህ ይላል። «ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በእውነትና በመንፈስ የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና»። በ2ኛ ዜና 7፡14-15 የተጻፈውን ተመልከት። «በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮቼም ያደምጣሉ»።

እርሱ ከእናንተና ከእኔ ለመስማት ይናፍቃል። ቃሉን ለማሰላሰል፥ ድምፁን ለመስማትና ወደሚሰማን ወደ እርሱ ለመጸለይ የተሰጠንን ይህን ልዩ ዕድል ለምን ችል እንላለን?

2. ለዕለታዊ የጥሞና ጊዜ የሚያስፈልጉህ ነገሮች

ሀ. የተወሰነ ጊዜና ቦታ (ማር. 1:35፤ ዮሐ. 18:1)።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ

ሐ. የጸሎት መዝገብ፡- የጸሎት መዝገብ ከሌለን ልንጸልይባቸው የሚገቡንን ነገሮች እንዘነጋቸዋለን። የጸሎት መዝገብ መኖሩ ግልጽ በሆነ መንገድ ጌታ የመለሰልንን በመመዝገብ በጸሎታችን መበርታትን እንድናገኝ ያደርገናል። ጸሎት የሚያስፈልጋቸውን የተለያዩ ሰዎችና የተለያዩ ሁኔታዎችን የመመዝገብ ልምድ ካለን በተለያዩ የሳምንቱ ቀናት ውስጥ ዝርዝሩን በመከተል የጸሎት ጥያቄዎችን ሳንዘነጋ እንድንጸልይ ያግዘናል።

መ. እግዚአብሔር በየቀኑ የሚያስተምረንን ለመመዝገብ የምንችልበት ማስታወሻ ደብተር ያስፈልገናል። በተከፈተ ልብ ወደ እግዚአብሔር ቃል ብንመጣ፥ እግዚአብሔር ይናገረናል። ንስሐ ልንገባባቸው ከሚገቡን አንዳንድ ኃጢአቶች አንጻር ይገሥጸናል። አዲስ የሆነ የተስፋ ቃል በመስጠት ሊያበረታታን ይችላል። እንድንታዘዘው ትእዛዝ ሊሰጠን ይችላል። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የተናገረንን ማናቸውንም ነገሮች በማስታወሻ ደብተራችን ልንጽፈው ይገባል።

ሠ. የተከፈተ፥ ሊቀበል የተዘጋጀና እግዚአብሔር የሚያስተምርህን ነገር ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሆነ ልብ።

3. የጥሞና ጊዜ ደረጃ በደረጃ

ሀ. በጥቂት የጸሎት ጊዜ ጀምር። ጌታም በመንፈሱ እንዲያስተምርህ ጠይቅ። ልብህን እንዲያነጻውና ለቃሉም መታዘዝ እንድትችል እንዲያዘጋጅህ ጌታን ጠይቅ።

ለ. የምታነበውን መጽሐፍ ምረጥ። የመጀመሪያውን ምዕራፍ ሦስት ጊዜ አንብበው። ለመጀመሪያ የምዕራፉን አሳብ ለማግኘት ፈጠን ብለህ አንብበው። እያንዳንዱን ጥቅስ ደግመህ አንብብ። በመጨረሻም ለአንተ ለግልህ የሚናገርህን ለማየት ደግመህ አንብበው። በሚቀጥለው ቀን የሚቀጥለውን ምዕራፍ በተመሳሳይ መንገድ አንብብ። አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ከሆንህ ከዮሐንስ ወንጌል ጀምረህ እንድታነብ እመክርሃለሁ።

ሐ. ያነበብኸውን ነገር አሰላስል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ።

- ልታዘዘው የሚገባ ምን ትእዛዝ አለ?

- ለራሴ ልይዘው የሚገባ አዲስ ተስፋ አለ?

- ልተወው ስለሚገባ ኃጢአት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ አለን? በዚህ ሰዓት ንስሐ ገብቼ ልተወው የሚገባ የምሠራው ነገር አለን?

- ስለ እግዚአብሔር ልማረው የሚገባኝ ምን አዲስ ነገር አለ? ስለ ራሴም? ስለ ሌሎችም?

መ. እግዚአብሔር ያስተማረህን ነገሮች በራስህ አገላለጽ ጻፍ። የግልህም አድርገው። ይህም እግዚአብሔር ለዕለቱ የሰጠህ መልእክት ነው።

ሠ. ጸልይ። እግዚአብሔር የሰጠህን መልእክት ውሰድና ከእርሱ ጋር ተነጋገርበት። ከዚያም እርሱን ለማስደሰት እንዴት መታዘዝ እንደምትችል ጠይቀው። ስላደረገልህና ወደፊት ስለሚያደርግልህ ሁሉ አመስግንና አምልከው። ከዚያም የጸሎት መዝገብህን በመከተል ስለ ሌሎች ጸልይ።

ረ. የተማርኸውን ለሌሎች አካፍል። የምታካፍለውን ታስታውሰዋለህ። ሌሎች ክርስቶስን እንዲያውቁ ወይም በእርሱ እንዲያድጉ ልትረዳ ትችላለህ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ በምድረበዳ የመገበው መና በየዕለቱ ሊበሉትና ሊከፋፈሉት የተገባ ነበር። ባከማቹት ጊዜ ግን ሊተላ እና ሊሸትት ጀመረ። እግዚአብሔር የአስተማረንን መልካም ነገር ልንደብቀው አይገባም። ለሌሎች ብናካፍለው እጥፍ በረከት ይሆንልናል።

ሰ. እግዚአብሔር ለተናገረህ ነገር ለመታዘዝ ጥረት አድርግ። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል። «ደስታህን ካጣኸው የመታዘዝ ሕይወትህን መርምር»። ለሚናገርህ ነገር በታዘዝኸው ቁጥር እርሱ ቃሉን አብዝቶ ይገልጥልሃል። ተቃራኒው ደግሞ እውነት ነው። የማትታዘዝ ከሆንህ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚስማማህ መሆኑ እየቀነሰ ይመጣል።

ኤር. 15፡16 «ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ፤ . . . ቃልህ ሐሤትና የልቤ ደስታ ሆነኝ»። ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል «በላው»። ይህም ልክ ጥሩ ምግብ እንደሚበላ በናፍቆት የጌታን ቃል አነበበው ማለት ነው። አላመጠው ማለትም ያሰላስለዋል። ብዙም ጊዜ ወደ አእምሮው መላለሰው። ዋጠው «የሕይወቱ ክፍል አደረገው።» ያም እርሱን ደስተኛና በምስጋና የተሞላ አደረገው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጢሞ. 2፡15 አንብብ። የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መያዝ አለብን? |

አምስተኛ ቀን፡- ይኼንን ክፍል በጥንቃቄ ደግመህ ከልስ። ወይም በግል በውይይቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖርህ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

አንድ ተማሪ ምረጥና ለጥሞና ጊዜ የሚያካፍለውን ቃል አዘጋጅቶ እንዲያመጣ አድርግ። አለበለዚያ የተለመደውን አሠራር ተከተል።

የመወያያ ርእሶች

1. በመጀመሪያው ቀን የተሰጡትን የሁለቱን ዓይነት የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሥልጠና በተመለከተ ተወያዩ። በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በሚገባ የሚሠራው የትኛው ነው? ሁለቱንም አሠራር መከተል ይቻላልን? የሚገኘው ጥቅምስ ምን ይሆናል?

2. ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት ትልቅ ሥራ ነው። በሚገባ ከተሠራ ግን ለቤተ ክርስቲያን የትምህርት ፕሮግራም ትልቅ በረከትና እርዳታ ሊሆን ይችላል። የሚያስፈልጉትን የትምህርት ዕቃዎች ለማዘጋጀትና ለማቅረብ ቤተ

ክርስቲያን አቀፍ ወይም ዲኖሚኔሽን አቀፍ የሆነ የሥርዓተ ትምህርት አውጪ ክፍል ስለሚቋቋምበት መንገድ ተወያዩ።

3. በእጃችሁ ስላለው የማስተማሪያ ቁሳቁስ በዝርዝር ተወያዩ። ምን ነገር ይጎድላል?

4. ስለ ግል የጥሞና ጊዜ ተነጋገሩ። ስለ ተማራችሁት አዳዲስ ነገሮች ተወያዩ። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፥ በማሰላሰልና በጸሎት ከጌታ ጋር ለመገናኘት እርስ በርስ መበረታታት አድርጉ።

# ትምህርት አሥራ አራት

# የጥናት ንዑስ ቡድኖች

## አንደኛ ቀን፡- የጥናት ንዑስ ቡድኖች ዓላማ በቤተ ክርስቲያን

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- የቤት ለቤት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተካፍለህ ታውቃለህን? በቡድኑ ውስጥ ስንት ሰዎች ነበሩ? የቡድንህ ዓላማ ምን ነበር? ምን አጠናችሁ? ዕድሉን ካገኘህ ሌላ የዚህ ዓይነት ቡድን ውስጥ ትካፈላለህን? የቤት ለቤት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጥናት ንዑስ ቡድን አንድ ዓይነት ናቸውን? አይደሉም ካልህ ልዩነታቸው ምንድን ነው? |

በዚህ ኮርስ ውስጥ ብዙ ጊዜ እንደተነጋገርነው ለአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን እንዲያውም በዓለም ሁሉ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ዓበይት ጉድለቶች ዋነኛ ፍላጎቶች አንዱ የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እና ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ ከዕለታዊ ኑሮ ጋር ማዛመድ አለመቻል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ መጽሐፍና ካርታችን እስከሆነ ድረስ አሸናፊ የክርስቲያን ኑሮን ለመኖር ልናውቀው ያስፈልገናል። የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንዲኖረን ልንጠቀምባቸው ከሚገቡ ዘዴዎች አንዱ የትናንሽ ቡድንና የኅብረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ናቸው።

1. የጥናት ንዑስ ቡድን ምንድን ነው? ለቤተ ክርስቲያንስ እንዴት ይረዳል?

የጥናት ንዑስ ቡድን ከ8-12 ሰዎች የሚገኙበት በየሳምንቱ በቤት ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት፥ ለመወያየትና ለጸሎት የመሰባሰብ ዓላማ ያለው ቡድን ነው። የዚህ ቡድን አባላት በቤታቸው በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። ንዑስ ቡድኖች ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ እንዲሰባሰቡ የሚያደርጉ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግና የተሳታፊዎቹ መሰጠት ጥልቀት እንዲያገኝ ቀጥተኛ ምክንያት ይሆናሉ። ብዙ የጥናት ንዑስ ቡድኖች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን ትንንሽ እንደሆኑ ማቆየቱ ግላዊ እንዲሆኑና የእያንዳንዱን ሰው ፍላጎቶችን እንዲያሟሉ ያደርጋቸዋል። ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት እና ለቡድኖች ጥቅም ሁሉም ቡድኖች ተመሳሳይ ጥናት ማጥናት አለባቸው። ይህም ደግሞ መበረታታትንና በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል የአንድነት ስሜትን ያመጣል።

2. የጥናት ንዑስ ቡድን ጥቅሞች

ሀ. የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ያግዛል።

የጥናት ንዑስ ቡድን አቀራረብ ሰዎች በትንሽ ቡድኖች ለመከፋፈል እንዲስማሙ ዕድል ይሰጣቸዋል። ሌሎቹን አባላት እርስ በርስ እየተዋወቁ ሲሄዱ ችግሮቻቸውንና የጸሎት ጥያቄዎቻቸውንም መከፋፈል ይጀምራሉ። በእግዚአብሔር ቃል በማጥናት ለችግሮቻቸው መፍትሔን ማግኘት ይጀምራሉ። ይህ ሁሉ ሳያቋርጡ ለመከፋፈል እንዲፈልጉ መበረታታትንና ጉጉትን ይፈጥራል። በተጨማሪም ለጓደኞቻቸውና ለጎረቤቶቻቸው በቡድኑ

ውስጥ እያገኙትና እየተደሰቱበት ስላለው በረከት መናገር ሲጀምሩ ሌሎቹም ወደ ጥናት ንዑስ ቡድኑ የመምጣት ፍላጎት ያድርባቸዋል።

ለ. የቤተ ክርስቲያንን የጸሎት አገልግሎት ያግዛል፤ ያስፋፋልም።

ትልቅ ቡድን በሳምንታዊ የጸሎት ፕሮግራም በሚገናኝበት ጊዜ የጸሎት ጥያቄዎቻቸውን የሚያቀርቡት ጥቂቶቹ ብቻ ይሆናሉ። እንዲሁም ጥቂቶች ብቻ ይጸልያሉ። በንዑስ ቡድን ውስጥ ግን እያንዳንዱ ተካፋይ የጸሎት ርእስ የመስጠት ዕድል ይኖረዋል። እንዲሁም ብዙዎች መጸለይ ይችላሉ። በተጨማሪም ሁሉም አባላት እርስ በርስ ስለሚተዋወቁ አንዱ ለሌላው ጓደኛው ልዩ ትኩረት በማድረግ በሳምንቱ ውስጥ በጸሎት ይረዳዋል። ይህም ማለት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጸሎቶች ወደ እግዚአብሔር ያርጋሉ ማለት ሲሆን፥ ስለ ወንጌል መስፋፋት፥ ስለ ግለሰቦችና ስላልዳኑ ሰዎች ይጸለያል ማለት ነው።

ሐ. ለውጥ በሚኖርባቸው ጊዜያት አመርቂ ውጤት ይኖረዋል።

የጥናት ንዑስ ቡድኖች ከቤተ ክርስቲያን እረኛና ሽማግሌዎች ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ባላቸው በሠለጠኑ ሰዎች ይመራሉ። በዚህም ምክንያት ስለ ቤተ ክርስቲያን አቋምና የወደፊት ዕቅድ ጥያቄ ሲኖር በቡድኑ ውስጥ ሊመለሱ ይችላሉ። ይህም ለሕዝቡ በአጠቃላይ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እየሠራ እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳል። ጥያቄአቸውን በትክክል በመመለስና የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች በትክክል ስለመያዛቸው እርግጠኞች እንዲሆኑ በማድረግ ይረዳቸዋል።

መ. መደበኛ ተሳትፎን ያበረታታል።

ብዙ ጊዜ በከተሞች አካባቢ ያሉ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያናት በየጊዜው ቁጥሩ የሚለዋወጥ ማኅበረ ምእመን ይኖራቸዋል። ሰዎች ለአንድ ወይም ለሁለት እሑዶች ይመጡና በሚቀጥለው ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ነገር ግን አንድ ሰው የጥናት ንዑስ ቡድን ውስጥ ገብቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በውይይት በጸሎትና በኅብረት የተካፈለ እንደሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የመቆየት አዝማሚያ እንደሚኖረው ታውቋል። ሰዎች እንደመጡ የሚመለሱበትን የጓለኛውን ድብቅ በር ይዘጋል።

ሠ. የዋስትናና የተፈላጊነት ስሜት ይሰጣል።

የጥናት ንዑስ ቡድኑ በግለሰባዊነት ጠባይ ምክንያት ለሰዎች የዋስትናንና የተፈላጊነትን ስሜት ይሰጣቸዋል። እያንዳንድ ሰው ዋስትናን ማግኘትና ተፈላጊ መሆንን ይፈልጋል። እያንዳንዱ ሰው በየሳምንቱ ወደ ትንሿ ቡድን መሄድ በማይችልበት ሰዓት ሌሎች ሊናፍቁት መቻላቸው፥ የተፈላጊነትን ስሜት ይሰጠዋል። በተጨማሪም በችግር ጊዜያት ሌሎች የቡድኑ አባላት ሲጠይቋቸው፥ ሲረዱቸው፥ ሲጸልዩላቸው፥ ለእነርሱ ግድ የሚለው ሰው እንዳለ ይሰማቸዋል። ይህ ለእያንዳንዱ ሰው በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይም በኅብረተሰቡ ውስጥ አዲስ ለሆኑ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ነው።

ረ. ሁሉም ቡድን አንድ ዓይነት ነገር ያጠናል።

ሁሉም ቡድን አንድ ዓይነት ነገር ማጥናቱ አስፈላጊ ነው። ይህም በጉባኤው ዘንድ የኅብረትና የአንድነትን ስሜት ይፈጥራል። ይህም ማለት እረኛውና ሽማግሌዎቹ በተጨማሪ ሕዝቡ ምን እየተማረ እንዳለ ስለሚያውቁ ትምህርቱን በአሑድ የአምልኮ አገልግሎት መደገፍ ይችላሉ። ይህም ማለት በጥናት ንዑስ ቡድኑ ውስጥ የተማሩትን ለመጥቀስ ስለሚችሉ ሕዝቡ የሚናገሩትን ነገር ተረድቶ እንደሆነ መገንዘብ ይችላሉ ማለት ነው።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፡- በጥናት ንዑስ ቡድኑ ውስጥ ልንጠቀምባቸው እንችላለን ብለህ የምታስባቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። ለዚህ ጉዳይ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የት.መ.ማ መጻሕፍት አሉን? በዝርዝር ጻፋቸው። ሌሎች የታተሙ ጥሩ የመጻሕፍት ጥናቶች አሉን? በዝርዝር ጻፋቸው። ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጥናት ተስማሚ ናቸው የምትላቸው አሉን? በዝርዝር ጻፋቸው። እነዚህ መረጃዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የጥናት ንዑስ ቡድኖችን ለማደራጀት በምትጀምሩበት ጊዜ በጣም የሚረዱዋችሁ ይሆናሉ። |

## ሁለተኛ ቀን፡- የጥናት ንዑስ ቡድኖች አመራር

I. እረኛውና የሽማግሌዎቹ ጉባኤ አመራር መስጠት አለባቸው።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጴጥ. 5፡1–4 አንብብ። ሽማግሌዎች ምን መሆን አለባቸው? በቁጥር 2 ላይ የተጠቀሱትን ሁለት ቃላት ተናገር። ሽማግሌዎች ማድረግ የሌለባቸውን ሦስት ነገሮች ጻፍ። ከዚያም ማድረግ ያለባቸውን ሦስት ነገሮች ጻፍ። ለታማኝ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምን ሽልማት ይጠብቃቸዋል? |

እንደገና እስኪ እግዚአብሔር ያወገዛቸውን የእስራኤል እረኞች ብቻ ጥቂት ባሕርያት ከሕዝቅኤል 34 እንመልከት። እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው።

- ለመንጋው ከመጠንቀቅ ይልቅ ለራሳቸው ይጠነቀቃሉ።
- ጮማውን ይበላሉ፤ ጠጉሩን ልብስ አድርገው ይለብሳሉ፤ የወፈሩትንም ያርዳሉ። ነገር ግን ስለ መንጋው ፈጽሞ ግድ የላቸውም።
- የደከመውን አላበረታቱም፤ የታመመውን አልፈወሱም ወይም የተሰበረውን አልጠገኑም። የባዘነውን አልመለሱም፤ የጠፋውንም አልፈለጉም።
- በኃይል እና በማስጨነቅ ገዙ። የዚህም ውጤት የመንጋው ሁሉ መበተንና ለዱር አራዊትም ምግብ መሆን ነበር። የእግዚአብሔር በጎች በተራራና በኮረብቶች ላይ ተቅበዝብዘው ነበር። ስለ እነርሱ ግድ ያለው ማንም አልነበረም። ስለዚህም እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እረኛቸው እንደሚሆን ተናገረ። እርሱ ወደ ስፍራቸው ይመልሳቸዋል፤ ይመግባቸዋልም፤ ንጹሕንም ውኃ ይሰጣቸዋል።

በቤተ ክርስቲያን ዘላቂና ቋሚ የሆነ በጸሎት የተሞላ አመራርን መስጠት የመጋቢውና የሽማግሌዎች ኃላፊነት ነው። ይህን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ?

ሀ. ባሪያዎች ሁኑ፡- 1ኛ ጴጥ. 5፡5 እንዲህ ይላል። «ሁላችሁም እርስ በርስ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ»። መሪዎች በራሳቸው ዙሪያ የራሳቸውን መንግሥት ወይም ደግሞ ስማቸውንና ታሪካቸውን ከፍ ለማድረግ ቢሞክሩ እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው አይችልም። የእርሱ ስለሆነ ክብሩን ለማንም ማካፈል አይወድም።

ለ. ንቁ፡- 1ኛ ጴጥ. 5፡8-9፥ «በመጠን ኑሩ፥ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና.... በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» ይላል።

ሐ. በእምነት የተሞላችሁ ሁኑ፡- ስኬታማ የጥናት ንዑስ ቡድኖች ያሏት ጠንካራ ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን አርቆ በመመልከት እንደሚፈጽመው በማመን ማድረግን ይጠይቃል። ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተወሰነ ግብ ልታበጅና እግዚአብሔርም እንደሚያከናውነው ልታምን ይገባታል። መሪዎች በስፋት ማሰብና ትልቅ እምነት ሊኖራቸው ይገባል።

መ. በሚገባ የተደራጃችሁ ሁኑ፡- የጥናት የንዑስ ቡድን አገልግሎት ሥራ ላይ እንዲውል በሚገባ መደራጀትን ይጠይቃል። የእያንዳንዱ የጥናት ንዑስ ቡድን መሪ መሠልጠን አለበት። ከዚያም ለእያንዳንዱ አምሳ የጥናት ንዑስ ቡድን ቤተ ክርስቲያን እረኛ መሾም አለባት። ይህ ሰው ተጠሪነቱ ለዋናው እረኛና ለሽማግሌዎች ሲሆን፥ የጥናት ቡድኖች አባላትን ለማበረታታት፥ ለማማከር፥ ለመጎብኘትና፥ እንዲሁም የቡድን መሪዎችንና የአባላትን ሥራ ለመመልከት የሚንቀሳቀስ ይሆናል።

ሠ. የምታበረታቱ ሆኑ፡- አንድ ልጅ ሲወለድ ሁለት ነገሮችን ማግኘት ይገባዋል። እነርሱም ምግብና የፍቅር እጆች ናቸው። ወላጆቹ እነዚህን ፍላጎቶች ካላሟሉለት ልጁ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ይራባል። ልክ እንደዚሁ ጎልማሶችም ጥሩ የሆነ መንፈሳዊ ምግብንና ፍቅርን ይፈልጋሉ። አዎን አካላዊ የፍቅር መግለጫንም በርግጥ ይፈልጋሉ። ነገር ግን በበለጠ የውስጥ ሕይወታቸውን የሚነካ ነገር ይፈልጋሉ። ይህ በሦስት መንገዶች ሊከናወን ይችላል።

1. እውቅና። መልካም አገልግሎት በግልም ሆነ በማኅበረሰብ ሊታወቅና ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ይህ ማለት ታማኝ የቡድን መሪዎችን ጀርባቸውን መታ መታ በማድረግ፥ «ይህን እንዴት አድርገህ ሠራኸው? በጣም ድንቅ ነው፤ እግዚአብሔር ይባርክህ» በማለት ይሆናል። ታማኝ አገልግሎትን በጉባኤ በማሳወቅ ወይም በተወሰነ ጊዜ የምስክር ወረቀት በመስጠት ሊሆን ይችላል። ለሁሉም የቡድን መሪዎች በዓመት ሁለት ጊዜ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት በመንፈስ በመመገብ፥ ችግሮቻቸውን ለመስማት ጊዜ በመስጠት፥ ለጥሩ ሥራቸው በማበረታታም ሊደረግ ይችላል። እነርሱም ሆነ ሥራቸው አስፈላጊ እንደሆኑ ማወቅ አለባቸው።

መጋቢዎችና ሽማግሌዎች እነዚህን በእረኝነት አገልግሎታቸው ሥር ያሉ የጥናት ንዑስ ቡድን መሪዎችን በግል ለማወቅ በሥራቸው ለማበረታታት ጊዜ መስጠት አለባቸው።

2. ማመስገን። ሁል ጊዜ የሌሎችን ጥሩ ማንነትና ሥራቸውን ለይቶ በማውጣት ስለ ሥራቸው ታላቅ ምስጋና ልንሰጣቸው ያስፈልጋል። ይህ በእርግጥ በሰዎቹ ልብ ውስጥ እሳትን ያቀጣጥላል። ማመስገን በጣም ጥሩ የሆነው የማነሣሻ መንገድ ነው። ይህንን ምስጋና ለመልካም ሥራ ከእውነተኛ ልብ የምንሰጠው መሆን አለበት።

3. ፍቅር። ሰዎችን ለማነሣሣት እውነተኛን ፍቅር ልንሰጣቸው ያስፈልጋል። ይህም በፊታችን አገላለጽ፥ በድምፃችን ቃላቴና፥ በተግባራችን የሚገለጽ ነው። ሰዎች ለእውነተኛ ፍቅርና ለጥቅማቸው ከሌሎች ለሚያገኙት እውነተኛ ትኩረት ምላሽ ይሰጣሉ።

ረ. በጥናት ንዑስ ቡድኑ አስፈላጊነት እመኑ። የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሽማግሌዎች የጥናት ንዑስ ቡድን ለቤተ ክርስቲያን የሞትና ሕይወት ጥያቄ ያህል አስፈላጊ በመሆኑ ማመን አለባቸው። ለአማኞች ሕይወት ጥልቀት፥ ለአዲስ አማኞች ትምህርትና በጣም ጥሩ በሆነ የወንጌል ስርጭት ሌሎችን ለመድረስ አገልግሎት አስፈላጊዎች እንደሆኑ ይቆጥራሉ። ሕዝቡ መሪዎቹ ለቡድኖች አስፈላጊነት ጥልቅ የሆነ ስሜት እንዳላቸው ማየት አለበት። ያለበለዚያ ቡድኖቹ ሊሞቱና ሊከስሙ ይችላሉ።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፦ ለመጋቢውና ለሽማግሌዎች ብቃት ከላይ የተጠቀሱትን አስፈላጊ ነገሮች ከተማርህ በኋላ የዚህ ዓይነት ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያንህ እንዲኖር ምን ዓይነት ለውጥ መደረግ አለበት ትላለህ? ምን ዓይነት ችግር ይገጥምሃል? ምን ተቃውሞ ይገጥምሃል? ይህን ፕሮግራም ማን ይቃወመዋል ብለህ ታስባለህ? እነዚህን ዓይነት መሰናክሎች ለመወጣት ምን ዓይነት ዘዴ አዘጋጅተሃል? |

## ሦስተኛ ቀን፦ የጥናት ንዑስ ቡድን መሪዎች ሥልጠና

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፦ የጥናት ንዑስ ቡድን መሪዎች እነማን ሊሆኑ ይችላሉ? ምን ዓይነት መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው? መጋቢ ወይም ሽማግሌ እንደመሆንህ መሪዎችን እንዴት አድርገህ ለሥራቸው በተሻለ መንገድ ማዘጋጀት ትችላለህ? |

1. የጥናት ንዑስ ቡድኑን የማደራጀት ደረጃዎች

ሀ. በትንሹ ጀምር። አሥራ ሁለት የሚሆኑ ቁልፍ መሪዎችን ምረጥና ለጥናት ንዑስ ቡድን መሪነት አሠልጥናቸው። የራሳቸው የሆነ የቤት የጥናት ቡድን ስብሰባዎች እንዲኖራቸው በማድረግ በጥንቃቄ ለስድስት ወይም ለስምንት ወራት ተከታተላቸው።

ለ. በጣም ጥሩ የሆኑትን መሪዎች ምረጥ። የቡድኑ ስኬታማነትም ሆነ ውድቀት በእነዚህ መሪዎች ይወሰናል። እነዚህ ሰዎች በመንፈስ የተሞሉ ሆነው ከዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል።

1. ጉጉት። ብዙ ጊዜ አዳዲስ አማኞች ጥሩ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ ልንል እንችላለን። ምክንያቱም ለአዲስ እምነታቸው ትልቅ ጉጉት አላቸው። ጉጉታቸውም የሚተላለፍና በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው።

2. መልካም ምስክርነት። እግዚአብሔር ስለ አደረገላቸው ነገር ግልጽና ኃይለኛ ምስክርነት ያላቸው ክርስቲያኖች ለወንጌል ዛሬም መሥራት ሕያው ማረጋገጫዎች ናቸው። ሕይወት በክርስቶስ ውስጥ እውነት እንደሆነ ያሳያሉ። ስለዚህም ሌሎች ወደ እነርሱ ይመጣሉ።

3. መስጠት። ለጌታ እና ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ናቸውን? የቤተ ክርስቲያንን ስብሰባዎች ያለማቋረጥ መካፈላቸው ለዚህ አመልካች ይሆናል፤ ደግሞም አሥራት የሚሰጥበት መዝገብ ይመሰክራል። ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብ ይረዳሉን? ሲሰጡስ በደስታ ነውን? ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ያለው መሰጠት እንዴት ነው። ታማኝና ደጋፊ ነውን? ወይስ ወቃሽና ፈራጅ?

4. በመንፈስ ቅዱስ ላይ መታመን። ያለጌታ ምንም ማድረግ የማይችል መሆኑን የተረዳ ነውን? ለማማከር፥ ለበሽተኞች ለመጸለይ፥ የቡድኑን ፍላጎት በጸሎትና በቃሉ ለመድረስ የሚችል መሆን አለበት።

5. ለማጥናትና ለመጸለይ ጊዜ ያለው። በጥናት ንዑስ ቡድን ውስጥ ያለ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ በብዙ ኃላፊነቶች መያዝ የለበትም። ለማጥናትና በጸሎት ጊዜን ለማሳለፍ ብሎም በእርሱ ቡድን ውስጥ ላሉት ሰዎች የፍቅር እንክብካቤን ለማድረግ ጊዜ ያስፈልገዋል። ደግሞም ችግሮችና ፍላጎቶች በሙሉ እንዲፈቱ በቂ የሆነ ገቢ እንዲኖረው ያስፈልጋል እንጂ ያለውን ኃይል ሁሉ በነዚያ ጉዳዮች ላይ ማዋል አይገባውም።

6. የጥናት ቡድኑን ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን። በአካል ውስጥ ሕዋሳት ሁልጊዜ እየተከፋፈሉ እድገትን እና መታደስን ያመጣሉ። በዚህ ዓይነት መልኩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የጥናት ቡድን መከፈል አለበት። በንዑስ ቡድኑ ውስጥ ትልቁ የአባላት ቁጥር 12 ወይም በጣም ከበዛ 15 ሊሆን ይገባዋል። ቡድኑ ከዚህ ቁጥር በላይ ካደገ የእያንዳንዱን ግለሰብ ፍላጎት ለማገልገልና ለመድረስ ያለው ነገር ሊቀንስ ይችላል። ስለዚህ መሪው ሁል ጊዜ በአእምሮው ውስጥ የመክፈል አሳብ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ቡድኑ ከዚያ ቁጥር በላይ በአደገ ጊዜ ወዲያውኑ መከፋፈል አለበት። አንዳንድ ጊዜ ለቡድኑ አባላት ይህ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም እርስ በርሳቸው መፈቃቀርንና መደናነቅን ተምረዋልና ነው። ለመለያየት አይፈልጉም። ይሁንና ለማደግ ጥቅም ሲባል እናም ለቡድኑ ጤንነት ሲባል መከፋፈል አስፈላጊ ነው።

7. የቡድኑ አገልግሎት አካል ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን። መሪዎች በአንድ ላይ ሥልጠና ይወስዳሉ። ለዚሁ ሥልጠና ለጸሎትና እርስ በርስ ለመበረታታት ይገናኛሉ። እናም ለዚያ ሥራ በተለይ በተሾመ መጋቢ ሥር ሆነው ይሠራሉ። መሪዎች አብረዋቸው ከሚሠሯቸውና በጌታ በላያቸው ከተቀመጡት ሰዎች ጋር በመስማማት ለመሥራት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው።

8. ለቡድኑ አባላት ለመጸለይና ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን እናም ለእነርሱ ጥሩ ሞዴል በመሆን ታሳያለህ።

ሐ. የጥናት ንዑስ ቡድን መሪዎችን አሠልጥን።

መጋቢውና ሽማግሌዎች የቡድኑን መሪዎች ማሠልጠን ይገባቸዋል። የትንሿ ቡድን አሠራር ምን እንደሆነ ማስተዋል አለባቸው። በዚህ በንዑስ ቡድን ስብሰባ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. <u>የአምልኮ ጊዜ</u>። ይህ መዝሙሮችንና አዝማቾችን በመዘመርና በመሪው ወይም በቡድን አባላት ጸሎት ሊካሄድ ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለው የቡድኑ አባላት ምስጋና በሚያቀርቡበት፥ ኑዛዜ በሚያደርጉበትና ለሌሎች በሚጸልዩበት ጊዜ ነው።

2. <u>አንዱ ሌላውን ስለማገልገሉ</u>። አባላት የጸሎት ርእስ ለመለዋወጥ ሊበረታቱና በርእሶቹም ጸሎት ሊደረግ ይችላል። እግዚአብሔር ጸሎትን ለመመለስ ይፈልጋል፤ በፈውስና በማንኛውም አቅጣጫ ለአባላት ሕይወት ተሐድሶ እንዲኖር ይፈልጋል።

3. <u>ወንጌልን ማሰራጨት</u>። የሰውን በር እየዞሩ ከማንኳኳት ይልቅ ብዙ ጊዜ ውጤታማ የሆነ የወንጌል ስርጭት በጥናት ቡድን ውስጥ ሁሉ ሊካሄድ ይችላል። አባላት ለጎረቤቶቻቸው ፍቅርንና እንክብካቤን በማሳየት ሌሎች ወደ ጥናት ቡድኑ እንዲመጡ ሊጋብዙዋቸውና ቃሉን ሊሰሙ፥ የተካፋዮቹን ደስታ በማየት ወደ ጌታ ሊሳቡ ይችላሉ። አባላት ምስክርነታቸውን በሚያካፍሉበት ጊዜ ያልዳኑትን ሰዎች ወደ ጌታ ለማምጣት ትልቅ ተጽዕኖ ያደርጋሉ።

4. <u>የእግዚአብሔር ቃል ጥናት</u>። ለጥናት ቡድኑ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያስጠኑበት ጊዜ ለቡድኑ መሪዎች የሚጠቅሙ ውጤታማ መረጃዎችን መጋቢውና ሽማግሌዎች ሊያቀርቡላቸው ይገባል። ይህ አስፈላጊ ነው። የትምህርት መረጃው ተግባራዊ መሆን አለበት። የጊዜው ጉዳይ ሊሆን ይገባል። እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን የመድረክ አገልግሎት ጋር የተዛመደ መሆን አለበት። ጥበባዊ መንገድን የተከተለ የተመረጠውን ክፍል ቁጥር በቁጥር የሚያስጠና ወይም በጊዜው አስፈላጊ ይሆናል ተብሎ በታሰበ ርእስ ላይ በሚገባ የተዘጋጀ ጥናት ሊሆን ይገባል። እናም ሁሉም የንዑስ ቡድን አባላት አንድ ዓይነት ጥናት ማጥናት አለባቸው።

5. <u>ጥቅሶችን በቃል ማጥናት</u>። የእግዚአብሔርን ቃል ከማጥናት ጋር መሪዎች የጥቅስ የቃል ጥናትን መምራትና ማበረታታት አለባቸው። ዳዊት ሲናገር፥ «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ. (119):11] ብሏል።

6. <u>የስብሰባው ጊዜ መወሰን አለበት</u>። ለጥናት ንዑስ ቡድኑ ቶሎ ቶሎ መሮጥና መጨረስ ቀላል ነው። የተለየ ሁኔታ ላለበት ቀን ትንሽ መዝናኛ ማድረግ ለንዑስ ቡድኑ ምንም አይደለም። ነገር ግን ምግብንና መጠጥን ማስተናገድ ለንዑስ ቡድኑ ዓላማ የማሰናከያ ድንጋይ ሊሆን ይችላል። ደግሞም የተሻለ ምግብ ለማቅረብ በመሐከላቸው ውድድር እንዲኖር

ያደርጋል። ስለዚህ ሰዎች የሚገናኙበትን ሰዓት መወሰን ጥሩ ነው። ብዙዎች በሥራ የተወጠሩ ናቸው። ስለዚህም እረፍትን እና ከቤተሰባቸው ጋር መሆንን ይፈልጋሉ። ስለዚህ የሰዓት ገደብ ሊደረግ ይገባል። ስብሰባው በሚገባ ከታቀደ አንድ ሰዓት ወይም አንድ ሰዓት ተኩል ይበቃል።

7. <u>የስም መጥሪያ መዝገብ ሊቀመጥ ይገባዋል</u>። የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ በዚህ የንዑስ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ መበረታታት አለባቸው። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ግዴታ ነው። በፈቃደኝነት ከሆነ የቤተ ክርስቲያን አባሎች የጥናት ቡድኖችን ዋጋ ይረዱ ዘንድ ስለ ጥናት ንዑስ ቡድኑ ሪፖርቶችንና ምስክርነቶችን መስማት አለባቸው። እንዲገቡም ሊገፋፉቸው ይችላል።

መ. የመሪዎች ሥልጠና የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

1. የሚቻል ከሆነ እያንዳንዱ የንዑስ ቡድን መሪ ሌላ ሰው በሚመራበት ቡድን ውስጥ ጊዜን ያሳለፈ መሆን አለባት። ይህም ለእርሷ/ ለእርሱ የመጀመሪያ ልምድ ይሆንላቸዋል።

2. በዓመት አራት ጊዜ በተለያዩ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ላይ ውይይት ለማካሄድ ስብሰባ መደረግ አለበት።

3. መሪዎች ከመጋቢያቸውና ከሽማግሌዎች ጋር የሚገናኙበትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ወቅታዊ መረጃና ዕቅድ እንዲያውቁ የሚደረግበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። በቤተ ክርስቲያን ስላሉ የጸሎት ጥያቄዎችና የምስጋና ርእሶች ጉዳዮች በየጊዜው ሊነገራቸው ይገባል።

4. ለጥናት ንዑስ ቡድኑ የሚሆን መመሪያ ለመሪዎች መቅረብ አለበት። ማንበብና መረዳት ግን የእነርሱ ኃላፊነት ነው።

5. መሪዎቹ የጥናት ቡድኖችን ለመምራት በሚገባ ለመዘጋጀት በቂ ጊዜ መውሰድ አለባቸው።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፦ ስለ ንዑስ ቡድን ባጠናህ ጊዜ ያስተዋልካቸውን ጥቅሞች መዝግባቸው። ስላለህበት ማኅበረ ምእመን አስብ። በእንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም የሚያስፈልጋቸውን መሠረት በሕይወታቸው ማግኘት የቻሉ ሰዎች አሉን? ይህ ፕሮግራም ወጣቶችን ያገለግላልን? በምን መንገድ? ለባለ ትዳሮች ያገለግላልን? በምን መንገድ? ለሽማግሌዎች ይህ ይረዳልን? በምን መንገድ? በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ከጥናት ንዑስ ፕሮግራም ጥቅም ሊያገኝ ያልቻለ ሰው አለን? እነማን ይሆኑ? |

## አራተኛ ቀን፦ የጥናት ንዑስ ቡድኖችን ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

በቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በጥናት ንዑስ ቡድን መካከል ብዙ ተመሳሳይነቶች አሉ። ይሁንና የጥናት ንዑስ ቡድኑን የተለየ የሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች አሉ።

1. የውይይት አመንጪ

እያንዳንዳቸው በጥናት ንዑስ ቡድን ውስጥ ያሉ አባላት የጥናት መጽሐፍ ወይም ማስታወሻ ስላላቸው ወደ ስብሰባ ከመምጣታቸው በፊት

አንብበው ሊዘጋጁ ያሻል። በዚህ መንገድ አባላቱ በሚሰበሰቡ ጊዜ ተሳትፎ ለማድረግ ተዘጋጅተው ይመጣሉ። መሪው ሊያስተምር አይመጣም። ነገር ግን በዚያው ምትክ ለውይይት ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ጥሩ ጥያቄዎችን ሊያዘጋጅ ወይም አባላቱ አሳብን እንዲያመነጩ ሊያነሣሣ ይችላል። ግን እርሱ አስተማሪ አይደለም። ቡድኑ ትንሽ እንደመሆኑ አባላት ከአሥራ ሁለት ባይበልጡ ጥሩ ነው። ያኔ እያንዳንዱ አባል የራሱን ድርሻ ለመናገር ዕድልን ያገኛል።

2. ማሰብ ይበረታታል

አባላት የሚያስጨንቃቸውን ጥያቄ ሁሉ የመጠየቅ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። መልስ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌሎች አባላትና በመሪው መፈለግ አለበት። ይህም ብዙ ጊዜ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይም በመደበኛ ስብሰባ ጊዜ ሊጠይቁት የማይችሉትን ከባድና አስቸጋሪ ጥያቄ ሊያስተናግድ ይችላል። ቡድኑ በቁጥር ትንሽና የሚረዳዳ ስለሆነ፥ ጥልቅ የሆነ የያገባኛል ስሜትን ለማካፈልና ለመወያየት ይችላል። ይህም ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲበስሉ ይረዳል።

3. የማይጎዳ መድረክ

የንዑስ ቡድኑ ያለ ጭንቀት አባላት ይሳተፉ ዘንድ በቁጥር ትንሽ ነው። መተማመንና መቀራረብ አድጎ ልብ ለልብ የሆነ ግንኙነት ይፈጥር ዘንድ ተስፋ ይደረጋል። ይህ ከአባላቱ ማንነት የተነሣ ሁልጊዜ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ለአንዳንድ የተጎዱ ሰዎች ብዙ ጊዜ ፈውስ ሊሆን ይችላል።

4. በአንድ ዓይነት ቡድን ውስጥ በቂ የሆነ ጊዜ

ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ክፍሉ ለተወሰኑ ሳምንታት ይቀጥላል። ኮርሱ እንዳለቀም ወዲያው ይዘጋል። በጥናት ንዑስ ቡድኑ ውስጥ ግን ይህንኑ ቡድን ቢያንስ ለዓመት ምናልባትም በገና ጊዜ እና ረዘም ላሉ የእረፍት ጊዜያት ቢቀጥል ጥሩ ነው። ይህም አንዱ በአንዱ ላይ መተማመን እንዲኖረው ጊዜን ይሰጣል። ቡድኖች ሲከፋፈሉ አዳዲስ ሰዎችን የመገናኘት ዕድል ይሰጣል።

5. በዓላማ መከፋፈል

የጥናት ቡድኑ አጠቃላይ ግቡ ቡድኑን በመከፈል ሁለት ቡድን ማድረግ ነው። ይህ ለመሪውም ሆነ ለአባላቱ ቀላል ነገር አይደለም። እኛ ሁላችን ትልቅን ነገር የመምረጥ ባሕርይ አለንና። ይህም ብዙ ጊዜ የመሪውንና የአባሎችን የእኔነት ስሜት ያነሣሣል። አንድ ጊዜ የቡድኑ ቁጥር እስከ 12 ደረጃ ከደረሰ በፍጹም ከእንደገና የእያንዳንዱን አባላት ተሳትፎ የማድረግ የመጀመሪያ አሳብ ሊፈጽም አይችልም። በምትኩም የራሱን ክልል በአዲስ ሰዎች ላይ በመፍጠር ጥቂት ተናጋሪ ሰዎች ውይይቱን ሁሉ በቁጥጥር ሥር ያደርጉታል። አንድ ሰው ከቡድኑ ውስጥ ከቀረ የሚፈልገው ሰው አይኖርም፤ ምክንያቱም ገና በቂ የሆኑ ሰዎች በቡድኑ ውስጥ አሉና የመከፋፈል ግብ ዓላማችን ውስጥ መኖር አለበት።

6. «የዕለታዊ የጥሞና ጊዜ» ይዘት

የጥናት ንዑስ ቡድኑ አባላት ጥበባዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አነባበብን ያዳብሩ ዘንድ ለመርዳት የዕለታዊ የጥሞና ጊዜን ይሄል። በሳምንት ውስጥ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን አባላት ብቻ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንደሚያነቡ ማወቁ አስደናቂ ነው። በአንዳንድ ባህሎች ጠዋት ከአልጋ ተነሥቶ ከመውጣት በፊት መጸለይ የተለመደ ነገር ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ጊዜ አይወስዱም። በጥናት ንዑስ ቡድን ውስጥ ማንኛውም አባል በእያንዳንዱ ቀን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነብ ይበረታታል፤ እናም ከንዑስ ቡድኑ የተቀበለውን ጥቂቱን በረከት እንዲያካፍል ዕድልን ይሰጠዋል። ሁሉም አንድን ክፍል እስከ አነበቡ ድረስ እያንዳንዱ ከዚህ ካየው ነገር ጥቅምን ሊያገኝ ይችላል።

7. ፍላጎትን ያገናዘበ የጥናት ጽሑፍ

የጥናት ጽሑፍ አባላት ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ፍላጎታቸውን የተከተለ ነው። በዚህ ኮርስ ውስጥ በጥብቅ ያየናቸው ሁለት ነገሮች የእኛ ማስተማርና መስበክ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ጥሩ መሠረትን የሚሰጥ መሆን እንዳለበት ነው። ደግሞ በዕለታዊ ኑሮአችን ውስጥ መተግበር አለበት። በተግባር ላይ ካልዋለ እውቀትን መጨመር ብቻ ይሆንብናል። ያም የሚመግበው እኔነትን ብቻ ነው። እናም የትዕቢትን ችግር ይፈጥራል። ቅዱሳት መጻሕፍት በዕለታዊ ኑሮአችን ማለትም በሥራ ቦታችንና በቤት ብሎም በኅብረተሰቡ ውስጥ መተግበር አለባቸው።

8. በሥርዓት የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል

የጥናት ንዑስ ቡድኑ በዓላማ የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል ይኖረዋል። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እየተሰጠ እንደሆነ ያረጋግጣል። ምንም እንኳን ጊዜው ለሚመነጩ ጥያቄዎች የመወያያ ጊዜ ቢሆንም አለማወቅ እያበዛ መሄድ የለበትም። «ይመስለኛል» የሚሉትን አደገኛ ዓረፍተ ነገሮችን ከመጠቀም ልንጠነቀቅ ይገባል። ይልቁኑ የተማርነውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረት አለብን።

9. ለአዲሶች ቀላል የመግቢያ በር

ምንም እንኳን ከረጅም ዕረፍት በኋላ የሚጀምሩ ቢሆንም፥ የንዑስ ቡድኑ መሪና የአባሎች ልብ አዲስ አባልን በማንኛውም ሰዓት ወደ ቡድኑ ለማስገባት የተዘጋጀ መሆን አለበት። አንድ አዲስ ሰው ከመጣ መቀበልና በአግባቡ ማስተናገድ ያሻል። የማጥኛ ጽሑፎችን /መጻሕፍትን መስጠትና ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ የቡድኑ ዓላማ ተብራርቶለት ቡድኑ እንዲዋሃደው ያስፈልጋል። ይህም ሊሆን የሚችለው ቡድኑን ትንሽ አድርጎ ከ5–6 በሚደርስ ቁጥር በመጀመር ለዕድገትም ቦታ በመተው ነው።

10. የውይይት ጸሎት

ብዙ ጊዜ አዲስ አማኞች ወይም እንግዶች አንድ ሰው ረጅምና የተቀነባበረ ጸሎት ለዓለም ሁሉ ቢያደርግ ሊቸገሩና ጥሩ ስሜት ላይሰማቸው ይችላል። የውይይት ጸሎት አጭርና በተወሰነ ርእስ ላይ ሊያተኩር ይገባል። ከዚያም አንድ ሰው አጭር ጸሎት እንደዚያው ይጸልያል። ይህ አዲስ

አማኞች የሚባለውን ባለማወቅ እንዳይቸገሩና እንዳይሰማቸው ያበረታታቸዋል። አንድ አባል ከፈለገ ብዙ ጊዜ መጸለይ ይችላል። ነገር ግን በየጊዜው አጭር ጸሎት መጸለይ አለበት።

11. ጥቅስን በቃል ማጥናት

ለንዑስ ቡድኑ በታቀደው የጥናት ጽሑፍ ውስጥ በቃል የሚጠኑ ጥቅሶች ሊካተቱ ያስፈልጋል። በቃል ማጥናት ታላላቅ እውነቶችን ለማዋሐድ ጥሩ መንገድ ነው። በሚያስፈልግበት ጊዜ ለሰዎች የሚረዳ ይሆናል።

12. እያንዳንዱ የጥናት ጊዜ ልንቆጣጠረው የምንችለው ሰዓት ይኑረው።

ቡድኑ ፕሮግራሙን በሰዓቱ ማቆም አለበት። እናም ስብሰባው መራዘም የለበትም። የጥናቱ ንዑስ ቡድን የመጨረሻው ረጅም ሰዓት 1 ሰዓት ተኩል ነው። አንዳንዶች ከስብሰባው በኋላ ለኅብረት ሊቆዩ ከፈለጉ ይችላሉ። ይሁንና ስብሰባው ከአንዱ ወደ አንዱ የሚሸጋገር ባይሆን ጠቃሚ ነው። ደግሞም ከስብሰባው በኋላ በየጊዜው እዚያው የመቆየት ነገር የአንዳንዶች ልማድ መሆን የለበትም። ስብሰባውን ለሚያስተናግዱ ማለትም ቦታቸውን ለሰጡን ግድ ሊለን የተገባ ነው።

13. የስብሰባውን ቦታና ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ መወሰን

የጥናቱ ንዑስ ቡድን ስብሰባ የሚካሄደው የት መሆን አለበት? ይህ አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ቦታዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ሊሆኑ ይገባል። ምናልባት የቢሮ ጸሐፊዎች በመሥሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በምሳ ሰዓታቸው ሊሰበሰቡ ይችላሉ። ነጋዴዎች ሁሉም በሚመቻቸው አማካይ ቦታ ጠዋት ጠዋት ሊሰበሰቡ ይችላሉ። የቤት እመቤቶች ደግሞ ልጆቻቸው ወደ ት/ቤት በሄዱበት ጊዜ ቀን ስብሰባን በቤት ውስጥ ሊያደርጉ ይችላሉ። በየሳምንቱ በምሽት የሚገናኙ ቡድኖች ስብሰባቸውን በቤት ውስጥ ሊያደርጉ ይችላሉ። አንዳንድ ቡድን ድብልቅ ሊሆን ይችላል። አንዳንዱ ደግሞ ወንዶች ብቻ፥ ሴቶች ብቻ ወይም ወጣቶች ብቻ ያሉበት ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ክፍሎች ውስጥ መሰባሰብ ይቀላል።

14. ለቤተ ክርስቲያንና ለዓላማዋ የተሰጡ መሪዎች

የንዑስ ቡድኑ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የአገልግሎት ፍልስፍና የተሰጡ ናቸው። በጥንቃቄ የተወሰዱና የበሰሉ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። የጥናት ንዑስ ቡድኑ እንደ ክርስቲያን ለማደግ ፍጹም የተመቻቸ ከመሆኑም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለማርገብ ከሁሉ ከተሻሉ መንገዶች አንዱ ነው። ትናንሽ ችግሮች ወደ ትልልቅ ችግሮች የሚለወጡበት ዋናው ምክንያት ለሰዎች ተቃውሞ አዳማጭ ስለሌለ ነው። የተሳሳቱ ግንዛቤዎችና እርግጠኛነት የጎደላቸው ጉዳዮች ውስጥ ስለሚገለጡ ጥሩ የሆነው የቡድን መሪ ሊያብራራ ወይም የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም ሽማግሌ መጥቶ ግለሰቡን እንዲረዳው ሊያደርግ ይችላል። በዚህ ዓይነት መንገድ የጥናት ንዑስ ቡድን ሰዎቹ የሚሰማቸው ነገር እንዲደመጥና ጉዳዮቻቸው እንዲብራሩ ሳምንታዊ ዕድልን ይሰጣል።

15. አንድ ወጥ ሥርዓተ ትምህርት

በቡድኖች መካከል ግንኙነት እንዲዳብር የጥናት ንዑስ ቡድኖች ሁሉ አንድ ዓይነት ጥናት ያጠናሉ። አስፈላጊ ከሆነም አባላት ከአንዱ ቡድን ወደ ሌላው ቡድን የመዛወር እንቅስቃሴ ያመቻቻል። ለምሳሌ አንድ ሰው ያለበትን ስፍራ ቢቀይር በዚያ አካባቢ ወደ ሌላ ቡድን ሊገባና ያን ቀድሞ ያጠናው የነበረውን ሥርዓተ ትምህርት መቀጠል ይችላል።

---

7ኛ ጥያቄ፦ ዛሬ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ካለ ከአንድ ሰው ጋር ከምትነጋገርባቸው ጉዳዮች አንዱ የጥናት ንዑስ ቡድንን ጉዳይ ይሁን፤ የተማርካቸውን ዋና ዋና ነጥቦችን ማውጣት እስክትችል ድረስ እነዚህ አራት ትምህርቶች በበቂ ሁኔታና በጥንቃቄ አጥና። ያነጋገርኸው ሰው ለዚህ አዲስ አሳብ ያለውን ምላሽ ጻፍ።

---

አምስተኛ ቀን፦ በጥናት ንዑስ ቡድኖች ላይ የተሰጠውን ይህን ትምህርት ከልስ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የዚህን አቀራረብ ድክመትና ጥንካሬ በትክክል አስብ። ለመወያያ ጥያቄዎችም ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ርእሶች

1. በንዑስ ቡድኖች ጥቅም ላይ ተወያዩ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ችግር ሊፈታ የሚችል ፕሮግራም ነውን? ከዚህ ብዙ የሚጠቀመው ማን ነው? እንዲህ ዓይነት ፕሮግራም ለመጀመር እነማን ይሳተፋሉ? ሥልጠና የሚያስፈልገው ማን ነው?

2. አሁን ያሉህን አንዳንድ ፕሮግራሞች የጥናት ንዑስ ቡድኖች ሊተኩት ይችላሉን? አሁን ካለህ ፕሮግራም ይልቅ እነርሱ አባሎችንና ለማሳደግ የበለጠ ተግባር ያከናውናሉን? በምን መንገድ?

3. የጥናት ንዑስ ቡድኖችን ለመጀመር አሁን ባለው የአስተዳደር መርህ ምን ዓይነት ለውጥ መደረግ አለበት?

## ትምህርት አሥራ አምስት

## የወንጌል ስርጭትና ሌሎችን መድረስ

### አንደኛ ቀን፦ ወንጌላዊ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይ ለመረዳት የምንፈልገው ስለ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የወንጌል ስርጭት ነው። በመጀመሪያ የምንወያየው ሌሎችን ለመድረስ በምንፈልግበት ጊዜ ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለብን ይሆናል። ከዚያም እንዴት መመስከር እንዳለብንና በምንመሰክርበት ጊዜ ሊያጋጥሙን ስለሚችሉ ችግሮች እንወያያለን። በመጨረሻም አዲስ ለተለወጡ ሰዎች ክትትል ስለማድረግ እንነጋገራለን።

1. ወንጌላዊው በጌታ ይመራል።

እያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚከበርበትን ሕይወት የመኖርና ለጌታ እውነተኛ አምባሳደር የመሆን ኃላፊነት አለበት። አንዳንዶቻችን እንዲህ ብለን እንጠይቃለን፤ «ያንን እንዴት ላደርግ እችላለሁ?» ለመልሱ እስኪ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከኢየሱስ ጋር ስላስተዋወቀው ስለ ፊልጶስ ሕይወት እንመልከት።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- የሐዋርያት 8፡26-38 አንብብ። ከዚህ ምንባብ ስለ ምስክርነት የተማርካቸውን ቢያንስ አራት ነገሮች ጻፍ። |

ሀ. የፊልጶስ ሕይወት ጥሩ ምስክር ነበር።

ፊልጶስ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላበት ሰው ተብሎ ለዲቁና ተመርጦ ነበር (የሐዋ. 6፡3)። አዲስ በተወለዱ ሰዎች ሕይወት ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይኖራል፤ ነገር ግን በሕይወታችን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ መሥራት ይችለው ዘንድ በየቀኑ ራሳችንን በመመርመርና ኃጢአታችንን በመናዘዝ ከእግዚአብሔርም ይቅርታን በመጠየቅ ሕይወታችንን ከኃጢአት መጠበቅ አለብን (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። ከአንድ ሰው ጋር ተጣልተን ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ነገሮችን ካስተካከልን በኋላ ከተጣላነው ሰው ጋር ነገሮችን ማስተካከል አለብን። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ሙሉ ለሙሉ ይቆጣጠረን ዘንድ ራሳችንን ለእርሱ መስጠት አለብን። እርሱ የማስተማርን፥ የመምራትን፥ ጥበብ የመስጠትን፥ የመገሰፅን፥ በኃይል የመሙላትን ሥራ በሕይወታችን የሚሠራው ያን ጊዜ ብቻ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ያለ ሕይወት እግዚአብሔርን ያከብራል፤ ደግሞም ለዓለም ኃይለኛ ምስክር ይሆናል።

ለ. ፊልጶስ ለመንፈስ ቅዱስና ለጌታ ምሪት ንቁ ሆኖ የተዘጋጀ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 8፡26 የእግዚአብሔር መልአክ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚወስደው መንገድ እንዲሔዱ እንደነገረውና እርሱም ያን እንዳደረገ ይነግረናል። በመታዘዝ፥ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለመገናኘት ተመራ። እንደገና በቁጥር 29 መንፈስ ፊልጶስን፥ «ወደዚያ ሠረገላ ሂድና ትንሽ በዚያ ቆይ» በማለት ተናገረው። ወዲያው ፊልጶስ ወደ ሰረገላው ሮጠ። ከዚህ በፊት ተገናኝቶት የማያውቀውን ሰው ለመገናኘት ድፍረት ተሰጥቶት ነበር።

ሐ. ፊልጶስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያውቅ ነበር።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከኢሳይያስ 53 ያነብ የነበረ ሲሆን፥ ፊልጶስም አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ ጠየቀው። ፊልጶስ ያንኑ ምዕራፍ በመውሰድ በትንቢታዊነት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት ከሚያወራው ከዚህ ክፍል ተነሥቶ ስለ ኢየሱስ የምሥራቹን ዜና አበሰረው። በክርስቶስ ኢየሱስ ስላለው ደኅንነትና ስለ ጥምቀት ሳይነግረው አልቀረም፤ ምክንያቱም ወዲያውኑ ሰውየው ለመጠመቅ ሲጠይቅ እናያለን። ሰውዬው በክርስቶስ ስለማመኑ በሰጠው የአፍ ምስክርነት መሠረት ፊልጶስ አጠመቀው።

መ. ፊልጶስ እርሱ እንደ መሣሪያ ብቻ መሆኑን ተገንዝቦ ነበር። በዚያ ጃንደረባ ልብ ውስጥ ወደ ደኅንነት ያመጣው ዘንድ ሥራውን የሠራው እግዚአብሔር ነበር።

ይህ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ወዳለው እምነት ይመጣ ዘንድ እግዚአብሔር ሁሉን አዘጋጅቶ ነበር። ኢሳይያስ 53ን እንዲያነብ ያደረገውና ፊልጶስን በትክክለኛው ወቅት ልኮ መልእክቱን በግልጽ እንዲያብራራለት ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነበር።

ለሕዝቡ ፍቅር ባላቸው፥ ለዘላለማዊ ፍጻሜያቸው ግድ የሚላቸውና የጠፉትን ለመፈለግ ማንኛውንም ጥረት ለማድረግ በሚፈቅዱ ታዛዥ አገልጋዮቹ አማካኝነት እንደሚሠራ ልብ ልንል ያሻል።

---

2ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 41፡10 አንብብ። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተሰጠው ዋስትና ምንድን ነው? 1ኛ ቆሮ. 1፡26-32 አንብብ። ከመመስከራችን በፊት ሁሉንም ልናውቅ ይገባናልን? ምን መናገር እንዳለብን ለማወቅ ጥበብ የሚሰጠን ማን ነው? ክብሩ የሚሆነው ለማን ነው? ፊልጵ. 4፡13 ደግሞ አንብብ። ጥንካሬን የሚሰጠው ማን ነው? ይህ እውነት ለኩራትና ለትዕቢት ዕድል ይሰጣልን? 1ኛ ቆሮንቶስ 4፡7 ደግሞ አንብብ።

---

2. ወንጌላዊውን ጌታ ያስችለዋል

እግዚአብሔር ለወጣቱ ለኤርምያስ እንዲህ አለው፤ «በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ»። ኤርምያስ በመገረም እንዲህ አለ፤ «እነሆ፥ እኔ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም» (ኤር. 1፡4-6)። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ትልቅ ሥራ እንዳለው እርግጠኛ አደረገው እንዲህ በማለት አረጋገጠለት፤ «እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ . . . እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ፥ እግዚአብሔርም፦ እነሆ፥ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ» አለ (ኤር. 1፡8፥9)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ኤርምያስ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ታላቅ ነቢይ ነበር። ታሪኩን በኤርምያስና በሰቆቃወ ኤርምያስ መጻሕፍት ውስጥ ማንበብ ትችላለህ።

3. ወንጌላዊ በፍቅር መነሣሣት አለበት

1ኛ ቆሮ. 13፡4-7 የእግዚአብሔርን የፍቅር ባሕርይ ተግባራት ያብራራል። ለእርሱ በተሰጠን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ፍቅር ከሕይወታችን ውስጥ መፍሰስ ይጀምራል።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፦ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-7 ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የፍቅር ገጽታዎች ጻፍ። ስለተለያዩት የፍቅር መግለጫዎች አሰላስል። ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት የደከምህበትን ወይም የጎደልክበትን ቦታ ጻፍ። ከዚያም ለሌሎች ሰዎች ተጨማሪ ፍቅርን ለማሳየት ምን መሥራት እንደምትችል ጻፍ። |

ሰዎች በጣም እንደምንወዳቸውና ስለ ዘላለማዊ ፍጻሜያቸው ግድ እንደሚለን በአወቁ ጊዜ እግዚአብሔር ለእነርሱ ታላቅ ፍቅር እንዳለው መገንዘብ ይጀምራሉ። እነርሱ ይህን በሕይወታችን ምሳሌነት ውስጥ ተገልጦ ሊመለከቱ ይሻሉ።

4. ወንጌላዊ ወደ ጌታ ቀርቦ መኖር እንዴት እንደሚችል

ሀ. በየዕለቱ በጸሎት እና ቃሉን በማጥናት ከጌታ ጋር የሚሆንበትን መደበኛ ጊዜ ማዘጋጀት።

ለ. በግል ሕይወትህ የሚያስፈልግህን መንፈሳዊ ነገር ለይ።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስን በተከታታይ ባነበብህ ጊዜ በሕይወትህ ውስጥ ላለው ድክመት እርዳታን ታገኛለህ።

መ. ለመነቃቂያ፥ ለእርማትና ለምሪት በየቀኑ ይህንን ምንባብ አሰላስለው፤ በቃልህም አጥናው፤ መዝ. (119):59-60 አንብብ።

ሠ. የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለይተህ ለመታዘዝ የነቃህ ሁን።

ረ. ምስክርነትህን ልታካፍል ከምትችልበት ከጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነትን መሥርት፤ ያንንም አጽና።

«ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን» (ቆላ. 4:6)። ማንኛውም ለጌታ ለመመስከር የሚፈልግ ሁሉ ለጌታ በመታዘዝ ሊኖር ይገባዋል። ለጥበብ በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍና ሰዎችን በፍቅር በመድረስ መኖር አለበት።

ሁለተኛ ቀን፡- መልእክቱ

ለጌታ ለመመስከር ብዙ መንገዶች አሉ። ከፊልጶስ ታሪክ እንዳየነው ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎች በሚያነሡት ጥያቄ ወይም አሳብ ምክንያት በሮችን ይከፍትልናል። የእኛ ድርሻ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጥንቁቅ እና ክፍት መሆን ነው።

ሆኖም እኛ ራሳችን አንድ ሰው ክርስቲያን እንዲሆን ምን ማወቅ እንዳለበት ግልጽ የሆነ አሳብ እንዲኖረን መዘጋጀት አለብን። ፊልጶስ ግልጽ ባልሆኑ አባባሎች አልተናገረም። ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ያነበው የነበረውን ምንባብ ወሰደ። ከዚያው ከኢሳይያስ 53 ስለ ስቅለቱ ከሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መረዳትና እንደ አዳኙ የመቀበልን አስፈላጊነት እንዲያውቅ መራው። ከዚያም በጥንቃቄ ስለ ጥምቀት አስረዳው።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- ላልዳኑት በምትመሰክርበት ጊዜ የተጠቀምህባቸውን ቢያንስ ሁለት ዘዴዎች ጻፍ። የቀድሞ ሃይማኖታቸው ምን ነበር? ለምስክርነትህ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተው ነበርን? እስከ አሁን ስለ እነርሱ እየጸለይህ ነውን? |

I. አንድን ሰው በክርስቶስ ወዳለ እምነት ለመምራት የተሰጡ ዘዴዎች

ሀ. አንዱ ሰውን ወደ ክርስቶስ የመምራት ዘዴ በትምህርት አምስት 4ኛ ቀን ትምህርት <u>ልጅን ወደ ክርስቶስ መምራት</u> በሚለው ርእስ ውስጥ ተብራርቷል። ይህ ዘዴ 5 ቀላል ዘዴዎችን በቅደም ተከተል የሚገልጹ እውነቶችን አካትቷል።

- እግዚአብሔር ይወደዋል (ዮሐ. 3:16)።
- ኃጢአተኛ ነው (ሮሜ 3:23፥ ሮሜ 3:10-18)።

- ኢየሱስ ለኃጢአቱ ሞቶለታል (ሮሜ 5:8፤ ዮሐ. 1:7)።

- ኢየሱስ ሊያድነው እንደሚችል ማመን አለበት (የሐዋ. 16:31፤ ሮሜ 10:9–10)።

- ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ መቀበል አለበት ( ዮሐ. 1:12)።

ይህ ለጎልማሶችም በእኩል ደረጃ የሚጠቅም ነው። ጠያቂው ጥቅሶቹን እንዲያነብ አድርግ። እናም ትርጉሙ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያውቅ እርዳው።

ለ. ሌላው ዘዴ ደግሞ ጥሩ የሆነ ስለ ደኅንነት የሚናገር በራሪ ወረቀት (ትራክት) መስጠት ነው። አንድ ሰው በእርግጥ ፍላጎት ካለውና ክርስቶስን ይቀበል ዘንድ እንደተዘጋጀ ከተሰማህ ትራክትህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በመጠቀምና በትራክቱ ውስጥ የተጠቀሱ ክፍሎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ አብሮ በማንበብ ማብራራት ነው።

ሐ. ሦስተኛው ዘዴ የሕይወት ድልድይ በመባል ይታወቃል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ልክ ላልዳነ ሰው እንደምናወራ አድርገን እንጽፋለን። ከአንድ ሰው ጋር ስትነጋገር ይህንን ዘዴ ለመጠቀም እንድትችል ደረጃዎቹ በሚገባ እንዲገቡህ ይህን ክፍል በሚገባ አጥና። ይህ ዘዴ የተገኘው ከትራክት ውስጥ ነው። ይህም ካለህ ከሰውየው ጋር ተጠቀምበት።

ደረጃ አንድ፡– እግዚአብሔር ለአንተ ከሁሉም የሚሻለውን ይሻል።

ኢየሱስ፥ «እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» ብሏል (ዮሐ. 10:10)።

ምንም ዓይነት ኑሮ በአሁኑ ሰዓት ይኑርህ እግዚአብሔር የተሻለ ይሆን ዘንድ ይፈልጋል። ፍላጎትህን ሊያሟላ ይፈልጋል። ለአንተ በእርግጥ ይጠነቀቃል። እናም በጣም ይወድሃል።

ደረጃ ሁለት፡– ከእግዚአብሔር ዕቅድ የጎደልነው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር በነፃ ምርጫ ፈጥሮናል። እኛም በእርሱ ላይ ዓመፅን። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነበር። በእኛና በእግዚአብሔርም መካከል መለያየትና ክፍተትን ፈጠረ። (በኤድን ገነት ውስጥ፥ በአዳምና ሔዋን ስለ ተፈጸመው ታሪክና ኃጢአት እንዴት ወደ ዓለም እንደገባ አብራራለት)። በገነት ያሉ ዛፎች እንደ ዓይነታቸው ፍሬን እንዳፈሩ፥ እንዲሁ አዳምና ሔዋን ኃጢአተኞች ሆነው ከእነርሱም የሚወጡ ዘሮቻቸው ሁሉ በተፈጥሮ ኃጢአተኞች ሆኑ። ኃጢአተኞች ስለሆንን ኃጢአት እናደርጋለን፤ እናም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማድረግ ይልቅ የራሳችንን መንገድ እንመርጣለን። የዚህም ውጤቱ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጠረው ከፍተኛ ክፍተት ነው።

ደረጃ ሦስት፡– ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ክፍተቱን መሙላት ይችላል።

በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሔርን የማወቅ ምኞት አለ። ለብዙ ዘመናት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የራሳቸውን ድልድይ

ለመሥራት ጥረዋል። እርሱን ለማስደሰት ጥሩ ሥራን ለመሥራት ሞክረዋል። ትምህርታዊ በሆነ አስተሳሰብ፥ የተማሩ እንደሆነ እርሱን ለማግኘት የሚችሉ እየመሰላቸው ብዙ ደክመዋል። አንዳንዶች ደግሞ በተመስጦ ልምምድ ወደ ተቀደሱ ቦታዎች በመሄድ፥ ምጽዋት በመስጠትና ረጅም ጸሎት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ እንችላለን ብለው ያምናሉ። ኢሳይያስ 64:6፥ «ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው» ይላል።

ኤፌሶን 2:8–9 ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የሚደረገውን የሥራ ሙከራ ከንቱነት ግልጽ ያደርገዋል። «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» እግዚአብሔር ራሱ ወደ እርሱ የምንመጣበትን መንገድ አዘጋጅቷል። ይህም በእምነት በሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። «አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ኛ ጢሞ. 2:5)።

እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በራሱ ላይ ይሸከም ዘንድ አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከው፤ ኃጢአት የሌለበት ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ለእኛ ኃጢአት ሲል በመስቀል ላይ ሞተ። እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ፤ የእኛ የነበረውን ቅጣታችንንም ወሰደ (ኢሳ. 53:6)። ከሁሉም በላይ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፤ ይህም ሕይወቱን ለኃጢአት መሥዋዕት ማድረጉን እግዚአብሔር እንደተቀበለው ይመሰክራል። ራሱን መሥዋዕት ማድረጉ ለኃጢአታችን ሁሉ ይቅርታ በቂ ነበር። እርሱ ከሙታን ተነሣ። በአዲስ ሕይወቱም ለእኛ አዲስን ሕይወት ሰጠን።

ደረጃ አራት፡– በክርስቶስ አምነን እንደ አዳኛችን ልንቀበለው ይገባል።

ኃጢአተኞች እንደሆንን እና ኃጢአታችን ከእግዚአብሔር እንደለየን ካወቅን፥ ወደ ክርስቶስ በእምነት መቅረብ እንችላለን። ኃጢአታችንን ከመንገድ እንዳስወገደው ስናምንና እርሱን ስንቀበል ያነጻናል። ደግሞም አዲስን ሕይወት ይሰጠናል። ክፍተቱም ይሞላል። ያኔ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ይኖረናል። በኃጢአታችን እርሱ ከዚህ ወዲያ አይቆጣም፤ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቀብሎናልና።

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ለመቀበል ከወሰንህ የሚከተለውን አጭር ጸሎት ጸልይ።

ውድ ጌታ፥ ኃጢአትን እንዳደረግሁና ከአንተም ተለይቼ እንደነበርሁ እናዘዛለሁ። ኃጢአቴን ስለወሰድህ፥ በልጅህም በኢየሱስ በክርስቶስ ላይ ስላደረግኸው አመሰግንሃለሁ። ከቀድሞ መንገዴ በመመለስ ኃጢአቴን ይቅር እንድትለኝና ሕይወቴን እንድታነጻ እጠይቅሃለሁ። ወደ ሕይወቴ ግባና አዳኜ ሁን። መንፈስ ቅዱስ ሕይወቴን እንዲቆጣጠርና ለአንተ እንድኖር እንዲያስችለኝ እጠይቅሃለሁ። ስለ አዳንከኝና አዲስ ሕይወት ስለ ሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፤ አሜን።

ደረጃ አምስት፦ አሁን አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።

ዮሐንስ 1፡12፥ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ይላል።

እግዚአብሔር አፍቃሪ አባት ነው። እርሱ አሁን አባትህ ነው። ልጁን በመላክ አድኖሃል። እናም ልጁ አደርጎሃል። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ትችላለህ፥ ቃሉ ለአንተ ነው። ወደ እርሱ ልትጸልይ፥ ስላደረገልህም ነገር ልታመሰግነውና ችግርህን ልትነግረው ትችላለህ። እርሱ ያጽናናሃል፤ ያበረታታሃልም። እርሱ የልጆቹን ጸሎት መስማት ይወዳል፤ እናም ለእኛ መልካም ነው ብሎ በሚያስበው መንገድ ይመልሰናል።

በክርስቶስ በማመንህ ስላገኘኸው አዲስ ደስታ ለሌሎች መናገር አለብህ። ይህም እምነትህን ያጠነክራል። አዲስ የሆነ ደስታንም ይሰጥሃል።

መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው። እርሱ አሁን በልብህ ውስጥ ይኖራል። አዲስ አድርጎ የሠራህና በክርስቶስ አዲስ ሕይወት የሰጠህ እርሱ ነው። እርሱ ሁልጊዜ ሊያጠነክርህና ሊመራህ ከአንተ ጋር ነው። በሕሊናህ ውስጥ እየተናገረህ ትክክለኛውን እንድታደርግና ክፉውን እንድትቃወም ያነሣሣሃል። ባለመታዘዝህ እርሱን አታሳዝን። የእግዚአብሔርን ቃል እንድታስተውል ይረዳሃል። በየቀኑ እያነበብክ በቃሉ ውስጥ የሚናገርህን ታዘዘው። ከዚያም ደስተኛ ሕይወት ትኖራለህ።

መ. አራተኛው ዘዴ የራስህን ምስክርነት መስጠት ነው። ጌታ ለአንተ ያደረገልህን ለሌሎች ተናገር። የራስህን ምስክርነት በምትሰጥበት ጊዜ ብዙ ነጥቦች መካተት አለባቸው።

- ለክርስቶስ ራስህን የሰጠኸው መቼ ነበር?
- የክርስቶስን ወንጌል ለአንተ ያካፈለህ ማን ነበር?
- የክርስቶስን ወንጌል ለአንተ ለማካፈል የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበር?
- ከዳንህ ጊዜ ጀምሮ በሕይወትህ ውስጥ ምን ለውጥ ተፈጠረ?
- ዛሬ ሕይወትህ የተለየ የሆነው እንዴት ነው?

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፦ ከ150-200 በሚደርሱ ቃላት ምስክርነትህን ጻፍ። ለአንድ ሰው ለመመስከር ወይም በምትመሰክርበት ጊዜ ከላይ ባሉት ከአንዱ ዘዴ ጋር ለማካተት ተጠቀምበት። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንህ አንተ ሕያው ምስክር ነህ። በፍጹም የተለወጠ ሕይወት ሊኖርህ ይችላል። የግል ምስክርነት ኃይል ያለው ምስክርነት ነው። ዕድል በአገኘህ ጊዜ ሁሉ ተጠቀምበት። |

መመስከር እንችል ዘንድ ብዙ መንገዶች አሉ። በምንመሰክርበት ጊዜ መካተት ያለባቸው ጠቃሚ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. እግዚአብሔር የሚወዳቸው መሆኑን ሊረዱ ይገባል።
2. ኃጢአተኛና ከእግዚአብሔር የተለዩ እንደሆኑ ሊገባቸው ያሻል።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ለግላቸው እንደ ሞተና በሞቱም የእነርሱን የኃጢአት ዕዳ እንደ ከፈለላቸው ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል።

4. በልባቸውም ማመን አለባቸው።

5. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል እርግጠኛ የሆነን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል።

**ሦስተኛ ቀን፦ በምትመሰክርበት ጊዜ የሚገጥምህ ተቃውሞና ጥያቄ**

በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ለመድረስ በተነሣህ ጊዜ ብዙ ችግር እንዳለባቸው ትረዳለህ። ሊያጋጥሙህ ከሚችሉት ችግሮች ጥቂቶቹን በመዘርዘር በችግሮች ውስጥ የሚያልፉትን ሰዎች ትረዳ ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ለመስጠት እንሞክራለን። የምታገኛቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ሌሎቹ ደግሞ ገና ያልዳኑ ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ሊገጥሙህ ለሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች የሚሆኑ ምላሾች

ሀ. ለምንድን ነው የምጨነቀውና የምሠቃየው?

- ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው [መዝ. (119)፡67፥ 71፥75]።

- እግዚአብሔር ከእነዚህ ሁሉ ያድንሃል [መዝ. (34)፡19]።

ለ. በጭንቀት ተሞልቻለሁ

- ጭንቀት በጸሎት ሊወገድ ይችላል (ፊልጵ. 4፡6-7)።

- እግዚአብሔር ለአንተ እንደሚጠነቀቅ አስታውስ (1ኛ ጴጥ. 5፡7)።

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስን ብቀበል የዘላለም ሕይወት እንደሚኖረኝ እንዴት እርግጠኛ እሆናለሁ?

- የዘላለም ሕይወት ተስፋ በእግዚአብሔር ቃል ተሰጥቶሃል (ዮሐ. 3፡16)።

- እግዚአብሔር ፈጽሞ አይዋሽም።

- እርግጠኛ መሆን ትችላለህ (1ኛ ዮሐ. 5፡11-13)።

መ. መጽናናት እፈልጋለሁ።

- ኢየሱስ መልካሙ እረኛ (መዝ. 23)።

- እርሱ ፈጽሞ አይተውህም (ዕብ. 13፡5-6)።

ሠ. እጅግ ተስፋ ቆርጫለሁ።

- ተስፋ አትቁረጥ (ገላ. 6፡9)።

- እግዚአብሔር ይረዳሃል፤ ያጠነክርሃልም (ኢሳ. 41፡10)።

ረ. ባዶነት ይሰማኛል።

- ክርስቶስ ያረካሃል [መዝ. (107)፡8-9]።

- ምኞትህን ያሟላልሃል [መዝ. (37)፡4-5]።

ሰ. ኃጢአት አድርጌያለሁ።

- የይቅርታና የመንጻት ተስፋ ተሰጥቶሃል [መዝ. (32)፡5፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡]።

ሸ. ክርስቶስን ተቀብያለሁ። ግን በደለኝነቱ አሁንም ይሰማኛል።

- ኩነኔ የለም (ሮሜ 8:1)።
- እርሱ ይቅር የማይለው ትልቅ ኃጢአት የለም (ኢሳ. 1:18)።

ቀ. በጣም ብቸኛ ነኝ።
- የእርሱ ህልውና ቃል ኪዳን አለህ (ዕብ. 13:5-6)።
- በመገኘቱ ውስጥ ደስታ አለ [መዝ. (16):11]።

በ. ለምን እሠቃያለሁ? (መከራ እቀበላለሁ?)
- መከራ መቀበል ትርፍ አለው (ዕብ. 12:6-11)።
- እምነትን ጥልቅ ያደርጋል (1ኛ ጴጥ. 1:6-7)።
- የሚጠበቅ ነው (1ኛ ጴጥ. 2:19-23)።
- የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ነው (2ኛ ቆሮ. 12:9-10)።

ተ. ስለ ፈተና ምን ላድርግ?
- እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል (ማቴ. 26:41)።
- ውድቀት ከየት ይመጣል (ያዕቆብ 1:13-14)።

ቸ. ድል
- በክርስቶስ ነው (ፊልጵ. 4:13)።
- ውስጣዊ የኃይል ምንጭህ (ዮሐ. 4:4)።
- የእግዚአብሔርን እርዳታ ፈልግ (1ኛ ቆሮ. 10:13)።

ነ. ጭንቀት
- እግዚአብሔር ያዘጋጃል (ፊልጵ. 4:19)።
- በእርሱ እምነት ይኑርህ (ሮሜ 4:20-21)።
- ቃል ኪዳኑን ያዝ (1ኛ ዮሐ. 5:14-15)።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡- ጥቅሶቹን ሁሉ አውጥተህ አንብባቸውና ተረዳቸው። አንዳንዶቹን ልታስታውሳቸው ይገባል። ቢያንስ ቢያንስ በቀላሉ እንድታገኛቸው በመጽሐፍ ቅዱስህ ላይ ልታሰምርባቸው ትችላለህ። |

2. ሊገጥሙህ ለሚችሉ ተቃውሞዎችና ምክንያቶች የምትሰጣቸው ምላሾች።

ሀ. እኔ በጣም መጥፎ ነኝ (ዕብ. 7:25፤ ኢሳ. 1:18ን ተጠቀም)።

ለ. ተስፋ የሚያስቆርጥ ብዙ ችግር አለ ( ማር. 8:36፤ ዮሐ. 2:15-17)።

ሐ. እፈራለሁ ልደርስበት አልችልም (1ኛ ጴጥ. 1:5፤ ፊልጵ. 1:6)።

መ. አንዳንዶች ሊያስቡ ስለሚችሉት ነገር እፈራለሁ (ማቴ. 10:32-33)።

ሠ. አሁን ሳይሆን ሌላ ጊዜ (ምሳ. 2:14፤ 2ኛ ቆሮ. 6:7)።

ረ. የምችለውን ነገር ሁሉ እያደረግሁ ነው (ኤፌ. 2:8-9፤ ኢሳ. 64:6)

ሰ. በጣም መጥፎ አይደለሁም (ያዕ. 2:10፤ ኢሳ. 53:6)።

ሸ. እግዚአብሔር ማንንም አይኮንንም (ዮሐ. 3:18፥36፤ ዕብ. 9:27)።

ቀ. እግዚአብሔር እንደተቀበለኝ እንዴት አውቀዋለሁ? (ዮሐ. 6:37፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9)።

በ. መጽሐፍ ቅዱስን ማስተዋል አልችልም (1ኛ ቆሮ. 2:14፤ 2ኛ ቆሮ. 5:17)።

ተ. ክርስቶስ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ በምን አውቃለሁ? ( ዮሐ. 14:6፤ የሐዋ. 4:12)።

ቸ. አሁን ራሴን ባስደስት ይሻላል (መክበብ 11:9፤ 1ኛ ቆሮ. 6:2)።

ኀ. ክርስቶስን መከተል ብዙ ዋጋ ያስከፍላል (ማር. 8:36፤ ሉቃ. 18:29–30)።

ነ. ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ አልነበረም (ዕብ. 1:3፤ ዮሐ. 10:30)።

ኘ. የሚያሳምን አይመስልም (ኢሳ. 55:8–9፤ 1ኛ ቆሮ. 1:18፤ 23)።

አ. ዕድሌን እሞክራለሁ (ዕብ. 10:31፤ ሉቃስ 12:16–21)።

ከ. በክርስቶስ አላምንም (ሮሜ 3:3፤ የሐዋ. 4:12)።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡– ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ ላለመቀበል ሰዎች ምክንያቶችን ያቀርባሉ። እነዚህ ጥቅሶች የጥቂቱን መልሶች እንድታገኝ ይረዱሃል። ሌሎች የገጠሙህን ተቃውሞዎች ጻፋቸው። ምን መልስ ነበር የሰጠኸው? ምን ጥቅስ ነበር የተጠቀምኸው? |

ዓለማችን ችግር ባለባቸው ሰዎች የተሞላች ናት። አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ቃል መጽናናትና ዋስትና ያስፈልጋቸዋል። እነርሱን በማበረታታት የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያነቡና የሚናገረውን ቃል እንዲታዘዙ የምትችለውን ሁሉ አድርግ። ሌሎቹ ገና ያልዳኑና ቅጥ ያጣ ሕይወት የሚመሩ ናቸው። ስለ እነርሱ በብዙ ጸልይ። መጽሐፍ ቅዱስን አንብብላቸው። እጅግ የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ኢየሱስን እንደ አዳኝና ጌታ አድርጎ መቀበል እንደሆነ እንዲያውቁ እርዳቸው።

## አራተኛ ቀን፡– አንድ – ለአንድ በመሆን የሚደረግ አዲስ አማኞችን መርዳት

ቢንያምና በለጠች ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅ ወልደዋል። በተወለደው ልጅ ቢንያም ፊቱ እስከሚያበራ ድረስ ደስ አለው። በለጠች ምንም እንኳን ቢደክማትም በደስታ መልካም ምኞታቸውን የሚገልጡላትን ሰዎች ትቀበል ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆስፒታል ወደ ቤቷ መጥታለች። ከዚያም ምን ታደርጋለች? ውድ ልጇን በአልጋ ላይ አስተኝታ «አሁን እንግዲህ አንተ ወጣት ራስህን ጠብቅ፥ እኔ እና አባትህ ሥራ ይበዛብናል፥ የምትችለውን አሁን ማድረግ ትችላለህ» ትለዋለችን? በፍጹም አትለውም። ቀንና ሌሊት በተራበ ጊዜ ትንከባከበዋለች። ታጠባዋለች፥ ልብሱን ትቀይርለታለች፥ የሽንት ጨርቁን ታጥብለታለች፥ በሚያለቅስ ጊዜ ታባብለዋለች። እናም ታሞቀዋለች ምቾትንም ትሰጠዋለች።

አዲስ ሕፃን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በተወለደ ጊዜ ምን እናደርጋለን? በዚህ ጠፍቶ በነበረው «በግ» ከሰማይ መላእክት ጋር ሐሴት እናደርጋለን፤ ከዚያስ በኋላ? የሚችሉትን እንዲያደርጉ ልንተዋቸው ይገባልን?

8ኛ ጥያቄ፡— አንድ ሰውን ወደ ክርስቶስ መርተህ ከሆነ እንዴት ነበር የረዳኸው/ የረዳሃት? የጠየቁህ ጥያቄዎች ምን ነበሩ? ምን መለስህላቸው? ምን ዓይነት መመሪያ ሰጠሃቸው? ምን ያህል ጊዜ ከእነርሱ ጋር አሳለፍህ? እስከ አሁን ክርስቶስን ተከትለው በእምነታቸው እያደጉ ነውን? አብራራ።

1. አዲስ አማኝን ማማከርና መርዳት

ሀ. እርግጠኛነት። አዲስ አማኝ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ሁሉ ማወቅ አለበት። ወደ ዮሐንስ 3፡16 ወስደኸው ስሙን በጥቅሱ ውስጥ አስገብቶ እንዲጠቀም አድርግ። ስሙ ያዕቆብ ከሆነ እንዲህ ሊል ይችላል፤ «እግዚአብሔር ያዕቆብን ከመውደዱ የተነሣ አንድያ ልጁን ስለ ያዕቆብ አሳልፎ ሰጠ። ያዕቆብ በእርሱ ያመነ እንደሆነ አይጠፋም። ነገር ግን ያዕቆብ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል።» ያዕቆብን ማን እንደወደደው ጠይቀው። ምን ያህል ነው የወደደው? ያዕቆብን ምን እንዳደረገ ጠይቀው (በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን) ይህን ስላደረገ ምን አይደርስበትም? (አይጠፋም)። እንደገና የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ አብራራ (ሮሜ. 3፡23)። ኢየሱስ በእርሱ ፋንታ ሞቶ የኃጢአት ዕዳውን ከፍሎለታል። ስለዚህ እርሱ ምን አለው? (የዘላለም ሕይወት) ምን ማለት እንደሆነ አብራራ።

ሌላ ለእርግጠኝነት የሚሆን ጥቅስ ዮሐንስ 10፡27–30 ነው። ያዕቆብ ቃሉ ምን እንደሚል እንዲያስብ ልክ እንደዚያው በጥያቄ አንብበው። በተጨማሪ እንደ ላይኛው አንድ ነጥብ ኢየሱስ ሲናገር «ማንም ከእጄ አይወስዳቸውም» (ቁ. 28) አለ። አንድ ትንሽ ነገር በእጅህ ላይ ካደረግህ በኋላ ከአንተ ነጥቆ ለመውሰድ እንዲሞክር አድርግ። መውሰድ ችሏልን? (ቁ. 27ን አንብብ)። ከሁሉ በሚበልጥ አባት በእግዚአብሔር እጅ ያዕቆብም አለ። ትንሹ ነገር በሁለት እጆችህ ውስጥ ሆኖ ከእጅህ ያዕቆብ መውሰድ ችሏልን? አንተ ሰው እስከሆንህ ድረስ ያዕቆብ በኃይለኛው በእግዚአብሔር እጅና በኢየሱስ እጅ ሆኖ እንዴት የተጠበቀ እንደሆነ እንዲያስብ አድርግ። የደኅንነትን መሠረት ለማስተማር ከሌላ ጥቅስ ጋር መጠቀም ይቻላል።

ለ. ትምህርት— ማመንና መቀበል። በክርስቶስ ገና አዲስ ሕፃን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚነበብ አያውቅም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን የት ቦታ እንደሚገኝ አያውቅም። አዲስ ኪዳንንና ብሉይ ኪዳንን ደግሞም ምዕራፎችና ቁጥሮች እንዴት እንደሚከፈሉ ልታሳየው ያስፈልጋል። የመጽሐፎች ማውጫ የት እንደሆነና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ እንዴት ሊያወጣና ሊጠቀም እንደሚችል አሳየው። እንዴት እንደሚጸልይና የጥሞና ጊዜ እንዴት ሊኖረው እንደሚችል አስተምረው። መጽሐፍ ቅዱስን በቃሉ እንዲያጠናና የእግዚአብሔርን ቃል በልቡ መሰወር እንዲችል እርዳው። ምስክርነቱን ለሌሎች ክርስቲያኖች ከዚያም በኋላ ለሌሎች ለቤተሰቡና ለጓደኞቹ እንዲሰጥ አበረታታው። ይህ እርሱን ያጠነክረዋል። ጳውሎስ ሲናገር «በወንጌል አላፍርም» (ሮሜ. 1፡16) ብሏል። ይህንን ሁሉ ደረጃ በደረጃ የምታስተምረውን ትምህርት መቀበል እስኪቻለ ድረስ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ታስተምረዋለህ።

ሐ. መመገብ። ከእርሱ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት ጀምር። አስቸጋሪ ያልሆነ መጽሐፍ ተጠቀም። ዮሐንስ ጥሩ ሊሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ

ጥናትና የቤት ውስጥ ንባብ የሚጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረው ያስፈልጋል። ለእግዚአብሔር ቃል የተጠማና ሁሉም ለእርሱ አዲስ ነው። መግበው። ከዘገየህ የማንበብና የማጥናት ፍላጎትን ሊያጣ ይችላል።

መ. መጠበቅ። የድሮ ጓደኞቹ ሊሳለቁበት ይችላሉ። ብቸኝነት ስለሚሰማው አዲስ ጓደኛ እስከሚያገኝ ድረስ ጓደኛ ልትሆነው ያስፈልጋል። ጸልይለት፤ ምናልባትም ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የወሰነውን ውሳኔ ቤተሰቦቹ ጠንክረው ከተቃወሙ ከቤት ሊያስወጡት ይችላሉ። መበረታታትና ከተቻለም የሚያርፍበት ቦታ ያስፈልገዋል። አንተ ልክ እንደ አዲስ እናት ነህ። ለራሱ መጠንቀቅ እስከሚችል ድረስ ለዚህ አዲስ አማኝ ልትጠነቀቅለት ይገባል።

ሠ. ንስሐ መግባት። ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ እንደገና ኃጢአትን ያደርጋል። ምናልባት ወደ ድሮ የሕይወቱ ልማድ ሊንሸራተት ይችላል። ስሕተት እንዳደረገ ያውቃል። ሕሊናው ስለሚያስጨንቀው በደለኝነት ይሰማዋል። ደኅንነቱን ያጣ መስሎት ይጨነቃል። ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም።

አንተም የኃጢአት ይቅርታ እንዳለ እንዲያውቅ ልትረዳው ይገባል። ወደ ዮሐንስ 1፡9 ወይም ምሳሌ 28፡13 ውሰደው። ማንኛችንም ፍጹም እንዳይደለን አብራራለት። በዚህ ምድር ላይ እስከኖርን ድረስ ደካሞች ሰዎች ነን። ከዳንን በኋላ እንኳን ኃጢአትን እናደርጋለን። ወደ ጌታ እንደገና በትሕትና በመምጣት ንስሐ በመግባት ይቅርታን መጠየቅ አለብን። መሐሪ ስለሆነ ከዓመፃ ሊያነፃንና ይቅርታን ሊሰጠን ይችላል። ከዚያም ከጌታ ጋር ባለን ኅብረት ልንደሰትና ደስታችን ሊመለስልን ይችላል።

ረ. ጥያቄዎቹን መልስለት። የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና መመልከት በጀመረ ጊዜ ጥያቄ ይኖረዋል። ለአንተ ቀላል የሚመስሉ ቢሆኑም በትዕግሥት መልስለት። ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ይጓጓል። እርዳው።

ሰ. በቤተ ክርስቲያን በቋሚነት እንዲካፈልና በዕድሜው ክልል ካሉ ሰዎች ጋር እንዲቀላቀል አበረታታው። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሰባሰብን ቸል እንዳንል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዕብ. 10፡25)።

| |
|---|
| ፱ኛ ጥያቄ፦ ከላይ ያሉትን ነጥቦች ባሰብህ ጊዜ አዲስ ክርስቲያንን ስለመከታተል ወደ አሳብህ ምን ይመጣብሃል? የሚያስፈልገውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛና የተዘጋጀህ ሆነሃል? ይህ ጉዳይ ከአንተ ምን ዓይነት ነገር ይፈልጋል? (ማር. 3፡14 አንብብ)። |

II. ክትትል የሚያደርገው ሰው የብቃት መመዘኛ

ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ጊዜ የተወደደ ነገር ነው። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ስታይ የተወደደውን ሰዓትህን ለዚህ አዲስ አማኝ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን እንዳለብህ ትመለከታለህ፤ አለበለዚያ ሊጸና አይችልም። «ኢየሱስ እነርሱ ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ። ከኢየሱስ ጋር ብዙ ጊዜ አብረው ነበሩ፤ እርሱም ከእነርሱ ጋር ነበር» (ማር. 3፡14)።

- ይህን አዲስ ክርስቲያን ለማስተማር ለመምራትና ለማዘጋጀት ፈቃደኛ ሁን።

- የዚህን አዲስ አማኝ እርግጠኛነትና ዋስትናውን ለማረጋገጥ ፈቃደኛ ሁን። እያንዳንዱ ሰው መረጋጋትና ተፈላጊነት እንዲኖረው ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤቱ እስከሚሰማው ድረስ እነዚህን ሁሉ ማድረግ አለብህ።

በአካባቢህ ብዙዎች ወደ ጌታ ከመጡ ይህን የክትትል ሥራ በቡድን ማድረግ ትችላለህ። ዋናው ነገር ለአዲስ አማኞች ውጤታማ ክትትል መደረጉ ነው።

አምስተኛው ቀን፡- ትምህርት አሥራ አምስትን ከልስ። ቤተ ክርስቲያን ወደ ቅርብ አካባቢዎች ወንጌላውያንን ልካለችን? ወደ ሩቅ ስፍራዎች ተልከዋልን? በባሕል-ዘለል መንገድ ለመድረስ ከአገር ውጪ ልካቸዋለችን? ይህን ማድረግ ነበረባትን?

## ሳምንታዊ ስብሰባ

በማቴዎስ 28፡18-20 ላይ መልእክትህን አዘጋጅ። ጥሩ ዕቅድ ተጠቀም።

የመወያያ ርእሶች

1. አንድ ሰው ስለ ክርስትና ጥያቄ ቢጠይቅህ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀህ ነህን?

2. ክርስቲያን ካልሆኑ ጓደኞችህ ጋር ከሆንህ በክርስቶስ ስላለህ እምነት ለመናገር ታፍራለህን? ከሆነ ይህንን እፍረት ወይም ፍርሃት የምታስወግድበትን መንገድ አካፍል።

3. ቤተ ክርስቲያንህ ወንጌላውያንን ትረዳለች? እናም ትልካለችን? ጌታ ከጠራህ ለመሄድ ፈቃደኛ ነህን? እንደ ወንጌላዊ ሆነህ ብትሄድ ምን አዲስ ሁኔታ ይገጥምሃል?

4. ላልዳኑት ሰዎች ለመመስከር ከኅብረተሰባችን ውስጥ የግድ መውጣት አለብን? በቤት አካባቢ መመስከርስ ያስፈልጋልን?

5. ለክርስቶስ ከመመስከር ነፃ የሆነ ሰው አለን? አንዳንዶች ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በተሻለ ሁኔታ የመመስከር ስጦታ አላቸውን? ይህ ማለት ስጦታ ያላቸው ብቻ ይመስክሩ ማለት ነውን?

6. ለመመስከር በምትሞክርበት ጊዜ የሚገጥሙህን ችግሮችና ከባድ ጥያቄዎች ተወያዩባቸው። ሌሎች የክፍል አባሎች በሚመሰክሩበት ጊዜ ከተጠየቋቸው ጥያቄዎች ጋር አዛምድ። እንዴት እንደመለሱ ያካፍሉ። ሊመልሱ በተቻሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ልትመሰክር በተነሣህ ጊዜ የገጠሙህን ችግሮችና ከባድ ጥያቄዎች ተወያይባቸው ። የክፍሉ አባሎች በሚመሰክሩ ጊዜ የአላቸውን ልምምድና ከባድ ጥያቄ የተጠየቁትን አዛምድ። እንዴት መልስ መስጠት እንደቻሉ ያካፍሉ። ሊሰጡ የሚችሉትን መልሶች ተወያይባቸው።

# ትምህርት አሥራ ስድስት

## የእምነት ማጽኛ ክፍሎች

በትምህርት አሥራ ስድስት አንደኛ፥ ሁለተኛና ሦስተኛ ቀናት የተካተቱት ትምህርቶች ተጠቃልለው (በአንድነት) በ«አዲስ አማኞች የማስተማሪያ ክፍል» ውስጥ ሊጠኑ (ሊሰጡ) ይችላሉ።

### አንደኛ ቀን፦ የአዲስ አማኞች ማስተማሪያ ክፍል

በቤተ ክርስቲያን አዳዲስ አማኞች በሚኖሩበት ጊዜ ልንመግባቸው ይገባል። በመጨረሻው ትምህርታችን በወንጌል ስርጭት ላይ እንደጠቀስነው እነዚህ በክርስቶስ ሕፃናት የሆኑትን ልንከባከባቸው ይገባል። የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ምግብ ሊያገኙ ይገባል።

ትምህርትህን ይረዱት ዘንድ ቀለል አድርገው፤ ነገር ግን በአመኑበት ጊዜ ምን እንዳደረጉ እንዲያውቁና ያንን እንዲረዱ የጠለቀ መሆን አለበት።

ዳግመኛ የተወለዱ ስለመሆናቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ስለመምራት በትምህርት 5 አራተኛ ቀን እና ትምህርት 15 ሁለተኛ ቀን ውስጥ የተሰጠውን ትምህርት እንደገና ተጠቀም።

1. ሊተኮርባቸው የሚገባ አንዳንድ ጠቃሚ ርእሰ ጉዳዮች።

ሀ. ንስሐ

ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር ሰውን በወደቀበት ስፍራ አልተወውም። የሚድንበትን መንገድ አዘጋጅቶአል። የመዳንን መንገድ እንዲያዘጋጅለት አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከው።

1) የንስሐ ትርጉምና አስፈላጊነት

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፦ የሐዋ. 3፡19-20፤ ገላ. 5፡19-20 እና ኢሳ. 55፡6-7 አንብብ። ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው? ኃጢአት ምንድን ነው? ሉቃ. 13፡1-5፤ ማቴ. 3፡1-2 እና የሐዋ. 17፡30 በተጨማሪ አንብብ። በእነዚህ ምንባቦች ውስጥ ስለ ንስሐ የሰበኩትንና ያስተማሩትን ሦስት ሰዎች በዝርዝር ጻፍ። ለምን አስፈላጊ ሆነ? |

ንስሐ ማለት ኃጢአተኛው መንገዱን እና አሳቡን ትቶ ወደ ጌታ መመለስ አለበት ማለት ነው። ይህ ማለት አቅጣጫን ሙሉ ለሙሉ ቀይሮ ወደ ጌታ መመለስ ማለት ነው። ሰው የራሱን መንገድ መርጧል። በእግዚአብሔር ላይ ዓምፆአል። አሁን የራሱ መንገድ የተሳሳተ መሆኑን መገንዘብ አለበት። ጥረቱ ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ ራሱን ማዳን እንደማይችል ማወቅ ይገባዋል (ኤፌ. 2፡8-9)። ከዚያም ተመልሶ ወደ እግዚአብሔር መምጣት አለበት። ከላይ እንደተመለከትነው መጥምቁ ዮሐንስ የንስሐን አስፈላጊነት ሰብኳል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰዎች ከኃጢአታቸው ተመልሰው ንስሐ እንዲገቡ ሲለምናቸው ነበር። ሐዋርያት በተለይም ጳውሎስ ሰዎች ንስሐ መግባት እንዳለባቸው አስተምሯል። (የሐዋ. 20፡20-21፥ 26፡16-20 ተመልከት)።

ንስሐ ለመግባት ሰው የራሱ መንገድ የተሳሳተ እንደሆነ መገንዘብ አለበት። አሳቡ የተሳሳተ እንደሆነ ለጌታ መናገር አለበት። ስለ ዓመፁ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው መጠየቅ አለበት። ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት።

ለ. እምነት - ማመንና መቀበል

---

2ኛ ጥያቄ፡- ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 16፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡7 አንብብ። የእምነትን ትርጉም ጻፍ። እምነት ረቂቅ ጽንሰ አሳብ ስለሆነ ምን ማለት እንደሆነ ለመግለጥ ሞክር። በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ያካተታቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

---

እምነት እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ያዘጋጀውን ለመቀበል ከሚዘረጉት ሁለት እጆች ጋር ሊነጻጸር ይችላል። ወይም እግዚአብሔር ለእኛ የሠራውን ነገር አይቶ የተናገረው እውነት እንደሆነ ከሚያምነው ዓይን ጋር ሊነጻጸር ይችላል። ዕብራውያን 11፡1 እንዲህ በማለት እምነትን ለማብራራት ይሞክራል፤ «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።»

ከንስሐ በኋላ አንድ ሰው እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ዓመፀኝነቱንና የኃጢአተኝነቱን ዋጋ በሙሉ እንደከፈለለት ማወቅ አለበት። እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃ የተናገረውን ቃል ማመን አለበት። በኢየሱስ ከአመነ እግዚአብሔር ልጁ እንደሚያደርገው በልቡ እርግጠኛ መሆን አለበት።

ልክ እንደ መንትያ ማመን ማለት መቀበል ማለት ነው። በእምነት የመቀበልን ደረጃ መውሰድ አለብን። እምነት በአእምሮና በልብ የሚደረግ ነገር ነው። መቀበል የፈቃዳችን እርግጠኛ ርምጃ ነው። የምናምነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደ ሞተና ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃን ብቻ ሳይሆን ወደ አብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጸለይ ስለ ኃጢአታችን ንስሐ እንደገባን በመናገር ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ለመቀበል እንደምንፈልግ መጠየቅ አለብን። አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ በምትመራበት ወይም አዲስ አማኝን በምታስተምር ጊዜ እነዚህን ጠቃሚ ደረጃዎች አትተው። አንዳንዶቹ በስሜታዊነት ለጌታ ሕይወቴን ሰጥቻለሁ ብለው ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስን ግን በእርግጥ እንደ ግል አዳኛቸው አልተቀበሉትም። ይህ ዳግመኛ የመወለድ ክፍል እንደገባቸው በጣም እርግጠኛ ሁን።

የአዲስ አማኞች ክፍልን በጥሩ ሁኔታ ለመምራት በወንጌላዊ ኪዳሞ ሜቻቶ የተጻፈውን «ሙሉ መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ» የሚለውን ትንሽ መጽሐፍ እንድትጠቀም እመክራለሁ። ይህ መጽሐፍ በተለይ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የተዘጋጁ 20 ትምህርቶች አሉት። ዋጋው ሁለት ብር ብቻ ሲሆን በጊጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥነጽሑፍ ክፍል ይገኛል።

2. የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ትምህርት አስተምራቸው።

ወደ አንደኛ ትምህርት 3ኛ ቀን ተመለስ። በተለይም የእምነት አቋም ዓረፍተ ነገር ናሙና ታገኛለህ። መሠረታዊ የሆነ የክርስትና እምነትን ለማስተማር ይህንን አስተዋጽኦ ወይም የትምህርት መጽሐፍ ተጠቀም።

ለአንድ አዲስ ክርስቲያን መሠረታዊ የሆኑትን የክርስትና ትምህርት እውነቶችን መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ስምንቱን ትምህርቶች ተመልከት፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በመጠቀም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰይጣን፥ ስለ ሰው፥ ስለ ኃጢአትና ስለ ደኅንነት፥ ስለ መንግሥተ ሰማይና ስለ ሲዖል፥ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ወንጌል ስርጭት አስተምራቸው።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፦ ከዚህ በላይ ወደ ተጠቀሱት የኮርሱ የተለያዩ ክፍሎች በመመለስ ለአዳዲስ አማኞች አስተምራለሁ የምትላቸውን ነጥቦች አስተዋጽኦ ከነጥቅሱ አውጣ። ስለ ጥምቀት፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አባልነትና ስለ ጋብቻ ትምህርት እንቀጥላለን። በአስተዋጽኦህ ውስጥ እነዚህን ርእሶች ለመጨመር ባዶ ስፍራ ተው። |

## ሁለተኛ ቀን፦ ለውኃ ጥምቀትና ለጌታ እራት መዘጋጀት

ደኅንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው (የሐዋ. 4:12፤ ዮሐ. 4:14)። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብሮ የተሰቀለውና በመሞት ላይ የነበረው ወንበዴ በኢየሱስ እንዳመነና ኢየሱስ፥ «እውነት፥ እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» እንዳለው እናውቃለን። (ሉቃ. 23:40–43 አንብብ።)

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፦ እንግዲህ የመጠመቅ ጥቅሙ ምንድን ነው? (ሮሜ 6:3–4 ማቴ. 28:19–20 አንብብ።) |

### 1. የአማኞች ጥምቀት

ሀ. ጥምቀት የተሰጠው በክርስቶስ ምሳሌነትና በራሱ ትእዛዝ ነው (ማቴ. 3:13–17)። እናም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይካሄድ ነበር።

ኢየሱስ ይህን ሥርዓት ለሁሉም አማኞች የደቀ መዝሙርነት ምልክት አደረገው። (ማቴ. 28:19፤ ማር. 16:16 አንብብ።) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጥምቀት ከንስሐ በኋላ ወዲያው የሚደረግ በክርስቶስ የማመን ምስክርነትና ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጨመሪያ መንገድ ሆኖ ታይቷል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ የተጠቀሱት አይሁዶች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እምነታቸውን በግልጽ ለማወጅ የሚያደርጉት መደበኛ ልማድ ነበር። ከቆይታዎች በኋላ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደምናገኘው የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት ለሌላቸውና ነገር ግን በክርስቶስ በማመን የእምነት ምስክርነት ለሰጡት ለጥምቀትና ለቤተ ክርስቲያን አባልነት የሚያዘጋጃቸው የመፈተኛ ጊዜ ከመመሪያና ከትምህርት ጋር ይሰጣቸው ነበር።

መልእክቶችን በምንመለከትበት ጊዜ ጥምቀት አማኞች ከክርስቶስ ጋር በሞቱ፥ በመቀበሩና፥ በትንሣኤው አንድ እንደሆኑ፥ ወይም እንደተባበሩ በተምሳሌትነት የሚያሳይ እንደሆነ የሚገልጡ ብዙ ጥቅሶችን እናገኛለን።

(ሮሜ 6፡1–9፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ገላ. 3፡27፤ ቆላ. 2፡12፤ ዕብ. 6፡2፤ እና 1ኛ ጴጥ. 3፡21 አንብብ)። ጥምቀት ከሚከተሉት ነገሮች ጋር ይዛመዳል።

1. ስላለፈው ኃጢአት ንስሐ መግባታችንን
2. በሞቱ ከእርሱ ጋር መተባበራችንን፥ እርሱ ፍርዳችንን መውሰዱን
3. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፥ አዳኝና ጌታ መሆኑን ማመናችንን
4. ወደ ጽድቅና ቅድስና የሚመራንን በክርስቶስ ያለን አዲስ ሕይወት
5. መንፈስ ቅዱስን መቀበላችን
6. ከክርስቶስ አካል ከቤተ ክርስቲያን ጋር መዋሐዳችን
7. ለእግዚአብሔር የጥሩ ሕሊና መልስ መስጠት ("Drumond"/ድራሞንድ፥ ገጽ 55)።

| 4ኛ ጥያቄ፡– መጠመቅ ያለብን ለምንድን ነው? |
|---|

ለ. እግዚአብሔር እንድንጠመቅ አዝዟል። «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል። ያላመነ ግን ይፈረድበታል» የሚያድነን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ነው። በጥምቀታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነታችንን በሕዝብ ፊት እንመሰክራለን፥ ደግሞም፥ እግዚአብሔር አድርጉ ያለንን እንታዘዛለን።

5ኛ ጥያቄ፡– የሐዋ. 2፡38–42 አንብብ። አዲስ ክርስቲያኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመጨመራቸው በፊት ምን አድርገው ነበር?

ሐ. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ንስሐ የገቡትና የተጠመቁት ኃጢአታቸው ይቅር ተብሎላቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር። ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ። የወንጌልን መልእክት በማመን ጊዜ የሚሆኑት ነገሮች እነዚህ ናቸው። ከዚህ ከጠማማ ትውልድ ይድኑ ዘንድ ጴጥሮስ ይለምናቸው ነበር። እርሱ ዛሬ እዚህ ቢኖር ኖሮ ይህንኑ ዓይነት ነገር ይናገር ነበር። ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ፥ እንዲያምኑ፥ ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉና ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባልላቸው፥ መንፈስ ቅዱስን ወደ ሕይወታቸው እንዲቀበሉና እንዲጠመቁ መልእክቱን መስበክ ጊዜ የማይሰጠው አስቸኳይ ነገር ነው።

6ኛ ጥያቄ፡– በሮሜ. 6፡3–11 ጳውሎስ የሚያስተምረው ተጨማሪ እውነት ምንድን ነው? ይህ ምንባብ ምን ማለቱ እንደሆነ አብራራ።

መ. በሞቱና በትንሣኤው ራሳችንን ከክርስቶስ ጋር ካመሳሰልን አሁን «ለኃጢአት እንደ ሞትን፥ ለእግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ሕያው እንደሆንን መቁጠር» እንችላለን። ከእንግዲህ ወዲህ የኃጢአት ባሪያዎች መሆን አያስፈልግም። ቁጥር 12ን ተመልከት፤ «እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ።» ቀጥልና የቁጥር 14 የመጨረሻውን ክፍል አንብብ። በክርስቶስ በኃጢአት ላይ ድል ማግኘት እንችላለን። ሰውነታችንን ስሕተት የሆነ ነገር ለማድረግ ባቀረብን ጊዜ ኃጢአት እንሠራለን። እጆችን ወይም እግራችን ወይም አእምሮአችንን

ሊሆን ይችላል። ወይም የምግብ ፍላጎታችን ሊሆን ይችላል። በጥምቀታችን ለኃጢአት ሞተን ለክርስቶስ በሕይወት እንደምንኖር እንዳወጅን ማስተዋል አለብን። ስለዚህ እርሱ በሚሰጠን ድልና ኃይል መኖር አለብን።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡- የጥምቀት ትምህርት እያስተማርህ ከሆነና ተማሪዎቹም ለመጠመቅ ዝግጁ መሆናቸውን ከገለጹልህ፥ ዝግጁ እንደሆኑ የምታረጋግጠው እንዴት ነው? |

ሠ. አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ግልጽ መሆን ያለባቸው ነጥቦች

1. አዲሱ አማኝ ክርስቶስን እንዴት እንደተቀበለ፥ ማን ወደ ክርስቶስ እንደመራውና ምን እንደተነገረው ጥርት ያለ ምስክርነት መስጠት መቻል አለበት።
2. አዲሱ አማኝ በአመለካከቱና በድርጊቱ መለወጡን ማስመስከር አለበት (የሐዋ. 16፡30-34)።
3. ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለው ፍቅር የሚታይ ሊሆን ይገባል።
4. ለሌሎች አማኞች ፍቅርና አሳቢነት ሊኖረው ይገባል።
5. ላልዳኑት ሰዎች እምነቱን ለማካፈል ትልቅ መሻት ሊኖረው ይገባል።

2. የጌታ እራት

አዲስ አማኞች በእውነት ካመኑና ከተጠመቁ በኋላ ከሌሎች አማኞች ጋር አብረው የጌታን እራት እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። በአዲሱ አማኞች ክፍልህ ውስጥ ይህንን ሥርዓት እንዲካፈሉ ማዘጋጀት መልካም ነው።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፡- ማቴ. 26፡26-29፤ ሉቃ. 22፡19-20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡17-31 አንብብ። የጌታ እራት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው። የጌታን እራት በምንወስድበት ጊዜ ምን እናስታውሳለን? ከመውሰዳችን በፊት ምን ማድረግ አለብን? |

ሀ. ክርስቶስ ራሱ የጌታን እራት እንድንካፈል አዝዞናል።

ከላይ ከማቴዎስና ከሉቃስ ከጠቀስናቸው ምንባቦች ክርስቶስ ራሱ የጌታን ራት ሥርዓት እንዳቋቋመና ሥጋውንና ደሙን መሥዋዕት አድርጎ እንደሰጠ በማሰብ ኅብስቱንና የወይኑን ፍሬ ጭማቂ መውሰድ እንዳለብን ያዛል።

ለ. የጌታን እራት በተመለከተ

1. ክርስቶስን የምናስብበት የመታሰቢያ እራት ነው (ማቴ. 26፡26-29፤ ሉቃ. 22፡19-20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡26)።
2. የጌታን ሞት ያሳስባል (1ኛ ቆሮ. 11፡24-25)።
3. ሥጋውንና ደሙን በሚወክሉ ነገሮች መሰተፍ ነው (ዮሐ. 6፡33-35)።
4. በእምነታችን ዳግመኛ መምጣቱን እንመሰክራለን (1ኛ ቆሮ. 11፡26)።
5. ከሌሎች አማኞች ጋር ያለንን አንድነትና ኅብረት እናውጃለን (1ኛ ቆሮ. 16፡10-17)።
6. ራስን የመመርመሪያ፥ ራስን የማያና ቅዱስ ካልሆነ ነገር ሁሉ መለየትን የሚያካትት ጥብቅ ሥርዓት ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡28)።

ሐ. የጌታን እራት በምንካፈልበት ጊዜ የምናደርጋቸው ነገሮች፡-

1. በእኛ ቦታ የተቀበለውን ሥቃይና ሞቱን እናስባለን። ይህም ለእኛ ያለውን ታላቅ ፍቅር የምናስብበት ጊዜ ነው (1ኛ ዮሐ. 4:10፥ 19፤ ዮሐ. 3:16፥ ሮሜ. 5:8)።

2. በሕይወታችን ውስጥ ንስሐ ያልገባንበት ኃጢአት እንዳለ ልባችንን እንመረምራለን (1ኛ ቆሮ. 11:27-29)። ከዚያም ንስሐ በመግባት ጌታን ይቅርታ መጠየቅ አለብን።

3. በክርስቶስ በተፈጸመው ሥራ ደግም እንደሰታለን።

4. በሲና ተራራ ላይ ለብሉይ ኪዳን መመሥረቻ ከፈሰሰው ከእንስሳት ደም ይልቅ የተለየው የአዲስ ኪዳን ደም በወይኑ እንደሚወከል እናስባለን። የብሉይ ኪዳኑ ደም ደግሞ ደጋግሞ መፍሰስ ነበረበት። ክርስቶስ አዲሱን ኪዳን በዘላለማዊ መሥዋዕት ለሁሉም ዘመን እንዲሆን አትሞታል።

9ኛ ጥያቄ፡- በዚህ ትምህርት ውስጥ የተማርናቸው ሁለት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች የትኞቹ ናቸው? ለአዳዲስ አማኞች በክርስትና ሕይወት ጥሩ ጅማሬ እንዲሆንላቸው በሚያስችል መንገድ ትምህርቱን በጥንቃቄ ታስተምር ዘንድ ይህንን ትምህርት ከልስ።

ሦስተኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን አባልነት

1. የቤተ ክርስቲያን ትርጉም

በግሪክ ቋንቋ «ቤተ ክርስቲያን» ማለት «የአንድ ከተማ ዜጎች ጉባኤ» ወይም «የግለሰቦች ጉባኤ» ማለት ነው። ክርስቶስና ሐዋርያቱ እንደተጠቀሙበት ቤተ ክርስቲያን ማለት፡-

> በክርስቶስ ሞት ድነው ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁና አዲስ ሕይወት የተቀበሉ ሰዎችን የሚያጠቃልል አካል ነው። ይኸውም በሰማይም ሆነ በምድር ያሉትን እንዲህ ያሉ ሰዎች ያጠቃልላል። በተፈጥሮው ዓለም አቀፋዊ ቢሆንም፥ የክርስቶስን አካል ባሕርያት በሚያንጸባርቅ መልኩ አማኞች በየአጥቢያቸው በሚያደርጉት ኅብረት ይገለጻል። (ሚላርድ ኤሪክሰን/ "Millard Erickson", ገጽ 1034)

2. የቤተ ክርስቲያን አባላት

ሀ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሰዎችን ያካትታል (2ኛ ቆሮ. 6:16፤ 2ኛ ተሰ. 2:13-15)።

ለ. ከእግዚአብሔር ሕዝብ ቅድስና ይጠበቅበታል (ኤፌ. 5:25-27)።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (1ኛ ቆሮ. 12:27)።

- ክርስቶስ በአማኝ ውስጥ ይኖራል (ቆላ. 1:27፤ ገላ. 2:20)።

- ክርስቶስ የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው (ቆላ. 1፡18፤ ኤፌ. 1፡10)።
- አካሉ ከክርስቶስ በሚቀበለው ምግብ ያድጋል (ቆላ. 2፡19፤ ዮሐ. 15፡1-11)።
- ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ጌታ ነው።

መ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የግለሰቦች እርስ በርስ መተሳሰር

- የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሆነው ሳሉ አንድ አካል ናቸው (1ኛ ቆሮ. 12፡12፥13)።
- መንፈሳዊ ስጦታዎች ማኅበሩን ለማነጽ ይውሉ ዘንድ ተሰጥተዋቸዋል (1ኛ ቆሮ. 14፡4-5፤12)።
- እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው (1ኛ ቆሮ. 12፡14-25፤12፡27-31)።
- እያንዳንዱ አባል ሌሎችን ይፈልጋል፥ እርሱም በሌሎች ይፈለጋል (ኤፌ. 4፡11-16)።
- እያንዳንዱ አባል የሌላውን ሸክም ይሸከም ዘንድ ይገባል (ገላ. 6፡2)።

ሠ. እያንዳንዱ አባል ሌላውን ደቀ መዝሙር ማድረግና ሲስቱም መመለስ አለበት (ማቴ. 18፡8፥17፤ ሮሜ 16፡17፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡12-13)።

ረ. አባላት እውነተኛ ኅብረት (አንዱ ሌላውን በመቅረብና በመረዳት፥ መተሳሰብና መበረታታት አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 12፡26)።

ሰ. አባላት አንድ መሆን አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 11፡17-19፤ 12፡12-13፤ ኤፌ. 4፡4-6፤ ቆላ. 3፡11፤ ሮሜ 11፡25-26፥ 32፤ ገላ. 3፡28)።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ ተመልከትና ከ ሀ-ሰ ከተዘረዘሩት አሳቦች የተማርከውን የሚያጠቃልል አንድ ዓረፍተ ነገር ጻፍ። |

3. የቤተ ክርስቲያን ኃይል

ሀ. ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ይኖርባታል (1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ 3፡16-17፤6፡19)።

ለ. መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ይሰጣል (ገላ. 5፡22-23፤ ዮሐ. 16፡7፥8)።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የሠፈሩትን ጥቅሶች ተመልከትና ከቤተክርስቲያን ጋር እንዴት እንደሚገናኙ አብራራ። |

4. የቤተ ክርስቲያን ተግባራት

ሀ. ወንጌልን ማሰራጨት (ማቴ. 28፡18–20፤ ዮሐ. 14፡15)።

ለ. አማኞችን ማነጽ /ማሳደግ/ (ኤፌ. 4፡12፥16፥29)።

- በኅብረት (1ኛ ቆሮ. 12፡26፤ ገላ. 6፡2፤ ማቴ. 18፡15–17፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡1–2)።
- በምሪትና ትምህርት (ማቴ. 28፡20፤ ኤፌ. 4፡11፤ የሐዋ. 18፡26)።
- በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፥ ኮሌጆችና ሰሚናሪዎች።
- በስብከት (1ኛ ቆሮ. 14፡3–4)።

ሐ. አምልኮ (1ኛ ቆሮ. 16፡2፥ 14፤ 15–17)።

መ. ማኅበራዊ ጉዳዮች (ሉቃ. 10፡25–37፤ ማቴ. 25፡31–46፤ ያዕ. 1፡27፤ 2፡1–11፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡17–18፤ ሉቃ. 3፡19–20)።

ሠ. የቤተ ክርስቲያን ድጋፍ

እያንዳንዱ አማኝ ቤተ ክርስቲያን በምትሰጣቸው የድጋፍ ተግባራት መተባበር አለበት።

- በመባና በአሥራት (2ኛ ቆሮ. 9፡6–15፤ ያዕ. 2፡14–17)።
- በበጎ ፈቃድ አገልግሎት
- በትርፍ ጊዜ አገልግሎት

12ኛ ጥያቄ፡– የቤተ ክርስቲያን ዶክትሪንን አጥናና በራስህ ቃላት የቤተ ክርስቲያንን ትርጉም ጻፍ።

13ኛ ጥያቄ፡– ሉቃ. 8፡38–39፤ ሮሜ 12፡5–11፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡5–7፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡14፤ ፊልጵ. 1፡27፤ 1ኛ ተሰ. 1፡8፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2ን አንብብ። ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሣት የክርስቶስ አካል የሆነችውን የቤተ ክርስቲያን አባላትን ተግባራት በተመለከተ የደረስክበትን ማጠቃለያ ጻፍ።

14ኛ ጥያቄ፡– ሉቃ. 8፡38፥ 39፤ ሮሜ 12፡5–11፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡5–7፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡14፤ ፊልጵ. 1፡27፤ 1ኛ ተሰ. 1፡8፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2 አንብብ። ከዚህ ምንባብ ተነሥተህ አማኞች በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አካል ውስጥ ስላላቸው ኃላፊነት የራስህን ማጠቃለያ ጻፍ።

## አራተኛ ቀን፡– የቅድመ–ጋብቻ ምክር

በአፍሪካ አንዳንድ አካባቢዎች ወላጆች ለልጆቻቸው የትዳር ጓደኛን ይመርጡላቸዋል። ቀኑንና ሰዓቱን፥ የሠርጉንም ዝርዝር ነገር ሁሉ ያዘጋጃሉ። በሌላ ስፍራ ወጣቶች እርስ በርሳቸው ይሳሳባሉ። ከዚያም ወጣቱ ወጣቷን ለሚስትነት እሺ ትለው እንደሆነ በደብዳቤ ይጠይቃታል። ከተስማማች ነገሩን ወደ ኅብረተሰብ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይወስደዋል። እነርሱም ከቤተሰቦቻቸውና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሆነው ሁሉንም ነገር በማዘጋጀት እንዲተጫጩና በኋላም እንዲጋቡ ያደርጋሉ።

በአንዳንድ ቦታዎች ወላጆችና ሽማግሌዎች ወጣቶችን በባሕላቸው ይመክሩና ያሠለጥኗቸዋል። ይህም አንድ ላይ የጋብቻ ኑሮ ሲጀምሩ ምን እንደሚጠበቅባቸው ለማስተማር ነው። በሌሎች አካባቢዎች ምንም እርዳታ ወይም ምክር ስለማይሰጥ ወጣቶች በጋብቻቸው ግንኙነት ውስጥ ምን እንደሚጠበቅባቸው አያውቁም።

እግዚአብሔር ጋብቻን በተመለከተ ለእኛ የጻፈልንን ለመማር እስቲ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንመልከት።

1. ለጋብቻ የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፡- ምሳ. 2፡16-17፤ ሚል. 2፡14 አንብብ። እግዚአብሔር የሚናገረው ጋብቻ ምን እንደሆነ ነው? በእግዚአብሔር ዓይን ጋብቻ ቋሚ መሆኑን እንድናስተውል ይህ እንዴት ሊረዳን ይችላል? ማቴ. 19፡1-5 አንብብ። |

እግዚአብሔር የጋብቻን ግንኙነት እንደ ቃል ኪዳን ተናግሮታል። ቃል ኪዳን ክብር ያለው ስምምነት ማለት ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን የሚያየው የተቀደሰና ቋሚ እንደሆነ ግንኙነት ነው። ስለዚህም ወንድ ሚስትን ሲያገባና ሴት ባልን ስታገባ በፈቃደኝነት አንዱ ለአንዱ ይሰጣጣሉ። በእግዚአብሔርና ለእውነተኝነታቸውና ለታማኝነታቸው ምስክርነት በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ለመረጡት የሕይወት ጓደኛቸው ቃል በመግባት ወደዚሁ ግንኙነት ይገባሉ። ጋብቻ የሚጀምረው ሁለት ሰዎች ለእርስ በርሳቸው እስከ መጨረሻ ዘመናቸው ድረስ ጥርት ያለና እንከን የለሽ ተስፋ በሚገቡበት ጊዜ ነው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 2፡18-25፤ 1፡28 አንብብ። ከዚህ ምንባብ ክፍል እግዚአብሔር ለምን ጋብቻን እንደመሠረተ ለማሳየት የተቻለህን ያህል ብዙ ምክንያቶችን ስጥ። |

እግዚአብሔር ጋብቻን ለምን እንደመሠረተ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶችን እናገኛለን።

ሀ. አዳም ጓደኛ አልነበረውም።

ከዚህ በላይ እንዳነበብከው እግዚአብሔር ለፈጠራቸው እንስሶች ሁሉ ስም ያወጣላቸው ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው። ከግልገሎቻቸው ጋር በሜዳው ላይ ሲፈነጩና በተራራው ላይ ሲሰማሩ ማየቱ ለአዳም ትልቅ ደስታን ሰጥቶት ነበር። ነገር ግን አዳምን የሚረዳው ጓደኛ፥ ከእርሱ ጋር የሚነጋገር፥ የሚተባበር፥ የሚያጽናናውና የሚያበረታታው አልነበረም። እግዚአብሔርም አለ፤ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» (ቁ. 18)። ለእርሱ የሚስማማው ረዳት አልተገኘም። አዳም ሙሉ አልነበረም፥ እግዚአብሔርም አዳም ለእርሱ የሚመች ረዳት ካላገኘ በስተቀር ሙሉ እንደማይሆን አየ። ስለዚህም ሴትን ፈጠረለት።

ለ. አዳም የጾታ ተጓዳኝ አልነበረውም።

እግዚአብሔር ሴት ለአዳም የቅርብ ተጓዳኝ ትሆነው ዘንድ ፈጠራት። እንዲህም አለ። «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» (ቁ. 24)። አዳም የቅርብ ተጓዳኝ ይፈልግ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ከአዳም የጎን አጥንት ጓደኛውን፥

አኩያውን፥ ጥልቅ ስሜታዊ ፍላጎቱን የምትካፈለውን ፈጠረለት። በአንዳንድ አገሮች ሴቶች ለወንዶች ምቾት ብቻ የተቀመጡ ናቸው። በጋብቻ አማካይነት የእርሱ ንብረት ሆና ልጆችን የምትወልድ ብቻ ትሆናለች። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ ግንኙነት ትምህርት ግን ከዚህ የጠለቀ ነው። ባልና ሚስት አንድ ይሆናሉ። ይህም የሚሆነው በሁሉ ነገር ጥልቅ በሆነ ደረጃ መከፋፈል እንዲችሉ ነው። ይህ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንዲሁም የሕይወት ዘርፎችንም ሁሉ ያጠቃልላል። (1ኛ ቆሮ. 7፥1-5፤ ዕብ. 13፥4 አንብብ)።

በዚህ ስፍራ «መተው» የመጀመሪያው መመዘኛ ነው። ከመተው ውጪ ምንም ዓይነት ጋብቻ ሊኖር አይችልም። በጋብቻቸው ጊዜ አንዱ ለአንዱ በሕዝብ ፊት ለታማኝነት ቃል ከተገባቡ በኋላ፤ ባልና ሚስቱ ወላጆቻቸውን በመተው ብቻቸውን መኖር ለመጀመር የሚቀጥለውን እርምጃ ይወስዳሉ። ወላጆቻቸውን በአካልም ሆነ በስሜት መተው አለባቸው። ወላጆችም ደግሞ እንዲሄዱ መፍቀድ አለባቸው።

እውነተኛ መተው ካለ እውነተኛ «መጣበቅ» አለ። መጣበቅ ማለት መለጠፍ፥ መያያዝ፥ አንድ ላይ መቆራኘት ማለት ነው። መጣበቅ ለአንድ ሰው እስከ መጨረሻው ድረስ የሚኖር የተለየ ፍቅር ነው። በታማኝነት ለመኖር የሚወስነው የበሰለ ፍቅር ነው። እናም ከአንዱ ሰው ጋር ሕይወቱን በሙሉ መካፈል ነው። አንድ ላይ የተጣበቁ ሁለት ቁራጭ ወረቀቶች ከተለያዩ ይቀደዳሉ፥ እናም ይጣላሉ። እንደዚሁ መፋታት ከተከሰተ ሁለቱም ተጋቢዎች እንዲሁም ልጆች ይጎዳሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ሥጋቸውን ብቻ ሳይሆን ያላቸውን ነገር ሁሉ ማለትም ንብረታቸውን፥ አሳባቸውን፥ ስሜታቸውን፥ ደስታቸውንና ኃዘናቸውን፥ ተስፋቸውንና ፍርሃታቸውን፥ ስኬታማነታቸውንና ውድቀታቸውን ሁሉ ተካፍለዋል። ይህ የጋብቻ የውስጠኛው ትርጉም ነው። እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚፈልገው ይህንን ነው።

ሐ. ጋብቻ እግዚአብሔርን የሚመስሉ ልጆች እንዲያድጉ ያደርጋል

ዕብራውያን 13፥4 «መኝታው» ወይም የመቀራረቡ ስፍራ በጋብቻ ውስጥ ንጹሕ መሆን እንዳለበት ይነግረናል። እግዚአብሔር ይህን ጥልቅ የፍቅር መግለጫ ስሜት አክብሮታል። ይህ ለሁለቱ ብቻ ነው፤ እናም በሌላ ግንኙነት መቃወስ የለበትም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ባረካቸውና እንዲባዙ ምድርንም እንዲሞሏት ተናገራቸው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆኑ በጋብቻ ውስጥም ልክ እንደ እግዚአብሔር በረከት ልንቀበላቸው ይገባል።

ጋብቻ ተመሳሳይ እምነት ካለው ሰው ጋር የሚመሠረት፥ የጸናና የማይፈርስ ግንኙነት ነው። እናም ለእያንዳንዱ ተጓዳኝ የጓደኝነትን ፍላጎት ያሟላል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ለተጋቡ ተጓዳኞች ይደሰቱ ዘንድ ያሰበውን የጠበቀ ግንኙነት ይጨምራል፤ ይህም የግብረ ሥጋ ግንኙነትንም ጨምሮ ሁሉንም የሕይወት መስክ የሚያካትት ነው። ጋብቻ ለልጆች ውልደትና ቤተሰባዊ ሕይወት ደስታ፥ ሕጋዊነትንና ትክክለኛነትን ይከስታል።

2. ልታገባ ባቀድህ ጊዜ ራስህን ልትጠይቃቸው የሚገቡህ ጥያቄዎች፡-

ሀ. እኔ የወደድሁት ሰው ዳግመኛ የተወለደ አማኝና የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መጨረሻ ባለሥልጣን አድርጎ የሚመለከት ነውን? ያ ሰው እግዚአብሔርን በማወቅ፥ በቃሉና በጸሎት ሕይወቱ ያድጋልን?

ለ. ራሱን የሚቆጣጠርና ራሱን የሚገዛ ነውን? እርሱ ወይም እርሷ የሥጋውን ፍላጎት፥ አሳቡን፥ ባሕርዩን ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት መቆጣጠር የሚችል ነውን?

ሐ. ያ ሰው ዓላማና መሻት፥ እንዲሁም የሕይወት ግብ አለውን? በኃላፊነት ቦታ ላይ የመሥራት ልምድ አለውን? እርሱ/እርሷ ለዝርዝር ነገሮች አትኩሮት ይሰጣሉን? ቀጠሮ ያከብራሉን?

መ. ስሕተቱን ይቀበላልን? ለዚያስ ኃላፊነትን ወስዶ ከስሕተቱ ይማራልን?

ሠ. ገንዘብ መያዝ ይችላልን? እርሷ/ እርሱ በገንዘብ ጉዳይ ኃላፊነት ሊጣልበት የሚችል ነውን?

ረ. እርሷ/እርሱ ለቤተሰቡ፥ ለወላጆቹ ለወንድሞቹና ለእኅቶቹ ፍቅርን፥ አክብሮትንና አድናቆትን ያሳያልን? እርሱ/እርሷ ቤተሰቤንና ወላጆቼን ያከብራልን?

ሰ. የተፈታና በራሱ እንኳ ለመሳቅ የሚችል ነውን? በባሕርዩ የረካና ደስተኛ ነውን?

ሸ. ጥበብን የተሞላና በሌሎች ነገሮች ላይ ያልተደገፈ ውሳኔን መስጠት ይችላልን?

ቀ. ይህ ሰው ስለ ቤተሰብና ስለ ልጆች አስተዳደግ ያለው አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአንተ/ከአንቺ አስተሳሰብ ጋር የተስማማ ነውን?

3. ቅድመ–ጋብቻ የማማከር ክፍለ ጊዜ

ለመጋባት የሚፈልጉ ወጣቶችን ለማማከር ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በአእምሮ በመያዝ የቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች ወደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ከመግባታቸው በፊት ብዙ የማማከር ክፍለ ጊዜያት ልንሰጣቸው እንደ ሚያስፈልግ ግልጽ ነው። እነዚህ ወጣቶች በጋብቻ ውስጥ የሚመጡትን ኃላፊነቶችና ጥቅሞች እንዲረዱ ለመርዳት ለአምስትና ለስድስት ሳምንታት የምክር ጊዜ መስጠት መልካም እንደሆነ ይታመናል።

በማማከር ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሊሸፈኑ የሚገባቸው ርእሶች፡–

ሀ. የተጋቢዎቹን የምርጫ ትክክለኛነት ወስን (2ኛ ቆሮ. 6፡14–18)።

ለ. ከጋብቻ ውስጥ የሚጠብቁትን ነገር ጠይቃቸው። እያንዳንዳቸው ለጋብቻ ግንኙነት ምን የሚያዋጡት ነገር አለ? ሁል ጊዜ ትርፍን ለማግኘት ይመኛሉ? ወይስ ጋብቻቸውን አስደሳች ግንኙነት ለማድረግ ያላቸውን ለመስጠት ተዘጋጅተዋልን?

ሐ. ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ አስብ። ተነጋገርበት።

መ. በጋብቻ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ምን እንደሚሆን ጠይቃቸው። ትዳራቸውን ስኬታማ ለማድረግ ድርሻቸውን ያስተውሉ ዘንድ ምራቸው።

ሠ. በግልና በኀብረት ዕለታዊ የጥሞና ጊዜን እንዲመሠርቱ ምራቸው። የቤተሰብ የጥሞና ጊዜ እንዴት እንደሚኖራቸውና ልጆቻቸውንና ሌሎች የቤተሰቦቻቸውን አባላት ጨምሮ እንዴት እንደሚያዘጋጁ አሳያቸው።

ረ. በጋብቻ ውስጥ ባለው የግንኙነት አስፈላጊነት ላይ ተወያዩ።

ሰ. እውነተኛ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ (1ኛ ቆሮ. 13)።

ሸ. ከአማቶችና ከአማቾች ጋር ጥሩ ዝምድና እንዲያዳብሩ እርዳቸው

ቀ. ጥበብ የተሞላበት የገንዘብ አጠቃቀምና የበጀት ዕቅድ አወጣጥ መመሪያን ስጣቸው።

በ. ምን ያህል ልጆች ሊኖራቸው እንደሚያስፈልግ፥ የሥነ ሥርዓታቸውን ሁኔታ፥ ለክርስቶስ ልጆቻቸውን የማሠልጠን ኃላፊነትን ተወያዩ።

ተ. ስለ ሠርጉ ዝርዝር ሁኔታ ማለትም ስለ ሠርጉ ቀን፥ ስለሚጠሩት ሰዎች፥ ስለ ዝግጅቱ ተወያዩ።

ቸ. ባሕሎች በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ካለው ባሕል ጋር የሚሄዱ ከሆነ ሊታዩ ይገባል።

ተጋቢ የሆኑ ወጣቶች ጤነኛ የሆነን ጋብቻ እንዲመሠርቱ የማድረግ ዝግጅት በቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ አንድ ዋና አገልግሎት መታየት አለበት። በዚህ አጭር ምዕራፍ ውስጥ እንደዚህ ዓይነቱን በማማከር ውስጥ የሚገባውን ሁሉ መናገር የማይቻል ነው። ተጨማሪ እርዳታ መስጠት የሚችሉ በዛ ያሉ መጻሕፍት አሉ። አንዱ «የጋብቻ ዝግጅት» የተባለው መጽሐፍ በኤስ. አይ. ኤም ማተሚያ ቤት የታተመው ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም «በወጣቶች የሚነሡ ጥያቄዎች»፥ «ትዳርና የቤተሰብ ሕይወት 1ኛ እና 2ኛ መጽሐፍ» የተባሉ መጻሕፍትም አሉ።

---

17ኛ ቀን፡- ትምህርት አሥራ ስድስትን ከልስ። በሳምንታዊ ስብሰባ ውይይት ጊዜ ድርሻ እንዲኖርህ ተዘጋጅ

---

## ሳምንታዊ ስብሰባ

የተለመደውን ደንብ ተከተል

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ትክክለኛ ንስሐ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተወያይ። ንስሐ ለደኅንነት የመጀመሪያ እርምጃ ነው ለማለት የምንችለው ለምንድን ነው?
2. ስለ እምነት ተነጋገሩ፤ ዳግመኛ ለመወለድ ማመን ብቻ በቂ ነውን? ሌላስ ምን ያስፈልጋል?
3. ስለ አማኞች ጥምቀትና ስለ ጌታ እራት ተወያዩ። እነዚህ ሥርዓቶች በቤተ ክርስቲያኖቻችሁ ውስጥ ትምህርትና ጥንቃቄ የተሞላበት ማብራሪያ ተደርጎባቸዋልን?
4. በቤተ ክርስቲያን ሥራ ውስጥ እያንዳንዱ አባል ትርጉም ባለው መንገድ ሊሳተፍ በሚችልባቸው መንገዶች ላይ ተወያዩ።

5. ወጣቶችን ለጋብቻ ለማዘጋጀት ምን የማማከር አገልግሎት ተደረገ? በቤተ ክርስቲያናችሁ ያሉት ጋብቻዎች በመሠረቱ ጤነኞች ናቸውን? ጉድለት ያለበት ቦታ የት ነው? ቤተ ክርስቲያንስ እንዴት ልትረዳ ትችላለች?

# ትምህርት አሥራ ሰባት

## የክርስቲያናዊ ትምህርት አመራር

### አንደኛ ቀን፦ መሪ የመሆን ጥሪ

በዚህና በሚቀጥለው ምዕራፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ መጋቢዎች፥ ሽማግሌዎች፥ በጠቅላላው ስለ መሪነት መመሪያን እንሰጣለን። ከመሪነት ጥሪና ከውስጣዊ ኃይሉ በመጀመር የመሪውን ብቃትና የተለያዩ ኃላፊነቶችን ጥምር እናጠናለን። ከዚያም ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ችግሮች አንሥተን የመፍትሔ አሳቦችን እናቀርባለን። ስለ መሪነት ሥልጠና አስፈላጊነት፥ ስለ ውክልናና ሪፖርት ስለ መስጠት፥ በመጨረሻ ስለ ረዥም ጊዜ ዕቅድ እንነጋገራለን።

ጥሩ መሪዎች ለጤነኛ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል አንዳንድ ሰዎች የመሪነት ስጦታ እንዲኖራቸው አድርጓል።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 12፡3-8 አንብብ። ሁሉም አንድ ዓይነት ስጦታ አላቸውን? በዚህ ጥቅስ ውስጥ የምታገኛቸውን ስጦታዎች በዝርዝር ጻፍ። የመሪነት ስጦታ ያለው ሰው ስጦታውን መጠቀም የሚችለው እንዴት ነው? |

1 የመሪነት ስጦታ

ሀ. የተከበረ መሻት

1ኛ ጢሞ. 3፡1 እንዲህ ይላል። «...ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል...»። ጳውሎስ መልካም ወይም የተከበረ ሥራ ይለዋል። የሚናገረው ስለ ኤጲስ ቆጶስ የሥልጣን ስፍራ ሳይሆን ስለ ኤጲስ ቆጶስ አገልግሎት ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ሥራ የመመኘት አሳብ መምጣት ያለበት ለክርስቶስ ካለው የጠለቀ ፍቅርና ለቤተ ክርስቲያንና ለዕድገቷ ካለው እውነተኛ ፍቅር ነው።

ጳውሎስ እነዚህን ቃላት በጻፈ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአስቸጋሪ ስደት ውስጥ እያለፈች እንደነበር ልናስታውስ ይገባናል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኤጲስ ቆጶስ ወይም መሪ መሆን ቀላል ተግባር አልነበረም። ክብርና ሥልጣን እንዲሁም የሕዝብ እውቅናን የሚሰጥ ቀላል ሥራ ስለሚመስላቸው አንዳንዶች መጋቢ ወይም መሪ ለመሆን ይፈልጋሉ። ነገር ግን በጳውሎስ ጊዜ እንዲህ አልነበረም። ብዙ ጊዜ መሪዎች ትላልቅ አደጋዎች ይገጥሙዋቸው ነበር። መሪ መሆን ብዙ ጊዜ ችግርን፥ መዋረድንና መገፋትን የሚያስከትት ነበር

ማንኛውም ሰው የእኔነት ወይም የራስ ወዳድነት ውስጣዊ ዓላማ ካለው ጥሩ መሪ ሊሆን አይችልም። ኤርምያስ ባሮክን ሲመክረው፥ «ለራስህ ታላቅ ነገርን ትፈልጋለህን? አትፈልገው» (ኤር. 45፡5) ብሎታል። ባሮክ በግብጽ

አገር መሆንና ከኢየሩሳሌምም ምርኮ ማምለጥ ከወንድሞቹ ጋር ሊደርስበት ካለው መከራ እንደሚጠብቀው አስቦ ነበር። ኤርምያስ ትልቅ ለመሆን እንዳያስብ አስጠንቅቆት ነበር። ጌታ የት እንዳለ ስለሚያውቅ ከእግዚአብሔር ጋር በቅንነት ካልሄደ ያንኑ ዓይነት ቅጣት ያደርግበታል። (ይህንን አረጋግጥ።)

የማስጠንቀቂያው አስኳል ትልቅነትን «ለራስህ» መፈለግ እንደሌለብህ ነው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «. . . ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማር. 10፡43-45) ብሷል። መሪ መሆን እኔነት የሌለበት አገልግሎት ለሰዎች የመስጠት ጥሪ ነው። ጌታችን የእንደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ፍጹም የሆነ ምሳሌ ነው። እርሱ እንዲገለገል አልመጣም፤ ነገር ግን ሊያገለግልና ሕይወቱን ለመስጠት መጣ። ስለዚህም ምክንያት ለመምራት ችሎታ ነበረው።

እንደ መሪ ለመሥራት ብትመኝና እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ እንደሰጠህ ቢሰማህ መልካም ነው። በልብህ ያለውን መነሣሣት ደጋግሞ መመርመርን ይጠይቃል። ጥልቅ የሆነው ምኞትህ እግዚአብሔርን ለማክበርና ደስ ለማሰኘት፥ እንዲሁም ሰዎችህን በትጋት ለማገልገል እስከሆነ ድረስ በሥራህ የተባረክህ ትሆናለህ።

ለ. መለኮታዊ የሆነ ማስቻል

ሙሴ እግዚአብሔር ለአርባ ዓመታት በኃይል የተጠቀመበት ታላቅ መሪ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ እንዲያወጣና የተስፋ ምድር ወደሆነችው ወደ ምድረ ከነዓን እንዲመራቸው በጠራው ጊዜ ሙሴ ፈርቶ ነበር።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፡- ዘጸአት 3፡1 እስከ 4፡17 አንብብ። ሙሴ መሪ ላለመሆን ያቀረባቸውን ተቃውሞዎች በዝርዝር ጻፍ። በታውን ይፈልገው ነበርን? ሙሴ እርግጠኛ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ጻፍ። ሙሴ በመጨረሻ ምን አደረገ? (ቁጥር 18) |

1. እግዚአብሔር «ከአንተ ጋር እሆናለሁ» ብሎት ነበር (ዘጸ. 3፡12)

ሙሴም እግዚአብሔርን «ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ» አለ (ቁ. 11)። ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ሥራ በሚገጥመን ጊዜ ብቁ አለመሆናችን ይሰማናል። እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገር የነበረው «የአንተ ማንነት ምንም አይደለም። ዋናው ነጥብ እኔ ካንተ ጋር መሆኔ ነው።» ታያለህ፥ እግዚአብሔር ያለው የሕዝቡን መከራና ጭንቀት እንዳየና ሊያድናቸው እንደመጣ ነው (ቁ. 7-10)። አንዳንድ ጊዜ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ እንደሚሠራ እንረሳለን። እኛ የእርሱ መሣሪያዎች ብቻ ነን። 1ኛ ቆሮ. 3፡9፥ «ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» ይላል።

2. እግዚአብሔር እንዲህ «እኔ እኔ ነኝ» ይላል (ዘጸ. 3፡14-15)።

ሙሴ የእስራኤል ሽማግሌዎች አይቀበሉኝ ይሆናል ብሎ ስለፈራ «ማን ላከኝ እላለሁ?» ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ። እግዚአብሔርም «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ አለው፤ እንዲህ ለእስራኤል ልጆች ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው» (ዘጸ. 3:14–15)። «እኔ ነኝ» የሚለው «ያለና የሚኖር» የጊዜ መግለጫ ነው። ይህንን አገላለጽ በመጠቀም እግዚአብሔር ለሙሴ የሚናገረው ለሚፈልገው ነገር ሁሉ ከእርሱ ጋር እንዳለ ነበር። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ያው የማይለወጥ ነው። እናም ማንኛውም ፍላጎቱን ሊያሟላ ዝግጁ ነው። ጥበብ በሚያስፈልገው ጊዜ እግዚአብሔር እዚያ ነበር (ያዕ. 1:5)። ድል የሚያስፈልገው ከሆነ እግዚአብሔር እዚያ ነበር (1ኛ ቆሮ. 15:57)። መጽናናት በሚያስፈልገው ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ ነበር (1ኛ ጴጥ. 5:1)። እግዚአብሔር ታላቁ ያለና የሚኖር፥ በራሱ ህልውና የሆነ፥ የሚያስፈልገንን ሁሉ የሚያሟላ አምላካችን ነው።

3. እግዚአብሔር «እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፥ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ» አለው (ዘጸ. 4:12)።

የእስራኤል መሪዎች እግዚአብሔር ሙሴን እንደላከው እንዲያውቁ መግለጫ አድርጎ እንዲጠቀምበት፥ እግዚአብሔር ለሙሴ ሦስት ተአምራት አሳየው። ከዚህ በኋላ እንኳን ሙሴ አለመብቃት ስለተሰማው እንዲህ አለ፤ «አፈ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ» (ዘጸ. 4:10)። እግዚአብሔርም አፉን የሠራው እርሱ እንደሆነ የሚናገረውን እንደሚያስተምረውና እንዲናገርም እንደሚረዳው አረጋገጠለት።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ መስክ ለመሪነት ቀርበህ ከሆነና እግዚአብሔርም ይህን እንድታደርግ እንደጠራህ ከተሰማህ፥ ምንም እንኳን አለመብቃት ቢሰማህም፥ ሦስት ልታስታውሳቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልሃል። እርሱ ታላቅ ያለና የሚኖር ነው። እናም ይረዳሃል፤ ደግሞም ያስተምርሃል። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» (ፊልጵ. 2:13)።

2. የመሪው የኃይል ምንጭ።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡– ሕዝ. 22:30–31፤ ኤር. 5:1፤ 1ኛ ሳሙ. 13:13–14 አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች አገላለጽ፥ እግዚአብሔር ምንን ይፈልጋል? በመጨረሻው ምንባብ ያገኘው ማንን ነው? እግዚአብሔር ለምን በእርሱ መጠቀም ቻለ? |

ሀ. የእግዚአብሔር ቃልና ማሰላሰል

እግዚአብሔር ሰዎች መሪ እንዲሆኑ ይፈልጋል። አንድ ዓይነት ሰዎችን ይፈልጋል። ምንም ሰዎች ከሌሉ እግዚአብሔር ዓላማውን ሊፈጽም አይችልም። ዳዊትን የመረጠበት ምክንያት ዳዊት እንደ ልቡ ስለሆነለት ነበር። በሕዝቡም ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ አዝዞታል (1ኛ ሳሙ. 13:14)።

አንድ ሰው እንደ እግዚአብሔር ልብ የሚሆነው እንዴት ነው? ዳዊት በጎች ሲጠብቅ ብዙ ዓመታትን አሳልፎአል። ብዙዎቹን መዝሙሮቹን የጻፈው ገና ወጣት ሆኖ ሳለ እንደነበረ እናምናለን። በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ ብሎ

የሚቀመጥበትና የእርሱን ታላቅነት የሚያሰላስልበት ጊዜ ነበረው። መሪ ለመሆን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማሰላሰል ያስፈልግሃል። ጌታ ለኢያሱ ሲናገረው፥ «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፥ የዚያን ጊዜ መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልህማል» ብሎት ነበር [ኢያ. 1፡8፤ መዝ. 1፡2-3፤ (119)፡97 በተጨማሪ አንብብ]።

እግዚአብሔርን ለማወቅ ወደ ቃሉ ወስጥ መግባትና ቃሉም ወደ እኛ ውስጥ መግባት አለበት። ወደ ቃሉ ውስጥ የምንገባው ሲሰበክ ስንሰማ፥ ስናነበው፥ ስናጠናውና በቃላችን ስንይዘው ነው። ቃሉን በምናሰላስለው ጊዜ ወደ ውስጣችን ይገባል። ወደ ውስጣችን እንዲገባ ጊዜንና በጸጥታ ማሰላሰልን ይጠይቃል። ከዚያም በሚናገረን ነገር ለመታዘዝ ምላሽ የሚሰጥ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል።

ለ. ጸሎት

4ኛ ጥያቄ፡- ሉቃ. 18፡10-14 አንብብ። ከእግዚአብሔር ዘንድ መልስ ያገኘው የማን ጸሎት ነበር? የሌላኛው ጸሎት ያልተመለሰው ለምን ነበር? ይህ ታሪክ ስለ ጸሎት ያስተማረህን አንድ ነገር ጻፍ።

እግዚአብሔር በቃሉ ይናገረናል፤ እኛም በጸሎት ለእርሱ እንናገራለን። ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በምንመጣበት ጊዜ የትሕትና መንፈስ ሊኖረን ይገባል። መዝሙር (51)፡17፥ «የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው። የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» ይላል። አለመብቃታችንን በምንገልጽበት ጊዜ እግዚአብሔር ይሰማናል፤ ፍላጎታችንንም ሁሉ ያሟላልናል (ፊልጵ. 4፡19)።

5ኛ ጥያቄ፡- ያዕቆብ 5፡16 አንብብ። ጸሎትን ውጤታማ የሚያደርገው ምንድን ነው?

የሐዋርያት ሥራ 12፡5 በእግዚአብሔር ዘንድ ስለተሰማ ሌላ ጸሎት ምሳሌን ይሰጠናል። ጴጥሮስ በእስር ቤት ሆኖ ፍርድን እየተጠባበቀ ነበር። «በቤተ ክርስቲያንም ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።» በትጋት የሚካሄድ ጸሎት ነበር። እግዚአብሔር መልስ ሰጠ? አዎን ተአምራዊ በሆነ መንገድ መልስ ሰጥቷል። ታሪኩን ካላወቅህ የሐዋርያት ሥራ 12፡1-19 አንብብ። ጴጥሮስ ምንም እንኳን በ16 ወታደሮች ተከብቦ በየቀኑ ቢጠበቅም በመልአክ ተፈትቶ ነፃ መሆን ችሏል።

6ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 11፡6 አንብብ። በጸሎት ውስጥ የሚያስፈልግ አንድ ተጨማሪ ነገር ተጠቅሷል። ያዕቆብ እግዚአብሔር አይመልስም ብሎ የሚጠራጠር ሰው ምንም ነገር እንደማያገኝ ይናገራል። የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚመታ የባሕር ሞገድ ይመስላል። ሁለት አሳብ ያለውና በመንገዱ ሁሉ የማይጸና ሰው ነው። ማመን እንጂ መጠራጠር የለበትም (ያዕ. 1፡6-8)።

በዕብራውያን የተጠቀሰው ምንባብ ስለ ጸሎት ሌላም እውነት ያስተምረናል። እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ በእውነት ካላመንን በስተቀር እርሱን ማስደሰት አንችልም። እግዚአብሔር እንዳለ ማመን አለብን። እግዚአብሔር ስሙ «ያለና የሚኖር» መሆኑን እንደተናገረ

ማስተዋል አለብን። እርሱ አለ። ስለዚህም ይመልሳል። እርሱን በቅንነት ለሚፈልጉትም ዋጋቸውን ይሰጣቸዋል (ዕብ. 11፡6)።

> 7ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ዮሐ. 5፡14-15 ደግሞም ዮሐ. 16፡24 አንብብ። በምንጸልይበት ጊዜ ማስታወስ ያለብን ሁለት ነገሮች ጥቀስ።

በመጨረሻም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መጠየቅ አለብን። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የምንችለው ቃሉን በምናነብና በምናሰላስልበት ጊዜ ብቻ ነው። በተጨማሪም በኢየሱስ ስም መጠየቅ አለብን። እርሱ ታላቅ ሊቀ ካህናችን ነው። «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» (ዕብ. 4፡16)።

> 8ኛ ጥያቄ፡- ስለ ጸሎት የተማርናቸውን ስድስት ነጥቦች ዘርዝር። እያንዳንዱን መልስህን የሚደግፉ ተስማሚ ምንባብን ስጥ። ምናልባት ይህንን መመሪያ ስለ ጸሎት በምታስተምርበት ጊዜ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

## ሁለተኛ ቀን፡- መሪዎች የሚያሟሏቸው አስፈላጊ ብቃቶች -1

ባለፉት ምዕራፎች በክርስቲያናዊ ትምህርት የተለያዩ ዘርፎች ለመሪነት ስለሚያስፈልጉ ብቃቶችና መመዘኛዎች ተወያይተናል። በዚህና በሚቀጥለው ትምህርት የአንድን ታላቅ መሪ የሕይወት ታሪክና ውጤታማ ያደረገውን ምሥጢር እንመለከታለን።

> 9ኛ ጥያቄ፡- ነህ. 1፡1-4 አንብብ። ይህን መጽሐፍ ማን ጻፈው? የት ነበር? በዚያ የነበረው ለምን ነበር? (የብሉይ ኪዳን አሰሳ ጥናትህን አስታውስ።) ሥራው ምን ነበር? የሚሠራው ለማን ነበር? ከወንድሞቹ ከነአናኒ የሰማው ምን ነበር? ይህን ዜና እንዴት አስተናገደው?

ነህምያ የንጉሥ አርጤክስስ ጠጅ አሳላፊ ነበር። ንጉሡ ወይን ከመጠጣቱ በፊት እርሱ ይቀምሰው ነበር። ደግሞም ንጉሡ ከመብላቱ በፊት ምግቡን ይቀምስለታል። በዚህ ደረጃ ምክንያት በንጉሥና በወይን ጠጅ ቀማሹ መካከል መቀራረብ የነበረ ሲሆን፥ ታሪክ አጥኚዎች እንደሚሉት በንጉሡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነበረው።

ይህም ሆኖ ነህምያ አገልጋይ ነበረ። የእርሱ ሕዝቦች ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን አሸንፎ በያዛት ጊዜ በምርኮነት መጡ። ከጦርነቱ የተረፉት ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። ይህ መጽሐፍ በሚጀምርበት ጊዜ ነህምያ በፋርስ ዋና ከተማ በሱሳ ነበር። በዚያን ጊዜ ባቢሎናውያንን አሸንፈው የዓለም ገዢዎች ሆነው ነበር።

በቂሮስ ትእዛዝ አይሁዶች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸው ነበር። በዘሩባቤል መሪነት አንድ ቡድን ተመለሰ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ አንድ ቡድን በዕዝራ መሪነት ተመለሰ። ዕዝራ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ አደሰ። አናኒ የነህምያ ወንድምና አንዳንድ ሰዎች ከይሁዳ ለጉብኝት መጡ። ነህምያም ከምርኮ ስለተመለሱት ወይም ስላመለጡት ሰዎች ጠየቃቸው። የተሰጠው መልስ እርሱን በጣም አሳዘነው። በዚያ ያሉት ቅሬታ በታላቅ መከራና ስድብ ነበሩ። የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈርሷል። በሮቿም ሁሉ በእሳት ተቃጥለው ነበር።

10ኛ ጥያቄ፡- ነህምያ ቀጭ ብሎ አለቀሰ። ለጥቂት ቀናት አዘነ። እናም በእግዚአብሔር ፊት ጾመ፤ ጸለየም። ወደ እግዚአብሔር የጮኸውን የልቡን ጩኸት ከ1፡5-11 አንብብ። በነህምያ ውስጥ የሚታየውን የመሪነት ብቃት ዘርዝር።

1. የመሪነት ብቃት ዓይነተኛ ባሕርይ

ሀ. መሪ ስለሚያስፈልጉ ነገሮች ግልጽ ግንዛቤ ያለውና የሚገደው ነው።

ነህምያ ሕዝቦቹ በኢየሩሳሌም እየተሠቃዩ ስለነበር በጣም ተነክቶ ነበር። የነበሩበትን ሁኔታ ተረድቶ ነበር። ስለ ችግሮቻቸው በቀሎ የሚሰማው ሰው ነበረ። በጾምና በጸሎት በመትጋት ከእግዚአብሔር መፍትሔ ይፈልግ ዘንድ ስለ ጉዳዩ ግድ ይለው ነበር።

ለ. ጠንካራ መሪ ችግሮችን ሁሉ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል።

ነህምያ ጸሎቱን ሁሉ በሁሉ የሆነ አምላኩን በማወደስ ጀምሮ ለሕዝቡ ለእስራኤል የሚጸልየውን ጸሎት እንዲሰማውና እንዲመለከተው ተማጸነ። የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት ተናዘዘ። እግዚአብሔር ለተመረጡት ሕዝቦቹ የገባውን የተስፋ ቃል አሳስቦ እንዲሰማው ደግሞ ጠየቀ። በመጨረሻም እንዲህ አለ፡- «ዛሬም ለባሪያህ አከናውንለት፥ በዚህም ሰው ፊት ምሕረትን ስጠው» (ቁ. 11)።

ሐ. መሪ ሥርዓት ያለውና ፍላጎቶችን ለማርካት ብቁ ሆኖ የሚገኝ መሆን አለበት፤ ብርቱ፥ ደፋር፥ ዘዴኛ፥ እንዲሁም ተግባቢ ነው።

ነህምያ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ሄዶ ለመርዳት ፈቃደኛ ነበር። ይሁንና ነፃ ሰው አልነበረም። የሚያስፈልገውን ፈቃድ ሁሉ አግኝቶ እንዲሄድ በንጉሡ ልብ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲሠራ ይፈልግ ነበር። ይህም ድፍረትን፥ ዘዴኝነትንና ተግባቢነትን ይጠይቃል (ነህ. 2፡1-10 አንብብ)።

ነህምያ በቅንነት በመጸለይ ነገሩን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ። ጊዜውን አላባከነም። ነገር ግን በሚገባ በማሰብ ሊያቅድ ጊዜን ወሰደ። ምሳሌ 16፡9 «የሰው ልብ መንገዱን ያዘጋጃል፥ እግዚአብሔር ግን መንገዱን ያቀናለታል» ይላል።ከንጉሡ ጋር እንዲነጋገር እግዚአብሔር ዕድልን ከአራት ወራት በፊት አልከፈተለትም ነበር። ንጉሡን በሚያገለግልበት ጊዜ ፊቱ የኃዘን ፊት ሆኖ አያውቅም ነበር። ነገር ግን ረጅሙ ጥበቃ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቶ ነበር። ንጉሡ ለምን የኃዘን ፊት እንዳሳየ ጠየቀው። ነህምያ ፈርቶ ነበር፤ ነገር ግን በጀግንነት ምክንያቱን ነገረው። ንጉሡም፥ «ምን ትፈልጋለህ?» ብሎ ጠየቀው። ነህምያም በፍጥነት በልቡ ጸለየና መለሰ፤ «ንጉሡን ደስ ቢያሰኘው...ወደ ይሁዳ ከተማ ይላከኝ... እኔም እሠራው ዘንድ» (2፡5)። ነህምያ በተጨማሪም በወንዝ ማዶ ላሉት እንዲያደርሱኝ በቤቱ አጠገብ ላሉ የግንብ በሮች እንጨት እንዲሰጠኝ ለንጉሥ አሳፍ ደብዳቤዎች ይሰጡኝ አለ።

እግዚአብሔር ሠርቶለት ነበር። ይልኩት ዘንድ ንጉሡን ደስ አሰኝቶ ስለነበር የሚፈልገውን ደብዳቤ ሰጠው። ንጉሡ ይጠብቁት ዘንድ ከእርሱ ጋር የሠራዊቱን አለቆችና ፈረሰኞችን ሰደደ። «እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው ለእርሱ... ክብር ይሁን...» (ኤፌ. 3፡20)። ምሳሌ 21፡1፥

«የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል» ይላል።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፦ ነህ. 2፡11–16 አንብብ። ነህምያ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ምን ነበር? ለምን ነበር ያንን ለማድረግ ጥበበኛ የሆነው? ስለ ጥሩ መሪ ይህ ምን ያስተምረናል? |

መ. አንድ መሪ በሕዝብ ፊትና በግል ሕይወቱ የታመነ መሆን አለበት። በጥንቃቄ ለማቀድ ጊዜን ይወስዳል።

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ ቢያንስ ወደ 1300 ኪ. ሜ ተጉዟል። በጣም ተንሣሥቶ ነበር። ይሁንና ብቸኛ የመሆንን ዋጋ አውቆ ነበር። መሪ ሁልጊዜ ከሕዝቡ ዓይን አይወጣም ብለን እናስብ ይሆናል። ሆኖም ነህምያ በዚያ ለሦስት ቀን ቆየ (2፡11)። ነህምያ በሚገባ ለማሰብና ጥበብ የተሞላበት ዕቅድ ለማውጣት ይችል ዘንድ ብቻውን ሆኖ ነበር። በሕዝቡ ፊት ታማኝ እንደሆነ ሁሉ በግሉም እንዲሁ ነበር። ችግሮችን ለመገንዘብና በጸሎት የተደገፈ ዕቅድ ለማውጣት ጠንቃቃ ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር መሥራት ያለበትን ነገር በልቡ ሊያስቀምጥበት ችሎ ነበር።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፦ ነህ. 2፡17–18 አንብብ። ነህምያ ዕቅዱን ያቀረበው እንዴት ነበር? የሕዝቡስ ምላሽ ምንድን ነበር? |

ሠ. መሪ በከፍተኛ ደረጃ የተነሣሣና ሌሎችን ለሥራ የሚያንቀሳቅስ ነው።

ነህምያ ከሕዝቡ ጋር (ራሱን አንድ አድርጎ) እንዲህ አለ፤ «ያለንበትን ጉስቁልና ታያላችሁ።» ያለውን ችግር በትክክለኛ መንገድ አቀረበ «ኢየሩሳሌም እንደ ፈረሰች፥ በሮችዋም በእሳት እንደ ተቃጠሉ» የመፍትሔውን አሳብ አቅርቦ ነበር። «ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ።» ምክንያትም ሰጣቸው– «መሳለቂያ እንዳንሆን።»

ሕዝቡን በቶሎ አንድ ነገር ስላልሠሩ ቢወቅሳቸውና ቢኰንናቸው ለሥራው ከፍተኛ የሆነ ቅንዓት ይኖራቸዋል ብለህ ታስባለህን? ብዙ ጊዜ ችግርን የሚፈጥሩትን ሰዎች መርምረን በማግኘት እየወቀስናቸው እኛ ወጥመድ ውስጥ እንገባለን። ይህ ለችግሩ መፍትሔ ይሰጠዋል ወይስ የነገሩን ሁኔታ ይለውጣል?

ነህምያ እግዚአብሔር እስከዚህ ነጥብ ድረስ እንዴት እንዳደረሰው ምስክርነትንም ደግሞ ሰጥቷል። ሕዝቡም እርሱ ሊታመኑበት የሚችሉት መሪ እንደሆነ ለማየት ችለው ነበር። ምላሻቸው እንዴት ነበር? «እንነሣና እንሥራ» አሉ።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፦ በነህምያ ላይ እንዳየነው የመሪን ዓይነተኛ ባሕርያት ዘርዝር። |

## ሦስተኛ ቀን፦ አስፈላጊ የሆኑ የመሪዎች ዓይነተኛ ባሕርያት–2

የጌታ ሥራ እምብዛም ያለ ተቃውሞ አይካሄድም። ይህንንም በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከት ሲሆን፥ ከራሳችን ልምምድም እናውቀዋለን። የነህምያ ሥራ ወዲያውኑ ተቃውሞ ገጠመው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፦ 2፡19–20 አንብብ። የቅጥሩን እንደገና መገንባት የተቃወመው ማን ነበር? ተቃዋሚዎቹ የተጠቀሙበት ዘዴ ምን ነበር? የነህምያ ምላሽ እንዴት ነበር? |

ረ. አንድ መሪ ከተቃውሞ በላይ ለመሆን በእግዚአብሔር ላይ ይደገፋል። ተቃውሞን እንዴት መቋቋም እንደሚችል ያውቃል።

ማንኛውም መሪ ትችት ይገጥመዋል። ትችቱ እውነት ከሆነ ተቀብለን ነገሩን መለወጥ አለብን። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በትችት ውስጥ ይናገረናል፤ እንደዚያ ሲሆን ልንሰማውና በሕይወታችን ወይም በሥራችን አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን ልናደርግ ይገባል።

ትችቱ እውነተኛ ካልሆነና ከእግዚአብሔር ካልመጣ ጸንተን መቆም አለብን። ነህምያ ይህ ተቃውሞ እግዚአብሔርን ከማይፈሩና አይሁዳዊ ካልሆኑ ሰዎች እንደመጣ ያውቅ ነበር። የቅጥሩን ግንባታ ሊያስተጓጉሉ ፈልገው በነህምያና በሕዝቡ ላይ ያላግጡ ነበር። ይህን ጉዳይ በድፍረትና በዝምታ ያዘው። ቁጥር 20፥ «እኔም መልሼ የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል» አልኳቸው ይላል። ምንጩንም መርምሮና ተገንዝቦ እንዲህ አላቸው፤ «እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ዕድል ፈንታና መብት መታሰቢያም የላችሁም።»

ነህምያ በጥንቃቄ የግንባታውን ሥራ አጠናከረ። ምዕራፍ 3ን ተመልከት። ተቃውሞው ጠፍቷል ብለህ ታስባለህን? አይደለም። በ4፡1-3 የሰንበላጥን ጨካኝነት እናገኛለን። በጓደኞቹ ፊት ሠራተኞቹን ይሰድብ ነበር። ጦቢያም ተጨምሮ «በድንጋይ በሚሠሩት ቅጥራቸው ላይ ቀበሮ ቢመጣበት ያፈርሰዋል አለ» (4፡3)።

ነህምያ መልስ እንኳን አልሰጣቸውም። በጌታ ፊት ብቻ አያቀረበ (4፡4-5) ግንቡ ዙሪያውን ሁሉ የቁመቱ ግማሽ እስኪደርስ ድረስ መገንባት ቀጠሉ (4፡6)።

ይሁንና ነህምያ ያደረገው አንድ ነገር ሊያስገርመን ይችላል። ቁጥር 4፡5 እንደገና ተመልከት። እግዚአብሔር ስሕተታቸውን ይቅር እንዳይል ጠየቀ። አንዳንድ መሪዎች ብድር በመመለስና በበቀል ውስጥ ይገባሉ። ነህምያ ግን ይህን አላደረገም። ተቃውሞውን እግዚአብሔር እንዲያየው ለጌታ አሳልፎ ሰጠ። ዳዊትም ይህንን መርሆ ያውቅ ነበር። «ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው» (1ኛ ሳሙ. 17፡47፤ ሮሜ 12፡19፥ «ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፥ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና።» ነህምያ መልስ ከመስጠት ይልቅ ለእግዚአብሔርና ለፍርዱ አሳልፎ ሰጣቸው።

---

15ኛ ጥያቄ፡- 4፡7-12 አንብብ። የሚቀጥለውን የተቃውሞውን ዘዴ ግለጽ። በአይሁድ ሕዝብ ምን ሆነ?

---

ሰ. አንድ መሪ ተስፋ መቁረጥን በእውነተኛነት ይመለከታል።

አንድ ሥራ በታላቅ ቅንዓት ጀምረን ከዚያም ግማሹ ከአለቀ በኋላ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ የምንሰምጠው ስንት ጊዜ ነው? ግንቡ ግማሹ ተሠርቶ አልቆ ነበር። ተቃውሞው እነርሱን ለመግደል በማስፈራራት ተጀመረ። ሕዝቡም መስማት ጀምረዋል። ዓይናቸውንም ከጌታ ላይ አንሥተው በሁኔታዎች ላይ አሳረፉ። ኃይላቸው ዝሎ ዓይናቸው ፍርስራሹን ድንጋይ ማየት ጀምሮ ነበር (4፡10)።

ነህምያ ያደረገው ምን ነበር? በቀጥታ ተጋፈጠው።

1. በመጀመሪያ ሕዝቡን በማረጋጋት ወደ ጌታ እንዲመለከቱ አደረገ (4:14)።

2. ወንዶችና ሕዝቡን አስታጥቆ ሥራውን እንዲጠብቁ አደረገ (4:9፤ 16-23)።

በጌታ መታመንን ቀጠለ፥ እናም ከተማዋን ለመመሸግ ማድረግ የሚችለውን አደረገ። አንዳንድ ጊዜ የራሳችንን ፋንታ አናደርግም። በእምነት ብቻ እንራመዳለን እንላለን። ጌታን እንታመናለን፥ ነገር ግን ምንም አናደርግም። ነህምያ ሁለቱም ጠቃሚ እንደሆኑ ያውቅ ነበር። ጌታን በሙላት ልንታመነው ያስፈልጋል፤ እናም ማድረግ የምንችለውን በእኛ በኩል እናድርግ።

| | |
|---|---|
| 16ኛ ጥያቄ፦ 6:1-14 አንብብ። አዲሱ የተቃውሞ ዘዴ ምን ነበር? ነህምያ የመለሰው እንዴት ነበር? መልሶችህን በነጥብ መልክ ጻፋቸው። | |

ረ. መሪ በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ መጽናት አለበት።

የነህምያ ዓይኖች በጌታ ላይ ነበሩ። ምንም እንኳን እርሱ ደካማ ቢሆንም ጌታ ጠንካራ እንደሆነ ያውቅ ነበር። በኢየሩሳሌም ታላቁ ባለሥልጣን እርሱ ቢሆንም በትሕትና አመለካከት ያለውን መታመን ጠበቀ። ይህም ጽናትንና የመጣበትን ችሎታ በሚፈልገው ነገር ላይ ሰጥቶታል።

ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥራ እንዲስተጓጎል ለማድረግ ሞክሮ ነበረ፤ ነህምያ አንድ ዓላማ ነበረው። ከዚያም ንቅንቅ አላለም። ውጤቱ ምን ነበር? ም. 6:15 ድምፅህን ከፍ አድርገህ አንብበው። «ቅጥሩም በኤሉል ወር በሀያ አምስተኛው ቀን በአምሳ ሁለት ቀን ተጨረሰ»።

ሁላችንም «እግዚአብሔር ይመስገን» ብለን ልንጮህ እንችላለን። ይህም የጥሩ መሪነት ውጤት ነው። ዋና ነጥቦቹን እንደገና እንቃኛቸው።

- መሪ ስለሚያስፈልጉ ነገሮች ግልጽ ግንዛቤ ያለውና ግድ የሚለው ነው።
- መሪ ችግሮቹን ሁሉ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል።
- መሪ ራሱ ፍላጎቶችን ለማርካት ብቁ ሆኖ የሚገኝ መሆን አለበት። ሥርዓት ያለው፥ ብርቱ፥ ደፋርና ዘዴኛ እንዲሁም ተግባቢ ነው።
- መሪ በሕዝብ ፊትና በግል ሕይወቱ ታማኝ ነው። በጥንቃቄ ለማቀድ ጊዜን ይወስዳል።
- መሪ በከፍተኛ ደረጃ የተነሣሣና ሌሎችን ለሥራ የሚያንቀሳቅስ ነው።
- አንድ መሪ ከተቃውሞ በላይ ለመሆን በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ አለበት።
- መሪ ትችቶችን እንዴት ማርገብ እንደሚችል ያውቃል።
- መሪ ተስፋ መቁረጥን በእውነተኛነት ይመለከታል።
- መሪ በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ይጸናል።

| | |
|---|---|
| 17ኛ ጥያቄ፦ የመሪነት ስፍራ ተሰጥቶህ ችግር የገጠመህን ጊዜ የሚያብራራ አንድ አንቀጽ በ200 ቃላት ጻፍ። የነበረህን ኃላፊነት ግለጽ። የገጠሙህን ችግሮችና | |

እንዴት መፍትሔ እንዳገኘህላቸው ግለጽ። በመጥፎ መንገድ እንዳየኸው አሁን የሚሰማህ ከሆነ ምን ማድረግ ትችል እንደነበር ተናገር።

## አራተኛ ቀን፦ በመሪነት ውስጥ ያሉ መሰናክሎች

ታሪኩ ብዙ የሚያስተምረን እውነት ስላለው ከታላቁ መሪ ከነህምያ መማራችንን እንቀጥላለን።

18ኛ ጥያቄ፦ 5፡1–13 አንብብ። የይሁዳ ሕዝብ የገጠሟቸውን ችግሮች በዝርዝር ጻፍ። ነህምያ ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር? ያደረገው ምን ነበር?

መሪ እውነትን ከስሕተት ለይቶ ያውቃል፤ ለፍትህም ይቆማል።

ወደ ምዕራፍ 5 በመመለስ የግንባታው ሥራ ቆሞ እንደነበር እናነባለን። በኢየሩሳሌም ችግሮች ነበሩ። ከሕዝቡ ዘንድ ታላቅ የሆነ ጩኸት ስለነበር የሕዝቡን ማጉረምረም ይሰማ ዘንድ ነህምያ ጊዜን ወሰደ።

1. አያሌዎች ብዙ ቤተሰብ ይዘው በቂ ምግብ አልነበራቸውም (5፡2)።

2. አንዳንዶቹ እህል ያገኙ ዘንድ ቤታቸውንና ንብረታቸውን በብድር አስያዘው ነበር (5፡3)።

3. ሌሎች ግብር ለመክፈል ብር መበደር ነበረባቸው። የተጣለባቸው ወለድ ከፍ ያለ ስለነበር ልጆቻቸውን ለባርነት ሸጠው ነበር (5፡5)።

አንደኛው ምክንያት በዚያን ጊዜ ረሃብ ነበረ (5፡3)። ሌላው ምክንያት ደግሞ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ወለዱን ከፍ አድርገውት ነበር።

ነህምያ ይህንን በሰማ ጊዜ በጣም ተቆጣ። መሪ የሚቆጣበት ጊዜ አለን? አዎን ሁላችንም ፍትሐዊ ባልሆነ ጉዳይ እንቆጣለን። ነገር ግን ነህምያ እንዴት አድርጎ ቁጣን መያዝ እንዳለበት ያውቅ ነበር። «በልቤም አሰብሁ» (5፡7)። እንዴት አስተዋይ ነበር። ከመናገሩ በፊት ያስባል። ቁጣውን ሊያፈነዳው ይችል ነበር። የፍርድ መዛባትንና ትክክል ያልሆነ ነገር ስታይ ምን ታደርጋለህ?

ከሁሉም በፊት በልቡ የችግሩን ምንጭ ተገነዘበ። ከገዛ አገራቸው ሰዎች ገንዘብን በአራጣ ይቀበሉ ነበር። ያም እግዚአብሔር የከለከለው ነገር ነበር። (ዘጸ. 22፡25፤ ዘዳ. 23፡19–20፤ እና ዘሌ. 25፡35–40 ተመልከት።) ነህምያ ትክክለኛውን ነገር ትክክል ካልሆነው ለይቶ ያውቅ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ለአይሁዶች የሚከተለውን ያዝዛል።

1. አይሁዳውያን ላልሆኑ ሰዎች ገንዘብን በወለድ ማበደር ስሕተት አልነበረም።

2. ለአይሁዳዊ ገንዘብን ማበደር ስሕተት አልነበረም።

3. ለአይሁዳዊ በብድር ወለድን መብላት ስሕተት ነበር።

4. አይሁዳዊን ባሪያ ማድረግ ስሕተት ነበር።

ችግሩን ከገመገመ በኋላ እርምጃ ወሰደ። በቀጥታ ስሕተቱን ወደ ፈጸሙት የተከበሩ ሰዎችና አለቆች ሄዶ አፋጠጣቸው።

«ሁላችሁ ወለድን ከአገራችሁ ሰው ትወስዳላችሁ» (5፡7) «የምታደርጉት ነገር መልካም አይደለም ጠላቶቻችን አሕዛብ እንዳይሰድቡን አምላካችንን

በመፍራት ትሄዱ ዘንድ አይገባችሁምን?» ሁሉንም ነገር ወዲያውኑ እንዲመልሱ ተናገራቸው (5፡9–11)። ነገሩን ወዲያውኑ እንዲፈቱት ጠየቃቸው።

ነህምያም የተናገረው እውነት እንደሆነ ስለ ተገነዘቡ ተሸነፉ። «እንመልሳለን» አሉ። «ከእነርሱም ምንም አንሻም» (5፡12)። ነህምያ ካሳን እንዲከፍሉ አዘዘ። ስሕተትን አድርገው ስለነበር አሁን ግን በወለዱና በንብረት ከሕዝቡ የወሰዱትን ነገር መመለሳቸው ነበር። ይህ በአሁኑ ዘመን ብዙ ጊዜ የማይታሰብበት ነው። አንዳንዶች ስሕተትን መቀበልና ይቅርታን መጠየቅ በቂ ይመስላቸዋል። ነህምያ ግን እንዲመልሱ አደረገ። ነገሩን ለመጨረስ በትክክል መደረግ እንዳለበት ያውቅ ነበር። በተጨማሪም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ባያደርጉ ኖሮ በዓለም ሁሉ ፊት ምስክርነታቸው የተበላሸ እንደሚሆን ያውቅ ነበር።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፡– ሉቃ. 19፡8 አንብብ። ዘኬዎስ ስላደረገው ስሕተት ሁሉ ምን እመልሳለሁ አለ? (ዘጸ. 22፡1 ዘሌ. 6፡3–5፤ ዘኁ. 5፡7 እና ሕዝ. 33፡14–15 አንብብ)። ዘኬዎስ ይህን በሚልበት ወቅት በብሉይ ኪዳን ለተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዙ ነበር። እግዚአብሔር በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እንዲደረግ ያዘዘውን በዝርዝር ጻፍ። ዛሬ ለዚህ ትእዛዝ ብንታዘዝ የስሕተት መጠን ይቀንስ ይሆን? |

ነህምያ የሰውን ልብ ስለሚያውቅ ካህናትን ጠርቶ ሀብታሞች ሰዎች ቃል የገቡትን ነገር እንዲፈጽሙ መሀላ አስገባቸው። ቃላቸውን እንዲጠብቁም አስጠነቀቃቸው (5፡12፥13)። አንዳንድ ጊዜ ስለ ስሕተታችን እንወቀሳለን። ግን በጉዳዩ ላይ አንዳችም እርምጃ አንወስድም። ነህምያ መሀላ እንዲምሉና ወዲያው እርምጃ በመውሰድ መልሰው እንዲከፍሉ አስደረገ። መሪ ትክክለኛውን ነገር ከስሕተት ለይቶ ለፍትሕ መቆም አለበት።

2. መሪ ለማንነቱ ያለውን ታማኝነት ሳይለቅ ዕድገትን ይቀበላል።

ብዙዎቻችን ከብልጽግና ይልቅ ድኅነትን፥ ከክብር ይልቅ ትሕትናን፥ ከመሻሻል ይልቅ ታዋቂነትን በተሻለ መንገድ እናስተናግዳለን። ክርስቲያኖች ዕድገትን መፍራት የለባቸውም። ክርስቲያኖች በሕዝብ ላይ መልካም ተጽዕኖ ለማሳደር ወደ ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ መምጣት ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ደረጃ ጥቂት ክርስቲያኖች አሉ። ነገር ግን ብዙዎች ይፈለጋሉ። ይሁንና አደገኝነትም አለበት።

ሀ. ዕድገት ጥቅሞችን ያስገኛል።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፡– ነህምያ ዕድገቱን እንዴት ነው የያዘው? ምዕራፍ 5፡14–19 አንብብ። ነህምያ ሊያደርጋቸው ሲችል ያላደረጋቸውን ነገሮች ዘርዝር። በአዲሱ የሥልጣን ደረጃ ሊያገኝ የሚችላቸውን ጥቅሞች እንዳይወስድ ያደረገው ምን ነበር? |

ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው እንደ ግንበኛ ሆኖ ነበር፤ ነገር ግን ወዲያው አገረ ገዢ ሆኖ ተሾመ። ለአሥራ ሁለት ዓመት እንደ ገዢ ሆኖ አገለገለ። በዚያ የሥልጣን ደረጃ ሆኖ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው አንዳንድ መብቶች ነበሩት።

1. በሰዎች ላይ ከባድ ግብር በመጣል፥ ለገዢዎች የሚገባውን ምግብና የወይን ጠጅ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችል ነበር።

2. እርሱና በዚያ የነበሩት ሁሉ በሰዎች ላይ ጌታ መሆን ይችሉ ነበር።

3. ለራሱ መሬት መግዛት ይችል ነበር።

ከእድገት ጋር አዲስ መብት፥ ጥቅምና የተለየ ክብር ይመጣል። ጠቢብ የሆነ መሪ እነዚህን በአግባቡ ሊጠቀምባቸው ይችላል። ለራሱ ያለውን ታማኝነት ለመጠበቅ ክርስቲያን እጅግ ጥንቁቅ መሆን አለበት።

1. ከጥቅሞች ጋር ፈተናዎች ይመጣሉ። ራስን የማበልጸግ ፈተና አለ። በገንዘብ የማጭበርበር ወጥመድ ውስጥ ለመውደቅ ብቻ ዕድገትን የተቀበሉ ሰዎች ስንት ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ፥ «አትስረቅ» (ዘጸ. 20፡15) ይላል። መልሰው ለመክፈል ያቅዳሉ፤ ነገር ግን ፈጽሞ አያደርጉትም። በገንዘብ ጉዳይ በፍጹም ታማኝ ካልሆኑ፥ የእግዚአብሔር በረከት ከቤተ ክርስቲያናቸው ይርቃል።

2. ሥልጣን ስላለህ ሌሎችን የመጨቆን ፈተና ይኖርብሃል። ነህምያ አስቀድሞ ሲናገር ገዢዎቹ ከፍተኛ ቀረጥ እንዲሁም ምግብና ወይንም ጥምር ሕዝብ እንዲያመጣ አድርገው እንደነበር ገልጾአል። እግዚአብሔርን ከመፍራቱ የተነሣ ነህምያ ይህን አላደረገውም።

3. ስስታም የመሆንም ፈተና አለ። ሌሎች ገዢዎች መሬትን አግኝተዋል፤ ነህምያና የእርሱ ሰዎች ግን እንዲህ አላደረጉም።

ለ. እድገት የአሠራር መርሆችን ይፈታተናል።

ለማንነቱ ታማኝ የሆነ ሰው ዕድገትን ከተቀበለ በኋላ ከማይስማማባቸው አሠራሮች ጋር ሊገናኝ ይችላል። የቀደሙት የኢየሩሳሌም ገዢዎች ኢ-ፍትሐዊ ነበሩ። ነህምያ እነዚያን ኢ-ፍትሐዊ የአሠራር መርሆዎች እንዲቀጥልባቸው የሚፈልጉ፥ ከነርሱ የሚጠቀሙ ሰዎችም ይኖሩ ይሆናል። የአሠራር መርሆው ሲቀየር አንዳንዶቹ ሥራቸውን እንኳ ሊያጡ ይችሉ ነበር። ነህምያ እንዳይቀጥል ግፊት ነበረበት። የነህምያ አጭር መልስ እንዲህ ነበር፤ «እኔ ግን... እንዲህ አላደረግሁም» (5፡15)። ፍትሐዊ ያልሆኑትን የአሠራር መርሆዎች ፍትሐዊ አደረጋቸው።

ሐ. ዕድገት ዝነኝነትን ያመጣል።

ነህምያ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ባለሥልጣን ነበር። ከአካባቢው ከሚኖሩ አገሮች ከሚመጡት በተጨማሪ በየዕለቱ አንድ መቶ አምሳ ለሚሆኑ አይሁዶችና አለቆች በገበታው ፊት (5፡17) መልካም የእንግዳ አቀባበል ማድረግ ነበረበት። ቋሚ የመምጣትና መሄድ ሁኔታ ነበር። በዚህ ሁሉ መካከል ነህምያ ግቡን አልሳተም። ይህም የፈረሰውን ቅጥር መገንባት ነበር። እብሪተኛ ወይም ትዕቢተኛ ፈጽሞ አልሆነም። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በማስተካከል ሥራውን ቀጠለ።

መ. ዕድገት ሰዎችን ይነካል።

ነህምያ ለእንግዶች የሚያስፈልገውን መስተንግዶ ሁሉ ያመጡ ዘንድ ሕዝቡን አላዘዘም። ምክንያቱም ከሕዝቡ ላይ የሚፈለገው በጣም ከባድ

እንደነበር ያውቅ ነበር። ራሳቸውን እንደገና በይሁዳ እየመሠረቱ ነበር። ረሃብ ነበር። ከንግዳቸውና ከግብርናቸው ተለይተው የግንባታ ሥራ ላይ ነበሩ። ነህምያ ለሕዝቡ የሚሆን ልብ ነበረው። እርሱና የእርሱ ሰዎች በሕዝቡ ላይ ተጨማሪ ሸክም ከማድረግ ይልቅ ይረዳቸው ዘንድ ገንዘብና እህል ያበድሯቸው ነበር (5፡11)።

በዕድገት ውስጥ ብዙ ፈተናዎች ይመጣሉ። ነህምያ ግን አልተነቃነቀም። በጽናት በመቆም ፍትሐዊና ትክክል የሆነውን ያደርግ ነበር። ለማንነቱ ያለውን ታማኝነት ጠበቀ።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፡- በሀ. ለ. ሐ. መ. እንዳለው የእድገትን አራት ውጤቶች በዝርዝር ጻፍ። ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ በሥራህ ወይም በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያጋጠመህ የትኛው ነው? እንዴት አሳለፍክ? ይህንን ምዕራፍ ከአጠናህ በኋላ ዕድገትን በተመለከተ ምን ዓይነት የአመለካከት ለውጥ ይኖርሃል? |

**አምስተኛ ቀን፡- ትምህርት አሥራ ሰባትን ከልስ። በሳምንታዊ ስብሰባ ጊዜ በመወያያ ርእሶች ላይ ለመሳተፍ ተዘጋጅ።**

## ሳምንታዊ ስብሰባ

የተለመደውን ደንብ ተከተል። በሚከተሉት ርእሶች ላይ ተወያዩ።

1. ስለ ሙሴ የሕይወት ታሪክ አስብ። በዘጸአት 3 ውስጥ እግዚአብሔር ለመሪነት ሲጠራው ስለነበረው ምላሽ ተወያዩ። ለምን እንደዚያ ዓይነት ምላሽ ሰጠ? ሙሴ ግብፅን ከለቀቀ በኋላ ለውጥን ታይበታለህን? እግዚአብሔር አሁን ለመሪነት ሊጠቀምበት ከቻለ ይህ እንዴት ምክንያት ሊሆን ይችላል?

2. በሁለተኛና በሦስተኛ ቀን ትምህርት ላይ የተመለከትናቸውን 8 የመሪ ዓይነተኛ ባሕርያት በዝርዝር ጻፍ። ስለ እያንዳንዱ ምን ማለት እንደሆነ ተነጋገር።

3. ሁሉም ሰው ዕድገትን ይፈልጋል። በአራተኛ ቀን ትምህርት ከተጠቀሱት መሰናክሎች ለአንተ አዲስ አሳብ የሆነብህ የትኛው ነው? ነህምያ ከሚያጋጥሙት ፈተናዎች ነፃ ሆኖ ለመቆየት እንዴት ቻለ? አንተስ እንዴት ትችላለህ?

4. ይህንን ምዕራፍ በአጠናህ ጊዜ በኃጢአት የተወቀሰ ሰው አለን? ካሳ መክፈል የሚገባህ ሁኔታ አለን? እግዚአብሔር እየተናገረህ ከሆነ ለጸሎትና ንስሐ ለመግባት ጊዜን ውሰድ። ከዚያም ትክክለኛውን ነገር ማድረግ እንድትችል ለፍትህ እንድትቆምና ለማንነትህ ታማኝ እንድትሆን እርስ በርስ አንዱ ለአንዱ ይጸልይ።

# ትምህርት አሥራ ስምንት

## የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፥ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት

### አንደኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የብቃት መመዘኛዎች

መጋቢነት፥ ሽማግሌነት እና ዲያቆንነት የተከበሩ ተግባራት ናቸው። በልዩ ልዩ አገሮች እነዚህ መሪዎች በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ። በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ምንም ዓይነት ስያሜ ይኑራቸው በዚህ ምዕራፍ ባለው ትምህርት ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው እናጠናለን። ደግሞም ተግባራቸውን እንመለከታለን።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎአል። «ብዘገይ እንኳን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ። የእግዚአብሔር ማደሪያ የሕያው አምላክ ቤተ ክርስቲያን ነው። የሕያው አምላክ ቤተ ክርስቲያን «የእውነት ዓምድና መሠረት ነው» (1ኛ ጢሞ. 3፡15)። እግዚአብሔርን የሚፈሩ የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በሆነችው በእግዚአብሔር ማደሪያ ላይ ስለ ተሾሙ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። ቤተክርስቲያን እውነትን የምትጠብቅ ናት። ሕንፃ ካለ ጠንካራ ላዕላይ መዋቅርና ጥሩ መሠረት ለረጅም ጊዜ ሊቆም አይችልም። ለቤተክርስቲያን እንዲሁ ዓይነት እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሪዎች መጠበቅ አለባቸው።

> 1ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጢሞ. 3፡1-12 አንብብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለት የመሪዎች ቡድኖች ምን ምን ናቸው? ለእያንዳንዳቸው የተሰጠውን የመመዘኛ ዝርዝር ጻፍ። ዝርዝሩን ጎን ለጎን አድርገህ አወዳድር። ከመመዘኛዎቹ የሚመሳሰሉት ምን ያህሉ ናቸው? በተለዩት ላይ ምልክት አድርግ። ስለ እነርሱም አስብ። ከቲቶ 1፡6-9 ጋር አነጻጽር።

1. የቤተክርስቲያን የብቃት መመዘኛዎች

ሀ. ማኅበራዊ መመዘኛዎች

የቤተክርስቲያን መሪ (ሀ) የማይነቀፍ (ቁ.2) መሆን አለበት። ሕይወቱ ለተቃውሞ ወይም ለትችት የተከፈተ መሆን የለበትም። ለ) ደግሞም «ልከኛ» (ቁ.2) መሆን ይገባዋል። ሰዎች በአክብሮት የሚያዩት፥ በሚሠራውና በሚናገረው ሁሉ የተከበረ ሰው መሆን አለበት። እንዲሁም ሐ) መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል። በቁ.7 ይኸው መልካም ምስክርነት በውጭ ላሉት እንደሚሆን ተገልጾአል። ከበሬታን እንዲያገኝ በኅብረተሰቡ፥ በሥራ ቦታና በቤተክርስቲያን ውስጥ ጠባዩን ማስተካከል አለበት።

ለ. በቤት ውስጥ የሚጠበቁ የብቃት መመዘኛዎች

ቁ. 4 እንዲህ ይላል «ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር»። ቁ. 12 ይህንኑ አሳብ እንዲህ በማለት ይደግመዋል «ልጆቻቸውንና የራሳቸውን ቤቶች በመልካም እየገዙ»። ብዙ መሪዎች እነዚህን ጥቅሶች አጠንክረው አይመለከቷቸውም። በቤትህ ውስጥ ፈጽሞ የማትገኝ የቤተክርስቲያን መሪ ነህን? እርግጥ ነው፤ ብዙ ኃላፊነት ይኖርብሃል። ይሁንና እግዚአብሔር የመሪነትህ ችሎታ መፈተን የሚጀምረው ከቤትህ እንደሆነ ተናግሮአል። ሚስትህንና ቤተሰብህን በአግባቡ ለመንከባከብ እስከማትችል ድረስ ሥራ የሚበዛብህ ከሆነ እውነትም ሥራ ብዙ ነህ።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡8ን ተመልከት። በአኗኗርህ ላይ አንዳንድ ለውጦች ማድረግ አለብህ። በዚህ ምዕራፍ በሦስተኛው ቀን ስለ ውክልና እንመለከታለን። ይህ ምናልባት አንዳንዱን የሥራህን ውጥረት መቀነሻ መንገድ ሊሆን ይችላል።

በምዕራፍ 3፡11 ላይ ለሚስቶችም የተጻፈ መልእክት እናገኛለን። የመሪዎች ሚስቶች «ጭምቶች፥ የማያሙ፥ ልከኞች፥ በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል»። ከኤፌሶን 5 ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ለመቀደስ ከቃሉ ጋር አንጽቶ በማጥራት ቅድስትና ያለነውር እንድትሆን እንዳደረጋት እንማራለን፤ እንዲሁ ባሎች ሚስቶቻቸው በቁጥር 11 ላይ እንደተጠቀሰው እንዲሆኑ ሊንከባከቧቸው ይገባል። ሚስቶችም ለቃሉ ምላሽ የሚሰጡ በመሆን ቅዱስና ንጹሕ ኑሮ ለመኖር የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

በብዙ ባህሎች እነዚህ ከእግዚአብሔር ቃል የተገኙት መመሪያዎች ተረስተዋል ወይም ችላ ተብለዋል። ባሎች ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የቤተክርስቲያን መሪ የቤት ሕይወት በጣም አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው «ቅድስና በቤት ይጀምራል» ሲል በትክክል ተናግሯል።

በተጨማሪ መሪው «እንግዳ ተቀባይ» መሆን አለበት (ቁ.2)። ይህንን ለመተግበር የሚስቱ ሙሉ ትብብር ያስፈልገዋል። ባልና ሚስት ደስታ ያለበት ግንኙነት ካላቸው ለጎብኝዎቻቸው ሐሤትንና ተቀባይነትን ያንጸባርቃሉ። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መሪ ብዙ እንግዳ መቀበል ይጠበቅበታል። መሪው እርሱና ቤተሰቡ እንግዳ ተቀባይነትን በሙላት እንዲለማመዱ የሚያስፈልጋቸውን ቸርነት እንዲሰጣቸው በእግዚአብሔር መደገፍ አለበት።

ሐ. ግብረገባዊ የብቃት መመዘኛ

መሪ በሁሉም ነገር «ራሱን የሚገዛ» መሆን አለበት (ቁጥር 2)። በማንኛውም ነገር ከልክ በላይ መሄድ የለበትም። ይህም በሌላ አገላለጽ፥ «ራሱን የሚቆጣጠር» ማለት ነው። ማናቸውም ዓይነት ሱሶችን ሁሉ

ማስወገድ አለበት። ግብረገባዊ በሆነ መንገድ ራሱን ንጹሕ አድርጎ መጠበቅ አለበት (ቁ.3)። ሰውነቱ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ መሆኑን ስለሚያውቅ ልቅ ከሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት መሸሽ አለበት (1ኛ ቆሮ. 6፡18–20)።

የቤተክርስቲያን መሪ «የአንዲት ሚስት ባል» (ቁ.2) መሆን አለበት። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፤ «በአንድ ጊዜ አንድ ሚስት!» ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው እንደዚህ አይደለም? አዲስ ኪዳን ሲያስተምረን «ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ባል ይኑራት» (1ኛ ቆሮ. 7፡2) ይላል። ሮሜ 7 ደግሞ ሞት እስከሚለያቸው ድረስ ለትዳር ጓደኞቻቸው ታማኝ እንዲሆኑ ይነግረናል። ከዚያ በሕይወት ያለው ሰው ከፈለገ እንደገና ለማግባት ይፈቀድለታል።

መ. የባሕርይ ብቃት መመዘኛ

መሪዎች ጨዋ ሊሆኑ ይገባል። ጠበኛ ወይም አምባገር ፈጣሪ መሆን የለባቸውም። ትሑትና ጣፋጭ ምላሽ መስጠት የሚችል መሆን አለበት።

በተጨማሪ ገንዘብ የሚወዱ ወይም ታማኝነት የጎደለውን ጥቅም የሚፈልጉ መሆን የለባቸውም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲያስጠነቅቀው «. . . ገንዘብ መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ» ብሏል (1ኛ ጢሞ. 6፡10–11)። መሪዎች በገንዘብ ጉዳዮች ሁሉ ታማኝ መሆን አለባቸው። ታማኝነትን በማጉደል ገንዘብን ለመጠቀም የሚመጣውን ፈተና ሁሉ በጽናት መቃወም አለባቸው።

መሪ ገንዘብ መበደር የለበትም። ሮሜ 13፡8 ሲናገር «እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ» ይላል። መሪ ባለዕዳ ከሆነ ጥሩ ምስክርነት ሊኖረው አይችልም። ምሳሌ 22፡7 «ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው» ይላል። የዕዳ እሥረኛ መሆን የለበትም። ይህ ብዙ ጊዜ ወደ ጠላትነት ይመራል።

ሠ. የብስለት የብቃት መመዘኛዎች

ጳውሎስ አዲስ አማኞችን በመሪነት ስፍራ ማስቀመጥን በማስጠንቀቅ ጽፎአል። ሊኮሩና ሊታበዩ ይችላሉ። ሰይጣን የወደቀው በትዕቢት እንደሆነ እናውቃለን። ስለዚህም መሪዎች በዚህ ወጥመድ መያዝ የለባቸውም። ቁ.10 «አስቀድመው ይፈተኑ» ይላል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከመሆናቸው በፊት በአነስተኛ ሥራ ራሳቸውን መፈተን አለባቸው። በበሰሉ ጊዜ ግን መሪ ሊሆኑ ይችላሉ።

2ኛ ጥያቄ፡– ከዚህ በላይ የቤተክርስቲያን መሪዎች መመዘኛዎች የሆኑትን አምስቱን ክፍሎች አይተናል። ከጸፍካቸው ከሁለቱ ዝርዝሮች ጋር አወዳድራቸው። አንተ

ከጻፍከው ከሀ እስከ ሠ ከአለው መመዘኛ ጋር የማይሄደውን አውጣ። የቀሩት የትኞቹ ናቸው?

ክፍሉን በጥንቃቄ ከአየህ «ለማስተማር የሚበቃ» እና «በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ» የሚሉ መመዘኛዎች እንዳሉም ይታያል። እነዚህን ሁለቱን አስፈላጊ መመዘኛዎች በሚቀጥለው ትምህርታችን ላይ እናያቸዋለን።

## ሁለተኛ ቀን፦ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር

1. ተጨማሪ የቤተክርስቲያን መሪዎች የብቃት መመዘኛ

### ሀ. አእምሮአዊና መንፈሳዊ መመዘኛዎች

የቤተክርስቲያን መሪዎች ማስተማር መቻል አለባቸው። እነዚህ ቃላት በግሪክ የሚያመለክቱት ማስተማር መቻል ብቻ ሳይሆን ለማስተማር መዘጋጀትን ወይም ፈቃደኛ መሆንንም ጭምር ነው። መሪዎች የሕዝቡን ውስጣዊ ሕይወት እንዴት መገምገም እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ለዚያም የሕዝቡን ፍላጎት ለማሟላት እውነትን ይጠቀማሉ። ሐኪም በሽተኛውን ይመረምራል። በሽታው ምን እንደሆነ ለይቶ ያውቅና ይፈወስ ዘንድ ትክክለኛውን መድኃኒት ይሰጠዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሚፈውሳቸው የተለያዩ ዓይነት የነፍስ በሽታዎች አሉ። ጠቢብ የሆነው አስተማሪ የሰሚዎችን ፍላጎት ለማርካት የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንደሚጠቀም ማወቅ አለበት።

3ኛ ጥያቄ፦ ሚል. 2፡1-9 አንብብ። ነቢዩ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገረው ለማን ነበር? ቁ.6-7 አንብብ። እውነተኛ የሆኑት የሌዊ ልጆች ማድረግ ይገባቸው የነበረውን በዝርዝር ጻፍ።

ሚልክያስ ካህናትን በሥራቸው ታማኞች ስላልነበሩ ይገሥጻቸዋል። ሚል. 2፡1-9 እውነተኛውን ካህን በሚከተለው ሁኔታ ይገልጸዋል።

- የእውነት ሕግ በአፉ ውስጥ ነበረች።
- በከንፈሩም ውስጥ በደል አልተገኘበትም።
- ከጌታም ጋር በሰላምና በቅንነት ሄደ።
- ብዙ ሰዎችንም ከኃጢአት መለሰ።
- እውቀትን ጠበቀ።

ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል።

«የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና» ሕይወቱና ትምህርቱ መስማማት አለባቸው።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር የቤተክርስቲያን መሪዎች «ለማስተማር የሚበቁ» መሆን እንዳለባቸው (ቁ. 2) እና «በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ» እንደሚገባቸው ገልጾአል (ቁ.9)። ጴጥሮስ ለሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መንጋ በተገቢው መንገድ እንዲመግቡ እና እንዲጠብቁ ጽፎላቸዋል (1ኛ ጴጥ. 5፡2)። እስኪ እንደገና ወደ ነህምያ መጽሐፍ ሄደን በምዕራፍ ስምንት የሆነውን እንመልከት።

---

4ኛ ጥያቄ፡- ነህ. 8፡1–8 አንብብ። እንዲሁም ዕዝራ 7፡6 አንብብ። ከላይ ካለው ምንባብ ስለ ዕዝራ ምን እናውቃለን? የሕጉን መጽሐፍ እንዲያነብ የጠየቀው ማን ነበር? ለመስማት የተሰበሰቡት እነማን ነበሩ? የሕዝቡ ምላሽ እንዴት ነበር?

---

በሕዝቡ ጥያቄ ካህኑ እና ጸሐፊው ዕዝራ የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ አወጣ። ዕዝራ በሙሴ ሕግ ዕውቀት የጠለቀ እውቀት ያለው አስተማሪ ነበር። በማስተዋል መስማት በሚችሉ ወንዶችና ሴቶች ስብሰባ ፊት መጽሐፉን አመጣ። ንባቡን ለማዳመጥ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ። በትኩረትም ያዳምጡ ነበር። ከማለዳ ጀምሮ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ድምጹን ከፍ አድርጎ አነበበላቸው።

በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል ንባብ እንደነበረ እናያለን። መጀመር ያለብን በቃሉ እንጂ በሰው አመለካከት አይደለም። ነገር ግን በተመሠረተው በእግዚአብሔር እውነት መጀመር ያሻናል (1ኛ ጢሞ. 4፡13)።

ሁለተኛ ለእግዚአብሔር ቃል ጥልቅ የሆነ አክብሮት ነበር። ሕዝቡም ለማዳመጥ ጓጉተው ነበር።

ሦስተኛ የሚሰማው ሁሉ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያገኝና የመልእክቱ እውነት ተብራርቷል። ነህምያ 8፡8 ሲናገር «የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ፤ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥ ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር» ይላል። አነበቡት። ከዚያም ግልጽ አደረጉት። በመጨረሻም ትርጉሙን ሰጡ። እነዚህ ነገሮች እያንዳንዳቸው በማስተማር ውስጥ መካተት አለባቸው። መሪዎች ቃሉን ለሕዝቡ ማንበብ ይገባቸዋል። ቃሎቹን ሁሉ መያዝ እንዲችሉ ግልጽ ማድረግ አለባቸው። ከዓውደ ንባቡና ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር እንዴት እንደሚስማማ ማስተዋል ይኖርባቸዋል። ከሁሉም መጨረሻ ትርጉሙን መስጠት አለባቸው። ሰዎች ያስተውሉና ይገባቸው ዘንድ ቅዱሳት መጻሕፍት መብራራት አለባቸው።

ጥንቃቄ ከተሞላው ትምህርት የተነሣ ልባቸው ተነክቶ ነበር። ሕዝቡ ሁሉ ያዝኑና ያለቅሱ ነበር። በደለኝነት የተሰማቸው የእግዚአብሔር ቃል ስለገባቸውና እንዳልታዘዙት ባወቁ ጊዜ ነው። በአንገባቸው ውስጥ መጥፎ ሥራቸውን ትተው ወደ ጌታ ለመመለስ ያላቸውን ፍላጎት ገለጹ።

5ኛ ጥያቄ፦ ነህ. 8፡9-12 አንብብ። በቁ.9 ላይ የሆነውን ነገር አስረዳ። ስለ ነገሩም መሪዎች ያደረጉትን ነገር አብራራ (ቁ.11፥12)።

ነህምያ፥ ዕዝራና ሌዋውያን ሕዝቡን እንዳያለቅሱ ነገሯቸው። የተለየ ቀን ስለሆነ እንዲደሰቱና በዓል እንዲያደርጉ አበረታቷቸው። ምክንያቱም መቅደሳቸው እንደገና ተሠርቷል። እናም የመቅደስ አገልግሎት እንደገና ተመሥርቷል። ከጠላቶቻቸውም ይጠብቃቸው ዘንድ ቅጥራቸው እንደገና ቆሞአል። አንዳንዶቹ በኢየሩሳሌም፥ ሌሎቹም በገጠር ውስጥ ቤታቸውን ገንብተዋል። የሙሴን ሕግ አንብበው እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ዓላማ ተረድተዋል። መሪዎች ላልተዘጋጁት ሰዎች ሄደው ደስታቸውን እንዲያካፈሉ አበረታቷቸው። የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላቸው እንደሆነ አሳሰቡዋቸው (6፡9-10)።

የዳስ በዓልን አክብረው ከጨረሱ በኋላ (8፡13-17) ሕጉን ማንበብ ቀጠሉ (9፡1-3)። ቃሉን እየሰሙ ኃጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር (ዕብ. 4፡12-13)። የእግዚአብሔር ቃል በወንዶችና በሴቶች ልብ ውስጥ ይሠራል።

በየቤተክርስቲያናችን የሚፈለገው በታማኝነት የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርና መስበክ ነው። ይህ የመሪዎች ኃላፊነት ነው። በነህምያ ጊዜ እንደሆነው ዓይነት መነቃቃት ያመጣል። ሕዝቡም በሕይወታቸው ያለውን ኃጢአት ይመረምራሉ እርስ በርስ ፍቅርን ማሳየት ይጀምራሉ እናም በዙሪያቸው ላሉ ጌታን ማወቅ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ይደርሳሉ።

እንደ መሪ ለአንተ በጣም አስፈላጊው አገልግሎት ሰዎች አስተውለው ምላሽ ይሰጡ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ማስተማርና ማስረዳት ነው።

6ኛ ጥያቄ፦ በትምህርት ሦስት አንደኛ ቀን ትምህርት ስብከትን ለማዘጋጀት ተምረሃል። በትምህርት አራት ሁለተኛ ቀን ትምህርት ደግሞ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ተምረሃል። አእምሮህን ለማደስ እነዚህን ሁለት ትምህርቶች ከልሳቸው። ትምህርትህን ለማሻሻል እነዚህንና ሌሎች ዘዴዎችን ተጠቀም። እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ የሆነ ስብከትንና ማስተማርን ይባርካል፤ ሕይወትንም ይለውጣል።

## ሦስተኛ ቀን፦ ውክልና፥ ተጠያቂነትና ችግርን ማቃለል

ከቤተክርስቲያን መሪዎች የሚጠበቁ ነገሮች በርካታ ናቸው። የሚጠበቁባቸውን ኃላፊነቶች በሙሉ በጥቂት ሰዎች በታማኝነት መወጣት የማይቻል ነገር ነው። ሥራውን በሚገባ ለማከናወን ብቸኛው አማራጭ ሥራውን ማካፈል፥ ሌሎች መሪዎችን ማሠልጠንና የተጠያቂነትን ዘዴዎች ማዘጋጀት ነው።

1. ውክልና

7ኛ ጥያቄ፦ ዘጸአት 18፡1-27 አንብብ። ከአማቱ ከዮቶር ምክር የተነሣ ሙሴ በሥራው ላይ ያለውን ከባድ ጫና ለመቀነስ ያደረገው ነገር ምንድን ነበር?

«አንዱ የመሪነት ትርጉም የሰዎችን የተለየ ችሎታ ከማይችሉት ነገር ለይቶ በማወቅ እያንዳንዱን በችሎታው በጥሩ ሁኔታ በሚሠራበት ቦታ ማስቀመጥ ነው» ("Sanders"/ ሳንደርስ፥ ገጽ 127)።

ስጦታውና ችሎታው ላላቸው የቤተክርስቲያን ሰዎች ሥራውን ማካፈል ውክልና ነው። ትክክለኞቹን ሰዎች በትክክለኞቹ ሥራዎች ላይ ለማስቀመጥ መለየት ያስፈልጋል። በብዙ ጸሎትና በጥንቃቄ በተሞላ ምልከታ መሪዎች የሚያስፈልገውን ነገር የሚያደርጉትን ሰዎች መምረጥ ይችላሉ። ይህ የውክልና የመጀመሪያ ክፍል ነው። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፤ «የሺህ ሰዎችን ሥራ ለመሥራት ከመሞከር ይልቅ አንድ ሺህ ሰዎችን በሥራው ላይ ማስቀመጥ ይሻላል»።

ሁለተኛው ክፍል ሥራውን እንዲሠሩ ሥልጣንን መስጠት ነው። ሥልጣኑን ራሱ ለመያዝ ለሚወድ መሪ ለሌሎች መስጠቱ አስቸጋሪ ሊሆን ቢችልም አስፈላጊ ነው። የሚተማመንባቸውን ሰዎች መምረጥ አለበት። ሥራውን እንዲሠሩ ነጻነት መስጠት አለበት። ይህ ከእነርሱ ውስጥ የተሻለውን ነገር ያወጣል። እነርሱም ልምድን ያገኛሉ። ሊያበረታታቸው ይገባል፤ ምንም እንኳን ለጊዜው እርሱ እንደሚሠራው አድርገው ባይሠሩም እስከሚያድጉ ድረስ ሊታገሣቸው የግድ ነው። ብዙ ጊዜ ወጣት ወንዶች የተሻለ ነገር ይሠራሉ፤ ምክንያቱም ወቅታዊውን ሕይወት በተሻለ ስለሚያውቁ ነው። በተጨማሪም የተለየ ችሎታቸውን ለማወቅ ይረዳል።

ሦስተኛው የውክልና ክፍል የተግባራቸውን ዝርዝር መጻፍ ነው። ኃላፊነታቸውን በግልጽ ሁኔታ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ይህ አለመግባባትንና የሥራ መደራረብን ለማስወገድ ይረዳል።

---

8ኛ ጥያቄ፦ ዘጸ. 18፡21-22 አንብብ። ዮቶር ለሙሴ ያሳሰበው ምን ዓይነት ሰዎችን እንዲመርጥ ነበር?

---

ዮቶር ሙሴን የመከረው የሚበቁ እና «ችሎታ ያላቸው ሰዎች»ን እንዲመርጥ ነበር። «እግዚአብሔርን የሚፈሩ»ና «የግፍን ረብ የሚጠሉ» መሆን ነበረባቸው። ይህም ጉቦ ለመቀበል የማይከጅሉ ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የዚህ ውጤት የሙሴን ሸክም ከማቅለሉም በላይ ጊዜውን ሕጉንና ደንቡን ለማስተማር እንዲሰጥና እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንዲያሳይ ያስችላል።

ብዙ መሪዎች ሌሎችን ስለማይወክሉ በብዙ ሁለተኛ ደረጃ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ተውጠዋል። ስለማይወክሉ መሥራት የሚገባቸውን አስፈላጊ ነገሮች ለመሥራት ጊዜ የላቸውም። በአንዳንድ ሁኔታ መሪዎች እግዚአብሔር እንዲሠሩ ከሚፈልገው ሥራ ይልቅ ብዙ ሥራዎችን ይይዛሉ። እግዚአብሔር አንተ እንድትሠራው የሰጠህን ማወቅና ሌሎችን ነገሮች ችሎታ ያላቸው ሰዎች እንዲሠሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

2. ተጠያቂነት

ተጠያቂነት ኃላፊነትን የመቀበል አንዱ ክፍል ነው። የትም ቦታ ብንሆን ብዙውን ጊዜ ስለ ሥራችን ተጠሪ የምንሆንለት ኃላፊ ሰው ከእኛ በላይ ይኖራል። በቤተክርስቲያን ሥራ ውስጥ የመጨረሻው ኃላፊና ጠያቂያችን እግዚአብሔር ስለሆነ እርሱን በመፍራት የምንችለውን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን። ይህም ሆኖ የበላይ ኃላፊዎች የሚሆኑና የምንጠየቅባቸው ሰዎች ይኖራሉ።

እያንዳንዱ መሪ መወከል ያስፈልገዋል። ከዚያም ለእርሱ ሪፖርት የሚደረግበት አሠራር ሊኖረው ያስፈልጋል። ያልነው መወከልና ሰውየው ሥራውን በሚገባ እንዲሠራ ሥልጣን መስጠት አለበት ነው። ይሁንና ቋሚ የሆነ ሪፖርት አሰጣጥ ሊኖርና ሊጠበቅ ያስፈልጋል። የቤተክርስቲያን መሪዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ውጤቶችን በሙሉ ሊያውቁ ያስፈልጋል። ማወቅ አስፈላጊ ነው፤ ይህም የሚሆነው በዋነኝነት በሪፖርት ነው። እርግጥ ነው መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይመለከታሉ። በየሦስት ወሩ ወይም በመንፈቅ ወይም በዓመት አንድ ጊዜ ሪፖርቶች ቢዘጋጁ በተለያዩ የአገልግሎቶች አካባቢ ምን እየሆነ እንዳለ ለማወቅ ለመሪዎች በጣም ይረዳል።

ሪፖርት የሚቀርብባቸው ስብሰባዎች ጌታን ለማመስገን በተለያዩ አገልግሎቶች የተሳተፉትን ለአገልግሎታቸው እውቅና ለመስጠትና ለማበረታታት በጣም ጥሩ ጊዜዎች ናቸው። ተጨማሪ ሥልጠናን የመስጠት ጊዜም ሊሆን ይችላል።

3. የመሪዎች ሥልጠና

መሪዎችን ለማሠልጠን በጣም ጥሩ ከሆኑት መንገዶች አንዱ መወከል ነው። ይህ ኃላፊነትን እንዲወስዱ፥ በሥራው ላይ ካለው ችግር ጋር እንዲጋፈጡና በጥበብና በልምድ እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ትምህርት ያስፈልጋቸዋል።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጢሞ. 2፡1-4 አንብብ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዲያደርግ የሚነግረው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው? |

ሀ. «በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ» (ቁ. 1)። መሪዎች ብርታታቸው ሁሉ በጸጋ እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ክርስቶስ ብርቱ የመሆንን ጸጋ ይሰጣል።

ለ. «ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ»። የተማርከውን ነገር ለመወከል ከተጠያቂነት ጎን ለጎን የማያቋርጥ ትምህርት መኖር አለበት። ትምህርት አሥራ ሰባትና ይህ ትምህርት በተከታይ መሪዎችን ልታስተምራቸው ከምትችላቸው አሳቦች ጥቂቶቹ ናቸው። መሠልጠን አለባቸው። ይህ የክርስቲያናዊ ትምህርት ኮርስ ለጥናታቸው በጣም ጠቃሚ ነው።

በቤተክርስቲያንህ የት.መ.ግ ኮርስ ጀምረህ በየሳምንቱ እያስተማርህ በጥናታቸው ልታበረታታቸውና ልትመራቸው ትችላለህ።

«ሌሎችን ደግሞ ለማስተማር የሚበቁ ሊሆኑ ይችላሉ»። ሂደቱ መቀጠል አለበት።

ሐ. ጳውሎስ በተጨማሪ ለጢሞቴዎስ «መከራን ተቀበል» ብሎታል። ወታደሮች አገራቸውን ለመከላከል እንዲችሉ ማንኛውንም መከራ መጋፈጥ እንዲችሉ ይሠለጥናሉ። እኛስ እንዴት ነን? ወንዶችና ሴቶች፥ ልጃገረዶችና ወጣት ወንዶች ወደ ክርስቶስ መጥተው በእምነታቸው እንዲያድጉና ሌሎችን ለማምጣት ሲሄዱ እንድናይ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ መከራን መቀበል አይገባንምን?

4. ችግርን መፍታት

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁልጊዜም መፈታት ያለባቸው ችግሮች ይኖራሉ። አንዳንድ ሰዎች ችግሮችን ችላ ያሏቸው እንደሆነ የሚጠፉ ይመስላቸዋል። ይህ በፍጹም እውነት አይደለም። አንድ ችግር ከተተወ ሥር ይሰድድና ሌሎች አዳዲስ ችግሮችን ያበቅላል። በቀጥታ ችግሮችን መጋፈጥ የተሻለ ነገር ነው።

---

10ኛ ጥያቄ፦ የሐዋ. 6፡1–7 አንብብ። ችግሩ ምንድን ነበር? ጻፈው።

---

መፍትሔው ምን ነበር?

ችግሩን ለመፍታት ያቀዱት እንዴት ነበር?

ማንን ነበር የመረጡት? መመዘኛው ምን ነበር?

ያደረጉት መቼ ነበር?

ሀ. ችግሩን ለይቶ ማወቅ

ቁጥር አንድ ችግሩን ይዘረዝራል። «በዚያም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጎራጎሩባቸው። በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና» (የሐዋ. 6፡1)።

ይህ ችግር ፈንድቶ ቤተክርስቲያንን በዘር ሊከፋፍላት ይችል ነበር። ምግብን ለመበለቶች በማከፋፈሉ ረገድ አድልዎ ነበር። የአይሁድ መበለቶች እንክብካቤ ሲያገኙ የግሪክ መበለቶች ቸል ተብለው ነበር። ይህም በቀላሉ ወደ ማጉረምረም ያመጣ ሲሆን መራርነትን ሊያሳድግ ይችል ነበር። በሁኔታው ላይ ጠንከር ያለ መጥፎ ስሜት የነበራቸው ሰዎች ቢኖሩም ሐዋርያት ብልህ ነበሩ። ሁኔታውን መርምረው እውነተኛውን ችግር ደረሱበት። የአከፋፋዮቹን የተዛባ አስተዳደር መውቀስ ይችሉ ነበር። ኃላፊ የሆነውን ሰው በመፈለግ ይቀጡት ዘንድ ብዙ ስብሰባዎችን ለማድረግ ጊዜ መውሰድ ይችሉ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ አላደረጉም።

ለ. መፍትሔውን ማምጣት

ብዙ ጊዜ መፍትሔው የችግሩ ተቃራኒ ነው። ችግሩ ተገቢ ያልሆነ የምግብ ስርጭት ከሆነ መፍትሔው ተገቢ የሆነ የምግብ ስርጭት ነው። መፍትሔውን በሚገልጹበት ጊዜ ደቀ መዛሙርትን ሁሉ መጥራታቸው ብልህነት ነበር። በዚህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርት ማለት ያመኑትን ሁሉ ማለት ነው። ምክንያቱም በቁ. 1 ላይ «በእነዚያ ቀናት የደቀ መዛሙርት ቁጥር እያደገ በሄደ ጊዜ» ይላል። መፍትሔውን በሕዝቡ ፊት መናገር በቤተክርስቲያን አባላት ልብና አእምሮ ሰላምን ያመጣል።

ሐ. ዘዴውን መግለጽ

ዘዴው ችግሩ «እንዴት» እንደሚፈታ ያብራራል። «ምግቡ እኩል በሆነ መንገድ ሊሰራጭ የሚችለው እንዴት ነው?» የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ሐዋርያቱ «ይህ ነገር በጥሩ ሁኔታ አልተያዘም፤ አሁን እኛው ራሳችን በትክክል እንዲሠራ እናደርገዋለን» ሊሉ ይችሉ ነበር። እንደዚያ ነበር ያሉት? አይደለም! ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባውን ጉዳይ ሳይለውጡ «የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ አይደለም» አሉ (ቁ.2)።

መ. ዘዴው በሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ መግለጽ

ይህ ደረጃ «ማን» ወደሚለው ያተኩራል። ማን ነው ሥራውን የሚሠራው? ሐዋርያት ራሳቸው ካልሆኑ ማን መሥራት አለበት?

ሥራውን የሚሠሩ ሰዎችን ወከሉ። ለዕለታዊ ምግብ ስርጭት ሰባት የተመረጡ ወንዶች ኃላፊነት እንዲወስዱ ወሰኑ። ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንደሚገባቸው ገለጹ። የሚሠራውን ሥራና ሰዎቹን አገናኙአቸው። ለጉባኤው እንዲህ በማለት ተናገሩ «በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ» (ቁ. 3)።

ሥራውን እንዲሠሩ ሥልጣንን ሰጧቸው። እንዲህም አሉ። «ይህንን ኃላፊነት በእነርሱ ላይ አድርገነዋል» (ቁ. 3)። ይህ ነገር ሐዋርያት «ለጸሎት እና ቃሉን ለማገልገል» ነጻነት ሰጣቸው (ቁ.4)።

ችግሩን ፊት ለፊት ተጋፈጡት፤ መፍትሔውም ተገለጸ፤ በተሻለ መንገድ ነገሩን በሥራ ላይ ለማዋል ዘዴው ቀረበ እናም ዕቅዱ ተከናወነ፤ ውጤቱም «ነገሩም ጉባኤውን ሁሉ ደስ አሰኘ» የሚል ነበር።

ሠ. ጊዜን መወሰን

የመጨረሻው ውሳኔ ዕቅዱ የሚፈጸመው «መቼ» ነው የሚለው መሆን ነበረበት። ችግሩን በጥንቃቄ በመመርመር ለመፍትሔው ተግተው ሠርተዋል። ነገር ግን መደረግ ያለበት መቼ ነበር? ብዙ ጊዜ ሊጠፋ የሚችልበት አካባቢ ይኼ ነው። እነርሱ ግን ወዲያውኑ እርምጃ ወሰዱ።

ሰባት መመዘኛ የሚያሟሉ ሰዎች ተመረጡ። ደቀ መዛሙርት ሰባት ሰዎችን ለሐዋርያት አቀረቡ። «ጸልየውም እጃቸውን ጫኑባቸው።» ነገሩ በቶሎ ተጠናቀቀ። ውጤቱስ? «የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ። ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ» (ቁ. 7)።

በችግር ውስጥ መሥራት፥ መፍትሔን መፈለግ፥ የአሠራር መንገድ መቀየስ፥ ዕቅድ ማስፈጸምና ጊዜን መወሰን የቤተክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት ነው። አያንዳንዱ ነገር በትጋትና በፍጥነት ከተደረገ ችግሮች በጣም ጥቂት ይሆናሉ፤ እናም የመሪዎች ኃይል አስፈላጊ ለሆነው ሥራ ለጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል ለማገልገል ይውላል።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፦ የዚህን ትምህርት 4 ዋና ዋና ክፍሎች ጻፍ። በእያንዳንዱ ክፍል ሥር ለምን እያንዳንዱ ጠቃሚ እንደሆነ ጻፈው። በእያንዳንዱ ክፍል ሥር ብዙ ምክንያቶችን ስጥ። ከራስህም ልምድ ምሳሌዎችን ልታመጣ ትችላለህ። ይህን የቤት ሥራ በሳምንታዊ ስብሰባ ወቅት ልትካፈሉት ይገባል። |

## አራተኛ ቀን፦ የመሪዎች የረዥም ጊዜ ዕቅድ

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በምናነብበትና እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለሙሴ የሰጠውንና እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት ጊዜ የተፈጸሙትን ትእዛዛት በምንመለከትበት ጊዜ ሁሉም ነገር በእንዴት ያለ ሥርዓት እንደተሠራ በመመልከት ያለማቋረጥ እንደነቃለን። ንጉሡ ዳዊት ለጌታ አገልግሎት ካህናት ሌዋውያን፥ መዘምራንና በር ጠባቂዎችን እንዴት በጥንቃቄ እንዳደራጀ አስብ። እርሱ ያቀናጀው አሠራር በኋላ በልጁ በሰሎሞን እናም ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት መልካምን ነገር ባደረገው የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን ድረስ በሥራ ላይ ውሎአል።

አንዳንድ ሰዎች «የቀውስ አስተዳደርን» ይከተላሉ። ችግር ወይም ቀውስ እስከሚመጣ ድረስ ምንም ነገር አያቅዱም ወይም አይሠሩም። ይህ ዓይነቱ አሠራር ብቁ አይደለም። ብዙ ጊዜም ለችግሮች መፍትሔ አይገኝላቸውም። ጊዜው ያልፋል። አሁን ማቀድ ጊዜ ይወስዳል፥ ነገር ግን በኋላ ጊዜን ያድናል ችግርን ያስወግዳል።

በዚህ ትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ የሚሆንባቸውን አንዳንድ አካባቢዎችን እንጠቁማለን። ቤተክርስቲያን በዓመት ውስጥ የምታደርጋቸውን ነገሮች ማቀድ አለባት። ይህ ሁሉም መሪዎች አጠቃላዩን ፕሮግራም እንዲያውቁና እያንዳንዱን ክፍል የሚነካውን ድርጊት እንዲያውቁ ያስችላቸዋል።

1. የቤተክርስቲያን ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር)

የቤተክርስቲያን መሪዎች አዲሱ ዓመት ከመጀመሩ በፊት ጊዜን ወስደው በዓመት ውስጥ የሚደረገውን ጠቅላላ ዕቅድ በሳምንታት ከፋፍለው ማቀድ አለባቸው። ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

-ሰባኪያን

-የተለየ ዝማሬ

-እንግዳ ሰባኪያንና ለጉባኤ የሚሰጡ የተለዩ ትምህርቶች

-የጌታ እራት

በዚህ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ፕሮግራሞችን የሚነኩ ዓመታዊ ድርጊቶች ይካተታሉ።

-ዓመታዊ ወይም የግማሽ ዓመት ኮንፈራንስ

-የተለዩ እሑዶች ወይም ዕረፍት ቀኖች የገና በዓል፥ ፋሲካ፥ ወዘተ. . .

- ሌሎች የተለዩ ቀናት፥ ለምሳሌ ልጆችን ለጌታ ማስረከብና ጥምቀት

በሳምንታዊ ዕቅድ ውስጥ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ የተመሠረተ ተከታታይ ትንተናዊ ስብከት መታቀድ አለበት። ለምሳሌ በኤፌሶን መጽሐፍ ላይ ተከታታይ ትምህርት የሚዘጋጅ ከሆነ በሚከተለው መንገድ ሊካሄድ ይችላል።

1ኛ እሑድ 1፡1–3 መግቢያ፥ ጸሐፊው፥ የተጻፈበት ጊዜ፡ ተቀባዮች፥ ዋና ዋና ርእሶች

2ኛ እሑድ 1፡3–14፥ መንፈሳዊ በረከት በክርስቶስ

3ኛ እሑድ 1፡15–22፥ እና 3፡14–21 የጳውሎስ ጸሎት

4ኛ እሑድ 2፡1–10፥ በክርስቶስ ሕያው መሆን

5ኛ እሑድ 2፡11–22፥ በክርስቶስ አንድ መሆን

6ኛ እሑድ 3፡1–13፥ ጳውሎስ ለአሕዛብ ሰባኪ

7ኛ እሑድ 4፡1–16፥ በክርስቶስ አካል አንድ መሆን

8ኛ እሑድ 4፡17–32፥ እንደ ብርሃን ልጆች መኖር

9ኛ እሑድ 5፡1–20፥ እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ

10ኛ እሑድ 5፡21–6፥4፥ የቤት ውስጥ ትእዛዝ

11ኛ እሑድ 6፡10–20፥ የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ

12ኛ እሑድ 6፡21–24፥ የመጨረሻ ሰላምታና መደምደሚያ

ከዛሬዋ ቤተክርስቲያን ድክመት አንዱ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ቋሚ የሆነ ትምህርት አለማግኘታቸው ነው። ሁሉንም የእግዚአብሔርን ምክር ለማግኘት በቤተክርስቲያናችን ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር አለብን።

## 2. የሥልጠና ፕሮግራሞች

በተለያየ የቤተክርስቲያን አገልግሎት መሪዎችን ለማሠልጠን ሴሚናሮች መታቀዳቸው የግድ ነው። ምናልባት አሁን ያለው አገልጋይ ሊያሠለጥን ይችል ይሆናል። ወይም ከውጪ የተለየ እውቀት ያላቸውን መጋበዝ ሊኖርብህ ይችላል። ሰዎች በሥራ የተወጠሩ ስለሆኑ ቀኖቹን በአጀንዳቸው ውስጥ አስቀድሞ አስፍረው በፕሮግራሙ ላይ እንዲገኙ መናገር ይቻላል። በሚገባ ታቅዶ መነገር አለበት።

እነዚህ ሴሚናሮች ለሚከተሉት ተግባራት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

-ለእሑድ ትምህርት አስተማሪዎች ሥልጠና

-ለወጣቶች ሥልጠና

- ለመዘምራንና የሙዚቃ ሥልጠና

-ለት.መ.ግ መሪ ሥልጠና

## 3. ለተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች ማቀድ

የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል የራሱ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል። ይህም እነዚህን ሊያካትት ይችላል።

- የእሑድ ትምህርት ቤት መሪዎች በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ማተኮር አለባቸው። የትምህርት ዝግጅት፥ መዝገብ አያያዝ፥ ወዘተ. . . እንዲሁም ማንኛውም የተለየ ነገር የሚያደርጉበትን ቀን ለምሳሌ የእሑድ ትምህርት አስተማሪን ለጌታ የመስጠት ቀን በዓመቱ መጀመሪያ ማቀድ አለባቸው። ይህ በእሑድ አገልግሎት ውስጥ ሊደረግ ይቻላል። ነገር ግን በእሑድ ትምህርትና በዓመታዊው የቤተ ክርስቲያን የቀን መቁጠሪያ ውስጥ መግባት አለበት።

- የወጣቶች ኅብረት

- የወንድሞች ኅብረት

- የሴቶች ሳምንታዊ፥ ወርሃዊና ዓመታዊ ስብስባ

- የጥናት ንዑስ ቡድን ወይም የቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

- የአዲስ አማኞች ክፍሎች

- የጥምቀት ክፍሎች

የመሪዎች ማዕከላዊ አመራር ዕቅዱን ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍል መሪዎች እንዲሠሩበት መስጠት አለበት። እንደ ሰንበት ትምህርት ቤት እያንዳንዱ የሥራ ክፍል ለዓመቱ የሚሆን የዝርዝር መግለጫ ዕቅድ ያስፈልገዋል። በተጠናቀቀ ጊዜ እንዲያዩትና አሳባቸውን እንዲጨምሩበት፥ እንዲያጸድቁትም ለማዕከላዊው አካል መቅረብ አለበት።

4. የወንጌል ስርጭት

የቤተክርስቲያን የመድረስ እና ወንጌልን የማሰራጨት ፕሮግራም እንደገና ሊታይ እና ሊታቀድ ይገባዋል። ይህም እነዚህን ሊያካትት ይችላል።

- አሁን በአገልግሎት ላይ ያሉ ወንጌላውያን፥ አገልግሎታቸው፥ ውጤታማነታቸውና የሚያስፈልጋቸውም ነገር፥ መቀጠል የማይችሉና መተካት የሚያስፈልጋቸው ናቸውን? ለወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ያለው ገንዘብ እንደገና ሊታይና ወቅታዊ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።

- መስፋት። ወንጌል ሊሰበክባቸው የሚገባ አስፈላጊ ስፍራዎች አሉን? ማን ነው መሄድ ያለበት? መታቀድና በቤተ ክርስቲያን መጽደቅ ያለበት ምን ያህሉ ጸድቀዋል።

5. ጉብኝት

ጉብኝት እጅግ ጠቃሚ የሆነ የአገልግሎት ክፍል ነው። ኢየሱስና ያዕቆብ ሁለቱም የታመሙትን፥ በእስር ያሉትን፥ ወላጅ የሌላቸውንና መበለቶችን የመጠየቅን አስፈላጊነት ገልጸዋል። አዲስ አማኞች በቶሎ መጎብኘትና መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። ተፈላጊነት ያጡ የሚመስላቸው ሰዎች እንደሚናፈቁ ሊያውቁ ይገባል፥ ወደ ኅብረተሰቡ የመጡ አዲስ ገቢዎች ወደ ቤተክርስቲያን ሊጋበዙ ይገባል። የቤተክርስቲያን የጉብኝት ፕሮግራም በሚገባ የተደራጀ መሆን አለበት። ምክንያቱም ትኩረት የሚፈልግ ሁሉ መታወስ አለበት። አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ይህንን ማድረግ አይችሉም። ይህንን ለመሥራት በደንብ የተደራጁ ግለሰቦች መኖር አለባቸው። በሚገባ እንዲሠሩ የሠለጠኑ መሆን አለባቸው።

## 6. የቤተክርስቲያን ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ

የቤተክርስቲያን ዋና መሪዎችን ብቻ የሚመለከቱ ድርጊቶች ስለሚኖሩ ለራሳቸው የጊዜ ሰሌዳ ሊያዘጋጁ ይገባል።

-የየወሩ የሥራ ስብሰባ

-ዓመታዊ የሥራ ስብሰባ

-የጸሎት ስብሰባ

-የቋሚ ሠራተኞች ስብሰባ

-የአውራጃ የሥራ ስብሰባ

-የገንዘብ ኮሚቴ ስብሰባ

የመሪዎች አንዱ በጣም አስፈላጊ ኃላፊነት ለማኅበሩ በየጊዜው መረጃ መስጠት ነው። ስለሆነም እነዚህን ነገሮች ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

- እነርሱን የሚመለከቱ ክንውኖች

- ማንኛውም የቤተክርስቲያን የአሠራር ለውጦች

– የገንዘብ ሪፖርት

ስለዚህ ጥንቃቄ የተሞላ የተለያዩ የጊዜ ሠሌዳን ማድረግ መሪዎች ለታማኝና ደጋፊ አባሎች አስፈላጊ ማስታወቂያ ለመናገር ይቀላቸዋል። ማንኛውም የቤተክርስቲያን የአሠራር ለውጥ በጥንቃቄ ሊብራራና ሊታይ ይገባል። ከዚያም እያንዳንዱ ሰው ለውጡ ምን እንደሆነና የለውጡን ምክንያቶች ያውቃል።

የገንዘብ ሪፖርት መደበኛ በሆነ መንገድ መሰጠት አለበት። ይህም ጉባኤውን ገንዘቡ በትክክል በሥራ ላይ እየዋለ እንደሆነ እርግጠኛ እንዲሆን ያደርገዋል። ከዚያም በቤተክርስቲያን ውስጥ ለጌታ ሥራ ለመስጠት ፈቃደኛ ይሆናሉ። ሁሉም የቤተክርስቲያን አባላት በሚገኙበት ዓመታዊ የቤተክርስቲያን የሥራ ስብሰባ ዓመታዊው የገንዘብ ማስረጃ ቀርቦ ውይይት ሊደረግበት ይገባል። ከዚያም ውይይት በመነሣት ለሚመጣው ዓመት በጀት ይሠራል። ይህ በሙሉ ማብራሪያ ከተደረገ ሰዎች ኃላፊነታቸው ምን እንደሆነና ገንዘቡ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ያውቃሉ። በዕቅድህ ሁሉ እየጸለይህ ወደ እርሱ ስትመለከት እግዚአብሔር ይመራሃል፤ ይባርክሃልም። ግትር መሆን የለብህም፤ አንዳንድ ጊዜ በዕቅድ ውስጥ ለውጥ መደረግ ይኖርበታል። ነገር ግን ወደምትሄድበት ቦታ ጥሩ የሆነ ምሪትን ይሰጥሃል።

---

12ኛ ጥያቄ፡– በጥንቃቄ ያቀደና ጥሩ ምሳሌ ሊሆንልህ የሚችል አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርይ ምረጥ። ሲያቅድ የወሰዳቸውን ደረጃዎችና ውጤቱ ምን እንደነበር ተናገር።

---

አምስተኛ ቀን፡– ይህንን ትምህርት በጥንቃቄ ከልስና ለውይይት ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

በዚህ ትምህርት የእያንዳንዱ ቀን ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ተወያይባቸው። በቤተክርስቲያንህ የተሻለ አደረጃጀትና የአሠራር ችሎታ እንዲኖር ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ዘዴዎች ካሉ ተነጋገር።

# ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

# የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም ግምገማ

### አንደኛ ቀን፡– የምንገመግመው ለምንድን ነው?

ገበሬ ከሆንህ የእርሻ ቦታህን እየተዘዋወርህ ታያለህ። ምን ዓይነት እህል እንደምትዘራ ትወስናለህ። ይህ በአፈሩ ዓይነት ላይ ይወሰናል፤ በገበያውና ምን እህል የበለጠ ትርፍ እንደሚያስገኝ በዚያ ይወሰናል። የእርሻ ቦታው በሚገኝበት ስፍራና በምትጠብቁት የዝናብ መጠን ይወሰናል።

ነጋዴ ከሆንህ ወደ ገንዘብ ሠንጠረዥህ ትመለከታለህ። አትርፈሃል ወይም ከስረሃል? ትርፉን ወይስ ኪሳራውን ያመጣው ምንድን ነው? መለወጥ

የሚያስፈልጉህ ነገሮች አሉን? ቆጠራ ማካሄድ ያስፈልግሃል? የሠራተኞችህን ውጤታማነት መመርመር ያስፈልግሃል? አንዳንድ ሰዎችን ማዛወር ወይም ማሰናበት ወይም ደግሞ መቅጠር ያስፈልግሃል? ግምገማ ይህ ነው።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፦ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን መገምገም ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ለመልሶችህ ምክንያት ስጥ። |

የምንሠራውን ነገር ሁሉ መገምገም በጣም አስፈላጊ ነው። ለቅዱስ መንፈሱ ለመታዘዝ የነቃን ስንሆን እርሱ እንድንሠራ የሚፈልገውን ጌታ እንደሚመራን እውነተኛ ነገር ነው። ውጤቶቹም እርሱ የሚገባባቸው ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ሰብአዊ ፍጥረቶች ስለሆንን ማድረግ ያለብንን ሁሉ አናደርግም። መገምገም የሚያስፈልገን ለዚህ ነው። ሁል ጊዜ በቋሚነት ማሻሻል ይኖርብናል። ሮሜ 8፡28–29 እንዲህ ይላል። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና»። በሕይወታችን የሚሆነው ማንኛውም ነገር ሁሉ የሚመጣው እኛ እንድንለወጥና እንድንሻሻል በይበልጥም ክርስቶስን እንድንመስል ነው። ያ የእግዚአብሔር ዋና ዕቅድ ነው። በምንወድቅበት ወይም ለእርሱ ክብር በምንሠቃይበት ጊዜ «ጌታ ይህ ነገር እንዲሆን ለምን ፈቀደ? ምንስ ሊያስተምረኝ ይፈልጋል?» ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ምላሾቻችን በጣም አስፈላጊ ናቸው። በሕይወታችን ውስጥ በሚገጥመን ማንኛውም ነገር ክርስቶስን ወደ መምሰል በይበልጥ ማደግ ይኖርብናል።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡28 ላይ «ሰው ግን ራሱን ይፈትን፤ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከወይኑም ይጠጣ» ብሏል። ይህ ራስን መፈተን (መገምገም) ነው። ሰው ወደ ሕይወቱና ወደ ሥራው በመመልከት በሁሉም አቅጣጫ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘቱን ማረጋገጥ አለበት።

*ታዲያ የቤተ ክርስቲያናችንን ክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም የምንገመግመው ለምንድን ነው?*

*1. የታቀዱ ግቦች በሚገባ ተደርሰባቸው ወይም አልተደረሰባቸው እንደሆነ ለማየት*

የትኛውንም ፕሮግራም በምንጀምርበት ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ ፕሮግራም ውስጥ ሊሠራቸው የሚያቅዳቸውን ነገሮች ግብ አድርገን ማስቀመጥ አለብን። በክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራማችን ውስጥ የማኅበረ ምእመናን እያንዳንዱ አባል ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲያገኝ አንዱ ግብ ከሆነ ይህም የጌታ ፈቃድ እንደሆነ እናውቃለን። ያን ጊዜ እንዲህ ብለን መጠየቅ እንችላለን። «በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኘው እያንዳንዱ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አግኝቷልን?» መልሱ አዎን ከሆነ አብረን ጌታን

እናመሰግናለን። መልሱ አይደለም ከሆነ ያንን ግብ ለመምታት ምን ማድረግ አለብን ብለን እናስባለን።

የታወቁና የተወሰኑ ግቦች ከሌሉን የተገኘውን ዕድገት ለመገምገም ምንም ዓይነት መሠረት ሊኖር አይችልም።

2. አዳዲስ ግቦች ማቀድን ለመርዳት

ከግቦቹ አንዳንዶቹ ከተሟሉ (ከተደረሰባቸው) ሥራው እንዲያድግ አዳዲስ ግቦችን ማቀድ ያስፈልገናል። ግቦቹ ሊደረስባቸው የማይችሉ ከሆኑ ካለንበት እውነታ ጋር በመስማማት የሚደረስባቸው እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርብን ይሆናል። ሆኖም ግቦች ከሌሉን ምንም ነገር ላይ ልንደርስ አንችልም። ይህ ልክ አዳኝ የቀስቱን ፍላፃ ወደ ጨለማ እንደሚወረውር ይመስላል። ዒላማውን ይመታልን? በፍጹም አይመታም።

3. የሠራተኞቻችንን ውጤታማነት ለመመርመር

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ፕሮግራም ከመሪዎቹና ከሠራተኞቹ ይልቅ ጠንካራ አይደለም። ለእያንዳንዱ ክፍል በጣም ጥሩ የሆኑትን መሪዎችና ሠራተኞች መምረጥ አለብን። አንዳንዶች ስጦታ ከሌላቸውና በራሳቸው የአገልግሎት መስክ ጥሩ መሥራት ካልቻሉ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር ሊያስፈልጋቸው ይችላል። በአንዳንድ በተወሰኑ አቅጣጫዎች ላይ የሠለጠኑና የተዘጋጁ አዳዲስ አባላት ሊመጡ ይችላሉ። ለእነርሱም ቦታ ማዘጋጀት አለብን።

4. ድካምን ለማወቅ

ምንም ዓይነት ዓላማና ግብ ይኑረን ግምገማ በምንጀምርበት ጊዜ ድካሞች እንዳሉ እናውቃለን። ድካሞች ምን እንደሆኑ ማወቅና እነዚያን የድካም አካባቢዎች ለመፈወስ የእግዚአብሔርን ምሪት መፈለግ አለብን። ስሕተቱ ምናልባት በዕቅድ ጊዜ ይሆናል። ወይም ግባችንን በምናስቀምጥበት ጊዜ ከተጨባጭነት ርቀን ይሆናል። ምናልባትም በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሁኔታዎች ዓላማችን ላይ መድረስ እንዳንችል አድርገው ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በሠራተኞች ለውጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መቀያየር ምክንያት ለውጥን ወይም ወደ ኋላ መቅረትን አስከትሎ ይሆናል። የችግሮቹን ምክንያቶች መፈለግና ችግሮቹን መፍታት ግዴታችን ነው።

5. ብርታታችንን ለማወቅ

ግምገማ ሁሉ አሉታዊ አይደለም። ብዙዎች ፕሮግራሞቻችሁ በእርግጥ እንደተከናወኑና በሚገባ እንደተሠሩ ታውቃላችሁ። ይህ ለእናንተና ለቤተ ክርስቲያንም ትልቅ ማበረታቻ ነው። ፕሮግራሙ በሚገባ እንዲካሄድ ያደረጉትን ምክንያቶች ፈትሹ። ለወደፊቱ ሊረዱችሁ የሚችሉ ነገሮችን ልትማሩ ትችሉ ይሆናል።

6. ዕድገትንና ትምህርትን ለማበረታታት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ፕሮግራሞች በጥሩ ሁኔታ ከተካሄዱ ሠራተኞችና ተካፋዮቹ በጣም ይበረታታሉ፤ ይህም በበለጠ እንዲሠሩ ያነሣሣቸዋል፤ ጥልቅ ፍላጎትንና ደስታን ይፈጥራል። በአገልግሎታቸው ላይ ከፍተኛ ጥረትን እንዲያደርጉ ያነሣሣቸዋል።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፦ የቤተ ክርስቲያናችንን የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም የምንገመግምበትን ምክንያቶች ዘርዝር። |

የተገኘውን ዕድገት ለማወቅ፥ የውድቀትና የድካማችን ምክንያቶችን ለመፈለግና በአዎንታዊ ውጤቶች ለመበረታታት የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን መገምገም አስፈላጊ ነው።

## ሁለተኛ ቀን፦ የክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራም እንዴት ይገመገማል?

ባለፈው ትምህርታችን ፕሮግራማችንን ለምን መገመገም እንደሚያስፈልገን ምክንያቶችን አይተናል። አሁን ደግሞ እንዴት እንደምንገመግም ለማሰብ እንፈልጋለን። ሁለት ዓይነት ግምገማዎች አሉ፦ ሂደቱን መገምገምና ውጤቱን መገምገም ናቸው። ሁለቱም ያስፈልጋሉ።

1. ሂደቱን መገምገም

በዚህ የግምገማ ክፍል ውስጥ ግድ የሚለን በትምህርት ፕሮግራሙ ውስጥ ያለው ሂደት ነው። ይህ በዋናነት የሚመለከተው አስተዳደሩንና መምህራኑን ነው።

አስተማሪዎቻችንን በሥራው ላይ እያሠለጠንናቸው ነበር እንበል። በሳምንታዊ ስብሰባችን ላይ እንዴት ትምህርቶቻቸውን እንደሚያዘጋጁና እንደሚያስተምሩ፥ በክፍላቸው ውስጥ ሥነ ሥርዓትን እንዴት እንደሚያስከብሩ፥ ወዘተ. . . አስተምረን ነበር። እንዴት ልንገመግማቸው እንችላለን?

አንደኛው መንገድ ትምህርቱን ካዘጋጁ በኋላ እናንተ እንድታርሙት ሊሰጧችሁ ይችሉ ይሆናል። ሌላኛው መንገድ በሥልጠና ክፍል ውስጥ የናሙና ትምህርት እንዲያስተምሩ ማድረግ ነው። ሦስተኛው መንገድ በሚያስተምሩበት ጊዜ መጎብኘትና ሲያስተምሩ መመልከት ነው።

ሦስተኛው መንገድ ከሁሉ የተሻለው መንገድ መሆኑ እውን ነው። ምክንያቱም የትምህርቱን ይዘት ብቻ ሳይሆን የአስተማሪውን ጠባይ እና የተማሪዎቹን የመቀበልና ምላሽ የመስጠት ችሎታ ለማየት ያስችላል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችሁን መጠየቅ ትችላላችሁ። ትምህርቱን ያስተዋወቀው እንዴት ነው? ተማሪዎቹን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የመራቸው እንዴት ነው? ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱ

ያደረጋቸው እንዴት ነው? በመማር/ ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲያድግ እንዴት አደረገ? የትምህርቱ አጨራረስ እንዴት ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ ከማስተማሩ ሂደት ጋር የሚሄዱ ናቸው። ሂደቱ ደካማ ከሆነ አስተማሪዎቻችን እንዲሻሻሉ በነዚህ አቅጣጫዎች ተጨማሪ ሥልጠና መስጠት እንችላለን። በጥሩ ሁኔታ በሚገባ የሚሠሩ ከሆነ ልናመሰግናቸውና ጥሩ ዘዴያቸውን ከሌሎች ጋር እንዲካፈሉ ልናደርግ ይገባል።

አስተዳደርን የምንገመግም ከሆነ በየሳምንቱ እያንዳንዱ ክፍል አስተማሪ እንዳለው ማጣራት ይኖርብናል። በክርስቲያናዊ ትምህርት ፕሮግራምና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ነገሮች በጥንቃቄ ተመዝግበው መቀመጣቸውን እናያለን። ይህ የሰዎች መገኘትን፥ መባን፥ ጉብኝትን፥ የወንጌል ስርጭትን፥ ጥምቀቶችን፥ አዲስ የተለወጡ ሰዎችን ያካትታል። ለአስተማሪዎች የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላታቸውን እናረጋግጣለን። ለሠራተኞቹ ፍላጎት አስተዳደሩ ንቁ ነበርን? ለቤተ ክርስቲያን ቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ ተከፍሏልን? ለአዳዲስና ጊዜያዊ ሁኔታዎች ሰዎች በጊዜው እንዲያውቁና በተከታታይ መረጃ ሲሰጣቸው ቆይቷልን?

2. ውጤቶችን መገምገም።

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያለውን ትምህርት ውጤት ለመለካት መንገዶችን መፈለግ አለብን። የመልካም ትምህርት ውጤት መለኪያ አንዱ መንገድ ሳምንታዊውን በየክፍሉ ያለ የተካፋይ ብዛት መመልከት ነው። ክፍሎች እያደጉ ነውን? አንዱ ክፍል እያደገ ከሆነ አስተማሪው ጥሩ እየሠራ ነው ማለት ነው። አስተማሪው ተማሪዎችን ሲያነሣሣ፥ በውስጣቸው ፍላጎትን ሲቀሰቅስና ስለ ክፍላቸው ለሌሎች ተናግረው ሌሎች እንዲመጡ ሲስብ ነበር ማለት ነው።

በአመለካከቶች ላይ ለውጥ ታያላችሁን? ይህን መለካት ከበድ ይላል፤ ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ በሰዎቹ መካከል ተጨባጭ የአመለካከት ለውጥ ሊኖር ይገባል።

በአባሎች መካከል የበለጠ ፍቅር፥ ርኅራኄና የእርስ በርስ መተሳሰብ ሊኖር ይገባል። መሪዎች በክርክሮችና ባለመስማማቶች፥ በጋብቻ ችግር፥ በዓመፀኛ ወጣቶች ላይ ያጠፉት ጊዜና ሁኔታ አነስተኛ ነበርን?

የጠባይ ለውጥ ነበርን? ያረጁ ዓለማዊ አሳቦች ተሸንፈዋልን? ሰዎቻችሁ በሚመለከታቸው ዓለም ፊት ስለሚኖሩት ምሳሌነት ተጨማሪ ጥንቃቄ ወስደዋልን? ቁጣ ቀንሷልን? መልካም ያልሆነ አነጋገር ቀንሷልን? ራስ ወዳድነት ቀንሷልን? ኩራት ቀንሷልን?

ሰዎች ላልዳኑት ካለፈው የበለጠ ግድ ይላቸዋልን? የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በታማኝነት ከተሰጠ፥ ተማሪዎች ክርስቲያን የመሆንን ደስታ ላላወቁት ሰዎች ለማካፈል ከፍ ያለ ተቆርቋሪነት ይሰማቸዋል። በምስክርነት

ትጋትን ያሳያሉ። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት የበለጠ በንቃት ይሠራሉ።

3. የምንገመግመው ሊታይ እና ሊለካ የሚችል መሆን አለበት።

ከላይ እንደጠቀስነው ሊታዩና ሊለኩ የሚችሉ ነገሮች በግምገማ ጊዜ ይከናወናሉ። ሂደቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ ከተገኘ ውጤቱን ራሱ ያሳያል።

መዝገብን (የቁጥር መረጃዎችን) በተመለከተ ምን ይሆን እንደ ነበረ በቀጥታ መመልከት እንችላለን። ለምሳሌ የስም መቆጣጠሪያ መዝገብን በመመልከት ቤተ ክርስቲያን እያደገች መሆኑን ወይም አለመሆኑን መለካት እንችላለን። አንዳንዶቹ ሌሎች አካባቢዎች በቀላሉ ሊደረስባቸው አይችልም። ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ሊታዩ የሚችሉ ውጤቶች አሉ። በአመለካከትና በጠባይ ለውጥ ከታየ በጥንቃቄ ለሚያይ ሰው ግልጽ ይሆናል።

ለግምገማችን የሚሆን መረጃ የምናገኝበት ሌላው ምንጭ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚሠሩ አስተማሪዎችና መሪዎች ምላሽ በመስማት ነው። ለውጥን ለማየት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኘው ለእያንዳንዱ ሰው በበቂ ሁኔታ ቅርብ ላትሆኑ ብትችሉም፥ የሚያስተምሩና የሚያስተዳድሩት በይበልጥ ቀረብ ብለው ለማየት ይችላሉ። የተገነዘቡትን ነገር እንዲገልጹ የሚሞላ ቅጽ ልትሰጡአቸው ትችላላችሁ። የተሻለው መንገድ ለመሪዎቻችሁ ትልቅ ስብሰባ አዘጋጅቶ ውይይት ማካሄድ ችግሮችን የመመልከት ጊዜ ማድረግ ይሆናል። በጣም ብዙ ጊዜ ይህ ጠቅላላውን ፕሮግራም እንድትገመግሙ የሚያስችሉ ብዙ ነጥቦችን ይገልጻል።

ሌላኛው መንገድ የሚሆነው ደግሞ ከተለያዩ ክፍል አባላት ጋር በመገናኘት እነርሱ የሚሉትን ማድመጥ ይሆናል። ጥሩ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ውስጥ ከሚማሩት ብዙ ነገሮችን ልትማሩ ትችላላችሁ።

3ኛ ጥያቄ፡- ይህንን ትምህርት ስትመለከት ስለ ግምገማ አስፈላጊነት ያገኘኸው ምን አዲስ አሳብ አለ? ጻፈው። በቤተ ክርስቲያንህ ስለሚካሄድ ግምገማ የምታወቀው ነገር አለን? ተሳትፈሃልን? እንደዚያ ከሆነ፥ ግምገማውን በማድረግ ያገኘሃቸውን አንዳንድ መበረታታቶች ጻፍ። የተደረሰባቸውን አንዳንድ ድክመቶች ጻፍ። ምን ምን የመፍትሔ አሳቦች ተሰጥተዋል?

ግምገማ በጣም አስፈላጊ ነው። ከግምገማ ብዙ ነገር መማር ይቻላል። ሁለቱ የግምገማ ዓይነቶች ሂደትና ውጤቶች ናቸው። ግምገማ በምናደርግበት ጊዜ የግምገማውን ውጤት ከዓላማችን ጋር በማስተያየት ዒላማችንን መትተን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማየት ለፕሮግራሙ ያለን ዓላማ በበቂ ሁኔታ ግልጽ መሆን አለበት።

ስለ ክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና እና ዓላማ የሚያወራውን የትምህርት አንድ ሦስተኛ ቀን ትምህርት እንደገና አንብብ። የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና በቤተ ክርስቲያን የትምህርት አደረጃጀት ሥራ ላይ

ሂሳዊ አስተሳሰቦችን ማስገባት እንደሆነ ተናግረናል። የእምነት አቋማችንንና ይህንን ለሰዎች ለማስተማርና እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የምናደርገውን ጥረት ይመለከታል።

የክርስቲያናዊ ትምህርታችን ዓላማ ፍልስፍናውን ተግባራዊ ወደሚሆንበት ሁኔታ አምጥቶታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን እያንዳንዱን የዕድሜ ክልል ፍላጎት ለመድረስ ጥንቃቄ የተሞላበትን ዝርዝር የፕሮግራም ዕቅድ ይጨምራል። ዓላማዎቹ ይዘቱን፥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዘዴዎችና ዕቃዎች እንዲሁም የፕሮግራሙ ውጤት ይሆናሉ ተብሎ የሚጠበቁትን ያጠቃልላሉ። ውጤቶች ደግሞ ተማሪው ከትምህርቱ የተነሣ ሊያብራራ የሚችለውን ነገርና በሕይወቱ ውስጥ የታየውን ለውጥ ይጨምራሉ።

ስለዚህም ግምገማችን ከዓላማችን ጋር መወዳደር አለበት። ይህ ልንሠራው ያሰብነውን ነገር መሥራታችንን ወይም አለመሥራታችንን እንድንመረምረው ይረዳናል።

ሦስተኛ ቀን፡- ምን እንደምንገመግም

የግምገማ ዓላማ ጠቅላላውን የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ፕሮግራም ለማሻሻል እስከሆነ ድረስ ሁሉንም ፕሮግራም መገምገም ያስፈልገናል። ከዚህ ኮርስ በጤናማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ፕሮግራሞች እንደሚካሄዱ ትረዳላችሁ።

I. የምንገመግማቸው ፕሮግራሞች

1. የሰንበት ትምህርት ቤት፡- ሂደቱንና ውጤቶቹን በማካተት የሰንበት ትምህርት ቤትን መገምገም ትችል ይሆናል። ሁለተኛ ቀንን ተመልከት። ለሚከተሉት ፕሮግራሞችም ለእያንዳንዳቸው የሚሠራና እውነት ይሆናል።

2. የወጣቶች ፕሮግራም

3. የወንዶች አገልግሎት ፕሮግራም

4. የሴቶች አገልግሎት ፕሮግራም

5. የጥናት ቡድኖች

6. የወንጌል ስርጭትና ሌሎችን የመድረስ ፕሮግራም

7. ልዩ ክፍሎች

8. የመሪዎች ሥልጠና ፕሮግራም ስለዚህ በምዕራፍ አሥራ ሰባት የበለጠ እንማራለን።

II. የሠራተኞች ግምገማ

እንደዚህ ዓይነቱ ግምገማ በብዙ ጸሎትና በብዙ ዘዴ መካሄድ አለበት። አብዛኛው የሠራተኞች ግምገማ የሚካሄደው ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በመመልከት ነው። ሆኖም መደረጉ በጣም አስፈላጊ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ላይ የተሰጡ ሊረዱን የሚችሉ ሁለት መመዘኛዎች አሉ። የቁጥር 26

ክፍል እንዲህ ይላል፡- «ሁሉ ለማነጽ ይሁን»። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠራው ማንኛውም ነገር የሚሠራው ቤተ ክርስቲያንን በማነጽ ዓላማ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ማለት ሰዎች እንደሆኑ እናውቃለን። ስለዚህም ሁሉም የሚሠራው ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለማጠንከር መሆን አለበት። በዚህ መንገድ በቤተ ክርስቲያን የማይጠቅሙ ሠራተኞች ካሏችሁ መዛወር ወይም መተካት ይኖርባቸው ይሆናል። እግዚአብሔርም በእያንዳንዱ ሁኔታ ይመራችኋል። ሌሎች ሠራተኞች ደግሞ በጣም ጠቃሚ ይሆኑና እነርሱን ለመርዳትና ለማበረታታት የምትችሉትን ሁሉ ለማድረግ ትፈልጋላችሁ።

ሁለተኛ ጥቅስ 14:40 ሲሆን፥ «ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን» ይላል።

III. የመሰብሰቢያ ቦታዎች ግምገማ

ላሏችሁ ፕሮግራሞች ሕንፃዎቻችሁ ምን ያህል በቂ እንደሆኑ መፈተሽ ይኖርባችኋል። ቤተ ክርስቲያናችሁ የምታድግ ከሆነ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ለመሥራት ወይም ባለው ሕንፃ ላይ ለመጨመር ማሰብ ያስፈልጋችሁ ይሆናል። ለትምህርት የሚሆኑ ክፍሎች አሏችሁን? የአስተዳደር ሠራተኞችና አስተማሪዎች ሊሰበሰቡ የሚችሉበት ከመጋቢና ከሽማግሌዎች ቢሮ ሌላ ክፍሎች አሏችሁን?

IV. የመዝገብ አያያዝ ግምገማ

ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘገባዎች መታየትና በየጊዜው ወቅታዊ መደረግ አለባቸው። በየዓመቱ የተካሄደውን ለማወዳደርና ለመገምገም በፋይል ውስጥ መዝግቦ መያዝና በቋሚ ቅጽ ሞልቶ ማስቀመጥ በጣም ይረዳል።

V. ሥርዓተ ትምህርትን መገምገም

በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተካሄዱትን የትምህርት ፕሮግራሞች በምትመለከቱበት ጊዜ የተለያዩትን ቡድኖች ፍላጎት ያሟላ ነበርን? ተማሪዎች እንዲጠቀሙ በትክክለኛው ደረጃ የተሰጠ ነውን? የቤተ ክርስቲያንን የመድረክ አገልግሎት አግዟልን? ከሥርዓተ ትምህርታችሁ ጋር በሚጣጣም መንገድ ሌሎች ጥያቄዎችን መጨመር ትፈልጉ ይሆናል።

VI. የእምነት አቋምን፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት ፍልስፍና ዓላማህን መገምገም።

በመጨረሻም በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስለሚካሄደው የትምህርት ፕሮግራም ያቀዳችሁትን ዕቅድ ተመልሶ መመልከት አስፈላጊ ነው። የቤተ ክርስቲያንን እያንዳንዱን የሥራ መስክ በምትገመግሙበት ጊዜ አንዳንዶቹን መለወጥ ወይም ደግሞ ወቅታዊ ማድረግ ትፈልጉ ይሆናል።

4ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያናችሁ ጠቅላላ ፕሮግራም ውስጥ መገምገም ያስፈልጋቸዋል የምትላቸውን የተለያዩ መስኮች በዝርዝር ጻፍ። ይህ ግምገማ ወደ

ዓመታዊ ሪፖርት ሊያድግ ይችላልን? አንዳንዱ ክፍልስ በምሥጢር ለሽማግሌዎች ቦርድ ብቻ የሚሆን ይሆንን?

## አራተኛ ቀን፡— መቼ እንደምንገመግም።

### 1. መቼ እንደምንገመግም

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ ችግር እስካልደረሰባቸው ድረስ የግምገማን አስፈላጊነት አይረዱትም። ስለዚህም የችግራቸውን ጭብጥ ለመረዳት ተደጋጋሚ ስብሰባዎች በማድረግ ብዙ ጊዜ ይፈጃሉ፥ ቋሚ የሆነ የግምገማ ጊዜ ቢኖራቸው ኖሮ ከዚያ እጅግ ባነሰ ጊዜ ያቃልሉት ነበር።

የግምገማ ጊዜ ቋሚ በሆነ መንገድ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሊደረግ ይገባል። በየዓመቱ ልንጠቀምበት እንድንችል በጥሩ ዘዴ ፈጽሞ ሊሠራና ሊዘጋጅ ያስፈልጋል። አንድ ጊዜ ከተሠራ በየዓመቱ ለመጠቀም በጣም ቀላል ይሆናል። ግምገማ ለማድረግ ጥሩው ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ የሥራ ስብሰባ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ ቢሆን ነው። ከዚያም ምሥጢራዊ ያልሆኑትን የግምገማ ክፍሎች በየዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ በማስገባት መጠቀም ይቻላል። ዓመታዊ ሪፖርቶች (ዘገባዎች) ለማኅበረ ምእመናኑ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ምክንያቱም ስለ ሥራው ዕድገት መረጃ በመስጠት ለመቀጠል የሚያበረታታ ይሆንላቸዋል።

በየወሩ ወይም በየሦስት ወሩ የሚደረግ ግምገማ ለማካሄድ የምትፈልጉበት ምክንያት ሊኖራችሁ ይችላል። ይህ ከአስተዳደር ሠራተኞቻችሁ ጋር በመነጋገር ልትወስኑት የምትችሉት ጉዳይ ነው።

ሌላው ሕጋዊ ያልሆነ ግምገማ (ሁልጊዜ) ማካሄድ ይቻላል የሚል አሳብ አለ። አስተማሪዎቹ ለመሻሻል ለመሞከር በየሳምንቱ የማስተማር ዘዴዎቻቸውን መገምገም አለባቸው። የሥራ መሪዎችም ጥሩ ተመልካች፥ ሥራውንም ለማሻሻል በሚያስፈልግ ሁሉ ሠራተኞቻቸውን ለማበረታታት፥ ለማሠልጠን፥ ለማረም፥ ለመገሠጽ የሚገመግሙ መሆን አለባቸው።

### 2. የግምገማ ጥቅም

ግምገማ ብዙ ጥቅሞች አሉት

ሀ. ችግሮች ወደ ቀውስነት ከማደጋቸው በፊት ለይታችሁ እንድታውቁዋቸው ይረዳል። በብዙ ሁኔታዎች ችግሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያድጉት የትምህርት ማነስ ስላለ ነው። ጥሩ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም ከጥሩ አስተማሪዎችና መሪዎች ጋር ካላችሁ ብዙዎች ችግሮች አያድጉም። ሆኖም ችግሮች ይነሣሉ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ንቁና ጠንቃቃ ከሆኑ ችግሮች ወደ ተራራነት ከመለወጣቸው በፊት በሚገባ በጊዜው አስፈላጊ ነገሮችን በማድረግ ይረቷቸዋል።

ለ. ግምገማ የትኞቹ ፕሮግራሞች በጥሩ ሁኔታ እንደሚካሄዱ የትኞቹ ደግሞ ገና እንደሚፍገመገሙ ለማወቅ ይረዳል። አዎንታዊ እና አሉታዊ የሆኑትን ምክንያቶች ለይታችሁ እንድታውቁ ይረዳል።

ሐ. በየክፍሉ ስለሚደረገው ነገር ሁልጊዜ መረጃ እንዲኖራችሁ ያደርጋል። ይህም በእውቀት እንድትጸልዩና ምሪትን በመስጠት ብዙ እንድታግዙ ያደርጋችኋል።

3. በግምገማ ጊዜ የምናካትታቸው አንዳንድ ነገሮች

ሀ) የእምነት አቋም፥ ፍልስፍናና ዓላማዎች

1. ከላይ የተጠቀሱት የተገመገሙት መቼ ነበር?
2. ምን ለውጦች ተደርገው ነበር? ለምን?
3. ዓላማዎቹ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሁሉንም የአገልግሎት መስኮች ያጠቃለሉ ነበርን? ካልሆነ መጨመርና መዘለል ያለበት ነገር ምንድን ነው?

ለ. ድርጅትና አስተዳደር

1. እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ሠራተኞች ለእርዳታና ለምሪት ፍለጋ ሲሄዱ ሊጠይቁት የሚችሉት መሪ አለን?
2. የሰንበት ትምህርት ቤት የሥራ መሪ አለውን?
3. በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ስንት ክፍሎች አሉ?
4. ስንት አስተማሪዎች አሉ?
5. ለአስተማሪዎች ቋሚ የሥልጠና ስብሰባዎች ይደረጋሉን?

(እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ጥያቄዎች ለእያንዳንዱ ፕሮግራም ሊሠሩ ይገባል።)

6. ቤተ ክርስቲያኒቱ የመሪነት ሥልጠና ፕሮግራም አላትን?

ሐ. መዝገብ

1. በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች የሚመጡ ሰዎች ቁጥር ተመዝግቦአልን?
2. እነዚህ የተመዘገቡት በቀላሉ ካለፉት ዓመታት ጋር ለማወዳደር እንዲቻል ተጠብቀዋለን?
3. እነዚህ መዝገቦች ሊያዩዋቸው ለሚፈልጓቸው በቀላሉ ሊያገኟቸው እንደሚችሉ ናቸውን?
4. እነዚህን መዝገቦች የፕሮግራሞችን ዕድገት ለመገምገም ተጠቅመንባቸዋልን?

መ) የመሰብሰቢያ ቦታና መሣሪያዎች

1. ለታቀዱት ፕሮግራሞች የሚሆኑ በቂ ክፍሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሉን?

2. በቂ የሆኑ መሣሪያዎችስ አሉን? (ጥቁር ሠሌዳ፥ አግዳሚ ወንበር፥ ጠረጴዛ፥ ወዘተ. . . )

ሠ. ሥርዓተ ትምህርት

1. ሥርዓተ ትምህርቱን ያዘጋጀው ማን ነው?
2. አሁን ያለው ሥርዓተ ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት አያሟላ ነውን?
3. ሥርዓተ ትምህርቱ በቤተ ክርስቲያን የሚካሄደውን የስብከት ፕሮግራም የሚረዳ ነውን?
4. ሥርዓተ ትምህርቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ ትክክለኛና መለኮታዊ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ ያቀርባልን?
5. የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ በሁሉም መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማሉን?
6. የትምህርት መሣሪያዎቹ ተማሪዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ወደ ሕይወታቸው እንዲያዛምዱ የሚያበረታቱ ናቸውን?
7. የተጠቀምንበት መጽሐፍ ለአስተማሪው በቂ የሆነ እርዳታ ይሰጣልን?
8. የትምህርት መሣሪያዎቹ ለጠንካራ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አቋም ትኩረት ይሰጣሉን?
9. የትምህርት መሣሪያዎቹ የተማሪዎችን የዕድሜ ክልል ለመድረስ የተዘጋጁ ናቸውን?

ይህ በግምገማ ጊዜ ሊጠየቁ የሚችሉ ጥያቄዎች ዝርዝር ነው። ከዚህ ላይ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ትፈልጉ ይሆናል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች ታውቃላችሁ፥ ስለሆነም ምን መጨመር እንደሚያስፈልግ ታያላችሁ።

---

5ኛ ጥያቄ፡- ይህንን የተጠቆመ ግምገማ አንድ ጊዜ በደንብ ተመልከቱና ለቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎት በሚስማማ መልኩ ለማሻሻል ጨምሩበት ወይም ቀንሱበት።

---

ጊዜውን የጠበቀ ግምገማ ቤተ ክርስቲያንን በጣም ሊያግዛት እንደሚችል አይተናል። ይህንን ሥራ ለመሥራት ጊዜ መውሰድ እውነተኛ ጥቅም አለው። ጥብቅ ከሆነ ግምገማ የተወሰደ ትምህርትና መሪዎች ከዚህ ውስጥ ሊያዩና ሊወያዩበት የቻሉት ነገር ከቤተ ክርስቲያን ሥራ አንዳንድ ችግሮችን በማጥፋት አዲስ መንገድን አይታን ይሰጣል።

አምስተኛ ቀን፡- በትምህርት አሥራ ዘጠኝ ውስጥ ያሉትን ነጥቦች በሙሉ ክለሱ። በሳምንታዊ ስብሰባ ውስጥ ለሚሰጡት የመወያያ ጥያቄዎች ተዘጋጁ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ለስብሰባው የተለመደውን አሠራር ተከተሉ።

**የመወያያ ርእሶች**

1. በቤተ ክርስቲያንህ ግምገማ ተካሂዶ ያውቃልን? ግምገማ እናድርግ የሚለውን አሳብ በምታቀርብበት ጊዜ ይገጥሙኛል ብለህ የምታስባቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

2. ግምገማን በማድረግ የሚገኘው ጥቅም ምን ይሆናል ብለህ ትጠብቃለህ?

3. ብዙዎቻችሁ ለምትሳተፉበት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ላለ ፕሮግራም ግምገማ አድርጉ። ዘዴያዊ በሆነ መንገድ አንዱን ፕሮግራም ምረጡና ተመልከቱት። ዓላማዎች ከሌሉት ጻፉለትና ፕሮግራሙ ተስማሚና በቂ እንደሆነ አወዳድሩ። ዓላማዎቻችሁን፥ ግምገማችሁንና ማጠቃለያችሁን ጻፉ።

## ትምህርት ሃያ

## ክለሳ

### አንደኛ ቀን፦ የታላቁ ምሳሌያችን የኢየሱስ የማስተማር ዘዴዎች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ በጣም ጥሩ አስተማሪ ነበር። እንደ ክለሳ አድርገን አእምሮአችንን ለማደስ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን የእርሱን የማስተማር ዘዴዎች መመልከት እንፈልጋለን።

1. ለትምህርቱ ጥሩ መግቢያ በመስጠት ትኩረታቸውን ያገኝ ነበር።

ሀ) ዮሐንስ 4:7–15 አንብቡ።

- ከዚህች ሴትዮ ጋር እንዴት አድርጎ ግንኙነት ፈጠረ? (4:7)
- ይህ ጥሩ የግንኙነት ነጥብ ነው ብለህ ታስባለህን? (4:9፤ 11:15) ለምን?
- ኢየሱስ ሊያስተምር የቻለው መንፈሳዊ እውነት ምንድን ነው? (4:14)

ለ. ማቴ. 5:1–12 አንብብ።

- ኢየሱስ የተራራውን ስብከት በሚጀምርበት ጊዜ ደስተኛ ለመሆን የተለያዩ ሁኔታዎችን ሰጠ። ይህ ጥሩ ግንኙነት የሚሆነው ለምንድን ነው?

- በዮሐንስ 6:3–13 የሚገኘውን የምታስተምር ብትሆን፥ ምን ዓይነት አቀራረብ ወይም የግንኙነት ነጥብ ትሰጠው ነበር?

2. ከሚታወቀው ወደ ማይታወቀው ይሄድ ነበር።

ሀ. ማቴ. 5:21–22፤ 27–28፤ 31–34 አንብብ።

- በማቴ. 5፡27 ላይ ተማሪዎቹ አስቀድመው ያውቁት የነበረው ነገር ምንድን ነው?

- በማቴ. 5፡28 ያስተማራቸው ተጨማሪ እውነት ምንድን ነው?

ለ. ሉቃ. 10፡9 አንብብ።

- በዚህ ጥቅስ ውስጥ ኢየሱስ ራሱን ከማን ጋር ያወዳድራል?

- ተማሪዎቹ በዚህ ምንባብ ውስጥ ቀደም ብለው የሚያውቁት ነገር ምን ነበር?

- ኢየሱስ ራሱን ከበር ጋር በሚያወዳድርበት ጊዜ ሊረዱት የጀመሩት አዲስ እውነት ምን ነበር?

3. ትምህርቱን ከተማሪዎች አንገብጋቢ ችግሮችና ፍላጎቶች ጋር ያዛምድ ነበር።

ሀ. ዮሐንስ 3፡1–6 አንብብ።

- የኒቆዲሞስ አንገብጋቢ ፍላጎት ምን ነበር? ኢየሱስ ወዲያውኑ ኒቆዲሞስን በፍላጎቱ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ ጠየቀው። ከዚያም መልሱን በዝርዝር አብራራለት።

ለ. ሉቃስ 5፡29–32 አንብብ።

- ኢየሱስ ከሌዊ ጋር በሚበላበት ጊዜ የፈሪሳውያንና የጻፎች ፍላጎት ምን ነበር?

- ኢየሱስ በዚህ ምንባብ ውስጥ ምን ሊያስተምራቸው ሞከረ?

- የተማሪዎቻችችሁን ሦስት ፍላጎቶች ከጻፋችሁ በኋላ እነዚያን ፍላጎቶች የሚያሟሉ ጥቅሶች ጻፉ።

4. ታሪኮችን ከነገረ በኋላ ከዕለታዊ ሕይወታቸው ሁኔታ ጋር ያዛምድ ነበር። ብዙ ጊዜ ምሳሌዎችን ይጠቀም ነበር። ምሳሌ በሕይወት የሚደረስበት መንፈሳዊ ትርጉም ያለው እውነታ ነው።

ሀ. ሉቃ. 15፡1–6 አንብብ።

- ታሪኩን በአጭሩ ተናገር። ይህ ታሪክ ከሰሙት ሰዎች ጋር እንዴት ይዛመዳል! (15፡7)

ለ. ሉቃ. 10፡25–37 አንብብ።

- እዚህ የመልካሙን ሳምራዊ ታሪክ እናገኛለን። ኢየሱስ ተማሪዎች ይህንን ታሪክ ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ምን አደረገ? (ሉቃ. 10፡36–37)

ሐ. ማር. 12፡1–12 አንብቡ።

ይህ ታሪክ ከሰሚዎቹ ሕይወት ጋር የሚገናኘው እንዴት ነው?

5. እውነቱን ግልጽ ለማድረግ የገለጻ ምሳሌዎችን ይጠቀም ነበር።

- በማቴ. 5፡13 ላይ የሚገኘው የገለጻ ምሳሌ ምንድን ነው? ምን እውነት ያስተምራል?

– በማቴ. 5፡14 ላይ የሚገኘው የገለጻ ምሳሌ ምንድን ነው? ምን እውነት ያስተምራል?

– ኢየሱስ በዮሐንስ 15፡5 ላይ የተናገረውን አንብብ። ወይኑ ስለ ክርስቶስ ምን ያስተምረናል? ቅርንጫፎቹ ስለ ክርስቲያኖች ምን ያስተምራሉ?

6. ኢየሱስ እውነቱን ለማብራራት ግልጽ የሆኑ ሥዕላዊ ቃላትን ተጠቅሟል።

– ኢየሱስ የተማሪዎችን አሳብ ለመማረክ ሥዕላዊ ቃላትን ተጠቅሟል። በማቴዎስ 6፡2 ላይ የምታገኙት ሥዕላዊ ቃል ምንድን ነው? በእነዚህ ቃላት ኢየሱስ ሊያተኩር የፈለገው እውነት ምንድን ነው?

– የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ። ማቴ. 6፡19፤ 6፡22፤ 6፡16፤ 23፡27፤ 23፡24። ወደ ታች በዝርዝር ከጻፋችኋቸው በኋላ ከፊት ለፊት ግልጽ የሆነውን ኢየሱስ የተጠቀመበትን ሥዕላዊ ቃል ጻፉ። ሰዎች እንዴት በቀላሉ የሚታለሉ መሆናቸውን የምታስተምሩ ከሆነ ስለ መታለል የምትሰጡት ሥዕላዊ ቃል ምንድን ነው?

7. ኢየሱስ በሚያስተምርበት ጊዜ የሚታዩ የትምህርት መርጃዎችን ይጠቀም ነበር።

– ሉቃ. 18፡15–17 ተመልከት። ኢየሱስ የተጠቀመው «የሚታይ የትምህርት መርጃ» ምንድን ነው? ምን እውነት ያስተምራል?

– ማቴ.6፡26 አንብብ። ኢየሱስም አለ፥ ..........ተመልከቱ

– ማቴ. 6፡28 አንብብ ኢየሱስም አለ፥ ............. ተመልከቱ

በምታስተምርበት ጊዜ እውነቱን ግልጽ እና የሚገባ ለማድረግ የሚረዱህ ዕቃዎች የሚገኙ ሥዕሎች ካሉ እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ጸልይ።

8. አእምሮን የሚያሠሩ ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር።

ሀ. ማር. 4፡30 አንብብ። ኢየሱስ እንዲያስቡት አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው። መልስን አልጠበቀም ነበር። ሊያብራራላቸው ጀመረ። ጥያቄው ምን ነበር?

ለ. በሚከተሉት በእያንዳንዱ ምንባቦች ውስጥ የጠየቃቸው አእምሮን የሚያሠሩ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? (ማቴ. 16፡26፤ ሉቃ. 20፡1–8)

# ማጠቃለያ

እንኳን ደስ ያለህ! ይህንን የክርስቲያናዊ ትምህርት ኮርስ አሥራ ዘጠኝ ትምህርቶችን አጠናቀሃል። የመጨረሻ ፈተናዎቹን በአራት ክፍለናቸዋል። በዚህ በመጨረሻው ሳምንት በእያንዳንዱ ቀን አንድ ፈተና ብትሠራ፥ አምስተኛውን ቀን መከናወንን የሰጠህን እግዚአብሔርን የምታከብርበት ልዩ የበዓል ቀን ልታደርገው ትችላለህ።

አንደኛ ቀን፡— ከትምህርት አንድ እስከ አራት ያሉትን ከልስ። ለዚህ ክፍል የተመደበውን ፈተና ሥራ /ጻፍ/።

ሁለተኛ ቀን፡— ከትምህርት አምስት እስከ አሥር ያሉትን ከልስ። ለዚህ ክፍል የተመደበውን ፈተና ሥራ /ጻፍ/።

ሦስተኛ ቀን፡— ከትምህርት አሥራ አንድ እስከ አሥራ አምስት ያሉትን ከልስ። ለዚህ ክፍል የተመደበውን ፈተና ሥራ/ጻፍ/።

አራተኛ ቀን፡— ከትምህርት አሥራ ስድስት እስከ አሥራ ዘጠኝ ያሉትን ከልስ። ለዚህ ክፍል የተመደበውን ፈተና ሥራ/ጻፍ/።

አምስተኛ ቀን፡— በዓል አድርግ!

# BIBLIOGRAPHY


Arthur, Kay. How to Study Your Bible. Eugene, Ore., Harvest House Publishers, 1994.

Baker, Pat. Help! I've Just Given Birth to a Teenager. Grand Rapids, MI., Baker Book House, 1981.

Billheimer, Paul E. Destined for the Throne. Minneapolis, MN., Bethany House Publishers, 1975.

Briscoe, Jill. Women Who Changed their World. Wheaton, IL., Victor Books, 1991.

Cho, Paul Yonggi. Successful Home Cell Groups. Phainfield, NJ., Logos International, 1981.

Church in Africa Today and Tomorrow. Malawi, AEAM, 4th General Assembly.

Coleman, Lucien E. Jr. Why the Church must Teach. Nashville, Tenn. Broadman Press, 1984.

Daniel, Eleanor, John W.Wade, Charless Gresham. Introduction to Christian Education. Cincinnati, Ohio, Standard Publishing, 1980.

Douglas, J.D. New Bible Dictionary, 2nd edition. Leicester, England, Inter-Varsity Press, 1982.

Drummond, Lewis. What the Bible Says. New York, Abindon Press, 1974.

Eavey, C.B. Principles of Teaching for Christian Teachers. Grand Rapids, MI. Zondervan Publishing House, 1940.

Edge, Findlay B. Teaching for Results. Nashville, Tenn., Broadman Press, 1956.

Eims, Leroy. Be the Leader you were Meant to Be. Wheaton, IL., Victor Books, 1975.

Eyrich, Howard A. Three to Get Ready. Phillipsburg. NJ., Presbyterian and Reformed Publishing Co., 1978.

Graendorf, Werner C. Introduction to Biblical Christian Eduation. Chicago, Moody Press. 1981.

Hakes, J.Edward. An Introduction to Evangelical Christian Education. Chicago, Moody Press, 1964.

Hendricks, Howard G. Teaching to Change Lives. Portland, Oregon, Multnomah Press, 1986.

Hess, Margaret. Unconventional Women. Wheaton, IL., Victor Books, 1981.

Holland, Grace. Which way for a Changing Africa? Nairobi, Kenya, Evangel Publishing House, 1992.

Kaydamo Machato. Full Salvation in Christ Jesus. Addis Ababa, Geja Word of Life Literature Services, 1984.

LeBar, Lois E. Education that is Christian. USA, Scripture Press Publications, 1989.

Lewis, Ralph L. and Gregg Lewis. Learning to Preach like Jesus. Westchester, Ill., Crossway Books, 1989.

Mekane Yesus Seminary. Christian Education, An Introductory Course. 1990.

Pearson, J.E., Teaching in the Church. A study Guide. Brussels, Belgium, ICI. 1980.

Phillips, Mary L. Teaching Women. Wheaton, IL., Victor Books, 1982.

Reapsome, James & Martha, Marriage, God's Design for Intimacy. London, Scripture Union, 1984.

Richards, Lawrence O. Creative Bible Teaching. Chicago, Moody Press, 1970.

Roadcup, David. Ministering to Youth. Cincinnati, OH., Standard Publishers. 1980.

Roberts, Barbara, and Maryann Samms. Toward Effective Teaching. Manila, Philippians, Conservative Baptist Publishing Inc., 1980.

Robinson, Haddon W. Biblical Preaching. Grand Rapids, MI., Baker Book Hse. 1980.

Sanders, Oswald J. Spiritual Leadership. Chicago, Moody Press, 1967.

Smart, James D. The Teaching Ministry of the Church. Philadelphia, The Westminster Press, 1954.

Swindoll, Charles R. Growing Deep in the Christian Life. Portland, Oregon, Multnomah Press, 1986.

Swindoll, Charles R. Hand me Another Brick. Nashville, Thomas Nelson Publishers, 1978.

Tsehai, Berhane Selassie, Gender Issues in Ethiopia. Addis Ababa, Institute of Ethiopian Studies, 1991.

**Wells, James Allan. Cell Groups. as a Strategy for Renewal and Growth. Regina, SK., James Allan Wells, 1993.**

**Wilhoit, Jim, Leland Ryken. Effective Bible Teaching. Grand Rapids, MI., Baker Book House, 1988.**

**Wright, H. Norman. Premarital Counselling. Chicago, Moody Press, 1981.**

**Wright, Norman. Communication—Key to your Teens. Irvine, CA., Harvest House Publishers, 1978.**

# በጥናት መምሪያና ማብራሪያ (በት.መ.ማ መልክ) የተዘጋጁ መጻሕፍት፣

1. የብሉይ ኪዳን አሰሳ፣ 1ኛ መጽሐፍ
2. የብሉይ ኪዳን አሰሳ፣ 2ኛ መጽሐፍ
3. ኦሪት ዘፍጥረት
4. ኦሪት ዘሌዋውያን እና ዕብራውያን
5. ትንቢተ ኢሳይያስ
6. ትንቢተ ዳንኤል
7. የአዲስ ኪዳን አሰሳ፣ 1ኛ መጽሐፍ
8. የዮሐንስ ወንጌል
9. የሐዋርያት ሥራ
10. የሮሜ መልእክት
11. 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ
12. የገላትያና ያዕቆብ መልእክቶች
13. የዮሐንስ ራዕይ
14. መንፈስ ቅዱስ
15. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና የጥናት መምሪያ
16. ክርስቲያናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ